Now, the appellants did not sue for a share of Woz. Tsekawie's land, but on the contrary, claim that the land in the possession of the respondents used to belong to Woz. Medhin, and that they as her successors have exclusive title to it. It is clear from the phrase "land which is jointly owned by members of one family..." in Article 1168(1), second paragraph, that a claim is not barred by prescription only on the condition that it was inherited from some common ancestor and has been owned jointly or individually by members of the same family. In such a case, Article 1168(1) provides that the law of prescription does not bar a member of the family who has been absent for a long time from claiming his share of the land from his relatives, provided that he is entitled to a share and that the law of prescription is unknown in matters pertaining to land in that particular part of the country.

As pointed out earlier, the present appellants claim that the land formerly belonged to Woz. Medhin, while the respondents' position is that it belonged to Woz. Tsekawie. Hence, the dispute involves two families and not members of one family. Article 1168(1) provides that, even in an area where the law of prescription is not used, a claim is not barred by prescription only when the claim is made by a member of the family who has been absent and has come home. This exception does not cover those cases that involve members of different families.

The failure to bar by prescription suits that are brought against a family or individual whose ownership of certain property has gone uncontested for a long time would breed nothing but unnecessary litigation and obstruct peasants from attending to their farming. It is axiomatic that a court cannot possibly arrive at a fair decision by relying on witnesses who testify that they have heard people say that a certain piece of land used to belong to a certain person centuries ago. In fact, the law of prescription was enacted to meet exactly that problem.

Thus, the law of prescription would have been sufficient to defeat the appellants' claim, but the respondents went further and traced the title to the land and explained under what circumstances they came to own it.

At the start of the case, some of the respondents argued that they should not have been made parties to the suit because their land falls under the "Jiraff

Gotit" category. They should not have been joined as defendants, but as the appellants' claim has been dismissed, there is no need to go into the merits of their allegation.

For the above reasons, the Supreme Imperial Court affirms the High Court decision and imposes E$20 more on the appellants in court costs and damages.

Delivered in the presence of both parties on May 5, 1965.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

አዛናው ፡ ዓለሜ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ሴንጀር፡ የስፌት፡ መኪና፡ ኩባንያ ፡ መልስ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፴፱/፶፮ ፡ ዓ. ም. ።

ስለ ፡ ንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት - ለብቻ ፡ ተጠቃሚ ፡ ስለመሆን - ስለማስመዝገብ ።

ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድር - ስለ ፡ ንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት - የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፩፻፴፪ ፡ ፩፻፴፫ ፡ እና ፡ ፩፻፴፬ ።

ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ በሚጠቀሙባቸው ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ስላለ ፡ ተጠቃሚውን ፡ ሕዝብ ፡ በማደናገር ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድርን ፡ ስለሚፈጥር ፤ ተከሳሹ ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ወደፊት ፡ እንዳይጠቀሙ ፡ ሲል ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ - የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ተገልብጦ ፡ ክሱ ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ።

፩) አንድ ፡ ነጋዴ ፡ በሚጠቀምበት ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ እንዳይጠቀሙበት ፡ ለመከልከል ፡ የሞኖፖል ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ የዚሁ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ባለቤት ፡ ለመሆኑ ፡ ከሌሎቹ ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶችን ፡ ለመመዝገብ ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አስመዝግቦ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለረዥም ፡ ዘመናት ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሲጠቀም ፡ መቆየቱ ፡ ብቻውን ፡ በቂ ፡ አይሆንም ።

፪) የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶችን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ባይኖርም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በልምድ ፡ የሚሠራበትን ፡ ደንብ ፡ በመከተል ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

ሰኔ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ.ም. ። ዳኞች ፤ - ም/አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ሐጐስ ፡ ተወልደ ፡ መድኅን ፡ ዶክተር ፡ ዊሊያም ፡ ቡሐጅያር ፡ አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ።

የመልስ ፡ ሰጭ ፡ ኩባንያ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷/፶፮ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ሲከስ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ክስ ፡ አቅርቦበታል ።

ያለ ፡ አግባብ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራን ፡ ለማቆም ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡ ከሳሽ ፡ የሚከተለውን ፡ በማክበር ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ/ ከሳሽ ፡ በስፌት ፡ መኪናዎች ፡ በመለዋወጫና ፡ በመገጣጠሚያ ፡ ዕቃዎቻቸው ፡ ስለሚነግድ ፡ በትልቅ ፡ ኤስ(ካፒታል) ውስጥ ፡ መኪና ፡ የምትሰፋ ፡ ሴትና ፡ በእንግሊዘኛ ፡ ቋንቋ ፡ የሴንጀር ፡ ስፌት ፡ መኪናዎች ፡ የሚል ፡ የተጻፈበት ፡ የንግዱ ፡ ምልክት ፡ ባለቤት ፡ ነው ። (ኤግዚቢት ፡ ፒ/ ፩)

፪ኛ/ የከሳሹ ፡ የተጠቀሰው ፡ የንግድ ፡ ምልክትና ፡ ሌሎችም ፡ ፲፩ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ኢ.ኤ.ኢ. ከታኅሣሥ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኘው ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ ቆንሲል ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ተመዝግበዋል ። በጊዜው ፡ ይሠራበት ፡ በነበረ ፡ ኩሪየር ፡ ዴኢትዮጲ ፡ በሚባለው ፡ ጋዜጣ ፡ ኢ.ኤ.ኢ. ታኅሣሥ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓ. ም. ባወጣው ፡ ቁጥሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በተባለው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ቢጠቀም ፡ በሕግ ፡ ተከሶ ፡ የሚቀጣ ፡ መሆኑን ፡ ለሕዝብ ፡ በማስታወቂያ ፡ አውጥቶ ፡ ነበር ።

፫ኛ/ የከሳሹ ፡ የቀድሞ ፡ ሠራተኛ ፡ የነበሩት ፡ ተከሳሽ ፡ የከሳሽን፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በማስመሰል ፡ ተጠቃሚው ፡ ሕዝብ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚሸጠው ፡ ዕቃ ፡ የከሳሹ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ እንዲገዛቸው፡ በማሰብ፡ ኢ.ኤ.ኢ. የካቲት፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ.ም. (የካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ.ም.) በኢትዮጵያ ፡ ሄራልድ ፡ ጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ አውጥተዋል ። (ኤግዚቢት ፡ ፒ/ ፪)

፬ኛ/ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድርን ፡ የሚያሳይ ፡ የሚከተለው ፡ በጉልህ ፡ ይታያል ፤ -

(ሀ) ዋናውን ፡ ምልክት ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ በማድረግ ፡ ሁለቱም ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች፡ ትልቅ ፡ "ኤስ ' ን (ካፒታል) " S " ያሳያሉ ። በተለይም ፡ የካፒታሉ ፡ " S " ፊደል ፡ ጫፍና ፡ ጫፎች ፡ በትክክልና ፡ በግልጥ ፡ ተመሳሳይነታቸው ፡ የሚታይ ፡ ነው ።

(ለ) ተከሳሽ ፡ በጽሑፍ ፡ "ሳባ ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ መደብር" በማለት ፡ የጻፉ ፡ ሲሆን ፡ ከሳሹ ፡ " የሴንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪናዎች " በማለት ፡ ጽፈዋል ። ይህ ፡ የሚያሳየው ፡ ተከሳሹ ፡ ሳባ ፡ በሚለው ፡ ስም ፡ አስቦ ፡ የተጠቀሙት ፡ በካፒታል ፡ " S " ፊደል ፡ አስመስለው ፡ ለመጠቀም ፡ ነው ።

(ሐ) ሁለቱም ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ከሳሹ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲጠቀምበት ፡ ለኖረ ፡ ለስፌት ፡ መኪናዎችና ፡ መለዋወጫ ፡ ዕቃዎች ፡ ናቸው ።

፭ኛ/ ፩. እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባንድላይ ፡ ሲጠራቀሙ ፡ ተጠቃሚውን፡ ሕዝብ ፡ ስለሚያደናግሩ ፡ በንግድ፡ ሕግ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፴፪ ፡ እና ፡ ፩፻፴፫ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (፪) (ሀ) ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ በከሳሽ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ በደል ፡ በማድረስ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድርን ፡ ይፈጥራሉ ።

፮ኛ/ ማስመሰል ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ መፈተኛ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በግልጽ ፡ እንደሚታየው ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ ስለሆኑ ፤

(ሀ) በኤግዚቢት ፡ ፒ/፪ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ተከሳሹ ፡ ወኪሎቹ ፡ አሸከሮቹ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ነገረ ፡ ፈጆቹ ፡ ወራሾቹና ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡

የሚያዛውርላቸውና ፣ እንዲሁም ፣ ከእነርሱ ፣ ጋር ፣ በሥራ ፣ ተካፋይ ፣ የሚሆኑት ፣ ሁሉ ፣ እንዳይጠቀሙ ፣ እንዲታገዱና ፣ ዘላቂ ፣ የማገጃ ፣ ትእዛዝ ፣ እንዲሰጣቸው ።

(ለ) ተከሳሹ ፣ የንግድ ፣ ምልክታቸውን ፣ እንዲለውጡ ፣ እንዲደረግ ።

(ሐ) ከዚህ ፣ በላይ ፣ የሚሰጡትም ፣ ብይኖች ፣ በንግድ ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፴፬ ፣ በንዑስ ፣ አንቀጽ ፣ (፩) (ሀ) እና ፣ በአንቀጽ ፣ (፪) (ሀ) የተመለከቱትን ፣ የከሳሹ ፣ መብቶች ፣ ሳይነኩ ፣ እንደተጠበቁ ፣ እንዲሆንልንና ፤

(መ) ተከሳሹ ፣ አሁን ፣ ለቀረበባቸው ፣ ክስ ፣ ለተደረገው ፣ ኪሣራ ፣ ከዳኝነ ትና ፣ ከጠበቃ ፣ አበል ፣ ጋር ፣ እንዲከፍሉ ፣ እንዲታዘዝልን ፣ በማክበር ፣ አመለክ ታለሁ ።

ከዚህ ፣ በላይ ፣ ለተመለከተው ፣ ክስ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ (የስር ፣ ተከሳሹ) ቀጥሎ ፣ በግልባጭ ፣ የተጻፈውን ፣ የክስ ፣ መቃወሚያ ፣ አቅርበዋል ።

ከሳሹ ፣ የካቲት ፣ ፴ ፣ ቀን ፣ ፶፯ ፣ በተጻፈ ፣ የክስ ፣ ማመልከቻቸው ፣ ተከሳሹን ፣ የከሰሱበት ፣ ምክንያት ፣ “ ኤስ ” የሚባለውን ፣ የአውሮፓውያን ፣ ፊደል ፣ እኔ ፣ ብቻ ፣ በሞኖፖል ፣ ለመያዝ ፣ ይፈቀድልኝ ፣ ሲሉ ፣ ነው ።

ተከሳሽ ፣ ለተከበረው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ከዚህ ፣ በታችና ፣ በላይ ፣ የተመለከተ ውን ፣ ከሳሹ ፣ የአቀረቡትን ፣ ሕጋዊ ፣ ያልሆነ ፣ ክስ ፣ በመቃወም ፣ መልሱን ፣ በጽ ሕትና ፣ አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ ተከሳሹ ፣ ሳባ፣የስፌት ፣ መኪና ፣ ትምህርት ፣ ቤት፣በማለት ፣ ስለንግድ ፣ ሥራ ፣ መቋቋም ፣ በወጣው ፣ በንግድ ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፣ ፳፪ ፤ ስለንግድ ፣ ሥራ ፣ መሥ ራት ፣ ነፃነት ፣ በሕጉ ፣ አግባብ፣ የሕጉን ፣ መስመር ፣ ተከትዬ ፣ እንዲሁም ፣ የንግድ ፣ ሕግን ፣ ቁጥር ፣ ፹፰ ፣ አፈጻጸም ፣ አሟልቼ ፤ በኢትዮጵያ ፣ ሕ. ፣ መንግሥት ፣ አን ቀጽ ፣ ፵፯ ፣ እና ፣ ፵፰ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ለኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ ፣ የሰጡትን ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ አድርጌ ፣ ስሙ ፣ በአርእስቱ ፣ በተጠቀሰው ፣ ሳባ ፣ የስፌት ፣ መኪና፣ ትም ህርት ፣ ቤት ፣ በሚል ፣ መጠሪያ ፣ ሥራዬን ፣ አቋቁሜ ፣ በማካሄድ ፣ ላይ ፣ ነኝ ።

፪ኛ/ ከሳሹ ፣ ግን፣ ሲንጀር ፣ የስፌት፣መኪናዎች፣ብለው ፣ በመሰየም ፣ አንድ ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ቤት ፣ በመኪና ፣ ስትሰፋ ፣ ወይም ፣ ቁጭ ፣ ብላ ፣ የምትታይላቸውን ፣ የከሳሹን ፣ ኩባንያ ፣ መጠቀሚያ ፣ ምስል ፣ ተከሳሹ ፣ ጨርሶ ፣ አልነካሁባቸውም ።

፫ኛ/ ከሳሹ ፣ በክስ ፣ ማመልከቻቸው ፣ ላይ ፣ ለተከበረው ፣ ፍ/ ቤት ፣ በተራ ፣ ቁጥር ፣ አንድና ፣ ሁለት ፣ የጻፉት ፣ ለአሥራ ፣ አምስት ፣ ዓይነት ፣ የንግድ ፣ ምል ክት ፣ ባለቤት ፣ ነኝ ፣ ከማለት ፣ በስተቀር ፣ በኢትዮጵያ ፣ የንግድ ፣ ሚኒስቴር ፣ የንግድ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ በዘመኑ ፣ ያልተመዘገበላቸው ፣ መሆኑን ፣ በየካቲት ፣ ፴ ፣ ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ. ም. በጻፉት ፣ መሠረት ፣ ነገሩን ፣ በግልጽ ፣ አምነዋል ።

፬ኛ/ ከሳሹ ፡ ብዙውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ለብቻቸው ፡ በሞኖፖል ፡ ለመያዝ ፡ በግልጽ ፡ አስበው ፡ ሲሠሩበት ፡ ቆይተዋል ። ማስረጃውም ፡ የካቲት ፡ ፴/፺፯ ፡ ዓ. ም. ከሳሹ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ባቀረቡት ፡ የክስ ፡ ማመልከቻቸው ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፪ኛ ፡ እ. ኤ. አ. ከታኅሣሥ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ለሰላሣ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ አለኝ ፤ ነበረኝ ፡ ከማለታቸውም ፡ በላይ ፤ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፲፯ ፡ መሠረት ፡ ክርክራቸው ፡ ውድቅ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ለአንድ ፡ የስፌት ፡ ሥራ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የሚፈቅድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አልነበረም ፤ አሁንም ፡ በአዲሱ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የለም ። በቁጥር ፡ ፩፻፲፮ ፡ እና ፡ ፩፻፲፯ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ፍትሕ ፡ እለምናለሁ ።

፭ኛ/ ከሳሹ ፡ “ ኤስ ” የተባለውን ፡ ፊደል ፡ መነሻ ፡ ማድረግ ፡ የሚችል ፡ ነጋዴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሊኖር ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ ካላቸው ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በ “ ኤስ ” መነሻ ፡ ይጠሩበት ፡ የነበሩ ፡ ብዙ ፡ የንግድ ፡ ስሞች ፤ ለምሳሌ ፡ ሲንክሌር ፡ (ኤስ) ፡ ሳባ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ (ኤስ) ፡ ሳቢያን ፡ ኮርፖሬሺን ፡ (ኤስ) ፡ ባካፌት ፡ የፊያት ፡ መኪና ፡ አስመጭዎች ፡ (ኤስ) እንዴት ፡ ሊደረጉ ፡ ነው ?

ክቡር ፡ ሆይ ፤

አሁን ፡ የተከበረውን ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለተከሳሹ ፡ እንዲያደርግልኝ ፡ አጥብቄ ፡ የምለምነው ፡ ከሳሹ ፡ በሕጉ ፡ አግባብ ፡ መሠረት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ጠቅሶ ፡ እንዲከስ ፤ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተከፈተው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳/፺፯ ፡ የትእዛዝ ፡ መዝገብ ፡ እንዲዘጋልኝ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትህትና ፡ እለምናለሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሳሹና ፡ ተከሳሹ ፡ በየበኩላቸው ፡ የአቀረቡትን ፡ ክስና ፡ የክስ ፡ መልስን ፤ አስረጂአቸውንም ፡ ከመዘገበ ፡ በኋላ ፤ የከሳሹን ፡ ጥያቄ ፡ በመቀበል ፡ “ ኤስ ” የተባለውን ፡ የፈረንጅ ፡ ፊደል ፡ ተከሳሹ ፡ ማለት ፡ የአሁን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይችልም ፡ ሲል ፡ በረዥሙ ፡ አትቶ ፡ ይህ “ ኤስ ” “ S ” የሚባለው ፡ የፈረንጅ ፡ ፊደል ፡ ከሳሹ ፡ በሞኖፖል ፡ የግል ፡ ንብረቱ ፡ አድርጎ ፡ ሊጠቀምበት ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ ፈርዶ ፤ ተከሳሹ ፡ በንግድ ፡ ሱቁ ፡ በር ፡ መስኮቶችና ፡ ግምብም ፡ ላይ ፡ የአደረገውን ፡ የንግድ ፡ ሥራው ፡ ልዩ ፡ ምልክትን ፡ እንዲያነሳ ፡ በማዘዝ ፡ ፍርዱን ፡ ሰጥቶአል ።

የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ በይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ በኩል ፡ የንግድ ፡ ሥራችን ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ነው ፤

ሲሉ ፡ የሚከራከሩበትን ፡ “ ኤስ ” የተባለው ፡ የፈረንጅ ፡ ፊደል ፡ የፈጠረውን ፡ መግት ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምሮአል ።

ይህ ፡ ክርክር ፡ ከአመሰራረቱ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ስንመለከተው ፡ በሁለት ፡ ሕጎች ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፤

<u>አንደኛው ፡ ሕግ</u> ፡ የትሬድ ፡ ማርክ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ምዝገባና ፡ የመብቱ ፡ ጥበቃ ፡ ሕግ ፡ ሲሆን ፤–

<u>ሁለተኛው ፡ ሕግ</u> ፡ ደግሞ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድርን ፡ ሥራ ፡ ለማስወገድ ፡ በሚያዘው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በመጀመሪያ ፡ በተጠቀሰው ፡ በትሬድ ፡ ማርክ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ምዝገባና ፡ የመብቱ ፡ ጥበቃ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ በጠቅላላ ፡ ስንመለከተው ፤ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የታወጀ ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ስለሌለና ፡ ባለመኖሩም ፡ በርትዕ ፡ ሚዛን ፡ ክሱንና ፡ መልሱን ፡ ለማመዛዘን ፡ ተገቢ ፡ ሲሆን ፡ በከሳሽና ፡ በተከሳሹ ፡ መካከል ፡ የዚህ ፡ የፊደል ፡ “ኤስ” “ S ” የንግድ ፡ ምልክት ፡ ባለቤትነት ፡ ቀዳሚነትን ፡ ለማወዳደር ፡ እንገደዳለን ። የቀዳሚነት ፡ አስረጅ ፡ የሚገኘውም ፡ ሕጉ ፡ በወሰነው ፡ የቀዳማይ ፡ ተመዝጋቢነት ፡ አስረጅን ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

እንደ ፡ ሕጉ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በርትዕ ፡ ሚዛን ፡ እንበለው ፤ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ የአንድ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ቀዳማይ ፡ ባለቤት ፡ መሆኑ ፡ ታውቆለት ፡ በዚሁ ፡ ምልክት ፡ ሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ እንዳይጠቀሙበት ፡ ለመከልከል ፡ ሞኖፖላዊ ፡ መብትን ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ የዚያ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ባለቤት ፡ ለመሆኑ ፡ ከሌሎቹ ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶችን ፡ ለመመዝገብ ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አስመዝግቦ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ምንም ፡ ለረዥም ፡ ዘመናት ፡ በንግድ ፡ ሥራው ፡ ሲጠቀምበት ፡ መኖሩን ፡ ቢታወቅም ፡ ባለቤትነቱን ፡ አስመዝግቦ ፡ በማግኘቱ ፡ የባለቤትነት ፡ ቀዳማይ ፡ መብትን ፡ ካልጨበጠ ፡ በስተቀር ፡ የግል ፡ የንግዱ ፡ ምልክት ፡ ነውና ፡ ሌሎች ፡ ሊጠቀሙበት ፡ አይችሉም ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ሕግ ፡ አይፈቅድለትም ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚመረምረው ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ክርክር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለዚሁ ፡ የታወጀ ፡ ሕግ ፡ ባይኖርም ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ የታወጀ ፡ እና ፡ የሚሠራበትን ፡ የሕግ ፡ መንፈስ ፡ በመከተልና ፡ በርትዕ ፡ የሁለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ መብትን ፡ ብናወዳድር ፤ በኢትዮጵያ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በልምድ ፡ የሚሠራበትን ፡ ደንብ ፡ በመከተል ፡ ከሁለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ ይህንን ፡ የሚከራከሩበትን ፡ “ኤስ” “ S ” ፊደል ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ በንግድና ፡

የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስመዘገበው ፡ ማን ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ብንመረምር ፤ ከቀረቡልን ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ አስረጂዎች ፡ እንደተመለከትነው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አቶ ፡ አዛናው ፡ ዓለሜ ፡ መሆኑ ፡ መዝገቡ ፡ በግልጽ ፡ አስረድቷል ።

የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የንግዱ ፡ ልዩ ፡ የግል ፡ ምልክቴ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የከሰሰበትን ፡ መለዮ ፡ ባለቤት ፡ መሆኑን ፡ ለማሳወቅ ፡ አስቦ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አለማስመዝገቡን ፡ በአቀረበው ፡ ጽሑፍ ፡ ቃሉ ፡ አረጋግጦአል ። የአገሩ ፡ የልምድ ፡ ሕግን ፡ አክብሮ ፡ ማስመዝገብ ፡ ያልፈቀደበትን ፡ ምክንያትም ፡ አልተረዳነውም ።

ስለዚህ ፡ “ ኤስ ” “ S ” የተባለው ፡ ፊደል ፡ የንግዱ ፡ ምልክት፡ ሆኖ ፡ የምጠቀምበት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ነኝና ፡ መብቴ ፡ ይጠበቅልኝ ፡ ብሎ ፡ የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበው ፡ ክስ ፡ ከሕግና ፡ ከርትዕ ፡ ውጭ ፡ በማይገባ ፡ የቀረበ ፡ ስለሆነ ፡ ውድቅ ፡ አድርገነዋል ።

በተጨማሪም ፡ በሁለተኛው ፡ የሕግ ፡ዓይነት ፡ መሠረት ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግንቦት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ.ም. ቀርቦ ፡ በችሎቱ ፡ ጊዜ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄ ፡ በሰጠው ፡ መልሱ ፡ በቃል ፡ አብራርቶ ፡ እንደገለጸው ፡ ያቀረብነው ፡ ክስ ፡ ስለማይገባ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በትሬድ ፡ ማርክ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ምዝገባና ፡ የመብቱ ፡ ጥበቃ ፡ አልከሰስንም ፡ ብለዋል ።

በከሰሰበት ፡ የማይገባ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድርን ፡ የሚመለከቱና ፡ ይደግፉኛል ፡ ሲል ፡ የጠቀሳቸው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾችም ፡ ፩፻፴፪ ፡ ፩፻፴፫ ፡ (፪) (ሀ) እና ፡ ፩፻፴፬ ፡ (፩) (ሠ) እና ፡ (፪) (ሀ) ናቸው ።

እነዚህ ፡ የሕግ ፡ አንቀጾችም ፡ በቅጂ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ፤ “ <u>ቁጥር ፡ ፩፻፴፪ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ሥራ ።</u>

በውድድር ፡ ሥራ ፡ ጥፋት ፡ አድርጎ ፡ በሚገኝ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነጋዴው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ኃላፊነት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺሕ፶፯ ፡ መሠረት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችላል ። ”

“ <u>ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ የሚያሰኘው ፡ ነገር ።</u>

፪ (ሀ) አንድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሚያወጣው ፡ ዕቃ ፡ ለማሳከር ፡ ሲባል ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የሚሠሩት ፡ የውድድር ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ። ”

“ ቁጥር ፡ ፩፻፴፱ ፡ የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

፩ (ሀ) በማይገባ ፡ የተወዳደረው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ያደርጋል ።

፪ (ሀ) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺ፩፻፳፰ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ በማይገባ ፡ በተወዳደረው ፡ ኪሣራ ፤ የከሳሹን ፡ ንግድ ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ በሐሰት ፡ የተነዛውን ፡ ነገርና ፡ ወሬ ፡ በሚገት ፡ ለማጥፋት ፡ በማስታወቂያ ፡ እንዲገለጽ ፡ ያዝለታል ። ”

የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ በደምበኛዬ ፡ በሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ፈጽሟል ፡ ሲል ፡ ክሶ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቅጅ ፡ ተጽፈው ፡ የማነበቡትን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ በመጥቀስ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ እንዲፈረድለት ፡ ሲለምን ፡ ለክሱ ፡ ደጋፊ ፡ ማስረጃ ፡ አድርጐ ፡ የአቀረበው ፡ ያው ፡ “ ኤስ ” “ S ” የተባለውን ፡ የፈረንጅ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ “ኤስ ” “ S ” የተባለው ፡ የፈረንጅ ፡ ፊደልም ፡ ምናልባት ፡ የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የንግዱ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ መሆኑን ፡ ለማሳወቅ ፡ ባያስመዘግብም ፡ እንዲያው ፡ በንግዱ ፡ ሥራው ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አድርጐ ፡ የሚጠቅም ፡ በት ፡ መሆኑን ፡ እንዲያስረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቢጠይቀው ፤ “ኤስ” “S” ፊደልን ፡ ከስፌት ፡ መኪና ፡ ላይ ፡ የተቀመጠች ፡ ሴትንና ፡ በእንግሊዘኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪናዎች ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ የተጻፈበትን ፡ በማጣመር ፡ እና ፡ በመደመር ፡ እንጂ ፡ በዚሁ ፡ “ኤስ” “S” በተባለው ፡ ፊደል ፡ ብቻውን ፡ በነጠላው ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ አድርጎ ፡ ተጠቅሞበት ፡ የማያውቅ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የአቀረባቸው ፡ የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ መለያዎችን ፡ አይቶ ፡ ተረድቶታል ። እነዚህ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ የንግድ ልዩ ፡ ምልክቶችም ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ ስለሚገኙ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የንግድ ፡ ሥራው ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አድርጐ ፡ ተጠቅሞበት ፡ የማያውቀውን ፡ “ኤስ” “S” የተባለውን ፡ ነጠላ ፡ ፊደል ፡ ዛሬ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አቶ ፡ አዛናው ፡ ዓለሚ ፡ በዚሁ ፡ ፊደል ፡ ላይ ፡ የንግሥት ፡ ሳባ ፡ ዘውድን ፡ ምልክት ፡ አድርጐ ፡ በፊደሉ ፡ ስፋት ፡ ውስጥ ፡ ሳባ ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጽፎ ፡ በፊደሉ ፡ መካከል ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ራስ ፡ ስዕል ፡ በማድረግ ፡ ሲጠቀምበት ፡ አይቶ ፡ በሕግ ፡ አሳብቦ ፡ ወይም ፡ አስመስሎ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ተወዳዳሪውን ፡ ለማጥቃት ፡ ፈልጐ ፡ የማጥቃት ፡ ምኞቱን ፡ ለመፈጸም ፡ በዚህ ፡ ፊደል ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ ይታገድልኝ ፡ ሲል ፡ የአቀረበበት ፡ ክስ ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ። የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራቱ ፡ አንድም ፡ አስረጅ ፡ አላቀረበበ

ትም ። ስለዚህ ፣ ይደግፉኛል ፣ ሲል ፣ የጠቀሳቸው ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በቀኟ ፣ ተጽ ፈው ፣ የሚነበቡ ፣ የሕግ ፣ አንቀጾች ፣ በይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ላይ ፣ የቀረበበት ፣ አስረጅ ፣ ሳይኖር ፣ ተፈጻሚ ፣ ሊሆኑ ፣ አይችሉም ። በዚሁ ፣ ሁሉ ፣ ምክንያት ፣ የንጉሠ ፣ ነገ ሥት ፣ ጠቅላይ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የመልስ ፣ ሰጭው ፣ ኩባንያ ፣ ነገረፈጅ ፣ ያቀረበ ውን ፣ ክስ ፣ ውድቅ ፣ አድርጐታል ።

ስለዚህ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ በሰፈው ፣ በትጻፈው ፣ ምክንያት ፣ ሁሉ ፣ የከፍተኛ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ መዝገብ ፣ ቁጥር ፣ ፲፱፳/፶፯ ፣ የሰጠው ፣ ፍርድ ፣ በጉዳዩ ፣ ከተጠቀሱት ፣ የሕግ ፣ አንቀጾች ፣ ጋር ፣ አግባብ ፣ የሌለውና ፣ በአስረጅ ፣ ያልተደገፈ ፣ ሆኖ ፣ ስላገኘነው ፣ ሽረነዋል ። ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ አቶ ፣ አዛናው ፣ ዓለሜ ፣ የሚገለገልበት ፣ የንግዱ ፣ ልዩ ፣ ምልክትና ፣ የሴንጀር ፣ የስፌት ፣ መኪና ፣ ኩባንያ ፣ የሚጠቀምበት ፣ የንግዱ ፣ ልዩ ፣ ምልክት ፣ አንዱ ፣ ከአንዱ ፣ ጋር ፣ የማይመሳሰሉ ፣ መልካቸውና ፣ አሠራራቸው ፣ የተራራቀ ፣ ስለሆነ ፣ ማንንም ፣ ሊያሳስት ፣ የማይ ችል ፣ ሁለቱም ፣ በየበኩላቸው ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ መለዮ ፣ ያላቸው ፣ ምልክቶች ፣ ስለ ሆኑ ፤ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ አቶ ፣ አዛናው ፣ ዓለሜ ፣ የንግዱ ፣ ልዩ ፣ ምልክትን ፣ በንግድና ፣ በኢንዱስትሪ ፣ ሚኒስቴር ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ባስመዘገበው ፣ ዓይነት ፣ ሆኖ ፣ በሙሉ ፣ ሕጋዊ ፣ መብት ፣ ሊሠራበትና ፣ ሊጠቀምበት ፣ ይችላል ፣ ብለን ፣ መብቱን ፣ በዚህ ፣ ፍርድ ፣ አጽንተንለታል ፤ መልስ ፣ ሰጭው ፣ ይግባኝ ፣ ባዩን ፣ በማይገባ ፣ ክስ ፣ ባጉ ላላበት ፣ ስለ ፣ ኪሣራ ፣ የጠበቃ ፣ አበል ፣ የኢት/ ብር ፣ አንድ ፣ መቶ ፣ ሃምሣ ፣ እን ዲከፍለው ፣ ፈርደናል ። ዳኝነቱን ፣ በደረሰኙ ፣ መሠረት ፣ መልስ ፣ ሰጭው ፣ ለይግ ባኝ ፣ ባይ ፣ ይክፈለው ። የከፍተኛ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ፍርዱ ፣ መሰረዙንና ፣ በዚሁ ፣ በአሁኑ ፣ ፍርድ ፣ መተካቱን ፣ እንዲአውቀው ፣ እና ፣ ፍርዱን ፣ እንዲያስፈጽም ፣ የዚሁ ፣ መዝገብ ፣ ቅጂ ፣ ይተላለፍለት ።

ይህ ፣ ፍርድ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩና ፣ የመልስ ፣ ሰጭ ፣ ነገረ ፣ ፈጅ ፣ ባሉበት ፣ በን ጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ጠቅላይ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በድምፅ ፣ ብልጫ ፣ ሐምሌ ፣ ፩ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፮ ፣ ዓ. ም. ተሰጠ ።

ዶክተር ፣ ቦሐጅያር ፣ የተለዩበት ፣ የፍርድ ፣ አስተያየት ።

ከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ግንቦት ፣ ፳ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፮ ፣ ዓ. ም. ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ በንግድ ፣ ሱቆቹ ፣ ላይ ፣ ያደረገውን ፣ በማስታወቂያም ፣ መልክ ፣ በኢትዮጵያን ፣ ሄራልድ ፣ የእንግሊዘኛ ፣ ጋዜጣ ፣ እ. ኤ. አ. ፣ የካቲት ፣ ፳ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፵፱ ፣ ዓ. ም. አሳትሞ ፣ ያወጣውን ፣ የንግድ ፣ ሥራውን ፣ ልዩ ፣ ምልክት ፣ እንዲያነሳ ፣ ወደፊ ትም ፣ በማናቸውም ፣ ዓይነት ፣ በዚሁ ፣ የንግድ ፣ ምልክት ፣ እንዳይጠቀም ፣ ሲል ፣ የሰ ጠውን ፣ ፍርድ ፣ በመቃወም ፣ የቀረበ ፣ ይግባኝ ፣ ነው ። ይግባኝ ፣ ባዩም ፣ የንግድ ፣ ሥራው ፣ ልዩ ፣ ምልክት ፣ አድርጐ ፣ የተጠቀመበት ፣ "ኤስ" "S" የተባለውን ፣ ነጠላ ፣ (ካፒታል) ፣ ፊደል ፣ ሲሆን ፣ በዚሁ ፣ ፊደል ፣ ላይ ፣ የዘውድ ፣ ምልክትና ፣

በፊደሉ ፡ ስፋት ፡ ውስጥም ፡ ሳባ ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጽፎ ፤ በፊደሉ ፡ መካከል ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ይገኛል ።

መልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያም ፡ በንዶዚሁ ፡ ያለ ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ የመሸጥ ፡ ንግድ ፡ የተሠማራ ፡ ሲሆን ፡ ከሚጠቀምባቸው ፡ ከንግድ ፡ ምልክቶቹ ፡ አንዱ ፡ “ ኤስ ” “ S ” የሚባል ፡ ነጠላ ፡ ፊደልና ፡ ከስፌት ፡ መኪና ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጠች ፡ ሴት ፡ ይገኛል ። መልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያም ፡ በሁለቱ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ መሃል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ስላለ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማሳሳትን ፡ በመፍጠር ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድርን ፡ ይፈጥራሉ ፡ ሲል ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ተከሳሽ ፡ ወኪሎቹ ፡ አሽከሮቹ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ነገረ ፡ ፈጆቹ ፡ ወራሾቹና ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ የሚያዛውርላቸው ፡ እንዲሁም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ በሥራ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑት ፡ ሁሉ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴፫(፪) (ሀ) እና (ለ) መሠረት ፡ ለዘለቄታው ፡ በንግዱ ፡ ምልክት ፡ ከመጠቀም ፡ እንዲታገዱ ፡ ጠየቀ ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ይግባኝ ፡ ያለባቸው ፡ መነሻዎች ፡ ሰፋ ፡ ያሉ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ለነገሩ ፡ አግባብ ፡ የሌላቸውና ፡ ትርፍ ፡ እነጋገር ፡ ናቸው ። ይሆም ፤ በይግባኙ ፡ ላይ ፡ ስለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጠቅላላውን ፤ በአንዳንድ ፡ ዳኞች ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ የተደረገው ፡ ትችት ፡ አግባብ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁንና ፡ በጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ የይግባኙ ፡ መነሻ ፤ ሀ/ የይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገበ ፡ ሲሆን ፡ የመልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያ ፡ ግን ፡ አልተመዘገበም ። ለ/ በመልስ ፡ ሰጪው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ቅርጽና ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ቅርጽ ፡ መካከል ፡ ተመሳሳይነት ፡ የለም ። ሐ/ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያ ፡ “ኤስ” “ S ” የተባለውን ፡ ፊደልና፡ የስፌት ፡ መኪናን፡ ንግድ ፡ በሞኖፖል ፡ ሊይዘው ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

የመልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጸንቶ ፡ በነበረው ፡ ሕግ ፡ ይኸውም ፡ በፌደራል ፡ ወንጀሎች ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የተመዘገበ ፡ ለመሆኑ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስረጃ ፡ ቀርቦለታል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ አንቀጽ ፡ አምስት ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ መልስ ፡ ሰጪውን ፡ ኩባንያ ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ ሊያግደው ፡ አይችልም ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ይኸው ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባደረጋቸው ፡ በማናቸውም ፡ ኮንትራቶች ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ፡ ይላል ፡ እንጂ፤ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ ክስን ፡ አያግድም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የመልስ ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በዩናይትድ ፡ እ ቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ ቢሆንም ፡ በኢትዮጵያ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገበ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ወደ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ጠልቆ ፡ ከመግባት ፡ በፊት ፡ የዚህ ፡ ክስ ፡ አመሠራረት ፡
የተመዘገበን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ነክቶብኛል ፡ ወይም ፡ መብቴ ፡
አልተጠበቀም ፡ አለመሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። ምክንያቱም፡ ስለንግድ ፡ ምል
ክት ፡ ወይም ፡ ትሬድ ፡ ማርክ ፡ አመዘጋገብ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የታ
ወጀ ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይህንኑ ፡ ቅርጽ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ምል
ክት ፡ አድርጐ ፡ በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለማስመዝገቡ ፡ ማስረጃ ፡
አቅርቦአል ። ነገር ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ምልክቶች ፡ አመዘ
ጋገብና ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ የመብት ፡ ጥበቃ ፡ ሕግ ፡ እስከወጣ ፡ ድረስ ፡ የን
ግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ እየተቀበለ ፡ እስካሁን ፡ የሚመዘግባቸው ፡ ምልክቶች ፡ ምንም ፡
ዓይነት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ሊሰጣቸው ፡ አይችልም ። ይህ ፡ የአሁኑ ፡ ክርክር ፡
በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ (፪) እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ አግባብ፡ የሚሠራ ፡
የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድርን ፡ ለማቆም ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡
ንዑ ስ ፡ አንቀጽ ፡ አንድ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ሁሉ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ከሐ
ቀኝነት ፡ አደራረግ ፡ ውጭ ፡ የሚሠራው ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡
ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ንዑ ስ ፡ አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ ደግሞ ፡ የማይገባ፡ የውድድር ፡
ሥራዎች ፡ ተብለው ፡ የሚቆጠሩትን፡ ይዘረዝራል ። ከነዚሁም ፡ አንዱ ፡ አንድ ፡
ዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሚያወጣው ፡
ዕቃ ፡ ለማሳከር ፡ ሲባል ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የሚሠሩት ፡ የውድድር ፡ ሥራ
ዎች ፡ ተገቢ ፡ አለመሆናቸውን ፡ ይገልጻል ። አሁን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የገ
ጠመው ፡ ጉዳይ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ከላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ እስካሁን ፡
ድረስ ፡ "ኤስ" " S " በተባለው ፡ ፊደልና ፡ እንዲት ፡ ቤት ፡ በስፌት፡ መኪናው ፡
ውስጥ ፡ ተቀምጣ ፡ በምትታየው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሲጠቀም ፡ እንደመ
ቆየቱ ፡ መጠን ፡ ይግባኝ፡ ባይ ፡ "ኤስ" " S " በተባለው ፡ ፊደልና ፡ የስፌት ፡
መኪና ፤ ከፊደሉም ፡ ላይ፡ ዘውድ ፡ ባለበት፡ የንግድ፡ ምልክት፡ በመጠቀሙ ፤ ይግ
ባኝ ፡ ባይ ፡ የሚሸጠው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ የሚከታተለው ፡ ንግድ ፡ የመልስ ፡ ሰጪው ፡
ነው ፡ በማለት ፡ ተጠቃሚውን ፡ ሕዝብ ፡ በማሳከር ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡
ሥራ ፡ ውድድርን ፡ ፈጥሯልን ፤ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አመዘጋገብ ፡ ሕግ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ የክሱ ፡ አ መ
ሠራረት ፡ ተከሳሹ ፡ በመመዝገብ ፡ የግሉ ፡ የሆነውን ፡ የከሳሽን ፡ ምልክት ፡ በዕቃ
ዎቹ ፡ ወይም ፡ በንግዱ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተጠቅሞባቸዋል ፡ የሚል ፡ ይሆናል ። እንዲህ ፡
ዓይነት ፡ ሕግ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ የነጋዴው ፡ መብት ፡ እንዲጠበቅ ፡ በማ
ለት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ሥራ ፡ ፈጽሟል ፡ በማለት ፡ ክስ ፡
እንዲያቀርብ ፡ ይደግፈዋል ። ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድር ፡ በብዙ ፡
ዓይነት ፡ መንገድና ፡ ዘዴ ፡ ሊከናወን ፡ ይችላል ። ከነዚሁም ፡ አንዱ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡
ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ የሚጠቀምበትን ፡ ቅርጽ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ምል

ክት ፤ አስመስሎ ፥ ሠርቶ ፤ ለራስ ፤ በመጠቀም ፤ ነው ። ሕጉም ፤ በንግድ ፥ ሥራ ፤ ውስጥ ፤ በአንድ ፤ ዓይነት ፥ ምልክት ፤ ቅርጽ ፤ ወይም ፤ ስም ፤ በቅድሚያ ፤ ሲጠቀምበት ፤ የቆየውን ፥ ማንኛውንም ፥ ሰው ፥ ሌላው ፤ ተወዳዳሪ ፤ ሕዝብን ፤ በማታለል ፤ የራሱን ፤ ዕቃ ፥ የሌላ ፥ ሰው ፥ ዕቃ ፤ በማስመሰል ፤ እንዳይሸጥና ፥ በነዚሁ ፥ ምልክቶች ፥ እንዳይጠቀም፥ ለመከላከል ፤ መብት ፤ ሰጥቶታል ። ተገቢ ፥ ያልሆነ ፥ የንግድ ፤ ሥራ ፤ ውድድርን ፥ መሠረት ፥ አድርጎ ፤ ክስ ፤ ለማቅረብ ፥ ዋናው ፥ መነሻ ፥ የሚሆነው ፥ ተከሳሹ ፥ በማይገባ ፥ አኳኋን ፥ በግላጭ ፥ ወይም ፥ በሠወርዋራ ፥ መንገድ ፤ ራሱ ፥ የሠራቸውን ፥ ሸቀጦች ፥ በሌላ ፥ ሰው ፥ እንደተሠሩ ፥ አስመስሎ ፤ ለሕዝብ ፥ ሲያቀርብ ፤ ተገኝቶአል ፥ በማለት ፥ ነው ። ሕጉም ፥ የሚሰጠው ፥ መፍትሔ ፤ የተመሠረተው ፥ ከሳሹ ፥ በዚሁ ፥ በንግድ ፥ ሥራው ፥ መልካም ፥ ስምንና ፥ ደንበኛ ፥ ገበያተኛን ፥ በማትረፉ ፥ ይኸውም ፥ ሐብቱ ፥ እንደመሆኑ ፥ መጠን ፤ ማንም ፥ ሰው ፥ እንዳይነካበት ፥ ሕጉ ፥ ይጠብቅለታል ። በከፊልም ፥ ሕዝቡ ፥ ከመጭበርበር ፥ እንዲድን የተወጠነ ፥ ሕግ ፥ ነው ፤ ምክንያቱም ፥ ከአንዱ ፥ ደምበኛው ፥ የገዛ ፥ ሲመስለው ፤ ከሌላው ፤ መግዛቱ ፤ ስለማይታወቀው ፥ ነው ።

በመሠረቱ፣ መልስ ፥ ሰጪው፥ ኩባንያ ፥ “ ኤስ ” “ S ” በተባለው ፥ ፊደልና ፤ በስፌት ፥ መኪና ፤ አጠገብ ፥ እንዲት ፥ ሴት ፤ ቁጭ ፤ ብላ ፥ በምትገኘው ፥ ምልክቱ ፤ ከብዙ ፥ ዘመን ፥ ጀምሮ ፥ በዚህም ፥ አገር ፥ ሆነ ፤ በውጭ ፤ አገር ፤ ሲጠቀምበት ፥ መቆየቱ ፥ አልተካደም ። እንዲያውም ፥ መልስ ፥ ሰጪው ፤ ኩባንያ ፥ ከብዙ ፤ ዘመን ፤ በፊት ፥ እ. ኤ. አ. በመስከረም ፥ ፳፯ ፥ ቀን ፤ ፲፱፻፴ ፥ ዓ. ም. በጊዜው ፥ ይሠራበት ፥ በነበረው ፥ ኩሪየር ፥ ዴ ፥ ኢትዮጵያ ፥ በሚለው ፥ ጋዜጣ ፥ በዩናይትድ ፥ ስቴትስ ፥ የተመዘገበውን ፥ የንግድ ፥ ምልክት ፥ ግልባጭና ፥ ማንም ፥ ሰው ፥ በተባለው ፤ የንግድ ፥ ምልክት ፥ ሲጠቀም ፥ ቢገኝ ፥ በሕግ ፥ ተከሶ ፤ የሚቀጣ ፥ መሆኑን ፥ ጭምር ፤ ለሕዝብ ፥ በማስታወቂያ ፥ አውጥቶ ፤ ነበር ። ይግባኝ ፤ ባዩ ፥ የሳባ ፥ የስፌት ፥ መኪና ትምህርት ፥ ቤት ፥ የሚል ፤ ማኅበር ፥ አቋቁሞ ፥ ይህም ፤ ማኅበር ፥ በሕጉ ፥ መሠረት ፤ በንግድና ፥ በኢንዱስትሪ ፤ ሚኒስቴር ፤ ተመዝግቦአል ። ለንግዱም ፤ ሥራ ፥ ልዩ ፤ ምልክት ፤ የሆነው ፤ ዘንድ ፥ “ ኤስ ” “ S ” የተባለውን ፥ ነጠላ ፥ ፊደል ፥ በዚም ፤ ፊደል፣ ላይ፣ የዘውድ ፥ ምልክትና፣ በመካከሉም፣ የስፌት፣ መኪና ፥ አድርጎአል ። እውነት ፥ ነው ፤ ይግባኝ ፤ ባዩ ፥ እንዳመለከተው ፥ ሁሉ ፥ ማንም ፥ ሰው ፥ እንንግድ ፥ ምልክት ፤ አድርጎ ፤ አንድ ፥ ነጠላ ፥ ፊደልን ፤ ብቻውን ፥ በሞኖፖል ፥ ሊጠቀምበት ፥ አይችልም ። ነገር ፥ ግን ፤ አንድ ፥ ነጠላ ፥ ፊደል ፤ በብዙ ፤ ዓይነት ፤ መንገድ ፥ ሊጠቀሙበት ፥ ይቻላል ። መገንዘብም ፥ የሚያሻው ፤ ሕጉ ፤ ለመጠበቅ ፥ የሚፈልገው ፥ በአንድ ፥ ሰውና ፥ በሌላ ፥ ተወዳዳሪ ፥ ንግድ ፤ መሃል ፤ የሚነሳውን ፥ መሳሳትና ፤ መሳከር ፥ ነው ። ይግባኝ ፤ ባዩ ፥ በትችቱ ፤ ላይ ፤ እንደሳባ ፥ መጻሕፍት ፥ ቤት ፤ ሳካፈት ፤ ሲንክሌር ፤ ሳቢአን ፥ ኮርፖሬሽን ፥ ያሉትን ፥ ንግድ ፤ ሥራዎች ፥ ጠቅሷል ። እነዚህንም ፥ የንግድ ፥ ቤቶች ፥ የጠቀሰበት ፤ ምክን

ያት ፣ የሁሉም ፣ የመጀመሪያው ፣ ፊደል ፣ "ኤስ" "S" በመሆኑ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ በንደዚህ ፣ ዓይነት ፣ አጋጣሚ ፣ ጊዜ ፣ የመጀመሪያው ፣ "ኤስ" "S" ፊደል ፣ ምንም ፣ ዓይነት ፣ ማሳሳትን ፣ ሊፈጥር ፣ አይችልም ። ምክንያቱም ፣ ከነ ዚህ ፣ ከተጠቀሱት ፣ ኩባንያዎች ፣ መሃል ፣ አንዳቸው ፣ እንኳን ፣ በስፌት ፣ መኪና ፣ ንግድ ፣ ስለማይጠቀሙ ፣ ነው ። የሚጠቀሙ ፣ ቢሆን ፣ ኖሮ ፣ ግን ፣ ውጤቱ ፣ በተ ለየ ፣ ነበር ።

በዚህ ፣ በአሁኑ ፣ ክርክር ፣ ይግባኝ ፣ ባይ ፣ የተጠቀመበት ፣ ሳባ ፣ ለተባለው ፣ ቃል ፣ የመጀመሪያ ፣ ፊደል ፣ የሆነው ፣ "ኤስ" "S" ቅርጹ ፣ መልስ ፣ ሰጪው ፣ ከሚጠቀምበት ፣ "ኤስ" "S" ፣ በማናቸውም ፣ አኳኋን ፣ ፈጽሞ ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፣ ነው (አይለያይም) ። ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ግን ፣ የሱ ፣ "ኤስ" "S" የስፌት ፣ መኪና ፣ ከሚፋፋም ፣ ላይ ፣ የንግድ ምልክት ፣ ሳባ ፣ ዘውድ ፣ ምልክት ፣ ሲኖርበት ፣ የመልስ ፣ ሰጭው ፣ "ኤስ" "S" ግን ፣ ስፌት ፣ መኪናው ፣ አጠገብ ፣ የተቀመጠች ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሴት ፣ ይገኝበታል ፣ ብሏል ። አጠያየቁ ፣ ግን፣ "የይግባኝ፣ ባይ ፣ "ኤስ" "S" ደንበኞችን ፣ በማሳሳት ፣ የሱ ፣ የንግድ ፣ ሥራ ፣ የመልስ ፣ ሰጪው ። የንግድ ፣ ሥራ ፣ ወይም ፣ የሱ ፣ ዕቃ ፣ የመልስ ፣ ሰጪው ፣ ዕቃ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ እንዲገምቱ ፣ ያደርጋቸዋልን ?" ሆኖ ፣ ይገኛል ። ይህንንም ፣ ጥያቄ ፣ ለመመለስ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ መመልከት ፣ ያለበት ፣ በርግጥ ፣ መሳሳት ፣ መፈጠሩን ፣ ሳይሆን ፣ በፍርድ ፣ ቤቱ ፣ አስተያየት ፣ በልማዳዊው ፣ የንግድ ፣ ተግባር ፣ መሠረት ፣ መሳሳት ፣ ሊፈጥር ፣ ይ ችል ፣ እንደሆነ ፣ መመርመር ፣ ነው ። መሳሳት ፣ ሊፈጠር ፣ ይችል ፣ እንደሆነም ፣ ለመወሰን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ሁለቱን ፣ የንግድ ፣ ምልክቶች ፣ ጐን ፣ ለጐን ፣ አይቶ ፣ ማመዛዘኑንና ፣ በክርክሩም ፣ ወቅት ፣ ተመሳሳይነቱና ፣ ልዩነቱ ፣ የተብራራለት ፣ መሆኑን ፣ መገንዘብ ፣ የለበትም ። የይግባኝ ፣ ባይ ፣ የንግድ ፣ ምልክት ፣ ማሳሳት ፣ ወይም ፣ ማሳከርን ፣ ይፈጥር ፣ ይሆን ፣ የሚለውን ፣ ጥያቄ ፣ ለመመለስ ፣ ገዢው ፣ ሁለቱንም ፣ ቅርጾች ፣ ጐን ፣ ለጐን ፣ አድርጐ ፣ ለማመዛዘን ፣ ዕድል ፣ የማያገኝ ፣ መሆኑ ፣ መታወስ ፣ አለበት ። ምንም ፣ እንኳ ፣ ሁለቱ ፣ ምልክቶች ፣ ጐን ፣ ለጐን ፣ ሆነው ፣ ሲታዩ ፣ እምብዛም ፣ የሚያሳስቱ ፣ ባይሆንም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ገዢው ፣ ሁለቱን ፣ ምልክቶች ፣ ጐን ፣ ለጐን ፣ አድርጐ ፣ ለማስተያየት ፣ ዕድል ፣ እንደማያ ገኝ ፣ መጠን ፤ ሁለቱ ፣ ምልክቶች ፣ በአንድነት ፣ ካልታዩ ፣ በስተቀር ፣ ለአእምሮ ፣ ማደናገርን ፣ ሊፈጥሩ ፣ እንደሚችሉ፣ መገንዘብ፣ አለበት ። በዚህ ፣ ክርክር ፣ ውስጥ ፣ ሁለቱን ፣ የንግድ ፣ ምልክቶች ፣ በተለይ ፣ አንድ ፣ የሚያደርጋቸው፣ ሁለቱም ፣ ምል ክቶች፣ ላይ ፣ አቀራረጹ ፣ አንድ ፣ የሆነው፣ ፊደል ፣ "ኤስ" "S" መሆኑ ፣ አይጠ ረጠርም ። የይግባኝ፣ ባዩም፣ "ኤስ" "S" ሆነ፣ የመልስ፣ ሰጪው፣ "ኤስ" "S" ሁለቱም ፣ የስፌት ፣ መኪና ፣ ሥዕል ፣ ይገኝባቸዋል ። ሆኖም ፣ የመልስ ፣ ሰጪው ፣ ኩባንያ ፣ መኪናው ፣ አጠገብ ፣ አንዲት ፣ ሴት ፣ ተቀምጣ ፣ ስትገኝ ፣ የይግባኝ ፣ ባዩም፣ "ኤስ" "S" ከበላዩ ፣ ዘውድ ፣ ይገኝበታል ። ይሁንና ፣ ከነዚህ ፣ ጥቃቅን ፣

ልዩነቶች ፡ በቀር ፡ በነዚህ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየውና ፡ ዓይን ፡ የሚማርከው ፡ ፊደሉ “ኤስ” ነው ። ይኸውም ፡ “ኤስ” “ S ” እና፡ የሰሩ ት፡ መኪናውም ፡ ሲጨመር ፡ በኔ ፡ ሐሳብ፡ መሳሳትንና ፡ ማሳከርን ፡ በመፍጠር ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ (፪) ፡ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድርን ፡ ይፈጥራል ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ። በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ይግባኙን ፡ ውድቅ ፡ አድርጌ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ፍርድ ፡ አጸንቻለሁ ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 7

AZANAW ALEME v. SINGER SEWING MACHINE CO. LTD.

Civil Appeal No. 1240/56

Trademarks — Exclusive use — Registration.

Unfair competition — Trademarks — Arts. 132, 133 and 134 Comm. C.

On appeal from a judgment of the High Court ordering the defendant to remove his trademark on the ground that it is so similar to that of the plaintiff as to cause confusion and thus constitute unfair competition.

Held: Judgment reversed and suit dismissed.

1. A person may monopolise a trademark and have other businessmen barred from using it only if he is the first person to have that trademark registered with the authorities empowered to register such trademarks; the mere fact that a person has used a trademark for a long time is not sufficient.

2. In the absence of legislation providing for trademark registration, registration must be made according to current practice with the Ministry of Commerce and Industry.

Sene 14, 1956 E.C. (June 21, 1964 G.C.); Justices: Vice-Afenegus Hagos Tewolde Medhin, Dr. W. Buhagiar, Ato Mengesha Wolde Amanuel: — The Supreme Imperial Court, having examined the judgment given by the High Court in Civil Case No. 260/56 and having examined appellant's submissions and documentary evidence, and also having examined respondent's opposition to the appeal and defence, and having carefully studied and examined all the legal objections and interpretations of the law as given by the litigants, delivers the following judgment.

The statement of claim submitted to the High Court by the respondent's counsel in Civil Case No. 260/56 reads as follows:

1. The petitioner is the owner of the trademark depicting a capital "S" with a woman at a machine and the English wording "Singer Sewing Machines", applying to sewing machines, their parts and attachments (Exhibit P/1).
2. The trademark in question, together with 15 other trademarks of the petitioner have been duly recorded at the Consulate General of the United States of America at Addis Ababa since December 17, 1930; publication to that effect was made in the newspaper of that time known as Courrier d'Ethiopie, dated December 26, 1930, whereby notice

was also given to the public that legal proceedings would be taken against anyone infringing the said trademark in Ethiopia.

3. The respondent, who was a previous employee of the petitioner, published a cautionary notice in the Ethiopian Herald on February 20, 1964, whereby a trademark similar to that of the petitioner was published which tends to mislead the consuming public into the belief that the goods which the respondent intends to market are actually the goods of the petitioner (Exhibit P/2).
4. In particular, the following degrees of similarity are immediately apparent and constitute a cause of unfair competition:
   (a) Both trademarks show a capital "S" with a sewing machine as the main mark; in particular, the projecting ends of the letter "S" are identical and conspicuous.
   (b) Respondent's description in writing reads "Sheba Sewing Center" as against petitioner's description of "Singer Sewing Machines." This shows that respondent has intentionally used the name of Sheba in order to make use of the capital "S".
   (c) Both trademarks are for sewing machines and spare parts in which petitioner has been operating for over a century.
5. The above degrees of similarity will, in their cumulative effect, confuse the public and create unfair competition to the great prejudice of petitioner, within the provisions of Articles 132 and 133 (2) (a) of the Commercial Code.
6. As similarity is the test of unfair competition and as the respondent is evidently guilty of such unfair competition:
   (a) A perpetual injunction should be granted enjoining and restraining the defendant, his agents, servants, employees, attorneys, successors and assigns and those in active concert or participation with them from using the trademark as published under Exhibit P/2 aforesaid (Article 2122 of the Civil Code and Article 134(2) (b) of the Commercial Code).
   (b) The defendant should be ordered to change his trademark.
   (c) The above remedies should be without prejudice to the petitioner's rights under Articles 134(1) (a) and 134(2) (a) of the Commercial Code.
   (d) Respondent should be condemned to pay the costs of the present action including court and advocate fees.

In reply to the petition, the present appellant, Ato Azanaw Aleme, submitted his opinion as follows:

The gist of the petitioner's claim dated March 9, 1964, is that he should be allowed to monopolise the European letter "S".

1. I, the defendant, have established a trading business enterprise by the name of "Sheba Sewing Machine School" in accordance with the pro-

visions of Articles 22 and 88 of the Commercial Code which gives me such right, and by virtue of Articles 47 and 48 of the Revised Constitution of Ethiopia by which the Emperor has given freedom to Ethiopians to establish and carry on trading businesses.

2. The defendant has never used the plaintiff's trade name Singer Sewing Machine nor infringed his trademark wherein a foreign lady is seen sitting under a sewing machine.

3. Petitioner, apart from saying that it is the owner of 15 trademarks under paragraphs 1 and 2 of its petition, has clearly admitted by its application dated March 9, 1964, the fact that it is not registered with the Ministry of Commerce and Industry as required by the Commercial Code.

4. The petitioner has over the past years monopolised the various businesses in which he is interested in the Empire and it is indeed his intention to continue to monopolise them. This intention on the part of the petitioner is clearly manifested by paragraph 2 of the statement of claim submitted to the Court, wherein the petitioner claimed that he has the exclusive right to use 15 trademarks for a period of 34 years starting from December 26, 1930. This contention of the petitioner is null and void by virtue of Article 117 of the Commercial Code. Neither the Commercial Code nor the law in force before the Code authorizes the use of 15 trademarks for a single business. The defendant therefore prays that the Court decide against the petitioner on this issue in accordance with Articles 115 and 116 of the Commercial Code.

5. If it is the petitioner's clear intention to state that no one in the Empire should be allowed to begin his trademark with the capital letter "S", what will happen with those trademarks which have been depicted by the letter "S" previously, to wit Sinclair — "S", Sheba Book Shop — "S", Sabean Corporation — "S", and the S.A.C.A.F.E.T. Company, importers of Fiat cars — "S". The defendant therefore prays that the honourable Court order the petitioner to cite the relevant Civil Code articles in his petition and that Order File No. 260/56, instituted in the Court, be closed.

In light of the allegations of both parties and the evidence brought forward on both sides the High Court found for the plaintiff. In its opinion it dealt at length with the issue raised by the use of the letter "S", concluded that the plaintiff was entitled to monopolise it and ordered the defendant, present appellant, to remove the signs displayed on the door, walls and windows of his shop.

The Supreme Imperial Court has carefully considered the dispute caused by the letter "S" which is claimed to be the trademark of both parties. In the opinion of this Court, the entire case is based on two legal provisions:

(a) the law on registered trademarks and sole ownership;

(b) the Commercial Code provisions intended to prevent unfair commercial competition.

It does not help to approach the dispute in light of the law on registration of trademarks and sole ownership because there is no such law in Ethiopia. And since we must resort to equity to arrive at a solution, we are compelled to determine who registered this letter "S" as a trademark first by consulting the register kept by the proper authorities. Under the law, or more appropriately, in equity, a businessman may monopolise a trademark and have other businessmen barred from using it only if he was the first person to have that trademark registered with the authorities empowered to register such trademarks. The mere fact that a person has used a trademark for a long time does not entitle him to claim that he is the sole owner and that others are prohibited from using it, unless he was the first person to have the trademark registered and reserved for his exclusive use. In the absence of any legislation on trademarks, both equity and the spirit of foreign legislation on the subject, and the practice abroad, dictate that we study the registers to determine the rights of both parties. Such a study discloses that the appellant, Ato Azanaw Aleme, was the first person to register the said trademark with the Ministry of Commerce and Industry pursuant to the current practice in Ethiopia.

In addition, the statement submitted by the advocate for the Singer Company indicates conclusively that it had not registered with the proper authorities the trademark of which it claims to be the sole owner and on account of which it instituted this suit. This Court cannot understand its reluctance to register it in accordance with the usage of the country.

Therefore, the action brought by the advocate for the respondent company alleging sole ownership and requesting the enforcement of its exclusive ownership is null and void under the law and in equity.

Moreover, the respondent company's advocate, in answering questions put to him by the Supreme Imperial Court in its session of May 6, 1964, said that the suit was not brought on the basis of the trademark, as such, but rather to curb unfair commercial competition. He cited Commercial Code Articles 132, 133(2) (a) and 134(1) (a) and (2) (a) to support his case.

These Articles provide as follows:

Article 132. *Unfair commercial competition.*

A trader may claim damages under Article 2057 of the Civil Code from any person who commits an act of competition which amounts to a fault.

Article 133. *Cases of unfair competition.*

The following shall be deemed to be acts of unfair competition: . . .

(2) (a) any acts likely to mislead customers regarding the undertaking, products or commercial activities of a competitor.

Article 134. *Effect of unfair competition.*

(1) The court may, in cases of unfair competition:

(a) order that damages be paid by the unfair competitor; ...

(2) the court may in particular:

(a) order the publication, at the cost of the unfair competitor, of notices designed to remove the effect of the misleading acts or statements of the unfair competitor, in accordance with Article 2120 of the Civil Code.

The only evidence the respondent company's advocate produced to support his allegation that the appellant had been guilty of unfair commercial competition under the provisions reproduced above, was the aforementioned letter "S". Although the respondent has not registered the said "S" letter to be a trademark of the Singer Sewing Machine Company in the Empire of Ethiopia, he was asked by the Court to prove that he was using the said letter "S" as his trademark. He produced various trademarks used by the Singer Company, which show that it never used the letter "S" alone as its trademark, but used it with a woman shown sewing within the framework of the letter and the words "Singer Sewing Machines" written along the contours of the letter.

In light of the fact that the Singer Company never used the letter "S" alone as its trademark and that the appellant placed the Queen of Sheba's crown over the letter, wrote "Sheba Sewing Center" following the outline of the letter and depicted a sewing machine at the center of the letter, the respondent company's claim and its request to the Court that the appellant be prohibited from using the letter "S" is nothing more than an attempt to harass a competing businessman under the guise of the law.

The advocate for the Singer Company has not adduced any evidence to prove that the appellant has engaged in unfair commercial competition. Consequently, the elements of the offence, according to the articles he cited, which are reproduced verbatim above, are not satisfied and the Supreme Imperial Court hereby dismisses the suit.

For the reasons given above, we find the High Court's decision in Civil Case No. 260/56 in conflict with the law cited and based on no evidence, and it is hereby reversed. There is not even a remote similarity, either in appearance or arrangement, between the trademarks used by the two parties; the possibility of confusing customers does not arise, because the two trademarks are distinctly different. Therefore, this Court rules that the appellant, Ato Azanaw Aleme, is entitled to use the trademark he had duly registered with the Ministry of Commerce and Industry. The respondent company shall pay the appellant $ 150 to cover court costs and the damages it caused him by instituting a suit without good cause.

A copy of this decision should be sent to the High Court to notify it that its decision has been reversed and to have it execute the new decision.

Majority decision given on July 8, 1964, in the presence of the appellant and the respondent's advocate.

MINORITY OPINION

Dr. W. Buhagiar, dissenting:- This is an appeal against a judgment given by the High Court on May 16, 1964, by which the appellant was ordered forthwith to remove from his business premises and to cease to use in any way whatever the distinguishing mark, or trademark, of which a sample was published in the Ethiopian Herald of February 20, 1964. This distinguishing mark consists of a capital "S" entwined around a sewing machine with a crown over the "S"; the words "Sheba Sewing Center" are written within the "S".

The respondent company also deals in sewing machines and one of the trademarks used in connection with the business is a capital "S" with a European lady sitting at a sewing machine. The respondent company considered that there was similarity between the two designs such that it created confusion and amounted to unfair competition to the great prejudice of the respondent company; for this reason the respondent company brought an action in the High Court against the appellant, praying that the appellant, his servants, agents, employees, attorneys, successors and assigns, and those in active concert and participation with them, be enjoined and restrained from using the design complained of, and this in terms of Article 134(2)(a) and (b) of the Commercial Code.

The grounds of appeal of the appellant are lengthy and contain matters which are completely irrelevant and undesirable; the Court refers to the comments made about the High Court or individual members of that Court. Substantially, however, the grounds of appeal are that (a) the respondent company is not a company registered in Ethiopia while the association of the appellant is; (b) that there is no similarity between the design of the appellant and that of the respondent company, and (c) that the respondent company cannot be entitled to a monopoly in the business of sewing machines, and he cannot monopolise the letter "S".

As regards registration, it should be stated that the respondent company has been registered in Ethiopia under the law in force at the time, that is, the Federal Crimes Proclamation (Proc. No. 138 of 1953, as amended); evidence to this effect has been produced before this Court; for this reason the respondent company is not precluded from bringing an action by reason of Article 1 of ARTICLE V of the Decree to Provide for the Registration of Business Enterprises (Decree No. 27 of 1957, as amended and renumbered Proc. No. 184 of 1961). Furthermore, it may be added that that Article precludes a non-registered company from bringing an action "upon any contract made by it in Ethiopia;" it does not seem that the Article precludes the bringing of *all* actions. Be that as it may, there is no question in the present case that the appellant company has been registered in Ethiopia, although its head office is in the United States of America.

Before proceeding further it is important to mention that this case is not based on the infringement of a "registered trademark"; there is no law in Ethiopia for registration of trademarks. It is true that the appellant has brought evidence to show that he has registered the said design with the Ministry of

Commerce and Industry as a trademark; but unless and until legislation is enacted for the registration of trademarks and for the protection of such registered trademarks, the actual registrations that are at present accepted by the Ministry of Commerce and Industry are of no legal effect and consequence. The present case is based on "unfair competition" as explained in Article 133(2) of the Commercial Code; the first paragraph of Article 133 provides that any act of competition contrary to honest commercial practice shall constitute a fault; paragraph (2) lays down what acts are deemed to be unfair competition, and one of these acts is an act likely to mislead customers regarding the undertaking, products, or commercial activities of a competitor. The question before the Court in the present case is whether the act of the appellant in using the "S" with the machine and the crown, when the respondent company has been using the "S" with the lady at the sewing machine as described above, amounts to an act of unfair competition in that it is likely to mislead customers regarding the undertaking, products or commercial activities of the respondent company.

When there exists legislation for the registration of trademarks, the gist of an action for the infringement of a registered trademark is that the defendant has used, or is using, on his goods, or in connection with his business, a mark which belongs to the plaintiff *by virtue of registration*. In default of such legislation, the law still protects a trader by means of the action for unfair competition; now unfair competition may be committed in various ways and means, and one of them is by using or imitating a mark, design or name which is used by a competitor in the same type of business. The law recognises the right in any person, who has been using a particular mark, name or design in connection with his business or goods to prevent others from using such mark, name or design so as to deceive the public into thinking that the business carried on by such person or the goods sold by him, are the business and goods of other persons. The essence of the action for unfair competition is that the defendant has wrongfully represented to the public, expressly or impliedly, that the business carried on by him or the goods sold by him, are the business or the goods of the plaintiff. The remedy which the law affords is based on the theory that the plaintiff has acquired in his business a reputation and goodwill which is his property and which the law protects from appropriation by another, and also partly upon the theory of protecting the public against fraud, in the sense that the public thinks it is doing business with or buying the goods of one person when it is dealing with another person.

It is not contested that the respondent company has been using the design "S" with the woman at a sewing machine for many years, both in this country and elsewhere; in fact the respondent company many years ago, on December 26, 1930, published in the newspaper of that time, the Courrier d'Ethiopie, a copy of the trademark (the letter "S" with the lady as described above) registered in the United States of America with the usual notice that action would be taken against any person who infringes that mark. The appellant has formed an association called The Sheba Sewing Center duly registered at the Mi-

nistry of Commerce and Industry and in connection with his business he used as a design the letter "S" with a sewing machine and a crown on top of the "S". Now it is true as the appellant submitted that no person can monopolise and use as an exclusive design a letter of the alphabet; but a letter of the alphabet can be used in very different ways; and it is also to be remembered that what the law is trying to protect against is the confusion that may arise between one person and a competitor in the same type of business; the appellant has referred to such businesses as Sheba Book Shop, S.A.C.A.F.E.T., Messrs. Sinclair, and Sabean Corporation; in such instances the initial "S" could not possibly create confusion and amount to unfair competition because none of these businesses deal with sewing machines; if they did, the position might be different.

In the present case there is no question that the letter "S" used by the appellant as the first letter of the word "SHEBA" is of exactly the same design as that of the respondent company; it is the same in all respects. But the appellant states that while the "S" of the respondent company has a foreign lady sitting at a sewing machine, his "S" has only a machine with, on top, the crown of the Queen of Sheba. But the question is: "Is the 'S' of the appellant likely to mislead customers into thinking that his undertaking is the undertaking of the respondent company or into thinking that the appellant is dealing with the goods of the respondent company?" In deciding this question the test is not whether confusion has actually occurred but whether the Court is of the opinion that there is a probability of confusion arising in the normal course of trade. In considering the probability of confusion the Court should not be guided by the fact that it has had the opportunity of seeing the two designs side by side and the fact that it has had pointed out to it during the trial the points of resemblance and difference between the two designs. In considering whether the design of the appellant is such as to cause confusion or deception, it must be remembered that the two designs are not seen side by side by the prospective customer. Although there may not be confusion when the two designs are seen side by side, the Court must take into consideration that the prospective customer does not see the two designs side by side and that there is a probability of memory confusion when the two designs are not seen simultaneously. There is no question that the main characteristic of the two designs in this case is the letter "S" with particular typographical characteristics (the same in both cases); the "S" of the appellant and the "S" of the respondent company both have a sewing machine incorporated in the "S" but that of the respondent company has a lady sitting at the machine; furthermore the "S" of the appellant is surmounted by a crown. Notwithstanding all these different details, however, the main characteristic and the principal feature in the design which attracts the eye is the "S", and this with the sewing machine (in one form or another) is, in my opinion, likely to create confusion and amount to an act of unfair competition within the meaning of Article 133(2)(a) of the Commercial Code.

For these reasons, I would dismiss the appeal and confirm the judgment of the High Court.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አንደኛ ፡ ችሎት ።

የሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ መንግሥቱ ፡ ታዬ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹ሐ፲፱፻፶፯ / ፶፰ ፡ ዓ. ም. ።

ግዴታዎች—ከውል ፡ ውጭ ፡ የሚደርስ ፡ ኃላፊነት—ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተግባር ፡ አላፊ ፡ ስለመሆን—በተቀጣሪ ፡ ሠራተኛና ፡ በሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ መሐል ፡ ያለው ፡ ልዩነት— የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፪ሺ፩፻፴ ፡ እና ፡ ፪ሺ፩፻፴፪ ።

የይግባኝ ፡ ባይ ፡ የሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ምክትል ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የሆነው ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ለመንገድ ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ ከመልስ ፡ ሰጭው ፡ ግል ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ቆፍሮ ፡ ለዚሁ ፡ ኩባንያ ፡ ስላቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የተወሰደውን ፡ ድንጋይ ፡ ዋጋ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭ ፡ ይከፍላል ፡ ሲል ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

<u>ውሳኔ፤</u>— የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ተገልብጦ ፡ የመልስ ፡ ሰጭ ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ ሆኗአል ።

፩፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፻፴፩፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ለተቋረጠበት ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ መሣሪያ ፡ እንዲያቀብለው ፡ አንድ ፡ ራሱን ፡ የቻለና ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራ ፡ የበታች ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ቢቀጥር ፡ ምክትል ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ የተጠየቀውን ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ በሚያደርገው ፡ ጥፋት ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ኃላፊነት ፡ የለበትም ።

፪፤ ለሚያቀርበው ፡ መሣሪያ ፡ እየተከፈለው ፡ በራሱ ፡ ኪሣራና ፡ ኃላፊነት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ፈልጎ ፡ ለማቅረብና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀቶችና ፡ ማዘዣዎች ፡ ራሱ ፡ ለማስወጣት ፡ ግዴታ ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፩፻፴፩፡ እንደተመለከተው ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺ፩፻፴፬ እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ ሠራተኛ ፡ አይደለም ።

ሐምሌ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ዳኞች ፤— አፈንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ ብላታ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ። የሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ከአውራ ፡ ጎዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ሁኖ ፡ የመንገድ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ተዋውሏል ።

ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ በበኩሉ ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ከሚባል ፡ ጋር ፡ ስለዚሁ ፡ መንገድ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ተዋውሏል ። ሙሴ ፡ ካሉስ ፡ ከሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ጋር ፡ ከተዋዋለ ፡ በኋላ ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ የሚሆን ፡ ድንጋይ ፡ ከግል ፡ ባለመሬቱ ፡ ላይ ፡ ቆፍሮ ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ አቅርቧል ።

በይግባኝ ፡ ተከሳሹ ፡ ባላምበራስ ፡ መንግሥቱ ፡ ታየ ፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያን ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰው ፡ ስለተወሰደባቸው ፡ ድንጋይ ፤ መሬት ፤ ኪሣራ ፡ እንዲከፍላቸው ፡ ጠይቀዋል ።

ተከሳሽ ፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ድንጋይ ፡ እንዲያቀርብልን ፡ ዋጋውን ፡ ልንከፍለው ፡ የተዋዋልነው ፡ ከካሎስ ፡ እና ስታሲዮስ ፡ ነው ። ከከሳሽ ፡ አንድም ፡ ግንኙነት ፡ አንድም ፡ ውል ፡ የለንም ። ስለ ዚህ ፡ ከሳሽ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ኪሳራ ፡ ለመክፈል ፡ አሳፊነት ፡ የለብንም ፡ ብለው ፡ ተከራከሩ ። ከሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ጋር ፡ ያላቸውንም ፡ ውል ፡ ለከሳሽ ፡ ሰጡ ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያን ፡ ክርክር ፡ አልተቀበለ ውም ። ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ (በይግባኝ ፡ ከሳሽ) ለባላምበራስ ፡ መንግሥቱ ፡ ታዬ ፡ (አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ተከሳሽ ፡ ለሆኑት) አምስት ፡ ሺህ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አርባ ብር ፡ እንዲከፍል ፡ ፈርዷል ።

ይግባኙ ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ሶሴል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያ ፡ ያቀረበው ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ ነው ። ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ከአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋር ፡ የመንገድ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ የተዋዋለ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ፤ እንግዲህ ፡ እሱ ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ነው ።

ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊውን ፡ ድንጋይ ፡ ለሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ለማ ቅረብ ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ከሶሴህ ፡ ቦኒህ ፡ ጋር ፡ ተዋዋለና ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ የሚ ሆነውን ፡ ድንጋይ ፡ ከያለበት ፡ የቆፈረ ፤ የፈለጠና ፡ ለሶሰል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያ ፡ ያቀ ረበው ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ መሆኑን ፡ በሶለል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያና ፡ በሙሴ ፡ ካሎስ ፡ መካ ከል ፡ በተደረገው ፡ ውልና ፡ በመከላከያ ፡ ምስክሮች ፡ ተረጋግጧል ።

ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ለመንገዱ ፡ ሥራ ፡ የሚሆነውን ፡ ድንጋይ ፡ ከካሎስ ፡ ከመቀበል ፡ በቀር ፡ ራሱ ፡ ከባለመሬቱ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ቆፍሮ ፡ አውጥቶ ፡ አልወሰደም ። ካሎስ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ባቀረበለት ፡ ድንጋይ ፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ የሚያሠራው ፡ መንገድ ፡ መሠራቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

ሶሰል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያ ፡ ለከሳሽ ፡ አሳፊነት ፡ አለበትን ? - ከከሳሽ ፡ መሬት ፡ ፈንቅሎ ፡ ለሶሴል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያ ፡ ለአቀረበው ፡ ድንጋይ፡ ግምቱን፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ለከሳሽ ፡ መክፈል ፡ አለበትን ? - ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከከሳሹ ፡ አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ተከሳሽ ፡ ከሆኑት ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ በተወሰደው ፡ ድን ጋይ ፡ ተከሳሽ ፡ (በይግባኝ ፡ ከሳሽ) ተጠቅሞበታልና ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ፡ ብሏል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ አሠሪ ፡ ካሎስ ፡ ሠራተኛ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ከሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ጋር ፡ የተዋዋለ ፡ ቢሆ

ንም ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራ ፡ ሠራተኛ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ አግኝቶታል ።

ሶሴል ፡ ቦኔሀ ፡ ኩባንያና ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ የተዋዋሉት፡ ውል ፡ እስከ ፡ አራተኛው ፡ ቁጥር ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ «ሥራ ፡ ተዋዋዩ፡ በራሳቸው፡ ኪሣራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የድንጋ ፡ ማውጫ ፡ ሥፍራ ፡ ለማግኘት ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ ሠርተው ፡ ለማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀቶችና ፡ ማዘዣዎች ፡ ለመቀበልና ፡ ለመያዝ ፡ ኃላፊ ፡ ናቸው ፤ ስለዚህም ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮችን ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ ሊያስጠይቃቸው ፡ አይችሉም » ይላል ።

የውሉም ፡ ፭ኛው ፡ ቁጥር ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ለሶሴል ፡ ቦኒሀ ፡ ኩባንያ ፡ ለሚያቀርበው ፡ ድንጋይ ፡ የሚከፈለውን ፡ ዋጋ ፡ ይናገራል ።

እንግዲህ ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺሕ፩፻፴፱ ፡ እንደተመለከተው ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺሕ፩፻፴ ፡ እንደተመለከተው፡ ያለ ፡ ሠራተኛ ፡ አይደለም ፤ ድንጋዩን ፡ በቀጥታ ፡ የሚያስቆፍረው ፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ፡ ኩባንያ ፤ ሙሴ ፡ ካሎስ የጉልበቱን ፡ ዋጋ ፡ እየተቀበለ ፡ በሶሴል ፡ ቦኒህ ፡ ሥር ፡ የሚሠራ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺሕ፩፻፴ ፡ መሠረት፡ የሚታይ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚሁ ፡ አይደለም ፤ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ተዋዋይ ፡ ሆኖ ፡ እሱ ፡ ከፈለገው ፡ ካገኘበት ፡ ቦታ ፡ ድንጋይ ፡ ፈልጎ ፡ ቆፍሮ ፡ ለሶሴል ፡ ቦኒህ ፡ ሊያቀርብና ፡ ዋጋውን ፡ ሊቀበል፡ ስለሆነ ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ፪ሺሕ፩፻፴፱ ፡ እንደተመለከተው ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራ ፡ ሠራተኛ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺሕ፩፻፴፱ ፡ «አንድ፡ ሰው፡ የተጠየቀውን፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ለሥራው ፡ ጥፋት ፡ ጥፋተኛው ፡ በሥራ ፡ ሰጪው ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነፃነቱን ፡ እንደያዘ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ አሠሪው ፡ በኢ ላፊነት ፡ አይጠየቅም » ይላል ።

ከዋናው ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ከሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ የበታች ፡ ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የሆነው ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ በሥራ ፡ ሰጭው ፡ በሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ ሥር ፡ ያልሆነ ፡ ነፃነቱን ፡ ይዞ ፡ የተዋዋለ ፡ ነው ። ለእንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ሠራተኛ ፡ አሠሪው ፡ አላፊነት ግ ሰበትም ፡ ተብሎ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺሕ፩፻፴፱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተደንግጓል -

ሶሰል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያ ፡ ድንጋይ ፡ ከተቆፈረበት ፡ ባለመሬት ፡ ጋር ፡ ውል ፡ የለውም ፤ ውሉ ፡ ድንጋዩን ፡ ከአስቆፈረው ፡ ከሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ በዚሁ ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ባስቆፈረና ፡ በአቀረበው ፡ ድንጋይ ፡ ሶሴል ፡ ቦኔህ ፡ ለሙሴ ፡ ካሎስም ፡ ባለመሬት ፡ ነኝ ፡ ለሚለውም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሊከፍል ፡ ነውን ? - ድንጋዩ ፡

ከእኔ ፡ መሬት ፡ ተቆፍሮ ፡ አንተ ፡ ለምታሠራው ፡ መንገድ ፡ ገብቷል ፡ ብሎ ፡ በከሰሰው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ከካሎስ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ውል ፡ ሰጥቶ ፡ እኔ ፡ አላፊነት ፡ የለብኝም ፡ ብሎታል ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከሳሽ ፡ (አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ተከሳሽ) ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ የሚያስቆፍረውን ፡ ሰው ፡ ለይቶ ፡ አውቋል ፤ ሶሌል ፡ ቦኒህም ፡ ውሉን ፡ በመስጠቱ ፡ ከሳሽ ፡ (አሁን ፡ በይግባኝ ፡ ተከሳሽ) ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ በሚጠየቀው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እንዳይደናገር ፡ በማድረጉ ፡ አንድም ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቅ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ፤ ከሳሽ ፡ ግን ፡ ቀጥታ ፡ ድንጋይ ፡ ወሰደ ፡ የተባለውን ፡ ካሎስን ፡ ትቶ ፡ ክሱን ፡ በሶሌል ፡ ቦኔህ ፡ ላይ ፡ መቀጠሉን ፡ ወደደ ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበው ፡ ድንጋይ ፡ የተጠቀመው ፡ ሶሌል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ ፈርዷል ።

ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቤቱን ፡ ለአንድ ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ በቁርጥ ፡ ዋጋ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነና ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ድንጋይ ፡ አሸዋም ፡ ከፈለገበት ፡ አምጥቶ ፡ ቤቱን ፡ የሠራ ፡ እንደሆነ ፡ ባለድንጋዩ ፤ ባለ ፡ አሸዋው ፡ ከቤትህ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የኔ ፡ ድንጋይ ፡ የእኔ ፡ አሸዋ ፡ ገብቷል ፤ ዋጋውን ፡ ክፈለን ፡ ብለው ፡ ሊጠይቁት ፡ ይችላሉ ፡ ወይ ? - አይችሉም - እውነት ፡ ነው ፤ ባለቤቱ ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ የሚከፍለው ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳለበት ፡ በቀሪው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ መጠየቅ ፡ ይችሉ ፡ ይሆናል ፡ እንጅ ፡ ባለቤቱ ፡ ለሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይቻልም ።

ስለዚህ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ከሕግ ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘውም ፤ በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባላምባራስ ፡ መንግሥቱ ፡ ታዬ ፡ በሶሰል ፡ በኒህ ፡ ኩባንያ ፡ ላይ ፡ ያቀረቡትን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ አድርጎታል ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ለውጦ ፡ ሙሴ ፡ ካሎስ ፡ ከባላምበራስ ፡ መንግሥቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወስዶ ፡ ለሶለል ፡ ቦኒህ ፡ ኩባንያ ፡ አቅርቧል ፡ የሚባለውን ፡ ድንጋይ ፡ ግምት ፡ ለመክፈል ፡ ሶሌል ፡ ቦኔህ ፡ ኩባንያ ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ ፈርዷል ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 1 A

SOLEL BONEH LTD. v. MENGISTU TAYE

Civil Appeal No. 1147/56

Obligations — Extra-contractual liability — Liability for the actions of others — Distinction between employee and independent contractor — Arts. 2130 and 2134 Civ. C.

On appeal from a judgment of the High Court awarding damages to respondent in payment for stone quarried from respondent's land by appellant's sub-contractor and used by appellant in the construction of a road.

Held: Judgment reversed and respondent's claim dismissed.

1. A contractor is not liable for the fault of an independent sub-contractor, regardless of the fact that the contractor makes use of materials supplied by the sub-contractor and which are the subject of the fault, Art. 2134 Civ. C.

2. A person who contracts with another to find materials and supply them at his own cost and upon his own responsibility, to obtain the necessary licenses and permits himself, and to be paid for what he supplies, is an independent contractor and not an employee, within the meaning of Arts. 2130 and 2134 Civ. C.

Hamle 11, 1956 E.C. (July 18, 1964 G.C.); Justices: Afenegus Kitaw Yitateku, Blatta Bekele Habte Michael, Ato Taddesse Tekle Giorgis: — Solel Boneh Ltd. contracted with the Highway Authority to build a road and then sub-contracted with Mr. Kalos in connection with building the road. Mr. Kalos, on the basis of this contract, quarried stone from the land of a private individual, Balambarass Mengistu Taye, to be used for the road.

The respondent, Balambarass Mengistu Taye, instituted a case in the High Court against Solel Boneh Ltd., claiming compensation for the value of the stone and land taken from him and for the resulting damages.

The defendant, Solel Boneh Ltd., contended that it had contracted to pay Mr. Kalos for the supply of stones necessary for the construction of the road and as no relationship, contractual or otherwise, existed between it and the plaintiff, it could not be held liable to pay damages claimed by him. Defendant then handed over to the plaintiff the document evidencing the agreement between it and Mr. Kalos.

The High Court did not accept the contention of Solel Boneh Ltd., and decided against Solel Boneh, ordering it to pay E$5940 to Balambarass Mengistu Taye.

The appeal is against this judgment.

The argument of Solel Boneh is based not on a question of fact, but on a question of law. It is not denied that Solel Boneh had contracted with the Highway Authority to build a road, and that it is, therefore, the main contractor.

It has been ascertained by defence witnesses and from the contract that Mr. Kalos was quarrying and supplying stone to Solel Boneh.

Apart from receiving stones from Mr. Kalos, Solel Boneh did not directly quarry or take any stones from the respondent's land. It has not been denied that Solel Boneh built the road with the stones it took from Mr. Kalos according to its contract. Therefore, the question is whether Solel Boneh is responsible to the respondent. Is Solel Boneh liable to pay the value of the stone that was taken from the respondent's land and given to it? The High Court has said that, since the appellant made use of the stone quarried from the land of the respondent, the appelant must pay.

But it is necessary to recognize that although Solel Boneh is the main contractor and Mr. Kalos is a sub-contractor, Mr. Kalos is an independent person who must fulfill his own legal obligations.

The fourteenth clause of the contract between Solel Boneh and Mr. Kalos states: "The sub-contractor shall be responsible for finding the appropriate quarries and for obtaining and securing the necessary licences and permits for exploitation of same at his own cost, and without in any way involving the contractors."

Clause nine of the contract fixes the price to be paid by Solel Boneh to Mr. Kalos. Therefore, Mr. Kalos is an independent worker under Article 2134 of the Civil Code, but not an employee governed by Article 2130 of the Civil Code. Article 2130 would have applied if it were Solel Boneh who was quarrying the stone and Mr. Kalos was a hired labourer doing such work for him.

Since Mr. Kalos is an independent contractor who has agreed to find stone from any place upon his own responsibility and to be paid for what he supplies, he is an independent worker, or contractor, under Article 2134.

Civil Code Article 2134 states: "A person shall not be liable for the faults or offences committed by another while carrying out work which he has asked him to do, where the author of the offence is not subject to the former's authority and is to be considered as having retained his independence."

Mr. Kalos was working as a sub-contractor and thus was not directly under the supervision of Solel Boneh but rather contracted independently under his own free-will. Civil Code Article 2134 clearly states that contractors like Solel Boneh are not responsible for their sub-contractors when the relationship is as it was in this case.

Solel Boneh does not have any contract with the owner of the land from which stone was quarried. Solel Boneh's contract was signed with Mr. Kalos. Must Solel Boneh pay twice for the stones he receives, once to Mr. Kalos and

a second time to the land-owner? When the respondent sued for the value of the stones used by Solel Boneh in its construction, Solel Boneh showed the respondent the contract he had with Mr. Kalos, which stated that it was not responsible. At this time, therefore, the land-owner must have known exactly the person who was quarrying the stones from his land. Solel Boneh, in showing the contract to the respondent, tried to help the respondent not to make an error in filing suit. But the respondent, rather than suing Mr. Kalos, preferred to sue Solel Boneh.

The High Court, noting only that it was Solel Boneh who used the stones for construction, gave its decision in favour of the respondent.

If a person gives a contract for the construction of a house, can it be said that the owner of the stones and sand used in building the house may claim from the owner of the house for the value of such materials?

This is not possible. It is true that, if there is an amount which the owner has not paid to the contractor, the owner of the materials may claim from the person on whose behalf the work was done to the extent of the amount due by him to the independent contractor.

Therefore, we do not find the judgment of the High Court to be in conformity with the law. For these reasons, the Supreme Imperial Court has dismissed the claim of Balambarass Mengistu Taye against Solel Boneh Ltd.; reversing the judgment of the High Court, the Supreme Imperial Court holds that Solel Boneh is not liable to pay Balambarass Mengistu Taye.

ጠቅላይ ፣ የንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፤

አንደኛ ፣ ችሎት ።

ስለ ፣ ወይዘሮ ፣ በየነች ፣ አባ ፣ ነብሮ ፣ ንብረት ፣ ጉዳይ ።

የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ይግባኝ ፣ ቁጥር ፣ ፪፻፷፯/፶፰ ዓ. ም. ።

ስለ ፣ ውርስ — የኑዛዜ ፣ ፎርም — ልማዳዊ ፣ ሕግ — የተናዛዥ ፣ ችሎታ — የምስክሮች ፣ ተጠቃሚነት — ከወራሽነት ፣ ስለመቀንል — የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጾች ፣ ፰፻፹ ፣ ፰፻፹፩ ፣ ፰፻፹፪ ፣ ፱፻፴፩ ፣ ፱፻፴፰ እና ፣ ፪፲፪፻፶፰ ፤ የፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ አንቀጽ ፣ ፵፩ ።

አመልካቾች ፣ ኑዛዜው ፣ እንዲሻርላቸው ፣ ያቀረቡትን ፣ ማመልከቻ ፣ ከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ስላልተቀበላቸው ፣ ይህ ፣ ይግባኝ ፣ ቀረበ ።

ውሳኔ ፤ የከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ፍርድ ፣ ጸንቶአል ።

፩/ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ከመጽናቱ ፣ በፊት የተደረገ ፣ ኑዛዜ ፣ በተናዛዡና ፣ በምስክሮች ፣ ፊት ፣ የተነበበ ፣ ከሆነ ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ ይሐው ፣ ሥርዓት ፣ መፈጸሙ ፣ የተጻፈበት ፣ ባይሆንም ፣ በልማዳዊ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የጸና ፣ ይሆናል ።

፪/ በልማዳዊው ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የተናዛዡና ፣ የምስክሮቹ ፣ ፊርማ ፣ በኑዛዜው ፣ መጨረሻ ፣ ገጽ ፣ ላይ ፣ ብቻ ፣ የሰፈረ ፣ እንደሆን ፣ በቂ ፣ ነው ።

፫/ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፰፻፹፩ ፣ እና ፣ ፰፻፹፪ ፣ በተናዛዡ ፣ ጽሑፍ ፣ የሚደረግ ፣ ኑዛዜ ፣ የተናዛዡ ፣ ፊርማ ፣ በየገጹ ፣ ላይ ፣ እንዲሰፍር ፣ ያዛሉ ፣ እንጂ ፣ በግልጽ ፣ ለሚደረግ ፣ ኑዛዜ ፣ ላይ ፣ ይህ ፣ ሥርዓት ፣ ተፈጻሚ ፣ አይሆንም ፣

፬/ ኑዛዜው ፣ በተደረገበት ፣ ወቅት ፣ ተናዛዡ ፣ በአካል ፣ የደከሙ ፣ ቢሆንም ፣ ግልጽ ፣ የሆነ ፣ የአእምሮ ፣ መጓደል ፣ ነበረባቸው ፣ ካልተባለ ፣ በቀረ ፣ ኑዛዜ ፣ ሊሻር ፣ አይቻልም ።

፭/ በኑዛዜ ፣ ውስጥ ፣ ለገዳም ፣ የተሰጠ ፣ ንብረት ፣ ያለ ፣ እንደሆነ ፣ በዚሁ ፣ ገዳም ፣ አገልጋይ ፣ የሆኑ ፣ የኑዛዜ ፣ ምስክሮች ፣ በኑዛዜው ፣ ተጠቃሚዎች ፣ ናቸው ፣ አያሰኛቸውም ።

፮/ አውራሽ ፣ ከወራሾቹ ፣ መሐል ፣ አንዱን ፣ ካንዱ ፣ ለማላቅ ፣ መብት ፣ አለው ።

፯/ በልማዳዊው ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ አውራሽ ፣ ሕጎ ፣ ከሚፈቅድላቸው ፣ ከወራሾቹ ፣ አንዱን ፣ ምክንያቱንያቱን ፣ ለመግለጽ ፣ ሳይገደድ ፣ ከወራሽነት ፣ ለመንቀል ፣ ይችላል ።

ጥቅምት ፣ ፲፱ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፰ ፣ ዓ·ም ። ዳኞች ፤ - አፈ ፣ ንጉሥ ፣ ቅጣው ፣ ይታጠቁ ፣ ብላታ ፣ በቀለ ፣ ሀብተ ፣ ሚካኤል ፣ አቶ ፣ ታደሰ ፣ ተክለ ፣ ጊዮርጊስ ። በከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ከሳሾች ፤ አሁንም ፣ በይግባኝ ፣ ከሳሾች ፣ የሆኑት ፣ ወይዘር ፣ አስቴር ፤ ወይዘሮ ፣ ባንቺ ፣ አይሞሉ ፤ ወይዘሮ ፣ አሳመነች ፣ ናቸው ፤ ተከሳሽም ፣ ወይዘሮ ፣ አበካለ ፣ ናቸው ።

በከሳሾችና ፡ በተከሳሽ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ክርክር ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ አባ ነብሮ ፡ ውርስ ፡ ነው ። ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ አባነብሮ ፡ ኑዛዜ ፡ አላቸው ፤ ኑዛዜው ፡ የተደረገው ፡ በኅዳር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ነው ። ሶስቱ ፡ በይግባኝ ፡ ከሳሾች ፡ ኑዛዜው ፡ እንዲፈርስ ፡ ጠያቂዎች ፡ ናቸው ። ኑዛዜው ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚጠይቁባ ቸው ፡ ምክንያቶች ፤

፩- የኑዛዜው ፡ ጽሑፍ ፡ በየገጹ ፡ ያልተፈረመበት ፡ ነው ፤ ስርዝ ፤ ድልዝ ፤ ፍቀት ፤ አለበት ።

፪- ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ አጻፉ ፡ በተባለበት ፡ ቀን ፡ አእምሮአቸው ፡ ትክ ክል ፡ አልነበረም ።

፫- እናዛዦች ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ለራሳቸው ፡ ስጦታ ፡ ለማግኘት ፡ የጻፉት ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ አይደለም ።

፬- ለአስቴር ፡ አባት ፡ ለዓለማየሁ ፡ ፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ የሰጡትን ፡ እል ቅናና ፡ ርስት ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ አፍርሶታል ፡ በማለት ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ኑዛዜ ፡ የተባለው ፡ ፈርሶ ፤

፭- ፊታውራሪ አባነብሮ ፡ ለዓለማየሁ ፡ በኑዛዜአቸው ፡ የሰጡትን ፡ ልጁ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ እንድትወስድ ፤ የቀረውን ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ውርስ ፡ ውስጥ፡ የሚገኘውን ፡ ንብረት ፡ ሶስቱ ፡ ከሳሾችና ፡ ተከሳሿ ፡ እኩል ፡ መካፈል ፡ ይገባቸ ዋል ፡ ሲሉ ፡ አመልክተዋል ።

ተከሳሽ ፡ ግን ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ሲናዘዙ ፡ አእምሮአቸው ፡ ትክክል ፡ ነበር ። የኑዛዜአቸውም ፡ ጽሑፍ ፡ ሚችቷም ፡ እናዛገሮችም ፡ የፈረሙበት ፡ ስለሆን፡ ደንብ ፡ የሞላ ፡ ነው ፤ የኑዛዜ ፡ ምስክሮች ፡ የሆኑት ፡ ለራሳቸው ፡ የሚጠቀሙበት ፡ ስጦታ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ የለም ።

ዓለማየሁ ፡ በእናቱ ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ላይ ፡ የተኮሰ ፤ ለመግደል ፡ የሞከረ ፡ ስለሆነ ፤ ልጁ ፡ ከወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ውርስ ፡ ማግኘት ፡ አይገባትም ፤ በፊታውራሪ ፡ አባ ፡ ነብሮ ፡ ኑዛዜ ፡ ለዓለማየሁ ፡ የተሰጠውን ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ አፍ ርሶ ፡ ለሌላ ፡ አልሰጠም ፡ ብለው ፡ ተከራክረዋል ።

በይግባኝ ፡ ከሳሾች ፡ ሶስቱም ፡ በአንድነት ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ ይፍ ረስ ፡ ባዮች ፡ ስለሆኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ኑዛዜው ፡ ይፈርሳል ፡ አይፈርስም ፡ የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ዓይተን ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ውርስ ፡ ለወራሾች ፡ ሚተላለፈው ፡ በኑዛ ዜው ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ መወሰን ፡ አለብን ።

ስለዚህ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ የሚጸና ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ እንመረምራለን ።

ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ የተናዘዙት ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ነው ። ስለዚህ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ·ም ፡ አዲሱ፡ የፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ፡ በፊት፡ የተደረገ፡ ኑዛዜ፡ ነው ።

አዲስ ፡ ሕግ ፡ ሲወጣ ፡ በአዲሱ ፡ ሕግና ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሲኖር ፡ መፈረድ ፡ የሚገባው ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ ክርክር ፡ ስለሚነሳ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፪ ፡ እና ፡ ፳፩ ፡ የተመለከተው ፡ መሸጋገሪያ ፡ ሕግ ፡ የተሠራው ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ክርክር ፡ ነው ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከጸናበት ፡ ከመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ·ም ፡ በፊት ፡ ስለተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፩ ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ "ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተደረገ ፡ ኑዛዜ ፡ የሚጸናው ፡ (ሀ) በተሻረው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚጸና ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፤ (ለ) ይህ ፡ ደንብ ፡ በሚጠይቀው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ነው" ይላል ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፰ ፡ እንደሚያዘው፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተሠራ ፡ ኑዛዜ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ በሁለቱም ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የተሠራ ፡ ኑዛዜ ፡ ይጸናል ።

አዲሱ ፡ ሕጋችን ፡ ከቀድሞ ፡ የኑዛዜ ፡ ሕጋችን ፡ (ልማዳችን) ይስማማል ፤ በአንዳንድ ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ልዩነት ፡ ቢኖረውም ፡ በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ነው ።

በቁጥር ፡ ፳፻፳ ፡ እንደተመለከተው ፤ በአዲሱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጋችን ፡ ሶስት ፡ ዓይነት ፡ የኑዛዜ ፡ ፎርሞች ፡ አሉ ፤

(ሀ) በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡

(ለ) በተናዛዥ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡

(ሐ) በቃል ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ሶስቱም ፡ ዓይነት ፡ ኑዛዜዎች ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ በልማዳችንም ፡ ያሉ ፡ ናቸው ።

የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ የተባለው ፡ ዓይነት ፡ ነው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፳፩ ፡ በግልጽ ፡ ስለሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ (፩) በግልጽ ፡ የሚደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ተናዛዡ ፡ እየተናገረ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ወይም ፡ ተናዛዡ ፡ ራሱ ፡ የሚጽፈው ፡ ነው ፤ (፪) ኑዛዜው ፡ በተናዛዡና ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ካልተነበበና ፡ ይኸም ፡ ሥርዓት ፡ (ፎርማሊቲ) መፈጸሙንና ፡ የተጻፈበትንም ፡ ቀን ፡ የሚያመለክት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፤ (፫) ተናዛዡና ፡ ምስክሮቹ ፡ በኑዛዜው ፡ ላይ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፊርማቸው ፡ ወይም ፡ ያውራ ጣት ፡ ምልክታቸውን ፡ ካላደረጉበት ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ይላል ።

ስለ ፡ ኑዛዜው ፡ አጻጻፍ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፩ ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ። " አዝዞስ ፡ ይኩን ፡ በጽሒፍ ፡ ወዘእንበለ ፡ ጽሒፍ ፡ በትእዛዝ ። በእንተ ፡

ጽሒፍ ፡ ትትፌጸም ፡ በጽሒፈ ፡ ጸሐፊ ፡ አው ፡ በጽሒፍ ፡ ዘያማሕፅንዎ ። ወስምዓ ፡ ይኩኑ ፡ በውስቴታ ፡ እለ ፡ ጉቡአን ፡ እሙንቱ ፡ ወይኩን ፡ ሁልቆሙ ፡ ፯ ፡ ፡ አው ፡ ፭ ፡ ለእመ ፡ ይትከሀል ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ሰለስተ ፡ አው ፡ ክልኤተ ። ” “ በደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ መናዘዝ ፡ (ማናዘዝ) ይገባል ፤ ያለደብዳቤ ፡ መናዘዝ ፡ ይገባል ፤ በደብዳቤ ፡ የምትሆን ፡ ኑዛዜ ፡ ጸሐፊ ፡ ቢጽፋት ፡ ባላደራ ፡ ቢጽፋት ፤ ተናዛዡ ፡ ቢጽፋት ፡ ያም ያም ፡ ቢጽፋት ፡ ከምስክሮቹ ፡ አንድ ፡ የምትሆን ፡ ደብዳቤ ፡ በምትጻፍበት ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮቹ ፡ ቢቀመጡ ፡ ትጸናለች ፤ የምስክሮቹ ፡ ቁጥራቸው ፡ ቢቻል ፡ ሰባት ፤ አምስት ፤ ባይቻል ፡ ግን ፡ ሶስት ፤ ሁለት ” እንዲሆኑ ፡ ይፈቅድ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ምስክሮቹ ፡ ከአራት ፡ ያነሱ ፡ እንደሆነ ፡ ኑዛዜው ፡ የማይጸና ፡ ነው ፡ ብሏል ። ብዙ ፡ ምስክሮች ፡ ለማግኘት ፡ የማያስችል ፡ የመከራ ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፤ በልማዳችን ፡ ለኑዛዜ ፡ ምስክሮች ፡ ከ፯ ፡ ከ፭ ፡ ምስክሮች ፡ ያነሱ ፡ አይደረግም ፡ ነበር ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፹፩ ፤ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ በመሠረቱ ፡ ከቀደሞ ፡ ሕጋችን ፡ የተስማማ ፡ ነው ፤ ቢሆንም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ከቀድሞው ፡ ሕጋችን ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ኑዛዜው ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ በተናዛዡና ፡ በ፬ ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ካልተነበበና ፡ ይኸውም ፡ ሥርዓት ፡ መፈጸሙን ፡ የሚገልጽ ፡ ቃል ፡ ኑዛዜው ፡ ላይ ፡ ካልተጻፈ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ነው ። በቀድሞ ፡ ሕጋችን ፡ ኑዛዜው ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ በተናዛዡና ፡ በምስክሮቹ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ይነበባል ፡ እንጂ ፡ ተነቧል ፡ ተብሎ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ አይጻፍም ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኑዛዜው ፡ አይፈርስም ፡ ነበር ።

በአሁኑ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ የኑዛዜው ፡ ቃል ፡ በተናዛዡና ፡ በ፬ቱ ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ተነቧል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በኑዛዜው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ ኑዛዜ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ የተደረገው ፡ የንስሐ ፡ አባታቸው ፡ ጭምር ፡ ፯ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ነው ። በኑዛዜውም ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ በጣት ፡ ፊርማ ፡ ፈርመዋል ፤ የምስክሮቹም ፡ ፊርማ ፡ አለበት ።

እንግዲህ ፡ አዲሱም ፡ ሕግ ፡ እንደሚጠይቀው ፡ ደንብ ፡ ኑዛዜው ፡ በተናዛዡና ፡ በምስክሮቹ ፡ ፊት ፡ ተነባል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ካለመጻፉ ፡ በስተቀር ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ አጻጻፉ ፡ ከቀድሞው ፡ ከአዲሱም ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ነው ።

የከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ በየገጹ ፡ ላይ ፡ አልተፈረመበትም ፡ ይላሉ ። ኑዛዜው ፡ በሁለት ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ ሆኖ ፡ የተፈረመው ፡ በኑዛዜው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ከቀድሞው ፡ ሕጋችን ፡

ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ነው ። በአዲሱም ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፹፬ ፡ ኑዛዜው ፡ በየገጽ ፡ ላይ ፡ እንዲፈረምበት ፡ የሚያዘው ፡ በግልጽ ፡ በምስክሮች ፡ ፊት ፡ ሳይሆን ፡ በተናዛዡ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚደረገውን ፡ ኑዛዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፣ በቁጥር ፡ ፫፻፹፭ ፡ መሠረት ፡ በግልጽ ፡ የሚደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ ተናዛዡና ፡ ምስክሮቹ ፡ በኑዛዜው ፡ ላይ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፊርማቸውን ፡ ወይም ፡ ያውራጣት ፡ ምልክታቸውን ፡ ያደርጋሉ ፡ ይላል ፡ እንጅ ፣ በየገጹ ፡ ካልተፈረመበት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ አይልም ። ስለዚህ ፡ ከሳሾች ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኑዛዜው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ በይግባኝ ፡ ከሳሾች ፡ ኑዛዜው ፡ ስርዝ - ድልዝ ፣ ፍቀት ፡ አለበት ፡ ይላሉ ፤ ግን ፡ በኑዛዜው ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የለበትም ።

ኑዛዜው ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ አእምሮ ፡ በትክክል ፡ አልነበረም ፡ ስለተባለው ፡ ተከሳሽ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የኑዛዜ ፡ ምስክሮች ፡ አስመስክረዋል ። ምስክሮቹ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ እራሳቸው ፡ እየተናገሩ ፡ ከምስክሮቹ ፡ አንዱ ፡ አቶ ፡ አርአያ ፡ ማሞ ፡ እየጻፈ ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ ተነበ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ እኛም ፡ ምስክሮቹ ፡ ፈርመንበታል ፣ ማኅተሟ ፡ ቢታመሙም ፡ የተናዘዙት ፡ አልጋቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነው ፣ አእምሮአቸው ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መስክረዋል ። ከሳሾችም ፡ ስለ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ አእምሮ ፡ ያስመሰከሩአቸው ፡ ምስክሮች ፡ አንዳንዶች ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ የደከሙ ፡ ምግብ ፡ የማይቀበሉ ፡ ነበሩ ፤ የሚነጋገሩትም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በደከመ ፡ ቃል ፡ ነበር ፤ ቢሉም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የአእምሮ ፡ መጥፋት ፡ ነበረባቸው ፡ ካልተባለ ፡ በቀር ፡ ኑዛዜ ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ። ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ የተናዘዙት ፡ የሞቱትም ፡ ደብረሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሆድ ፡ ህመም ፡ እንደነበረባቸውና ፡ በዚሁ ፡ ሕመም ፡ እንደሞቱ ፡ ምስክሮቹ ፡ መስክረዋል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የኑዛዜ ፡ ምስክሮችን ፡ ሰምቶ ፡ የእነሱን ፡ ምስክርነት ፡ የታመነ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ በትክክል ፡ አእምሮ ፡ ነው ፡ የተናዘዙት ፡ ብሏል ፣ ይህም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሃሳብ ፡ ይስማማል ።

የኑዛዜ ፡ ምስክሮች ፡ በኑዛዜው ፡ ተጠቃሚዎች ፡ ናቸው ፡ ለተባለው ፡ በኑዛዜአቸው ፡ ውስጥ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ የካ ፡ የሚገኘውን ፡ ርስቴን ፡ ከነቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ማህበር ፡ ለተክለሃይማኖት ፡ ስለዝክሬ ፡ ይሁን ፡ ብዬ ፡ ሰጥቻለሁ ። ይኸውም ፡ በወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይሁን ፡ ማለት ፡ የኑዛዜ ፡ ምስክሮች ፡ በኑዛዜው ፡ ተጠቃሚዎች ፡ ናቸው ፡ አያሰኛቸውም ። ከምስክሮቹም ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ አገልጋይ ፡ የሆኑ ፡ ቢኖሩባቸውም ፡ ለነፍሴ ፡ ብለው ፡ ከሟቿ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰጠውን ፣ ለምስክሮች ፡ የተሰጠ ፡ ነው ፡ አይባልም ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነጋገሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ኑዛዜው ፡ እንዲፈርስ ፡ ሶስቱም ፡ በይግባኝ ፡ ከሳሾች ፡ የጠየቁት ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ።

ሶስቱ ፡ ከሳሾች ፡ በአንድነት ፡ ሆነው ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ ይፈርሳል ፡ ብለው ፡ የተከራከሩበትን ፡ ጨርሰን ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ዓለማየሁ ፤ ፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ለአባቱ ፡ ለአቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ በኑዛዜ ፡ የሰጡትን ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ተናዘውበታል ፤ አይጸናም ፤ ሁለተኛም ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ እኔን ፡ በግልጽ ፡ ከውርስ ፡ የሚነቅለኝ ፡ ቃል ፡ የለበትምና ፡ አይጸናብኝም ፤ ድርሻዬን ፡ ማግኘት ፡ ይገባኛል ፡ ብለው ፡ የተከራከሩትን ፡ እንመረምራለን ።

ፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ለልጃቸው ፡ ለወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ሲናዘዙ ፡ ለወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ልጅ ፤ ለፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ለአቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ መናዘዛቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። የፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ኑዛዜ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ። "አንቺ እንደእኔ ፡ የቀደምሽ ፡ እንዳሆን ፡ እልቅናውን ፡ ለዓለማየሁ ፡ ስጭ ። ግን ፡ እኔ ፡ ስጭ ፡ ስላልኩሽ ፡ ፈቃድሽን ፡ የማይፈጽም ፤ ርስት ፡ የሚሸጥ ፤ ሰው ፡ የማይሰበስብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አይተሽ ፡ ለወለድሻቸው ፡ ልጆች ፡ ስጭ ። አልዳርኩትምና ፡ አሳምረሽ ፡ ዳሪው ። አንድ ፡ ጥንድ ፡ በሬ ፡ ከነመጫሪያው ፡ ሁለት ፡ ጊደሮች ፡ ሰይዶ ፡ የሰጠኝን ፡ በቅሎ ፡ አንድ ፡ ኢጋሰስ ፡ ሁለት ፡ ምንጣፍ ፤ አንድነት ፡ አንድ ፡ ጀባ ፡ ሐሮ ፡ አርባ ፡ ሁዳድ ፡ ቡናውንና ፡ ማሣውን ፡ ከጨፌው ፡ ግማሹን ፡ ይውሰድ ፡ ከዚሁ ፡ ከከተማው ፡ ከቡናው ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ቀጠና ፡ መሬት ፡ ለችና ፡ አቧንና ፡ አረዳውን ፡ ከነቡናው ፡ ይውሰድ ።" ቀጥሎ ፡ ኑዛዜው ፤ "መሬቱ ፡ ጊዶ ፡ ከነቡናው ፡ ለልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ መሪ ፡ ጌትነቱን ፡ ሰጥቻለሁ" ይላል ። ፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ በዚህ ፡ ኑዛዜ ፡ ለልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ የሰጡትን ፡ ርስት ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ አልተናዘዙበትም ። የወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ግንዛብ ፡ ነው ።

ወይዘሮ ፡ በየነችም ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ ተናዘዋል ። "አባቴ ፡ በእግሬ ፡ የረገጥኩትን ፡ በእጄ ፡ የጨበጥኩትን ፡ ብለው ፡ ስለሰጡኝ ፤ እኔም ፡ በጠቅላላው ፡ አባቴ ፡ እንደእኔ ፡ በሆንሽ ፡ ጊዜ ፡ ከወለድሻቸው ፡ ልጆች ፡ መርጠሽ ፡ ስጪ ፡ ስላሉኝ ፡ እኔም ፡ በጠቅላላው ፡ በእጄ ፡ የሚገኘውን ፡ እርስቴን ፡ ወላ ፡ ስማውን ፡ በሞላ ፡ ለወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ መሸሻ ፡ እርስቴን ፡ ከነእልቅናው ፡ ጭምር ፡ ሰጥቻታለሁ ።"

እልቅናውንና ፡ የእልቅናውን ፡ መብት ፡ ቢኖር ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ለልጃቸው ለወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ ሰጥተዋል ። ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ዓለማየሁ ፡ እልቅናውን ፡ ፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ የሰጡት ፡ ለአባቴ ፡ ለአቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ስለሆነ ፡ ለእኔ ፡ መተላለፍ ፡ ይገባዋል ፡ ይላሉ ።

የፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ኑዛዜ ፡ እልቅናው ፡ ለዓለማየሁ ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚለው ፡ ብዙ ፡ ግዴታዎች ፡ የተፈጸሙ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

አንደኛ ፤ « አንቺ ፡ እንደእኔ ፡ የቀደምሽ ፡ እንደሆን » ይላል ።

> « ፈቃድሽን ፡ የማይፈጽም ፤ ርስት ፡ የሚሽጥ ፤ ሰው ፡ የማይሰበስብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አንቺ ፡ ዓይተሽ ፡ ለወለድሻቸው ፡ ልጆች ፡ ስጭ » ይላል ።

ፊታውራሪ ፡ አባነብር ፡ አንቺ ፡ እንደኔ ፡ የቀደምሽ ፡ እንደሆነ ፡ ያሉት ፡ እሳቸው ፡ ከልጃቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ በየነች ፡ በፊት ፡ ስለሞቱ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነችም ፡ ከልጃቸው ፡ ከዓለማየሁ ፡ በፊት ፡ የሞቱ ፡ እንደሆነ ፡ ማለታቸው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ከእናቱ ፡ ከወይዘሮ ፡ በየነች ፡ በፊት ፡ ሞቷል ። እሱ ፡ ቋሚ ፡ ሆኖ ፡ ያልወረሰውን ፡ እልቅና ፡ ልጁ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ልትወርስ ፡ አይገባትም ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ፈቃድሽን ፡ የማይፈጽም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አንቺ ፡ ለፈቀድሽው ፡ ስጭ ፡ ስላሏቸው ፡ እሳቸውም ፡ እንደአባቴ ፡ ቃል ፡ እኔም ፡ ለወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ ሰጥቻለሁ ፡ ብለው ፡ ተናዘዋል ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በእልቅና ፡ ምክንያት ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ የሚሻርበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

ሁለተኛ ፤ - የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴርን ፡ በግልጽ ፡ ከርስት ፡ አይነቅልም ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ነገር ፤

ኑዛዜ ፡ በሌለና ፡ የሟች ፡ ውርስ ፡ ለወራሾች ፡ የሚተላለፈው ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፤ ሟችን ፡ የሚወርሱት ፡ በሕይወት ፡ ያሉት ፡ ልጆችና ፡ ከልጆች ፡ አንዱ ፡ ዘር ፡ ትቶ ፡ ከአባቱ ፡ ቀድሞ፡ ሞቶ ፡ እንደሆነ ፡ በአባቱ ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴርን ፡ ወልዶ ፡ ከእናቱ ፡ ከወይዘሮ ፡ በየነች ፡ በፊት ፡ በኢጣሊያኖች ፡ እጅ ፡ ተደብድቦ ፡ በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞቷል ።

የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ኑዛዜ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴርን ፡ አያነሳም ። ስለዚህ ፡ በአባታቸው ፡ ተተክተው ፡ መውረስ ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚሉ ፡ ክርክር ፡ ተነስቷል ።

የወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ ጠበቃ ፤ አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ወራሽ ፡ መሆን ፡ የማያስችለው ፡ በደል ፡ በእናቱ ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ላይ ፡ መፈጸሙን ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስመስክሬአለሁ ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ከወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ የማያወርሰውን ፡ የወይዘሮ ፡ በየነችን ፡ ኑዛዜ ፡ አጽድቆታል ፡ ብለው ፡ ተከራክረዋል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ በእናቱ ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ሠርቷል ፡ ለተባለው ፡ ነገር ፡ ጽሑፍ ፡ ማስረጃና ፡ የምስክሮች ፡ ቃል ፡ ተቀብሏል ።

ጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በየካቲት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም. የጨርጨር ፡ አውራጃ ፡ አበጋዝ ፡ አዛዥ ፡ ወርቅነህ ፡ የጻፉት ፡ ነው ። ወይዘሮ ፡ በየነች ፡

ዓለማየሁና ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ የሚባሉ ፡ ዋንዘቤን ፡ ዘርፈውኛል ፡ ብላለችና ፡ ዓለ ማየሁና ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ የሚባሉ ፡ ተይዘው ፡ እንዲመጡ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ነው ።

ምስክሮችም ፡ አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በእናቱ ፡ በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ጥይት ፡ ተኩሰባቸዋል ፤ ዘወትርም ፡ ይጣሉ ፤ ይረግሙት ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ መስክረዋል ። የተመሰከረው ፡ ቃልና ፡ ጽሑፍም ፡ ዓለማየሁ ፡ በእናቱ ፡ ላይ ፡ የመ ግደል፡ሙከራ፡የገንዘብም ፡ መውሰድ፡በደል፡ሠርቶባቸው፡እንደነበረ፡አስረድቷል።

የወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ጠበቃ ፤ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ "ኢጣሊያኖች ፡ ወስደው ባቸው ፡ እርስት ፡ ለማስመለስ ፡ በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በጻፉት ፡ የልመና ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፤ ዓለማየሁን ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ሽፍታ ፡ ነህ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶብሃል ፡ ስላሉት ፡ ልጄን ፡ ከምትገድሉት ፡ እርስቴን ፡ ልፈ ርምላችሁና ፡ ያበያ ፡ በሬ ፡ እናቱ ፡ ትቃረዳለችና ፤ ስለልጄ ፡ እኔን ፡ ግደሉኝ ፤ እሱን፡ በእስራት ፡ ቅጡት ፡ ብዬ ፡ ልመና ፡ ባቀርብ ፡ አንምርም ፡ ብለው ፡ እፊቴ ፡ በዘጠኝ፡ ጥይት ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ። ከ፫ ፡ ወር ፡ በኋላም ፡ መሬቶችን ፡ ሁሉ ፡ አንው ሰድ ፡ ፈርመሽ ፡ ልቀቂልን ፡ ቢሉኝ ፡ ሕይወቴን ፡ ያቆየሁ ፡ መስሎኝ ፡ መፈረሜ እርግጥ ፡ ነው" ብለው ፡ ጽፈዋል ፡ አሉ ።

ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ አባነብሮ ፡ ቢበድለኝም ፡ ምሬዋለሁ ፡ ብለው ፡ በኑዛ ዜአቸው ፡ ለልጅ ፡ ካላወረሱ ፡ ይህ ፡ ርስታቸውን ፡ ለራሳቸው ፡ ለማስመለስ ፡ የጻ ፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ልጃቸውን ፡ ዓለማየሁ ፡ አባነብሮን ፡ የማሩት ፡ መሆኑን ፡ የሚያ ስረዳ ፡ አይደለም ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳልነው ፡ የፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ኑዛዜ ፡ "አንቺ ፡ እንደእኔ ፡ የቀደምሽ ፡ እንደሆነ ፡ እልቅናውን ፡ ለዓለማየሁ ፡ ስጭ ። ግን ፡ እኔ ፡ ስጭ ፡ ስላልኩሽ ፡ ፈቃድሽን ፡ የማይፈጽም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ዓይተሽ ፡ ለወለ ድሻቸው ፡ ልጆች ፡ ስጭ" ይላል ።

ወይዘሮ ፡ በየነችም ፡ "አባቴ ፡ በእግሬ ፡ የረገጥሁትን ፡ በእጄ ፡ የጨበጥሁ ትን ፡ ብለው ፡ ሰለሰጡኝ ፤ እኔም ፡ በጠቅላላው ፡ አባቴ ፡ እንደእኔ ፡ በሆንሽ ፡ ጊዜ ፡ ከወለድሻቸው ፡ ልጆች ፡ መርጠሽ ፡ ስጭ ፡ ስላሉኝ ፤ እኔም ፡ በጠቅላላው ፡ በእጄ የሚገኘውን ፡ ርስቴን ፡ ወላስማውን ፡ በሞቴ ፡ ለወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ መሸሻ ፡ እር ቴን ፡ ከነእልቅናው ፡ ጭምር ፡ ሰጥቻለሁ" ብለው ፡ ተናዘዋል ።

ፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ "አንቺ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ የቀደምሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዓይ ተሽ ፡ ለወለድሻቸው ፡ ልጆች ፡ ስጭ" ፡ በሚለው ፡ ኑዛዜ ፡ መሠረት ፡ የልጅ ፡ ልጃ ቸውን ፡ አስቴርን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ባንቺ ፡ አይሞሉንና ፡ ወይዘሮ ፡ አሳመ ነችንም ፡ ትተው ፡ እልቅናውን ፡ ለወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ ሰጡ ። ንብረቱን ፡ ከአስገ ኙት ፡ ከአባታቸው ፡ ከፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ በተሰጣቸው ፡ መብትና ፡ በራሳቸ ውም ፡ መብት ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ፈቃዴን ፡ የፈጸመች ፡ አስካለ ፡ ነች ፡ ብለው ፡

እልቅናውንና ፡ የሚበልጠውን ፡ ንብረት ፡ ለወይዘሮ ፡ እስካለ ፡ ቢሰጡ ፡ የሚቀነስበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። አውራሽ ፡ ከአውራሾቹ ፡ አንዱ ፡ ፈቃዴን ፡ ፈጽሟል ፡ ብሎ ፡ ለማላቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ለወይዘሮ ፡ ባንቺ ፡ አይሞሉና ፡ ለወይዘሮ ፡ አሳመነች ፡ አነስተኛ ፡ ውርስ ፡ ሰጥተዋል ። ለወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ አባት ፡ ይገባ ፡ የነበረውን ፡ ለወይዘሮ ፡ እስካለ ፡ ሰጥተዋል ። ለወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ግን ፡ ለአባቷ ፡ ይገባ ፡ የነበረውን ፡ አባቷ ፡ ስለበደላቸው ፡ ለልጁ ፡ ለወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ አላስሰተላለፉም ። በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴርም ፡ ወይዘሮ ፡ ባንቺአይሞሉም ፡ ፤ ወይዘሮ ፡ አሳመነችም ፤ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ የእልቅናውን ፡ ንብረት ፡ ለሌላ ፡ መስጠት ፡ አይገባቸውም ፡ ብለው ፡ ለመቃወም ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

በወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ውርስ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ከአባታቸው ፡ ከፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ከተላለፈላቸው ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፤ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ለወይዘሮ ፡ ባንቺ ፡ አይሞሉና ፡ ለወይዘሮ ፡ አሳመነች ፡ የሰጧቸው ፤ ለወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ አባት ፡ ከፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ተሰጥቶ ፡ ለወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ የተላለፈው ፡ ንብረት ፡ ያነሰ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ በሕሊናም ፡ ፍርድ ፡ ቢሆን ፡ ከፊታውራሪ ፡ አባነብሮ ፡ ሀብት ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ እንደ ፡ ወይዘሮ ፡ ባንቺ ፡ አይሞሉና ፡ ወይዘሮ ፡ አሳመነች ፡ እንኳ ፡ ሳያገኙ ፡ እንዲያው ፡ ቀሩ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ የለም ። ለሁሉም ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ለእልቅና ፡ ለወዘሮ ፡ እስካለ ፡ የተሰጠው ፡ ቀርቶ ፡ ወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ለወይዘሮ ፡ እስካለ ፤ ለወይዘሮ ፡ ባንቺአይሞሉ ፤ ለወይዘሮ ፡ አሳመነች ፡ በኑዛዜ ፡ የሰጧቸው ፡ ርስት ፡ አለና ፡ እሱን ፡ ልካፈል ፡ ብለው ፡ አልጠየቁም ። የጠየቁት ፡ ኑዛዜው ፡ ፈርሶ ፡ ለወይዘሮ ፡ እስካለ ፡ በእልቅና ፡ የተሰጠውን ፡ ሌሎችም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተሰጠውን ፡ ለመካፈል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለወይዘሮ ፡ እስካለ ፡ በእልቅና ፡ የተሰጠውን ፡ ሌሎችም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተሰጠው ፡ የሚፈርስበት ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

የእልቅናው ፡ ከወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ የቀረባቸው ፡ አባታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ በየነችን ፡ ስለበደሉ ፡ ነው ። ለሁሉም ፡ የወይዘሮ ፡ በየነች ፡ ልጆቻቸውም ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸውም ፡ ለወይዘሮ ፡ እስካለ ፡ በብልጫ ፡ አይሰጥም ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ መንገድ ፡ የላቸውም ።

ይህ ፡ ነገር ፡ የሚፈረደው ፡ በአዲሱ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ነው ። በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ ልጁን ፡ የልጅ ፡ ልጁን ፡ ከርስት ፡ የሚነቅል ፡ አውራሽ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ቃል ፡ እንዲገልጽ ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፴፯ ፡ እና ፡ ፰፻፴፰ ፡ ያዛል ። ቤት ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ አጽንተን ፡ ይግባኙን ፡ ሠርዘን ፡ ይግባኝ ፡ ባይን ፡ አሰናብተናል ።

በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ አውራሽ ፡ ከባድ ፡ በደል ፡ ያደረገበትን ፡ ወራሽ ፡ በደሉን ፡ ምሮ ፡ በኑዛዜ ው ፡ ካላወረሰው ፡ የሚችን ፡ ቃል ፡ ማክበርና ፡ የኑዛዜውን ፡ ማጽናት ፡ ልማዳችን ፡ ነው ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፤

ይግባኙን ፡ ውድቅ ፡ አድርገን ፤ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደው ፡ ይጽና ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 1 A

ESTATE OF BEYENETCH ABA NEBRO

Civil Appeal No. 227/56

Successions — Form of Will — Customary Law — Capacity of Testator — Interest of Witnesses — Disherison — Arts. 880, 881, 884, 937, 938 and 3355 Civ. C. — Art. 41 Fetha Negast.

On appeal from a judgment of the High Court denying a petition for the invalidation of a will.

Held: Judgment affirmed.

1. A will made prior to the coming into force of the Civil Code is valid according to customary law if it is read in the present of the testator and witnesses, although no mention of this formality is made in the will itself.

2. According to customary law only the last page of a will must bear the deceased's thumb print and the witnesses' signatures.

3. Arts. 881 and 884 Civ. C. require that a holographic will, but not a public will, be signed by the testator on every page.

4. A will cannot be invalidated because the testator was physically weak when the will was made.

5. A will leaving property to a monastery cannot be said to benefit witnesses of the will some of whom are attached to the monastery.

6. A testator may give preferential treatment to one of his descendants.

7. In customary law a testator is not required to justify the disherison of heirs-at-law.

Tekemt 12, 1957 E.C. (October 22, 1964 G.C.); Justices: Afenegus Kitaw Yitateku, Blatta Bekele Habte Michael, Ato Taddesse Tekle Giorgis: — The present appellants were plaintiffs and the respondent was the defendant in the High Court. The cause of the dispute is the succession to the property of Woz. Beyenetch Aba Nebro.

The three appellants have asked for the invalidation of her will drawn on November 19, 1957 on the following grounds:—

1. The said will was not signed on every page and certain words therein were erased or crossed out;
2. Woz. Beyenetch was not sane when she had the purported will drawn up;
3. The said will was not drawn according to her wishes but in the interest of those who helped draw it;
4. Woz. Beyenetch's alleged will revokes the "Ilquina" willed to Alema-

yehu — Woz. Aster's father — and incorporates the land he inherited from Fitawrari Aba Nebro.

The appellants argue that the land willed to Alemayehu by Fitawrari Aba Nebro devolves upon his daughter, Woz. Aster, and should not be included in Woz. Beyenetch's succession. The rest, they contend, should be divided equally among themselves and the respondent.

The respondent, on the other hand, maintains that the will was valid because (1) Woz. Beyenetch was sane when she made her will, (2) the will was signed by the testator and witnesses, (3) there is no gift earmarked for the witnesses, (4) Woz. Aster is unworthy of succeeding Woz. Beyenetch because her father, Alemayehu, had tried to kill Woz. Beyenetch with a gun. Finally she denies that Woz. Beyenetch's will revoked Fitawrari Aba Nebro's will.

In light of the three appellants' request for the invalidation of the will, we will first consider its validity and then decide whether the succession of the deceased is testate or intestate.

Since the will was made in 1957, it means that it was made before the coming into force of the Civil Code. Title XXI and Title XXII of the Civil Code were enacted to help courts decide what law to apply in a specific situation where there is a conflict between the repealed and newly enacted law.

Article 3355 provides that, "Wills made prior to the coming into force of this Code (September 11, 1960) shall be valid where (a) they were valid under legislation repealed by this Code or (b) they comply with the requirements of this Code." Thus a will is valid if it meets the requirements of any one of the two sub-sections of this Article.

In most respects the provisions of the Civil Code on wills are a carryover from customary law.

According to Article 880, there are three types of wills, namely (a) public wills, (b) holographic wills and (c) oral wills. All of these were known in the Fetha Negast and customary law. Woz. Beyenetch's will comes under the first category. In connection with that Article 881 runs as follows:—

(1) A public will shall be written by the testator himself or by any person under the dictation of the testator.

(2) It shall be of no effect unless it is read in the presence of the testator and of four witnesses, and mention of the fulfilment of this formality and of its date is made therein.

(3) It shall be of no effect unless the testator and the witnesses immediately sign the will or affix their thumb mark thereon.

And Article 41 of the Fetha Negast provides that, "A will may be made in writing or orally. A written will shall be valid if it is written by a scribe,

the liquidator or the testator himself in the presence of seven or five witnesses if possible, otherwise three or two will do."

But under the Civil Code the will is not valid if it is attested by less than four witnesses. No less than five witnesses were required by our customary law, unless the times were such that one could not gather that many witnesses. Basically Article 881 (2) of the Civil Code is similar to our customary law, but there is one important difference in that "(the will) shall be of no effect unless it is read in the presence of the testator and of four witnesses and mention of the fulfilment of this formality and of its date is made therein." Formerly the will would still be read in the presence of the testator and the witnesses, but no mention of this formality was made in the will, nor could failure to mention it be a cause of nullity.

Woz. Beyenetch made her will in the presence of her father confessor and six other witnesses and the last page of the will bears her thumb print and the witnesses' signatures. Thus her will is in accordance with both customary law and the Civil Code except for the fact that no mention is made that it was read out in the presence of the testator and the witnesses.

As pointed out by the appellant's advocate, only the last page of the will bears the deceased's thumb print and the witnesses' signatures, but this can be no cause for nullity. In the first place that was the accepted practice in customary law and secondly — as provided by Article 884 — it is only a holographic will that must be signed on every page. But Article 881 merely provides that "the testator and the witnesses (must) immediately sign the will or affix their thumb mark thereon," and nowhere is it said that the will is of no effect unless it is signed or thumb-printed on every page.

That along with the fact that, contrary to their allegations, the will contains no erasures, cancellations or words written over others defeats the appellants' first ground for appeal.

Let us now proceed to the second ground of appeal. The witnesses who attested the will testified that the deceased, sitting propped up in bed though very weak, dictated her will to one Araya Mammo and that she was perfectly sane. Some of the appellants' witnesses said that owing to the fact that she could not take in any food, her voice trailed off once in a while. But the will cannot be invalidated on the strength of that alone, because it does not prove that she was notoriously insane when she dictated her will. They added that she died of stomach ulcers in the monastery of Debre Libanos.

We concur with the High Court opinion and hold that the deceased was sane when she dictated her will.

The third point raised by the appellants is that the will was drawn in such a way as to benefit the witnesses. Admittedly some of them were attached to the monastery of Debre Libanos, but since she donated the land and house at Yeka to the monastery, we fail to see what personal benefit the witnesses could derive from it.

For all the above reasons we find the three appellants' request for the invalidation of the will groundless.

We will now consider Woz. Aster's request separately. Her position is that the will is void because it includes the land and other property her father, Alemayehu, inherited from Fitawrari Aba Nebro. Moreover she claims she is entitled to a share of the deceased's property because she was not explicitly disinherited by the deceased.

Though Woz. Beyenetch succeeded to the bulk of her father's property, it has been proved that Fitawrari Aba Nebro left some of it to Alemayehu. The Fitawrari's will runs as follows: "If your fate is similar to mine, pass down the 'Ilquina' to Alemayehu. But if he does not obey you, dissipates his inheritance or does not look after the welfare of the family, appoint one of your other children." It goes on to specify what land, animals and household goods he left his grandson, none of which form part of the deceased's succession.

Woz. Beyenetch's will reads: "Since I inherited all of my father's property and he bade me bequeath it all to one of my children, I hereby bequeath whatever I own and my 'Ilquina' to my daughter Askale Meshesha."

Woz. Aster's contention is that the "Ilquina" devolves upon her because her father, Alemayehu, had been appointed "aleka" by Fitawrari Aba Nebro. But Alemayehu could have earned the "Ilquina" only if several conditions were fulfilled. The first was that Woz. Beyenetch's fate be similar to her father's or, to spell it out, Alemayehu would have to survive her, just as she survived Fitawrari Aba Nebro. But he died long before she did, hence the "Ilquina" could not be transmitted to his daughter.

Moreover Fitawrari Aba Nebro bade Woz. Beyenetch bequeath her property to one of her other children if she did not find Alemayehu obedient etc. and she willed it to Woz. Askale.

Therefore the will cannot be invalidated on account of the "Ilquina."

And now for Woz. Aster's second claim wherein she argued that she is entitled to a share of the deceased's property, because she was not disinherited in so many words.

If a person dies intestate his children are the first to be called to his succession, but if one of his children is dead and is survived by descendants, he shall be represented by such descendants. Ato Alemayehu was shot by the Italians in 1936 and is survived by his daughter, Woz. Aster. The deceased's will makes no mention of Woz. Aster and that has given rise to the argument that she must represent her father in the succession.

Woz. Askale pointed out that she had proved in the High Court that Alemayehu was unworthy of succeeding his mother and that the Court had found the will valid. Documentary evidence in the form of an order issued by Azaj Workeneh on March 7, 1934, wherein he ordered the arrest of Alemayehu and one Wolde Tsadik for robbing Woz. Beyenetch was introduced in the High

Court. Moreover witnesses testified that once Alemayehu tried to kill his mother with a gun, that they never got along well and that she used to curse him constantly.

Woz. Aster tried to rebut that with the contents of a petition submitted to His Majesty wherein Woz. Beyenetch begged Him to restore to her the land she had signed away to the Italians so as to save herself when they threatened to kill her five months after she had unsuccessfully pleaded with them to spare Alemayehu in exchange for her land. But this petition written to recover her land does not prove that she pardoned Alemayehu, because she did not expressly say in her will that she had pardoned him.

The deceased was within her rights when she disinherited her daughters, Banchi Aymolu and Asamenech, and her granddaughter, Aster, and bequeathed all the property she inherited from her father along with what she acquired herself and the "Ilquina" to her daughter, Askale. A testator may give preferential treatment to one of his successors. In the present case, Woz. Askale succeeded to the bulk of Woz. Beyenetch's property and nothing much was left to the appellants. Be that as it may, they cannot contest the will on that ground.

In fact, what the deceased bequeathed to her two daughters, Banchi Aymolu and Asamenech, is roughly equivalent to what Ato Alemayehu inherited from Fitawrari Aba Nebro and was later transmitted to his daughter, Aster. Thus it can be said that the three appellants got an equal share of their grandfather's succession.

However, Woz. Aster did not claim a share of the land bequeathed to the three sisters, Banchi Aymolu, Asamenech and Askale Meshesha; rather she moved for the invalidation of the will and for a new distribution of the deceased's property. But there is no legal ground that justifies the invalidation of the will.

The "Ilquina" did not devolve upon her, because her father proved himself unworthy of succeeding his mother. Anyway, neither the deceased's children nor her grandchildren can challenge her partiality towards Woz. Askale. The deceased was not required to give reasons to justify the disherison of her heirs-at-law, as provided by Articles 937 and 938 of the Civil Code, because only customary law is applicable to this case. In customary law the disherison holds good unless the deceased pardoned his heir and called him to his succession.

For the above reasons the appeal is dismissed and the High Court decision affirmed.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

ጀየፍሬ ፡ ሬናቶ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ፖል ፡ ሪየስና ፡ ኩባንያው ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፲፬/፶፮ ፡ ዓ. ም. ።

የውል ፡ ግዴታዎች—ስለ ፡ ንግድ ፡ ተላላኪዎች—ውል ፡ እንዳይቀጥል ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያገኙት ፡ ካሣ—የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፴፱ (፩) ፡ እና ፡ ፭፱ ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለተከሳሹ ፡ ኩባንያ ፡ ከሳሹ ፡ የንግድ ፡ ተላላኪው ፡ ቢሆንም ፡ በተደራቢ ፡ በግል ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራም ፡ ስለነበረው ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፱ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ አንድ ፡ መሠረት ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፫ ፡ የተመለከተውን ፡ ውል ፡ እንዳይቀጥል ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠውን ፡ ካሣ ፡ ሊያገኝ ፡ አይገባውም ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ቀረበ ። ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ በበኩሉ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ይህንኑ ፡ አውቆ ፡ የፈቀደለት ፡ ሁኔታ ፡ ስለሆነ ፡ የካሣ ፡ መክፈል ፡ መብቱ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ አመለከተ ።

<u>ውሳኔ</u> ፤—ይግባኙ ፡ ተከልክሎ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ጸንቶአል ።

በሥራ ፡ ውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ለራሳቸው ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ሲነግዱ ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አሠሪው ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ አውቆ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፤ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻እና ፡ ፭፫ ፡ የተነገረውን ፡ የኪሣራ ፡ መክፈል ፡ መብታቸውን ፡ ያጣሉ ።

ጥቅምት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም ። ዳኞች ፤— ም/ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ሐጐስ ፡ ተወልደ ፡ መድኅን ፡ አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ሐና ፡ ቅጣው ። ይህ ፡ ይግባኝ ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ማመልከቻ ፡ ሚያዝያ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ዓ·ም ፡ በተጻፈው ፡ መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ እንደተገለጸው ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፰፰/፶፭ ፡ የካቲት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ አቶ ፡ ጀፍሬ ፡ ሬናቶ ፡ በይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ እንደተገለጸውና ፤ መዝገቡም ፡ እንደሚያስረዳው ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ የፖል ፡ ሪየስና ፡ ልጆቹ ፡ (የኢትዮጵያ) ሊሚትድ ፡ ኩባንያ ፡ የንግድ ፡ ተላላኪ ፡ የነበረ ፡ መሆኑን ፡ ግራ ፡ ቀኙ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ተማምነውበታል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሥራ ፡ ግንኙነት ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ከመልስ ፡ ሰጭ ፡ ጋራ ፡ ሲሠራ ፡ ቆይቶ ፡ ግን ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ከሥራው ፡ አሰናብቶታል ። ይግባኝ ፡ ባይም ፡ ከመልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ሲሠራ ፡ ቆይቶ ፡ አለፈቃዱ ፡ ከሥራ ፡ እንዲሰናበት ፡ በመደረጉ ፡

በንግድ ፡ ሕግ ፡ ፺፫ኛ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍለው ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር፡፳፰/፺፰ ፡ መልስ፡ ሰጪው ፡ ኩባንያን ፡ ከሶ ፡ ተከራክሯል ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ከሳሽና፡ ተከሳሹን፡ አቃርቦ ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ለሚከራከሩበት ፡ ጭብጥ ፡ በየበኩላቸው ፡ ይደግፈናል ፡ የሚሉትን ፡ የሙግት ፡ ሐተታን ፡ በመቀበል ፡ ካበጠረው ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ ኩባንያ ፡ ከሳሹ ፡ የንግድ ፡ ተሳላኪው ፡ ቢኖርም ፡ በተደራቢ ፡ በግል ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራም ፡ ስለነበረው ፡ በ፺፫ኛ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተውን ፡ ካሣ ፡ እንዲያገኝ ፡ የዚሁ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ፴፱ነኛ ፡ አንቀጽ ፡ (፩) ፡ ስለማይፈቅድለት ፡ ሊጠይቀኝ ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ያቀረበውን ፡ መከላከያ ፡ በመቀበልና ፡ ሕጉን ፡ በመጥቀስ ፡ የካቲት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፮ ፡ ዓ. ም. በሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ የይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ክስ ፡ ሠርዞበታል ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በዚህ ፡ የአሁኑ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የአቀረበው ፡ መግቱን ፡ የበለጠ ፡ ለማብራራት ፡ አስፋፍቶ ፡ ጽፏል ፡ እንጂ ፡ የጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ያው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ፺፫ኛ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይደግፈኛል ፡ ብሎ ፡ መጀመሪያ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ ባቀረበበት ፡ ጽሑፍ ፡ አሁንም ፡ በይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ ለሙግቱ ፡ መሠረት ፡ ባደረገው ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ የጠቀሰው ፡ ፺፫ኛ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ።

" ቁጥር ፡ ፺፫ ፡ ውል ፡ እንዳይቀጥል ፡ በተሠረዘ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያገኙት ፡ ካሣ ፤ የንግድ ፡ ተሳላኪዎች ፡ የንግድ ፡ ተሳላኪዎችና ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ውላቸው ፡ ሳልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነጋዴው ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ውሉታውን ፡ በሠረዘ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺሕ፩፻፸፫ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ በርት ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።"

መልስ ፡ ሰጭው ፡ የሥር ፡ ተከሳሹ ፡ ኩባንያም ፤ የንግድ ፡ ተሳላኪ ፡ ነበርኩ ፡ ሲል ፡ ካሣን ፡ በመጠየቅ ፡ ለከሰሰው ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ክርክርን ፡ ሲቃወም ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ የሚጸናው ፡ በንግድ ፡ ተሳላኪነት ፡ የሚሠራው ፡ ሰው ፡ ለአንድ ፡ ነጋዴ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜው ፡ አገልጋይ ፡ በመሆኑ ፡ በተደራቢ ፡ የግል ፡ ንግድን ፡ ሳይዝና ፡ ሳይሠራ ፡ ሙሉው ፡ ጊዜውና ፡ እውቀቱን ፡ ለቀጠረው ፡ ነጋዴ ፡ ጥቅም ፡ በሚሠራ ፡ የንግድ ፡ ተሳላኪ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ እንደራሴ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ከሳሹ ፡ የአሁን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በተደራቢ ፡ የግል ፡ ንግዱን ፡ እየሠራ ፡ አጣምሮ ፡ ደግሞ ፡ የሌላ ፡ ነጋዴ ፡ የንግድ ፡ ተሳላኪ ፡ በመሆን ፡ ለሚሠራ ፡ ሰው ፡ አይረጋም ፤ ሊሠራበትም ፡ አይችልም ፤ ምክንያቱም ፡ በንግድ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፴፬ (፩)

እንደተጻፈው ፣ የንግድ ፡ ተላላኪ ፡ ሆኖ ፡ ተቀጥሮ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ የግል ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሲያካሂድ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በሕጉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ የተነገረውን ፡ የኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ፡ ይላልና ፤ ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ የንግድ ፡ ተላላኪ ፡ ነበርኩ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ የግል ፡ ንግዱን ፡ ይነግድ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ ካሣ ፡ ሊጠይቀኝ ፡ አይገባም ፡ ሲል ፡ በሰፊው ፡ ጽፎ ፡ ተከላክሎአል ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ ለመከላከያው ፡ የጠቀሰው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፱ (፩) የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ።

“ ቁጥር ፡ ፴፱ - ስለ ፡ ግል ፡ ንግድ ”

“ (፩) በሥራ ፡ ውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ለራሳቸው ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ሊነግዱ ፡ አይችሉም ። የግል ፡ ንግድ ፡ ሲነግዱ ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፪ ፡ እና ፡ ፴፫ ፡ የተነገረውን ፡ የኪሣራ ፡ መክፈል ፡ መብታቸውን ፡ ያጣሉ ። »

እንግዲህ ፡ ይግባኝ ፡ ባይና ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ የሚከራከሩት ፡ ሁለቱም ፡ ሕጉን ፡ በየበኩላቸው ፡ ለየግላቸው ፡ ይጠቅመናል ፡ ብለው ፡ ባመኑበት ፡ መሆኑ ፡ እንኳ ፡ ቢመስልም ፤ ሕጉን ፡ በቀና ፡ ሕጋዊ ፡ መንፈስ ፡ ለሚከተለው ፡ የሚያሻማ ፡ ሐሳብ ፡ አያስከትልም ።

ሕጉ ፡ በ፴፰ኛ ፡ አንቀጽ ፡ እንዲከፈል ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ የካሣ ፡ ክፍያ ፡ መብትን ፡ እንዲያገኙ ፡ የፈቀደላቸው ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ወኪሎች ፡ ስለሥራቸው ፡ አፈጻጸምና ፤ ስለአቀጣጠራቸውም ፡ ዓይነት ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፱ ፡ አስቀድሞ ፡ አብራርቶ ፡ ወስኖታል ።

አንድ ፡ የንግድ ፡ ተላላኪ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ በሥራ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ከቀጣሪው ፡ ነጋዴ ፡ ጋር ፡ የአደረገው ፡ ስምምነት ፡ ከሌለው ፡ በስተቀር ፡ የግል ፡ ንግዱን ፡ ደርቦ ፡ መሥራት ፡ አለመቻሉን ፡ በሕጉ ፡ የተከለከለና ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ፡ ግልጽ፡ ነው ። ቀጥሎም፡ ይህ፡ የሕግ፡ ፴፱ኛ፡ አንቀጽ ፡ (፩) ፡ እንደገለጸው ፡ የግል፡ ንግድ፡ ሲነግዱ ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፪ ፡ እና ፡ ፴፫ ፡ የተነገረው ፡ የኪሣራ ፡ መክፈል ፡ መብታቸውን ፡ ያጣሉ ፡ ይላል ።

ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የመልስ ፡ ሰጭ ፡ የንግድ ፡ ተላላኪ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የግል ፡ ንግዱም ፡ እንደነበረው ፡ በጽሑፉ ፡ እያመነ ፡ በጽሑፍ ፡ ሳይሆን ፡ በድርጊት ፡ አፈጻጸም ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ይህን ፡ አውቆ ፡ የፈቀደልኝ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሆነ ፡ የካሣ ፡ መክፈል ፡ መብቴ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ይገባኛል ፡ ያለው ፡ ሕጉ ፡ በጥሬ ፡ ቃሉና ፡ በአነባበቡ ፡ መንፈስም ፡ የጣለው ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘነው ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በማይገባ ፡ መልስ ፡ ሰጭውን ፡ በዚህ ፡ የይግባኝ ፡ ክርክር ፡ ስላጕላላው ፡ ለጠበቃ ፡ አበልና ፡ ኪሣራ ፡ በድምሩ ፡ የኢት ብር ፡ ፶ ፡ (ሃምሣ ብር) ብቻ ፡ እንዲከፍለው ፡ በተጨማሪ ፡ አዘናል ።

የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዙ ፡ መጽናቱን ፡ እንዲያውቀው ፡ የዚህ ፡ ቅጂ ፡ ከሸኝ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ ይተላለፍለት ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 7

GIOFRE RENATO v. PAUL RIES & SONS (ETHIOPIA) LTD.

Civil Appeal No. 1114/56

Contractual obligations — Commercial travellers — Termination of contract — Compensation — Arts. 39(1), 42 and 43 Comm. C.

On appeal from a judgment of the High Court dismissing appellant's claim for compensation for termination of his contract as a commercial traveller, under Art. 42 Comm. C., on the ground that appellant carried on a private business on the side and therefore lost his right to compensation under Art. 39(1) Comm. C.; appellant maintained that respondent was aware of the private business and consented to it.

Held: Judgment affirmed and appeal dismissed.

Unless otherwise provided in the contract of employment, if commercial travellers or representatives engage in their own private business on the side, they lose their right to compensation under Art. 39 (1) Comm. C., regardless of the fact that the employers is aware of such outside activities.

Tekemt 26, 1957 E.C. (November 5, 1964 G.C.); Justices: Vice-Afenegus Hagos Tewolde Medhin, Kegn Geta Gebre Hanna Kitaw, Ato Mengesha Wolde Amanuel: — We have given the following order after examining the record and arguments submitted by both parties.

As indicated by the introductory passage of the appellant's application, this is an appeal against the High Court order given on February 24, 1964 in Civil Case No. 28/55.

The respondent company does not contest the fact that it had hired the appellant, Giofre Renato, as a commercial traveller. Later on it dismissed him from his job and the appellant instituted Civil Case No. 28/55 in the High Court to collect compensation for dismissal as provided by Article 42 of the Commercial Code.

The respondent company argued that the appellant was not entitled to any compensation because, apart from serving it as a commercial traveller, he also carried on his own private business on the side. Thus, as provided by Article 39(1) of the Commercial Code, he lost any compensation due to him under Articles 42 and 43. The High Court supported the defendant's argument and dismissed the case in its order given on February 24, 1964.

Except for the fact that his pleading is more detailed, the appellant still relies on Article 42 which provides as follows: "Where the trader terminates the contract without good cause, commercial travellers and representatives

who are bound by a contract entered into for an undefined period of time shall be entitled to fair compensation fixed in accordance with Article 2583 of the Civil Code."

In its statement of defence, the respondent company argued that this provision is applicable only to those cases where the traveller is a full-time employee devoting all his time and skill to the service of the employer, but that it is not applicable to cases similar to the present one where a person carries on his own business while serving another as a commercial traveller because in that case Article 39(1) provides that he loses the compensation he could claim under Article 42.

Article 39(1), cited by the respondent company, provides that: "Unless otherwise provided in the contract of employment, commercial travellers and representatives may not carry on private business. Where they carry on private business, they shall lose their compensation as provided in Articles 42 and 43".

Therefore, although both parties presented the two provisions in the light most favourable to them, these provisions raise no difficulties if they are viewed objectively.

Article 39(1) specifies the conditions of employment and service that must be met so that the commercial travellers and representatives mentioned in Article 43 may be entitled to claim compensation. It provides that in the absence of any agreement to the contrary in the contract of employment, commercial travellers or representatives may not engage in their own private business, and that if they do, they lose the compensation they could claim under Articles 42 and 43.

The appellant admits that he carried on his own private business, but argues that he is still entitled to compensation, because, despite the absence of any agreement in writing, the respondent company was aware of his activities and did in fact consent to it.

Neither the literal interpretation of the provision nor the legislative intent is susceptible of any such interpretation. Thus, the High Court's order is affirmed and the appeal is dismissed.

The appellant shall pay the respondent E$50 advocate's fees and court costs. Let a copy be sent to the High Court to notify it that its order has been affirmed.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አንደኛ ፡ ችሎት ።

የጀስ ፡ ሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ መስፍን ፡ ደምሴ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷/፶፯ ፡ ዓ.ም ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት — ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ — ስለ ፡ ይግባኝ — የአሠሪና፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ — ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥርዓት፡ አፈጻጸም ፡ የወጣ፡ ደንብ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ።

የአስተዳደር ፡ ሕግ — ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ — የአሠሪና ፡ ሠራተኛ፡ ጉዳይ፡ ቦርድ — ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸም ፡ የወጣ ፡ ደንብ ። *

አሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ ያሰናበቱት ፡ በቂ ፡ ባል ሆነ ፡ ምክንያት ፡ ስለሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ትዕዛዝ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

<u>ውሳኔ ፤</u> — የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ውሳኔ ፡ ጸንቶአል ።

፩ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸም ፡ በወጣው ፡ ደንብ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ መሠረት ፡ ክሱን ፡ የሚደግፍ ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረቡ ፡ ግዴታ ፡ የከሳሹ ፡ ቢሆንም ፡ ከሳሽ ፡ ይህንን ፡ ሳያደርግ ፡ ቀርቶ ፡ ተከሳሹ ፡ ስለተመሠረተበት ፡ ክስ ፡ መከላከያ፡ ማስረጃ ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነ ፤ ቦርዱም ፡ ይህንኑ ፡ የተከላከለበትን ፡ መከላከያ ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ ለከሳሽ ፡ ፍርድ ፡ ቢሰጥ ፤ የከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ ሳይሰማ ፡ ውሳኔ ፡ ተሰጥቶአል ፡ ተብሎ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መ ጓደል ፡ ብቻ ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በይግባኝ ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ።

፪ ፤ የይግባኙ ፡ መነሻ ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ ያሰናበቱት ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ ሳይሆን ፤ ቦርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ከሳሹን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ባለማዘዙ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ደንብ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ጥሷል ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ይግባኙ ፡ የተመሠረተው ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠበት ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ሳይሆን ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቦርዱ ፡ ሠራተኛው ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበተተበት ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመመርመር ፡ አይችልም ።

ታኅሣሥ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ.ም ። ዳኞች ፤ አፈንጉሥ ፡ ቅጣው፡ ይታጠቁ ፡ ዶክተር ፡ ቡሐጂያር ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ።

ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበው ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ በቂ ፡ ባል <u>ሆነ ፡ ምክንያት</u> ፡ ነው ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበተውና ፡ ወደሥራው ፡ ይመለስ ፡ ብሎ ፡

* ለይግባኙ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኛጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ውሳኔ፡ በገጽ ፡ ፻፶፬ ፡ ይገኛል ።

የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ በመስከረም ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም
በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ኩባንያ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ነው ።

የጆስሐንሰን ፡ የሠራተኞች ፡ ማሕበር ፡ በጆስሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ ላይ ፡ ለአሠ
ሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ባቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ የጠየቀው ፡ አቶ ፡ መሥ
ፍን ፡ ደምሴ ፡ (መልስ ፡ ሰጭ) ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ጥናት ፡ ወደ ፡ ካም
ፓላ ፡ በፈቃድ ፡ ሄደው ፡ እንደተመለሱ ፡ ያለአንዳች ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡
የመሰናበቻ ፡ ደብዳቤ ፡ በመጻፉና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከአንዱ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡
ክፍል ፡ በማዘዋወር ፡ በአዲሱም ፡ ክፍል ፡ የሥራ ፡ ችሎታ ፡ የላቸውም ፤ ከሠራተ
ኞችም ፡ አይስማሙም ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ በመፍጠር ፡ ለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ
በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰/፶፯ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ (ሐ) ፡ የተመለከተው ፡ ሳይጠ
በቅ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ደምሴን ፡ ከሥራ ፡ ያሰናበተ ፡ አለአግባብ ፡ ነው ፤ ወደ ፡
ሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ በማለት ፡ ነው ።

የሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ (ሐ) ፡ እና ፡ (መ) ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ "የሠራተኛ ፡
አባል ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ከሥራ ፡ ማሰናበት ፡ ክልክል ፡
ነው" ካለ ፡ በኋላ ፡ "ስለሆኑ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አሠሪ ፡ በቂና ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ምክን
ያት ፡ ማናቸውንም ፡ ሠራተኛ ፡ ከሥራ ፡ አግዶ ፡ ለማቆየት ፡ ለማሰናበት ፡ ከሥራ ፡
ለማስወጣት ፡ ወይም ፡ ለማዛወር ፡ በዚህ ፡ በሰላማኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈው ፡ አይ
ከለክለውም" ይላል ።

የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ያስወጣበ
ትን ፡ ምክንያት ፡ በማመልከቻው ፡ የጻፋቸውን ፡ እንዲያስረዳ ፡ ጠይቆ ፡ ያቀረበ
ውን ፡ ማስረጃ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ።

« አሠሪው ፡ ኩባንያ ፡ ያቀረባቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ እንደዚሁም ፡ ሠራተኛው
በበኩሉ ፡ ያቀረበውን ፡ አቤቱታ ፡ ቦርዱ ፡ በዝርዝር ፡ አጥንቶ ፡ ሊረዳው ፡ የቻለው ፡
በአሠሪውና ፡ በሠራተኛው ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ የተነሳው ፡ የሠራተኞች ፡ ማሕበር ፡
ከተቋቋመ ፡ በኋላና ፡ እየከረረም ፡ የሄደው ፡ ሠራተኛው ፡ ስለ ፡ ሠራተኞች ፡ አስተ
ዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጥናት ፡ ጉዳይ ፡ በፈቃድ ፡ ወደ ፡ ካምፓላ ፡ ሊሄድ ፡ ከተነ
ሳበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። የሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ ልምድና ፡ ችሎታው ፡ ወደማ
ይፈቅድበት ፡ ቴክኒክ ፡ ክፍል ፡ አሠሪው ፡ አዛውሮ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድረግና ፡ ችሎታ
የለህም ፡ ማለት ፤ ከካምፓላ ፡ በተመለሰ ፡ በ፫ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማስረጃ ፡ በሌለው ፡
ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ ማሰናበት ፤ ከኩባንያው ፡ በዱቤ ፡ ገዝቶ ፡ የሠራተኛው ፡ ንብ
ረት ፡ የሆነውን ፡ አቶሞቢል ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያልተጠበቀ ፡ ግዴታ ፡ ቢኖር ፡ በፍ
ርድ ፡ ቤት ፡ መክሰስ ፡ ሲገባው ፡ እኩባንያው ፡ ጋራዥ ፡ ካላስቀመጥህ ፡ ብሎ ፡
ከሥራ ፡ የማስወጫ ፡ ምክንያት ፡ ማድረግ ፤ አሠሪው ፡ በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡
ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዳደረገበት ፡ ቦርዱ ፡ በቀላሉ ፡ ለመረዳት ፡ ችሏል »

ብሎ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ ያስወጣው ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ የአዋጁን ፡ አንቀጽ ፡ ፰ ፡ (ሐ) በመተላለፍ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ውሳኔ ፡ ደርሷል ።

ስለይግባኝ ፡ የአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ (ሀ) "ቦርዱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ የሚቃወም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ የቦርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ወገኖች ፡ በተሰጠ ፡ በሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ። ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ የሚቻለውም ፡ በሕግ ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ቦርዱ ፡ ነገሩን ፡ መርምሮ ፡ የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ የመጨረሻና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዘንድ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ፡" ይላል ።

በይግባኝ ፡ የተጠየቀው ፡ የኩፓንያው ፡ የሠራተኞች ፡ ማሕበር ፡ ከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ ሲቀርብና ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ደምሴን ፡ ኩፓንያው ፡ ከሥራ ፡ ያስወጣው ፡ የሠራተኞቹ ፡ ማሕበር ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲያመለክት ፤ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ደንብ ፡ (የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ) በአንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ መሠረት ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲያስረዳ ፡ ሳይታዘዝ ፡ መታለፉ ፡ ቦርዱ ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ ጥፏልና፡ ነገሩ ፡ እንደገና ፡ ወደ ቦርዱ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲጣራ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያዝ ፡ ነው ። ይግባኙ ፡ የቀረበው ፡ በዚህ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ውሳኔአችን፡ በዚሁ ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ነው ።

የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ ያስወጣበትን ፡ ተገቢና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዲያስረዳ ፡ አዞት ፡ ከአስረዳና ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ ፎርም ፡ ምክንያት ፡ የቦርዱ ፡ ውሳኔ ፡ አይፈርስም ።

በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደንብ ፡ ቁጥር፡ ፴፮ ፡ በመሠረቱ ፡ ማስረጃውን ፡ የሚያቀርብ ፡ ከሳሽ ፡ ቢሆንም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ተከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

ለሁሉም ፡ ነገር ፡ ማስረጃ ፡ ከሳሽ ፡ ሳያቀርብ ፡ ተከሳሽ ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ በስረ ፡ ነገሩ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚያዝ ፡ ደንብ ፡ የለም ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፤
ይግባኙን ፡ ውድቅ ፡ አድርገነዋል ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 1 A

JOS. HANSEN & SOEHNE (ETHIOPIA) LTD. v. MESFIN DEMISSIE

Civil Appeal No. 160/57

Civil procedure — Burden of proof — Appeals — Labour Relations Board — Art. 36 Court Procedure Rules.

*Administrative law — Burden of proof — Labour Relations Board — Court Procedure Rules.**

On appeal from a decision of the Labour Relations Board which held that the reasons given by the appellant employer for dismissing an employee were not sufficient to justify the dismissal and ordering that the employee be reinstated.

Held: Affirmed.

1. While the burden is on the plaintiff in a proceeding before the Labour Relations Board to introduce evidence in support of his claim (Art. 36, Court Procedure Rules), where he does not do so but the defendant introduces evidence purportedly in contradiction of the plaintiff's claim, it is not a procedural error such as to require reversal for the Board to decide in favour of the plaintiff without requiring the plaintiff also to submit evidence.

2. Where the Labour Relations Board held that the reasons given by an employer for dismissing an employee were not sufficient to justify the dismissal and the employer appealed from the Board's decision only on the procedural ground that the Board erred in failing to require the employee to submit evidence, the merits of the Board's decision are not before the Court on appeal, and it is not for the Court to say whether the Board was correct in holding that the reasons given by the employer were insufficient.

Tahsas 6, 1957 E.C. (December 15, 1964 G.C.); Justices: Afenegus Kitaw Yitateku, Dr. W. Buhagiar, Ato Taddesse Tekle Giorgis: — This is an appeal against a decision given on October 2, 1964, by the Labour Relations Board which held that the respondent was dismissed from his employment by the appellant company without good reason. The appellant is appealing against that decision not on the merits of the case but on a point of procedure and that is that the Board was wrong in calling upon the appellant to produce evidence in defence when the respondent had not attempted to prove the allegations on which his case was based as was incumbent upon him under the Court Procedure Rules and in particular under Article 36 of those Rules.

The respondent's case was that he was dismissed from his employment because he was a member of the employees' association of the appellant com-

* The Labour Relations Board decision from which this appeal was taken appears at p. 348.

pany. It is correct, as the appellant submitted, that under the rules of procedure the plaintiff must prove the allegations on which he bases his claim; if he does not or if he adduces evidence which does not prove the facts on which the claim is based, the defendant may submit to the court that there is no case to answer and that the plaintiff's claim should be dismissed. In the present case it has never been contested that the respondent was a member of the employees' association and it has not been denied that the respondent has been dismissed. On these uncontested facts it was for the respondent to show that his dismissal was connected with the fact that he was a member of the employees' association; no such evidence was adduced by the respondent and the Labour Relations Board did not ask for such evidence but called upon the appellant to produce the evidence in defence. The evidence of the respondent might have consisted in stating that he did nothing which justified his dismissal or that he knew of no reason why he should have been dismissed except that he was a member of the employees' association; he might also have been subjected to cross-examination by the appellant. The fact however remains that although the respondent did not adduce such negative form of evidence, it cannot be said that the Labour Relations Board did not have before it the evidence, as adduced by the appellant, to show why the respondent was dismissed. On such evidence the appellant tried to show that the respondent was dismissed not because he was a member of the employees' association but for reasons which justified the dismissal of any employee. The Board, however, did not accept the reasons given as being good reasons for the dismissal of the respondent. Whether the Board was right or not in reaching such a decision it is not for this Court to say as there is no appeal on the merits of the case but only on the point of procedure, and in the circumstances of this case this Court does not consider that there has been a miscarriage of justice on the ground that the rules of procedure were not strictly followed and for these reasons the appeal must be dismissed.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

የአውራ ፡ ጐዳና፡ባለሥልጣን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ሶሌል ፡ በኔህና ፡ ማህበርተኞቹ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፰/ ፶፯ ፡ ዓ. ም. ።

የውል ፡ ግዴታዎች — የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚያደርጓቸው ፡ ውሎች — ውልን ፡ በግድ ፡ ስለማስፈጸም - የግልግል ፡ ስምምነት - የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጾች ፡ ፫፻፺፬/፩ ፡ ፫፻፺ ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ፫፻፺፰ ።

የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከሶሌል ፡ በኔህና ፡ ኩባንያው ፡ ጋር ፡ ባደረገው ፡ ስምምነት ፤ በውላቸው ፡ መሠረት ፡ ክርክሩ ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንዲቀርብ ፡ ሲል ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ቀረበ ።

<u>ውሳኔ</u> ፤— የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ጸንቶአል ።

በውሉ ፡ ድርድር ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚያዝ ፡ አንቀጽ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣናችን ፡ ይህንኑ ፡ ግዴታ ፡ እንዲያከብሩ ፡ ከማዘዝ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፺፬ ፡ አያግዳቸውም ።

ግንቦት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ዳኞች ፤— ም/ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ አበጀ ፡ ደባልቅ ፡ አቶ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍ/ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፹፪/ ፶፯ ፡ የካቲት ፡ ፲፰/ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ። መዝገቡ ፡ እንደሚያስረዳው ፡ ፍሬ ፡ ውሳኔው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፺፬- (፩) መሠረት ፡ ዳኞች ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግዴታውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ማስገደድ ፡ የሚችለው ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ፕሮሲጀር ፡ ነክ ፡ በሆነ ፡ ጥያቄ ፡ ሳይሆን ፤ በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ለሚነሳ ፡ ክርክር ፡ ነው ። እንደ ፡ ሕጉ ፡ አነጋገር ፡ ግዴታ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ በውል ፡ የተሰጠን ፡ ሥራ ፡ መፈጸም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በቀረበው ፡ ክርክር ፡ ግን ፡ በውሉ ፡ የተመለከተው ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ አሁን ፡ አመልካቾቹ ፡ የሚጠይቁት ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ግል

ግል ፡ ለመግባት ፡ ስለሆነ ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፭፻፶፱ ፡ (፩) መሠረት ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ግልግል ፡ ለመግባት ፡ አልገደድም ፡ ማለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ስላልሆነ ፡ ለቀረበው ፡ ክስ ፡ ደንበኛ ፡ መልስ ፡ ይሰጥበት ፡ በማለት ፡ ስለተወሰነ ፡ ውሳኔውን ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ።

ፍሬ ፡ ይግባኙም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፭፻፶፱ ፡ "ዳኞች ፡ ኪሣራ ፡ ማስከፈል ፡ እንጂ ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግዴታውን ፡ እንዲፈጽም ፡ ሊያስገድዱት ፡ አይችሉም" ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕጉን ፡ ተከትሎ ፡ ጥያቄአችንን ፡ ተቀብሎ ፡ ኪሣራም ፡ አስከፍሎና ፡ የቀረበለትን ፡ ክስ ፡ ሰርዞ ፡ በማሰናበት ፡ ፈንታ ፡ ሕጉን ፡ አላግባብ ፡ በመተርጐምና ፡ ከሕጉ ፡ መንፈስ ፡ ውጭ ፡ ለቀረበው ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡ እንድናቀርብ ፡ ያዘዘው ፡ በማይገባ ፡ ስለሆነ ፡ ውሳኔው ፡ እንዲሠረዝልን ፡ በማለት ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ።

የመልስ ፡ ሰጭውም ፡ ጠበቃ ፡ በበኩሉ ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፭፻፶፱ ፡ (፩) የጠቀሰው ፡ አላግባብ ፡ ነው ። ካቀረበውም ፡ ክርክር ፡ ጋር ፡ የሚገናኝ ፡ አይደለም ።

ምክንያቱም ፡ በውላችን ፡ የተመለከተው ፡ የመንገድ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞ ፡ ርክክብ ፡ የተደረገበት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ግልግል ፡ የማይገባበት ፡ ምክንያት ፡ ስለሌለ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያዘዘው ፡ ጸንቶ ፡ ልሰናበት ፡ በማለት ፡ ተከራክሯል ።

የክርክራቸው ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳለው ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለክርክሩ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፭፻፶፱ ፡ እንደተመለከተው ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ እንደሚለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ አንድ ፡ " ዳኞች ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግዴታውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ሊያስገድዱት ፡ አይችሉም " የሚል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። እንግዲህ ፡ የሕጉ ፡ አነጋገር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳለው ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ «ግዴታ» የሚለው ፡ የሕግ ፡ ቃል ፡ አግባብና ፡ ትርጉም ፡ እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ግልግል ፡ ለመግባት ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ በዚሁ ፡ ግዴታ ፡ በተባለው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ይሸፈን ፡ ወይንም ፡ አይሸፈን ፡ እንደሆነ ፡ ማወቅ ፡ ስለሚኖርበት ፤ ለተባለው ፡ ጥያቄ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ አስቀድሞ ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ በመከላከያ ፡ የሚከራከሩበትን ፡ የዚህኑ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፭፻፶፱ ፡ (፪) መመልከት ፡ ሊያሻ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ "ያስተዳደሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሳይወድ ፡ ቢቀር ፡ ዳኞች ፡ ኪሣራ ፡ ለማስከፈል ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ" ፡ ይላል ።

የይግባኝ ፡ ባይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነገረ ፡ ፈጅም ፡ በይበልጥ ፡ አጥብቆ ፡ የሚከራከረው ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ እንዲወሰንለት ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

ስለዚህ ፡ «ግዴታ» ፡ ለተባለው ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ ከመስጠት ፡ አስቀድሞ ፡ በተነገረው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ «ኪሣራ» ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ አፈጻጸሙ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ማስረዳት ፡ ሊኖር ፡ ነው ።

ኪሣራ ፡ የሚለውንም ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሚረዳው ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ሆኖ ፡ ይኸውም ፡ አንድ ፡ አመልካች ፡ ውሉ ፡ ስላልተፈጸመለት ፡ የጉዳቱን ፡ ልክ ፡ ዘርዝሮ ፡ ሲያመለክት ፡ የሚቆረጥ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ከዚሁ ፡ ወደ ፡ ፍሬ ፡ ክርክሩ ፡ ብንመለስ ፡ አሁን ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጥያቄ ፡ ሳይሆን ፡ በውላችን ፡ መሠረት ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ እንግባ ፡ የሚልና ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራን ፡ የማይጠይቅ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

መሠረተ ፡ ክርክሩ ፡ በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ እንደሚለው ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለከሣሽ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ በማስከፈል ፡ ለተከሣሽ ፡ ደግሞ ፡ ግዴታው ፡ እንዲቀርለት ፡ በማድረግ ፡ ሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡ ማካካስ ፡ በቻለ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በውላችን ፡ መሠረት ፡ ወደ ፡ ዘመድ ፡ ዳኛ ፡ እንድንገባ ፡ ይታዘዝልን ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፤ ይገባል ፡ አይገባም ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ ለክርክሩ ፡ አፈጻጸም ፡ አግባብ ፡ የሌለውን ፡ ኪሣራ ፡ እንዴት ፡ መቁረጥ ፡ ይቻላል ? ኪሣራ ፡ በአንድ ፡ ተከሣሽ ፡ ላይ ፡ ከመቁረጥ ፡ አስቀድሞ ፡ የከሣሹን ፡ ጉዳት ፡ ልክ ፡ ማወቅ ፡ ስለሚኖር ፡ ነው ። መልስ ፡ ሰጭ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ሥራውን ፡ ፈጽሞና ፡ አስረክቦ ፡ ቀሪውን ፡ ገንዘብ ፡ በውላቸው ፡ መሠረት ፡ በሽምግልና ግልግል ፡ ታይቶ ፡ ይከፈለኝ ፡ ሲል ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ፕሮግራም ፡ አልገባም ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሊያስገድደኝ ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ያቀረበውን ፡ ክርክር ፡ ሕጋዊ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ።

ስለ ፡ ሕጉም ፡ ትርጉም ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ሌላ ፡ የዚህኑ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፷፪ ፡ በተጨማሪ ፡ ብንመለከት ፡ በይበልጥ ፡ ነገሩን ፡ የሚያብራራ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

ምክንያቱም ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ (፩) "መንግሥት ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚያዋውሏቸው ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላውና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ፡ የተሰጡት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ይጸኑባቸዋል" ፡ ሲል ፡ ፪) ደግሞ ፡ "ውሉ ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባሉትን ፡ ደንቦች ፡ የሚያሟሉ ፡ ወይም ፡ በነሱ ፡ ፈንታ ፡ የሚተኩ ፡ ይሆናሉ" ፡ ይላል ።

የዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ግልግል ፡ በዚሁ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ አንቀጽ ፡ ከ፫ሺሕ፡ ፫፻፳፭ ፡ ጀምሮ ፡ የተፈቀደ ፡ ስለሆነና ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በተመለከቱት ፡ ደንቦችና ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ ግልግል ፡ ስላልተከለከለ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺሕ፩፻፴፭ ፡ (፪) እንደሚያዘው ፡ ማጓያ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺሕ፩፻፶፬ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፩) የተመለከተውን ፡ ግዴታ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ አልገደድም ፡ በማለት ፡ የሚያቀርበው ፡ ምክንያት ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም ።

ግዴታ ፡ የተባለውም ፡ ቃል ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አብራርቶ ፡ እንደተረጐመው ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የምንሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ የለም ።

በእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የሚለወጥበት ፡ ምክንያት ፡ ስለሌለ ፡ ውሳኔውን ፡ አጽንተን ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብተናል ።

ውሳኔው ፡ መጽናቱን ፡ እንዲያውቀው ፡ የዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይድረሰው ፤ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ ስለሆነ ፡ ኪሣራ ፡ መቁረጥ ፡ አላስፈለገም ።

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 5

HIGHWAY AUTHORITY v. SOLEL BONEH LTD.

Civil Appeal No. 670/57

Contractual obligations — Administrative contracts — Specific performance — Arbitration — Arts. 3131, 3194 and 3325 Civ. C.

On appeal from a judgment of the High Court ordering the Highway Authority to comply with a clause of its contract with Solel Boneh Ltd. that provided for submission of all disputes under the contract to arbitration.

Held: Judgment affirmed.

Art. 3194 Civ. C. does not prevent the courts from ordering administrative authorities to comply with contract clauses providing for submission of disputes to arbitration.

Guenbot 6, 1957 E.C. (May 14, 1965 G.C.); Justices: Vice-Afenegus Abedje Debalik, Blatta Bekele Habte Michael, Ato Kassa Beyene: — This is an appeal from the High Court's decision given on February 25, 1965 in Civil Case No. 242/57. The crux of that decision was that according to Article 3194(1) court cannot order administrative authorities to perform their obligations, but that it can order specific performance in procedural matters. In legal terminology the word "obligation" means performing what one contracted to do. In the case at bar, the plaintiff has already performed its obligation and its request is that the defendant be ordered to refer to an arbitrator as provided in the contract. The defendant's argument that Article 3194(1) exempts it from being compelled to submit to third party arbitration has no legal basis. Hence it should submit a proper statement of defence.

The appellant contends that in light of Article 3194(1), which provides that "the court may not order the administrative authorities to perform their obligation," the Court should have only awarded damages and granted its motion to dismiss the case, but that it distorted the interpretation of the provision and ordered the present appellant to defend the case on its merits. Thus, the appellant moves that the High Court decision be quashed.

On the other hand, the position of the respondent's advocate is that Article 3194(1) has no bearing on the dispute because the plaintiff has already accepted the road the respondent contracted to construct. Hence, there is no reason why it should not refer to an arbitrator and the High Court decision should be affirmed.

As pointed out by the appellant's advocate, Article 3194(1) does indeed provide that "the court may not order the administrative authorities to perform their obligation." In order to determine the meaning of the word "obligation" in the legal context and to find out whether an agreement to refer to an arbitrator falls within its scope, we must study Article 3194(2) on which the advocate for the plaintiff relies most to make his case. It reads: "The court may, however, make an order for the payment of damages unless the administrative authorities prefer to perform their obligations." Before interpreting the word "obligation", we must explain under what circumstances "damages" are awarded.

As we see it "damages" is compensation awarded to a party who suffered a detriment due to the other party's failure to perform his obligation. Under this definition the present case does not involve damages, but merely a dispute over the plaintiff's refusal to refer a dispute to an arbitrator, pursuant to the contract. The Court could have awarded damages to the plaintiff and exempted the defendant from performing if the cause of the dispute had been the performance of its obligation. However, it merely involved a request to the Court to order the present appellant to refer to arbitration. In that case there was absolutely no reason to award damages, because an assessment of the loss incurred is a prerequisite to awarding damages.

The respondent delivered the road to the Highway Authority and asked it to refer to an arbitrator to assess the extra costs the respondent had incurred. The appellant's refusal to comply on the ground that no court can order it to refer to an arbitrator is untenable.

Article 3131 helps even more to elucidate the High Court's interpretation of the provision. Sub-section 1 of this Article provides that "Contracts concluded by the State or other administrative authorities shall be governed by the provisions of this Code which relate to contracts in general or special contracts." And sub-section 2 reads: "The provisions of this Title shall supplement or replace such provisions where the contract is in the nature of an administrative contract".

Since the Civil Code provides for arbitral submission from Article 3325 onwards, and the articles on administrative contracts do not prohibit referring to an arbitrator, by virtue of Article 3131(2) the rules concerning arbitral submissions are supplementary provisions. Therefore, the appellant's argument that the single word "obligation" in Article 3194(1) exonerates it from referring to an arbitrator is not valid. We cannot arrive at an interpretation of the word "obligation" other than that of the High Court.

For these two reasons, the High Court's decision is affirmed and the appeal dismissed.

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
አንደኛ ፡ ችሎት ።

ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የላፎንዲያሪያና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፬/፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ።

የላፎንዲያሪያና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ መልስ ፡ ሰጪ ፤

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፰፻፷፭/፶፭ ፡ ዓ ም ።

የውል ፡ ግዴታዎች—ሽምግልና—የዕርቅ ፡ ስምምነት—የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የሚሰጡት ፡ «በመጨረሻው ፡ » ውሳኔ ፡ ይግባኝ— ስለ ፡ ዋስትና ፡ (ኢንሹራንስ)—ተከታታይ ፡ ጉዳት—የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፯፻፴፪ ፡ እና ፡ ፲፯፻፴፭ ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ መኪና ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ላፎንድሪያ ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አላፊ ፡ የሚሆንበት ፡ ዐይነት ፡ አደጋ ፡ ነው በማለት ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ሲያጸድቅ ፤ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ መኪና ፡ ሳይታደስ ፡ በዘገየበትና ፡ መኪናው ፡ ሳይሠራ ፡ በቆመበት ፡ ጊዜ ፡ ለደረሰው ፡ ኪሣራ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ የወሰኑት ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ወጥተው ፡ ስለሆነ ፡ ሽረ ነዋል ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመቃወም ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ ተሻሽሎ ፡ መኪናው አደጋ ፡ ደርሶበት ፡ ተሰናክሎ ፡ ሥራ ፡ ለፈታበት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከ፲፫ ፡ ቀን ፡ ለሚሆነው ፡ ጊዜ ፡ ኪሣራ ፡ ተቆርጦል ።

፩/ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ነገራቸውን ፡ በሽማግሌ ፡ ሊጨርሱ ፡ የተዋዋሉበት ፡ ውል ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የሚሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ የመጨረሻና ፡ ይግባኝ ፡ የሌለበት ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የሕግ ፡ ስህተት ፡ ወይም ፡ ውሉን ፡ በመሠረቱ ፡ የሚያፈርስ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሰጡ ፡ በቀር ፡ ፍርዳቸውን ፡ በመቃወም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ።

፪/ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ያቀረቡለትን ፡ የአደጋውን ፡ ማስታወቂያ ፤ የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያው ፡ በዋስትናው ፡ መሠረት ፡ አላፊ ፡ የሚሆንበት ፡ አደጋ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎ ፡ አስፈላጊውን ፡ እርምጃ ፡ ከወሰደ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻው ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አላፊ ፡ የሚሆንበት ፡ አደጋ ፡ ዐይነት ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ክርክር ፡ ቢያቀርብ ፤ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ አላፊነትህን ፡ አውቀህ ፡ ተቀብለህልና ፡ የገባህበትን ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ አለብህ ፡ በማለት ፡ ውሳኔ ፡ ቢሰጥ ፤ ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይግባኝ ፡ ሊባልበት ፡ አይቻልም ።

፫/ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ መኪና ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ባልቻለበት ፡ ጊዜ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያው ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ አላፊነትም ፡ ባይኖርበትም ፡ ቅሉ ፤ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያው ፡ ለማሳደስ ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ሳይሠራ ፡ ቀርቶ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜያት ፡ መኪናው ፡ ሥራ ፡ በመፍታቱ ፡ ለሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ ኩባንያው ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

፬/ ፣ የኢንሹራንሱ ፣ ኩባንያ ፣ ጉዳት ፣ የደረሰበትን ፡ መኪና፣ በተወሰነ ፣ ቀን ፣ አሳድሶ ፣ ለማስረ ከብ ፣ ግዴታ ፣ የገባ ፣ እንደሆንና ፣ ይህ ፣ የተወሰነው ፣ የግዴታ ፣ መፈጸሚያ ፣ ዘመን ፣ ያለፈ ፣ እንደሆን ፣ መኪናው ፣ ሥራ ፣ ለፈታበት ፣ ጊዜ ፣ ኪሣራ ፣ ከመጠየቅ ፣ በፊት ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፳፲፱፻፶፯ ፣ የተመለከተውን ፣ ማስጠንቀቂያ ፣ መስጠት ፣ ግዴታ ፣ አይደለም ።

በኔ ፣ ፱ ቀን ፣ ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ.ም ። ዳኞች ፤ አፈ ፣ ንጉሥ፣ ቅጣው፣ ይታጠቁ ፣ ዶክ ተር ፣ ዊሊያም ፡ ቦሐጂያር ፣ አቶ ፡ ታደሰ፣ ተክለ ፣ ጊዮርጊስ ። ይህ ፣ ክርክር ፣ በኢ ንሹራንስ ፡ አድራጊው ፣ ባላፎንዲያሪያና ፣ በኢንሹራንስ ፣ ገቢው ፣ በአቶ ፡ ገብረ ፣ ሕይወት ፣ ደበሳይ ፣ መካከል ፣ የተደረገ ፡ ነው ።

የሰሌዳው ፡ ቁጥር ፣ ኤርትራ፣ ፳፫ሺሕ፫፻፶፯ ፡ የሆነው ፣ ተሽከርካሪ ፣ በ፳/፯/፰ (እ.ኤ.አ.) ዓ.ም. ላይ ፡ ደንቢዶሎ ፡ ጊምቢ ፣ መንገድ ፣ በደረሰበት ፣ አደጋ፣ ምክ ንያት ፣ ኢንሹራንስ ፣ አድራጊው ፣ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ፣ በላፎንዲያሪያ፣ ኢንሹራንስ፣ ኩባንያ፣ ላይ ፡ በ፲፱/፩/፰ (እ.ኤ.አ.) ዓ.ም. በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ክስ ፣ አቀረቡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፣ በሽምግልና ፣ ዳኝነት ፣ ሊገላገሉ ፣ ተስማምተው ፣ በሰኔ ፣ ፳፫ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፷፩ ፣ (እ.ኤ.አ.) ዓ.ም. ነገራቸ ውን ፣ በሽማግሌ ፡ የሚገላገሉበት ፣ውል ፡ ተዋዋሉ ።

ነገሩም ፡ በሽምግልናው ፡ ዳኝነት ፡ ቀጥሎ ፡ የሽምግልና ፣ ዳኛው ፣ ውሳኔአቸ ውን፣ በመጋቢት ፣ ፳፩ ፡ ቀን ፣ ፲፱፻፶፩ ፣ ዓ.ም. ፣ ሰጡ ፤ የላፎንዲያሪያ ፣ ጠበቃ ፣ በሽምግልና ፣ በተሰጠው ፣ ውሳኔ ፣ ላይ ፡ ይግባኛቸውን ፣ ለከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ አቀረቡ ።

ከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፡ በሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፣ ፲፱፻፶፰፣ ዓ. ም. የሽምግል ናው ፣ ዳኛ ፣ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ መኪና ፡ ሳይታደስ ፡ በዘገየበትና ፡ መኪናው ፣ ሳይ ሠራ ፣ በቆመበት ፣ ጊዜ ፣ ለደረሰው፣ ኪሣራ፣ የላፎዲንያሪያ ፣ ኢንሹራንስ ፣ ኩባንያ፣ ለአቶ ፣ ገብረ ፣ ሕይወት ፣ ደበሳይ ፣ ፳፩ሺ ፡ ብር ፡ ይክፈል ፡ ብለው ፣ የወሰኑት ፣ ከሥልጣናቸውና ፣ ከኢንሹራንስ ፣ ኩፓንያ ፣ ፖሊሲ ፣ ውል ፣ ወጥተው ፣ ስለሆነ ፣ ሽረነዋል ፣ ብሎ ፣ ውሳኔውን ፣ ሰጠ ።

ላፎንዲያሪያ ፣ አደጋ ፣ የደረሰበትን ፡ መኪና ፣ ማደሻ ፣ ዋጋ ፣ መክፈል ፣ የለብ ትም ፣ በማለት ፣ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፣ ግን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፣ ቤት ፡ አልተቀበ ለውም ።

በዚህ ፡ በከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ ኢንሹራንስ ፣ ኩባንያ ፣ ለዚህ ፣ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኙን ፡ አቀረበ ፤ ቁጥር ፡ ሺ፫፻፹፭/፶፯. . . እንዲሁም ፣ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይም ፡ መኪናቸው ፣ ሥራ ፡ ስለፈታበት ፣ ሽማግሌው ፡ የፈረደላቸውን ፡ የኪሣራ ፡ ፍርድ ፡ ከፍተኛው፣ ፍርድ ፡ ቤት ፣ ስለሻ ረው ፣ ይግባኛቸውን ፣ አቀረቡ ፤ ቁጥር ፡ ፻፴፬/፶፯ ።

የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሥልጣን ፡—

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ነገራቸውን፡ በሽምግልና ፡ ለመጨረስ ፡ የተዋዋሉበትን ፡ ውል ፡ መመልከት ፡ ይገባናል ።

የሽምግልናው ፡ ውል ፡ ቁጥር ፡ ፲፬/ ሽምግልናው ፡ የሚሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ውሳኔ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ሲሆን ፤ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ውሳኔውን ፡ በመቃወም ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ፡ ይላል ።

ስለዚህ ፡ የተመረጠው ፡ ሽማግሌ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ መጨረሻ ፡ እንዲ ሆን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ከተስማሙ ፤ ሽምግልናው ፡ ከተቋቋመበት ፡ ውል ፡ ወሰን ፡ ውስጥ ፡ በተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ማናቸውም ፡ አቤቱታ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀ ርብበት ፡ አይችልም ።

በሌላ ፡ ዐይነት ፡ እናጋገር ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛው ፡ ነገረተኞቹ ፡ በሽምግልና ፡ እንዲያይ ፡ በተዋዋሉበት ፡ ውል ፡ ከሰጡት ፡ ሥልጣን ፡ ካላለፈ ፡ በቀር ፡ የሽማግ ሌው ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ የሌለበት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ የሽማግሌው ፡ ውሳኔ ፡ በሽምግልና ፡ ለመገላገል ፡ ከተደረገው ፡ ውል ፡ ውጭ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ነው ።

የሽምግልናው ፡ ውል ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ።

“ የሽምግልናው ፡ ቦርድ፡ የኢንሹራንስ፡ ውል፡ ከኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ፡ ብሔር ሕግ ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ መጠን ፡ የውሉን ፡ ግዴታዎችና ፡ ሁኔታዎች ፡ በመመልከት ፤ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ የተጻጻፉትን ፡ ደብዳቤዎች ፡ በማጥ ናት ፡ ከሁለተኛው ፡ ወገን ፡ ከላፎንዳሪያ፡ ማኅበር ፡ ጋር፡ ስምምነት ፡ ያደረገውን ፡ የጂምንቲስሪ ፡ ማኅበር ፡ ውልና ፡ ሒሣብ ፡ ማለት ፡ ተሽከርካሪው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ እንዲታደስና ፡ ተሽከርካሪው ፡ ቀድሞ ፡ በነበረበት ፡ ሁናቴ ፡ ተመ ልሶ ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲረከብ ፡ የቀረበውን ፡ ሒሣብ ፡ በመመልከትና ፡ በማጥ ናት ፤ ጉዳዩን ፡ በወዳጅነት ፡ መንገድ ፡ ለመወሰን ፡ ተግባራቸው ፡ ይሆናል ። የሽም ግልናው ፡ ቦርድ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ የሚከፍለውን ፡ ወጭና ፡ አበል ፤ እንዲሁም ፡ የጠበቃ ፡ አበል ፡ ሳይሆን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አበል ፡ ለይቶ ፡ ይወስናል ” ይላል ። ስለዚህ ፡ የሽምግልና ፡ ውሳኔ ፡ ከኢንሹራንስ ፡ ውልና ፡ ከፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ የተ ስማማ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ሽማግሌዎቹ ፡ በሰኔ ፡ ፱/፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ በጻፉት ፡ ደብዳቤ፤“ በግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ዓ. ም. እ. ኤ. አ. የጸፍንልዎትን ፡ ደብዳቤ ፡ በጥንቃቄ ፡ ቢያነቡት ፡ መኪናው ፡ አደጋው ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረበት ፡ ሁኔታ ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ እንዲታደስ ፡ ብለን ፡ ያሳሰብን ፡ መሆና ችንን ፡ ሊረዱት ፡ ይችላሉ ።

እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ደብዳቤአችን፡ ያቀረብነውን ፡ ሐሳብ ፡ የተቀበሉ ፡ እንደሆነ ፡ ከተኰናታሪው ፡ ጋር ፡ ስምምነቱን ፡ የማያደርገውና ፡ ወጪውንም ፡ የሚከፍለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ኩባንያው ፡ መሆኑን ፡ ገልጸናል ”
ይላል ።

ስለዚህ ፡ ለሽማግሌዎቹ ፡ ጥያቄ ፡ በ፲፪/፲/፷፭ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) ላፎንዲሪ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ “ ፖሊሲ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፶.፫፻፴፱ ፡ ውለታዎች ፡ ግዴታዎችና ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፤ ሚስተር ፡ ሞንቲሶሪ ፡ ግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን፡ ፲፱፻፷፭ ፡ (እ. ኤ. አ.) ዓ. ም. ባቀረቡት ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ሰኔ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ ዓ. ም. ወይም ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ግድም ፡ የታርጋው ፡ ቁጥር ፡ ኤር. ፫ሺ፫፻፶፤ ፡ ላንቻ ፡ ዚታዎ ፡ መኪና ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ አደጋ ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ኩባንያችን ፡ የሚያሳድስ ፡ መሆኑን ፡ እናረጋግጣለን ።

በኛና ፡ በሚስተር ፡ ሞንቲሶሪ ፡ መካከል ፡ በዛሬው ፡ ቀን ፡ የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ትመለከቱት ፡ ዘንድ ፡ አያይዘን ፡ መላካችን ፡ እናስታውቃለን ፡ ” ብሏል ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሽምግልና ፡ ቦርድ ፡ ስለኪሣራ ፡ ነገር ፡ በሐምሌ ፡ ፲፩፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭፡ (እ ኤ. አ.) ዓ.ም. ለሁለቱም፡ ወገኖች ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፤ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያው፡ አደጋ፡ የደረሰበትን፡ መኪና፡ ከማደስ ፡ በላይ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ወገን ፡ ኪሣራና፡ ይህን፡ የመሰለውንም፡ ለመክፈልና ፡ አደጋው ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረበት ፡ ሁኔታ ፡ መኪናውን ፡ ለባለንብረቱ ፡ ለመመለስ ፡ ወይም ፡ ለማስረከብ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ? የመረካከቡን ፡ ጉዳይ ፡ የኢ. ቢስና ፡ ኩባንያ ፡ የመሐንዲስ፡ ክፍል ፡ ከመሰከረ ፡ በኋላና ፡ ኪሣራ ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ኪሣራው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ? የጊዜውስ ፡ ልክ ፡ ስንት፡ ነው ? ስለዚህ፡ ጥያቄ ፡ ምላሽ ፡ እንድትሰጡን ፡ ብሎ ፡ ጠይቋቸዋል ።

ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ለሽማግሌዎቹ ፡ በ፲፫ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፱፻፷፭ (እ. ኤ. አ.) ዓ. ም. በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፤ በ፲፩ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፱፻፷፭ (እ. ኤ. አ.) ዓ. ም. ለጻፋችሁልን ፡ ደብዳቤ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ፡ ካሉ ፡ ሀኋላ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ እንድትመረምሩና ፡ ውሳኔ ፡ እንድትሰጡበት ፡ ብሎ ፡ ምላሽ ፡ ጻፈ ።

ለሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ደብዳቤዎችና ፡ በሰኔ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ (እ. ኤ. አ.) ዓ. ም. የተጻፈው ፡ በሽማግሌዎች ፡ ለመገላገል ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ ነው ።

ይህን ፡ አደጋ ፡ የደረሰበትን ፡ መኪና ፡ ላፎንዲያሪያ፡ ኢንሹራንስ፡ ኩባንያ ፡ አላፊነቱን ፡ ተቀብሎ ፡ በኪሣራው ፡ አሳድሶ ፡ ለባለ ፡ ንብረቱ ፡ ለአቶ ፡ ገብረሕይወት ፡ ደበላይ ፡ ሊያስረክብ ፡ የተስማማ ፡ መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ጽሑፎች ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳሉ ።

የዚህንም ፡ ነገር ፡ ሽማግሌው ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ሽማግሌ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ መጨረሻ ፡ እንዲሆን ፡ የተስ ማሙ ፡ ስለሆነ ፡ ይግባኝ ፡ የሚባልበት ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለ ? ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ነገራቸውን ፡ በሽማግሌ ፡ ሊጨርሱ ፡ የተዋዋሉበት ፡ ውል ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግንና ፡ የኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲን ፡ እንዲከተሉ ፡ ይላል ። የሕግ ፡ ስህተት ፡ ወይም ፡ የኢንሹራንስን፡ ውል፡ የሚያፈርስ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሰጡ ፡ በቀር ፡ በፍርዳቸው ፡ ላይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታ ፡ የማይቀርብበት ፡ ነው ። እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ እንመርምር ።

<u>የላፎንዳሪያ ፡ ኩባንያ ፡ ይግባኝ</u> ፡—

ላፎንዲያሪያ ፡ ኩባንያ፡ በመጨረሻ፡ ያቀረበው፡ ክርክሩ፡ በ፳/፯/፸፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. በአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ መኪና ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ እንደ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ አላፊ፡ የሚሆንበት፡ ዐይነት፡ አደጋ ፡ አይደለም፡ የማለት ፡ ክርክር ፡ ነው ።

በመኪናው ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ አደጋ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት፡ በ፳/፯/፸፡ (እ. ኤ. አ.) ዓ.ም. እንዳስታወቁት፡ ሳይሆን፤ የቢርቢር ፡ ወንዝ ፡ ሞልቶ ፡ ሳለ ፡ በመኪናው ፡ አቋርጬ ፡ እሄዳለሁ ሲል ፡ በነጂው ፡ ቸልታ ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ለመሆኑ ፡ ግምቢ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ሰኔ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. ፸፯/፸፮ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ምስክሮች ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ለሽምግ ልና ፡ ዳኛ ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ ኩባንያ ፡ አመለከተ ። የሽምግልና ፡ ዳኛው ፡ ምስክሮ ቹን ፡ አቅርብ ፡ ብሎ ፡ ፈቅዶለት ፡ ለማግኘት ፡ ባለመቻሉ ፡ ይመስላል ፡ አላቀ ረባቸውም ።

ስለዚህ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ መስቀልያ ፡ ጥያቄ ፡ ለመጠየቅ ፡ ያልቻሉበትን ፡ ምስክርነት ፡ ማስረጃ ፡ አድርጌ ፡ አልቀበለውም ፡ ብሎ ፡ የላፎንዲያሪያን ፡ ክርክር ፡ ውድቅ ፡ አደረገበት ፤ ይህም ፡ ትክክል ፡ ነገር ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ በ፳/፯/፸ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. የሰጡ ትን ፡ የአደጋውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ አላፊ ፡ የሚሆንበት ፡ አደጋ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበትን ፡ መኪና ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስመጥቶ ፡ ለማሳደስ ፡ መዘጋጀት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ።

በመጨረሻውም ፡ ነገረተኞቹ ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ነገሩን ፡ ለመጨረስ ፡ በተዋዋሉበት ፡ ውል ፡ በቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እና ፡ በተጻጻፉትም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ላፎንዲያ ሪያ ፡ አላፊነቱን ፡ ተቀብሎ ፡ መኪናውን ፡ አሳድሶ ፡ ለአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ሊሰጥ ተስማምቷል ። ስለዚህ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛው ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የወሰነው ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊታይ ፡ ይገባል ፡ የሚባልበት ፡ ምንም ፡ የሕግ ፡ ስህተት ፡

የለበትም ፣ ይህንኑም ፡ ነገር ፡ የሽምግልና ፣ ዳኛው ፣ ሊወስን ፣ ሥልጣን ፣ ተሰጥቶ ታል ። ስለዚህ ፣ የላፎንዲያሪያን ፣ ይግባኝ ፡ ውድቅ ፣ አድርገነዋል ።

<u>አሁንም ፡ ወደ ፣ ሁለተኛው ፣ ነገር ፡ እንለፍ ፤ ሁለተኛው ፡ ነገር ፡ የአቶ ፣ ገብረ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ ይግባኝ ፣ ነው ።</u>

አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ ይህ ፡ መኪና ፣ ተሰናክሎ ፡ ባለመሠራቱ ፡ ምክንያት ፣ ላፎ ንዲያሪያ ፣ ለአቶ ፣ ገብረ ፣ ሕይወት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፣ የሽምግልናም ፣ ጓኛ ፤ የፈረደውን ፣ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ ስለሻረው ፡ አቶ ፣ ገብረ ፣ ሕይወት ፣ ደበሳይ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፣ አቅርበዋል ።

የዚህን ፡ የኪሣራ ፡ ነገር ፤ ላፎንዲያሪያ፡ መኪናውን ፡ በኪሣራው፡ አሳድሶ ፣ ለባለንብረቱ ፡ ለአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ሊያስረክብ ፡ ከተስማማበት ፡ ከ፲፱/፯/፸፩ ፣ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ወዲህ ፡ ያለውንና ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ አደጋው ፡ ከደረሰበት ፣ ከ፳/፯/፸ (እ. ኤ. አ.) ዓ. ም. ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፱/፯/፸፩ (እ.ኤ.አ) ዓ. ም. ድረስ ፣ ያለውን ፡ ለየብቻው ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

<u>ከ፳/፯/፸ ዓ.ም. እስከ፡ ፲፱/፯/፸፩ (እ.ኤ.አ) ዓ.ም. መኪናው፡ አደጋ፡ደርሶበት፡ ተሰናክሎ ፣ ሥራ ፣ ስለፈታበት ፣ ቀን ፡ ኪሣራ ።</u>

አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፣ ደበሳይ ፣ ኢንሹራንስ፡ ገቢው ፡ መኪናቸው ፡ በ፳/፯/፸ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ደምቢዶሎ፡ ግምቢ፡ መንገድ፡ አደጋ ፡ደርሶበታል ፡ ብለው ፣ በ፳፩/፯/፸ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ለላፎንዲያሪያ ፡ ኢንሹራንስ ፣ ኩባንያ ፣ አስታወቁ ። ላፎንዲያሪያ ፡ ኩባንያ ፡ መኪናዋን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስመጥቶ ፣ ለማሳደስ ፣ መዘጋጀት ፡ ጀመረ ።

የኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲ ፣ ቁጥር ፣ ፫ ፣ ማናቸውም ፡ ተሽከርካሪ ፡ አደጋ ፡ በደረ ሰበት ፡ ጊዜ ፡ ለጥቢቃውና ፡ እንደዚሁም ፡ እንስቶ ፣ ባቅራቢያው ፣ ወደሚገኘው ፣ ማደሻ ፡ ቤት ፡ ለመውሰድ ፡ የሚያስፈልገውን ፣ ወጭ ፣ ማኅበሩ ፡ ከፋይ ፣ ነው ፣ ይላል ።

ማኅበሩ ፣ ላፎንዲያሪያ ፣ ራሱ ፡ መኪናውን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለማስመ ጣት ፣ ከአቶ ፡ ገብረ ፣ ሕይወት ፡ መነጋገሩንና ፡ ለማምጣት ፣ ሥራውን ፡ ጀምሮ ፣ እንደነበረ ፡ የሽምግልናው ፣ ዳኛ ፡ ውሳኔ ፡ ያስረዳል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ውል ፡ ወይም ፡ መኪናውን ፣ ወደ ፣ አዲስ ፡ አበባ ፣ በተ ወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፣ እንዲያስመጣ ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ አልነበረም ።

በኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲው ፣ በቁጥር ፣ ፭(ለ) እንደተመለከተው ፣ አደጋ ፣ የደረ ሰበት ፡ መኪና ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፣ ባልቻለበት ፣ ጊዜ ፣ ላፎንዲያሪያ ፣ ኩባንያ ፣ ኪሣራ ፣ ለመክፈል ፡ አላፊነት ፣ የለበትም ።

እንደዚህም ፡ ከሆነ ፡ የላፎንዲያሪያ ፡ ኩባንያ ፡ ጥፋትና ፡ አላፊነት ፡ ይኖርበት ፡ ዘንድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሊደረግለት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ እንደውሉ ፡ ሳይፈጽምልኝ ፡ ቀርቶአል ፡ በማለት ፡ ክርክር ፡ ለማቅረብ ፡ የሚፈልገው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተዋዋይ ፤ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ግዴታውን ፡ እንዲፈጽምለት ፡ ለማድረግ ፡ አስቀድሞ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሊሰጠው ፡ ያስፈልጋል ፡ ይላል ።

ላፎንዲያሪያ ፡ መኪናውን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለማምጣትና ፡ ለማሳደስ ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ካልሠራ ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ በዚህ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ቁጥር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ለላፎንዲያሪያ ፡ መስጠት ፡ ይገባቸው ፡ ነበር ።

ማስጠንቀቂያ ፡ ተደርጐለት ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ መኪናውን ፡ ራሱ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ባያመጣ ፡ ወይም ፡ የሚያመጡበትን ፡ ኪሣራ ፡ ለአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ ባይከፍል ፡ ጥፋት ፡ ይሆንበት ፡ ነበር ፤ ለጥፋቱም ፡ አላፊነት ፡ ይኖርበት ፡ ነበር ።

ይህን ፡ ዐይነት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ለላፎንዲያሪያ ፡ ተደርጐለታል ፡ የሚል ፡ በሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ የለም ፤ ስለዚህም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበ ፡ የለም ።

የሽምግልና ፡ ዳኛው ፡ የኪሣራውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመወሰን ፡ የሽምግልናው ፡ ውል ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ቢሆንም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲ ፡ መሠረት ፡ እንዲወስን ፡ ነው ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ። በመኪናው ፡ ላይ ፡ በ፰/፯/፷ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. አደጋ ፡ ደርሷል ።

የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ ኩባንያ ፡ መኪናውን ፡ ከግምቢ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አምጥቶ ፡ እንዲያሳድስ ፡ ባስጠነቀቁት ፡ ደብዳቤ ፡ መሠረት ፡ መኪናውን ፡ ከግምቢ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስመጥቶ ፡ ለማሳደስ ፡ በ፲፱/፯/፷፩ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ከአዳሺው ፡ ከምንቲሶሬ ፡ ጋር ፡ ተዋዋለ ።

ከዚያ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተሰጥቶታል ፡ ሳይል ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ ከ፰/፯/፷ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፱/፯/፷፩ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ድረስ ፡ መኪናው ፡ ሥራ ፡ ላልሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ ለአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ የፈረደው ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ስላልሆነ ፡ ከ፰/፯/፷ ፡ ዓ. ም. እስከ ፡ ፲፱/፯/፷፩ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ባለው ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ የፈረደው ፡ ኪሣራ ፡ መሰረዝ ፡ ይገባዋል ።

<u>ከ፲፱/፯/፷፩ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ.ም. ወዲህ ፡ ስላለው ፡ ኪሣራ ፡</u>

፲፱/፯/፷፩ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳልነው ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ መኪናውን ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አሳድሶ ፡ ለባለቤቱ ፡ ለአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ሊሰጥ ፡ የተዋዋለበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ ላፎንዲያሪያ ፡ ውሉን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ሳይፈጸም ፡ እንዲዘገይ ፡ በማድረጉ ፡ ምክንያት ፡ መኪናው ፡ ሥራ ፡ ለፈታበት ፡ ጊዜ ፡ ኪሣራውን ፡ ለአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ እንዲከፍል ፡ ፈርዶበታል ። ውልን ፡ ባለመፈጸም ፡ የሚመጣውን ፡ ኪሣራ ፡ ተዋዋዩ ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ፡ የታወቀ፡ ደንብ ፡ ነው ። (ቁጥር ፡ ፲፯፻፹፭ ፡ (፪) ፡ የፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰፻፵፭ ፡ (ለ) መሠረት ፡ "ባለዕዳው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደሆነና ፡ ይህ ፡ የተወሰነው ፡ የግዴታ መፈጸሚያ ፡ ዘመን ፡ ያለፈ ፡ እንደሆነ " ማስጠንቀቂያ ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ አይደለም ።

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ የወሰነው ፡ ውሳኔ ፡ የሕግ ፡ ስህተት ፡ አለበት ፡ ወይም ፡ ነገሩን ፡ ለመወሰን ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ ይህን ፡ የኪሣራ ፡ ነገር ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ አልተሰጠውም ፡ የሚባልበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።

ስለዚህ ፡ ከ፲፪/፯/፷፩ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም ወዲህ ፡ የአቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ ደበሳይ ፡ መኪና ፡ ሥራ ፡ ስለፈታበት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛው ፡ የወሰነውን ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሻረው ፡ አንድም ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ ስለሆነ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤትን ፡ ውሳኔ ፡ ሰርዘነዋል ። ላፎንዲያሪያ ፡ የጠየቀውንም ፡ ጥያቄ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውድቅ ፡ አድርጎታል ።

ላፎንዲያሪያ ፡ ኩባንያ ፡ ከሞቲሶሬ ፡ ጋር ፡ እንደተዋዋለው ፡ ውል ፡ መኪናው ፡ ታድሶ ፡ ማለቅ ፡ የነበረበት ፡ እስከ ፡ ነሐሴ ፡ ፱፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ነሐሴ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ (እ.ኤ.አ.) ዓ. ም. ነበር ። የሽምግልናው፡ ዳኛ ፡ የመታደሱ ፡ ነገር፡ አንድ ፡ ወር ፡ ከ፳ ቀን ፡ መጨመር ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ብሎ፡ ስለጨመረ፡ የመታደሱ ፡ ነገር ፡ የሚያልቀው ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ከ፳ ፡ ቀን ፡ ሆኗል ። ስለዚህ ፡ መኪናው ፡ የሚታደስበት ፡ መጨረሻው ፡ ቀን ፡ መስከረም ፡ ፳፰፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. (ጥቅምት ፡ ፰/፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም.) ሆኗል ።

ስለዚህ ፡ በኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲ ፡ መሠረት ፡ ሳይሆን ፡ ከሞንቲሶሬ ፡ ጋር ፡ በተዋዋለው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ መኪናው ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራ ፡ ለቆመበት ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ከዚህ ፡ ቀን፡ ከመስከረም፡ ፳፰፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ (፰/፲/፩፱፻፷፩) ፡ ጀምሮ፡ ነው ። አላፊነቱ ፡ የሚዘጋበትም ፡ ቀን ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛው ፡ እንዳለው ፡ መኪናው ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ታድሶ ፡ በደህና ፡ የሚሽከረከር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢስ ፡ ኩባንያ ፡ የመሰከረበት ፡ ጥቅምት ፡ ፯፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ.ም. (፲፯/፲/፲፱፻፷፪፡ ዓ.ም.) ነው ። ከመስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ.ም. (፰/፲/፷፩ ፡ ዓ.ም.) እስከ ፡ ጥቅምት ፡ ፯/፲፱፻፶፭ (፲፯/፲/፷፪ ፡ ዓ.ም.) አንድ ፡ ዓመት ፡ ከአሥራ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።

የሽምግልናው ፣ ዳኛ ፣ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ስለኪሣራ ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ሺህ ብር ፡ ይከፍላል ፡ ላለው ፡ ማስረጃ ፡ ነገር ፡ ባይኖረውም ፤ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ መኪናው ፡ ሥራ ፡ ስለፈታበት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ኪሣራ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ይክፈል ፡ ያለው ፡ ተልክ ፡ ያለፈ ፡ የማይገባ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘውም ፡፡ ስለዚህ ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ በወሰነው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገባበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡፡

ስለዚህ ፡ ኢንሹራንሱ ፡ የሚከፍለው ፡ ኪሣራ ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ብር ፤ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ከአስራሶስት ፡ ቀን ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰላሣ ፡ ሶስት ፡ ብር ፡ ነው ፡፡ የሽምግልናው ፡ ዳኛ ፡ በመጋቢት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም. ውሳኔ ፡ ሲሰጠው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ የተፈረደበትን ፡ በተፈረደበት ፡ ቀን ፡ እንዲከፍል ፤ ያልከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ እስቲከፍል ፡ ድረስ ፡ ወለድ ፡ በዓመት ፡ በመቶ ፡ ፱ ብር ፡ ወለደ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ወስኖዋል ፡፡

ስለዚህ ፡ ከዚህ፡ በላይ፡ የተነገረው፡ ፲፪ሺሕ፬፻፴፫ ፡ ብር ፡ ሽምግልናው፡ ከወሰነው ፡ ተሻሽሎ ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ፡፡ የተባለው ፡ ገንዘብ ፡ ሽማግሌው ፡ ዳኛ ፡ እንደወሰነው ፡ የሚከፈለው ፡ ከነወለዱ ፡ ነው ፡፡ የዳኝነቱን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ኩባንያ ፡ ይከፍላል ፤ የጠበቃ ፡ ኪሣራም ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ ፪፻ ብር ፡ ይክፈል ፡፡

SUPREME IMPERIAL COURT
Div. 1 A

EBRE I IWET DEBASSAI v. LA FONDIARIA FIRE INSURANCE CO.

Civil Appeal No. 134/56

LA FONDIARIA FIRE INSURANCE CO. v. GEBRE HIWET DEBASSAI

Civil Appeal No. 1375/55

Contractual obligations — Arbitration — Arbitral submission — Appeal from "final" award — Misconduct of arbitrator — Insurance — Consequential damages — Arts. 1772 and 1775 Civ. C.

On appeal by both parties from an order of the High Court upholding an arbitral award that found that an accident had occurred to the insured truck within the terms of the insurance policy, while setting aside the award insofar as it granted compensation for consequential damages due to an unreasonable delay in the repairing of the vehicle.

Held: Order of the High Court and arbitral award altered to provide for compensation for consequential damages due to loss of use of the truck for a period of one year and 13 days.

1. An arbitral award can be set aside by the courts, in spite of a clause in the arbitral submission to the effect that the decision of the arbitrators shall be final and that the parties shall have no appeal against that decision, whenever:

a. the arbitral submission or the award has been improperly procured, as, for example, where the arbitrator is deceived or material evidence is fraudulently concealed; or

b. the arbitrator or umpire is guilty of misconduct.

2. The expression "misconduct on the part of the arbitrator or umpire" is of wide import; it includes, on the one extreme, bribery and corruption, and on the other, - mere mistake as to the scope of the authority conferred by the submission (many other examples of misconduct are given in paragraph seven of the judgment).

3. Where an insurance company accepts an accident report and acts according to it and only a year later tries to avoid responsibility under the insurance policy, an arbitrator acts within his authority when he requires the insurance company to prove that the report was false.

4. Although a clause of an insurance policy that excludes compensation for loss of use of the vehicle insured is a valid clause, it does not exclude liability for loss of use of the vehicle consequent upon unreasonable delay in repairing the vehicle.

5. Notice under Article 1772 of the Civil Code is not a prerequisite to a claim for compensation for loss of use when an insurance company has entered into a contract with a garage providing for repair by a specified date.

Sene 2, 1957 E.C. (June 9, 1965 G.C.); Justices: Afenegus Kitaw Yitateku, Dr. W. Buhagiar, Ato Taddesse Tekle Giorgis: — These two appeals arise out of an insurance policy which Ato Gebre Hiwet Debassai (hereinafter referred

to as "the insured") took out from La Fondiaria Fire Insurance Co. (hereinafter referred to as "the insurance company") for the insurance of the insured's truck used for the transport of merchandise. The insurance was against the risks normally included in such insurance policies. The insurance was not against all risks and for the purposes of this judgment it is sufficient to mention that one of the risks insured against was "loss or damage to the truck and accessories thereon resulting from accidental collision or overturning or collision or overturning consequent upon mechanical breakdown or consequent upon wear and tear but excluding accidental damage to tyres unless the truck is damaged at the same time." The estimated value of the insured truck is declared by the insured to be E$20,000. The policy contains the usual exemptions from liability and we need mention here the exemption from liability for "the consequential loss sustained by the insured for loss of the use of the truck." The policy provides also for arbitration in case of dispute arising between the insured and the insurance company.

During the insurance period the insured alleged that the insured truck sustained an accident and he duly reported such accident to the insurance company and submitted a claim for compensation; the accident was alleged to have taken place on June 20, 1960. The dispute was at first submitted to the High Court, but the matter was referred to arbitration as provided in the insurance policy. Eventually, and to be exact on June 30, 1961, a submission of arbitration was prepared; two arbitrators were appointed, one for the insured and the other for the insurance company; because of certain terms in the submission one of the arbitrators could in the absence of the other arbitrator give an award by himself (this point was the subject of a decision by the High Court and this Court). The remaining sole arbitrator, Mr. Sobhi Kronfli, gave his award on March 30, 1963. The insurance company appealed against that award on various grounds to the High Court. The High Court on July 22, 1963, gave an order holding that the arbitrator had exceeded his jurisdiction in awarding the insured E$24,500 as damages for a period of 2 years and 6 days at the rate of E$1,000 per month for loss of the use of the truck and the High Court set aside that part of the award.

The present two appeals are appeals against that order of the High Court.

The insured is appealing against that order on the ground that the question of settling the amount of damages, including damages resulting from loss of use of the truck, was within the jurisdiction of the arbitrator in accordance with the terms of the submission of arbitration, and that, therefore, the High Court was wrong in interfering with the award of the arbitrator. The insurance company is appealing against that order on the ground that the arbitrator has disregarded the conditions of the policy in that (a) the insured did not prove that an accident had taken place within the meaning of the risks of the policy which provides for collision and overturning and (b) the arbitrator allowed damages for loss of use of the truck when the policy excludes specifically damages resulting from loss of use of the truck.

The relevant terms of reference of the arbitration were:

"13. The Board of Arbitrators' duty is to amicably settle the dispute taking into consideration the Terms, Provisions and Conditions of the Insurance Policy as far as not inconsistent with the Civil Law of the Empire, taking into consideration the letters exchanged by both parties, the offer and the contract of Messrs. G. Montissori who contracted with the second party — La Fondiaria Insurance Co. Ltd. to bring the vehicle to Addis Ababa to repair it and hand it in good running order in same condition as it was when the accident occurred. The Board of Arbitrators will also decide in their decision what part of the expenses and fees each party will pay, i.e. fees paid to the Court, but not the advocates.

14. The decision given by the Board of Arbitrators unanimously or by majority shall be considered as final by the parties and the parties shall have no right to appeal against that decision or any part of it..."

The first point to be considered is whether in view of the provision in clause 14 of the submission for arbitration there could be an appeal to the High Court and whether the High Court was wrong in interfering with the decision of the Board of Arbitrators. There can be no question that, although in the arbitral submission it is agreed that the award shall be final, there are occasions (and this has been the constant practice of these Courts) when the award or part of it can be challenged in a court of law. The Civil Code has no provision on this point and neither have the existing rules of civil procedure; this is a matter, however, which should be considered in the enactment of a new Civil Procedure Code. Generally, however, it may be said that the grounds on which an award can be set aside are —

(a) that the arbitration or award has been improperly procured, as for example, where the arbitrator is deceived, or material evidence is fraudulently concealed;

(b) that the arbitrator or umpire misconducted himself.

The expression "misconduct on the part of the arbitrator or umpire" is of wide import; it includes on the one hand bribery and corruption and on the other a mere mistake as to the scope of the authority conferred by the submission. It is difficult to give an exhaustive definition to the expression "misconduct" but a few examples may be given: thus misconduct occurs if the arbitrator or umpire, as the case may be, fails to decide all the matters which were by the submission referred to him; if by his award he purports to decide matters which were not in fact included in the submission; if the award is inconsistent or is uncertain or ambiguous or is on its face erroneous in matters of law or even if there is some mistake of fact which is clear beyond any reasonable doubt; if there has been irregularity in the proceedings, as for example, where the arbitrator failed to give notice to the parties of the time and place of meeting or where the arbitrator refused to hear the evidence of a material

witness, or where the reference being to two or more arbitrators, they did not act together; if the arbitrator or umpire failed to act fairly towards both parties, as for example, where the arbitrator heard one of the parties and refused to hear the other, where he took instructions from or talked with one party in the absence of the other, or where he has taken evidence in the absence of one party or both parties or promised to hear certain witnesses and then made his award without hearing them; if the arbitrator or umpire acquires an interest in the subject matter of the reference; or if he takes a bribe from either party. As regards an error in law on the face of the award, it is to be mentioned that in order to be ground for setting aside the award, the error must be such that there can be found in the award, or a document incorporated therewith, some legal proposition which is the basis of the award and which is erroneous. If a *specific question of law* is submitted to the arbitrator for his decision and he decides it, the fact that the decision is erroneous does not make the award bad on its face so as to permit of its being set aside; and where the question referred for arbitration is a question of law, the decision of the arbitrator cannot be set aside only because the Court would itself come to a different conclusion; but if the arbitrator has proceeded illegally, as for example, if he has decided on evidence which was not admissible or on principles of construction which the law does not countenance, there is error in law which may be ground for setting aside the award.

Having established these principles let us consider first the objections to the award raised by the insurance company. These objections may be summarized as follows: it is submitted that the arbitrator went out of the terms of reference of the arbitral submission because according to such submission the arbitrator had to decide the dispute between the parties according to, *inter alia*, the policy of insurance; this policy of insurance does not cover *all risks* (as the arbitrator seems to have assumed — see the second paragraph of the award where it is stated: "Ato Gebre Hiwet insured the truck with the Insurance Company against certain fees in reference to the said policy as for any accident to the truck . . . ."). In the first place, the insurance company states, there was no accident at all for which the insurance company could be liable; secondly if there was an accident as reported by the insured, then such accident was not such as to be a risk covered by the insurance policy; and thirdly if there was an accident amounting to a risk covered by the insurance policy, then the arbitrator was wrong in law in allowing damages for loss of use of the truck because under the insurance policy there is an exemption from liability for such damages.

If this is the case, then clearly, in accordance with the principles laid down above, the arbitrator has been guilty of misconduct (such word being used in its general meaning) in that either he disregarded the terms and conditions of the insurance policy which under Article 13 of the arbitral submission were to be taken into consideration in settling the dispute or he has wrongly interpreted the legal effects of such terms and conditions.

The first objection of the insurance company is that there was no accident for which the company is liable under the policy. The facts on this point are as follows; when the alleged accident occurred the insured made a declaration in which a description of the accident was given as follows:

> "while the truck was on its way to Dembidollo -Ghimbi on June 20, 1960, at 18:30 hrs. p.m. and while it was proceeding on the road along the river Bir-Bir owing to rain one of the wheels was slipping thus causing the truck to go back and fall into the adjacent river".

The insurance company accepted this declaration and arrangements were made for the transport of the truck to Addis Ababa and for the necessary repairs by the insurance company. At a later stage the insurance company seems to have had some doubt about the veracity of the declaration regarding the accident and started to make certain investigations; during the proceedings of arbitration they submitted that there was evidence to show that the damage to the truck was caused by the negligence of the driver and not as a result of the accident as described by the insured; the negligence of the driver consisted in that the driver tried to cross the river Bir-Bir when the water was too high. This evidence, according to the insurance company, consisted of a witness who had given a statement to the Police at Ghimbi on July 4, 1961. The arbitrator gave the insurance company the opportunity of calling the witnesses, but they were not produced (apparently because they could not be found); in those circumstances, the arbitrator rightly rejected the allegation of the insurance company because the statements of the witnesses were made before the Police and there was no possibility for the insured to cross-examine them. For these reasons therefore the insurance company has no good reason for objecting to the finding of the arbitrator that there was an accident.

The second objection of the insurance company is that the accident, as reported by the insured, was not a risk which is covered by the insurance policy; the reason for this is that the policy covers loss of or damage to the truck insured resulting from any accidental collison or overturning or collision or overturning consequent upon mechanical breakdown or consequent upon wear and tear" — see clause 1 of the policy. Now, it is submitted by insurance company, in the present case there was no collision and there was no overturning. Furthermore, it is submitted that the policy does not cover damage resulting from flood and in the present case the damage was caused by the flooding of the river, (as a result of heavy rains) where the truck got stuck after getting to the bed of the river. With regard to the flooding there is nothing in the award which shows that the river did rise, after the truck got to the bed, as a result of heavy rains. As regards the collision and overturning it is to be noted that the insurance company accepted the declaration describing the accident and accepted such circumstances as amounting to a risk covered by the insurance policy so much so that preparations were being made to bring the truck to Addis Ababa and carry out the necessary repairs; it was only much later, about a year later, that the insurance company tried to avoid responsibility

and this was when they had some indication or suspicion that the declaration made by the insured was not true. In these circumstances, the insurance company accepted by their conduct that, although there may not have been collision or overturning of the truck, the accident was a risk covered by the policy. For these reasons this objection of the insurance company is unfounded.

The third objection is that the arbitrator was wrong in allowing damages for loss of use of the truck when under the insurance policy there is an exemption from liability for such loss. Now in clause (b) of the Proviso (dealing with exemptions from liability) of the policy it is stipulated that "the company shall not be liable to make any payment in respect of consequential loss sustained by the insured or loss of use of any vehicle described in the schedule hereto". In this connection it is important to mention that the policy contains also the following conditions:

> "4. In the event of loss or damage to any vehicle described in the schedule hereto the company may at its own option repair, reinstate or replace such vehicle or part thereof and/or its accessories or pay in cash the amount of loss or damage and the liability of the company shall not exceed the actual value of the parts damaged or lost plus the reasonable cost of fitting and in no case exceed the insured's estimate of the value of such vehicle... at the time of loss or damage whichever is the less."

It is also to be mentioned that soon after the accident the insurance company exercised the option to carry out repairs to the truck but such repairs were delayed. It was on June 12, 1961 that the insurance entered into an agreement with one Montissori for the carrying out of repairs which were to be completed not later than August 15, 1961. This agreement was made a few days before the date of the arbitral submission, which was June 23, 1961, and such agreement between the insurance company and Montissori was a matter which was to be taken into consideration by the arbitrator in settling the dispute. It is also to be mentioned that there was correspondence between the insurance company and the insured which was also to be taken into consideration. There was also a letter sent by the arbitrator to both parties in which certain issues were settled and to which the parties agree; the dispute, however, was clearly to be settled according to the insurance policy, the Civil Code of Ethiopia, and the Montissori contract and correspondence mentioned. Also there is no question that the arbitrator was given the power, subject to the above conditions, to specify the period or periods during which compensation for loss of use of the truck should be paid. The conclusion of the arbitrator on this point was that compensation was payable at the rate of E $ 30 a day for the period from the date of the accident until the day on which the truck was sanctioned by Messrs. A. Besse & Co. as being in a fit state of repair and in good running order; from this period the arbitrator excluded a period of 3 months and 20 days which is the time considered necessary to complete the repairs of the truck. (This period of 3 months and 20 days was the period of 2 months origi-

nally agreed to by Montissori plus another period of 1 month and 20 days which the arbitrator considered necessary in view of certain matters which arose in the course of reparations.) The period reckoned by the arbitrator during which compensation for loss of use was payable amounted to 2 years and 6 days. Now, it is true the insurance company exercised the option to bring the truck to Addis Ababa and to carry out the necessary repairs, but this undertaking does not, by itself, amount to an obligation to pay compensation for loss of use of the truck and this for two reasons, namely, (a) because it is clearly stated in the policy that the company is exempt from liability from loss of use of the truck consequential upon an accident and (b) because even if the option amounted to an obligation to carry out repairs, then under Article 1772 of the Civil Code the insured could not invoke non-performance of the contract by the insurance company except after the company had been placed in default by requiring the company by notice to carry out the obligation under the contract. And there is no evidence before the Court or before the arbitrator that the insured had placed the company in default by notice given. In view of this provision of law and the insurance policy there was no liability at this stage for compensation for loss of use of the truck. The position is, however, different under the contract entered into between the company and Montissori, which contract was also a basis for the settlement of the dispute; in this contract Montissori undertook to complete the repairs within a definite period of time (which original period of time was later extended by the arbitrator, the parties consenting). Under this contract it was not necessary for the insured to place the insurance company in default because under paragraph (b) of Article 1775 of the Civil Code no notice is necessary when the debtor has assumed to perform an obligation within a fixed period of time. In view of the Montissori contract the insurance company became liable for damages sustained by the insured as a result of the non-fulfillment of the obligation. Now the period which the arbitrator held to be reasonable for the carrying out of repairs was 3 months and 20 days; according to the Montissori contract the repairs were to be completed not later than August 15, 1961, with the extension of one month and 20 days, the date of completion should be October 3, 1961, and it is from this date that the insurance company should be held liable to pay compensation for loss of use of the truck, not under the policy but under the agreement with Montissori. The closing date of the liability has been found by the arbitrator to be the date on which Messrs. A. Besse and Co. sanctioned the truck to be in a good state of repair and in good running order, which is October 17, 1962. The period from October 5, 1961 to October 17, 1962 is one year and thirteen days (1 year, 13 days).

With regard to the amount awarded by the arbitrator on this account the insurance company submitted that there was no evidence before him to enable him to come to the conclusion that the loss sustained by the insured amounted to E$1,000 per month. Now it is true that there was no evidence on this point but this Court considers that E$1,000 is not an unreasonable amount though it may not conform exactly to the profit made by the insured by

the use of the truck; for this reason this Court sees no reason for interfering with the monthly rate as found by the arbitrator. The amount, therefore, to which the insured is entitled for loss of use of the truck is E$1,000 for the period of 1 year and 13 days, that is E$12,433 and in this respect this Court alters the award of the arbitrator and alters the order of the High Court.

As regards the appeal of the insured, who claims that the High Court was wrong in interfering with the award of the arbitrator because it was within the jurisdiction of the arbitrator to decide the question of damages, including damages resulting from loss of use of the truck, this Court holds that the High Court had jurisdiction to enter into the matter for the reasons set out above in this judgment in dealing with the objections of the insurance company and the appeal of the insured is allowed in so far as the High Court was wrong in disallowing all the damages as awarded by the arbitrator and in so far as this Court holds that the amount of damages to which the insured is entitled for loss of use of the truck is E$12,433.

The insurance company shall pay costs to the insured of E$200 and each party will sustain the court fees paid for this appeal.

ከፍተኛው ፍርድ ቤት ፤

አዲስ አበባ ።

መስፍን ፡ ዘለለው ፡ ከሳሽ ፤ የሥራና ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፩/፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ተሽከርካሪዎች ፡ ደንብ— የፈቃድ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥልጣን— ጨረታና ፡ ውድድ ርን ፡ ስለመወሰን— የትራንስፖርት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ፡ አንቀጽ ፳፩ ፡ (፪ሀ) እና ፡ ፳፩ ፡ (፫) ።

የአስተዳደር ፡ ሕግ — የፈቃድ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥልጣን — የትራንስፖርት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ።

የሥራና ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ በአዲስ ፡ አበባ— ጅማ ፡ መስመር ፡ የሚመላለሱትን ፡ የአመልካ ቹን ፡ አውቶቡሶች ፡ በወር ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲመላለሱ ፡ ከማድረግ ፡ ይታገድ ፡ ዘንድ ፡ ትዕ ዛዝ ፡ እንዲሰጠው ፡ የቀረበ ፡ ክስ ።

<u>ውሳኔ ፤</u>— የከልከላው ፡ ትዕዛዝ ፡ ተሰጥቶአል ።

፩ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ አንቀ ጽ ፡ ፳፩ ፡ (፫) ፡ መሠረት ፡ የትራ ንስፖርት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ የሰጣቸውን ፡ የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ አውቶቡሶች ፡ የጊዜ ፡ መቆጣ ጠሪያ ፡ ሰሌዳ ፡ ለመመደብ ፡ ሥልጣን ፡ ቢኖረውም ፤ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ለሕዝቡ ፡ ጥቅም ፡ የማያቋርጥ ፡ አገልግሎት ፡ መኖሩን ፡ ለመቆጣጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በባለአውቶቡሶች ፡ መሐከል ፡ ያለውን ውድድር ፡ ለመቀነስ ፡ የተሰጠ ፡ አይደለም ።

፪ ፤ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ (፪) ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የትራንስፖርት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለተጨማሪ ፡ አውቶቡሶች ፡ ፈቃድ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት በተወሰነው ፡ መስመር ፡ የሚሰጠውን ፡ የአውቶቡስ ፡ አገልግሎት ፡ በቂነት ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ። ነገር ግን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ፈቃድ ፡ በመስጠት ፡ የሠራውን ፡ ስህተት ፡ ለማረም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ፈቃድ ፡ የሰጣ ቸውን ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ የጉዞ ፡ መብት ፡ መቀነስ ፡ ወይም ፡ መጨቆን ፡ ከልኩ ፡ ሲያልፍ ፡ ፈቃድ ፡ እን ደመከልከል ፡ ስለሚቆጠር ፡ እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፡ ተግባር ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም ።

፫ ፤ የትራንስፖርት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በባለአውቶቡሶች ፡ የግል ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በሚ ያደርጉት ፡ የግል ፡ ጨረታና ፡ ውድድር ፡ ገላጋይ ፡ በመሆን ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፤ ይኸው ፡ ባለአውቶቡ ሶች ፡ የሚያደርጉት ፡ ጨረታና ፡ ውድድር ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሰጡትን ፡ አገልግሎት ፡ የሚያቃውስ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፤ ውሳኔው ፡ ሕግን ፡ የተመረከዘ ፡ አይሆንም ።

ሰኔ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ። ዳኞች ፤— ሚስተር ፡ እስቲቨንሰን ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ከልል ፡ ሻምበል ፡ ኢያሱ ፡ ገብረ ፡ ሐዋርያት ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ አመልካቹ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ዘለለው ፡ በትርፍ ፡ ሁለት ፡ ጉዞ ፡ የነበራቸውን ፡ ቀንሰን ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲጠቀሙ ፡ ሆኖ፡ ትርፍ ፡ ጉዞውን ፡ ቀንሰን ፡ ለሌሎች ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ አከፋፍለናል ፡ በማለት ፤ በደብዳቤ ፡ ሕጋዊ ፡ መብቴን ፡ ከልክለውኛል ፡ በማለት ፡ በደብዳቤ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ የትእዛዝ ፡ መዝገብ ፡ ከፍተዋል ።

አመልካቹ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ዘለለው ፡ በመሠረቱ ፡ የሁለት ፡ አውቶቡሶች ፡ ባለቤት ፡ ሲሆኑ ፡ በነዚሁ ፡ አውቶቡሶች ፡ በጅማ ፡ መንገድ ፡ እንዲሠሩ ፡ በጅማ ፡ መስመር ፡ ቁ. ፱ ፡ መለያና ፡ በጅማ ፡ መንገድ ፡ ቁ. ፫ ፡ መለያ ፡ በሚል ፡ ፈቃድ ፡ የተለዩ ፡ የመኪና ፡ ፈቃድ ፡ (ላይሰንስ) ፡ ተሰጥትዋቸው ፡ ስምንት ፡ ጉዞ ፡ በወር ፡ አግኝተው ፡ የሕዝብ ፡ ትራንስፖርት ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ እንደነበረ ፡ ተረጋጡዋል ። መልስ ፡ ሰጭውም ፡ አልካዱም ። በክሳቸው ፡ ላይ ፡ አመልካች ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ በላይሰንሴ ፡ መሠረት ፡ ቀድሞ፡ የተፈቀደልኝን ፡ ጉዞ ፡ እንዳይከለክለኝ ፡ እንዲታገድና ፡ የሰጠውም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ሲሉ ፡ ጠይቀዋል ። የመልስ ፡ ሰጭው ፡ መ/ቤት ፡ ነገረፈጅ ፡ በሰጠው ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ የአመልካች ፡ ሁለት ፡ ትርፍ ፡ የነበረው ፡ ጉዞ ፡ እንዲቀነስ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ሕጋዊ ፡ ነው ። የጉዞውን ፡ ጊዜ ፡ መቆጣጠርና ፡ የጉዞውን ፡ ፈቃድ ፡ መቀነስ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ፡ ሥልጣን፡ በመሆኑ ፡ አመልካች፡ እንዳችም ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ አይገባቸውም፡ ከማለታቸውም ፡ በላይ ፤ አመልካቹ ፡ ከሌሎች ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ ይበልጥ፡ በትርፍ ፡ ሁለት ፡ ተጨማሪ ፡ ጉዞ ፡ ስለነበራቸው ፡ ሌሎች ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ አቤቱታ ፡ ስላቀረቡ ፡ ጉዳዩ ፡ በቦርዱ ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ ትርፍ ፡ ጉዞ ፡ እንዲቀነስና ፡ ለሌሎች ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ እንዲከፋፈል ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቶበታል ። ውሳኔው ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠ ፡ ስለሆነ ፡ ትክክለኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ተከራክረዋል ።

በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የትራንስፖርት ፡ አዋጅ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፭ ፡ (፫) ፡ በተመለከተው ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ የትራንስፖርት ፡ ፈቃድ ፡ (ላይሰንስ) ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በላይሰንሱ ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ግዴታ ፡ ሊያገባበት፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፤ በተጨማሪም ፡ በላይሰንሱ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ እንኳን ፡ የተጣሰ ፡ እንደሆን ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ (ላይሰንስ) እንዲሰረዝ ፡ ሊያዝ ፡ ይቻላል ፡ የሚል ፡ ነው ።

አመልካቹ ፡ (ላይሰንስ) ፈቃድ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ባመለከቱበት ፡ ፎርም ፡ ግርጌ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ ተሽከርካሪ ፡ ለሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ እንዲያገለግል ፡ ከተፈቀደልኝ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሚሰጠኝ ፡ የጊዜ ፡ ሠሌዳና ፡ በተወሰነ

ልኝ ፡ ሰዓት ፡ መንገድና ፡ ዋጋ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ የሚሰጠኝን ፡ ደንብ ፡ እየተከተልኩ ፡ የምሠራ ፡ መሆኔን ፡ ተስማምቼ ፡ ፈርሚያለሁ ፤ የሚል ፡ የግዴታ ፡ ጽሑፍ ፡ ሰፍሮበት ፡ ስለሚገኝ ፡ አመልካች ፡ ከግርጌው ፡ ፈርመውበታል ። ለአመልካቹም ፡ በተሰጡት ፡ ሁለት ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀቶች ፡ (ላይሰንሶች) ላይ ፡ ከዚሁ ፡ በላይ ፡ በማመልከቻው፡ፎርም፡ግርጌ፡የሰፈረው፡ግዴታ፡በተራ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ። ከዚሀ፡በላይ፡ በተጠቀሰውና፡የትራንስፖርት፡ አዋጅም፡በሚፈቅድላቸው ፡ መሠረት ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ የጊዜና ፡ የዋጋ ፡ መቆጣጠሪያ፡ሰሌዳ፡ ከግዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ፡ማውጣትና፡መቆጣጠር ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

የመልስ ፡ ሰጪው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነገረፈጅ ፡ አንድ ፡ የአውቶቡሶች ፡ ጉዞ ፡ መደብ ፡ የሚያመለክት ፡ ሠንጠረዥ ፡ በአስረጅነት ፡ አቅርበው ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዟል ። ይህ ፡ የጉዞ ፡ መደብ ፡ ድልድል ፡ የሚያመለክት፡ ሠንጠረዥ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ለዚህ ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ ለሆነው ፡ ለጅማ ፡ መንገድ ፡ መስመር ፡ ለባለ ፡ አውቶቡሶች ፡ የተሰጠው ፡ ጠቅላላ ፡ ላይሰንስ ፡ አስራ ፡ ዘጠኝ ፡ ሲሆን ፤ በዚሁ ፡ ድልድል ፡ ሠንጠረዥ ፡ ላይ ፡ አመልካቹ ፡ እንዳመለከቱት ፡ ሁለት ፡ ጉዞ ፡ መስመር ፡ ተቀንሶ ፡ ለሌሎች ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ መከፈሉን ፡ ያመለክታል ። እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ የሰሌዳ ፡ ሠንጠረዥ ፡ የሌሎቹም ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ ጉዞ ፡ ተደልድሎ ፡ ተወስኖ ፡ ይገኛል ።

የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ በጅማው ፡ መስመር ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ በብዛት ፡ ፈቃድ ፡ (ላይሰንስ) ሰጥቶአል ። በጉዞው ፡ ድልድል ሠንጠረዥ ፡ የተመለከተው ፡ እንኳ ፤ በቁጥር ፡ አስራ ፡ ዘጠኝ ፡ ላይሰንስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በብዛት ፡ በአንድ ፡ መስመር ፡ ላይሰንስ ፡ በመስጠቱ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ ወድቆአል ። በትራንስፖርት ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ (፪) ፡ ንዑ ስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ እንደሚነበበው ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ ፈቃድ ፡ (ላይሰንስ) በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ላይሰንስ ፡ እንዳይሰጥ ፡ በሚከለክልበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ማመልከት ፡ አለበት ፡ ይላል ። የሕዝብ ፡ ማመላለሻ ፡ ወይም ፡ ለንግድ ፡ ፈቃድ ፡ በሚጠየቅበት ፡ ጊዜ ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲሰጥ ፡ የተጠየቀበት ፡ መንገድ ፡ መስመር ፡ ለሌላ ፡ መሰጠቱንና ፡ ቀድሞ ፡ መያዙን ፡ ወይም ፡ ነፃ ፡ መሆኑን ፡ ፈቃድ ፡ ሰጭው ፡ ማመልከት ፡ አለበት ፡ ይላል ። በዚህ ፡ አስተያየት ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ በጅማ ፡ መስመር ፡ በብዛት ፡ ፈቃድ ፡ ላይሰንስ ፡ በሚፈቅድበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚሁ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ የአዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተው ፡ አይመስልም ። ጉዳዩም ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ላይሰንስ ፡ አሰጣጥ ፡ ሁኔታ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ነገረፈጅ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፤ ማመልከቻ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ላይሰንሱ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይፈቀዳል ፡ በማለት ፡ የአንዝህላልነት ፡ አነጋገር ፡ ሠንዝረአል ።

የመልስ ፡ ሰጭው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ምቹ ፡ የሆነውን የመድረሻ ፡ የዋጋ ፡ የጊዜ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ሰሌዳ ፡ ወይም ፡ ሠንጠረዥ ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እንዳስፈላጊነቱ ፡ ለማውጣት ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የባለአውቶቡሶችን ፡ ጉዞ ፡ መቀነስ ፡ ወይም ፡ መጨቆን ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ፈቃድ ፡ በተሰጣቸው ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ በሚያደርጉት ፡ ጨረታና ፡ የግላቸው ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ገብቶ ፡ ገላጋይ ፡ መሆን ፤ ወይም ፡ የሚወሰን ፡ የመስመር ፡ ጉዞ ፡ ድልድል ፡ መሥራትና ፡ በነጋዴዎች ፡ የግል ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ እንዲገባ ፡ የትራንስፖርት ፡ አዋጅ ፡ አይፈቅድለትም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የአመልካቹን ፡ ጉዞ ፡ ለመቀነስ ፡ የተገደደበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ በብዛት ፡ በአንድ ፡ መስመር ፡ ላይሰንስ ፡ በመስጠቱ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሰውን ፡ አለመግባባት ፡ ለመሸፈን ፡ ያህል ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ነገረፈጅ ፡ ያቀረቡት ፡ የጉዞ ፡ ድልድል ፡ ሠጠረዥ ፡ የትራንስፖርት ፡ አዋጅ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የጊዜና ፡ የመነሻ ፡ ወይም ፡ መድረሻ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ የጊዜ ፡ ሰሌዳ ፡ ሳይሆን ፤ የነጋዴዎችን ፡ የግል ንግድ ፡ ውድድር ፡ የሚወስን ፡ የጉዞ ፡ ብዛት ፡ ድልድል ፡ በመሆኑ ፤ ውድድር ፡ ለመቆጣጠር ፡ ቦርዱ ፡ አዋጁ ፡ ስለማይፈቅድለት ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊ ፡ የጊዜ ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ሆኖ አላገኘነውም ። ቦርዱ ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ሊያስብበት ፡ የሚገባው ፤ ተሳፋሪዎች ፡ ወይም ፡ መንገደኞች ፡ ምቾት ፡ የሚያገኙበትን ፡ ጊዜያት ፡ እንዲሁም ፡ በላይሳንስ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ መቆጣጠር ፡ እንጂ ፡ ላይሳንስ ፡ ከተሰጠ ፡ በላይ ፡ ነጋዴዎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚያደርጉትን ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ ምክንያትና ፡ መነሻ፡በማድረግ ፡ የንግዱ ፡ ጭቆናና ፡ ቁጥጥር ፡ ለማድረግ ፡ ቦርዱ ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ አይገባም ።

ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የጉዞ ፡ ድልድልና ፡ የመጓጓዝ ፡ ውድድር ፡ ማስተካከል ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የተወዳዳሪዎች ፡ የግል ፡ መብት ፡ ነው ። የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ ግን ፡ በላይሳንሱ ፡ በተመለከቱት ፡ ግዴታዎችና ፡ በትራንስፖርት ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ መመራት ፡ እንጂ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ መስመር ፡ ፈቃድ ፡ ከሰጠ ፡ በላይ ፡ በላይሳንሱ ፡ የሌላውን ፡ ግዴታ ፡ በመጣል ፡ የአመልካቹን ፡ የጉዞ ፡ መብት ፡ መቀነስ ፡ የትራንስፖርት ፡ አዋጅ ፡ አይፈቅድላቸውም ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ አመልካቹ ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ ሁለቱን ፡ ጉዞ ፡ ሊቀንስብኝ ፡ የቻለው ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ መስመር ፡ እንዲሠሩ ፡ በተጨማሪ ፡ ላይሰንስ ፡ ስለሰጠ ፤ የኔን ፡ ጉዞ ፡ ቀንሶ ፡ አከፋፍሏቸዋል ፡ በማለት ፡ ተከራክረው ፤ ከአመልካቹ ፡ በኋላ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የባለ ፡ አውቶቡሶች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ያለበት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የተሰጣቸውን ፡ ፈቃድ ፡ አቅርበው ፡ ተመልክተነዋል ።

አመልካቹ ፡ እንዳሉት ፡ ለሌሎች ፡ ባለአውቶቡሶች ፡ በተጨማሪ ፡ በዚሁ ፡ መሥመር ፡ እንዲሠሩ ፡ ፈቃድ ፡ ስለተሰጣቸው ፤ የትራንስፖርት፡ ቦርድ ፡ የአመልካቹን ፡ ሁለቱን ፡ ጉዞ ፡ ቀንሶ ፡ ለነዚሁ ፡ ባለአውቶቡሶች፡ አከፋፍሏቸዋል ። ይህም ፡ አድራጎት ፡ ከአዋጁ ፡ ጋር ፡ የተዛባ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ፤ ምክንያቱም ፡ አንደኛ ፡ መስመሩ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ መያዙ ፡ እየታወቀ ፡ በብዛት ፡ ፈቃድ ፡ መስጠቱ ፤ ሁለተኛም ፡ እንዲሠራ ፡ የተፈቀደለትን ፡ ሰው ፡ ያለአንዳች ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ጉዞውን ፡ ቀንሶ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ መደልደል ፡ አድራጎቱ ፡ በሕሊና ፡ ግምት ፡ ሆነ ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ።

ስለዚህ ፡ የትራንስፖርት ፡ ቦርድ ፡ በሰጠው ፡ ትዕዛዝ ፡ የመገናኛ ፡ ሚኒስቴር ፡ የአመልካቹ፡ የትራንስፖርት ፡ ጉዞ፡ እንዲቀነስ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፶፰ ፡ ዓ. ም. የሰጠውን ፡ የደብዳቤ ፡ ትዕዛዝ ፡ ውድቅ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገናል ። አመልካቹ፡ ቀድሞ ፡ ለትራንስፖርት ፡ በተሰጣቸው ፡ የጉዞ ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ የትራንስፖርት ፡ ተግባራቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ መብታቸውን ፡ አውቀን ፡ ፈቅደንላቸዋል ።

አመልካቹ ፡ በማይገባ ፡ ለተጉላሉበት ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ መ/ቤት ፡ ኪሣራ ፡ ፪፻ ፡ ብር ፡ (ሁለት፡መቶ ፡ ብር) ፤ ዳኝነት፡በደረሰኝ፡እንዲከፍሉ ፡ ብለን ፡ ፈርደናል።

የዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ ለፍርድ ፡ አስፈጻሚና ፡ ለሚፈልጉት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ይጻፍላቸው ፡ ብለናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Com. Div. No. 1

MESFIN ZELELLEW v. THE MINISTRY OF PUBLIC WORKS AND COMMUNICATIONS

Civil Case No. 301/55

Common carrier regulation — Licencing power — Limitation of competition — Transport Board — Arts. 21 (iia) and 21 (iii) Proc. No. 35 of 1943.

Administrative law — Licencing power — Transport Board.

In an action to enjoin the Ministry of Public Works and Communications from limiting the petitioner's buses to six trips per month on the Addis Ababa-Jimma circuit.

Held: Injunction granted.

1. Although Art. 21 (iii), Proc. No. 35 of 1943, empowers the Transport Board to set up timetables for the operation of passenger buses licenced by it, this power may be exercised only in order to insure good and regular service in the interest of the public, and it may not be used as a means of limiting competition among bus operators.

2. The Transport Board should consider the adequacy of bus service on a given route before licencing additional buses for the route, Art. 21 (iia), Proc. No. 35 of 1943, but it may not correct its mistake in granting an excessive number of licenses by imposing new limitations on the licences which it has granted if such limitations amount to virtual deprivation of the licences.

3. A decision of the Transport Board interfering with private arrangements between bus owners, regulating competition between them, is unlawful where the private arrangements do not upset effective service.

Sene 12, 1955 E.C. (June 19, 1963 G.C.); Judges: Mr. S. Stephenson, Ato Kebede Kelel, Captain Eyassu Gebre Hawariat: — The petitioner is the owner of two motorbuses and holds valid licences for their use in public passenger transportation on the Addis Ababa - Jimma road.

By a letter dated April 20, 1963, Exhibit P/1, the Ministry of Public Works and Communications informed the petitioner that the Transport Board had decided on April 11, 1963, that in the future he was entitled to serve the Addis Ababa - Jimma circuit only six times per month, that is, three times with each bus, instead of eight times per month as he had been until then.

The petitioner now claims that the decision of the Transport Board was without any legal basis and prays that the Ministry of Public Works be enjoined from preventing him from making eight trips per month as hitherto.

The Ministry maintains in defence that the decision was lawfully given and that the petitioner has no valid objection to it. The Ministry contends that the restriction in the number of trips the petitioner is allowed to make with his buses is within the rights reserved to the Transport Board under the conditions upon which the licences were granted.

The Transport Proclamation of 1943, Proc. No. 35 of 1943, declares in Article 21 (iii) that the Transport Board, when approving the issue of a licence, may impose any conditions it thinks fit and that it may require the licencing officer to cancel a licence for a breach of any condition. The printed application forms that were used by the petitioner when he applied for his licences contain the following clauses:

> "In the event the above described vehicles will be licenced as public service vehicles I hereby promise and agree that such vehicles will be operated only over routes, on the time schedules, for the fares approved and in accord with the conditions laid down from time to time by the Transport Board."

The licences actually issued to him contain clauses to a similar effect.

It follows from this that the petitioner would be bound to observe any timetable set up by the Transport Board to ensure an effective and regular service of the circuit in the interest of the public. It should also be clear that he must comply with any amendments in existing schedules that the Board had considered fit to make from time to time with the said purpose in view.

The representatives of the Ministry produced in court the timetable by which the petitioner is allowed to serve the route only six times per month. The timetable shows that other bus owners licenced to use their buses in passenger transport over the same route were also restricted in the number of trips they were allowed to make. It might seem to follow easily from this that the petitioner cannot complain if the Board deemed it necessary to reduce the petitioner's number of trips in order to set up an effective timetable.

Such a conclusion, however, would not give sufficient attention to the real ground for the Board's decision. Clearly, the Board has approved too many licences for passenger buses on the Jimma circuit. There are at present 19 valid licences for this single circuit. It seems quite safe to say that the Board, in approving so many licences, has made an error. Article 21 (iia) of the Transport Proclamation provides that:

> "In the case of public service and commercial vehicles: The extent to to the following:

> "In the case of public service and commercial vehicles: The extent to which the route in respect of which the application is made is already served."

That the Board has overlooked this beneficient provision is quite clear from the remark of one of the Ministry's representatives in Court that: "People apply and we grant."

The issue of the case is in sight. The time schedule has been set up by the Board not for the single purpose of ensuring a regular and good service in the interest of the public, but chiefly to regulate and restrain the competition between too many licencees. There is no doubt on this point. That the Board, in restricting the petitioner's number of trips, has been motivated by a desire to obtain what it may have deemed a fair distribution among the bus owners of the trips over the route is evident from the letter, referred to above, that was addressed to the petitioner by the Ministry, and it is openly admitted by the defence that such a distribution of trips formed the real ground for the decision to restrict the number of trips and the resulting timetable.

We have now reached the true issue. The restrictive timetable was not set up for the sake of setting up a time schedule, but for the sake of regulating private competition. Neither the letter, nor the spirit, of the Transport Proclamation allows the Board to impose on licence holders a condition based on such a ground. Regulation of existing private competition is not the concern of the Transport Board.

The distinction may be subtle, but it would appear that no objection could be raised to a condition inherent in a timetable that, having due regard for the interests of the public, in a reasonable way obviated unnecessary scramble for passengers. But let us take an extreme example. Suppose that a licence was granted to use a vehicle as a public service vehicle on a route which could easily support daily service, and the Board there imposed the condition that the licencee could drive only once a month. That would be equivalent to depriving him of the benefit of his licence, and the condition would obviously be unlawful.

Let us consider the case of the petitioner according to this criterion. He has licences to serve the Jimma route in passenger transportation with two buses. Even allowing for layovers for repairs and the like, he could make many more than six trips per month without the least difficulty. With only six trips a month, he is prevented to too great an extent from using his buses to capacity. The condition imposed upon him amounts to nothing less than a virtual deprivation of his licences. It cannot be a lawful condition.

The result might have been different if the petitioner had applied for licences to use the buses on the route on a part-time basis, and had been granted his licences with that understanding, but that is not the case at all. The petitioner has no other use for his buses than to drive them in public passenger transportation over the Jimma route, and that was quite clearly understood when he applied for and was granted his licence. The situation might also have looked different if the Transport Board had allowed the petitioner to operate his buses on other routes when they were not used on the Jimma route, but the

Board has not done this. Rather, it has simply demanded that the buses stand idle for the greater part of the time.

That full and unrestrained competition on this circuit, since there are too many licence holders, might lead to failure for some bus owners, maybe for the petitioner, is not a point to be considered by the Court. The individual bus owners should have considered that possibility when acquiring their buses and applying for licences. The Transport Board could, and should, have considered it when approving licences. The error of the Board in approving too many licences cannot, however, be remedied by the Board afterwards by preventing the licencees from making use of their licences. What the Board can do is to refuse to grant additional licences and to cancel existing licences where lawful occasion to do so arises, as for instance when a bus becomes unserviceable.

It should finally be mentioned that in so far as the decision of the Transport Board interferes with a private arrangement between bus owners, regulating competition between them, the Board's decision is also illegal, provided that such arrangement does not upset the effective service of the route, which there is no indication that the arrangement did.

In view of what is mentioned, the Court holds that the injunction must be granted. The petitioner appears to be satisfied if allowed to drive eight trips per month with his two buses as previously. It is, therefore, sufficient for the Court to enjoin the Ministry of Public Works and Communications from preventing the petitioner from driving those eight trips per month.

The Court need not consider the manner in which the Ministry has set up a timetable for the circuit in view of this injunction.

The respondent, the Ministry of Public Works and Communications, shall reimburse the petitioner, Ato Mesfin Zelellew for court fees paid, according to receipt, and with E$200 for other costs of the case.

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ አንደኛ ፡ የንግድ ፡ ችሎት ።

ቤንጀር ፡ የቤፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ከሳሽ ፤ ሐዘናው ፡ አሰሚ ፡ መልስ ፡ ሰጭ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፰/፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ።

ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድር — ስለ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት—የንግድ፡ሕግ አንቀጾች ፡ ፩፻፴፪ (፩) ፡ እና ፡ ፩፻፵፩ (፩) ። *

አመልካች ፡ የቤንጀር ፡ መኪናዎች ፡ ባለ ፡ ፋብሪካ ፡ እናንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ መልስ ፡ ሰጭው፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ አውጥቶ ፡ ስለሚጠቀም ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ከመጠቀም መልስ ፡ ሰጭ ፡ እንዲታገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይሆን ፡ ክስ ፡ አቀረቡ ። መልስ ፡ ሰጭም ፡ የ የቤፌት ፡ መኪና ፡ ሻጭ ፡ ሲሆን ፡ ሁለቱ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ተመሳሳይ ፡ አለመሆናቸውንና ፡ የአመልካቹም ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያውቀው ፡ በአገር ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ የወጣ ፡ ቢሆንም ፤ በንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ አልተመዘገበም ፡ ሲሉ ፡ ተከራከሩ ።

<u>ውሳኔ</u> ፤ —ፍርድ ፡ ለአመልካች ፡ ተሰጥቶአል ። መልስ ፡ ሰጭ ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ እንዳይጠቀምና ፡ በንግድ ፡ ሲቀም ፡ የሰጠፈውን ፡ ይሆንኑ ፡ ምልክት ፡ እንዲያነሣ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶአል ።

ነጋዴው ፡ የመረጠው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ የንግዱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስሌዱ ፡ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ከሚጠቀምበት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝና ፤ ይህም ፡ በማኅበር ፡ ምክንያት ፡ የዚያኑ ፡ ነጋዴ ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ እንደ ፡ ተገቢ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ውድድር ፡ ተቈጥሮ ፡ ይኸው ፡ ተግባር ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴፪ ፡ (፩) እና ፡ ፩፻፵፩ ፡ (፩) መሠረት ፡ እንዲቆም ፡ ይከለከላል ።

ግንቦት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዳኞች ፤ ሚስተር ፡ እስቲቨሰን ፡ ሻምበል ፡ ኢያሱ ፡ ገብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ብላታ ፡ ይስሐቅ ፡ ተፈሪ ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ የቀረበው ፡ የክሱ ፡ ምክንያት ፡ አመልካች ፡ የቤንጀር ፡ ኩባንያ፤ የቤንጀር ፡ መኪናዎች ፡ ባለፋብሪካ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፤ የመኪና ፡ መሸጥና ፡ የመኪና ፡ መለዋወጫ ፡ ዕቃዎች ፡ ጭምር ፡ ይሸጣል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የመኪና ፡ ስፌት ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተምር ፡ የንግድ ፡ አዳም፡ ያለው ፡ ኩባንያ ፡ በመሆኑ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራው ፡ የፋብሪካውና ፡ ለሌላው ፡ ንግድ ፡ ምልክት ፡ አለው ። አመልካች ፡ ለዚሁ ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ የንግድ ፡ ምል

* የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴፮ን ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፷፫ን ፡ በተጨማሪ ፡ ተመልከት ።

ከት፡ አቅርበው፡ ፩ኛ፡ የአመልካች፡ ማስረጃ፡ ሲባል፡ መልስ፡ ሰጭው፡ ተመሳሳይ፡ የሆነ፡ የንግድ፡ ምልክት፡ አውጥቶ፡ ሕዝብን፡ ለማሳሳትና፡ የማይገባ፡ የንግድ፡ ውድድር፡ ለማድረግ፡ በጋዜጣ፡ ማስታወቂያ፡ ከማውጣቱም፡ በላይ፤ በንግድ፡ ቤቱ፡ በርና፡ በየመስኮቱ፡ በመለጠፍ፡ ከሕግ፡ ውጭ፡ የሆነ፡ ውድድር፡ በመፈጸም፡ ላይ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ይህን፡ ከማድረግ፡ እንዲታገድ፡ አመልካች፡ በዚህ፡ ትእዛዝ፡ መዝገብ፡ ጠይቀዋል። መልስ፡ ሰጭው፡ ያወጣው፡ የንግድ፡ ምልክት፡ እ. ኤ. አ. በየካቲት፡ ፳ ፲፱፻፶፮፡ ዓ፡ ም፡ የወጣውን፡ ኢትዮጵያን፡ ሔራልድ፡ ጋዜጣ፡ አቅርበው፡ ፪ኛ፡ የአመልካች፡ ማስረጃ፡ ተባለ። ተከሣሹ፡ ፪ኛ፡ የአመልካች፡ ማስረጃ፡ የተባለውን፡ በፍርድ፡ ቤቱ፡ ጥያቄ፡ መሠረት፡ አይቶ፡ የራሱ፡ የንግድ፡ ምልክት፡ ለመሆኑ፡ አምኖታል። በተጨማሪም፡ አመልካች፡ አሪጂናሉን፡ የንግድ፡ ምልክት፡ በአልበሙ፡ አቅርበው፡ ከተመለከትነው፡ በኋላ፡ ተመልሶላቸዋል።

መልስ፡ ሰጪው፡ ለቀረበበት፡ ክስ፡ የተብራራ፡ የመከላከያ፡ መልስ፡ አልሰጠም። ቢሆንም፡ በጠቅላላው፡ ምልክቱ፡ ተመሳሳይ፡ አይደለም፡ ብሏል። እንዲሁም፡ ለነገሩ፡ አግባብ፡ የሌለው፡ ሌላ፡ ክርክር፡ በማቅረብ፡ የአመልካች፡ የንግድ፡ ምልክት፡ አልተመዘገበም፡ ብሎ፡ ጠቅሳል። ይህ፡ ክርክር፡ ላሁኑ፡ ክስ፡ አግባብ፡ ሊኖረው፡ አይችልም፤ ምክንያቱም፡ የዚህ፡ ኩባንያ፡ ዋናው፡ መሥሪያ፡ ቤቱ፡ በአሜሪካ፡ እንደመሆኑ፡ መጠን፡ በዚያው፡ የታወቀና፡ የተመዘገበ፡ ሲሆን፤ ይህ፡ የንግድ፡ ምልክት፡ ለረጅም፡ ዘመን፡ በመላ፡ ዓለም፡ የታወቀ፡ ለመሆኑ፡ ግልጽ፡ ነው። በዚህ፡ ምክንያት፡ ይህን፡ ክርክር፡ አልተቀበልነውም።

በመሠረቱ፡ ይህ፡ የአመልካች፡ ኩባንያ፡ የሲንጀር፡ የስፌት፡ መኪና፡ ባለ፡ ፋብሪካ፡ ሲሆን፤ በፋብሪካው፡ እየተሠሩ፡ የሚወጡት፡ መኪናዎች፡ በመላ፡ ዓለም፡ ገበያ፡ የተበተኑ፡ ሲሆን፡ ይህም፡ ክርክር፡ የተነሳበት፡ የፋብሪካው፡ የንግድ፡ ምልክት፡ እንደዚሁ፡ ይህ፡ ፋብሪካ፡ ከቆመበት፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ የአመልካች፡ ማኅበር፡ መለያ፡ ምልክት፡ በመሆን፡ በሰፊው፡ በዓለም፡ የንግድ፡ ገበያ፡ ሲታወቅ፡ ይኖራል። እንደዚሁም፡ የአመልካች፡ ማኅበር፡ በኢትዮጵያ፡ ግዛት፡ ውስጥ፡ ለአያሌ፡ ዘመን፡ ተቋቁሞ፡ ስለሚሠራ፡ በዚሁ፡ መለያ፡ የንግድ፡ ምልክቱ፡ሲታወቅ፡ ኖሯል።

መልስ፡ ሰጪው፡ ለአያሌ፡ ዘመን፡ የአመልካች፡ ማህበር፡ ሠራተኛ፡ እንደ፡ ነበረ፡ የአመልካች፡ ጠበቃ፡ ባመለከቱት፡ ተገልጿል። እንዲሁም፡ የአመልካች፡ ማኅበር፡ ሌላ፡ ቤት፡ ተከራይቶ፡ ሲለቅ፡ መልስ፡ ሰጪው፡ ጥንት፡ የአመልካች፡ ማኅበር፡ ይኖርበት፡ የነበረውን፡ የንግድ፡ ቤት፡ ተከራይቶ፡ ተመሳሳይ፡ የሆነ፡ ሥራ፡ መክፈቱ፡ በማስረጃ፡ ተገልጿል።

የአመልካች ፣ ማኅበር ፣ በአስረጅነት ፣ በአቀረቡልን ፣ በንግድ ፣ ምልክቶች፣ አልቡም ፣ ውስጥ ፣ እንደተመለከትነው ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ዓይነት ፣ ምልክቶች ፣ አሏዋ ቸው ። መልስ ፣ ሰጭው ፣ ግን ፣ በቃል ፣ እንደ ፣ ገለጸው ፣ ነጭና ፣ ቀይ ፣ ቀለም፣ የተ ቀባ ፣ ምልክት ፣ እንዳለው ፣ ለፍ/ ቤቱ ፣ ገልጸዋል ። በመሠረቱ ፣ የመልስ ፣ ሰጭው፣ ምልክት ፣ በቀለሙ ፣ ሆነ ፣ በፊደሉ ፣ ቅርጽ ፣ ከአመልካች ፣ የንግድ ፣ ምልክት ፣ የተ ቀዳ ፣ ዓይነተኛ ፣ ግልባጭ ፣ እንደሆነ ፣ በቀረበው ፣ ማስረጃ ፣ ሊመዛዘን ፣ ተችሏ ዋል ። ከሁሉም ፣ ይልቅ ፣ አመልካች ፣ ማኅበር ፣ ለረጅም ፣ ዘመን ፣ በንግድ ፣ አገል ግሎት ፣ ሥራ ፣ በታወቀበት ፣ የንግድ ፣ ቤት ፣ ውስጥ ፣ መልስ ፣ ሰጭው ፣ በኪራይ ፣ መልክ ፣ ገብቶ ፣ በየበሩና ፣ በየመስኮቱ ፣ መስትዋት ፣ ላይ ፣ ይህን ፣ ምልክት ፣ ለጥፎ፣ ሲታይ ፤ መልስ ፣ ሰጭው ፣ የሠራው ፣ የንግድ ፣ ምልክት ፣ ከአመልካች ፣ ምልክት ጋር ፣ ተመሳሳይና ፣ አሳቻ ፣ በመሆኑ ፣ ተላላፊውን ፣ ሕዝብና ፣ ገበያተኛውን ፣ የሚ ያሳክር ፣ ሁኔታን ፣ የሚፈጥር ፣ ነው ።

መልስ ፣ ሰጭው ፣ በመሠረቱ ፣ ከየኩባንያዎች ፣ እየገዛ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ዓይነት ፣ መኪናዎች ፣ የሚሸጥ ፣ ነጋዴ ፣ ሲሆን ፣ አመልካቹ ፣ ከፋብሪካው ፣ እየሠራ ፣ የሚ ሸጥ ፣ የተቋቋመ ፣ ማህበር ፣ ነው ። በመሠረቱ ፣ ከሌላ ፣ ፋብሪካ ፣ ለመለየት ፣ በሚ ያወጣው ፣ የመኪና ፣ ዓይነት ፣ ስያሜውና ፣ የፋብሪካ ፣ ምልክቱን ፣ አደራጅቶ ፣ ሲጠራበትና ፣ በዓለም ፣ ሲታወቅበት ፣ ይኖራል ።

መልስ ፣ ሰጭው ፣ ግን ፣ ከትልልቅ ፣ ነጋዴዎች ፣ እየገዛ ፣ ለትርፍ ፣ የሚሠ ሠራ ፣ ቸርቻሪ ፣ ነጋዴ ፣ ሲሆን ፤ ለንግድ ፣ ቤቱ ፣ ስም ፣ መለያ ፣ የተለየ ፣ የሠሌዳ ፣ ጽሑፍ ፣ ከማድረግ ፣ ፋንታ ፣ እንደ ፣ ባለፋብሪካዎች ፣ (የፓቴንት) ፣ ወይም ፣ ልዩ ፣ ምልክት ፣ (ትሬድ ፣ ማርክ) ፣ መለጠፉ ፣ የተንኰል ፣ ውድድርን ፣ ለመክፈት ፣ የተ ገፋፋ ፣ ከንቱ ፣ ምኞት ፣ ከመሆኑም ፣ በላይ ፣ ተመሳሳይ ፣ የንግድ ፣ ምልክት ፣ በማ ድረግ ፣ ሕዝብንና ፣ ገበያተኛውን ፣ በማሳከር፣ በአመልካች ፣ ማኅበር ፣ ዝናና ፣ መለያ ስም ፣ ያላግባብ ፣ መጠቀም ፣ ይሆናል ። በአንድም ፣ በኩል ፣ ስንመለከተው ፣ በአነ ስተኛ ፣ የመነገጃ ፣ ገንዘብ ፣ ተነስቶ ፣ የንግድ ፣ ምልክቱን ፣ አሳቻ ፣ መሣሪያ ፣ በማ ድረግ ፣ በዓይነቱ ፣ ርካሽ ፣ የሆኑትን ፣ ዕቃዎች ፣ በመደርደር ፣ ሕዝብና ፣ ገበያተኛን፣ ማታለል ፣ ይሆናል ። በመሠረቱ ፣ ይህ ፣ ሁኔታ ፣ የንግድ ፣ ምልክቶች ፣ ለሕዝብ ፣ ከመታወቃቸውና ፣ ከመገለጻቸው ፣ በፊት ፣ አግባብ ፣ ያለው ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ በጥብቅ ፣ ሊያስብበት ፣ የሚገባው ፣ ተቀዳሚ ፣ ተግባር ፣ ነው ።

በንግድ ፣ ሕግ ፣ በቁ. ፩፻፷፫ ፣ (፪) ፣(ሀ) እንዲሁም ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፵፩ ፣(፪) እንደ ፣ ተመለከተው ፣ በቅድሚያ ፣ እንዲሠራባቸው ፣ የተሰጡት ፣ የንግድ ፣ ምል ክቶች ፣ በማናቸውም ፣ አኳኋን ፣ ሌላው፣ ነጋዴ፣ በመሰል፣ ሊሠራባቸውና ፣ ሊጠቀ ምባቸው ፣ እንደማይገባ ፣ ሕጉ ፣ አጥብቆ ፣ ይከለክላል ። ስለዚህ ፣ የአመልካች ፣፩ኛ ማስረጃ ፣ ቀርቦልን ፣ የተመለከትነው ፣ በአልቡም ፣ ላይ ፣ የተለጠፉት ፣ ንግድ ፣

ምልክት ፣ አመልካች ፣ ማኅበር ፣ በመላ ፡ ዓለምና ፣ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፣ በቅድ ምያ ፣ የሚታወቅባቸው ፣ መለያ ፡ ምልክቶች ፡ ስለሆኑ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፣ እንደ ፣ ገለ ጽነው ፣ ሁሉ ፣ መልስ ፡ ሰጭው ፣ ያላግባብ ፣ ለመጠቀምና ፡ በመስለ ፣ ወይም ፡በእ ሳቻ ፣ የንግድ ፣ ምልክት ፣ ገበያተኛን ፣ ለማሳከር ፡ የተደረገ ፣ ስለሆነ ፤—

መልስ ፣ ሰጪው ፡ አቶ ፣ አዛናው ፣ ዓለሜ ፣ ኢ. ኤ. አ. በ፳-፱-፲፱፻፷፬ ዓ ም በወጣው ፣ ኢትዮጵያን ፣ ሔራልድ ፣ ጋዜጣ ፡ የወጣው ፣ የንግድ ፡ ምልክት ፣ ይህ ፡ ፍርድ ፣ ከተሰጠበት ፡ ከግንቦት ፣ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፣ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፣ እንዳይሠራ በት ፣ አግደናል ። ይህ ፡ ፍርድ ፣ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፣ በንግድ ፡ ቤቱ ፣ ውስጥ ምልክቶችን ፡ እንዳይሠራባቸውና ፡ በንግድ ፡ ቤቱም ፡ የለጠፈውን ፣ በሙሉ ፣ እንዲ ያነሳ ፣ ፈርደናል ። መልስ ፣ ሰጪው ፡ በፍጥነት ፡ ፈቃደኛ ፡ ሆኖ ፣ ባያነሳ ፡ የፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ በክፍሉ ፡ ፖሊስ ፡ አማካይነት ፡ ምልክቶቹን ፣ እንዲያስነሳ ፣ ፍ/ ቤቱ ሥልጣን ፣ ሰጥቶታል ።

መልስ ፣ ሰጪው ፣ ፩፻ ፡ ብር ፡ ኪሣራና ፣ ዳኝነት ፣ በደረሰኝ ፡ ለአመልካች ፣ ለሴንጀር ፡ ኩባንያ ፡ እንዲከፍል ፤ ለመክፈል ፡ ፈቃደኛ ፣ ባይሆን ፡ ንብረቱ ፣ በሐ ራጅ ፣ ተሸጦ ፣ ኪሣራውንና ፡ ዳኝነቱን ፣ ፍርድ ፣ አስፈጻሚ ፣ እንዲያስፈጽም ፣ የፍርዱ ፡ ግልባጭ ፡ ይተላለፍ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አመልካች ፣ የደረሰበት ፣ ኪሣራ ፣ ቢኖርና ፣ የወንጀ ልም ፡ ኃላፊነት ፡ ቢኖር ፣ የመክሰሱ ፣ መብት ፣ እንደተጠበቀ ፣ ነው ፣ ብለን ፣ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ ፈርደናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Com. Div. No. 1

SINGER SEWING MACHINE CO. LTD. v. AZANAW ALEME

Civil Case No. 260/56

*Unfair competition — Trademarks — Arts. 133(2) and 141(2) Comm. C.**

Plaintiff, a manufacturer of sewing machines, brought suit to obtain an order restraining defendant from using a trademark the same as that of plaintiff. Defendant, a seller of sewing machines, argued that the trademarks are not similar and that plaintiff's trademark, although published in a local newspaper, was not registered.

Held: Judgment for plaintiff; defendant ordered not to make use of his trademark and to remove all such trademarks from where they are posted.

The use of a trademark or distinguishing mark which is likely to create confusion in a manner prejudicial to another trader who has been using an identical trademark constitutes unfair competition and is forbidden by Comm. C. Arts. 133(2) and 141(2).

Guenbot 8, 1956 E.C. (May 16, 1964 G.C.); Judges: Mr. S. Stephenson, Capt. Eyassu Gebre Hawariat, Blatta Yishack Tefferi: — In this case the plaintiff, Singer Manufacturing Company, is the manufacturer of Singer Sewing Machines. The said company has been authorised to sell sewing machines and spare parts throughout the Empire of Ethiopia. Moreover, the said company gives lessons in the use of sewing machines. To carry out these commercial activities the said company has a trademark of its own. The plaintiff has presented as Exhibit P/1 the trademark which is the subject of this case. Defendant also has produced a similar trademark in order to confuse people. This constitutes an act of unfair competition; the said trademark has been published in the newspaper. Defendant also posted the trademark on doors and windows. Plaintiff has requested the Court to stop these unfair activities under this file. The plaintiff has produced as Exh. P/2 the notice published in the Ethiopian Herald on February 20, 1964. The defendant has admitted that the trademark shown in the newspaper is his own. In addition to this the plaintiff has produced the original trademark in an album; the Court has examined it and given it back.

The defendant could not produce a clear statement of defence to the charge brought against him. He declared generally that the trademarks are not similar. He even brought in a point outside the issue by saying that the trademark of the plaintiff is not registered. This argument is not applicable to this case because, since the head office of this company is in America, it has registered

* See also Art. 134 Comm. C. and Arts. 2120 and 2122 Civ. C.

its trademark there, and this trademark has been known all over the world for many years. So for this reason we did not accept this argument.

Plaintiff company, as a manufacturer of sewing machines, has spread its products in the world market. Since the said trademark is the property of the company it is known all over the world. So, also, since plaintiff company has operated for a very long time in the Empire of Ethiopia this same trademark is popular in the country.

It has been revealed also that defendant had been an employee of plaintiff company for many years. Plaintiff has rented another building and transferred its business. Defendant occupied the same old building of plaintiff company and was carrying on the same kind of activity as his previous employer. Plaintiff company has shown to the Court its different trademarks. But, the defendant has declared orally that he has got a trade mark which is white and red. The Court has examined the trademark of the defendant and it has been found an accurate copy of plaintiff company's trademark, both in the letter and the colour.

The situation has been more confusing for the public due to the occupation of the same old building of plaintiff company by the defendant, and his pasting of the trademark on doors and windows.

In principle, the defendant is a retailer who buys sewing machines from other companies and sells them; whereas plaintiff company sells its own products. Plaintiff company has designated its own trademark in order to differentiate itself from other companies and it has been known all over the world by this name.

The defendant as a retailer should have used a different trademark instead of using that of a manufacturer of long standing. The defendant by doing this has entered into an unfair competition driven by malicious ill-will. By this very act he has also confused the public and consumers. He has also taken unfair advantage of the reputation and trademark of plaintiff company. In other words this act has been devised to sell a cheaper quality of goods at the expense of the good name of the company by using a similar trademark and at the same time confusing the consuming public. In fact, such acts should have been examined by the department concerned before such trademarks are exposed to the public.

Art. 133(2) and Art. 141(2) of the Commercial Code forbid unfair competition where the distinguishing mark is likely to create confusion in a manner prejudicial to another trader having used an identical distinguishing mark.

Having examined the trademarks submitted by the plaintiff company and the long usage of the same trademark both abroad and in Ethiopia prior to its usage by defendant, and having understood the intentional use of a similar or confusing trademark by the defendant in order to mislead the public, we

have ordered Ato Azenaw Aleme not to make use of the trademark published in the Ethiopian Herald on February 20, 1964, beginning from May 16, 1964, the date on which this judgment is delivered. We have also ordered defendant to remove the posted trademarks. If defendant fails to remove the said trademarks immediately, the Execution Office has been authorised to remove the said marks through the local police.

It has been ordered also that a copy of this judgment be sent to the Execution Office in order to enable that office to sell the property of the defendant in case he fails to pay E$100 costs and court fees by receipt presented.

We have unanimously given this judgment reserving the right of the plaintiff to proceed with the case if it has a civil or criminal claim against the defendant.

This judgment is given this 16th day of May, 1964, in the presence of counsel for plaintiff and defendant at the First Division of the Commercial Court.

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ አንደኛ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎት ፡፡

ከቡር ፡ ልጅ ፡ እርአያ ፡ አበበ ፡ ከሳሽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፩/፷፪ ፡ ዓ. ም. ፡፡

የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ — ስለ ፡ ግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ — « ሕግ » የሚለው ፡ አነጋገር— ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ እና ፡ ፻፭፪ — የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡፡

የግል ፡ ንብረት ፡ በተወሰደ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡፡

የፖስታ ፡ ቴሌግራፍ ፡ ቴሌፎን ፡ ሚኒስቴር ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ መሠረት ፡ የከሳሹን ፡ ዛፍ ፡ ስለቆረጠ ፡ ፩፻ ፡ ብር ፡ ዋጋ ፡ ይከፍለኛል ፡ ሲሉ ፡ ከሳሽ ፡ ያቀረቡት ፡ ክስ ፡፡

ውሳኔ ፤ ተከሳሹ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለቆረጠው ፡ ዛፍ ፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ አይገባውም ፡፡

፩/ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ የተወሰደ ፡ እንደሆነ ፡ ትክክለኛ ፡ ዋጋ ፡ አስቀድሞ ፡ መከፈል ፡ እንዳለበት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ተደንግጓል ፡፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሲባል ፡ የተወሰደ ፡ ንብረት ፡ በሰሴሰ ፡ ዛፈን ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ቆረጠብኝ ፡ ለሚለው ፡ ክርክር ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ አግባብ ፡ የለውም ፡፡

፪/ ፡ የፖስታ ፡ ቴሌግራፍ ፡ ቴሌፎን ፡ ሚኒስቴር ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ተብለው ፡ የተዘረጉት ፡ የስልክ ፡ መስመሮች ፡ መሰናከል ፡ የሆኑትን ፡ ዛፎች ፡ ለመቁረጥ ፡ የሚፈቀድለት ፡ ሕግ ፡ ስላለ ፡ (አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ ፡ አንቀጽ ፡ ፯) ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የተነሳ ፡ ዛፉ ፡ የተቆረጠበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ " ያለ ሕግ ፡ ንብረቴን ፡ አጣ" ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፡ (ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፵፫)፡፡

ሰኔ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም ፡፡ ዳኞች ፤ —ዶክተር ፡ ዊሊያም፡ ቡሐጅያር፡ አቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ባላምበራስ ፡ ዓለማየሁ ፡ ፈንታ ፡፡

የክሱ ፡ ምክንያት ፡ በ፩፻፲ ፡ ብር ፡ ነው ፡፡

ከሳሽ ፡ በጠበቃው ፡ አማካይነት ፡ መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. በተጻፈ ፡ የክስ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያመለክት ፡ ከሳሽ ፡ ገፈርሳ ፡ በተባለው ፡ ሥፍራ፡ አንድ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ አላቸው ፡፡ በዚሁ ፡ በአንድ ፡ ጋሻ ፡ መሬትም ፡ ላይ፡ ከሳሽ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዛፍና ፡ ሌላም ፡ አትክልት ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ተክለዋል ፡፡ ተከሳሹ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ ለቀምት ፡ የሚሔደውን ፡ የቴሌፎን ፡ መሥመር ፡ ለመዘርጋት ፡ በአሰበ ፡ ጊዜ ፡ ከሳሽ ፡ የቴሌፎን ፡ መሥመሩ ፡ ወደ ፡ ሌላ፡ቦታ እንዲዛወርላቸው ፡ ለተከሳሹ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት፡ ቢያሳስቡ ፡ አልተቀበላቸውም ፡፡

የመናገሻ ፣ አውራጃ ፣ ግዛት ፣ ከአገር ፣ ግዛት ፣ ሚኒስቴር ፣ የተላለፈ ፣ ትእዛዝ ፣ ነውና ፣ በመሬታቸው ፣ ላይ ፣ የሚገኘውን ፣ ዛፍ ፣ እንዲቆርጡ ፣ ግንቦት ፣ ፲፱ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፺፩ ፣ ዓ. ም. በተጻፈ ፣ ደብዳቤ ፣ ጽፎላቸው ፣ ነበር ። ከሳሽም ፣ በበኩላቸው ፣ መልስ ፣ ሰጥተውበት ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ የተከሳሹ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ በከሳሽ ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ የነበረውን ፣ የጥድ ፣ አትክልት ፣ ሠራተኛ ፣ ልኮ ፣ አስቆረጠው ። አሁን ፣ የከሳሽ ፣ መብት ፣ በሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ ቁጥር ፣ ፵፫ ፣ እና ፣ ፵፬ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግም ፣ በቁጥር ፣ ፲፬፻፸፰ ፣ መሠረት ፣ የተደገፈ ፣ ስለሆነ ፣ ተከሳሽ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ለተቆረጡት ፣ ዛፎች ፣ ግምት ፣ አምስት ፣ ሺህ ፣ ብር ፣ እንዲከፍል ፣ እንዲፈረድበት ፣ ብለው ፣ አመልክተዋል ።

እንዲሁም ፣ ተከሳሽ ፣ በነገረ ፣ ፈጁ ፣ አማካይነት ፣ የካቲት ፣ ፫ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፺፩ ፣ ዓ. ም. በጻፈው ፣ የመከላከያ ፣ መልስ ፣ ሲያመለክት ፣ ከሳሽ ፣ በክስ ፣ ማመልከቻው ፣ እንዳረጋገጡት ፣ የጥድ ፣ ዛፋቸው ፣ ከአዲስ ፣ አበባ ፣ ወደ ፣ ለቀምት ፣ የተዘረጋውን ፣ የስልክ ፣ መገናኛ ፣ በማሰናከሉ ፣ ከመስመሩ ፣ ግራና ፣ ቀኝ ፣ ሁለት ፣ ሜትር ፣ እርቀት ፣ ድረስ ፣ እንዲያስቆርጡ ፣ ባያስቆርጡ ፣ ግን ፣ ተከሳሹ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ለስልክ ፣ መገናኛ ፣ መሰናከል ፣ የሆኑትን ፣ ዛፎች ፣ ሕግ ፣ በሚፈቅድለት ፣ መሠረት ፣ በራሱ ፣ ሠራተኞች ፣ የሚያስቆርጥ ፣ መሆኑን ፣ ማስጠንቀቂያ ፣ ጽፎላቸው ፣ ነበር ። ተከሳሹ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ሕግ ፣ በሚፈቅድለት ፣ መሠረት ፣ ለስልኩ ፣ መስመር ፣ መሰናከል ፣ የሆኑትን ፣ ዛፎች ፣ ማስቆረጡ ፣ አይካድም ፣ ይሁን ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ የተከሳሽ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ አድራጎት ፣ በነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ አዋጅ ፣ ቁጥር ፣ ፶፲፬ ፣ የተፈቀደለት ፣ ስለሆነ ፣ ከሳሽ ፣ ያቀረቡት ፣ ክስ ፣ ከኪሣራ ፣ ጋር ፣ እንዲሰናበት ፣ ብሎ ፣ ክርክሩን ፣ አቅርቦአል ።

በከሳሽና ፣ በተከሳሽ ፣ በየበኩላቸው ፣ የቀረበው ፣ ክርክር ፣ ፍሬ ፣ ነገሩ ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ እንደተዘረዘረ ፣ ሆኖ ፣ ተከሳሽ ፣ ሐምሌ ፣ ፳፪ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፬ ፣ ዓ. ም. በቁጥር ፣ ፩፻፲፬/፶፪ ፣ ዓ. ም. የወጣው ፣ አዋጅ ፣ በአንቀጽ ፣ ስድስት ፣ መሠረት ፣ ለቴሌፎን ፣ ሽቦ ፣ እንቅፋት ፣ የሚሆነውን ፣ ዛፍ ፣ ሁሉ ፣ ለመቁረጥ ፣ ወይም ፣ ለማስቆረጥ ፣ ሥልጣን ፣ ተሰጥቶናልና ፣ በዚሁ ፣ አዋጅ ፣ መሠረት ፣ ከሳሽ ፣ ያቀረበው ፣ ክስ ፣ ውድቅ ፣ መሆን ፣ አለበት ፣ ብሎ ፣ ስለአቀረበው ፣ ክርክር ፣ አንደኛ ፣ የተከሳሽ ፣ ማስረጃ ፣ የተባለውን ፣ አዋጁን ፣ አቅርቦአል ።

ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በአዋጁ ፣ በአንቀጽ ፣ ስድስት ፣ የተጻፈውን ፣ ቃል ፣ ሲመለከተው ፣ “ በቴሌፎን ፣ ሽቦ ፣ አጠገብ ፣ የበቀለ ፣ ወይም ፣ የተጋደመ ፣ ዛፍ ፣ በዚሁ ፣ ሽቦ ፣ አጠገብ ፣ ሆኖ ፣ ወይም ፣ ወድቆ ፣ ለቴሌፎን ፣ ማስተላለፍ ፣ ሥራ ፣ እንቅፋት ፣ ሆኖ ፣ የሚያግድ ፣ ወይም ፣ ማናቸውንም ፣ የቴሌፎን ፣ ሥራ ፣ የሚያሰናክል ፣ ሆኖ ፣ የተገኘ ፣ ወይም ፣ የሚያሰናክሉ ፣ ዛፎች ፣ እንዲወገዱ ፣ ለማድረግ ፣ የፖስታ ፣ ቴሌግራፍ ፣ ቴሌፎን ፣ ሚኒስቴር ፣ አስፈላጊ ፣ መስሎ ፣ ቢታየው ፣ ባለቤቱ ፣ እንዲ

ቀርጥ ፡ ለወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት በጽሕፈት ፡ ያስታውቃል ፤ ባይቀርጥ ፡ ግን፡ የፖስታ ፡ ቴ. ቴ. ሚኒስቴር ፡ ለመቁረጥ ፡ ወይም ፡ እንዲያስቀርጥ ፡ ሥልጣን፡ ተሰጥቶታል ። ”

ተከሳሽ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በዚሁ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ በከሳሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ዛፎች ፡ ለስልኩ ፡ መሥመር ፡ የሚያውኩ ፡ ስለሆኑ ፡ ዛፎቹን ፡ እንዲቆርጡአቸው ፡ ብለው ፡ መጀመርያም ፡ በወረዳው ፡ ግዛት ፡ ቀጥሎም ፡ በአውራጃው ፡ ግዛት ፡ አማካይነት ፡ ያስታወቁአቸው ፡ ለመሆኑ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አልተካደም ።

ከሳሽ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፱ ፡ የተጻፈው ፡ ሕግ ፡ ይደግፈኛል ፡ በማለት ፡ ክርክሩን ፡ አቅርበዋል ፤ እንዲሁም ፡ የሕገ ፡ መንግሥት፡ አንቀጽ ቁጥር ፡ ፵፫ ፡ እና ፡ ፵፬ን ፡ ጠቅሰዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከሳሽ ፡ ይጠቅሙኛል ፡ ብለው ፡ የጠቀሱዋቸው ፡ የሕገ ፡ መንግሥት፡ አንቀጾች ፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡ በተነሳበት፡ ጉዳይ፡ ሊደግፏቸው፡ አይችሉም ። ምክንያቱም ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ተብሎ ፡ የተወሰደባቸው ፡ ወይም ፡ የተወረሰባቸው ፡ ንብረት ፡ የሌለ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ ምክንያት፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በቁጥር ፡ ፻፲፩ ፡ በአንቀጽ ፡ ስድስት ፡ መሠረት፡ የፖስታ ፡ የቴሌግራፍና ፡ ቴሌፎን ፡ ሚኒስቴር ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ ተብለው ፡ በተዘረጉት ፡ የስልክ፡ መስመሮች ፡ እንቅፋት ፡ የሚሆኑ ፡ ማናቸውንም ፡ ዛፎች ፡ ሁሉ ፡ ለመቁረጥ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑን ፡ በመመልከት ፡ ከሳሽ፡ በላስቆረጠው ፡ ዛፎች ፡ ፭ሺ ፡ ብር ፡ መክፈል ፡ ይገባኛል ፡ ብለው ፡ ያቀረቡትን ፡ ክስ ፡ አልተቀበልነውም ። ከሳሽ ፡ ለተከሳሽ ፡ መሥሪያ፡ቤት ፡ ኪሣራ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እንዲከፍሉ ፡ ፈርደናል ። ፍርዱን ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ ያስፈጽም ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Civ. Div. No. 1

H.E. LIJ ARAYA ABEBE v. THE IMPERIAL BOARD OF TELECOMMUNICATIONS OF ETHIOPIA

Civil Case No. 232/56

Constitutional law — Expropriation — Due process — Retroactivity of Rev. Const. — Arts. 43 and 122 Rev. Const. — Art. 6 Proc. No. 114 of 1950.

Property — Compensation for expropriation — Art. 1478 Civ. C.

In an action to recover E$5,000 as compensation for trees felled by the Ministry of Posts, Telegraph and Telephones, pursuant to Art. 6 of Proc. No. 114 of 1950.

Held: The defendant Ministry is not required to pay compensation for felling the trees.

1. Art 1478 Civ. C. deals with the taking of possession of immovable property and does not apply to the felling of trees by a government ministry where the ministry has not removed the trees from the owner's land.

2. The felling of trees which interfere with telephone service, pursuant to Art. 6 of Proc. No. 114 of 1950, does not constitute a deprivation of property without due process of law, even though there is no provision for compensation of the owner, because the enactment of Proc. No. 114 by itself satisfies the requirement of Art. 43, Rev. Const.

3. Art. 6 of Proc. No. 114 of 1950 is not void as contrary to Art. 43 Rev. Const., because it is only legislation enacted subsequent to the promulgation of the Rev. Const. which is null and void if contrary to the Constitution. Art. 122 Rev. Const.

4. The power conferred on the Ministry of Posts, Telegraph and Telephones by Art. 6 of Proc. No. 114 of 1950, is limited to felling trees which interfere with telephone service, and the Ministry may not carry the felled trees away.

Sene 1, 1956 E.C. (June 8, 1964 G.C.); Judges: Dr. W. Buhagiar, Ato Yosef Tekle Michael, Balambaras Alemayu Retta: — In this case the plaintiff is claiming the sum of E$5,000 as compensation for trees felled by the defendant authority.

The defence pleaded by the defendant is that it acted in pursuance of Article 6 of the Maintenance of Telephone Services Proclamation, Proc. No. 114 of 1950, and that no compensation is payable. This Article provides as follows:

"Where in the opinion of the Ministry of Posts, Telegraph and Telephones any trees are doing harm to the telephone services, the Ministry shall, by notice to be delivered to the Woreda Court require the owner to remove such trees. If the person so notified fails to comply the Ministry of Posts, Telegraphs and Telephones shall have authority to have their own personnel fell or lay down the trees."

It is not contested by the plaintiff that a notice under Article 18 was received by him; in fact he replied to such notice stating that if it is decided that the felling of the trees is helpful for the public utility, his right should be reserved in accordance with Article 44 of the Revised Constitution of Ethiopia and under Article 1478 of the Civil Code and that compensation be paid. Article 44 deals with expropriation and probably the plaintiff wanted to refer to Article 43 of the Constitution which provides that no one is to be deprived of property without due process of law. Article 1478 of the Civil Code deals with the taking of possession of immovable property under the general heading of "Expropriation"; this article of the Civil Code is not applicable to the circumstances in the present case.

The question to be decided is whether when the Ministry of Posts, Telegraph and Telephones acts in pursuance of Article 6 of Proc. No. 114 compensation is payable or not for any inconvenience or damage that may be suffered by the owner of the trees. There is no question that the right of the Ministry is limited to felling the trees which are doing harm to the telephone services; the Ministry has no right to carry away the trees felled. It is not contested by the plaintiff that the Ministry felled the trees and left them on the land, although it is alleged by the plainiff that some of the trees were later found missing. Now it is true that, as the plaintiff pointed out, the Constitution provides that no person shall be deprived of property without due process of law, but in the present case the due process of law is the enactment of Proc. No. 114 and this Proclamation does not provide for the payment of compensation for any damage sustained as a result of the felling of trees by the Ministry of Posts, Telegraph and Telephones when the trees were not felled by the owner after notice had been delivered to him in accordance with Article 6 of the Proclamation. The Proclamation is a special measure introduced in the general interest of the public, that is the telephone services.

The plaintiff referred to Article 122 of the Revised Constitution and stated that under this Article any law contrary to the Constitution is null and void;

he argues that the Proclamation, which does not provide for compensation, is contrary to Article 43 of the Constitution. What Article 122 provides is that any *future* legislation, decree, order, etc. that is inconsistent with the provisions of the Constitution is null and void; that Article does not affect any legislation, order etc. that was in force at the time the Constitution was promulgated. The Constitution was promulgated in 1955 and Proc. No. 114 was enacted in 1950.

For the above reasons, this Court holds that no compensation is payable when the Ministry of Posts, Telegraph and Telephones acts in accordance with Article 6 of Proc. No. 114 in felling trees and plaintiff's claim must be dismissed

The plaintiff shall pay E$100 costs to the defedant authority and the Execution Officer shall execute the order for such costs if the plaintiff fails to pay.

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ አንደኛ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎት ።

ማርፐልስ ፡ ሪጅዌይና ፡ ሸሪኮቹ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷ / ፶፷ ፡ ዓ. ም ።

ግብር — በረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸሙ ፡ የሥራ ፡ ውሎች — የአከፋፈሉ ፡ ሁኔታ — ዓመታዊው ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ አወሳሰን — ሥነ ፡ ሥርዓት — የድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱/፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. ፡ አንቀጾች ፡ ፴፮ ፡ (ለ) ፡ እና ፡ ፴፱ ። *

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ የአመልካቹ ፡ ትርፋቸውና ፡ ኪሣራቸው ፡ የሚታወቀው ፡ በዓመት ፡ በመዓቁ ፡ ሳይሆን ፡ በተቋረጠበት ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸም ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተለይ ተው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ ፈጽመው ፡ ሥራውን ፡ ጨርሰው ፡ ካስረከቡ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ በሒሳብ ፡ መዝገባቸው ፡ መሠረት ፡ ወጪው ፡ ታስቦላቸው ፡ የሚደርስባቸውን ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ውሳኔ ፤ — የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ተገልብጦአል ።

፩/ በውሉ ፡ የተመለከተው ፡ ሥራ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ የሚጠይቅ ፡ ከሆነና ፡ ተቋራጩ ፡ ሥራውን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ሁኔታ ፡ አከናውኖ ፡ ሳይገኝ ፡ ቢቀር ፡ የሚያስከትለውን ፡ ወጭና ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ እንደሆነ ፤ ሥራው ፡ ተፈጽሞ ፡ ወጪውና ፡ ኪሣራው ፡ እስኪታ ወቅ ፡ ድረስ ፡ በየዓመቱ ፡ የሚደርስበትን ፡ ግብር ፡ ክፈል ፡ ተብሎ ፡ ሊጠየቅ ፡ አይገባም ።

፪/ በድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. አንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ (ለ) መሠረት ፡ በሠንጠረዥ ፡ (ለ) ፡ ለተመለከተው ፡ ገቢ ፡ በዓመት ፡ የሚከፈል ፡ ሆኖ ፡ የገቢ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ግብሩ ፡ ከተከ ፈለበት ፡ ካመቱ ፡ መጨረሻ ፡ እንስቶ ፡ በሥላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ይሁንና ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ ከሚፈ ጸመው ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ለሚገኘው ፡ ገቢ ፡ ሥራው ፡ ካልተፈጸመ ፡ በቀር ፡ ግብር ፡ ከፋዩ ፡ የሚያገ ኘው ፡ ትርፍ ፡ ተጣርቶ ፡ ካልታወቀ ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆኑም ።

፫/ በድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. እና ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፫ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. አንቀጽ ፡ ፶፰ ፡ መሠረት ፤ ይግባኝ ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ የግብሩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለግብር ፡ ከፋይ ፡ ከተ ሰጠበት ፡ ቀን ፡ እንስቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

---

* በጊዜው ፡ ጸንቶ ፡ የሚገኘው ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፫ ፡ ስለሆነ ፡ የዚሁን ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ (ለ) ፡ እና ፡ ፲፪ ፡ (ሀ) ፡ ተመልከት ። ለመሸጋገሪያ ፡ ጊዜ ፡ ተብ ሎ ፡ ከተተውት ፡ አንዳንድ ፡ አንቀጾች ፡ በስተቀር ፡ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. የገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡

የወጣ ፣ ቍጥር ፣ ፲፱/፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም. ድንጋጌና ፣ የገቢ ፣ ግብር ፣ ስለማስከፈል ፣ በ፲፱፻፶፮ ፣ ዓ-
ጣው ፣ ማሻሻያ ፣ ድንጋጌ ፣ (ቍጥር ፤ ፴፬/፲፱፻፶፮ ዓ. ም. ድንጋጌ) ተሻር ፣ አዋጅ ፣ ቍጥር ፣ ፩፻፩፪
በነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ከወጣበት ፣ ከግንቦት ፣ ፳፰ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፫ ፣ ዓ. ም. ጀምሮ ፣ በዚሁ ፣ አዋጅ ፣ ተተክ
ቷል ። የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪ሺሕ፩፻፫ ፣ በተጨማሪ ፣ ተመልከት ።

ሰኔ ፣ ፩ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፺፮ ፣ ዓ. ም. ። ዳኞች ፦ ዶክተር ፣ ዊሊያም ፣ ቡሐጅያር ፣
አቶ ፣ ዮሴፍ ፣ ተክለ ፣ ሚካኤል ፣ ባላምበራስ ፣ ዓለማየሁ ፣ ፈንታ ።

ይህ ፣ ይግባኝ ፣ የቀረበው ፣ የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ሰሚው ፣ ጉባኤ፣ ሐምሌ ፣ ፲፱
ቀን ፣ ፲፱፻፶፰ ፣ ዓ. ም. በአመልካቹ ፣ ሂሳብ ፣ መዝገብ ፣ መሠረት ፣ ወጪ ፣ ታስቦ
ላቸው ፣ በተጣራው ፣ ትርፋቸው ፣ ድርሻውን ፣ ግብር ፣ እንዲከፍሉ ። በወጪው
ሳይስማሙ ፣ ቀርቶ ፣ ቢያመለክቱ ፣ ለወደፊት ፣ የሚታይላቸው ፣ መሆኑን ፣ መብ
ታቸው ፣ ተጠብቆ ፣ በከፊል ፤ በከፊል ፣ ከሚሠሩት ፣ ሥራ ፣ ላይ ፣ ግብሩን ፣ እንዲ
ከፍሉ ፣ ብሎ ፣ የሰጠውን ፣ ውሳኔ ፣ በመቃወም ፣ የቀረበ ፣ ይግባኝ ፣ ነው ።

አመልካች ፣ ኩባንያ ፣ በጠበቃው ፣ አማካይነት ፣ ነሐሴ ፣ ፲፰ ፣ ቀን ፣ ፲፱ ፣
፶፰ ፣ ዓ ፣ ም ፣ በጻፈው ፣ ማመልከቻ ፣ ሲያመለክት ፤ በሐረር ፣ ጠቅላይ ፣ ግዛት ፣
ከድሬ ፣ ዳዋ ፣ ከተማ ፣ ወደ ፣ ቅዱስ ፣ ገብርኤል ፣ ቁሉቢ ፣ የሚወስደውን ፣ መን
ገድ ፣ ለመሥራት ፣ ከአውራ ፣ ጐዳና ፣ ባለሥልጣን ፣ ጋር ፣ አንድ ፣ የሥራ ፣ ውል ፣
ተቀብለዋል ። አመልካቹ ፣ በተቋራጭነት ፣ የተባለውን ፣ መንገድ ፣ ለመሥራት ፣
ውል ፣ ያለው ፣ ለመሆኑ ፣ በሁለቱ ፣ ተከራካሪ ፣ ወገኖች ፣ አልተካደም ፡ የዚህ
ውል ፣ ግልባጭም ፣ ከመዝገቡ ፣ ተያይዞ ፣ ይገኛል ። በዚሁ ፣ በተጠቀሰው ፣ ውል ፣
የተዘረዘረው ፣ ሥራ ፣ ሁሉ ፣ በከፊል ፣ እንጂ ፣ ሥራው ፣ በሙሉ ፣ ተፈጽሞ ፣ አላስ
ረከበም ። የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ሰሚው ፣ ጉባኤም ፣ ላልተፈጸመ ፣ ሥራ ፣ ትርፉን ፣
ተስተካክሎ ፣ ባልታወቀ ፣ በግምት ፣ የአገር ፣ ውስጥ ፣ ገቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ የጠ
የቀውን ፣ ግብር ፣ ትከፍላላችሁ ፣ ብሎ ፣ የሰጠው ፣ ውሳኔ ፣ በሕግ ፣ ፊት ፣ ተገቢ ፣
ውሳኔ ፣ አይደለም ። ምክንያቱም ፣ ትርፉ ፣ የሚወሰነው ፣ ሥራው ፣ በተፈጸመ ፣
ጊዜ ፣ የአውራ ፣ ጐዳና ፣ ባለሥልጣን ፣ መሐንዲሶች ፣ በሚሰጡት ፣ ውሳኔ ፣ ወይም
ክርክር ፣ የተነሳ ፣ እንደሆነ ፣ በውሉ ፣ ላይ፣በተገለጸው፣ መሠረት ፣ ሽማግሌዎቹ ፣
በሚሰጡት ፣ ብይን ፣ መሠረት ፣ በማድረግ ፣ ስለሆነ ፣ ነው ። የግብር ፣ ይግባኝ ፣
ሰሚው ፣ ጉባኤም ፣ አመልካቹ ፣ ኩባንያ፣ገና ፣ ባልሠሩት ፣ ሥራዎችና ፣
ውጤታቸው ፣ ባልተረጋገጠ ፤ ለወደፊቱ ፣ አስተያየት ፣ ተደርጎ ፣ ሂሳባቸውን ፣
ሊቀንስ ፣ በሚችለው ፣ ሥራ ፣ ግብር ፣ ክፈል ፣ ብሎ ፣ በድንጋጌ ፣ ቁጥር ፣ ፲፱ ፣ በአ
ንቀጽ ፣ ፴፯ ፣ በፊደል ፣ (ለ) ፣ የተጻፈውን ፣ ቃል ፣ የተሳሳተ ፣ ትርጉም ፣ ሰጥቶ ፣
ያደረገው ፣ ውሳኔ ፣ የተሳሳተ ፣ ውሳኔ ፣ ነው ። የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ሰሚው ፣ ጉባ
ኤም ፣ ይህን ፣ ተገቢ ፣ ያልሆነ ፣ ትርጉም ፣ ሲሰጥ ፣ የሕግ ፣ ስሀተት ፣ አድርጐአል ፤
ምክንያቱም ፣ አመልካቹ ፣ ኩባንያ ፣ ትርፉን ፣ ወይም ፣ ኪሣራውን ፣ የሚያው

ቀው ፡ ወይም ፡ የሚታወቀው ፡ ሥራው ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በመጨረሻው ፡ በሚ ገኘው ፡ ውጤት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በአመልካቹና ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አመልካቹ ፡ ለሥራ ፡ ተብሎ ፡ የተቀ በለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደሥራ ፡ ውጤቱ ፡ ሊመልስ ፡ ወይም ፡ ሊቀንስ ፡ እንደሚ ችል ፡ ያመለክታል። አንድ ፡ ሰው ፡ ግብር ፡ የሚከፍለው ፡ ሠርቶ ፡ ከሚያገኘው ፡ ትርፍ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አሁን ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ ገና ፡ ባልተፈጸመ ፡ ሥራና ፡ ትርፉ ፡ ወይም ፡ ኪሣራው ፡ ባልታወቀ ፡ ግብር ፡ ትከፍላለህ ፡ ብሎ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ከሕግ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ስለሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ ውድቅ ፡ አድርጎ ፡ አመልካቹ ፡ ኩባንያ ፡ ሥራውን ፡ ፈጽሞ ፡ አስረክቦ ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ ተከፍሎ ፡ ከሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ግብር ፡ እንዲከ ፍል ፡ እንዲፈረድለት ፡ ብሎ ፡ አመልክቷል ።

እንዲሁም ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በበኩሉ ፡ በነገረ ፡ ፈጁ ፡ አማካይነት ፡ ጥቅ ምት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. በጻፈው ፡ መከላከያ ፡ ሲያመለክት ፤ አመልካቹ ያቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ በድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱/፲፱፻፶፱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፶፰ ፡ መሠ ረት ፡ ከተወሰነው ፡ ከሠላሳ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የከፈተው ፡ መዝገብ ፡ ሁኖ ፡ ቢገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገቡን ፡ መርምሮ ፡ አቤቱታው ፡ በይርጋ ፡ እንዲዘጋለት ፡ ካመ ለከተ ፡ በኋላ ፤ ስለፍሬ ፡ ነገሩ ፡ አመልካቹ ፡ ግብር ፡ እንዲከፍል ፡ የተጠየቀው ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. በሚያገኘው ፡ ትርፍ ፡ ሲሆን ፡ ግብሩም ፡ የተወሰነው ፡ አመ ልካቹ ፡ በአቀረበው ፡ የሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ መዝገብ ፡ መሠረት ፡ ነው ። በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፰/፶ ፡ በአንቀጽ ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ሒሳብ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ዓመት ፡ ሒሳብ ፡ አይተላለፍም ። አመልካቹ ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. ካገኘው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ ተገቢውን ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ ወደፊቱ ፡ ኪሣራ ፡ ይደርስበታል ፡ በማለት ፡ የዓመቱን ፡ ግብር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዓመት፡ ማስተላለፍ ፡ አይቻልም ። ከዚህ ፡ በላይም ፡ በድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ በአንቀጽ ፴፮ ፡ መሠረት ፡ እንዳመልካቹ ፡ የመሰሉት ፡ ኩባንያዎች ፡ ግብራቸውን ፡ በየዓ መቱ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ፡ ምናልባት ፡ ኪሣራ ፡ ቢደርስበትም ፡ በሕጉ ፡ መሠ ረት ፡ ኪሣራ ፡ ለደረሰበት ፡ ዓመት ፡ ግብር ፡ ክፈል ፡ ተብሎ ፡ አይጠየቅም ። ስለ ዚህ ፡ አመልካቹ ፡ ያቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ በነገሩ ፡ ሆነ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ይግባኝ ፡ ስለሆነ ፡ ከኪሣራ ፡ ጋር ፡ እንዲሰናበት ፡ ብሎ ፡ ክርክሩን ፡ አቅርቦአል ።

በአመልካቹና ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ በየበኩላቸው ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተዘረዘረው ፡ ሆኖ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፤ አመልካቹ ፡ የአሁኑን ይግባኝ ፡ ያቀረበው ፡ ሠላሳው ፡ ቀን ፡ የይግባኙ ፡ ጊዜ ፡ ከተላለፈ ፡ ነውና ፡ ይግ ባኙ ፡ መሰናበት ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ ስለአቀረበው ፡ ክርክር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አል ተቀበለውም ። ምክንያቱም ፡ መዝገቡን ፡ መርምሮ ፡ እንደተረዳው ፡ የግብር ፡

ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔውን ፡ የሰጠ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፱ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ. ም. ሆኖ ፡ ግልባጩ ፡ የደረሰው ፡ ሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለሆነ ፡ አመልካቹ ፡ የአሁኑን ፡ ይግባኝ ፡ የከፈተው ፡ በሕጉ ፡ የተወሰነው ፡ ሥላሳው ፡ ቀን ፡ ሳይተላለፍ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ይህ ፡ አሁን ፡ የቀረበው፡ ክርክር፡ የሚያስከትለው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ከማ ናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡ በወጡት ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ዓመ ታት ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ ለሚቀበሉ ፡ የሥራ ፡ ተ ቋራጮች ፡ ስለግብር ፡ አከ ፋፈል ፤ በሕጎች ፡ ውስጥ ፡ ተለይቶ ፡ ያልተገለጸ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በብዙ ፡ ዓመታት ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ የሚቀበሉ ፡ የሥራ ፡ ተቋራጮች ፡ ኩባንያዎች ፡ ትርፋቸውና ፡ ኪሳራቸው ፡ የሚታወቀው ፡ በዓመቱ፡ በዓመቱ ፡ ሳይ ሆን ፡ በተቀበሉት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተለይተው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ ፈጽ መው ፡ ሥራውን ፡ ጨርሰው ፡ በሚያስረክቡበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በየዓመቱ ፡ በሚቀበሉበት ፡ ወይም ፡ በሚያደርጉት ፡ሒሳብ ፡ መሠረት ፡ ግብር ፡ በሚከፈል በት ፡ ዓመት ፡ ትርፋቸው ፡ ወይም ፡ ኪሣራቸው ፡ ሊታወቅ ፡ የማይቻል ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በብዙ ፡ ዓመታት ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ የሥራ ፡ ውሉ ፡ የሚዋ ዋሉ ፡ ኩባንያዎች ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ የሥራው ፡ ውጤት ፡ እየታየ ፡ ለሥራው ፡ ማካሔጃ ፡ የሚሆን ፡ በየጊዜው ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚከፈላቸውና ፤ በዚሁ ፡ በየጊ ዜው ፡ ከሚከፍላቸው ፡ ገንዘብም ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ እየተቀነሰ ፡ የሚሰጣቸው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ተቀንሶ ፡ የሚቀረው ፡ ገንዘብ ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በተሰጠው ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ መሠረት ፤ መሐንዲሶቹ ፡ በሚያደርጉት ፡ ምርመራ ፡ ሥራውን ፡ በትክክል ፡ ሳይሠራ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ለሚያስከት ለው ፡ ጉድለት ፡ እንደገና ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራት ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ይህ ፡ እየተቀነሰ ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በመጥፎ ፡ ዐይነት ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ እንደገና ፡ ለመሥራት ፡ የሚውል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሥራ ፡ ተቋራጩ ፡ በውሉ ፡ በተዘረዘረው ፡ ሁኔታ ፡ ባለመሥራቱ ፡ እንደመቀጫ ፡ ታስቦ ፡ ገቢ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። እንደዚሁ ፡ የመሳሰሉ ፡ ውሎችና ፡ ግዴታዎች ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ ኩባንያዎች ፡ በሚያደርጉት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተዘ ርዝረው ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ። ይኸውም ፡ በብዙ ፡ ዓመት ፡ የሚሠሩ ፡ የአውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚውሉት ፡ ትልልቅ ፡ ቤቶች ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ አዳራሽ ፡ የመሰለ ፤ ወይም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለግሉ ፡ በሚሠራው ፡ ትልልቅ ፡ ቤቶች ፡ የገንዘቡን ፡ አከፋፈል ፡ የሥራውን ፡ ዐይ ነት ፡ ዝርዝር ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ተለይተው ፡ መዘር ዘር ፡ እንዳለበት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንደዚሁ ፡ በመሳሰሉት ፡ ሥራዎች ፡ ግብር ፡

በሚከፈልበት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይሁን ፡ ያህል ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ፡ ተብሎ ፡ ተለይቶ ፡ መወሰን ፡ በጣም ፡ የሚያስቸግር ፡ ነው ። በእንደዚህ ፡ በመሳሰሉት ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ ለመወሰን ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ በሙሉ ፡ ውሉን ፡ ተቀብሎ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ የተዘረዘሩት ፡ ግዴታዎችና ፡ የሥራው ፡ ዐይነት ፡ ሥራው ፡ በሚያልቅበት ፡ ጊዜም ፡ ሁሉንም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አመዛዝኖ ፡ መወሰን ፡ ካልሆነ ፡ በተቀር ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ግብሩን ፡ መወሰን ፡ የሚያዳግት ፡ ነው ።

ከማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለሚከፈል ፡ በወጡት ፡ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ግብር ፡ የሚከፈለው ፡ በዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዓመት ፡ አዛውሮ ፡ ማስከፈል ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ሕጉ ፡ እንደሚያዝ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በሕጎች ፡ ውስጥ ፡ እንደዚሁ ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ግብሩን ፡ መወሰን ፡ የሚያዳግት ፡ ነገር ፡ የለበትም ። ይኸውም ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ተሠርቶ ፡ በሚያልቀው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ደመወዘኛ ፡ በሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ከፕሮፌሽናልና ፡ ቮኬሽናል ፡ ሥራዎች ፡ ለእርሻ ፡ ሥራ ፡ የሚውለው ፡ መሬትና ፡ ከቤት ኪራዮች ፡ ከሚገኘው ፡ ገንዘብ ፤ በእንደዚህ ፡ በመሳሰሉት ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ በዓመቱ ፡ ግብር ፡ መወሰን ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል ። ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ባላቸው ፡ ኩባንያዎች ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሰፈው ፡ በታትቱት ፡ ምክንያት ፡ ግብር ፡ ለመወሰን ፡ የሚያዳግት ፡ ነው ። በአጭሩ ፡ ከማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ አሁን ፡ በአለንበት ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሥልጣኔ ፡ አረማመድና ፡ ግስጋሴ ፡ ስንመለከተው ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ሕጉ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ምክንያቱም ፡ ትልልቅ ፡ ኩባንያዎች ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ግብሩን ፡ ለመወሰን ፡ አዳጋች ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለጀመሩት ፡ ሥራ ፡ እንቅፋትና ፡ የኩባንያዎች ፡ መብትም ፡ አልተጠበቀላቸውም ፡ ለማለት ፡ የሚያበደፍር ፡ ነው ።

አሁን ፡ በክርክሩ ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ አመልካቹ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገቦች ፡ ያለው ፡ ስለሆነ ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤም ፡ በነዚሁ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገቦች ፡ መሠረት ፡ ግብር ፡ እንዲከፍል ፡ ወስኖበታል ። እነዚሁ ፡ መዝገቦችም ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የቁልቢን ፡ መንገድ ፡ ለመሥራት ፡ የተከፈለው ፡ ወይም ፡ አመልካቹ ኩባንያ ፡ የተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ይገልጻሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አመልካቹ ፡ ኩባንያ ፡ የተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ አመልካቹ ፡ ኩባንያ ፡ ከአውራ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ከገባበት ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ የተጣመረና ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። ይኸንኑም ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ጉባኤ ፡ ሊገነዘብለት ፡ ሲገባው ፡ አልተገነዘበለትም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአመልካ

ቹና ፣ በአውራ ፣ ጐዳና ፣ ባለሥልጣን፡ መሥሪያ፡ ቤት ፣ መካከል፡ ያለውን፡ ስንመለከተው ፤ ይህ ፣ በየጊዜው፡ በአመልካቹ፡ ኩባንያ ፣ የሚከፈለው ፣ ገንዘብ፡ በውሉ ፣ ተዘርዝረው ፣ በሚገኙት ፣ ሁኔታዎች ፣ የመጨረሻ ፣ ክፍያ ፣ አለመሆናቸውን ውሉ ፣ በግልጽ ፣ ያስረዳል ። በውሉ ፣ በሁለተኛው ፣ ክፍል ፣ የተጻፈውን ፣ ቃል፡ ስንመለከተው ፤ የአውራ ፣ ጐዳና ፣ ባለሥልጣን ፣ መሐንዲሶች ፣ አስፈላጊ ፣ መስሎ ፣ በታያቸው ፣ በማናቸውም ፣ ጊዜ፡ የሥራውን ፣ ፕላን፡ ለማሻሻል፡ ወይም፡ ለመለወጥ ፣ ሙሉ ፣ መብት ፣ ይሰጣቸዋል ። ምናልባት ፣ በጉዳዩ፡ ሁለት ፣ ወገኖች ሳይስማሙ ፣ ቢቀሩ ፣ ጉዳዩ ፣ በሽምግልና፡ መንገድ ፣ ታይቶ ፣ እንዲወሰን ፣ ያዛቸዋል ። እንዲሁም ፣ በውሉ ፣ በሦስተኛው ፣ ክፍልም ፣ የተጻፈውን ፣ ቃል ፣ ስንመለከተው ፣ ለአውራ ፣ ጐዳና ፣ ባለሥልጣን ፣ ውሉን ፣ ለመሰረዝ ፣ መብት ፣ ይሰጣቸዋል ። ይኸውም ፣ ሥራ ፣ ተቋራጭ ፣ በሚያደርገው ፣ ጉድለትና ፣ በውሉ ፣ መሠረት ፣ ሥራውን ፣ በተወሰነው ፣ ጊዜ፡ ጨርሶ ፣ ሳያስረክብ ፣ የቀረ ፣ እንደሆነ ፣ ኪሣራ ፣ መክፈል ፣ ያለበት ፣ መሆኑን ፣ ይገልጻል ። ቀጥሎም ፣ በውሉ ፣ በአራተኛው ፣ ክፍል ፣ የተጻፈውን ፣ ቃልም፡ ስንመለከተው ፣ አመልካቹ ፣ ኩባንያ ፣ ለሠራው ፣ ሥራ ፣ በየመጨረሻ ፣ ወር ፣ በክፊል ፣ ገንዘብ ፣ የሚከፈለው ፣ መሆኑን ፣ ያመለክታል ። በውሉ ፣ በስድስተኛው ፣ ክፍል ፣ እንደተመለከተው ፣ አመልካቹ፡ ኩባንያ ፣ የሠራው ፣ ሥራ ፣ ደስ ፣ በሚያሰኝ ፣ ሁኔታ ፣ የተሠራ ፣ መሆኑን ፣ በመሐንዲስ ፣ ከተመሰከረ ፣ በኋላ ፣ ለሚያስከትለው ፣ ወጭና ፣ ኪሣራ ፣ ለመክፈል ፣ ግዴታ ፣ የገባ ፣ መሆኑን ፣ ውሉ ፣ ይገልጻል ።

ስለዚሀ ፣ በውሉ ፣ ቃል ፣ መሠረት ፣ ለአመልካቹ ፣ ኩባንያ ፣ የሚከፈለው ፣ ማናቸውም ፣ ክፍያ ፣ ሁሉ ፣ ለጊዜው ፣ እንደተከፈለው ፣ የሚቆጠር ፣ ነው ። ምክንያቱም ፣ ይህ ፣ አመልካቹ ፣ በየጊዜው ፣ የተከፈለው ፣ ገንዘብ ፣ የሠራው ፣ ሥራ ፣ በመሐንዲስ ፣ ተመርምሮ ፣ ጉድለት ፣ የተገኘበት ፣ እንደሆነ ፣ ገንዘቡን ፣ መልሶ ፣ ለመክፈል ፣ ወይም ፣ በራሱ ፣ ገንዘብ ፣ ሥራውን፡ መልሶ፡ ለመሥራት፡ ግዴታ ፣ የገባ ፣ ስለሆነ ፣ ነው ። በዚህ ፣ ሁሉ ፣ ምክንያት ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ እንደ ፣ ተገለጸው ፣ በዓመቱ፡ለጊዜው ፣ እየተባለ ፣ በተሰጠው ፣ ገንዘብ ፣ ላይ ፣ ያገኘው ፣ ጥቅሙ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ እንደሆነ ፣ ግብሩን ፣ ለመወሰን ፣ የሚያስቸግር ፣ ነው ።

ፍርድ ፣ ቤቱም ፣ አሁን ፣ በአለው ፣ ሕግ ፣ ስለ ፣ ግብር፡ አከፋፈል ፣ ለአጋጠመው ፣ አስቸጋሪ፡ ሁኔታ ፣ ግብሩ ፣ በሁለት፡ መንገድ ፣ ለማስከፈል ፣ የቀና ፣ ሆኖ፡ ያገኘዋል ።

ሀ/ አንደኛው ፣ መንገድ፡ ለረጅም ፣ ጊዜ፡ የሚሰጡት ፣ ማናቸውም ፣ ውሎች፡ ሁሉ ፣ እንደ ፣ አንድ ፣ ሥራ ፣ በብዙ ፣ ዓመታት ፣ የሚሠራ ፣ ሥራ ፣ አድርጎ ፣ መቆጠርና፡ ሥራው ፣ በአለቀ ፣ ጊዜ ፣ በሚገኘው ፣ ትርፍ ፣ ላይ፡ የሚከፈለውን ፣ ግብር፡ መወሰን ፣ ነው ። እንደዚሁ ፣ የመሰለ ፣ መንገድ ፣ የተወሰደ ፣ እንደሆነ ፣ በኮንት

ራቱ ፣ መሠረት ፡ በጠቅላላው ፣ ያገኘው ፣ ትርፍና ፡ የደረሰበት ፡ ኪሣራ ፡ ቢችክ ክልና ፣ በግልጽ ፣ ለመረዳት ፡ እንደሚቻል ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ለ/ ሁለተኛው ፡ መንገድ ፡ ደግሞ ፡ በኮንትራቱ ፡ መሠረት ፣ ባጀቱ ፡ በሚ ዘጋበት ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ከጠቅላላው ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ፡በጊዜ፡ ውስጥ ፡ ከሥራው፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደተሠራ ፡ ታውቆ ፡ ወይም ፡ ተገምቶ ፣ በዚህ፣ በአንድ ፡ ዓመት ፣ በተሠራው ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ የተገኘው ፡ ጠቅላላ ፡ ትርፍ ፣ ወይም ፡ የደረሰበት ፣ ኪሣራ ፤ ወይም ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚደርስበት ፡ ኪሣራ ፣ ሁሉ ንም ፣ አንድ ፡ ላይ ፡ አመዛዝኖ ፣ የዓመቱን ፡ ግብር ፡ መወሰን ፡ ነው ።

በፊደል ፣ ሀ/ የተመለከተው ፣ ጉዳይ ፣ ለአፈጻጸሙ ፡ የቀና ፡ ሲሆን ፡ በፊደል፡ ለ/ የተመለከተው ፣ ጉዳይ ፣ ግን ፣ ለአፈጻጸሙ ፣ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፣ ነው ። በተ ለይ፣ በመንግሥት ፣ ገቢ ፣ ላይ ፣ ሆነ ፡ በግብር ፡ ከፋዮችም ፡ ከባድ ፣ እንቅፋት ፡ የሚ ያስከትል ፣ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፣ አሁን ፣ የቀረበው ፣ የግብር ፣ አከፋፈል ፤ በተለይም ፡ ከማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፣ ስለማስከፈል ፣ የወጡትን ፡ አዋጆች ፣ ስንመለከታቸው ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለሚፈጸሙ ፡ ሥራዎች ፡ የግብር፡አከፋፈላቸው፣ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ተለይቶ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ፍርድ ፣ ቤቱ ፡ በጉዳዩ ፡ ሳይቸገርበት ፡ አል ቀረም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፣ እንደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ የግብር ፡ ባለሥልጣኖች፡ በሚሰጡት ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይነካ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረት፡ማናቸውም፣ ግብር ፡ በረጅም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጸም ፡ በሚሠሩት ፡ ኩባንያዎች ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ መወሰን ፡ የሚገባው ፡ በውሉ ፡ መሠረት፡ ሥራቸውን፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፣ መሆን ፡ አለበት ።

ስለዚህ ፣ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሰፊው ፣ በተዘረዘረው ፣ ምክንያት ፣ ሁሉ ፣ የግ ብር ፣ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ በሐምሌ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፣ ዓ. ም. የሰጠ ውን ፣ ውሳኔ ፡ ውድቅ ፡ አድርጎ ፡ ግብሩ ፡ የሚከፈለው ፣ በአመልካቹ ፡ ኩባንያና ፣ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፣ ቤት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ሥራ ፣ ሲፈጸም ፣ አመልካቹ ፡ ግብሩን ፣ መክፈል ፡ አለበት ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ። ከዚህ ፣ በላይ ፣ መልስ ፡ ሰጭው ፣ ለአመልካቹ ፣ ዳኝነት ፣ በደረሰኝ ፡ ኪሣራ ፣ አንድ ፣ መቶ ፡ ብር ፡ እንዲከፍል ፡ ፈርደናል ።

HIGH COURT

Addis Ababa, Civ. Div. No. 1

MARPL 'S RIDGWAY & PARTNERS LTD. v. THE II 'LAND REVENUE DEPARTMENT

Civil Case No. 406/55

Civil procedure — Controlling law.

*Taxation — Long-term contracts — Conditional payments — Annual tax assessment — Procedure — Arts. 36 (c) and 55 Dec. No. 19 of 1956; Art. 55 Proc. No. 173 of 1961.**

On appeal from a decision of the Tax Appeal Commission, which held that the taxpayer's income tax liability should be determined from the payments and expenses shown on its books of account, even though the payments were received under a long-term contract and, because the payments were conditional, the taxpayer's profit on the contract could not definitely be determined until the contract was completed.

Held: Decision reversed.

1. Where a contract is to be performed over more than a single tax year and payments made during its performance are only conditional until it is completed, no income tax is due with respect to such payments until the conditions attached to them have been resolved and the taxpayer's profit on the contract can be definitely determined.

2. The requirement that income chargeable under Schedule C be declared annually, within 30 days of the end of the tax year, Art. 36(c) Dec. No. 19 of 1956, applies where assessable income can be determined each year, but it does not apply to income derived from long-term contracts, where the taxpayer's income cannot be definitely determined until the contract's completion.

3. An appeal from a decision of the Tax Appeal Commission must be filed within 30 days after the delivery of the notification of assessment of the tax to the taxpayer. Art. 55, Art. 55, Dec. No. 19, 1956; Art. 55, Proc. No. 173 of 1961.

4. As to matters of procedure, Proc. No. 173 of 1961 replaces Dec. No. 19 of 1956, where the proceedings take place subsequent to publication of Proc. No. 173, even though the proceedings concern a tax year prior to such publication.

Sene 1, 1956 E.C. (June 8, 1964 G.C.); Judges: Dr. W. Buhagiar, Ato Yosef Tekle Michael, Balambaras Alemayu Retta:— This is an appeal against a decision given by the Tax Appeal Commission on July 26, 1963, holding that the appellant is to pay tax according to his books of account on the income made by the appellant, subject to deduction of expenses incurred in the work producing the income; the right of the appellant was reserved to submit an

* See, for present law, Arts. 55(b) and 12(a) Proc No. 173 of 1961. Except for special provisions for a transitional period, Proc. No. 173 of 1961 expressly rescinded and replaced Dec. No. 19 of 1956 and Dec. No. 34 of 1959 as of the date of publication of Proc. No. 173 in the Negarit Gazeta, which was June 2, 1961.

appeal eventually if and when he does not agree with the allowance for expenses.

The appellant company has undertaken, under a contract with the Imperial Highway Authority, the construction of the Colubi Road in Harar Province. It is not contested that such a contract exists, which contains certain terms and provisions as indicated in he contract copy which has been submitted to the Court. One of the terms of the contract is that the work was to be completed within 36 months from the date of the execution of the contract, that is, not later han October 1963. and that for certain reasons the work was delayed until 1963; in other words the contract between the appellant company and the Imperial Highway Authority was not a contract to be performed wholly within one assessable year of income but was a long term contract.

The year of assessment in the present case is the year 1960.

The ground of appeal is that the Tax Appeal Commission was wrong in law in holding that the appellant company should pay taxes on unfinished work and on supposed profits when the work undertaken had not been completed and the final result not known; it is submitted on behalf of the appellant that the profits depended on the final determination of the Engineers of the Imperial Highway Authority or on awards to be given by arbitrators in case of disputes, as provided in the contract. It is submitted on behalf of the appellant company that the Tax Appeal Commission was wrong in law in basing its decision on the provisions of Article 36(c) of the Income Tax Decree of 1956 (Decree No. 19 published in the Negarit Gazeta No. 1 of the 16th Year), Decree No. 19 of 1956, which lays down that declaration of income shall be made in respect of income chargeable under Schedule C annually within 30 days from the end of the year for which the tax is due.

In his reply the respondent raised the question whether the appeal of the appellant was lodged in time. There is no ground in this plea because both under Article 55 of Decree No. 19 of 1956 and under Article 55 of Proc. No. 173 of 1961 (and the latter Proclamation applies on this point as the matter is one of procedure) the appeal is to be lodged within thirty days of the delivery of the notification of assessment of the tax to the taxpayer; in the present case the notification is dated July 30, 1963 (as shown in the photocopy submitted by the appellant) and the appeal to this Court was lodged within thirty days of that date.

On the merits, the respondent submitted that under the law the accounts of one year cannot be transferred to another year and that therefore the appellant cannot be relieved from the payment of tax for the year 1960 because of an expectation of a loss in the future; and companies like the appellant are to pay tax every year as prescribed by Article 36(c) of Decree No. 19; the respondent further submitted that if the appellant meets a loss in the

future, as feared, the appellant shall be free from payment of tax. The appellant, it has been submitted, has been taxed on profits derived in the year 1960 and therefore the appeal is groundless.

The difficulty in this case arises from the fact that the income tax legislation makes no provision for long term contracts, that is, contracts in which the final total loss or profit on works undertaken cannot be determined within the accounting period or the year of assessment; the profit or loss can only be determined at the end of the contract and subject to the special terms and conditions in the contract. In such contracts, called long term contracts, there is normally a provision under which payments are made periodically as the work is progressing, with a deduction of a percentage to cover any contingency for bad work in the performance of the work which is not according to specifications, and subject to checking by engineers regarding the quality of the work which may be rejected as not being in accordance with the specifications and consequently to refund of any money that may have been advanced during the progress of the work and to claim for damages that may arise as a result of bad work. Such conditions and terms are normal in long term contracts like contracts for road building or the construction of public buildings like a city hall or of private buildings like a huge block of flats. In these cases, it is impossible to determine what is the assessable income in one year, as the profits do not depend on the money that has been advanced in one accountable year and deducting the expenses incurred in that year; in view of the terms and conditions of the contract, any money paid to the contractor is only a conditional payment on which there may or there may not be a profit; to determine the profit or loss that may result, the whole contract for the whole period with the terms and conditions of the contract must be takes into consideration.

It is true that the present income tax legislation provides for the making of declarations of income annually and for the payment of tax annually; and this is clearly intended to apply to cases where it is possible to determine the assessable income annually as in the case of any ordinary business or in the case of persons receiving a salary or in the case of a person who exercises a profession or in the case of a landowner whose income is derived from rents; but for reasons which have been set out above, the existing provisions cannot apply to long term contracts. In other words, in this respect the income tax legislation is behind the fast economic progress that is developing in Ethiopia where work of great enterprises is being undertaken which cannot be completed during the period of one financial year or year of assessment.

In the present case the appellant has been keeping regular books of account and the Tax Appeal Commission has decided that the appellant must pay tax according to such books. These books naturally show the payments that have been made in respect of part of the road of Colubi built during the year 1960, but such payments must be considered in connection with the terms

and conditions of the contract. This the Commission has failed to do. If we look at the contract, we find various provisions which indicate that the payments made cannot in any sense be considered as final payments. Thus we find in the contract the following terms: clause 2 of the General Provisions of the Contract enables the engineer at any time to make changes in the drawings and/or specifications of the contract, and in case the parties fail to agree about the adjustments necessary, the matter is to be submitted to arbitration; clause 3 of the same General Provisions provides for termination of the contract in case of default and for damages for delay in the performance of the contract; clause 4 provides for partial payments at the end of each month for work completed and materials delivered, subject always to the right of inspection and examination and test by the engineer as provided in clause 8, paragraph (c) of which specifies that in case work is found defective or nonconforming in any material respect the contractor is to defray all expenses for the inspection and examination and of satisfactory reconstruction.

It is clear that under such terms any payment made in the period of any one year can be only a conditional payment, that is, any such payment is subject to any deduction or defraying of costs that may prove necessary after inspection and examination by the engineer for the work performed and materials supplied during that year, and the result of the inspection and examination by the engineer is not necessarily known within the same year. For these reasons it is impossible, as stated above, to reach a conclusion as to the assessable income for the year during which the conditional payments are made.

In such circumstances there are, in the opinion of this Court, two possible solutions to the problem created by the present state of the income tax legislation, namely —

(a) to consider long term contracts one task job over a period of years and to assess the taxable income after the whole job is completed; it is then possible to have a clear picture of the profits made and losses sustained on the whole contract; or

(b) to attribute to any particular accumulating period (year of assessment) such proportion of the entire profit or loss which has resulted, or which it is estimated will result, from the complete performance of the contract as is properly attributable to that accounting period having regard to the extent to which the contract was performed in that period.

The solution at paragraph (b) may not be of easy application in practice and may have unfavourable results to the general revenue and to the taxpayer except and unless the whole matter of assessment during the accounting periods is revised at the end of the contract. Taking all the above into consideration and particularly this present state of income tax legislation, which makes

no provisions for long term contracts, this Court is of the opinion that, without prejudice to the submission to the income tax authorities of yearly declarations, the assessable income cannot be determined except at the end of the contract and that therefore taxable income should be assessed at the end of the contract and tax is payable at the end of the contract.

For the above reasons this Court reverses the decision of the Tax Appeal Commission and holds that the taxable income is to be assessed at the end of the contract between the appellant company and the Imperial Highway Authority and tax is payable accordingly.

The respondent shall pay the appellant court fees of this appeal according to receipt and costs of E$100.

ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ የአስተዳደር ፡ ችሎት ።

ከሳሽ ፡ አቶ ፡ እገሌ ፤ ተከሳሽ ፡ የፖስታ ፡ ቴ. ቴ. ሚኒስቴር ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፶፱/፶፯ ፡ ዓ. ም. ።

የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ—«ሕግ» የሚለው ፡ አነጋገር—የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ — ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፫ ።

የአስተዳደር ፡ ሕግ—ነፃ ፡ በሆነ ፡ ወገን ፡ የመዳኘት ፡ መብት ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት — በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ።

ተከሳሹ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደፊት ፡ የከሳሽን ፡ ደመወዝ ፡ ከመቁረጥ ፡ እንዲታገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥለት ዘንድ ፡ የዚሁ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነው ፡ ከሳሽ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ ።

ውሳኔ ፤ —በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቷል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመጀመሪያ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተከሳሹ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለማክበሩና፡ ትእዛዙንም በመቃወት ፡ የከሳሽን ፡ ደመወዝ ፡ ከመቁረጥ ፡ ስላልታገደ ፡ ይህንኑ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የመጀመሪያ፡ ትእዛዝ ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲያከብር ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠው ፤ እስከአሁንም ፡ ከከሳሽ ፡ ደመወዝ፡ላይ የተቆረጠው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስለት ፡ ከሳሽ ፡ በድጋሚ ፡ አመለከተ ።

ውሳኔ ፤ —በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቷል ።

፩/ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሕይወቱን ፡ ነፃነቱን ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ አያጣም ። (ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፫ ።)

፪ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሱና ፡ በሠራተኞቹ ፡ መሐል ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ ራሱ ፡ ፈራጅ የሰጠውንም ፡ ውሳኔ ፡ ራሱ ፡ የሚያስፈጽም ፡ ከሆነ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በሕግ ፡ የተሰጠው ፡ መብቱ፡ ተጠብቆለትል ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ።

፫/ አንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከሠራተኞቹ ፡ አንዱን ፡ ባለዕዳ ፡ በማድረግ ፡ የሠራተኛው ፡ የወር፡ ደመወዝ በክፊል ፡ እየተቆረጠ ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ገቢ ፡ እንዲሆን ፡ ትእዛዝ ፡ ቢያስተላልፍ ፡ የሠራተኛው፡ ባለዕዳነት ፡ በፍርድ ፡ ተረጋግጦ ፡ ያልተወሰነ ፡ ስለሆነ ፡ ትእዛዙ ፡ ውድቅ ፡ ነው ።

፬/ የመንግሥት ፡ ሚኒስቴር ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸሙ ፡ ሥርዓት፡ ሚኒስቴሩ ፡ ባንክ ፡ ካለው ፡ ሒሳብ ፡ እንሥቶ ፡ ለተፈረደለት ፡ ሰው ፡ በመክፈል ፡ ነው ።

ሰኔ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ። ዳኞች ፤ - አቶ ፡ በላቸው ፡ ኢምራት ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ሙሴ ፡ ይሕደጐ ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ጌታሁን ።

መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ የሚከተለውን ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰጥተናል ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሕይወቱን ፡ ነፃነቱን ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ዓለ ፡ ሕግ ፡ አያጣም ። ከአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ንብረት ፡ ለመውሰድ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በሕግ ፡ ከሶ ፡ መብቱን ፡ በፍርድ ፡ አረጋግጦ ፡ ማስፈጸም ፡ አለበት ፡ እንጂ ፤ እርሱ ፡ ከሳሽ ፡ እርሱ ፡ ፈራጅ ፡ እርሱ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ መሆን ፡ አይገባውም ።

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ የአመልካችን ፡ ሲሶ ፡ ደሞዝ ፡ መቁረጡን ፡ አልካደም ። በአመልካች ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ አስተዳደር ፡ በሚፈቅድልኝ ፡ ሥልጣኔ ፡ ተገልግዬአለሁ ፡ ይላል ።

የአስተዳደር ፡ ውሳኔ ፡ የሰውን ፡ ንብረት ፡ ለመንፈግ ፡ ወይም ፡ ለመቀነስ ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ቢኖር ፡ አዘውትሮ ፡ የሚሠራበት ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ሰው የሠራበትን ፡ ደሞዝ ፡ በአስተዳደር ፡ ውሳኔ ፡ በየጊዜው ፡ ለመቁረጥ ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ዘንድ ፡ የሚቻል ፡ አፈጻጸም ፡ ሆኖ ፡ አይታየንም ።

ተከሳሽ ፡ ሠራተኞቹ ፡ አጎደሉ ፡ አጠፉ ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ የሚፈርድ ፡ ከሆነ ፤ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣንና ፡ የሰዎች ፡ መብት ፡ ተጠብቋል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

ስለዚህ ፡ ለወደፊቱ ፡ ተከሳሽ ፡ የአመልካችን ፡ ደሞዝ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያደርግ ፡ እንደነበረው ፡ እንዳይቆርጥ ፡ ስንል ፡ አዘናል ።

እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ተቆረጠብኝ ፡ ስለሚሉት ፡ ገንዘብ ፡ አመልካች ፡ ደንበኛ ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ ከፍተው ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ።

አመልካች ፡ ይህን ፡ መዝገብ ፡ ለመክፈት ፡ ያወጡትን ፡ ገንዘብ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ይክፈላቸው ። እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ የፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ ያስፈጽም ።

መስከረም ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ። ዳኞች ፤ አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ደሳለኝ ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ሙሴ ፡ ይሕደጐ ፡ አቶ ፡ ደነቀ ፡ አሸናፊ ።

የፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ጽ/ ቤት ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. በቁ. ፻፷ሕ፴፯/፷፯ ፡ የጻፈውና ፡ አመልካቹም ፡ መስከረም ፡ ፯/፷፯ ፡ ዓ. ም. የጻፉት ፡ ማመልከቻ ፡ ቀርቦ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዟል ። ቁጥሩ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ እንዲታዘዝለት ፡ የጠየቀው ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰኔ ፡ ፳፯/፷፯ ፡ ዓ. ም. በሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ነገረፈጁ ፡ ቀርቦ ፡ ቢጠየቅ ፡ ገንዘብ ፡ አላመጣሁም ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አመልክተናል ፤ ማገጃ ፡ እስከናመጣ ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጠኝ ፡ ሲል

ጠይቋል ። ከባሹ ፡ ባንክ ፡ ከአለው ፡ ሂሳብ ፡ ላይ ፡ ተቀንሶ ፡ ይሰጠኝ ፡ ብለው ፡ ስላመለከቱ ፡ በጠየቁት ፡ መሠረት ፡ ለማስፈጸም ፡ እንድንችል ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠን ፡ የሚል ፡ ነው ። አመልካቹም ፡ በዚሁ ፡ መዝገብ ፡ ያወጣሁትን ፡ ፻፷፮ ፡ ብር ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲከፍለኝ ፡ ቢጠየቅ ፡ አልከፈለኝም ፡ ከባንክ ፡ ሂሳቡ ፡ እንዲከፍለኝ ፡ እንዲታዘዝልኝ ፤ ደመወዜም ፡ ወደፊት ፡ እንዳይያዝብኝ ፡ ክቡር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠልኝን ፡ ትእዛዝ ፡ በመጋፋትና ፡ በእምቢተኛነት ፡ አሁንም ፡ ደመወዜ ፡ በየወሩ ፡ ከመቆረጥ ፡ አልታገደም ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰጠልኝ ፡ ወዲህ ፡ ፩፻፹ ፡ ብር ፡ ከደመወዜ ፡ ላይ ፡ ስለተያዘብኝ ፡ በድጋሚ ፡ ይህን ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ። ክቡር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ በትህትና ፡ የምለምነው ፡ ካሁን፡ ቀደም፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መንግሥት ፡ የፖስታ፡ ቴ. ቴ. ሚኒስቴር ፡ ያላከበረው ፡ በመሆኑና፡ እኔም፡ ከትእዛዝ፡ በኋላ ፡ ከባድ፡ በደል፡ የደረሰብኝ ፡ ስለሆነ ፡ ካሁን፡ በፊት ፡ ለተቆረጠብኝና ፡ ለወደፊትም ፡ ለሚቆረጥብኝ፡ ደመወዜ፡ ከባንክ ፡ ሂሣባቸው ፡ ላይ ፡ እየተያዘ ፡ እንዲከፈለኝ ፡ ቀዋሚ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥልኝ ፡ ብለው ፡ አመልክተዋል ። ከትእዛዝ ፡ ወዲህ ፡ ደመወዛቸው ፡ ለመቆረጡ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ታዘው ፡ ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ. ም. በቁ ፡ 09449/122/30 ፡ ለሂሣብ ፡ ክፍል ፡ ዋና ፡ ዲሬክተር ፡ ሲጻፍ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ግልባጭ ፡ አቅርበዋል ። ፎቶ ፡ ኮፒውም ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዟል ። እንዲሁም ፡ ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀንና ፡ ነሐሴ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ. ም. የተጻፈ ፡ ሁለት ፡ ደረሰኝ ፡ በጠቅላላ ፡ ፩፻፹ ፡ ብር ፡ የተከፈለበት ፡ አቅርበዋል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

<u>ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ</u> ፤ የአመልካቹ ፡ የአቶ ፡ ታምራት ፡ እስጢፋኖስ ፡ ደመወዝ ፡ እንዳይያዝ ፡ ሰኔ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዋለው ፡ ችሎት ፡ ታዞ፡ መዝገቡ ፡ ሲዘጋ ፡ በዚሁ ፡ አቤቱታ ፡ ምክንያት ፡ ለዳኝነት ፡ የከፈሉትን ፡ ገንዘብ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲከፍል ፡ ለመታዘዙ ፡ መዝገቡ ፡ ያስረዳል ። መልስ ፡ ሰጭው ፡ ግን ፡ እንዲከፍለው ፡ የታዘዘበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ፈቃደኛ ፡ ካለመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ወዲህ ፡ ከአመልካቹ ፡ ደመወዝ ፡ እየተቀነሰ ፡ ተመላሽ ፡ እንዲሆን ፡ በሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ ደመወዛቸው ፡ ላይ ፡ ፩፻፹ ፡ ብር ፡ ተመላሽ ፡ ለመሆኑ ፡ ደረሰኙ ፡ ቀርቦልን ፡ ተመልክተነዋል ። ፍርድ ፡ አስፈጻሚም ፡ ላፈጻጸሙ ፡ የገጠመውን ፡ ችግር ፡ ገልጾ ፡ ባንክ ፡ ካለው ፡ ሒሳብ ፡ እንዲከፍል ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥልኝ ፡ ብሎ ፡ አመልክቷል ። አመልካቹም ፡ ከትእዛዝ ፡ ወዲህ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በደል ፡ የደረሰባቸው ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ ከደመወዛቸው ፡ ተቆርጦ ፡ ተመላሽ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ባንክ ፡ ካለው ፡ ሂሣብ ፡ እንዲከፈላቸው ፤ ለወደፊትም ፡ እንዳይቆረጥባቸው ፡ ቀዋሚ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥላቸው ፡ አመልክተዋል ። በቀድሞው ፡ ትእዛዝ ፡ አመ

ልካቸ ፣ የከፈሉት ፣ ዳኝነትና ፣ ከፍርድ ፣ ቤት ፣ ትእዛዝ ፣ ወዲህ ፣ የተቀረጠባቸው ፣ ፬፻፹ ፣ ብር ፣ (አራት ፣ መቶ ፣ ሰማንያ ፣ ብር) ባንክ ፣ ካለው ፣ የመልስ ፣ ሰጭው ፣ ሂሣብ ፣ ለአመልካቹ ፣ እንዲከፈልና ፣ ካሁን ፣ ቀደም ፣ እንደታዘዘው ፣ ወደፊትም ፣ ቢሆን ፣ ተከሰው ፣ ሳይፈረድባቸው ፣ ከደመወዛቸው ፣ እንዳይቆረጥ ፣ በድጋሚ ፣ አዘናል ። ትእዛዙ ፣ ሳይከበር ፣ ቀርቶ ፣ ቢቆረጥባቸው ፣ ግን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ትእዛዙን ፣ ተቃውሞ ፣ በሚያዘው ፣ ባለሥልጣን ፣ ላይ ፣ ሌላ ፣ እርምጃ ፣ የሚወሰድ ፣ መሆኑን ፣ ከማስጠንቀቅ ፣ ጋር ፣ አዘናል ።

እንደ ፣ ትእዛዙ ፣ እንዲያስፈጽም ፣ ግልባጩ ፣ ለፍርድ ፣ አስፈጻሚ ፣ ይተላለፍ ፣ ብለናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Admin. Div.

X v. THE MINISTRY OF POSTS, TELEPHONE AND TELEGRAPH

Civil Case No. 292/56

Constitutional law — Due process — Administrative proceedings — Art. 43 Rev. Const.

Administrative law — Right to independent adjudication.

Civil procedure — Execution of judgments against the government.

In an action by an employee of the defendant Ministry to obtain an order restraining the Ministry from making further deductions from his pay.

Held: Order granted.

The plaintiff subsequently again petitioned the Court, alleging that the defendant had refused to comply with the Court's first order and seeking a further order directing the defendant to comply with the first order and also to repay the deductions already made.

Held: Order granted.

1. No one shall be deprived of life, liberty or property without due process of law. Art. 43 Rev. Const.

2. An administrative proceeding in which a government ministry adjudicates its own claim and then executes the resulting order does not afford the opposing party due process of law.

3. An administrative order of a government ministry which withholds a part of the pay of one of its employees in order to satisfy a claim which it has against the employee, the claim not having been independently adjudicated, is not sustainable at law.

4. A money judgment against a government ministry may be executed by levying on the Ministry's bank account.

Sene 26, 1956 E.C. (July 3, 1964 G.C.): Judges: Ato Belatchew Asrat, Ato Wolde Mussie Yihdego, Ato Makonnen Getahun:— After a study of the document, we have given the following order. No one shall be deprived of his life, liberty or property without due process of law. If one party claims that another owes him something, he has the right to bring an action against him in court, but no one can be party, judge and executor in one and the same case. It is very rarely that an administrative decision deprives a person of his property. But we are not of the opinion that an administrative decision which deprived a person of his monthly salary would be sustainable at law.

If every time a defendant claimed that his employees were at fault, he were to be the sole judge of such claims, then it cannot be said that the power of the courts and the rights of individuals are safeguarded.

Therefore, the defendant is hereby ordered not to deduct from the pay of the plaintiff hereafter.

The plaintiff can institute a suit against the defendant to recover the pay which has already been deducted.

Defendant is hereby ordered to pay the plaintiff's expenses in the filing of this suit.

The execution officer is hereby ordered to execute this order accordingly.

Maskaram 27, 1957 E.C. (October 7, 1964 G.C.): Judges: Ato Tefferi Dessalegn, Ato Wolde Mussie Yihdego, Ato Deneke Ashenafi:— A letter dated August 5, 1964, Ref. No. 3036/56, from the Execution Office, and a statement of claim dated September 17, 1964, from the plaintiff, are attached to the file. In the letter mentioned above, the Execution Officer stated that while his office was executing the order given on July 3, 1964, the advocate for the defendant, after receiving the execution letter, asked for continuance on the ground that he had applied to the Ministry of Justice for an injunction against the order of the Court. Plaintiff, on the other hand, asked that he should be paid from the defendant's bank account. The Execution Office then requested an additional order to carry out the execution according to the request of the plaintiff. In his statement of claim mentioned above, the plaintiff alleged that the defendant had refused to pay the sum of E$125 — plaintiff's expenses incurred in the opening of this file. He also alleged that the defendant had failed to abide by the order of the High Court and had continued to deduct from the plaintiff's monthly pay, which deduction now amounted to E$480. Plaintiff therefore respectfully requested the High Court for an order against the defendant, the Ministry of Posts, Telephone and Telegraph, for the payment of the plaintiff's expenses and deducted salary and also that it be re-trained from making further deductions from the plaintiff's pay. The plaintiff was asked to introduce evidence supporting his allegation that a deduction from his pay was made after the order of the High Court was given. He then introduced a letter dated July 25, 1964, Ref. No. 09499/122/30 and addressed to the accounting department, a copy of which was given to the plaintiff. He also introduced two receipts dated August 6 and September 3, 1964, for the payment of the sum of E$480.

Additional Order

The file shows that following the order given on July 3, to the effect that there should be no more deductions from X's pay, the defendant Ministry was ordered to pay the plaintiff's expenses incurred in the opening of the file. Defendant not only failed to pay the expenses but also failed to abide by the order of the Court, and the sum of E$480 was deducted from the plaintiff's pay after the said order was given. Stating the difficulty it faced in executing the order, the Execution Office has asked for an additional order to carry out the execution upon defendant's bank account. Plaintiff also has prayed the Court

for an additional order to restrain the defendant from making further deductions from the plaintiff's salary and also for a payment of the E$480 and court expenses from defendant's bank account.

Therefore, it is hereby ordered that plaintiff be paid from the defendant's bank account, the sum of E$480 deducted from his salary and also his expenses incurred in obtaining the previous order. It is also ordered, as was provided in the previous order, that there shall be no further deduction from the plaintiff's salary unless such deduction is ordered by a court following a proper filing of a suit. Failure to abide by this order and a further deduction from the plaintiff's salary would entail grave consequences for the authorities concerned. A copy of this order shall be sent to the Execution Office to carry out the execution according to the given order.

ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አስመራ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎት ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አቶ ፡ እገሌ ፤ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ታቦቱ ፡ ገብሬ ፡ ትንሣኤ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፶፯/፶፰ ዓ. ም ።

የልጅ ፡ ማሳደጊያ — አባትነትን ፡ ስለማወቅ — የልጅነት ፡ ሁኔታ — የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯፻፹፩ ፡ ፯፻፺ ፡ ፯፻፺፰ ፡ (፩) ።

መልስ ፡ ሰጭ ፡ ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ ልጅ ፡ ወልጃለሁና ፡ ልጅነቱ፡ እንዲታወቅልኝ ፡ ለልጅ ፡ ማሳደጊያም ፡ ቀለብ ፡ እንዲከፍለኝ ፡ በማለት ፡ ክስ ፡ አቅርባ ፡ የከረን ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ልጁ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ላይ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ የከረን ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ስለአጸደቀው ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ቀረበ ።

<u>ውሳኔ</u> — ይግባኙ ፡ ተፈቅዶለሏል ።

፩ ፤ በጽሑፍ ፡ ካልሆነ ፡ በቃል ፡ ወይም፡ በዝምታ ፡ የሚደረግ ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፡ ሁኔታ፡ ምንም ዓይነት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ አይሰጠውም ።

፪ ፤ በሴትኛ ፡ አዳሪነት ፡ ወንዶች ፡ እየተቀበለች፡ ከምትኖር ፡ ሴት፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ ከእናታቸው ፡ በስተቀር ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ የላቸውም ።

ኅዳር ፡ ፳ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ። ዳኞች ፤ – ሻምበል፡ ኢያሱ፡ ገብሬ ፡ ሐዋርያት ፡ ደጃዝማች ፡ ኢድሪስ ፡ ልጃም ፡ ፊታውራሪ ፡ ሱሌማን ፡ ኢልዲን ። በዚህ ፡ ነገር ፡ መልስ ፡ ሰጪዋ ፡ ወይዘሮ ፡ ታቦቱ፡ ገብሬ ፡ ትንሣኤ፡ ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ ልጅ ፡ ወልጃለሁ ፡ በማለት ፡ በከረን ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ አቅርባ ፡ ልጅነቱ ፡ እንዲታወቅላትና ፡ እንዲሁም ፡ ለልጅዋ፡ ቀለብ፡ እንዲከፍላት፡ ክስ፡ አቅርባ ፤ የከረን ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልጁ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ በመስጠቱና ፡ እንዲሁም ፡ የከረን ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዱን ፡ ስላጸደቀው ፡ ፍርዱን ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ።

የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ ይሠራበት ፡ በነበረው ፡ መሠረት ፡ ለፍርዳቸው ፡ መሠረት ፡ ያደረጉት ፡ የእናቲቱን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የከረን ፡ አውራጃ፡ፍርድ፡ቤት፡በሰጠው፡የፍርድ ፡ ሐተታ፡ይግባኝ፡ባዩ ፡ የሕጻኑ፡ መወለድና ፡ ልጅነቱን፡ተቀብሎታል፡ በማለት ፡ ነው፡፡በውሳኔውም፡ ላይ ፡ መልስ ፡

ሰጪዋ ፡ ልጅ ፡ ወልጃለሁ ፡ ብላ ፡ ለጻፈችለት ፡ የተደጋገመ ፡ ደብዳቤ ፡ መልስ ፡ ባለመስጠቱ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ፡ ልጅነቱን፡ ተቀብሎታል፡ በማለት ፡ የፍትሐ፡ ብሔር፡ አንቀጾች ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፺፯/፯፻፺፰ ፡ ጠቅሶ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቶአል ። የአውራጃው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የጠቀሳቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔ ር ፡ አንቀጾች ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ የላቸውም ።

ምክንያቱም ፡ የልጅ ፡ መቀበል ፡ ሁኔታ ፡ በግልጽና ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ እንደሚገባ ፡ የፍትሐ ፡ ብሐ ር ፡ አንቀጽ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፺፰ ፡ (፩) አጥብቆ ፡ ያዛል ። ከዚህ ሁኔታ ፡ በስተቀር ፡ የልጅነት ፡ ማወቅ ፡ ሁኔታ ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ መቀበል ፡ ሕጉ ፡ አይፈቅድም ።

ከዚህ ፡ በስተቀር ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ሐተታ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ልጅነቱን ፡ እንደተቀበለው ፡ ይገልጻል ። ይህ ፡ ማስረጃ ፡ በዚህ፡ጉዳይ አልቀረበም ። የልጅነት ፡ ማወቅ ፡ ሁኔታ ፡ ማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ አባት ፡ የሕጻኑን ፡ መወለድ ፡ ተቀብሎ ፡ ጐረቤት ፡ ሆኑ ፡ በአካባቢ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ልጁ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የሚያምንበት ፡ ሁኔታ፡ሲኖር፡ብቻ፡በሰው፡ምስክር ፡ ማስረዳት ፡ ይቻላል ።

ይህ ፡ ክርክር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተገለጸው ፡ ሕጋዊያን ፡ ሁኔታዎች ፡ የተለየ ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶአል ።

በመሠረቱ ፡ መልስ ፡ ሰጪዋ ፡ በሴተኛ ፡ አዳሪነት ፡ ተግባር ፡ ወንዶች ፡ እየተቀበለች ፡ የምትኖር ፡ ለመሆንዋ ፡ ራስዋ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመግለጽዋም ፡ በላይ ፡ ከአሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሌላ ፡ ወንዶች ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ የምትገናኝ ፡ ለመሆንዋ ፡ ራስዋ ፡ ገልጻለች ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ከምትገኝ ፡ ሴት ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ ከእናታቸው ፡ በስተቀር ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ እንደማይኖራቸው ፡ በፍትሐ ፡ ብሐ ር ፡ ሕግ፡ በቁጥር፡ ፯፻፹፩ (፫) ፡ ተደንግጓል ። እንዲሁም፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ በ፯፻፹፩ ፡ (፩) ከጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ በግብረ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በሆኑ ፡ ዓይነት ፡ በአንድ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ መካከል፡ የሚደረጉ፡ ግንኙነቶች ፡ በሕግ፡ ፊት ፡ ውጤት ፡ የሌላቸው ፡ ለመሆኑ ፡ ሕጉ ፡ ይናገራል ። ስለዚህ ፡ አባት ፡ ልጅነቱን ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተቀበለ ፡ በስተቀር ፡ ክሱ ፡ ውጤት ፡ ስለማይኖረው ፡ በቁጥር ፡ ፯፻፺፰ ፡ (፩) የተደነገገ፡ ሲሆን ፡ እንዲሁም፡ በአንቀጽ፡ ፯፻፹፩፡ (፩) (፫) እንደተገለጸው ፡ ከጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ውጪ ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ ሕጋዊ፡ መብት ፡ እንደሌላቸው፡ ተቆጥሮ ፡ ከእናታቸው ፡ ወገን ፡ በስተቀር ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መተሳሰር ፡ እንደሌላቸው ፡ ሲያመለክት ፡ የመልስ ፡ ሰጪዋ ፡ ክስ ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ መፍረድ ፡ ሕጉን ፡ የሚያፋልስ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ ክብርና ፡ የማህበራዊን ፡ ኑሮ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲጠበቅ ፤ ምንዝርና ፡ ዝሙት ፡ እንዲጠፉ ፤ ሕግ ፡ አውጪው ፡ በጥንቃቄ ፡ የመሠረታቸው ፡ ሕጋውያን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመሆናቸው ፡ ዳኞች ፡ በጥንቃቄ ፡ በማስተዋል ፡ ሕጉን ፡ እንዲተረጉሙት ፡ የሚያሻ ፡ ከመሆኑ ፡ በስተቀር ፡ በችሎታ ፡ ሲታለፍ ፡ የማይገባው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፯፻፵ ፡ መሠረት ፡ ልጁ ፡ የተወለደው ፡ እናቲቱ ፡ የተጠለፈች ፡ ወይም ፡ በመገደድ ፡ ወይም ፡ በኃይል ፡ ከተገናኘው ፡ ሰው ፡ ፍሬ ፡ የተወለደ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ በሰው ፡ ምስክር ፡ ማስረዳት ፡ ካለመቻሉም ፡ በላይ ፡ ክርክር ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ ሳይሆን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በመሆኑ ፡ የመልስ ፡ ሰጪዋ ፡ ክስ ፡ የሕግ ፡ ውጤት ፡ ሊኖረው ፡ ባለመቻሉ ፡ በመሠረቱ ፡ ውድቅ ፡ አድርገን ፡ የከረን ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ሽረነዋል ። ፍርዱ ፡ መሻሩን ፡ እንዲያውቀው ፡ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግልባጩ ፡ ይተላለፍላቸው ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ዛሬ ፡ ኅዳር ፡ ፳/፶፯ ፡ ዓ.ም. ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ባሉበት ፡ ተሰጠ።

HIGH COURT

Asmara, Civ. Div.

X v. TABOTU GEBRE TINSAYE

Civil Appeal No. 167/56

*Family law — Paternal filiation — Acknowledgment of paternity — Possession of Status — Arts. 721 and 748 Civ. C.**

On appeal from a judgment of the Awraja Court allowing an action for paternal filiation and a claim for maintenance by a woman in respect of her child.

***Held*: Appeal allowed.**

1. Acknowledgment of paternity may only be made in writing and no tacit admission of paternity will suffice to establish that fact.

2. No legal bond exists between a child and its father where the child is the outcome of an act of prostitution.

Hedar 8, 1957 E.C. (Nov. 17, 1964 G.C.); Judges: Captain Eyassu Gebre Hawariat, Dejazmatch Idris Lejam, Fitawrari Suleiman Eldieen:— This is an appeal against the judgment of the Keren Awraja Court which affirmed the decision of the Woreda Court whereby the present appellant was declared to be the father of the respondent's child and adjudged to pay a maintenance allowance.

The finding of the lower court was based solely on the mother's testimony under oath in accordance with the custom then existing.

The Awraja Court in its judgment laboured on the assumption that the appellant had acknowledged the paternity of the child. It held that by virtue of Articles 807 and 808 of the Civil Code the constant failure of the appellant to reply to the several letters written to him by the respondent revealing that a son has been born to him is a tacit acceptance of paternity. We are, however, of the opinion that the Articles so cited are irrelevant to this case.

The mandatory provisions of Article 748(1) of the Civil Code require that acknowledgment of paternity be clear and in writing. Any acknowledgment short of that, such as a tacit or oral acknowledgment, is legally ineffective.

In addition, the Awraja Court was of the opinion that the child had the status of being the appellant's child. Filiation by possession of the status of

* See also Art. 740 Civ. C.

child is based on evidence that the father has treated the child as his own and that the child is regarded as the child of the man by his neighbours and society. Possession of status must therefore be proved by witnesses.

The present dispute involves a very different legal issue.

The respondent has revealed to this Court that she earns her livelihood by prostitution and has admitted that she receives other men for the purpose of having sexual intercourse with them. It has been well established that by virtue of Article 721(3) of the Civil Code children born out of such relations have a juridical bond only with their mother. So also does Sub-article 1 of the same Article provide that relations established between a man and woman ouside of wedlock or outside of an irregular union shall have no juridical effect attached to them. In view of the provisions of Article 748(1), which clearly states that an acknowledgment of paternity has no effect unless it is made in writing, and also having regard to Article 721, which expressly provides that no legal effect shall be attached to parenthood outside of wedlock or outside of irregular union, to hold that the respondent's claim has a legal effect attached to it is in our opinion to violate the clear provisions of the Code.

The intention of the legislature in enacting this law was to restore dignity to the family and preserve the social order, to discourage adultery and prostitution, and it is the judges' duty to carefully interpret the law in light of this policy, a policy of relatively high importance that cannot be ignored or lightly passed over.

An action for declaration of paternity could only be instituted where the mother has been a victim of abduction, rape or duress and the child was conceived as a result. For all these reasons, we hold that filiation could not be proved by producing witnesses. Neither should a dispute be adjudicated in accordance with customary law but in accordance with the Civil Code. We, therefore, dismiss the claim of the respondent and quash the Awraja Court's judgment. We order that a copy of this judgment be sent to the Awraja Court to notify them of the reversal.

Delivered on this 17th day of November, 1964, in the presence of both parties.

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፤ የአስተዳደር ፡ ችሎት ።

ቢርናዶኒ ፡ ጁሴፔ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፯/፶፮ ፡ ዓ ፡ ም

የአስተዳደር ፡ ሕግ—በይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ ክርክሮችን ፡ የሚሰሙ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍሎች—ሥነ ፡ ሥርዓት—የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ጉባኤ ።

ቀረጥ—የአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት—የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፫/፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ፡ አንቀጽ ፡ ፶፯ ።

የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረውን ፡ ግብር ፡ ሲቀንስ በይግባኝ ፡ ባዩና ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ መ/ ቤት ፡ መካከል ፡ ያልቀረበለትን ፡ ጥያቄ ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ፡ይግባኝ ፡ ባይ ፡ መቀጫ ፡ ይከፍላል ፡ ሲል ፡ የሰጠውን ፡ ብይን ፡ በመቃወም ፡ ይሀ ፡ ይግባኝ ፡ ቀረበ ።

ውሳኔ ፤—መቀጫ ፡ ይከፍላል ፡ ሲል ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ተሽሮ ግብሩ ፡ ይቀንስለታል ፡ ሲል ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ጸድቆአል ።

፩ ፤ ተገቢውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ ሳይመረኰዝ ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ ውሳኔ፡አግባብ ፡ እንዳለመሆኑ ፡ መጠን ፡ ውሳኔው ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

፪ ፤ በይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ ክርክሮችን ፡ የሚሰሙ ፡ የአስተዳደር፡ ክፍሎች ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው፡ ወገን ይግባኝ ፡ ባላለበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም ።

፫ ፤ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ፡ በሚሰጠው ፡ በውሳኔው ፡ ሐተታ ፡ ላይ ፡ መቀጫ ፡ በግን ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ሊጨመር ፡ እንደቻለ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፤ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ ፡ መቀጫ ፡ ጨምሮ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፫ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፯ ፡ መሠረት ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

የካቲት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ዳኞች ፤— አቶ ፡ ተፈራ ፡ ደሳለኝ ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ ሙሴ ፡ ይሕድጎ ፡ አቶ ፡ አሳየኸኝ ፡ አዳል ።

መዝገቡን ፡ መርምረን ፡ እንደተረዳነው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በውሳኔው ፡ ቅር ፡ የተሰኘበትን ፡ ሲያስረዳ ፤

፩ኛ/ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ጉባኤ፡ በይግባኝ፡ ባዩና፡ በመልስ፡ ሰጭው ፡ መ/ቤት ፡ መካከል ፡ ያልቀረበለትን ፡ ጥያቄ ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ መቀጫ ፡ ፫ሺ፬፻፲፱ ፷፰ ፡ ብር ፡ ጨምሮ ፡ ይከፍላል ፡ ሲል ፡ የሰጠው ፡ ብይን ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ነው ።

ምክንቱም ፡ መ/ቤቱ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ግብር ፡ ሲጠይቅ ፡ ከላይ ፡ የተገለጸውን ፡ ፫ሺ፬፻፲፱፷፰ ፡ ጨምሮ ፡ አልጠየቀም ።

፪ኛ/ ፣ ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ መቀጫውን ፡ ጨምሮ ፡ ክፈል ፡ ተብልኩ ፡ በማለት፡ ይግባኝ ፡ አላቀረበም ።

ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ኮሚቴ ፡ ባልቀረበለት ፡ ይግባኝ ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲከፈል ፡ ያዘዘው ፡ በማይገባ ፡ ስለሆነ ፡ ውሳኔው ፡ እንዲሠረዝልኝ ፡ ብሏል ።

የመልስ ፡ ሰጪው ፡ መ/ቤት ፡ ነገረ ፡ ፈጅም፡ ሲመልስ፡ በመጀመሪያ፡ ጊዜ ፡ በአመልካቹ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው፡ ግብር፡ ፳፪ሺ፩፻፲፰፡ ብር ፡ ሲሆን ፤ አመልካቹ ፡ በውሳኔው ፡ ባለመስማማቱ ፡ የተነሳ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ኮሚቴ ፡ በማቅረቡ ፡ ምክንያት ፡ ፲ሺ፩፻፶፯ ፡ ብር ፡ ተቀንሶለታል ። ጉባኤው ፡ ለመቀነስም ፡ ሆነ ፡ ለመጨመር ፡ በአዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፯ ፡ በሚያዝለት ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ቢጨመርም ፡ አመልካቹ ፡ ሊከራከር ፡ አይገባውም ፡ በሚል ፡ መንገድ ፡ መቃወሚያውን ፡ በሰፊው ፡ ጽፎአል ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጨአገር፡ ውስጥ፡ ገቢ ፡ መ/ቤት ፡ በኩል ፡ ስላለው፡ የግብር ፡ አከፋፈል ፡ ክርክር ፡ መወሰን ፡ የሚገባው ፡ ግብር ፡ በዛ ፡ አነስ ፡ በማለት፡ ሳይሆን ፡ የሕግ ፡ አሠራር ፡ የተዛነፈ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ በሚገባ ፡ ተረድቷል ።

አመልካቹ ፡ ሕግ ፡ ተዛነፈብኝ ፡ የሚለው ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ኮሚቴ ፡ የግብርን ፡ አከፋፈል ፡ ለመቀነስም ፡ ሆነ ፡ ለመጨመር ፡ ሥልጣን ፡ ቢኖረውም ፤ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መ/ቤት ፡ ባለሥልጣን፡ የተመደበው፡ ግብር ፡ አንሶአልና፡ በግብር ፡ ከፋዩ ፡ ላይ ፡ ይጨመርበት ፡ ሳይል ፤ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ቢመጣ ፡ ለመጨመር ፡ ወይም ፡ የተመደበው፡ ግብር ፡ በዝቶብኛልና ፡ ይቀነስልኝ ፡ የሚል ፡ አቤት ፡ ባይ ፡ ቢመጣ ፤ ጥቅሙንና፡ ጉዳቱን፡ አመዛዝኖ ፡ በሚረዳው ፡ መጠን ፡ ለመቀነስ ፡ እንጂ ፤ ይግባኝ ፡ ባልተባለበት ፡ ነገር ፡ ለመወሰን፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ በማለት፡ ነው ።

ክርክሩ ፡ በሕጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚደገፍ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል። ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ የውሳኔው ፡ አሠራር ፡ በፕሮሲጀር ፡ መመሥረት ፡ ይኖርበታል ።

በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ በይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ ክርክሮችን ፡ የሚሰሙ ፡ ክፍሎች ፡ ይግባኝ ፡ በተባለበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ተገቢውን ፡ እርምጃ ፡ በመውሰድ ፡ ይግባኙን ፡ ይመረምራሉ ፡ እንጂ ፡ ይግባኝ ፡ ባልተባለበት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ይግባኝ ፡ ሳይል ፡ አቤቱ ፡ በተቀመጠ ፡ ሰው ፡ አዲስ ፡ መብት ፡ የሚያስገኝ ፡ ብይን ፡ ሊሰጡለት ፡ አይገባም ። እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፡ አሠራር ፡ ፈጽመው ፡ ቢገኙ ፡ ግን ፡ አሠራራቸው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ያልተከተለ ፡ ስለሚሆን ፡ በሕግ ፡ ሊሻሻል ፡ የሚገባ ፡ ይሆናል ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኝ ፡ ያለው ፡ በዚህ፡ ዐይነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጽም ብኛልና ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ውሳኔው ፡ ይለወጥልኝ ፡ በማለት ፡ እንደሆነ ፡ ተረ ድተናል ።

በመሠረቱ ፡ አመልካቹ ፡ የተጠየቀው ፡ የ፶፬ ፡ ዓ. ም. ግብር ፡ ፳፱ሺ.ሕ፩፻፷ ፡ ብር ፡ (ሃያ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ብር) ፡ እንዲከፍል ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ግብር ፡ መጠየቂያ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ እንደሌለበት ፡ በቁጥ. ፫፻፸፬/፶፮ ፡ የተጻፈው ፡ ማስታወቂያ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቦአል ።

የአሁን ፡ አመልካችም ፡ በይግባኝ፡ ያመለከተው ፡ ግብሩ ፡ በዛብኝ ፡ በማለት፡ እንጂ ፡ መቃወሚያ ፡ ተጣለብኝ ፡ በማለት ፡ አይደለም ።

ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ኮሚቴ ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መ/ ቤት ፡ የተመደበው ፡ የግብር ፡ ልክ፡መብዛቱን ፡ አምኖበት ፡ ሂሳቡን ፡ በመቀነስ ፡ ፲፫ሺ.ሕ፰፻፸፬ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ እንዲከፍል፡ሲወስን ፤ በሌላው፡በኩል ፡ ይግባኝ ፡ ባይ፡በሌለበት ፡ መቃወሚያ ፡ ይከፍላል ፡ ሲል ፡ ከመጀመሪያው፡ሒሳብ ፡ ውጭ ፡ በተጨማሪ ፡ ማዘዙን ፡ ተመል ክተናል ።

ግን ፡ የመቃወሚያውን ፡ ገንዘብ ፡ በማን ፡ ጥያቄ ፡ ሊጨመር ፡ እንደቻለ ፡ በው ሳኔው ፡ ሐተታ ፡ ላይ ፡ ያልጠቀሰ ፡ ስለሆነ ፡ አሠራሩ ፡ የይግባኙን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ ያልተከተለ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

ከፍ ፡ ብለን ፡ እንደገለጽነው ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ መ/ቤት ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በይግባኝ ፡ መቃወሚያ ፡ መልስ ፡ ሲሰጥ ፤ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ኮሚቴ ፡ ግብርን ፡ ለመጨመርም፡ ሆነ ፡ ለመቀነስ ፡ ሌላም ፡ ተስማሚ፡ የመሰለውን ፡ ውሳኔ፡ ለመስ ጠት ፡ በአዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፶፯ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ፡ ብሏል ።

በውነቱ ፡ የሕጉን ፡ ትርጓሜ ፡ በፍትሕ ፡ ሚዛን ፡ ሲከተሉት ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ኮሚቴ ፡ ይግባኝ፡ በሚባልበት፡ ሁኔታ፡ ላይ፡ ለመወሰን ፡ የተፈቀደለትን፡ ሥልጣን ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ ይግባኝ፡ ያልተባለበትንና ፡ ጥያቄ ፡ ያልቀረበበትን ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ አመንጭቶ ፡ በፈለገው ፡ ዐይነት ፡ እንዲወሰን ፡ አይፈቅድም ።

እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፡ ተግባር ፡ የሚከተል ፡ ከሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ኮሚቴ ባልተባለና ፡ አሠራሩም ፡ የግብር ፡ መዳቢን ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ አሠራር ፡ ለመ ሥራት ፡ ተደራቢ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ በሕጉ ፡ ተገልጾ ፡ በተነገረለት ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ኮሚቴ ፡ በ፳/፲/፶፯ ፡ ባደረገው ፡ ስብሰባ ፡ በሰ ጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ እንዲጨመር ፡ በማለት ፡ ይግባኝ ፡ ያለ ፡ ሳይኖር ፡ በራሱ ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ በአመልካቹ ፡ ላይ፡ ፫ሺ.ሕ፯፻፰፰ ፡ ብር ፡ መቃወሚያ ፡ ጨምሮ ፡ የወሰነው ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ ስላልታየንና ፡ ሕጉንም ፡ የሚቃወም ፡ ስለሆነ ፡ በመቃወሚያው፡ላይ ፡ የወሰደውን ፡ እርምጃ ፡ ውድቅ ፡ አድርገን ፡ በዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ተቀብለናል ።

የመቀመጫው ፡ ሒሳብ ፡ ተቀናሽ ፡ ሆና ፡ በዋናው ፡ ግብር ፡ ላይ ፡ ያገር ፡ ውስጥ፡ ገቢ ፡ መ/ቤት ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀ ፡ ስለሆነ ፡ እንዲያውቀው ፡ ግል ባጩ ፡ ይተላለፍለት ፡ ብለን ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብተናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Admin. Div.

BERNADONI GIUSSEPE V. THE INLAND REVENUE DEPARTMENT

Civil Appeal No. 457/56

Administrative law — Appellate administrative tribunals — Procedure — Tax Appeal Commission.

Taxation — Administrative procedure — Art. 56 Proc. No. 173 of 1961.

On appeal from a decision of the Tax Appeal Commission, which reduced the petitioner's tax assessment but also, on its own motion, imposed a fine on him.

Held: The decision with respect to the fine is quashed; the decision with respect to the assessment is sustained.

1. An administrative decision not based on proper procedure is contrary to the law and therefore void.

2. Appellate administrative tribunals are not empowered to decide matters not raised by either party.

3. Where the decision of the Tax Appeal Commission fails to show that either the Inland Revenue Department or the taxpayer had requested that a fine be imposed on the taxpayer, the decision of the Commission imposing such a fine is void. Art. 56 Proc. No. 173 of 1961.

Yekatit 15, 1957 E.C. (February 22, 1965 G.C.); Judges: Ato Tefferi Desalegn, Ato Wolde Mussie Yihdego, Ato Asayegn Adal:— Our examination of the file reveals that the appellant alleged:-

1. The decision of the Tax Appeal Commission that the appellant should pay a fine of E$3,768 was erroneous and not sustainable at law, because it was based on neither the allegations of the appellant nor on those of the respondent. In other words, the respondent did not ask that the appellant be required to pay an additional E$3,768 with the tax.

2. The appellant did not appeal to the Commission on the ground that he was requested to pay a fine.

Therefore, the appellent prayed that the Court quash the decision of the Tax Appeal Commission as regards the sum of E$3,768.

Respondent's advocate alleged in his statement of defence that according to the first assessment the appellant was directed to pay the sum of E$29,160.

But because appellant disagreed with that assessment, he appealed to the Tax Appeal Commission, whereupon the Commission reduced the assessment to E$22,608 including the E$3,768 fine. Since the Tax Appeal Commission took this step within its power given under Article 56 of Proc. No. 173 of 1961, respondent argued that appellant cannot contest that power of the Commission.

The High Court is aware that its duty on appeal is not to enter into the merits of the assessment but to decide on questions of law which arise on appeal.

Appellant alleged that his appeal was based on a question of law in that, while it was true that the Tax Appeal Commission has the power to vary the assessment, this power can be exercised only when either the Inland Revenue Department or the other party appeals for an increase or a reduction of the assessment. Otherwise, the Tax Appeal Commission has no power to decide points which are not appealed.

We have found appellant's allegation to be sustainable at law as a matter of procedure.

Any decision should be based on proper procedure.

Departments having appellate jurisdiction should consider and decide only matters which are appealed. They should not decide matters which are not appealed and thereby confer a right upon a party who has stayed at home without taking any appeal to them. If they do confer such a right, they are not following proper procedure and therefore their decision should be reviewed according to the law.

We have understood that the appellant appealed from the decision of the Commission and sought to have its decision reversed on the ground that it had followed an improper procedure in reaching its decision.

Basically, appellant was required to pay the sum of E$29,160 in tax, for the year 1962. That there was no fine attached to that request was shown by notice No. 374/46.

The appellant also appealed to the Commission on the ground that he did not agree with the assessment, but he did not appeal on the ground that he was fined.

From the facts we have gathered, the Tax Appeal Commission, being aware that the Inland Revenue Department was wrong in its assessment, has on the one hand reduced the amount to E$18,840, but on the other hand it has fined the appellant without any appeal from either party.

But since it was not stated in the decision on whose request the fine was imposed, the decision is found to be based on improper procedure.

As we have previously stated, respondent's advocate in his statement of defence alleged that Article 56 of Proc. No. 173 of 1961 has empowered the Tax Appeal Commission to reduce, increase or annul an assessment and make further consequential decision thereon.

In reality, the law if followed in its proper sense simply explains the authority of the Commission to decide on points of appeal, and it does not give the Commission the power to raise new points and give decision on them.

If the Commission could do this, it should not have been called an Appeal Commission but rather a Commission of first instance, whose duty would have been defined by the law as a first instance assessor.

Therefore, the decision of the Tax Appeal Commission delivered on June 15, 1964, as regards the fine in the sum of E$3,768 was not based on any point raised on appeal. It was based simply on the Commission's own view of the case. We think that it is therefore contrary to the law and thus void. Hence the decision of the Commission as regards the fine is quashed and the rest of the decision as regards the assessment sustained.

Since, after a reduction of the fine, the Inland Revenue Department's right to collect the tax is reserved, it shall receive a copy of this judgment to be notified of the decision.

Delivered on February 22, 1965.

ከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፤

አዲስ ፣ አበባ ፣ የአስተዳደር ፣ ችሎት ።

ሙሉጌታ ፣ አየለ ፣ ይግባኝ ፣ ባይ ፤ የአገር ፣ ውስጥ ፣ ገቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ መልስ ፣ ሰጭ ።

የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ነገር ፣ ቁጥር ፣ ፩፻፳፫/፶፮ ፣ ዓ. ም. ።

የአስተዳደር ፣ ሕግ — በይግባኝ ፣ ደረጃ ፣ ክርክርን ፣ የሚሰሙ ፣ የአስተዳደር፣ ክፍሎች፣ ሥነ ፣ ሥርዓት — የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ጉባኤ ።

ግብር — በግምት ፣ ስለመወሰን — የአስተዳደር ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት — የአዋጅ ፣ ቁጥር ፣ ፻፸፫ ፣ ፲፱፻፶፩ ፣ ዓ. ም. ፣ አንቀጽ ፣ ፭ ፣ እና ፣ ፶፯ ። *

የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ጉባኤ ፣ የአገር ፣ ውስጥ ፣ ገቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ በይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ላይ ፣ በግምት እንዲከፍሉ ፣ የወሰነባቸውን ፣ ግብር ፣ ከማድናቱ ፣ በላይ፣ በተጨማሪ፣ በገዛ ፣ ፈቃዱ ፣ የግብሩን ፣ ገንዘብ፣ ጨምር ፣ ይከፍላሉ ፣ ሲል ፣ የሰጠውን ፣ ውሳኔ ፣ በመቃወም ፣ ይህ ፣ ይግባኝ ፣ ቀረበ ።

ውሳኔ ፤ — የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ጉባኤ ፣ ግብሩን ፣ ቀጥሎ ፣ ይከፍላሉ ፣ ሲል ፣ የሰጠው ፣ ውሳኔ ፣ ተደም ስሶ ፣ ይግባኝ ፣ ባይ ፣ የአገር ፣ ውጥ ፣ ገቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ በገመተው ፣ መሠረት ፣ እንዲከፍሉ ፣ ተጠ ይቀዋል ።

፩/ የአገር ፣ ውስጥ ፣ ገቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ የግብር ፣ ከፋይ ፣ የሒሳብ ፣ መዝገብ ፣ በትክክል ፣ የተ ሠራ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ካላመነበት ፣ ግብሩን ፣ በግምት ፣ እንዲመድብ ፣ አዋጅ ፣ ቁጥር ፣ ፩፻፸፫ ፤ አንቀጽ ፣ ፭ ሥልጣን ፣ ሰጥቶታል ።

፪/ የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ጉባኤ ፣ በአገር ፣ ውስጥ ፣ ገቢ ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ ወይም ፣ በግብር ፣ ከፋይ ፣ ጥያቄ ፣ መሠረት ፣ ግብሩን ፣ ለመቀነስ ፣ ወይም ፣ ለመጨመር ፣ እንዲያውም ፣ ግብር ፣ ከፋይ ፣ ምንም ፣ ገቢ ፣ አላገኘሁም ፣ ብሎ ፣ ቢያመለክት ፣ ገቢ ፣ አለማግኘቱን፣ ተረድቶ ፣ ግብሩን ፣ እንዲፍቅለት ፣ አዋጅ ቁጥር ፣ ፩፻፸፫ ፣ አንቀጽ ፣ ፶፯ ፣ ሥልጣን ፣ ሰጥቶታል ።

፫/ የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ሰሚው ፣ ጉባኤ ፣ በገዛ ፣ ፈቃዱ ፣ ግብር ፣ ለመጨመር ፣ አይችልም ። የአዋጅ ቁጥር ፣ ፩፻፸፫ ፣ ፲፱፻፶፩ ፣ ዓ. ም. አንቀጽ ፣ ፶፯ ።

ግንቦት ፣ ፲፮ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ። ዳኞች ፤ አቶ ፣ ተፈሪ፣ ደግለኝ ፣ አቶ ፣ ወልደ ፣ ሙሴ ፣ ይሕደጐ ፣ አቶ ፣ አሳየኸኝ ፣ አዳል ። የይግባኝ ፣ ባይ ፣ ጠበቃ ፣ ያገር ፣ ውስጥ ፣ ገቢ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ አለአንዳች ፣ ምክንያት፣ የሒሳብ ፣ መዝገባቸውን ፣ በከፊል ፣ ሲቀበሉ ፣ ከፊሉንም፣ ነቅፎታል ። የሽያጩን፣ ዝርዝር፣ ከመዝገባቸው ፣ ወስዶ ፣ በመሰለው ፣ የወሰነባቸው ፣ በመሆኑ ፣ ለግብር ፣ ይግባኝ ፣ ጉባኤ ፣ በይግባኝ ፣

---

* ሲደግፍ ፣ መነሻ ፣ የሆነው ፣ የግብር ፣ ይግባኝ ፣ ሰሚ ፣ ጉባኤ ፣ የሰጠው ፣ ውሳኔ ፣ ገጽ ፫፻፴፱ ፣ ላይ ፣ ይገኛል ።

ቀርበው ፡ ነበር ። ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ክፍል ፡ በሸያጭ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሒሳብ ፡ ሲቀበሉ ፡ ሌላውን ፡ አልተቀበሉም ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኝ ፡ ያለበትና ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ያልጠየቀውን ፡ ጨምሮ ፡ የፈረደለት ፡ በመሆኑ ፡ ይህን ፡ ይግባኝ ፡ ለዚህ ፡ ለተከበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ተገዷል ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ያገኙትን፡ ጥቅም፡ የማያሳይ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ አላቸው ። ይግባኙም ፡ የቀረበው ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁ. ፲፫ ፡ በ፲፱፻፶፪፡ ዓ. ም. በቁ. ፶፫፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ እገልጻለሁ ። ከላይ ፡ እንደገለጽኩት ፡ ክቡር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያደርግልኝ ፡ የምለምነው ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በሕግ ፡ እንዲታገድልኝና ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ባለው ፡ መዝገብና ፡ አገኘሁ ፡ ባለው ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ግብሩን ፡ እንዲከፍል ፡ እንዲወሰንለት ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለጠበቃ ፡ ለዳኝነት ፡ ያወጣውን ፡ ከፍ ፡ ካሳ ፡ ኪሣራ ፡ ጋር ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ እንዲከፍለው ፡ እንዲፈረድበት ፡ ብሎ ፡ አመልክቷል ።

የመልስ ፡ ሰጪው ፡ ነገረ ፡ ፈጅም ፡ በጻፈው ፡ መልስ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ትክክለኛ ፡ መዝገብ ፡ አለኝ ፡ ሲል ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዳመለከተው ፡ ለግብር ፡ ሰብሳቢው ፡ ባለሥልጣንም ፡ እንደዚሁ ፡ አቅርቦ ፤ ከመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ አያሌ ፡ ሽያጭ ፡ ሳይመዘገብ ፡ ደብቆ ፡ ከተገኘበት ፡ በወንጀል ፡ ባለመከሰሱ ፡ ቅር ፡ የተሰኘ ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ከመዝገቡ ፡ ሳይመዘገብ ፡ የተገኘው ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ ብር ፡ $ 1,118,906,66 ፡ ሽጠ ፡ ተገኝቶአል ። ይኸም ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢው ፡ በምርመራ ፡ የደረሰበት ፡ ነው ። ተደብቆ ፡ የቀረም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሽያጭ ፡ እንዳለ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ሊያስረዳ ፡ ይችላል ። ግብር ፡ ሰብሳቢውና ፡ የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ክፍል በ፩ኛው ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፲፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በዓዋጅ ፡ ፩፻፸፫ ፡ በአንቀጽ ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ የይግባኝ ፡ ባዩን ፡ መዝገብ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረና ፡ ግብሩን ፡ በግምት ፡ የወሰነው ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ነው ። የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤም ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያት ፡ ስላገኘ ፡ በዓዋጁ ፡ ቁ. ፶፯ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ግብሩን ፡ በመጨመር ፡ ውሳኔ ፡ ሰጠ ። አመልካች ፡ እንዲከፍለው ፡ የተወሰነበትን ፡ እንዲከፍል ፡ በዓዋጁ ፡ በአንቀጽ ፡ ፰፱ ፡ መሠረት ፡ የማስፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ መልሷል ።

ያገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መ/ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ፡ እንዲከፍለው ፡ የመደበበት ፡ ብር ፡ $ 11,300 ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ አይገባኝም ፡ ይቀነስልኛል ፡ ሲል ፡ ለግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ በይግባኝ ፡ ቀርቦ ፡ ቢያመለክት ፡ የኢት. ፡ ብር፡ $ 2,831,50 ፡ ጨምሮ ፡ $ 14,121,50 ፡ እንዲከፍል ፡ ስለወሰነበት ፡ ይለወጥልኛል ፡ ሲል ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ቀርቦ ፡ አመልክቷል ። ይግባኝ ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ሁለት ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ነው ። ፩ኛው ፡ መዝገብ ፡ እያለኝ ፡ በግምት ፡ ስለተመደበብኝ ፡ በሒሳብ ፡ መዝገቤ፡ መሠረት፡ የምከፍለውን ፡ ግብር ፡ ልጠየቅ ፤ ፪ተኛውም ፡ ልከፍለው ፡ የማይገባኝን ፡ ግብር ፡ አላግባብ ፡ ስለተጠየቅሁ ፡

እንዲቀነስልኝ ፡ በይግባኝ ፡ ብቀርብ ፡ ከተመደበብኝ ፡ ግብር ፡ በላይ ፡ ጨምሮ ፡ እንድከፍል ፡ ስለበየነብኝ ፡ እንዲለወጥልኝና ፡ በሒሳብ ፡ መዝገቤ ፡ መሠረት ፡ እንድከፍል ፡ ይታዘዝልኝ ፡ በማለት ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ።

በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ለተሠራው ፡ በይግባኝ ፡ ለጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠበትን ፡ ግልባጭ ፡ አቅርቦ ፡ ጉዳዩ ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለሆነ ፡ በሱ ፡ መሠረት ፡ ይወሰንልኝ ፡ ሲል ፡ አመልክቷል ። መዳቢው ፡ ኮሚቴ ፡ መዝገብ ፡ እያለኝ ፡ በግምት ፡ ስለመደበብኝ ፡ በሒሳብ ፡ መዝገቤ ፡ መሠረት ፡ ካገኘሁት ፡ ጥቅም ፡ ግብር ፡ እንድከፍል ፡ ይደረግልኝ ፡ ያለውን ፡ አልተቀበለነውም ፤ ምክንያቱም ፡ መዳቢው ፡ ክፍሉ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገቡን ፡ በትክክል ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካላመነበት ፡ በግምት ፡ ሊመድብ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ደንቡ ፡ ስለሚፈቅድለት ፡ ነው ።

የተጠየቅሁት ፡ ግብር ፡ ካገኘሁት ፡ ጥቅም ፡ በላይ ፡ ስለሆነ ፡ በዝቶብኛልና ፡ ይቀነስልኝ ፡ ብሎ ፡ በይግባኝ ፡ ያቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ክፍል ፡ ደንቡ ፡ ለመጨመርም ፡ ሆነ ፡ ለመቀነስ ፡ ይፈቅድልኛል ፡ ብሎ ፡ ጨምሮ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በቂ ፡ አድርገን ፡ አልተቀበልነውም ፤ ምክንያቱም ፡ ደንቡ ፡ ለመጨመር ፡ ሆነ ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ ፈጽሞ ፡ ለመፋቅ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ቀጥሎ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሆኖ ፡ ሲቀርብለት ፡ ነው ። አነስ ፡ ብሎ ፡ በይግባኝ ፡ ሲቀርብለት ፡ ለመጨመር ፡ ይችላል ፤ በዛብኝ ፡ ብሎ ፡ እንዲቀነስለት ፡ በይግባኝ ፡ ሲቀርብም ፡ ለመቀነስ ፡ ይችላል ። አልሠራሁም ፡ ብሎ ፡ ለሚያመለክትም ፡ አለመሥራቱን ፡ ተረድቶ ፡ ግብሩን ፡ ይፍቅለታል ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባላጋራው ፡ አንሶታልና ፡ ይጨመርበት ፡ ብሎ ፡ ይግባኝ ፡ ባላለበት ፡ ጉዳይ ፡ በዝቶብኛልና ፡ ይቀነስልኝ ፡ ብሎ ፡ በይግባኝ ፡ በቀረበው ፡ ወገን ፡ ጨምሮ ፡ መፍረድ ፡ በወንጀል ፡ ተከሶ ፡ አስር ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ ተፈርዶበት ፡ እሥራቱ ፡ በዝቶብኛልና ፡ ይቀነስልኝ ፡ ብሎ ፡ ባቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ ሞት ፡ ይገባሃል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ መፍረድ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ያመለከተው ፡ በሚገባ ፡ ስለሆነ ፡ ተቀብለነዋል ። የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፭/፶፮ ፡ ዓ. ም. የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለውጠን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተመደበበትን ፡ የኢት. ብር ፡ $ 11,300 ፡ ብቻ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ይክፈል ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ለዳኝነት ፡ ያወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ በደረሱኙ ፡ ልክ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ለይግባኝ ፡ ባይ ፡ ይክፈል ።

ኪሣራ ፡ የየራሳቸውን ፡ ይቻሉ ፡ ብለን ፡ ፈርደናል ።

HIGH COURT
Addis Ababa, Admin. Div.

MULUGETA AYELE v. THE INLAND REVENUE DEPARTMENT

Civil Case No. 423/56

Administrative Law — Appellate administrative tribunals — Procedure — Tax Appeal Commission.

*Taxation — Assessment by estimation — Administrative procedure — Arts. 40 and 56 Proc. No. 173 of 1961.**

Appeal from a decision of the Tax Appeal Commission, which sustained the Inland Revenue Department's assessment of the appellant's tax by estimation and in addition increased the assessment on its own motion.

Held: Decision increasing the assessment quashed and the appellant taxpayer directed to pay the tax assessed by the Inland Revenue Department.

1. The Inland Revenue Department is empowered by Art. 40 of Proc. No. 173 of 1961, to assess income tax liability by estimation if it finds the taxpayer's account books unreliable.

2. The Tax Appeal Commission is empowered to increase or reduce tax assessments at the request of the Inland Revenue Department or the taxpayer, and it may annual an assessment if it is proved that the taxpayer had no income. Art. 56 Proc. No. 173 of 1961.

3. The Tax Appeal Commission may not increase a tax assessment on its own motion under Art. 56 of Proc. No. 173 of 1961.

Megabit 10, 1957 E.C. (March 19, 1965 G.C.); Judges: Ato Tefferi Desalegn, Ato Wolde Mussie Yihdego, Ato Asayegn Adal:— In his original appeal to the Tax Appeal Commission, appellant alleged that the Inland Revenue Department accepted only some of the accounts kept by him, arbitrarily rejected the rest, and made its final assessment on the basis of estimation. In accordance with Article 58 of Proc. No. 173 of 1961, this present appeal was lodged from the decision of the Tax Appeal Commission, which also accepted appellant's book of accounts in part and rejected the rest. It also imposed a fine on the appellant on its own motion without its being requested to do so by the Inland Revenue Department. Plaintiff further alleges that he had kept proper accounts to show the profit he earned in 1961 and requested this Court to quash the decision given by the Tax Appeal Commission and order the

* The Tax Appeal Commission decision from which this appeal was taken appears at p. 353.

Inland Revenue Department to make its assessment on the basis of what was shown in his books.

In its statement of defence, the respondent department alleged that the appellant had submitted the supposedly properly kept books to its tax assessor, who discovered that E$1,148,906,662 worth of sales were not recorded in the books — a sum that indicates how many more unrecorded sales have not yet been disclosed. Moreover, it argued that the steps taken by the Income Tax Authority were in accordance with Article 40 of Proc. No. 173 of 1961, which provides that the Authority may assess the tax by estimation if it finds the records and books of accounts kept by the taxpayer unacceptable. And Article 56 of the same Proclamation authorises the Tax Appeal Commission to increase an assessment made by the Income Tax Authority if it deems it just. Accordingly, the respondent department requested this Court to affirm the decision given by the Commission and applied for its execution.

The tax assessed by the Inland Revenue Department was E$11.300 but the Tax Appeal Commission increased it by $2,821.50 and ordered the appellant to pay E$14,121.50. The appellant argued that the tax should not have been assessed by estimation, but on the basis of the accounts he kept. He then requested this Court to quash the decision of the Tax Appeal Commission and order the respondent department to assess the tax on the basis of what is recorded in his account books. He even produced a copy of a decision of the Supreme Imperial Court in a similar case and asked for a decision along the same lines.

The first ground of appeal must be dismissed since Article 40 of Proc. No. 173 of 1961 empowers the Income Tax Authority to assess the tax by estimation if it finds the taxpayer's acount books unreliable.

However, this Court finds the Tax Appeal Commission's decision arbitrary because it may exercise the power vested in it by Article 56 of Proc. No. 173 of 1961 only under certain conditions. It may increase the tax if the Inland Revenue Department claims that it is too low; it may reduce the tax if the taxpayer proves that the assessment was too high, and it may annul the assessment if it is proved that the appellant did not earn anything. But under no circumstances may it increase the assessment on its own motion. Such a decision is comparable to condemning a person who appealed from a sentence of ten years imprisonment to death.

For the above reasons the decision given by the Tax Appeal Commission on August 5, 1964, is quashed. The appellant shall pay the tax assessed by the Inland Revenue Department. The parties shall bear their own costs, but the respondent shall pay court fees according to receipt.

A copy of this decision shall be sent to the Execution Office.

የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ።

የጆስ ፡ ሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ አመልካች ፤ የጆስ ፡ ሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

ስለ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ደምሴ ፡ ከሥራ ፡ መወገድ ፡ ጉዳይ ።

የተግባረ ፡ ሥራ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ ሥራ ፡ ተመልሶ ፡ ለመግባት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ማስረጃ ፡ የሚቀርቡ ፡ ግዴታ ፡ የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ (ሐ) ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማስረጃ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ። *

አሠሪው ፡ የጆስ ፡ ሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ ከዚሁ ፡ ኩባንያ ፡ ሠራተኞች ፡ አንዱን ፡ የሠራተኞች ፡ ማህበር ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ከሥራ ፡ ስላሰናበቱት ፤ የኸው ፡ አድራጎት ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ (ሐ) ፡ መሠረት ፡ አግባብ ፡ ስላልሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ ሥራው ፡ ተመልሶ ፡ እንዲገባ ፡ ሲል ፡ የዚሁ ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ያቀረበው ፡ ክስ ።

<u>ውሳኔ</u> ፤— መልስ ፡ ሰጭው ፡ ኩባንያ ፡ ሠራተኛውን ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ ሥራው ፡ እንዲመልሰው ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጥቶአል ።

አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ የሠራተኞች ፡ ማህበር ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ አሠሪው ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ ፡ (ሐ) ፡ የተደነገገውን ፡ በመጣስ ፡ ከሥራ ፡ ስላሰናበቱት ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ ለማድረግ ፡ ክስ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፤ ከሥራ ፡ የተሰናበትነው ፡ ሠራተኛ ፡ የማኅበሩ ፡ አባልና ፡ ዋና ፡ ጸሓፊ ፡ መሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሠራተኛው ፡ ከሥራ ፡ የወጣው ፡ የማኅበር ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ ባይችልም ፤ ክሱ ፡ በመሠረቱ ፡ ውድቅ ፡ አይሆንም ።

መስከረም ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ። የአሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ አባሎች ፤ ክቡር ፡ ብላታ ፡ ትርፌ ፡ ሹምዬ ፡ የተከበሩ ፡ ብላታ ፡ ክፍለ ፡ እግዚእ ፡ ይሕድጎ ፡ አቶ ፡ ይልማ ፡ ኃይሉ ።

የጆስ ፡ ሐንሰን ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. አቅርቦ፡ በቁጥር ፡ ፍ/ብ/፲፩/ ፳፱/ ፶፮ ፡ በተመዘገበው ፡ ማመልከቻ ፤ አሠሪው ፡

* የአሠሪና ፡ የሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ቦርድ ፡ ውሳኔ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ቀርቦለት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በገጽ ፪፻፶፯ ፡ ይገኛል ።

የጆስ ፡ ሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ደምሴ ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ጥናት ፡ ወደ ፡ ካምፓላ ፡ በፈቃድ ፡ ሄደው ፡ እንደተመለሱ ፡ ያለአንዳች ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ የመሰናበቻ ፡ ደብዳቤ ፡ መጻፉና ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከአንዱ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ በማዘዋወር ፡ በአዲሱም ፡ ክፍል ፡ የሥራ ፡ ችሎታ ፡ የላቸውም ፤ ከሠራተኞችም ፡ አይስማሙም ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ በመፍጠር ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰/፶፰ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ (ሐ) ፡ የተመለከተውን ፡ የሠራተኛው ፡ መብት ፡ ያልተጠበቀላቸው ፡ ስለሆነ ፤ ቦርዱ ፡ ጉዳዩን ፡ መርምሮ ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ያድርግልን ፡ የሚል ፡ ነው ።

አሠሪው ፡ የጆስ ፡ ሐንሰን ፡ ኩባንያ ፡ ለቀረበበት ፡ ተጠይቆ ፡ ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. አቅርቦ ፡ በቁጥር ፡ ፩/፩/፲፩/፴፩/፶፯ ፡ በተመዘገበው ፡ የጽሑፍ ፡ መከላከያና ፡ በቃልም ፡ እንዳመለከተው ፤ አቶ ፡ መስፍን፡ ደምሴ ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበቱት ፡ የግል ፡ ማኅደራቸው ፡ እንደሚያስረዳው ፡ በጠባያቸው ፡ ከሥራ ፡ ጓደኞቻቸውና ፡ ከክፍል ፡ አለቆቹ ፡ ጋር ፡ ባለመስማማታቸው ፤ ስለጠባያቸው፡ በየጊዜው ፡ ተመክረው ፡ ባለማሻሻላቸው ፤ ወደ፡ ካምፓላ ፡ ለትምህርት ፡ ሲሄዱ ፡ ኩባንያው ፡ በዱቤ ፡ ሽጦላቸው ፡ የነበረውን ፡ መኪና ፡ በኩባንያው ፡ ጋራዥ ፡ ውስጥ ፡ እንዲያስቀምጡ ፡ ተጠይቀው ፡ ባለማስቀመጣቸው ፡ ሴመንስ ፡ ክፍል ፡ አዛወርናቸው ። ችሎታቸው ፡ ለዚህ ፡ ክፍል ፡ በቂ ፡ ባለመሆኑ ፤ ማረፍ ፡ በሚገባቸው ፡ ሰዓት ፡ ሌሊት ፡ በሺባ ፡ ክበብ ፡ በመሥራታቸው ፤ ከመደበኛው ፡ ሥራ ፡ ስለቀሩና ፡ የሥራ ፡ ሰዓትም ፡ ባለማክበራቸው ፡ አሰናብተናቸዋል ፡ እንጂ ፤ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ እንዳመለከቱት ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ መሪ ፡ ወይም ፡ አባል ፡ በመሆናቸው ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የቀረበውን ፡ ክርክር ፡ በዝርዝር ፡ አጥንቶ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ቦርዱ ፡ ስድስት ፡ ስብሰባዎችን ፡ አድርጎ ፡ ነበር ።

ነሐሴ ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ያቀረቡትን ፡ ጽሑፍና ፡ የቃል ፡ መግለጫ ፡ ቦርዱ ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመልክቶና ፡ ሰምቶ ፤ አሠሪው ፡ ኩባንያ ፡ በሠራተኛው ፡ የግል ፡ ፋይል ፡ ስለጥፋቱ ፡ በቂ ፡ ማስረጃዎች ፡ አሉኝ ፡ ብሎ ፡ ያላቸውን ፡ ማስረጃዎች ፡ በሙሉ ፡ ለነሐሴ ፡ ፲፱ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. እንዲያቀርብ ፡ ታዘዘ ።

ነሐሴ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. በተደረገው ፡ የቦርዱ ፡ ስብሰባ ፡ አሠሪው ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎች ፡ ይሆኑልኛል ፡ ያላቸውም ፡ ቀርበው ፡ ታይተዋል ።

፩ ፤ በታኅሣሥ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯፡ ዓ ም. (እ. ኤ. አ.) ለሠራተኛው ፡ የተጻፈላቸው ፡ ደብዳቤ ፡ ፍሬ ፡ ነገር፡ ከዚህ፡ በፊት፡ ታኅሣሥ ፡ ፱ ፡ ቀን፡ የተጻፈውን፡

ደብዳቤ ፡ በማስታወስ፡ ብዙ ፡ ጊዜ፡ በሥራዎ ፡ ላይ፡ ስላልተገኙ ፡ ከየካቲት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ከሥራ ፡ ተሰናብተዋል ፡ የሚል ፡ነው ።

፪ ፤ ህዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.)የተጻፈላቸው ፡ ደብዳቤ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በሼባ ፡ ክበብ ፡ እያመኹ ፡ መሥራትዎን ፡ ስለሰማን ፡ ወደፊት ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ቢቀጥሉ ፡ ግን ፡ ከሥራ ፡ እናሰናብትዎታለን ፡ የሚል ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ነው ።

፫ ፤ ኅዳር ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡)ከአቶ ፡ መስፍን ፡ ደምቤ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ለተጻፈላቸው ፡ ደብዳቤ ፡ የሰጡት ፡ መልስ፡ ሲሆን ፡ ፍሬ፡ ነገሩም፡ የኑሮ ፡ ደረጃዬን ፡ ለማሻሻል ፡ በትርፍ ፡ ጊዜ ፡ መሥራት ፡ ማስፈለጉን ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።

፬ ፤ ታኅሣሥ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ስለዚሁ ፡ ስለሼባ ፡ ክበብ ፡ ጉዳይ ፡ ዳግመኛ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከአሠሪው ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ነው ።

፭ ፤ የካቲት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ፡ ም፡ አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ የጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ከካምፖላ ፡ እስኪመለሱ ፡ አውቶሞቢላቸውን ፡ በኩባንያው ፡ ጋራዥ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀመጥ ፡ እንዲያደርጉ ፡ የሚል ፡ ነው ።

፮ ፤ ሚያዚያ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. አቶ ፡ መስፍን ፡ ከካምፓላ ፡ ለኩባንያ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ስለትምህርቱና ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ሲመለስ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ በማብራራት ፤ አውቶሞቢላቸውም ፡ በጥሩ ፡ ሁናቴ ፡ ከእኅታቸው ፡ ዘንድ ፡ የተቀመጠች ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ የግል ፡ ደብዳቤ ፡ ነው ።

፯ ፤ ግንቦት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. አሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ የጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ሲሆን ፤ ፍሬ ፡ ነገሩ፡ ከሐምሌ ፡ ፴፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ከሥራ ፡ ተሰናብተዋል ፡ የሚል ፡ ነው ።

፰ ፤ በመሐከሉ ፡ ሐምሌ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. አሠሪው፡ ፡ ለሠራተኛው ፡ የጻፈላቸው ፡ ደብዳቤ ፡ ሲሆን ፡ ፍሬ ፡ ነገሩም ፡ ጠባይዎን ፡ ስላላሻሻሉ ፡ ወደ ፡ ሲመንስ ፡ ክፍል ፡ ተዛውረው ፡ እንዲሠሩ ፡ የሚልና ፡ እንዲሁም ፡ ከሐምሌ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ጉዳዩም ፡ እስከ ፡ ነሐሴ ፡ ፴፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ እና ስብበታለን ፡ የሚል ፡ ነው ።

፱ ፤ በመካከሉ ፡ ደግሞ ፡ ሐምሌ ፡ ፴፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ከአሠሪው ፡ ለሠራተኛው ፡ የተጻፈለት ፡ ደብዳቤ ፡ ሲሆን ፤ ፍሬ ፡ ነገሩም ፡ ከነሐሴ ፡

፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ከሥራ ፡ ተሰናብተዋል ፡ የሚል ፡ የአንድ ፡ ቀን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተዘረዘረው ፡ አሠሪው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎቹ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ካቀረባቸው ፤ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ምስክሮች ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተደጋገመ ፡ ቀጠሮ ፡ ተሰጥቶት ፡ አሠሪው ፡ በኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ የአንድ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊነት ፡ የተሰጠው ፡ ሚስተር ፡ ኬለር ፡ የሚባለውን ፡ በምስክርነት ፡ ቢያቀርብ ፤ ሠራተኛው ፡ የተባሉት ፡ ሰው ፡ ጠበኛዬ ፡ በመሆናቸው ፤ ከሥራም ፡ ለመውጣት ፡ ምክንያት ፡ የሆኑኝ ፡ እርሳቸው ፡ ስለሆኑ ፡ አይመስክሩብኝም ፡ ሲል ፡ ተቃወመ ። የምስክሩንም ፡ ቃል ፡ እውነተኛነት ፡ መገመትና ፡ ማመዛዘን ፡ ቦርዱ ፡ ስለሚችል ፡ አሠሪው ፡ ምስክሬ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ያቀረበውን ፡ ምስክር ፡ ተቀብሎ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ አስመስክሮአል ።

የምስክሩም ፡ ቃል ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ባጭሩ ፤ ምስክሩ ፡ በኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ ተቀጥሮ ፡ ሥራ ፡ እንደጀመረ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ የምስክሩ ፡ የሥራ ፡ ረዳት ፡ ሆኖ ፡ በመጋዘን ፡ ክፍል ፡ ሲሠራ ፡ ማወቁን ፡ በመግለጽ ፤ ምንም ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ለሥራው ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ ቢታዩም ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ አብረዋቸው ፡ በሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ የኩባንያውን ፡ የሥራ ፡ ዲስፕሊን ፡ የማይጠብቁ ፤ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ የማያከብሩ ፡ ለሌሎች ፡ መጥፎ ፡ አርአያ ፡ የሆኑ ፤ ከሥራ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፤ የቃል ፡ ምክርም ፡ ቢሰጣቸው ፡ ጠባያቸውን ፡ የማያሻሽሉ ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ መስክሮአል ።

በአሠሪው ፡ በኩል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ የጽሑፍ ፡ አስረጅ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ ከቀረቡትና ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ ሌላ ፡ ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ የሌኝም ፡ ስላለ ፤ ሠራተኛው ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ በበኩሉ ፡ ላለማጥፋታቸው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ እንዲቀርብ ፡ ተጠይቀው ፤ አሠሪው ፡ ያቀረባቸው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎች ፡ ላለማጥፋቴ ፡ ስለሚደግፉኝ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ አያስፈልገኝም ፡ ብሉአል ።

ቦርዱ ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ የሚፈጠረውን ፡ ያለመግባባት ፡ በውሳኔ ፡ ሳይሆን ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ተነጋግረውበት ፡ እራሳቸው ፡ በስምምነት ፡ እንዲፈጽሙ ፡ መጠየቅና ፡ ማበረታታት ፡ ተግባሩ ፡ ስለሆነ ፤ እነዚህም ፡ ተከራካሪዎች ፡ በእርቅ ፡ ጉዳያቸውን ፡ እንዲጨርሱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳስቦና ፡ የተደጋገመ ፡ ቀጠሮ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ያልተስማሙ ፡ ሆነው ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ስለጠየቁ ፤ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ የውሳኔ ፡ መቀበያ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲያ

ቀርቦ ፡ ጠይቆ ፡ መስከረም ፡ ፲፫ ፡ እና ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ያቀረቡትን ፡ ጽሑፍ ፡ ቦርዱ ፡ ተመልክቶ ፡ ጉዳዩንም ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ መርምሮ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ።

ው ሳ ኔ ።

፩ ፤ አሠሪው ፡ ኩባንያ ፡ ከሳሹ ፡ የወጣበት ፡ በሠራተኞች ፡ ማህበርተኝነት ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ ካልቻለ ፡ ጉዳዩ ፡ መዘጋት ፡ አለበት ፡ ያለውን ፡ ቦርዱ ፡ አልተስማማበትም ፤ ምክንያቱም ፡ ከሳሽ ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ አባልና ፡ የማኅበሩም ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ በመሆኑ ።

፪ ፤ አሠሪው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎቹ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ከ፩-፱ ፡ ያቀረባቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ከሥራ ፡ የማባረሪያ ፡ ማስታወቂያዎችና ፡ በትርፍ ፡ ሰዓት ፡ ሌሊት ፡ ሽብ ፡ ከሰብ ፡ ትሠራለህ ፡ ከአለቆችህና ፡ ከሥራ ፡ ጓደኞችህ ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ የለህም ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ አታከብርም ፤ አውቶሞቢልህን ፡ በኩባንያው ፡ ጋራዥ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አድርግ ፡ የሚል ፡ ስለሆነ ፤ ከሥራ ፡ ለማሰናበት ፡ የጥፋተኛነት ፡ ማስረጃነት ፡ የሌላቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ሆነው ፡ ቦርዱ ፡ ስላገኛቸው ፡ የቀረቡት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ሁሉ ፡ ለሠራተኛው ፡ አጥፊነት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አድርጎ ፡ አልተቀበላቸውም ።

ስለዚህ ፡ ሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ ያላከበረ ፡ ለመሆኑ ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ መቆጣጠሪያ ፡ ደብተር ፡ አሠሪው ፡ እንዲያቀርብ ፡ ቢጠየቅ ፡ የለኝም ፡ አለ ። የሥራ ፡ ሰዓት ፡ ባለማክበር ፡ ሠራተኛው ፡ ሳልሠራባቸው ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶች ፡ ከደመወዙ ፡ ላይ ፡ ለመቆረጡ ፡ ማስረጃ ፡ ቢጠየቁ ፡ አልተቆረጠበትም ፡ አለ ። ሠራተኛው ፡ እረፍት ፡ በሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ በአድካሚ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በማሠማራት ፡ በሽታ ፡ አትርፎ ፡ መደበኛ ፡ የሆነውን ፡ የኩባንያ ፡ ሥራውን ፡ ለማጓደል ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ ለመቅረቱ ፡ የሐኪም ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃዎች ፡ አሠሪው ፡ እንዲያቀርብ ፡ ቢጠየቅ ፡ የለኝም ፡ አለ ። ስለሠራተኛው ፡ ጠባይ ፡ ማለት ፡ ከሥራ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ያልተስማማ ፡ ለመሆኑ ፤ ሠራተኛው ፡ ጠበኛዩ ፡ ነው ፡ ከሚለው ፡ ከሚስተር ፡ ኬለር ፡ ሌላ ፡ መስል ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቹን ፡ ለምስክርነት ፡ አሠሪው ፡ እንዲያቀርብ ፡ ቢጠየቅ ፡ ምስክር ፡ የለኝም ፡ አለ ። ሚስተር ፡ ኬለር ፡ የሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ አጠራጣሪና ፡ የበላይ ፡ አለቃው ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ሠራተኛው ፡ ከሥራ ፡ ይቀራል ፡ ይዘገያል ፡ ለሚለው ፡ በጊዜያቱ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ ያልወሰደና ፡ የቀረበትም ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ አላውቀውም ፡ ስላለ ፡

ቦርዱ ፡ ምስክርነቱን ፡ በቂ፡ አድርጎ፡ዋጋ፡ አልሰጠውም ። ቢጠቅላላው፡ ሠራተኛው፡ ከሥራ ፡ እንዲለቅ ፡ የተደረገው ፡ በበቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ለመሆኑ ፡ አሠሪው ፡ ማስረ ጃዎች ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተደጋገመ ፡ ቀጠሮ ፡ ተሰጥቶት ፡ ለማቅረብ ፡ አልቻለም ።

፫ ፤ አሠሪው ፡ ያቀረባቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ እንደዚሁም ፡ ሠራተኛው ፡ በበኩሉ ፡ ያቀረበውን ፡ አቤቱታ ፡ ቦርዱ ፡ በዝርዝር ፡ አጥንቶ ፡ ሊረዳ ፡ የቻለው ፤ በአሠ ሪውና ፡ በሠራተኛው ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ የተነሳው ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ ከተቋቋመ ፡ በኋላና ፡ እየከረረም ፡ የሄደው ፡ ሠራተኛው ፡ ስለሠራተኞች ፡ አስ ተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጥናት ፡ ጉዳይ ፡ በፈቃድ ፡ ወደ ፡ ካምፓላ ፡ ሊሄድ ፡ ከተነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። የሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ ልምድና ፡ ችሎ ታው ፡ ወደማይፈቅድለት ፡ ቴክኒክ ፡ ክፍል ፡ አሠሪው ፡ አዛውሮ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድረጉና ፡ ችሎታ ፡ የለህም ፡ ማለት ፤ ከካምፓላ ፡ በተመለሰ ፡ በ፫ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማስረጃ ፡ በሌለው ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ ማሰናበት ፤ ከኩባንያው ፡ በዱቤ ፡ ገዝቶ ፡ የሠራተኛው ፡ ንብረት ፡ የሆነውን ፡ አውቶሞቢል ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያልተጠበቀ ፡ ግዴታ ፡ ቢኖር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መክሰስ ፡ ሲገባው ፡ እኩባንያው ፡ ጋራዥ ፡ ካላስቀመጥክ ፡ ብሎ ፡ ከሥራ ፡ የማስወጫ ፡ ምክንያት ፡ ማድረግ ፤ አሠሪው ፡ በሠራተኛው ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዳደረገበት ፡ ቦርዱ ፡ በቀላሉ ፡ ለመረዳት ፡ ችሎአል ።

፬ ፤ ስለዚህ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ እንዲወጣ ፡ ያደረገው፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰/፶፮ ፡ አንቀጽ ፡ ፴ሐ ፡ « የሠራተኛ ፡ ማህበር ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ከሥራ ፡ ማሰናበት ፡ ክልክል፡ ነው»፡ ተብሎ የታወጀውን ፡ በመተላለፍ ፤ በማህበሩ ፡ አባልነት ፡ እና ፡ መሪነት ፡ ምክን ያት ፡ በተዘዋዋሪነት ፡ ምክንያት ፡ በፈጠራ ፡ ዘዴ ፡ ስለሆነ ፡ ሠራተኛው ፡ ደመወዙ ፡ ከታገደበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያለው ፡ መብቱ ፡ በሙሉ ፡ ተጠብቆ ፡ ወደሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ ወስኖአል ።

LABOUR RELATIONS BOARD

EMPLOYEES' ASSOCIATION OF JOS. HANSEN & SOEHNE v. JOS. HANSEN & SOEHNE

Re: The dismissal of MESFIN DEMISSIE

Labour law — Burden of proof in action for reinstatement — Art. 30(c) Proc. No. 210 of 1963.

Civil procedure — Burden of proof — Labour Relations Board. *

Action by the employees' association of the respondent company to have a former employee of the company reinstated to his job. The employees' association alleged that the employee had been dismissed because of his membership in the association and that the dismissal therefore was unlawful under Art. 30(c) Proc. No. 210 of 1963.

Held: The respondent company is ordered to reinstate the employee.

In an action to have an employee reinstated on the ground that he has been dismissed for being a member of the employees' association, contrary to Art. 30(c) Proc. No. 210 of 1963, where the employee is a member and secretary of the association, the action may not be dismissed on the ground that the employee has failed to submit proof in support of his allegation.

Maskaram 22, 1957 E.C. (October 2, 1964 G.C.): Members of the Board: Blatta Tirfie Shumiye, Blatta Kifle Igzi Yihdigo, Ato Yilma Hailu:— The employees' association of Jos. Hansen & Soehne (Eth.) Ltd., lodged with this Board an application dated July 14, 1964 under File No. 5/1/11-29/56 in which it is stated that the employer, Jos. Hansen & Soehne, first served a letter of discharge on its employee, Ato Mesfin Demissie, when he came back from Kampala, where he had attended a training seminar in the field of "Labour Relations". After that the employer transferred him to different sections and complained that he was not capable of handling the work and that he did not co-operate with the employees. Finally, the employer dismissed him contrary to Article 30(c) of the Labour Relations Proclamation, Proc. No. 210 of 1963. The applicant therefore petitioned the Board to examine the matter and order the return of the employee to his post.

As per instructions issued to the employer, Jos. Hansen & Soehne, the respondent submitted a written reply dated August 5, 1964, inserted in File No. 5/1/11-31/56, and also made an oral statement as follows: The reason for the discharge of Ato Mesfin Demissie is evident from his personal file, from which

* The decision of the Supreme Imperial Court on appeal from the Labour Relations Board's decision appears at p. 259.

it can be seen that he failed to co-operate with the other employees or with his immediate supervisors. As a result, he occasionally was warned, but he did not improve. Furthermore, when Ato Mesfin was preparing to leave for Kampala he was requested by the company to park in the company's garage the vehicle which he had bought from the company on credit and for which he had not paid the full price, but he did not comply with that request. It appears also that he was transferred to the Simens Section, where he was unable to meet the requirements of the work. The employer concluded its submission by adding that the employee was working in the "Sheba Club" late at night, at a time when he had to rest as a result of which he came late to work and was paralyzing the operation of the whole section, which gave ample reason for his dismissal. The employer asserted that these being the reasons for his discharge, his being a key member of the association had nothing to do with the steps taken by the company.

The Board then adjourned the case six times in order to study the merits of the matter and to decide.

At the hearing on August 14, 1964, the Board examined the written and oral submissions of both parties and ordered the employer to submit to the Board on August 25, 1964, all documentary proof in support of its defence.

On the hearing date of August 25, 1964, the employer submitted the following documentary evidence to the Board.

1. The letter dated December 27, 1962, addressed to the employee, refers to a previous letter dated December 4 and notifies the employee of his dismissal from his work as of February 28, 1963, for being absent from his job many times.

2. The letter dated November 8, 1963, addressed to the employee, is a warning letter in which he was notified concerning his working at the "Sheba Club" during late hours and in which he was told to stop that work or he would be discharged.

3. The letter dated November 19, 1963, addressed by Ato Mesfin Demissie to the company in reply to the letter mentioned in item 2 above, gives an explanation to the effect that one has to work overtime in order to improve his living standard.

4. The letter dated December 3, 1963, addressed to the employee, is an additional warning letter asking him to quit his work at the "Sheba Club."

5. The letter dated February 17, 1964, addressed by the company to Ato Mesfin, is a letter in which the employee was asked to bring and park his car in the company's garage until he returned from Kampala.

6. The letter dated April 15, 1964, sent by Ato Mesfin from Kampala to the company, is a letter in which he explained the importance of his training

to the business of the company and said that the car in question was kept by his uncle in good condition.

7. The letter dated May 29, 1964, addressed to the employee, is a letter by which the company discharged Ato Mesfin as from July 31, 1964.

8. Then by a letter dated July 6, 1964, the company told the employee that he was transferred to the Simens Section and would work there until he improved his conduct; it further informed him that his dismissal as of July 31, 1964, was cancelled pending further consideration by the company until August 31, 1964.

The Board then granted a number of adjournments to permit the employer to produce any other documentary proof or witnesses in this matter, and finally the employer offered as its witness Mr. Keller, chief of one of the sections of the company. The employee objected to the testimony of this witness, saying that the witness was his adversary and was one of the reasons for his discharge. The Board, having in mind its ability to weigh the evidence of this witness, allowed him to give the following sworn statement.

The witness stated in short that he came to know Ato Mesfin when Ato Mesfin was working under him at the Stores Department. He said that, although Ato Mesfin was co-operative in the beginning, he later engaged in bad conduct which was not in line with the company's rules, such as coming late to work, being a bad example to the other employees, and disagreeing with his workmates. The witness further stated that Ato Mesfin was given written and oral warnings concerning these matters, but that he did not improve his conduct or discipline himself.

Then the employer informed the Board that it had no other documents or witnesses to be heard in this case. The Board asked Ato Mesfin if he wanted to produce witnesses on his part, and he said that he would not produce witnesses nor submit documentary evidence since the evidence submitted by the employer had proved his case.

Being aware that it is the duty of the Board to bring the employer and the employee together to settle their differences amicably without seeking the intervention of this Board, various adjournments were given in the hope of such a solution, and both parties were repeatedly advised to settle the matter by themselves. But the parties told the Board that they could not reach any agreement and asked the Board for a decision. Accordingly, the Board examined the final submissions of both parties, dated September 23 and 28, 1964, and hereby gives the following decision.

1. Because the applicant, Ato Mesfin, is a member and secretary of the employees' association, the Board cannot grant the employer's request that this matter be closed on the ground that the employee has failed to prove his allegation that he was dismissed only for being a member of the employees' association.

2. The documents (Exhibits 1-9) are letters by which the employer discharged the employee for working at the Sheba Club at night-time; for not being on good terms with his supervisors and workmates; for coming late to work; and for having failed to keep the car in the company's garage. In the Board's opinion, the said letters do not constitute good reasons for the employee's dismissal and, therefore, they are not considered sufficient evidence that the dismissal was justified.

With regard to the question of the time that the employee is said to have wasted, the employer, although having been asked to produce, cannot present the time-book to prove so. The employer also failed to prove that any amount had been deducted from the employee's salary for coming to work late. The employer was again asked to prove by a medical certificate that the employee has caused certain damage to the company's work by having been ill and coming late to work as a result of working at the Sheba Club late at night, but the employer failed to produce any such evidence. The employer was asked to call as its witnesses employees of the company other than Mr. Keller to prove that the employee was not on good terms with his workmates, but the employer said that it had no other witnesses. The Board cannot rely on the evidence given by Mr. Keller as to the conduct of the employee or his coming late to work, since Mr. Keller, in his own statement, admitted that although he was the employee's immediate supervisor, he has not kept any record of the alleged bad conduct or taken any step against the employee at the time. The employer on its part cannot produce any other evidence to show that the employee was discharged for good cause.

3. Having examined the documents submitted by the employer and the employee, the Board has concluded that the differences between the disputing parties arose at the time the employees' association was formed and their disagreement became worse when the employee began his preparation to leave for Kampala for training in the field of Labour Relations. Considering the fact that the employer transferred the employee to a new technical section and then complained of his inability to cope with the work before he was given adequate training; and considering the fact that the employer discharged the employee three days after he returned from Kampala and without good reason; and considering the fact that one of the reasons for the dismissal of the employee was that he failed to produce for safekeeping the car he had purchased on credit, the Board is of the opinion that none of these grounds constitute good cause for the discharge of the employee and that the employer has treated the employee's case unfairly.

4. Therefore, the Board is of the opinion that the employer has discharged the employee without good cause, which act is contrary to Article 30(c) of the Labour Relations Proclamation, Proc. No. 210 of 1963, which states "that no employee shall be discharged for being a member of an employees' association without good cause". We therefore have decided that the employee should be reinstated and that he is entitled to all of his previous rights.

የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባዔ ።

ሙሉጌታ ፡ አየለ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭ ።

<u>ስለ ፡ ግብር ፤</u> *

የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ የወሰነውን ፡ ግብር ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

<u>ውሳኔ ፤</u> — ግብሩን ፡ ከፍ ፡ በማድረግ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ $ 14121.50 (አሥራ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሐያ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ከአምሳ ፡ ሳንቲም) ፡ እንዲከፍሉ ፡ ተወስኖባቸዋል ።

ሐምሌ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ። የግብር ፡ ይግባኝ ፡ አባሎች ፤— አቶ ፡ ኃይለ ፡ ልዑል ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሻምበል ፡ ኢያሱ ፡ ገብረ ፡ ሐዋርያት ፡ አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሐዋዝ ፡ አቶ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ አቶ ፡ ነጋ ፡ ፋንታ ፡ ሐጅ ፡ አቡበከር ፡ ሸሪፍ ።

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ጠበቃቸውን ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ሁነኛውን ፡ ይዘው ፡ ቀርበው ፡ ለጉባኤው ፡ ጥያቄ ፡ በአንድ ፡ ኩይንታል ፡ ዱቄት ፡ ኮሚሲዮን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ እንዲሁም ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ፹፭ ፡ ሳንቲም ፡ የሚከፈለኝ ፡ ሲሆን ፡ ከዚሁም ፡ ወጪው ፡ ሲቀነስ ፡ የማገኘው ፡ የተጣራ ፡ ትርፍ ፡ አስር ፡ ሳንቲም ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የምሸጠው ፡ በኪሣራ ፡ ነው ፡ ሁልጊዜ ፡ ትርፍ ፡ አላገኝም ፤ መዝገቤም ፡ ገቢና ፡ ወጪዬን ፡ በትክክል ፡ የሚያስረዳልኝ ፡ ሲሆን ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መ/ቤት ፡ መዝገቤን ፡ የነቀፈው ፡ ወጪዬን ፡ ሳለመቀበል ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አሉ ። ተከራካሪው ፡ በሂሣብ ፡ መዝገባቸው ፡ ከተመለከተው ፡ $ 4.234.000 ሽያጭ ፡ በስተቀር ፡ ከሂሣብ ፡ መዝገባቸው ፡ ውጪ ፡ ለአሚኮስ ፡ $ 42,536,71 ፡ ለኒ. ፒ. ማሪስ ፡ $ 935.215 ፡ ለተባበሩት ፡ የዘይት ፡ ባለፋብሪካዎች ፡ $ 256,137,05 ለአቶ ፡ ውቤ ፡ መኰንን ፡ $ 41.800 ፡ ሂሣብ ፡ ሸጠዋል ፡ ሲሉ ፡ ዝርዝሩን ፡ አቅር በው ፡ አሳዩ ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ እንደገና ፡ ለተደረገላቸው ፡ ጥያቄ ፡ ሌላ ፡ የማቀር በው ፡ መቃወሚያ ፡ የለም ፤ ጉባኤው ፡ በቀረበው ፡ መርምሮና ፡ አመዛዝኖ ፡ ይወስን ልኝ ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ። ከዚሁ ፡ በኋላ ፡ ጉባኤው ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ተለዋውጦ ፡ እን ደሚከተለው ፡ ወስኗል ።

---

* የግብር ፡ ይግባኝ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በይግባኝ ፡ ቀርቦለት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፮ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የቀረበውን፡ ይግባኝ፡ መርምረናል። ያገር፡ ውስጥ፡ ገቢ፡ መ/ቤት፡ የይግ ባኝ፡ ባዩን፡ መዝገብ፡ ትክክለኛ፡ አይደለም፡ በማለት፡ ቢነቅፈውም፡ ሁለቱም፡ ወገኖች፡ በገቢው፡ አልተካካዱም። የይግባኝ፡ ባዩ፡ የዓመት፡ ጠቅላላ፡ ሺያጭ፡ $ 4.390.137፡ መሆኑ፡ ታውቋል። ስለዚህ፡ የተጣራ፡ ትርፋቸውን፡ አንድ፡ ትኩል፡ በመቶ፡ $ 6585.95፡ አስበን፡ ፲፫ኛ፡ ዓመት፡ ቁጥር፡ ፲፫፡ በወጣው፡ ነጋሪት፡ ጋዜጣ፡ በአንቀጽ፡ ፶፮፡ ለንጉሡ፡ በተሰጠው፡ ሥልጣን፡ መሠረት፡ ግብሩን፡ ከፍ፡ በማድረግ፡ ለ፲፱፻፶፫፡ ዓ.ም.፡ $ 14,121.50፡ (አሥራ፡ አራት፡ ሺህ፡ አንድ፡ መቶ፡ ሐያ፡ አንድ፡ ብር፡ ከአምሣ፡ ሣንቲም) እንዲከፍሉ፡ ይግ ባኝ፡ ባሉ፡ ጊዜ፡ ያስያዙት፡ ገንዘብ፡ ወደ፡ ግብሩ፡ እንዲታሰብላቸው፡ በስም ምነት፡ ወስነናል።

TAX APPEAL COMMISSION

MULUGETA AYELE v. THE INLAND REVENUE DEPARTMENT

Taxation. *

On appeal from the Inland Revenue Department's assessment of the appellant's income tax liability.

Held: Assessment increased to E$14,121.50.

Hamle 29, 1956 E.C. (August 5, 1964 G.C.): Members of the Commission: Ato Haile Leul Habte Giorgis, Captain Eyassu Gebre Hawariat, Ato Assefa Hawaz, Ato Wolde Amanuel, Ato Negga Fanta, Haj. Abubaker Sherif:— When asked how much profit he made on a "quintal" (1000 kgs.) the appellant answered that it varied from E$ 1.00 to E$ 0.75. But, he added, not even that, because there were times when he sold at a loss. Anyhow, he said, his expenses and profit were faithfully recorded in his books, and the Inland Revenue Department rejected the accounts he kept so as not to include his expenses and thereby lower the assessment.

The Inland Revenue Department's defence was that aside from the E$4,234,000 worth of sales shown in his books, the appellant had sold E$42,536 worth of grain and flour to A. Mikos, E$935,215 worth of the same item to P. Sarris, $256,137.05 worth of grain and flour to the Associated Oil Factories and E$41,800 worth of grain and flour to Ato Woube Makonnen. In support of its allegations it submitted the list of these sales to the Commission. The appellant said that he had no further evidence to introduce and requested a decision on the basis of the evidence already introduced. After due deliberation the Commission disposed of the matter as follows:

"Though the Inland Revenue Department rejected the accounts kept by the appellant, there was no controversy as to the income. It has been established that the yearly sale was E$14,390,137, and at the rate of 15% the appellant's profit amounts to E$65,852.95. Now pursuant to the power vested in this Commission by Article 56 of Proc. No. 173 of 1961, we have raised the tax to be paid by the appelant to E$14.212.50, the amount he deposited when he lodged the appeal to be included therein."

* The decision of the High Court on appeal from the Tax Appeal Commission's decision appears at p. 340.

አ ን ቀ ጾ ች ።

የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ አቅድ ፡ (ቅንጅት) ።

ክስቲቨን ፡ ሉወንሽቴን ፤
የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

ሀ/ የሕጉ ፡ አቅዋም ።

፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ስለሞራል ፡ ጉዳዮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን [1] ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሌላም ፡ ጊዜ ፡ በየ ቦታው ፡ የሚገኙ ፡ ነገሥታት ፡ ኃይላቸውን ፡ በቀጥታ ፡ በሚነኩባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ረገድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ የሚቻለውን ፡ ቢያስከብሩም ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በመሠረቱ ፡ አያሌ ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዓቶችን የሚመለከት ፡ ነበር [2] ። ኾኖም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡

1. በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ በአራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የተቋቋመው ፡ የኢት ዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ መሠረታዊት ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ (የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፮) ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ክርስቲያን ፡ በነበሩት ፡ በመካከለኛውና ፡ በሰሜን ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታዎች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አገሪቱ ፡ ተስፋፍታ ፡ ብዙ ፡ እስላምና ፡ አረማዊ ፡ ሕዝቦች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ ሆነዋል ። እ. ኤ. አ. ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ከኤምፐርሃም ፡ የተጻፈው ፡ ዘገበርንሚንት ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት) ፡ እሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፲፩ ፡ ጀምር ፡ ተመልከት ።

2. የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ከወደቀ ፡ አንስቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በመናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ሆነው ፡ አገሪቱን ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ሥር ፡ አድርገዋት ፡ በገዙ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቶችና በየጊዜው ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ኃይል ፡ አግኝተው ፡ ከመናገሻው ፡ ከተማ ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ወጥ ተው ፡ ይገዙ ፡ በነበሩ ፡ ንጉሦች ፡ መካከል ፡ ሲወላወል ፡ ኖሯል ። በአሁኑም ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የአገሪቱ ፡ መሪ ፡ የሚጠራው ፡ "ንጉሠ ፡ ነገሥት" ፡ ማለት ፡ "የንጉሦች ፡ ንጉሥ" በሚል ፡ ማዕረግ ፡ ነው ። እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ኢትዮጵያ ፡ ኦቭዘርቨር ፡ አምስተኛው ፡ ቮልዩም ፡ ገጽ ፡ ፻፶፪ ፡ "የአጼ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክን ፡ (ገድላን) ፡ (፲፬፻፴፬ —፲፬፻፷፰)" ፡ እ. ኤ. አ. የ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ኢትዮጵያ ፡ ኦቭዘርቨር ፡ ስድስተኛው ፡ ቮልዩም ፡ ገጽ ፡ ፳፫ ፡ የበዕደማርያም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክን (ገድላን) ፡ (የ፲፬፻፷፰-፲፬፻፸፰)" ተመል ከት ። በጠቅላላም ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከፐርሃም ፡ መጽሐፍ ፡ ከገጽ ፡ ፳፱ ፡ ጀምር ፡ የሚለጥ ቁትን ፡ ከገጽ ፡ ፲፭ ፡ ጀምር ፡ የሚለጥቁትን ፡ ገጾችና ፡ እንዲሁም ፡ ሬቻርድ ፡ ፓንክረስት ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. እጻፈው ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ሒስትሪ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (የኢትዮጵያ ፡ የኤኮኖሚክ ፡ ታሪክ) ፡ እትባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከ፲፱ ፡ ፡ ገጽ ፡ ጀምር ፡ ተመልከት ።

ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስከገባበት ፡ እስከ ፡ ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተቀነባ በረ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አልነበረም ።

ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በእስላም ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ለሚኖሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መምሪያ፡ እንዲሆን፡ወደ ፡ ፲፫ኛው፡ መቶ ፡ ዘመን፡ ግድም፡ በግብፅ ፡ ውስጥ፡ የተጻፈ፡ መንፈሳዊና፡ ዓለማዊ ፡ ነገሮችን፡ የሚመለከቱ፡ ከልዩ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ፡ በተራቀቀ፡ አኳኋን ፡ የተውጣጡ ፡ ሕጎች ፡ የተከማቹበት ፡ ነው [3] ። የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ኪዳን ሕጎችን ፡ ከሮማ ፡ ቤተክርስቲያንና ፡ ከእስላም፡ ትእዛዞች ፡ እንዲሁም ፡ ከኒቅያና ፡ ከአንጾኪያ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉባኤዎች ፡ ከተገኙ ፡ ውሳኔዎች ፡ ጋር ፡ አዋህዶ ፡ የያዘ፡ ሲሆን ፡ መጀመሪያ፡ በዐረብኛ፡ ተጽፎ [4] ፤ በኋላም ፡ ጥንታዊ ፡ ቋንቋ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተተርጉሞ፡ ክርስቲያኖች፡ በሚኖሩባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ አማካይነት፡ ይሠራበት ፡ ነበር [5] ። ስለወንጀሎች ፡ መጀመሪያ ፡ በሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ ስለወንጀለኛ ፡ አቀጣጥ ፡ ያሉት ፡ ክፍሎች ፡ ሃይማኖት ፡ ነክ ፡ ከሆነው ፡ ሁሉ ፡ እንደመደባለቅ ፡ ይላሉ [6] ። ይሁን ፡ እንጂ፡ በሕጉ ፡ የተጻፉት ፡ የወንጀለኛ፡

3. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ "በሦስት ፡ መቶ ፡ ሊቃውንት" ፡ ማለት ፡ "በሰላሳ ፡ ምዕት"፡ ወይም፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባቶች፡ እንደተጻፈ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማድ ይነገራል ። በቢንትር ፡ ፍራንሲ ፡ ዴ ፡ ድሩዋ ፡ ኮምፖሬ ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ታትሞ ፡ የወጣውን ፡ ከግራፎን ፡ የተጻፈውን ፡ አንትሩዳክሲዮ ፡ ለኮድ ፡ ፒናል ፡ ዴ ፡ ለኤምፓይር ዳኢትዮፒ (ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ) ተመልከት ። የዚህን ፡ የእንግሊዝኛና ፡ የአማርኛ ፡ ትርጉም ፡ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. የወጣውን የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺ ፡ እና ፡ ፪፻፹፮ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

4. ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከፐርሻም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፲፭፱ ፡ ተመልከት ።

5. አጥናሲዮ ፡ ጉዲ ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. በኦፕፎስ ፤ መጽሔተ ፡ ቋንቋ ፡ በተረጐመው ፡ በስተቀር ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አሁንም፡ ሲሆን፡ የሚገኘው ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ፡ ብቻ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ በማስተርጐም ፡ ላይ ፡ ነው ። ተርጓሚውም ፡ ባለ ፡ ፖለቲካል ፡ ሳይንስና ፡ ባለሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ዶክተር ፡ የሆኑት ፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ፃድዋ ፡ ናቸው ።

6. ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮችን ፡ የያዙ ፡ ክፍሎች ፡ ሲኖሩት ፤ የመጀመሪያው ፡ ክፍል፡ ስለ ሃይማኖት ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ ነው ። በመሠረቱ (ፍትሐ ነገሥቱ) ፡ ሃይማኖት ፡ ጠቀስ ፡ የሆነው ፡ የዚህ ፡ ሥራ ፡ አቀነባበር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክፍሎም ፡ እንኳ ፡ ውስጥ ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ሰፍሮ፡ ይታያል፤ ለምሳሌ፡ የሚከተሉትን ፡ የምዕራፍ አርእስቶች ፡ እንመልከት ። ምዕራፍ ፡ ፵፩ ፡ "ታላቁን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለሚከድ ፡ ለሚያዋርድና ፡ ሌላ ፡ አማልክትን ፡ ለሚያመልክ ፡ የሚሰጥ ፡ ቅጣት" ። ምዕራፍ ፡ ፵፯ ፡ "ነፍስ ፡ መግደል ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት" ይላል ።

መቅጫ ፡ ዕንሰ ፡ ሐሳቦች ፡ ከጊዜው ፡ ሥልጣኔ ፡ በጣም ፡ የቀረመዱ ፡ ነበሩ ። [7]

የመጀመሪያው ፡ ዘመናዊ ፡ የተቀናባበረ ፡ ጽሑፍ ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ የ፲፱፻፳፪ቱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እስከታወጀበት ፡ (ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እስከ ፡ ነገሡበት ፡ ቀን) ፡ እስከ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፤ ፍትሐ ፡ ነገሥትና ፡ በተለይም ፡ ክርስቲያን ፡ ባልሆኑት ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀለኞች ፡ የሚቀጡበት ፡ ሕግ ፡ ሁነው ፡ ቆዩ ። አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይሆን ፡ የማያሻሙ ፡ ቅጣቶችን ፡ በግልጽ ፡ ለተጠቀሱና ፡ ለተወሰኑ ፡ ወንጀሎች ፡ ይደነግጋል ፤ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ የአጥፊው ፡ ማዕርግና ፡ ሐብት ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይና ፡ ዓላማ ፡ እየታየ ፡ ነበረ ። የወንጀላቸው ፡ መነሻ ፡ "ሕገ ፡ ወጥነት" ፡ "ትዕቢት" ፡ "ቅንዓት" ፡ "ተንኰል" ፡ " በቀል" ፡ "ስግብግብነት" ፡ "ጠበኛነት" ፡ " ግዴለሽነት" ፡ "ጨቋኝነት" ፡ የሆኑ ፡ ወንጀለኞች ፡ ቅጣታቸው ፡ አነስተኛ ፡ ሲሆን ፡ ማዕረግና ፡ ሐብት ፡ ያላቸው ፡ አጥፊዎች ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ ይወድቅባቸው ፡ ነበር ።

7. በሙቀ ፡ ስለማተፋትና ፡ በቸልተኝነት ፡ ስለማጥፋት ፡ ዕንስ—ሐሳቦች ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እንደሚከተለው ፡ ያትታል (ምዕራፍ ፡ ፵፪) ፤

ክፍል ፡ ፩ ፡— የዱር ፡ አውሬ ፡ ለመግደል ፡ ወይም ፡ ለመምታት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለመግደል ፡ ወይም ፡ ለመምታት ፡ ሐሳብ ፡ ወይም ፡ ፍላጐት ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ የሚመለከት ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰውዬ ፡ ሌላ ፡ ሰውን ፡ ቢገድል ፤ ጉዳዩ ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ እስተያየት ፡ ይመረመራል ። የመጀመሪያው ፤ አደጋ ፡ ሲደርስ ፡ እንደሚችል ፡ የሚያውቀውን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከታል ፤ . . . . ማለት ፡ መሐል ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ እተሰበሰቡ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ወፍ ፡ ወይም ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ በር ፡ ወይም ፡ ርጦ ፡ ሲደባለቅ ፡ እያየበወ ፡ ወይም ፡ በአውሬው ፡ ላይ ፡ ቀስትን ፡ እንደሚተኩስ ፡ ያለን ፡ ሰው ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሰው ፡ የገደለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ፍላጐቱ ፡ ሰው ፡ ለመግደል ፡ ባለመሆኑ ፤ . . . ያለፈቃዱ ፡ ሰው ፡ እንደገደለ ፡ ሆኖ ፡ ተቆጥሮ ፡ ይፈረድበታል ። ወንጀሉም ፡ በሙቀ ፡ ወይም ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ከገደለ ፡ ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ ያነሰ ፡ ነው ። እንዲሁም ፤ የእጥርን ፡ ወይም ፡ የቤቱን ፡ ግድግዳ ፡ ባለመቆጣጠር ፡ ተንዶ ፡ ሰው ፡ ሲጐዳ ፤ ከቶ ፡ ባሪያውን ፡ ተናካሽ ፡ አውሬዎቹን ፡ ተራጋጭ ፡ ዐቅሎቹንና ፡ ገመሎቹን ፤ ተዋጊ ፡ በሬዎቹን ፡ በደንብ ፡ ሳይጠብቅ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ እነዚህ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ቢያደርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ያለፈቃዱ ፡ እንዳጠፋ ፡ ሆኖ ፡ ተቆጥሮ ፡ ይፈረድበታል ። በመሳም ፡ ሕግ ፤ ከአብጥሊስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፵፰ ፡ ጋር ፡ ከሚተካከለው ፡ ምዕራፍ ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ እንደተጻፈው ፤ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ጉድጓድ ፡ ቆፍረው ፡ ሳይደፍኑ ፡ የተወና ደረጃ ፡ ሠርተው ፡ ድጋፍ ፡ ሳይሠሩለት ፡ የቀሩ ፡ ያለፈቃድ ፡ እንዳጠፉ ፡ ሰው ፡ ይቀጣሉ ። ሁለተኛው ፡ ዐይነት ፡ ደግሞ ፤ ሲገሉ ፡ መኖሪያቸውን ፡ የማያውቁ ፡ ሰዎችን ፡ ይመለከታል ፤ ማለት ፡ ከብት ፡ መታሁ ፡ ብሎ ፡ በድንገት ፡ ሳያይ ፡ ሰው ፡ እንደሚመታ ፤ ወይም ፡ በበረት ፡ ሰው ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ እንደሚተኩስ ፡ የማይናድ ፡ ጠንካራ ፡ የመሰለውን ፡ ግንብ ፡ በድንገት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እንደሚንድ ፡ ሰው ፡ ያሉትን ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ ዓይነት ፡ የተማታ ፡ ወይም ፡ የገደለ ፡ ቅጣቱ ፡ ከሠገር ፡ መሰደድ ፡ (መውጣት) ፡ ነው ፤ ከቶ ፡ ባሪያ ፡ አደገኛ ፡ አውሬ ፡ እንዳለው ፡ የማያውቅም ፡ ሰው ፡ ባሪያው ፡ ወይም ፡ አውሬው ፡ ጉዳት ፡ ባደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ባሪያውን ፡ ወይም ፡ አውሬውን ፡ ለተጐዳው ፡ ዘመዶች ፡ አሳልፎ ፡ ከመስጠት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ኃላፊነት ፡ የለበትም ። ጉድጓድ ፡ የቆፈረውም ፡ ደረጃ ፡ የሠራውም ፡ እንዲሁ ፡ ከኃላፊነት ፡ ነፃ ፡ ነው ። ከአባ ፡ አውሎስ ፡ ፃድቅ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተረጐመ ።

የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡ ተብሏል [8] ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ይህን ፡ ማረጋገጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ሕጎች ፡ ሲነፃጸሩ ፡ በተለይም ፡ እያንዳንዱን ፡ ወንጀልና ፡ ቅጣቱን ፡ በግልጽ ፡ በሚያትተው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ትልቅ ፡ ልዩነት ፡ ይታይባቸዋል ። የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በጊዜ ፡ ቀደምትነት ፡ ካለው ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ቢሆንም ፡ ያልተብራራና ፡ በተወሰነ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ የሚመራ ፡ የሆነ ፡ በደንብ ፡ የተገለጹ ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦችና ፡ ስለወንጀለኞች ፡ ውሳኔና ፡ አስተያየት ፡ የተሟላ ፡ አቀራረብ ፡ የጐደሉት ፡ ነበር ።

ከነፃነት ፡ መመለስ ፡ ወዲህ ፡ ባሉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጎች ፡ ከታወጁ ፡ በኋላ ፡ በሥልጣኔ ፡ የምትገሠገሥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ ችግሮችን ፡ ለማስወገድ ፡ አዲስ ፡ የተሟላ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መንደፍ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ግልጽ ፡ ሆነ ። በጀኔቭ ፡ (ስዊዘርላንድ) ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሊቀ ፡ መምህርና ፡ የካሳሲዮን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የሆኑት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዣን ፡ ግራቨን ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንዲነድፉ ፡ አላፊነትና ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጣቸውና ፡ ሥራው ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ተጀመረ ። ፕሮፌሰር ፡ ግራቨን ፡ በፈረንሳይኛ ፡ የጻፉትን ፡ ረቂቅ ፡ (አባን ፡ ፕሮጀ) የታወቁ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ለነበሩበት ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ (የሕግ ፡ አዘጋጅ) ፡ አስረከቡ ። ብዙ ፡ ውይይትና ፡ ማሻሻል ፡ ተደርጎ ፡ የመጨረሻው ፡ ጽሑፍ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ሕጉ ፡ ወደ ፡ አማርኛና ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ [9] ፡ ተተርጉሞ ፡ ለፓርላማ ፡ ተሰጠ ። አዲሱ ፡ ሕግ ፡ መልካም ፡ ፈቃዳቸ

8. ከወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከጠቅላላ ፡ መሠረተ — ሐሳብ ፡ መካከል ፡ የሚከተሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣን ፡ ይጠቅሳሉ ።

፲፭ ፡ ጌታችንም ፡ በወንጌል ፡ ብዙ ፡ የሚያውቅ ፡ በብዙ ፡ ይቀጣል ፡ ጥቂት ፡ የሚያውቅ ፡ ግን ፡ በጥቂቱ ፡ ይቀጣል ፡ ብሏል ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፶፰ ።

፲፮ ። ሥለሱቱ ፡ ምእትም ፡ እንደ ፡ አእምሮው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ ሰውን ፡ መቅጣት ፡ እንዳይገባ ፡ አውቀው ፡ በሕፃንና ፡ በሰካር ፡ በዕብድና ፡ በዝንጉ ፡ ከሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ አእምሮ ፡ ባለው ፡ በትልቅ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ለይተውታልና ፤ ይህም ፡ ደንብ ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጋር ፡ እንዲስማማ ፡ ነው ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፵፯ኛ ውን ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፲ ፡ ተመልከት ።

9. የሕግ ፡ መጻሕፍትና ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በይፋ ፡ በኦፊሲዬል ፡ የሚታተሙት ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ቢኖር ፡ ትክክል ፡ ሆኖ ፡ እንደአዛዥ ፡ የሚወሰደው ፡ የአማርኛው ፡ እትም ፡ ነው ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፭ ፡ የአዋጅ ፡ ቁ. ፪ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ክፍል ፡ ፭) ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሲረቀቅ ፡ የተጻፈው ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር ፤ ይህንን ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋዎች ፡ መተርጐምና ፡ በሦስቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ የተጻፉትን ፡ ማስማማት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ችግር ፡ እንደሚፈጥር ፡ በቀላሉ ፡ መገንዘብ ፡ ይቻላል ።

ውን ፡ ለማግኘት ፡ ከፓርላማ ፡ ወደ ፡ ግርማዊነታቸው፡ ቀረበና፡ በሐምሌ፡ ፲፮፡ ቀን፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ታውጆ ፡ ከሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ተደረገ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ፰፻፷፭ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫና ፡ የደምብ ፡ መተላለፍ ፡ አንቀጾችን፡ ይዟል ። ይኸ ፡ ሕግ፡ ከጥንት፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን፡ የሕግ፡ ልማድ [10] ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከወጡት ፡ ከአውሮጳ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ አዳዲስ ፡ ሕጎች ፡ አብዛኛዎቹን ፡ አዋህዶ ፡ የያዘና ፡ የተራቀቀ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ከውጭ ፡ አገር፡ ሕጐች ፡ ውስጥ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ዋና ፡ ምንጮች ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፴፯፡ የወጣው ፡ የስዊዝ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ የነበረው ፡ የሲዊዝ ፡ የሕግ ፡ ፍልስፍናና ፡ ዕውቀት ፡ (የሕግ ፡ ሳይንስ ፡ ጥናት ፡ ጁሪስፕሩደንስ) ፡ እንደሆኑ፡ ግልጽ፡ ነው [11] ። የሁለተኛነትንም ፡ ደረጃ ፡ የያዙ ፡ ሌሎች ፡ ምንጮች ፡ አሉ ፤ ከእነሱም፡ ቀዳሚ ፡ የሆኑ፡ የ፲፰፻፲፡ (እ.ኤ አ.) የፈረንሣይ ፡ የወ

10. ከኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ ተወርሰው፡ አሁንም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው፡ ሕግ ፡ የሚገኙት ፡ ቅጣቶች ፡ ወንጀለኛ ፡ ለሌላው ፡ መቀጣጫ ፡ እንዲሆንና ፡ ወንጀሉን ፡ በመቀጣቱ ፡ እንዲከስ ፡ የሚያደርጉት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥርዐቶች ፤ የሞትና ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ወንጀሎችና ፡ በጠቅላላ ፡ ክፍሉ ፡ የሚገኙ ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፤ እንደ ፡ መጸጸት ፤ በሕግ ፡ ላይ ፡ መሳሳትና ፡ ቅጣትን ፡ የሚያከብዱና ፡ የሚያቃልሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ያሉ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቅሉ ፡ በአውሮፓውያኖችም ፡ ዘንድ ፡ ያልታወቁ ፡ ባይሆኑ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ የተወረሱ ፡ ናቸው ። እላይ ፡ የጠቀስነው ፤ ግራቨን ፤ ከገጽ ፡ ፰፯ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ላይ ፡ የዚሁ፡ እንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፰ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እንዲሁም ፡ በዣ ፡ ግራቨን ፡ የተጻፉትን "ሾር ፡ አ፡ ኑቦው ፡ ድሮዋ ፡ ፔናል ፡ ኢትዮጲዬን ፡ ደላ፡ፓር፡ እንሲያን፡ አላ ፡ ፐር፡ ሬይሳንት፡ ሊጅስላሲዩ፡ ዱ ፡ ምንድ" ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ዴ ፡ ክሪሚኖሎጂ ፡ ኤ ፡ ዴ ፡ ፖሊስቴክኒክ ፡ ፳ኛ፡ ቦልዩም፡ ገጽ ፡ ፪፻፶ — ፺፱ ፡ (እ.ኤ. አ. ፲፱፻፷፭) ፡ እና ፡ "ለኢቶዮፒ ፡ ሞደርን ፡ ኤላ ፡ ኮዱፊካሲዮ ፡ ዱ ፡ ኑቮውድሮዋ" ፡ ሬቭ ፡ ፔናል ፡ ስዊስ ፡ ፹፪ኛ ፡ ቦልዩም ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፮-፺፯ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፮) ፡ ተመልከት ።

11. በፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉትን ፡ የኢትዮጵያንና ፡ የስዊዝን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍሎች ፡ በጥንቃቄ ፡ ሲያስተያዩአቸው ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረቱ ፡ የስዊዝ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ልዩነቱም ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ ይሀ ፡ ልዩነት ፡ የመጣው ፡ የሲዊዝ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ ጽሑፎችና፡ የሕግ፡ ሳያንስ ፡ ትምሀርት ፡ ከወሰዱት ፡ እርምጃ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። ኤፍ. ዞርቸር ፡ ኮዱ ፡ ፔናል ፡ ስዊስ ፡ ኤክስፖዜ ፡ ደሞቲፍ ፡ ደላቫ ፡ ፕሮዥ ፡ በሚል ፡ እርእስት ፡ ጽፎ ትረ ኤ. ጉቲየር ፡ በ፲፱፻፲፰ ፡ (እ. ኤ. አ.) ወደፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ፡ የተረጐመውን ፤ ፒ ፡ ሎጉዝ ፡ ኮሜንቴር ፡ ዱ ፡ ኮድ ፡ ፔናል ፡ ሲዊዝ ፡ (በስዊዝ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ሐተታ)፡ በሚል ፡ እርእስት ፡ በ፲፱፻፴፱ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፈውን ፤ ቶርማንና ፡ ፎን ፡ አፈርርቤክ ፡ ሽዋይትዘርሽስ ፡ ሽትራፍ ፡ ጌዜትስቡኽ ፡ በሚል ፡ እርእስት ፡ በ፲፱፻፵ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፉትንና ፡ ሐፍተር ፡ ሌርቡኽ ፡ ዴስ ፡ ሽዋይትዘርሽን፡ ሽትራፍሬክትስ፡ አለገማይነር ታይል በሚል እርእስት በ፲፱፻፵፮ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፈውን ፡ ተመልከት ።

ንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (በጠቅላላ ፡ አዘገጃጀት ፡ ረገድ) ፤ [12] የ፲፱፻፶፭ ፡ (እ. ኤ. አ.) የዩጐዝላቪያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (በወታደራዊ ፡ ወንጀሎችና ፡ በመሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ በኩል) ፤ በተጨማሪም ፡ የኖርዌ ፡ (፲፱፻ ፪ ፡ እ. ኤ. አ.) ፡ የጣሊያን (፲፱፻፴ ፡ እ. ኤ. አ.) ፡ የፖላንድ (፲፱፻፴፪ ፡ እ. ኤ. አ.) የብራዚል ፲፱፻፵ እ. ኤ. አ.) እና ፡ የግሪክ ፡ (፲፱፻፶ ፡ እ. ኤ. አ.) ሕጎች ፡ ናቸው ። [13]

የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ውይይት ፡ ሲያደርግ ፡ ከተጻፉት ፡ ማስታወሻዎች [14] ፡ ሌላ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፤ ሕግ ፡ ለመሆን ፡ እንዴት ፡ እንደበቃ ፡ የሚገልጽ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የተጻፈ ፡ ታሪክ ፡ የለውም ። አርቃቂው ፡ ሕጉን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ የተጠቀሙበትን ፡ ማስታወሻ ፡ ወይም ፡ መጨረሻ ፡ ለወጣው ፡ ጽሑፍ ፡ ምንም ፡ መግለጫ ፡ አልሰጡም ። እንደዚሁም ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የፓርላማ ፡ መዝገቦች (ቃለ ፡ ጉባኤ) ፡ አይገኙም ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ባዲስ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የሚያሻሙ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዴት ፡ መተርጐም ፡ ይገባቸዋል ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይፈጠራል ። የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪ ፡ የሕግ ፡ ትርጓሜ ፡ አጋጊው ፡ (ሕግ ፡ ሰጪው) ፡ "ሕጉን ፡ ለመስጠት ፡ በፈለገው ፡ ስሜት ፤ ሊደርስበት ፡ ካሰበው ፡ ግብ" ፡ እና ፡ " በሕጉ ፡ መንፈስ" ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ይወስናል ። ሕጎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚተረጐሙና ፡ ጽሑፎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚብራሩ ፡ ከሚወስኑ ፤ በብዙም ፡ ተቀባይነትን ፡ ካገኙ ፡ ሐሳቦች [15] ፡ በስተቀር ፡ የስዊስ ፡ ሕግ ፡ በግልጽ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ በሆነበት ፡ ሥፍራ ፡ የስዊስ ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ፍልስፍናና ፡ ገላጭ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ እንደ ፡ ከፊል ፡ የአጋጊ ፡ ፍላጐት ፡ ተቆጥረው ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ መተርጐሚያ ፡ ያገለግሉ ፡ ይሆን ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይቀራል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ጠቅላላው ፡ ሐሳብ ፡ በአስገዳጅነት ፡ ሥልጣን ፡ ባይሆንም ፡ በአግባቢነት ፡ መንፈስ ፡ የስዊስን ፡

12. የፈረንሣይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ከፍተኛ ፡ ወንጀሎች ፡ ጥፋቶችና ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ በሚል ፡ አኳኋን ፡ በሦስት ፡ የተከፈለ ፡ ሲሆን ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሳይከተል ፤ ከፍተኛ ፡ ወንጀሎችንና ፡ ጥፋቶችን ፡ አጠቃልሎ ፡ መጀመሪያ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ፪ኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ በመባልና ፡ የደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ኮንትራቫንሲዮ) ፡ በመባል ፡ ብቻ ፡ ተከፍሏል ።

13. ፒ. ግራቨን ፡ <u>አን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ክሪሚናል ፡ ሎው</u> ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፲፱፻፷፭ . (እ . ኤ . አ.) የጻፈውን ፡ ተመልከት ። ሚስተር ፡ ኢስ ፡ ቴዲቪ ፤ በ፲፱፻፷፮ ፡ (እ. ኤ. አ.) በሚያወጣው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የኢጣሊያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጠቃሚ ፡ የአውሮፓዊ ፡ ንቅዕ ፡ መነሻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ጠበቅ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ አቅርቧል ።

14. እነዚህ ፡ ማስታወሻዎች ፡ በሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ልጅ ፡ ኤም . ፊሊፕ ፡ ግራቨን ፤ በፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፈው ፡ የተያዙ ፡ ሲሆኑ ፡ እስካሁን ፡ ገና ፡ አልታተሙም ።

15. ከቨችኖቪች ፡ <u>በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፩ ፡ (፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም.) "በአዋጅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ትርጉም (ፍች) በኢትዮጵያ" ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ የጻፈውን ፡ ተመልከት ። የአማርኛው ፡ ትርጉም ፡ ገጽ ፡ ፪፻፬ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የሕግ ፣ ዕውቀት ፣ ፍልስፍና ፣ በሙሉ ፣ ከመቀበል ፣ አንስቶ ፣ ጭራሹን ፣ የስዊስ ፣ ምንጮችን ፣ ችላ ፣ እስከማለት ፣ ቢለያይ ፣ የዚህ ፣ ጽሑፍ ፣ ደራሲ ፣ አንድ ፣ ተግቢ ማዕከላዊ ፣ ይዞታ ፣ እንደሚገኝ ፣ ያምናል ።

በስዊስ ፣ ጽሑፎች ፣ ስለ ፣ መጠቀም ፣ በባለሥልጣኖች ፣ የተሰጠ ፣ መምሪያና ፣ ስለሕጉ ፣ አወጣጥ ፣ የተጻፈ ፣ ታሪክ ፣ የለም ። ስለዚህ ፣ ተመሳሳይ ፣ ድንጋጌዎች ፣ ሲነፃጸሩ ፣ የስዊስ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ለኢትዮጵያ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ሕግ ፣ ምንጭ ፣ መሆኑ ፣ ግልጽ ፣ ከሆነና ፣ የሕግ ፣ አርቃቂው ፣ ፍላጐት ፣ ሕጉ ፣ ሲወጣ ፣ የተደረገው ፣ ክርክር ፣ እምብዛም ፣ በመሆኑ ፣ የሕግ ፣ አውጭው ፣ ፍላጐት ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ ሊቆጠር ፣ ስለሚችል ፣ ከዚህ ፣ ፍላጐት ፣ አዛብቶ ፣ ለመተርጐም ፣ የኢትዮጵያን ፣ የሕግ ፣ መስፋፋት ፣ እርምጃና ፣ የሕገሪቱን ፣ ልዩ ፣ ፍላጐት ፣ የሚመመለከቱ ፣ ደምበኛ ፣ ምክንያቶች ፣ ካልቀረቡ ፣ በስተቀር ፣ ለስዊስ ፣ ሕግ ፣ የሚሰጠው ፣ ትርጉም ፣ ለኢትዮጵያም ፣ ሕግ ፣ መሰጠት ፣ ይገባዋል ። የሕግ ፣ አርቃቂውም ፍላጐት ፣ በይበልጡን ፣ የሕጉ ፣ ትርጉም ፣ በስዊስ ፣ እንዳለው ፣ እንዲሆን ፣ መሆኑን ፣ ማሰብ ፣ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ሕጋዊና ፣ ማኅበራዊ ፣ ፍላጐት ላይ ፣ የተመሠረቱ ፣ አፍራሽ ፣ ምክንያቶች ፣ ከሌሉ ፣ ከ፲፱፻፵፱ ፣ ዓ. ም. በፊት ፣ የነበረውን ፣ የስዊስን ፣ ትርጉም ፣ መከተል ፣ ይገባል ፣ የሚል ፣ ግምት ፣ ይፈጠራል።

የስዊስ ፣ ታሪክና ፣ ዘመናዊ ፣ መስፋፋት ፣ ከኢትዮጵያው ፣ በጣም ፣ የተለየ ፣ ቢሆንም ፣ ይህን ፣ ዓይነቱ ፣ አስተያየት ፣ ለሕጉ ፣ አተረጓጎም ፣ የተወሰነ ፣ እርግጠኛነት ፣ ሊያስገኝና ፣ ዳኞችም ፣ እንዳሻቸው ፣ እንዳይፈርዱ ፣ ለመቆጣጠር ፣ ያስችላል ።

ይኸንን ፣ በምሳሌ ፣ ለመረዳት ፣ ሳይቻል ፣ አይቀርም ። "ሊፈጸም ፣ ስለማይቻል ፣ ወንጀል" ፣ በሚናገረው ፣ በኢትዮጵያ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ በቁ. ፩፻፬ ፣ ውስጥ ፣ አንድ ፣ ወንጀል ፣ ሊፈጸም ፣ በፍጹም ፣ የማይቻል ፣ ከሆነ ፣ ፈራጅ ፣ ቅጣቱን ፣ እንዲያቃልል ፣ ይፈቀድለታል ። "ፍጹም ፣ የማይቻል" ፣ ምን ፣ ማለት ፣ እንደሆነ ፣ ግልጽ ፣ አይደለም ፤ ስለ ፣ ጉዳዩም ፣ በሕግ ፣ አውጭው ፣ የተሰጠ ፣ ሐተታ ፣ የለም ። ስለዚህ ፣ የነዚህን ፣ ቃላት ፣ ትርጉም ፣ ዳኞች ፣ እንዲፈጥሩ ፣ ከመፍቀድ ፣ ይልቅ ፣ በስዊስ ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ ተመሳሳይ ፣ ቃላት ፣ እንዳሉ ፣ ከ፲፱፻፵፱ ፣ ዓ. ም. በፊት ፣ የነበሩትን ፣ የስዊስን ፣ ጽሑፎች ፣ ማመሳከር ፣ ያስፈልጋል ። "በፍጹም ፣ የማይቻል" ፣ የሚሉት ፣ ቃላት ፣ በስዊስ ፣ ሕግ ፣ ተመሳሳይ ፣ አንቀጽም ፣ ውስጥ ፣ ይገኛሉ ። [16] የስዊስ ፣ የሕግ ፣ ዕውቀትና ፣ መግለጫ ፣ ጽሑፎች ፣ [17] ሲመ

16. የስዊዝ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቁ.፩፻፬ ።

17. እላይ ፣ የሰጠነውን ፣ የግርጌ ፣ ማስታወሻ ፣ ቁ.፲፩ ፣ እና ፣ እንዲሁም ፣ ሬቡይ ፣ ኢፈሲያል ፣ ፳፯ ፣ አራተኛ ፣ ገጽ ፣ ፺፰ ፣ ዠርናል ፣ ዴ ፣ ትሪቪዩናል ፣ (እ. ኤ. አ.) ፲፱፻፶፱ ፣ ገጽ ፣ ፳፯ ፣ ሬቡይ ፣ ኢፈሲየል ፣ ፳፰ ፣ አራተኛ ፣ ገጽ ፣ ፺፯ ፣ ዠርናል ፣ ደትሪቢዩን ፣ (እ. ኤ. አ.) ፲፱፻፷ ፣ ገጽ ፣ ፶፰ ፣ ሬቡይ ፣ ኢፈሲየል ፣ ፹፫ ፣ አራተኛ ፣ ገጽ ፣ ፺፩ ፣ ዠርናል ፣ ዴ ፣ ትሪቢዩን ፣ (እ. ኤ. አ.) ፲፱፻፶፰ ፣ ገጽ ፣ ፪ ፣ እና ፣ ኤም ፣ ቫይብሊንገር ፣ "ላቴንታቲቭ ፣ ፫ኛ" በሚል ፣ አርእስት ፣ ሬቪ ፣ ፔናዲክ ፣ ስዊስ ፣ ቁ. ፩ሺ፸፱፻፩ ፣ ኦክቶበር ፣ ፲፱፻፶፪ ፣ (እ. ኤ. አ.) ውስጥ ፣ ተመልከት ።

ሪምሩ ፡ “ፍጹም” ፡ “ከተመዛዛኝ” ፡ ከማይቻል ፡ ጋር ፡ የተነጻጸረ ፡ መሆኑን ፡ ይረዷል ። አንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁናቴዎች ፡ በአንዱ፡ ክፍል ፡ ሲመደቡ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በሌላው ፡ ይመደባሉ ፡ አግጋቢ ፡ የሆኑ ፡ ተቃራኒ ፡ ምክንያቶች ፡ ካልኖሩ በቀር ፡ ለነዚህ ፡ ቃላት ፡ በስዊስ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ትርጉም ፡ መቀበል ፡ ይገባል ። ፍጹም ፡ እንደማይቻል ፡ ሲያውቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ ቢሞክርና ፡ ቢያቅተው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወንጀሉ ፡ በማንም ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻል ፡ ቢሆን ፡ የሞከረው ፡ ውስጣዊ ፡ ሐሳብ ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞት ፡ ወንጀል ፡ ለመፈጸም ፡ እንደቻለው ፡ ሰው ፡ አደገኛ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀለኞች ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቁ ፡ የማድረግ ፡ ተግባር ፡ እንዲስፋፋና ፡ እንዲያድግ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ወንጀሉን ፡ እንደፈጸሙ ፡ ያህል ፡ እንዲ ቆጠሩ ፡ ያስፈልጋል፡ ተብሎ ፡ ይታሰብ ፡ ይሆናል ። እነዚህ፡ ምክንያቶች “ፍጹም” የሚለው ፡ ቃል ፡ በጣም ፡ ጠባብ ፡ ትርጉሚ፡ እንዲያገኝና ፡ የወንጀሉ ፡ ለመፈጸም፡ አለመቻል ፡ የሚያስገኘውን ፡ ከፊል ፡ መከላከያ ፡ እንዲወስን ፡ ያደርጋሉ ። እንደ ዚህ ፡ ያሉት ፡ ምክንያቶች ፡ የስዊስን ፡ የሕግ ፡ ዕውቀትና ፡ ፍልስፍና ፡ እንቀበል ፡ ከሚለው ፡ ግምት ፡ ያመዝኑና ፡ በፍጥነት ፡ የሚለዋወጠው ፡ የሕግ ፡ አቅድ ፡ እንዳ ስፈለገው ፡ እንዲንቀሳቀስ ፡ ይረዳሉ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንዲታወጅ ፡ የተደረገው ፡ ለአገሪቱ ፡ ብሔ ራዊ ፡ አንድነት ፡ ማጠንከርያና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለሚያደርጉት ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ መምሪያ ፡ እንዲኖር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ሕዝቡ ፡ በጊ ዜው ፡ እንደዋና ፡ የማኅበራዊ ፡ ቁምነገር ፡ አድርጎ ፡ ከሚቆጥራቸው ፡ ነገሮች ፡ ከራቀ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውል ፡ ይቆይና ፡ እንዲያውም ፡ የሚ ፈለጉት ፡ ማኅበራዊ ፡ ቁምነገሮች ፡ የቆሙበትን ፡ መሠረት ፡ የሚያጥውጽ ፡ ይሆ ናል [18] ። ስለዚህ ፡ በሕግጋቱና ፡ በመስፋፋት ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ማኅበራዊ ፡ ቁምነገሮች ፡ መካከል ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ለመፍጠር ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገ ባል ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይፈጠራል ።

በዚህ ፡ ረገድ ፡ የአዲሱ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መጀመር ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ከእሥር ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ዓመታት ፡ በሚያህል ፡ ጊዜ ፡

18. አንዳንድ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቃለሉ ፡ ዕንስ - ሐሳቦች ፡ በተለይም ፡ ስለተበዳይ ፡ ፈቃድ ፡ በመላ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተንዣርጐ ፡ የሚገኘው፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ስለማይደረግ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላ ደረሱ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎችን፡ የሚመለከት ፡ ለፈተና፡ ስለሚለቀ፡ ጊዜ፡ (ውሳኔውን ፡ ስለማገድ) ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለመፍታትና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ በልዩው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ወንጀሎች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አዲስ፡ ናቸው ። ሌሎች ፡ መሠረተ—ሐሳቦች ፡ ደግሞ ፡ እንደ የዳኝነት ፡ ሥልጣንን ፡ የወንጀል ፡ ሥራን ፡ መሞከርን ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ መሆንን ፡ ማጥፋትን ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ አላፊነትንና ፡ የወንጀል ፡ ሥራዎችን ፡ መጣመርን ፡ የሚመለከቱ፡ አዲጋች ፡ በመሆናቸው ፡ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ ገና ፡ አልታወቁም ።

ውስጥ ፡ የገዛራሳቸውን ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብና ፡ ሕግጋቱም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውሉ ፡ የማይለዩትን ፡ ችግሮች ፡ ያጠኑና ፡ የሠለጠኑ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ በብዛት ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እየተስፋፉ ፡ በሚ፥ድ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ማኅበርና ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ መምህራን ፡ ሥፍራ ፡ ይዘው ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ በሕዝቡ ፡ እንዲታወቅና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ ይረዳሉ ።

ይኸ ፡ ብቻ ፡ ግን ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። በአውሮጳ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ እንደሚደረገው ፡ ሕግጋቱን ፡ ለማሻሻል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ የሕግ ፡ ኮሚቴዎች ፡ በፍጥነት ፡ እያደገ ፡ ከሚሄደው ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ ሕጐችን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲሄዱ ፡ ለማድረግ ፡ ሥራውን ፡ ያለማቋረጥ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ። በዳኝነት ፡ የሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ ረገድም ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ይዞታ ፡ መፈጠር ፡ አለበት ። ሕጐችን (በተለይም ፡ ከአውሮጳ ፡ የመነጩትን ፡) ከሚለዋወጠው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ በቂ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ የማድረግ ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ። ቢሆንም ፡ ወደፊት ፡ ሕጉ ፡ የሚያስከትለው ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ለመተንበይ ፡ ዳኞችን ፡ እንዳሰኛቸው ፡ እንደዳይፈርዱ ፡ ለመከልከል ፡ እንዲቻል ፡ በሕጉ ፡ በኩል ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ እርግጠኛነትና ፡ አቋም ፡ መኖር ፡ አለበት ። በእነዚህ ፡ ዘዴዎች ፡ አማካይነት ፡ አዲሶቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ ሥራቸውን ፡ ከሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ በበለጠ ፡ እንደሚዛመዱና ፡ ለአገሪቱም ፡ ተለዋዋጭ ፡ ፍላጐቶች ፡ አስፈላጊውን ፡ መፍትሔ ፡ እንደሚያቀርቡ ፡ ተስፋ ፡ ተጥሎባቸዋል ።

ለ/ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ አቅድ ፡ ውስጥ ፡ የቅጣት ፡ ዓላማዎች ።

የኢትዮጵያ ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ ፍልስፍና ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ በማስፈራራትና ፡ በመበቀል ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ይበልጡን ፡ የተመሠረተ ፡ ይመስላል ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ቅጣት ፡ እንደአጥፊው ፡ ሁናቴና ፡ እንደጥፋቱ ፡ መጠን ፡ ልክ ፡ እንዲሆን ፡ በከፊል ፡ በማድረጉ ፡ "ክፉ ፡ ለሠራብህ ፡ ክፉ ፡ መልስለት (ሌክስ ፡ ታሊዮኒስ)" ፡ ከሚለው ፡ ሕግ ፡ የተሻሻለ ፡ እርምጃ ፡ ቢወስድም ፡ አንዳንድ ፡ ሌሎች ፡ አሰቃቂ ፡ ቅጣቶችንና ፡ የመበቀልን ፡ ሐሳብ ፡ የተደገፉ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። እንደዚሁም ፡ የ፲፱፻፳፫

19. በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ በቁጥር ፡ ፫ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ፮) ቀጥሎ ፡ እንደተጻፈው ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ "የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ በሌሎችም ፡ በአንዳንድ ፡ መንግሥታት ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ። በአገራችንም ፡ ወደፊት ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ እንዲቀር ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ፈቃዳችን ፡ ቢሆን ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ ለሞት ፡ ፍርድ ፡ የማያደርስ ፡ አንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ ወንጀል ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ በግርፋት ፡ ፍርድ ፡ እንዲቀጡ ፡ እስካሁን ፡ የነበረውን ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ አጽንተን ፡ አቆይተነዋል" ።

ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እየአንዳንዱ ፡ ወንጀለኛ ፡ የአጠፋው ፡ ጥፋት ፣ ሰብአዊ ፡ ሁናቴውና ፡ አቅዋሙ ፣ ለጥፋቱ ፡ መነሻ፡ የሆኑት፡ ምክንያቶችና፡ ወንጀሉን ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ የአእምሮው ፡ ፍላጐት ፡ በይበልጥ ፡ እየ ታየ ፡ ቅጣቱም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ እንዲሆን ፡ ቢያደርግም ፤ ወንጀለኞች ፡ ወደ ጥፋት ፡ እንደገና ፡ እንዳይመለሱ ፡ የማረም ፡ ፍላጐት ፡ አልተገለጸበትም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለተበዳይ ፡ ወገኖች ፡ ደኅንነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አሳቢነት ፡ ነበረው ። ብዙ ፡ ዘመናውያን ፡ የቅጣት ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ያጡት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡ በጠቅ ላላው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቁ. ፲፰ ፡ እንዲሀ ፡ ይላል ፤ —

ስለ ፡ ስድብና ፡ ስለበትር ፤ ስለ ፡ አካል ፡ ጉዳይ ፡ ለተበዳዩ ፡ የሚከሰውና ፡ ስለ ፡ መቅጫ ፡ ለዳኝነት፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ድኃ ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ዳኛው ፡ ለመጠባበቂያ፡ ከሚያስቀምጠው ፡ ከመቅጫው፡ ገንዘብ ፡ ለተበ ዳዩ፣ ከፍሎ፣ በደለኛውን፣ አሥሮ ፡ ሥራ ፡ እያሠራ ፡ ካሣውንና ፡ መቅጫውን ፡ ያስከፍል። ለመጠባበቂያ ፡ የተቀመጠ፡ የመቅጫ፡ ገንዘብ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ መንግ ሥት ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

በመበቀል ፡ ላይ ፡ ቀድሞ ፡ የነበረው ፡ የከረረ ፡ ስሜት ፡ ዛሬ ፡ በመለወጥ ፡ ላይ ፡ ቢገኝም ፡ በቀልን ፡ የተመረኮዙ ፡ አንዳንድ ፡ ጸንተው ፡ የተመሠረቱ ፡ ቀዋሚ ነገሮች ፣ አሉ ፤ ከነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ ነው ። ከሰውነት ፡ ብልቶች ፣ አንዳንዱን ፡ በመቁረጥ ፡ ይፈጸም ፡ የነበረው ፡ ቅጣት ፡ ከተ ወሰኑ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ እንዲቀር ፡ ተደርጓል ። የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ ግን ፡ በ፲፱፻ ፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮ ፡ ይገኛል ። የዚሁ ፡ ሕግ ፣ ንዳፊ ፣ መጀመሪያ ፡ ከጻፋት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ አላስ ገቡም ፡ ነበር ። የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮንና ፡ ፓርላማ ፡ ግን ፡ ቅጣቱ ፡ እንዲ ጨመር ፡ አደረጉ ። የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ መጨመር ፡ በመደገፍ ፡ የተሰጡት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ ከቅጣት ፡ ልምድ ፡ ጋር ፡ ተስማሚነቱ ፡ በጣም ፣ የሚያ ሰቅቁ ፡ ወንጀሎች ፡ በተሠሩ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚፈጸም ፡ መሆኑና ፡ ሰዎችን ፡ ወደ ጥፋት ፡ እንዳይሔዱ ፡ የማድረግ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ነው ።[20] ፓርላማ ፡ ብዙ ፡ ከተከራከረበት ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ቁ. ፻፰ (ሀ) ፡[21] ሁኖ ፡ ገባና ፡ ከባድ ፡ ስርቆትና ፡ (ቁ. ፮፻፴፭ ፡ (፫)) ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ የወንበዴ ነት ፡ ሥራ ፡ (ቁ. ፮፻፴፮ (፩)) ፡ በተፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲሠራበት ፡ ተደ ረገ ። የጅራፍ ፡ ግርፋት ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸምባቸው ፡ ዕድሜያቸው ፡ በ፲፰ ፡ እና ፣

20. የፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ ኮሚሲዮን፣ የቃል፡ ውይይት (ፕሮሲ ፡ ቬርባል)፣ ሚያዝያ፣ ፱ ፡ ቀን፣ ፲፱፻፵፬ ፣ (እ. ኤ. አ.) ፣ ገጽ — ፫ ፣ የሕግ ፣ መወሰኛ ፣ ምክር ፣ ቤት ፣ ቃለ ፡ ጉባኤ ፣ ሐምሌ ፣ ፯ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፵፱ ፣ ዓ. ም. ጁላይ ፣ ፣ ፳ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፪ ፤ የመጨረሻው ፡ ውሳኔ ፡ ሐምሌ ፣ ፳ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፵፱ ፣ ዓ ፣ ም ፡ (ጁላይ ፣ ፲፩ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፶፪) ፣ ተመልከት ።

21. ፓርላማ ፣ የጨመረው ፣ መሆኑን፣ ለማስታወቅ ፡ " ሀ " የሚል ፡ ተጨማሪ ፡ ያለው ፣ ቁጥር ፣ ይህ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

በ፶ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ የሆኑ ፡ ወንዶች ፡ አጥፊዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ግርፋቱ ፡ ከዓርባ ፡ ጅራፍ ፡ መብለጥ ፡ የለበትም ። የሚፈጸመውም ፡ በሐኪሞች ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው ። ግርፋቱ ፡ የተቀጭውን ፡ ጤንነት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ የሚጥል ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ሐኪሙ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ግርፋቱ ፡ እንዲያበቃ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ። የግርፋትን ፡ ቅጣት ፡ በማራዘም ፡ "የሕዝብን ፡ መንፈስ ፡ ጸጥታ ፡ የሚነሱ" ብሎ ፡ በመደባቸው ፡ ሰባት ፡ ሌሎች ፡ ወንጀሎችን ፡ በሚሠሩ ፡ ላይ ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምባቸው ፡ የሚያውጅ ፡ አንድ ፡ ድንጋጌ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ወጥቷል ።[22]

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተወሰነው ፡ ቅጣት ፡ ፋንታ ፡ ግርፋትን ፡ ለመተካት ፡ እንደሚችልና ፡ ቅጣቱም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፳ (ሀ) መሠረት ፡ እንዲሆን ፤ ግን ፡ ከ፴ ፡ ጅራፍ ፡ እንዳይበልጥ ፡ ድንጋጌው ፡ ይናገራል ። የሞትም ፡ ቅጣት ፡ ባዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አልቀረም ፤ ይኸ ፡ ቅጣት ፡ በስቅላት ፡ መፈጸም ፡ እንዳለበትና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ከፈለገ ፡ ለሌሎች ፡ ምሳሌ ፡ እንዲሆን ፡ ስቅላቱን ፡ በይፋ ፡ ለመፈጸም ፡ እንደሚቻል ፡ ሕጉ ፡ ይደነግጋል ። (ቁ. ፻፲፮) ። ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልማድና ፡ የሕዝቡ ፡ ስሜት ፡ ነፍስ ፡ መግደልን ፡ እንደ ፡ ቤተሰብ ፡ ግል ፡ ጉዳይ ፡ ወደመቁጠርና ፡ የደም ፡ ካሣ ፡ በማስከፈል ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሚቹን ፡ በገደለበት ፡ ሁኔታ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዩን ፡ በመበቀል ፡ ተወስኖ ፡ እንዲቀር ፡ ወደማሰቡ ፡ ያዘነብላል ። እነዚህም ፡ ስሜቶች ፡ ጽኑ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ከተገዳዩ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አንዱ ፡ በተወሰነው ፡ ሥፍራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ የሰጠውን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በጠበንጃ ፡ ተኩስ ፡ ለመፈጸም ፡ ይፈቀድለት ፡ እንደ ነበር ፡ ይነገራል[23] ። ነገር ፡ ግን ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ በሆነና ፡ የተቀነሰ ፡ ኃላፊነት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ እንደማይደርስባቸውና ፡ ቁ. ፻፲፰ ፡ በልማድም ፡ ሆነ ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአን. ፶፬ ፡ መሠረት ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይስማማበት ፡ እንደማይፈጸም ፡ መታወቅ ፡ አለበት ።

22. የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (የቅጣት ፡ ሕግ) ፡ ድንጋጌ ፡ ቁ.፵፩ ። የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሕግ ፡ ሆነው ፡ የሚሠሩባቸውን ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ፓርላማ ፡ ሳያጸድቃቸው ፡ ብቻውን ፡ ሊያውጅ ፡ ይችላል ፡ ይላል ። ይኸም ፡ የሚሆነው ፡ አማካሪዎች ፡ ባልተሰበሰቡበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ መሆኑን ፡ ይኸው ፡ አንቀጽ ፡ ይገልጻል ። ፓርላማ ፡ በሚቀጥለው ፡ ስብሰባው ፡ የወጣውን ፡ ድንጋጌ ፡ ሊያጸድቅ ፡ ወይም ፡ ሊሽር ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፤ ግን ፡ በዚህኛው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ እርምጃ ፡ አልወሰደም ። ስለዚህ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይሠራበታል ፡ ብሎ ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ።

23. ከላይ የተጠቀሰው ፡ ፐርሃም ፡ ገጽ ፡ ፻፵፩ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ።

የ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. (እ.ኤ.አ. ፲፱፻፷፫-፷፬) ፡ ስታቲስቲክ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ፩፻፸፯ ፡ ሰዎች ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ሲጠበቁ ፡ ፴፱ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ተፈጽሞባቸዋል ፡፡ የዚሁም ፡ ምክንያት ፡ በከፊል ፡ ቅጣቱን ፡ ለመፈጸም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ ቅልጥፍ ፡ የሥራ ክንውን ፡ ባለመደረጉ ፡ ሊሆን ፡ ቢችልም ፤ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ይቅርታንና ፡ ምሕረትን ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣኑን ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚያደርገው ፡ ርኅራኄ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡፡ [24] ምንም ፡ እንኳን ፡ መበቀል ፡ በተለይም ፡ ሰውን ፡ ወደጥፋት ፡ እንዳይ ፡ ሄድ ፡ ማስፈራራት ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እንዳስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ተቆጥረውና ፡ በጣም ፡ ጉልተው ፡ ቢታዩ ፤ አዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ወንጀለኞችን ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄ ፡ በተመላበትና ፡ ይበልጥ ፡ ዘመናዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ማስተናገዱ ፡ እየተቃረቡ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፡፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ሕግ ፡ መንግሥት ፡ በወንጀል ፡ የተከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ ከጉዳት ፡ እንዲጠበቁ ፡ ከደነገጋቸው ፡ ሌሎች ፡ መከላከያዎች ፡ መሐከል ፡ ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነና ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በማሠቃየትና ፡ ሰብአዊ ፡ ባልሆነ ፡ ቅጣት ፡ እንደማይቀጣ ፡ ይወስናል ፡ (አን. ፶፩ና ፡ ፶፯) ፡፡

የ፲፱፻፵፱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ማስፈራራትን ፡ እንደ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ በማድረግ ፡ ቢያስቀርም ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግን ፡ ሐሳብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስገብቷል ፡፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ መቅድም ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ፤

- - - ማናቸውም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ፍትሕን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እያደጉ ፡ የሚሄዱትን ፡ አዳዲስ ፡ አሳቦች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ የአሳብ ፡ ምርመራን ፡ የአቀጣጥን ፡ ዕውቀቶች ፡ ጨምሮ ፡ ማሰብ ፡ የተገባ ፡ ነው ፡፡ ተገቢ ፡ የሚሆነውንም ፡ ፍትሕንና ፡ ነፃነትን ፡ ወንጀልን ፡ መከላከልንና ፡ መጨቆንን ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲውል ፡ ማድረግን ፡ የያዙትን ፡ የመሠረታውያኑን ፡ ነገሮች ፡ መንፈስ ፡ በመከተል ፡ ነው ፡፡ ቅጣት ፡ ግድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፤ ደግሞም ፡ "አጥፊ ፡ ሲቀጣ ፡ የሚያየው ፡ ብልህ ፡ ይሆናል" እንደተባለው ፡ ሁሉ ፡ ለሌላው ፡ አጥፊ ፡ ትምህርት ፡ እንዲሆነው ፡ ነው ፡፡

24. በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የዓመት ፡ ሪፖርት ፡፡ ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የምሕረት ፡ ወይም ፡ የይቅርታ ፡ ሥልጣን ፡ እታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁ. ፴፫ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ዋናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ፡፡

25. እታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፳፫-፴፪ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ዋናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ፡፡

ቁ. ፩ ፡ የሕጉን ፡ ግብና ፡ ዓላማ ፡ ሲናገር ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመል ካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግና ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሔድ ፡ ማድረግ ፡ የቅ ጣት ፡ ሕግ ፡ መሠረታውያን ፡ ዓላማዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ያረጋግጣል ።

በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ አያሌ ፡ ቁጥሮች ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመ ልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግን ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል፡ ለማድረግ ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ። ዳኛው ፡ ቅጣት ፡ በመምረጥ [25] ፡ ረገድ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ የማድረግ ፡ ሰፊ ፡ መብት ፡ ተሰጥቶታል ፤ በተለይም ፡ በቁ. ፻፯ ፡ ዳኛው ፡ ቅጣት ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ እንዲያደርግ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተሰጥቶታል፤ ፤—

> ቅጣት ፡ ሊወሰን ፡ የሚገባው ፤ ፡ ያጥፊውን ፡ ያደገኛነት ፡ ጠባይ ፡ እን ደመጠኑ ፡ በመገመት ፤ ያለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ለማጥፋት ፡ ያነሣሡ ትን ፡ ምክንያቶችና ፡ ያሳቡን፡ ዓላማ፤ የግል ፡ ኑሮውን ፡ ሁኔታና ፡ የትምህ ርቱን ፡ደረጃ ፤ እንዲሁም ፡ የጥፋቱን ፡ ከባድነትና ፡ ያፈጸጸሙን ፡ ሁኔታ ዎች ፡ በመገመት ፡ በራሱ ፡ አጥፊነት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ የቅጣት፡ አሰጣጥ ፡ መለኪያዎች፡ ወንጀለኛውን፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳሉ ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ስለቅጣት ፡ መታገድ ፡ ለፈተና ፡ ስለሚሰጥ ፡ ጊዜና ፡ ለአመክሮ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ስለመፈታት ፡ ያወሳል ። ዘመናዊውንም ፡ መንፈስ ፡ በጣም ፡ በተ ደገፈ ፡ አነጋገር ፡ "ለአመክሮ ፡ የመልቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በቅጣቱ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የተቀጭውን ፡ ጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ወደ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ መመ ለሻ ፡ ሆኖ ፡ መቆጠር ፡ ይገባዋል" (ቁ. ፪፻፭) ይላል ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ ወጣቶች ፡ አጥፊዎች ፡ እንዲታረሙ [26] ፡ የተለየ ፡ ቅጣቶችን ፡ ለሚሠሩት ፡ ወንጀል ፡ ኃላፊ ነት ፡ የሌላቸውም ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲ ሰጥ፡ በሁለት፡ በሁለትዓመት፡ቢደረግም (ቁ ፻፴፮) ፡ ላልተወሰነ፡ ጊዜ፡ በልዩ፡ በታ፡ እንዲጠበቁ ፡ ያዝዛል ። የጥበቃው ፡ ጊዜ፡ አለመወሰን ፡ አጥፊው፡ እንደገና ፡ ለመ ልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግ ፡ መሠረት ፡ ሐሳቦች ፡ በተሟላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ይረዳል ። ሰውን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ ማስፈራራትን ፡ እንደዋና ፡ ዓላማቸው ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ ተራ ፡ ቅጣቶች ፡ ግን ፡ ይኸንን ፡ ሊፈ ጽሙ ፡ አይችሉም ፤ ምክንያቱም ፡ ሕግ፡ ሰጭው፡ የያንዳንዱን ፡ ወንጀል ፡ አስጊነት በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ስለአይደራጃቸው ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሰው ፡ የተፈረደበት ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ ሳያልቅ ፡ መፈታት ፡ የሚገ ባው ፡ ቢሆንም ፡ እንደታሠረ ፡ መቆየት ፡ አለበት ፤ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ ወንጀል ፡ እን

26. አታች ፡ ከግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፶፭ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ቀኖናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

ደገና ፡ የመፈጸም ፡ አዝማሚያ ፡ ቢኖረውም ፡ የተፈረደበት ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፡ መፈታት ፡ አለበት ። የሆነው ፡ ሆኖ፣ ሁለቱም ፡ ሐሳቦች፣ ማለት ፡ ሰውን ወደጥፋት ፡ እንዳይሄድ ፡ ማድረግና ፡ ወንጀለኛው ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግ ፡ በሕጉ ፡ የተጉለጹ ፡ የቅጣት ፡ ግቦች ፡ መሆናቸውንና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አንዱ ፡ አንዱን፣ ለመጻረር ፡ እንደሚችል፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ።

ባዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ስለማድረግ ፡ የሚናገሩት ፡ ውሳኔዎች ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እርምጃ ፡ ተወስዷል ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የመጀመሪያዎቹ፡ እሥረኞች ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ እንዲፈቱ ፡ ተፈቅዶላቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን፡ እሥር፣ ቤቶችን ፡ የሚቆጣጠረው፡ ያገር ፡ ግዛት ሚኒስቴርና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ የሚያዘው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አስተያየት ፡ የተለያየ ፡ ስለሆነ ፡ ችግር ፡ ተፈጥሯል ። በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በእሥር ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የኀላፊነት ፡ መከፋፈል ፡ ሌሎች ፡ አከራካሪ ፡ ሁናቴዎችንም ፡ አስከትሏል ። ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ በፖሊሶች ፡ ተዘጋጅተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት የሚቀርቡት ፡ የወንጀለኛ ፡ ምርመራ ፡ መግለጫዎች ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፋይሎች ፡ ውስጥ ፡ ይቀራሉ ። ለእሥር ፡ ቤት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሚሰጠው ፡ የወንጀለኛው ሙሉ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ሳይሆን ፡ የፍርዱ ፡ ዐይነትና ፡ የተፈረደበት ፡ የእሥራት ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የእሥረኞች ፡ አከፋፈል ፡ የሚስማማው ፡ ለፍርዱና ፡ ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ እንጂ እያንዳንዱን ፡ ወንጀለኛ ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቃ ፡ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ፡ ለማርካት ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተቋቋሙት ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ሰውነት ፡ ፡ እንዲበቃ ፡ የማድረግ፡ የተቀደሱ፡ ሐሳቦች፡ በሚያጠግብ፡ ሁኔታ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ የፍርድና ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ ሥርዓት ፡ አቅጣጫውን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ እንዲለውጥ ፡ ያስፈልጋል ።

ሐ/ አካለ መጠን የደረሱ ወንጀለኞች ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስለደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ቁጥርና ፡ ዐይነት (ስታትስቲክስ) በየቦታው ፡ ባሉት ፡ የፖሊስ ፡ ክፍሎች ፡ ተሰብስበው ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ተከማችተው ፡ የሚገኙት ፡ ብቻ ፡ ናቸው። እነሱም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በፋፉ ፡ አዝማሚዎችን ፡ እንደሚያሳዩ ፡ እምነት ፡ ሊጣ

ልባቸው ፡ ምናልባት ፡ ቢቻልም ፣ ያልተሟሉ ፡ ከመሆናቸውም ፣ በላይ ፣ ስሕተት ፡ ሳይገኝባቸው ፡ አይቀርም ።[27]

በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፩ — ፷፪ ስታትስቲክስ ፡ የተሠራለት ፡ የመጨረሻው ፡ ዓመት) ፳፰ሺ፳፻፶፱ ተከሳሾች ፡ እንደተፈረደባቸው ፡ ተገልጧል ። ከነዚህም ፡ ፭ሺሕ፩፻፵፯ቱ በንብረት ፡ ላይ ፡ በፈጸሙት ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ ፩ሺሕ ፩፻፷፪ቱ ሆነብለው ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ነበር ። በንብረት ፡ ላይ ፡ የተፈጸሙት ፡ የወንጀሎች ፡ ብዛት ፡ ከተጠቀሰው ፡ ሳይበልጥ ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ይዞታ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ አያሌ ፡ ወንጀሎችን ፡ የሚያመለክት ፡ አኃዝ ፡ ባለመሰጠቱ ፡ ነው (ቁ. ፯፻፵፬ - ፵፪) ። አብዛኛዎቹ ፡ ወንጀሎች ፡ የተፈጸሙት ፡ በሸዋና ፡ በሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። የከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ በብዛት ፡ ተከማችተው ፡ በሁለቱ ፡ ስለሚገኙ ፡ ይኸ ፡ አያስደንቅም ።

አካለ ፡ መጠን ፡ በደረሱ ፡ አጥፊዎች ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎቹ ፡ የሚገኘው ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ርዝራዥና ፡ እምነት ፡ ሊጣልበት ፡ የማይቻል ፡ በመሆኑ ፡ ለወንጀሉ ፡ መነሾ ፡ ስለሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ ጊዜአዊ ፡ ከሆነ ፡ ግምት ፡ በላይ ፡ የተሻለ ፡ አስተያየት ፡ ለመውሰድ ፡ አያስችልም ። ባለርስት ፡ መሆን ፡ በአገሩ ፡ ልማድ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ መሆኑ ፥ ከገጠር ፡ ኑሮ ፡ ይልቅ ፡ የከተማ ፡ ኑሮ ፡ በፍጥነት ፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሔድ ፡ የሥራ ፡ እጦት ፡ መፈጠሩ ፤ እንዲሁም ፡ ድህነት ፤ በንብረት ፡ ላይ ፡ ለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ መነሾ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ ግልፍተኞች ፡ ሰዎች ፡ ክብራቸውንና ፡ አቋማቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ያላቸው ፡ የጠነከረ ፡ ፍላጎት ፤ በብዛት ፡ ለሚፈጸሙት፡በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የማድረስ ፡ ወንጀሎች ፡ መነሾ ፡ ከሆኑት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ። ወንጀል ፡ እንዳይሠራ ፡ በማስፈራራት ፡ ምክንያትን ፡ የተመረኰዘ ፡ ቅንጅት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የወንጀል ፡ አሠራር ፡ አመጣ

27. በልዩ ፡ ልዩ ፡ የወንጀል ፡ ዐይነቶች ፡ መሠረት ፡ ለእሥራ ፡ ውለት ፡ ተከፍሉ (ተመድቦ) ፡ በተለይ ፡ ይተዳደር ፡ ከነበረው ፡ ከኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በስተቀር ፡ ለሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ የስታቲስቲክስ ፡ መግለጫ ፡ ተሰጥቶአል ። ወንጀል ፡ ሆነው ፡ በፍርድ ፡ ከተገኙት ፡ በሙቀ ፡ ሥላሳው ፡ ልዩ ፡ ያልሆኑ ፡ ማንኛውም ፡ ናቸው ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በእስታቲስቲኩ ፡ ውስጥ ፡ ስሕተት ፡ ሞልቷል ። በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ (አውቆ) ሰው ፡ የመግደል ፡ ወንጀል ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ እንደነበረ ፡ ተገልጿል ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቤት ፡ ሰርሰራ ፡ ወንጀልነቱ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ያልተገለጸ ፡ ቢሆን፤ ይሆን ፡ ወንጀል ፡ ፈጽመዋል ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ቁጥርም ፡ ተመዝግቧል ፤ ተከሳሹ ፡ በቸልተኝነት ፡ ሰው ፡ መግደሉ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ ሰው ፡ መጉዳቱ ፡ በእርግጥ ፡ በቸልተኝነት ፡ መሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ በፖሊስ ፡ ሪፖርት ፡ ይገለጻል ።

ጥና ፡ የቅጣት ፡ አሰጣጥ ፡ ስነፍጥረት ፡ ጥናት ፡ እንዲሁም ፡ የሳይኮሎጂ ፡ ምርመራ፡ እንዲደረግ ፡ በጣም ፡ ያስፈልጋል ። [28]

በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሱ ፡ ወንጀለኞችን ፡ በማስተናገድ ፡ ረገድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ ለማድረግ፡ ያስችላል ። በተጨማሪም ፡ ዳኛው ፡ በተፈረደበት፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ ሲወሰን ፡ ለሚያደርገው ፡ ግላዊ ፡ አስተያየት ፡ የእያንዳንዱን ፡ ወንጀል ፡ ንኡስ ፡ ክፍል ፡ የሚያትቱት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ቁጥሮች ፡ ክልል፡ አበጅተውለታል ። [29] በጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ የሚገኘው ፡ ሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅጣትና ፡ የቅጣትን ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመለከቱ ፡ ሰፋፊ ፡ መሠረት ፡ ሐሳቦችን ፡ ይደነግጋል ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሦስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የቅጣት ፡ ዐይነቶችን ፡ ይወስናል ። እነሱም ፡ መቀጮ ፡ እሥራትና ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ ናቸው ። የመቀጮው ፡ መጠን ፡ የሚወሰነው ፡ የአጥፊውን ፡ ግላዊ ፡ ሁኔታና ፡ የጥፋቱን፡ መጠን ፡ በመመልከት ፡ ነው (ቁ.፹፰) ። ወንጀለኛው ፡ መቀጮውን ፡ ለመክፈል፡ እንዲችል ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጠው ፡ ይቻላል ፤ ባይከፍል ፡ ግን ፡ መቀጮው ፡ ሥራ ፡ በመሥራት፤ ባይሆን ፡ ሀብቱን ፡ በመያዝ ፡ ይኸም ፡ ደግሞ ፡ ባይቻል ፡ በእሥራት ፤ ሊለወጥ ፡ ይቻላል (ቁ.፺፩—፺፭) ። የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ በሚካሄድበት ፡ ጊዜ ፡ የተበደለውንም ፡ ወገን ፡ እንዲክስ ፡ ሕግ ፡ በተጨማሪ ፡ ይወስናል ። (ቁ. ፻ —፻፩) ። [30]

28. ወንጀል ፡ እንዲሠራ ፡ ስለሚያነቃቁት ፡ ምክንያቶች ፡ በሌላ፡አገር ፡ የሚደረገው ፡ ጥናት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያለው ፡ ጠቃሚነት ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ይመስለኛል ፤ ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ግንኙነቷን ፡ ተቋርጦ ፡ ስለነበረ ፡ ታሪኳና ፡ ማኅበራዊ ፡ ዕድገቷ ፡ ከሌሎች ፡ የተለየ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

29. የሚከተሉት ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫውን ፡ ሕግ ፡ ሰፊነት ፡ የሚያሳዩ ፡ በልዩው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ።

ቁ. ፭፻፳፫ ፡ በግዙፍ ፡ ስለሚሠራ ፡ ሐሰት ። . . . እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት፡ ሊደርስ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ቀላል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቢያንስ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።

ቁ. ፭፻፹፭ ፡ በዘመድ ፡ መካከል ፡ ስለሚፈጸመው ፡ የዝሙት ፡ ተግባር ። . . . እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። ይኸውም ፡ ከአባትነት ፡ ሥልጣን ፡ የመሻሩ ፡ ቅጣት ፡ ሳይቀር ፡ ነው ።

ቁ. ፮፻፴፯ ። ስለ ፡ ወንበዴነት ። . . . እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ሆኖም ፤ ዳኛው ፡ ከዚህ ፡ ከተሰጠው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ቅጣቱን ፡ ለመወሰን ፡ እንዲችል ፡ መመሪያ ፡ ተሰጥቶታል ። ቁ. ፹፮ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚወሰን ፡ ቅጣት ፡ የሚለውንና ፡ ከቁ. ፸፱–፹፮ ፡ ቅጣትን ፡ ስለማቃለልና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማክበድ ፡ የሚውሰውን ፡ ተመልከት ።

30. እንዲሁም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከቁ. ፻፺-፺፱ ተመልከት ።

ከእሥር ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ የእሥራት ፡ ቅጣት፣ ለጠቅላላው ፡ ጸጥታ ፡ መጠበቂያና ፡ ለወንጀለኛው ፡ ማረሚያ ፡ እንዲሆን፡ በማለት ፡ ከባድነቱ ፡ መካከለኛ ፡ የሆነ ፡ ጥፋትን ፡ ለሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ የታቀደ ፡ ነው ፡ (ቁ. ፻፭) ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግን ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና፡ ለመልካም ፡ ሰውነ እንዲበቃ ፡ ያደርገዋል ፡ ብሎ ፡ ካመነ ፡ በእሥራቱ ፡ ፈንታ ፡ የግዴታ ፡ ሥራን ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ፡ (ቁ.፻፮) ። የጽኑ ፡ እሥራት ፡ ቅጣት ፡ የሚወሰነው ፡ ከባድ ፡ ወን ጀሎች ፡ በሠሩ ፡ ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ የታቀደውም ፡ ተቀጭው ፡ እንዲታረም፣ እንደገና ፡ ለመልካም፡ ሰውነት፡ እንዲበቃ ፡ ማድረግና ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ልዩ ፡ መከላከያ ፡ ለመስጠት ፡ ሲሆን ፤ በተለይ ፡ የመጨቆንና ፡ የመጠበቅ ፡ ግብ ፡ አለው። የጽኑ ፡ እሥራት ፡ የጊዜ ፡ ርዝመት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከአንድ ፡ እስከ ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነው ። በግልጽ ፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል (ቁ. ፻፯) ። የእሥር ፡ ቤት ፡ ኃላፊዎችና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወንጀለኛው ፡ ጠባይ ፡ የተሻሻለና ፡ ወደፊትም ፡ የፈተና ፡ ጊዜ፡ የተሰጠው ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ እየተሻሻለ ፡ እንደሚሄድ ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጡ ፡ ምክንያቶች፣ እንዳሉ ፡ ካመኑ፤ የተፈረደበትን ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሲሦ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ፡ ቀዋሚ ፡ ባል ሆነ ፡ ውሳኔና ፡ ለአመክሮ ፡ በተወሰነ ፡ ገደብ ፡ ወንጀለኛው ፡ ሊፈታ ፡ ይቻላል፡ (ቁ. ፻፲፱ እና ፡ ፻፳፯) ።

ከተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ ማንኛቸውም ፡ የወንጀለኛን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ማኅ በራዊ ፡ ኑሮ ፡ መመለስ ፡ የማያራምዱ ፡ ሆነው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቢታዩና ፡ የወንጀ ለኛው ፡ ጥፋት ፡ በመቀጮ ፤ በግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ እሥራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱን ፡ ሊያግድና ፡ አጥፊውን ፡ በአመክሮ ፡ ሊያቆየው ፡ ይችላል (ቁ.፻፵፬ — ፻፭) ። ለወንጀለኛው ፡ የሚሰጠው ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ ርዝ መት ፡ በሁለትና ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ የአጠባበቁና፣ የጥሩ ፡ ጠባይ ፡ አመራር ፡ ደንቦችም ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠ ፡ ቁጥር ፡ መወሰን ፡ አለባ ቸው (ቁ. ፻፸ ፣— ፻፸፫) ። ወንጀለኞችን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ መልቀቅ ፡ ተግባር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ አልተሠራበትም።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶ ችን ፡ ባይደነግግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዋናዎቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ። ከተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ዋናዎቹ ፤ ግርፋት [31] ፡ ተግሣፅ ፡ ይቅርታ ፡ መጠየቅ ፡ ሕዝባዊ ፡ መብትን ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ በሙ ያው ፡ ለመጠቀም ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ መከልከልና ፡ ከጦር ፡ ኃይሎች ፡ ውስጥ ፡ መወገድ ፡ ወይም ፡ የማዕርግ ፡ መዋረድ ፡ ናቸው ። እያንዳንዱን ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት፡

31. እላይ ፡ ከገርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ከቁ. ፻፴-፻፶፱ ፡ ጋር ፡ የሚሔደውን ፡ ዋናውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመል ከት ።

የሚወሰነው ፣ የጠቅላላው ፣ ክፍል ፣ ቁጥር ፣ የቅጣቱን ፣ ዓላማና ፣ ቅጣቱ ፣ የሚፈጸ ምባቸውን ፣ ጥፋቶች ፣ ይደነግጋል (ቁ. ፻፳ — ፹፯) ።

ከዚህም ፣ በላይ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ አስፈላጊ ፣ መስሎ ፣ ሲታየው ፣ ከዋናዎቹ ፣ ቅጣቶች ፣ ጋር ፣ ተጨማሪ ፣ በማድረግ ፣ "ስለ ፣ ጥንቃቄና ፣ ስለ ፣ አጠባበቅ ፣ ጠቅ ላላ ፣ ደንቦች"፣ የተባሉትን ፣ ሊያዝ ፣ ይችላል ። ወንጀለኛው ፣ ጥፋት ፣ እንዳይሠራ፣ ለመከልከልና ፣ ሕዝቡን ፣ ለመጠበቅ ፣ የታቀዱ ፣ አንዳንድ ፣ ጠቅላላ ፣ እርምጃ ዎች ፣ ይገኛሉ ። ከነሱም ፣ ውስጥ ፣ ለመልካም ፣ ጠባይ ፣ አመራር ፣ ቃል ፣ መግ ባት ፣ አደገኛ ፣ መሣሪያዎችን ፣ መያዝ ፣ የሥራን ፣ የፈቃድ ፣ ወረቀት ፣ ማገድና ፣ ወይም ፣ መውሰድ ፣ ወደ ፣ አንድ፣ አንድ ፣ ቦታዎች ፣ እንዳይሄድ ፣ ወይም ፣ እንዲ ሄድ ፣ ማስገደድ ፣ መቆጣጠር ፣ እና ፣ አጥፊው ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ሰው ፣ ሲሆንም ፣ ከአገር ፣ ማስወጣት ፣ ይገኙባቸዋል (ቁ. ፻፴፰ — ፰) ።

ወንጀል ፣ እየደጋገሙ ፣ ለሚሠሩ ፣ ወንጀል ፣ የመሥራት ፣ ኃላፊነት ፣ ለሌላ ቸው ፣ እና ፣ አካለ ፣ መጠን ፣ ላልደረሱ ፣ ወንጀለኞች ፣ ሕጉ ፣ ልዩ ፣ እርምጃዎችን ፣ ወስኖአል ።[32] ለወንጀል ፣ ሥራ ፣ የአመለኛነት ፣ ዝንባሌ ፣ ስለአላቸው ፣ ጠባያ ቸውን ፣ ባለማረም ፣ በሥራ ፣ ፈትነትና ፣ ባልተገባ ፣ ሁኔታ ፣ በመኖር ፣ ወይም ፣ ወንጀል ፣ መሥራትን ፣ እንደ ፣ ሙያ ፣ ሥራቸው፣ በማድረግ ፣ የሚኖሩ ፣ ወንጀለ ኞች ፣ ከአምስት ፣ ዓመት ፣ እሥራት ፣ በላይ ፣ የማያስቀጣ ፣ ሌላ ፣ ወንጀል ፣ እንደ ገና ፣ ሲፈጽሙ ፣ በጽኑ ፣ ግዞት ፣ በተወሰነ ፣ ሥራ ፣ ተወስኖ ፣ በመኖር ፣ እንዲቀጡ ፣ ይደረጋል ። ጽኑ ፣ ግዞት ፣ ከሁለት ፣ ዓመት፣ ለማያንስ ፣ ወይም ፣ ከአሥር ፣ ዓመት ፣ ለማይበልጥ ፣ ላልተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ ለዚሁ ፣ ጉዳይ ፣ በተዘጋጀ ፣ በአንድ ፣ የግዞት ፣ ሥራ ፣ ውስጥ ፣ ይፈጸማል ። ከሁለት ፣ ዓመት ፣ በኋላ ፣ በማንኛውም ፣ ጊዜ ፣ የግ ዞቱ ፣ ፍራ ፣ አስተዳዳሪ ፣ ይገባል ፣ ብሎ ፣ ሐሳብ ፣ ሲያቀርብ ፣ ፍርድ፣ ቤቱ ፣ ግዞ ተኛውን ፣ በአመክሮ ፣ ሊለቀው ፣ ይችላል (ቁ. ፻፳፰ — ፴፱) ።

ምንም ፣ እንኳን ፣ አዘውትረው ፣ ወንጀል ፣ የሚፈጽሙ ፣ አጥፊዎች ፣ በተቻ ለ ፣ መጠን ፣ በዋናው ፣ የእሥር ፣ ቤት ፣ ክፍል ፣ ለብቻቸው ፣ ቢታሠሩ ፣ በገንዘብ ፣ እጥረት ፣ ምክንያት ፣ እነዚህ ፣ ውሳኔዎች ፣ ሥራ ፣ ላይ ፣ ሊውሉ ፣ አልቻሉም ። ወንጀል ፣ የማድረግ ፣ ኃላፊነት ፣ የሌላቸው ፣ ግን ፣ በተስማሚ ፣ ድርጅቶች ፣ ውስጥ፣ እንዲታከሙ ፣ አደገኞችም ፣ ካልሆኑ ፣ በተመሳሳሽነት ፣ እንዲረዱ ፣ ይደረጋሉ ። በልዩ ፣ ቦታ ፣ የሚጠበቁት ፣ ላልተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ ቢሆንም ፣ በየሁለቱ ፣ ዓመት ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ውሳኔውን ፣ እንደገና ፣ ማየት ፣ አለበት ። በልዩ ፣ ቦታ ፣ እንዲጠበቁ፣ የተወሰነበት ፣ ምክንያት ፣ ሲወገድ፣ ሥራ ፣ አስኪያጁ ፣ የሕክምናው ፣ ጊዜ ፣ እንዲ ያበቃ ፣ መጠየቅ ፣ አለበት ። ፍርድ ፣ ቤቱም ፣ ሰውየው ፣ እንዲለቀቅና ፣ ቢያንስ ፣

32. እነዚህ ፣ ከገጽ ፣ ማስታወሻ ፣ ከቁ. ፶፩ ፣ እና ፣ ተከታታዮቹ ፣ ጋር ፣ የሚሄደውን ፣ ዋናውን ፣ ጽሑፍ ፣ ተመልከት ።

ለአንድ ፡ ዓመት ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ እንዲቆይ ፡ ማድረግ ፡ አለበት (ቁ. ፻፴፫ — ፴፯) ። በአስፈላጊዎቹ ፡ ድርጅቶችና ፡ በአእምሮ ፡ መናወጽ ፡ ምርመራ ፡ ጥናት ፡ ረገድ ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ ዝግጅቶች ፡ ባለመገኘታቸው ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሱት ፡ ውሳኔዎች ፡ በሰፊው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውሉ ፡ አልቻሉም ።

የታሠሩ ፡ ወንጀለኞች ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሣዊ ፡ ይቅርታ ፡ ወይም ምሕረት ፡ ሊያገኙ ፡ ይቻላል (ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አን. ፴፭ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፴፱ — ፵)። በንግሥ ፡ በዓላቸውና ፡ በሌሎች ፡ ታላላቅ ፡ በዓሎች ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ በሰፊውና ፡ በልግስና ፡ መጠቀም ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. (፲፱፻፷፫—፷፬ እ. ኤ. አ.) ፻፳ ፡ ሙሉ ፡ ይቅርታና ፡ ፩ሺ፻፹፱ ፡ የቅጣት ፡ ቅነሳ ፡ መደረጉን ፡ የእሥር ፡ ቤቱ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ያሳያል ። [33]

አንዳንድ ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ በአውራጃው ፡ አንዳንድ ፡ ዋና ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በጠቅላላው ፡ በግምት ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። [34] በተጨማሪም ፡ ለ፩፻፱ ፡ እሥረኞች ፡ የሚበቃ ፡ የእርሻ ፡ ጣቢያ ፡ በሮቢት ፡ ተቋቁሟል ። የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ስታቲስቲክስ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ፲፯ሺ፩፻፺፱ ፡ ሰዎች ፡ ታሥረው ፡ ነበር ። የእሥረኞቹ ፡ ብዛት ፡ ከ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በ፰ሺ፷፬ ፡ ከ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. በ፭ሺ፰፻፳፪ ፡ መጨመሩ ፡ ነው ። [35] ፫ሺ፫፻፳፫ ፡ ሰዎች ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ ፩ሺ፻፳፩ ፡ ሰዎች ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለሚያንስ ፡ ጊዜ ፡ እሥራት ፡ ሲፈረድባቸው ፡ ዕድሜ ፡ ልካቸውን ፡ እንዲታሠሩ ፡ የተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ፯፻፯ ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ፯ሺ፬፻፷፩ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ እስኪሰጣቸው ፡ በመጠባበቅ ፡ ታሥረው ፡ ነበር ።

33. በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ (ሪፖርት) ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ።

34. ሆኖም ፡ ኤሪትርያ ፡ ወህኒ ቤቶቿን ፡ እንደቀድሞው ፡ ራስዋ ለብቻዋ ፡ ታስተዳድራለች ።

35. በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ዓመታዊ መግለጫ ፡ ከ፲፱፻፶፱ — ፷፫ ፡ ዓ. ም. ።

ከዚህ ፡ በአቆጣጠሩ ፡ ጥቂት ፡ የተለየውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም.) ፡ የተዘጋጀውን ፡ እስታቲስቲካል ፡ አብስትራክት ፡ ከገጽ ፡ ፲፱፻-፷፬ ፡ ተመልከት ። የእስረኞቹ ፡ ቁጥር ፡ የበዛው ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ከየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ከቀድሞው ፡ ይልቅ ፡ የተሟላ ፡ መግለጫ ፡ በመተላለፉ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።

በአገሪቱ ፡ ከሚገኙት ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የተራመደው ፡ በአ ዲስ ፡ አበባ ፡ ያለው ፡ የሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ነው ። [36] እሥረኞች፡ በጽኑ እሥራት ፡ ሦስት ፡ ንኡስ ፡ ክፍሎችና ፡ በሦስት ፡ ንኡስ ፡ የእሥራት ፡ ክፍሎች ፡ ይመደባሉ ።

ፍርድ ፡ የሚጠባበቁ ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እሥራት ፡ የተፈረደባቸው ፡ ወይም ፡ የሞትን ፡ ቅጣት ፡ የሚጠባበቁ ፡ እሥረኞች ፡ ከተራ ፡ እሥረኞች ፡ ተለይተው ፡ ይታሠራሉ ፤ በእሥር ፡ ቤቱም ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋዮች ፡ አይሆኑም ። የእሥር ፡ ቤቱ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የእሥረኞችን ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ማያገኙና ፡ ራሳቸውም ፡ ይኸን ፡ ስለማያዘጋጁ ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ ለማብቃት ፡ የሚደረገው ፡ ቅንጅት ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ።

የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት፡ ፕሮግራሞች ፤ በመጻጻፍ፡ የሚጠኑ ፡ ኮርሶችና፡ ያልተስፋፉ ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አገልግሎት ፡ እሥረኞች ፡ እንዲያገኙ ፡ ተደር ጓል ። እሥረኞቹ ፡ ፺፰ ፡ በመቶ ፡ የሚሆኑት ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ ሲገቡ ፡ መጻፍና ፡ ማን በብ ፡ አይችሉም ፤ [37] ፡ ከእሥራቱ ፡ ሲፈቱ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ በሚጠቅሟቸው ፡ የሙያ ፡ ትምህርት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻል በት ፡ በተለይም ፡ በርሻ ፡ በኩል ፡ እንዲሠለ ጥኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ፕሮግራሞች ፡ ወጥተዋል ። የሚያሳዝነው ፡ ግን ፡ ገንዘብ የማግኛ ፡ እቅዶች ፡ ገና ፡ ባለመውጣታቸው ፡ እሥረኞች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለሚ ሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሳይከፈላቸው ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲሀ ፡ ያለው ፡ አቅድ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በተረቀቀው ፡ የእሥር ፡ ቤት ፡ አዋጅ ፡ ታስቦበታል ። ረቂቁ ፡ በሥራ ፡ የሚገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ በሦስት ፡ የሒሳብ ፡ መደብ ፡ ማለት ፡ በየ

36. አብዛኛው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጻፈው ፡ ነገር ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተገኘና ፡ እኔም ፡ የአዲስ ፡ አበባን ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተመላልሼ ፡ በመጐብኘት ፡ የተረዳሁት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከሪንት፡ ፕሮጀክትስ ፡ ኤንድ ፡ ፕሪቬንሽን ፡ ኮንትሮል ፡ ኤንድ ፡ ትሪትመንት ፡ ኦቭ ፡ ክራይም ፡ ኤንድ፡ ዲሊን ፡ ኩዌንሲ፡ (ወንጀልንና፡ የወጣቶችን፡ ወሮበላነትነት) (ሥራ፡ ፈትነት) ፡ ለማቆምና፡ ለማስቀረት፡ በአሁኑ፡ ጊዜ ፡ ሊወሰድ ፡ የታቀደ ፡ እርምጃ) ፡ በሚል ፡ አትም ፡ ውስጥ ፡ ፲፫ ፡ ቮልዩም ፡ ከገጽ ፡ ፮—፱ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) አቶ ፡ እንዳርጋቸው ፡ ተሰማ ፡ "ኮሪክሽን፡ ኤን ፡ ኢትዮጵያ" ፡ (በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኞች ፡ እርማት ፡ መታረም) " በሚል ፡ አርእስት " ፡ የጻፉትን ፡ ተመልከት ።

37. አቶ ፡ ሜንያለው ፡ ተሾመ ፡ "ሚሞራንደም ፡ ኦን ፡ ዘ ኢምፕሩቭሜንት ፡ ኦቭ ፡ ፕሪዝን፡ አድሚኒስትሬሽን ፡ (ስለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ መሻሻል ፡ ማስታወሻ) ፡ በሚል ፡ ያቀረቡትን ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ።

ጊዜው ፡ የሚሠራበት ፡ ሒሳብ ፡ በሚጠራቀም ፡ ሒሳብና ፡ ለካሣ ፡ በሚከፈል ፡ ሒሳብ ፤ በመመደብ ፡ ይከፈፍለዋል ። [38]

የገንዘብ ፡ እጦት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ እንኳን ፡ ያሉትን ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ ባሳዛኝ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እንዲወድቁ ፡ አድርጓቸዋል ። በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ ሠራተኞች ፡ ለመቅጠርና ፡ ለማሠልጠን ፡ የማይቻል ፡ ሆኗል ። መዝናናት ፣ ጤንነትና ሕክምና ፡ የሚሰፋፉባቸው ፡ አቅዋሞች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። ከእሥራትም ፡ በኋላ ፡ ለሚደረገው ፡ ጥንቃቄ ፡ አስፈላጊው ፡ ፕሮግራም ፡ ገና ፡ አልተዘጋጀም ። እሥረኞች ፡ እንደሚማረሩና ፡ መታሠራቸውም ፡ በፍርድ ፡ መጓደል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ስሜት ፡ እንዳላቸው ፡ ይነገራል ። [39] የጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እሥር ፡ ቤቶች ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያላቸው ፡ መሰናዶ ፡ የባሰውን ፡ አነስተኛ ፡ ነው ፤ እሥረኞቹ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ የሚሰጣቸውም ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። አላፊነታቸውን ፡ የተረዱት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ መሠረት ፡ ሐሳቦች ፡ ፍሬ ፡ በማያስገኝ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ከተፈለገ ፣ ጥሩ ፡ የእሥር ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ማስፈለጉንና ፡ በጥንቃቄ ፡ የማቀድን ፡ ጠቃሚነት ፡ ስለተገነዘቡ ፤ ይህን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ጀምረዋል ።

መ/ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወንጀለኞች ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ስለደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ቁጥራቸው ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ መግለጫዎች ፡ ስለሚገኙና ፡ የተሟላ ፡ ጥናት ፡ በጉዳዩ ፡ ስላልተደረገ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወንጀለኞች ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ጥፋቶች ፡ የሚሰጡት ፡ ሐተታዎች ፡ ዘለቄታ ፡ ጊዜአዊ ፡ ከመሆን ፡ አያልፍም ። [40] በአዲስ ፡ አበባ ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ የወጣቶች ፡ ማቆያና ፡

38. ስለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ የሚወጣው ፡ ሕግ ፡ በአሁኑ ፡ የፓርላማ ፡ ስብሰባ ፡ ጊዜ ፡ ለፓርላማው ፡ እንዲቀርብ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ስለወህኒ ፡ ቤቶች ፡ የሚወጣው ፡ ሕግ ፡ በብዛት ፡ የሚያወሳው ፡ ስለእስረኞች ፡ ጥበቃ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ቢታሰብም ፤ እስከ ፡ አሁን ፡ ስለ ወህኒ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ምንም ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ የሕጉ ፡ መውጣት ፡ ወህኒ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ቅጥ ፡ ያለው ፡ አስተዳደር ፡ እንዲኖራቸውና ፡ አስተዳደሩም ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳል ።

39. ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአቶ ፡ ጫንያለው ፡ ተሾመ ፡ ጽሑፍ ፡ ገጽ ፡ ፪ ፡ ተመልከት ።

40. ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ የተላኩት ፡ አማካሪ ፡ ከጂ. ራይሌ ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ (የአካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ) አጥፊዎች (ወንጀለኞች) ፡ በጣም ፡ የተሟላ ፡ ጥናት (ምርምር) የመጨረሻ ፡ መግለጫ ፡ ለሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ ቀርቦለታል ። ሌላ ፡ ሁለት ፡ አጫጭር ፡ ጥናቶች ፡ በሚከተሉት ፡ ገና ፡ ያልታተሙ ፡ መግለጫዎች ፡ ውስጥ ፡ አሉ ፤ ከጂ. ርስ ፡ የተጻፈው ፡ "ጁቪናይል ፡ ዴሊንኩዌን ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች" እና ፡ ከወይንእሸት ፡ በሻህ ፡ ውረድ ፡ የተጻፈው ፡ "ሳም ፡ አቭ ፡ ዘ. ኮዝስ ፡ አንድ ፡ ኮንትሪቢዩቲንግ ፡ ፋክተርስ ፡ ቱ ፡ ዘ ፡ ሜኪንግ ፡ አቭ ፡ ጁቪናይል ፡ ዴሊንኩዌንሲ ፡ ኤንድ ፡ ፕሮስቲቲዩሽን (ወጣት ፡ አጥፊዎችና ፡ ሴት ፡ አዳሪዎችን ፡ በሰሚፈጥሩ ፡ አንዳንድ ፡ ምክንያቶችና ፡ እንሱን ለመፍጠር ፡ ስለሚረዱ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች) (፲፱፻፷፮ ፡ እ.ኤ.አ.) ። እንዲሁም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአቶ ፡ እንዳርጋቸው ፡ ተሰፋዬን ፡ ጽሑፍ ፡ (ከገጽ ፡ ፱—፲፩) ፡ ተመልከት ።

ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፋይሎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የየጉዳዩ ፡ ታሪክ ፡ ጽሑፎች ፡ ሲመረመሩ ፡ ግን ፤ እካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ስለሚፈጽሙአቸው ፡ ወንጀሎች ፡ አዝማሚያ ፡ ጥቂት ፡ ፍንጭ ፡ ይሰጣል ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከተጠቀሰው ፡ መረጃ ፡ ሊወጣጡ ፡ የሚችሉት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ማጠቃለያ ፡ ሐሳቦች፡በቅርቡ ፡ ለሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ በቀረበው ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ በአጭር ፡ ሠፍረዋል ። [41] አብዛኛውን፡ ጊዜ ፡ አካለ፡ መጠን ፡ ያልደረሱ፡ አጥፊዎች ፡ የሚፈጽሟቸው ፡ የወንጀሎች ፡ ብዛት ፡ የሚገኙት ፡ በጥቂት ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞች፡ ውስጥ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ጥፋቶች ፡ ለጊዜው ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆኑም ፡ ቁጥራቸው፡ እያደገ ፡ በመሔድ ፡ ላይ ፡ ነው ። [42] በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሥራ ፈትነት ፡ ወንጀል ፡ ረገድ ፡ እርምጃ ፡ እንዳይወሰድ ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ ቢወስኑም ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ጥፋቶች ፡ ሥራ ፡ ፈትነትና ፡ ቀላል ፡ ስርቆት ፡ ናቸው ። [43] በአሥራ ፡ ሁለትና ፡ በአሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ያለው የዕድሜ ፡ ደረጃ ፡ አብዛኛውን ፡ የወጣት ፡ ወንዶች ፡ አጥፊዎች ፡ ክፍል ፡ የያዘ ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ አጥፊዎች፡ መካከል፡ አባትና ፡ እናታቸው ፡ አብረው ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ የሚመጡት ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ በመቶ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እንዲሁም ፡ የአበል ፡ አነስተኛነት ፡ መሀይምነትና ፡ በሥራ ፡ እጦት ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ መሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ከሚፈጽሙአቸው ፡ ወንጀሎች ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ የወል ፡ ምክንያቶች ፡ ናቸው ።

አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ስለሚፈጸሙት ፡ ወንጀሎች ፡ መነሾ ፡ ማተት ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ቢሆንም ፡ መመርመር፡ ስለሚገባቸው፡ ጥቂት ፡ ጠቃሚ ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ተገቢ ፡ ይሆናል ። በፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ የሚሔደው ፡ የባላገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በተለይም ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መግባትና ፡ ይኸም ፡ ያስከተለው ፡ ከቤተሰብ ፡ አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ ክር

41. የተጠቀሰውን ፡ የራዳሌ ፡ ጽሑፍ ፡ ገጽ ፡ ፰ ፡ ፩፻—፩፩ ።

42. ስለወጣት ፡ ወንጀለኞች ፡ ብዛት ፡ ትክክለኛ ፡ የታወቀ ፡ ቁጥር ፡ የለም ፤ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ከድሬዳዋና ፡ ከአሥመራ ፡ ውጭ ፡ ብዙ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ የሉም ። ቢኖሩም ፡ ጉዳያቸው ፡ በቀላሉ፡ በይፋ ፡ ሳይሆን ፡ በፖሊስ ፡ ይወሰናል ። የተጠቀሰውን ፡ የራይሌ ፡ ጽሑፍ ፡ ከገጽ ፡ ፩፩—፩፪ ፡ ተመልከት ።

43. በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርሱን ፡ ስለመከላከል (የማኅበራዊ ፡ እደጋ ፡ መከላከያ) ፡ እ. ኤ. አ. —ኦገስት ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ በሞንሮቪያ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ጉባኤ ፡ ኢትዮጵያ ፡ "ዘካንትሪ ፡ ስቴትሜንት ፡ እቭ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ማስረጃ)" በሚል ፡ አርእስት ፡ ያቀረበችው ፡ ጽሑፍ ፡ በገጽ ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ "ከመቶ ፡ ውስጥ ፡ ፸፰ ፡ ልጆች ፡ የሚከሰሱ ፡ በጥቃቅን ፡ ስርቆትና ፡ ወሮበልነት ፡ ነው ፡ " ይላል ። አዲስ ፡ በተወሰደው ፡ እርምጃ፡ ምክንያት ፡ በወሮበልነት ፡ የሚያዙት ፡ ብዛት ፡ ተቀንሶ ፡ ከመቶ ፡ ውስጥ ፡ አምሳ ፡ የነበረው ፡ ከመቶ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሆኗል ። የተጠቀሰውን ፡ የራዳሌ ፡ ጽሑፍ ፡ ገጽ ፡ ፬ ፡ ተመልከት ።

ስቲያን ፡ መለየትና ፡ መራቅ ፡ ከምዕራባውያን ፡ የትምህርትና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ሐሳቦች ፡ መምጣት ፡ ጋር ፡ ተደርቦ ፡ በተለየ ፡ ወጣቶችን ፡ ለሚማርከው ፡ የሥርዓት ፡ መዘበራረቅ ፡ መነሻ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ከጥንት ፡ የቆየውን ፡ ሥልጣን ፡ አቋምና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ መፈራረስ ፡ መርቶታል ፤ ይኸም ፡ በተራው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሱ ፡ አጥፊዎች ፡ ሊፈጽሙ ፡ የሚችሉትን ፡ ወንጀል አበርክቶታል ። እነዚህ ፡ ለውጦች ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ አቅዋም ፡ ጥልቀት ፡ ባለው ፡ አኳኋን ፡ ነክተዋል ።

ይልቁንም ፡ የቤተ ፡ ሰብ፡ አቅዋም ፡ ጥንቱኑ ፡ ባልሆነበት [44] ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚፈጸም ፡ የወጣቶች ፡ ወንጀል ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ የሳይኮሎጂ ፡ ሁናቴ ፡ ሥሩን ፡ የሰደደ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ድኅነት ፡ የሥራ ፡ እጦትና ፡ ትምህርት ፡ ለመማር ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ መወሰን ፡ በወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ለሚፈጸሙት ፡ ወንጀሎች ፡ በተለይም ፡ አዘውትሮ ፡ ለሚፈጸመው ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ተጨማሪ ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልጆች ፡ የሚሠሩት ፡ የወንጀሎች ፡ ቁጥር፡ አነስተኛ፡ የሆነበት ፡ ከፊል ፡ ምክንያት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ ጥንት ፡ በቆዩት ፡ ድርጅቶች ፡ ብርታት ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። በልጆች ፡ የሚፈጸመውን ፡ ወንጀል ፡ ማስወገጃና ፡ አጥፊዎቹን ፡ ማስተናገጃ ፡ ለሚሆን ፡ ለተሟላና ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ለሚያስገኝ ፡ አቅድ ፡ ትክክለኛውን ፡ መሥመር ፡ ለመዘርጋት ፡ እንዲቻል ፡ ይኸን ጊዜአዊ ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ለመደገፍም ፡ ሆነ ፡ ለመቃወም ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አስተያየቶችን ፡ ለማቅረብ ፡ ጥልቅ ፡ ጥናትን ፡ የተመረከዘ ፡ ምርምር ፡ ማድረግ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አካለ ፡ መጠን ፡ ስላልደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የወጣው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሕግ ፡ "የ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም. ስለ ፡ ዘዋሪዎችና ፡ ስለ ወሮበሎች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ" ፡ ነበር ። [45] አዋጁ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከ፲፰ ፡ ዓመት፡ በታች ፡ የሆኑ ፡ ልጆች ፡ ደንበኛ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ሳይኖራቸው እየዞሩ ፡ ቢገኙ ። [46] በልዩ ፡ ቦታ ፡ እንዲጠበቁ ፡ ያውጃል ። የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.

44. ኡለንዶርፍ ፡ የጻፈውን ፡ ዘኢትዮጵያንስ ፡ (ኢትዮጵያውያን) (፲፱፻፷ ፡ እ. ኤ. አ.) ገጽ ፡ ፻፸፰ ፡ እና ፡ ሊፕስኪ ፡ የጻፈውን ፡ —ኢትዮጵያ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ (፲፱፻፷፪ ፡ እ. ኤ. አ.) ገጽ ፡ ፺ ፡ ተመልከት ።

45. ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ. ም. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ። የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ትንሽ ፡ ይጠቅሳል ፤ ቁ.፸፮ ፡ እና ፡ ፻፶ ፡ ተመልከት ።

46. ወጣቱ ፡ አጥፊ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወንጀል ፡ ሲሠራ ፤ በእነሱ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ ለእናት ፡ አባቱ ፡ ይሰጣል ፤ ክፍል ፡ ፰ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ይኸንን ፡ አዋጅ ፡ ሽሮታል ።[47]

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት[48] ፡ ያልሞላ ፡ ሕፃናት ፡ ወንጀል ፡ ቢሠሩ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳላቸው ፡ ሆነው ፡ አይቈጠሩም ። እንዲህ ፡ ባሉት ፡ ሕፃናት ፡ የሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ በቤተሰብ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ በሚመለከተው ፡ ምግባራት ፡ አስፈላጊው ፡ እርምጃ ፡ ይወሰዳል (ቁ. ፶፪) ። ዕድሜያቸው፡ በዘጠኝና ፡ በ፲፭ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ የሆኑ ፡ ልጆች ፡ "አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች፡ ወይም ፡ ወጣቶች" ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፤ ለአዋቂዎች ፡ ጥፋተኞች ፡ በተመለከቱት ፡ በደንበኞቹ ፡ ቅጣቶች ፡ መሠረት ፡ አይቀጡም (ቁ. ፶፫)።

ጥፋቱ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ቅጣቱ ፡ የሚወሰነው ፡ በአጥፊው ፡ ወጣት ፡ ዕድሜ ፡ በጠባዩ ፡ በአእምሮውና ፡ በግብረ ፡ ገብነቱ ፡ የደረሰበትን ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ እንደዚሁም ፡ የሚፈጸሙበት ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዓላማ፡በመልካም ፡ ጠባይ ፡ ለማሳደግ ፡ እንዲሆን ፡ በማሰብ ፡ መመራት ፡ አለበት (ቁ. ፶፬) ።

47. የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ "በ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብና ፡ ለርሱ ፡ ማሻሻያ ፡ ሆነው ፡ የወጡት ፡ አዋጆችን ፡ ሁሉ ፡ ጭምር" በግልጽ፡ ይሽራቸዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የሕግ ፡ ቁ.፫ ፡ "ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ማሟያ ፡ የሚሆኑት ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ደንቦችና ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው" ቢል ፤ ስለዘዋሪዎችና፡ ወሮበሎች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ወንጀል ፡ ጠቀስ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ከመሆን ፡ ይልቅ ፡ የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግን ፡ ለማሻሻል ፡ የወጣ ፡ ይመስላል ። አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥራፈትነትን ፡ የሚመለከት ፡ ቁጥር ፡ ስለ ፡ አለው ፤ (ቁ. ፩፻፷፮ ፡ አደገኛ ፡ የሆኑ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት) ስለዚህ ፡ አጋጊዎች ፤ ለምንም ፡ እንኳ ፡ በግልጽ፡ ባይጽፉት ፡ ስለ ፡ ሥራ ፈትነት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ለመሻር ፡ የፈለጉ ፡ ይመስላል ። ስለዘዋሪዎችና ፡ ወረበሎች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ መሻሩን ፡ የሚያመለክተውን ፤ በፓብሊክ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፡ ኢንስቲትዩት ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኮንሶሊዴትድ ፡ ሎውስ ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ሕጎችን ፡ በጠቅላላ፡ የሚያሳይ) የሚለውን ፡ ተመልከት ። ሆኖም ፤ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ችሎት ፡ ሁለት ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎችን ፡ስለ፡ ዘዋሪዎችና፡ ወረበሎች፡በወጣው፡አዋጅ፡ሕግ፡ ቁ.፰ ፡ መሠረት ፡ ፈርዶባቸዋል ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ የወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ችሎት ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ ቁ. ፩፻፳፪/፶፰ ፡ ዓ.ም. ፤ ይኸን ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሎውንስታይን ፡ በ፲፱፻፷፭ ፡ እ. ኤ. አ. ፡ በጻፈው ፡ —ማቴሪያልስ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ስተዲ፡ ኦቭ ፡ ዘ ፡ ፒናል፡ ሎው ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ (የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለማጥናት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጽሑፎች) በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻—፲ ፤ ታገኘዋለህ ።

48. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አርቃቂ ፡ በፈረንሣይኛ ፡ የጻፈው ፡ ረቂቅ ፡ "ዐሥር" ዓመት፡ ይላል ፤ — " ሌ ዲስፖዚሲዮ፡ ዲ ፡ ፕሬዛንት፡ ኮድ፡ ነ፡ ሶንት ፡ አፕሊካብልዝ ፡ አዝ፡ እንፋ ፡ ን ፡ አያ፡ ፓዝ ፡ አቴያ ፡ ላ፡ አዥ፡ ዴ ፡ ነፍ ፡ እንሬቮሉ ።" ስለወጣት፡ (አካለ ፡ መጠን፡ ያላደረሱ) አጥፊዎች ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በተጠቀሰው ፡ ዕድሜ ፡ ሁሉ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ የአተረጓጐም ፡ ስሕተት፡ ተደርጓል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተደነገጉት ፡ ቅጣቶች ፡ አንዱን ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ከነሱም ፡ በጣም ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ወደሕክምና ፡ ድርጅቶች ፡ መግባት ፤ በዘመዶች ፤ ባሳዳጊ ፤ በማደጎ ፡ ልጅነት ፡ በሚቀበለው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ የርኅራኄ ፡ ተግባር ፡ በሚፈጽም ፡ ድርጅት ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ በበጎ ፡ አስተዳደግና ፡ በትምህርት ፡ መጠበቅ ፡ ተግሣፅ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ናቸው (ቁ. ፻፸፩ — ፸፱) ። ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመቀጮ ፡ ክፍያ ፤ የአለንጋ ፡ ቅጣት ፡ ወይም ፡ የተፈጸመው ፡ በደል ፡ ለአሥር ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ እሥራት ፡ የሚያስቀጣ ከሆነና ፡ አጥፊው ፡ የማይታረም ፡ መስሎ ፡ ከታየ ፡ እንዲያውም ፡ እሥራት ፡ ሊያዝ ፡ ይ ይችላል (ቁ. ፻፸ — ፩፻) ።

ለማሳከም ፡ ወይም ፡ በተጠባባቂነት ፡ ለማስተማር ፡ የተወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ የሚቋረጡት ፡ የሕክምናው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የጥበቃ፡ ተቈጣጣሪው፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ አለበለዚያም ፡ የአጥፊው ፡ ወጣት ፡ ዕድሜ ፡ አሥራ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሲሞላ ፡ ነው ። ወደ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ድርጅቶች ፡ የተላኩ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ወጣቶች ፡ ግን ፡ እዚያው ፡ የሚቈዩት ፡ ከአንድ፡ዓመት ለማያንስ ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ያጥፊው ፡ ዕድሜ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ከሞላ ፡ በኋላ ፡ እሥራቱ ፡ የሚቀጥለው ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው (ቁ. ፻፸፯) ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለፈተና ፡ በአመክሮ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ሕጉ ፡ ያዛል (ቁ. ፻፸፯) ። ነገር ፡ ግን ፡ ቅጣቱን ፡ አሳማዶ ፡ የፈተና ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት፡ በኩል፡ የተደራጀ ፡ ነገር ፡ በመታጣቱ፡ይኸ ፡ ውሳኔ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ አይቻልም ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በተጨማሪ ፡ ዕድሜያቸው ፡ በ፲፭ ፡ እና ፡ በ፲፰ ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ለሆነ ፡ ጥፋተኞች ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ አበጅቷል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ ደንበኞቹ ፡ ቅጣቶች ፡ ሊፈጸሙ ፡ ቢቻል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጣት ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ ጥፋቱን ፡ የሚያቃልሉ፡ ልዩ፡ ምክንያቶች፡ ሲመለከትና፡ ቅጣቱን፡ ሊያቃልል ፡ ይችላል (ቁ. ፶፮) ።

ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ ወጣት ፡ አጥፊዎች ፡ ከልጁ ፡ መልካም ፡ አጠባበቅ ይልቅ ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ወደሚታይበት ፡ ለአዋቂ ፡ አጥፊዎች ፡ ወደ ፡ ተዘጋጁ ፡ ተራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይቀርቡ ፡ ነበር ። በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በአዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ በወጣቶች ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ክስ ፡ ለመስማት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ያሉበት ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቋቋመ ። ይኸ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሳምንት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ፡ እንዲያስችል ፡ ልዩ ፡ የወጣቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ እስከ ፡ ተቋቋመበት ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም፡ ድረስ ፡ አገለገለ ። የሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ የማኅበራዊ ፡ አደጋ ፡ መከላከያ ፡ ዲሬክተር ፡ ለወጣቶች ፡ በተቋቋመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡትን ፡

ክሶች ፣ ለመስማት ፣ የወረዳ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ዳኛ ፣ ሁኖ ፣ ተሹሟል ። በጠቅላይ ፣ ግዛቶች ፣ ውስጥ ፣ አሁንም ፣ ቢሆን ፣ ወጣቶች ፣ አጥፊዎች ፣ የሚቀርቡት ፣ ለዓዋቂ አጥፊዎች ፣ በተቋቋሙት ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ነው ።

የ፲፱፻፶፬ ፣ ዓ. ም. የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ወጣት ፣ አጥፊዎችን ፣ በሚመለከቱ ፣ ጉዳዮች ፣ በኩል ፣ ልዩ ፣ የአቀጣጥ ፣ ሥነ ፣ ሥርዐት ፣ ደንቦችን ፣ ያዛል (ቁ. ፻፸፩—፻፹) ። እነዚህ ፣ ደንቦች ፣ የተፈጸመው ፣ ወንጀል ፣ ከአሥር ፣ ዓመት ፣ ለሚበልጥ ፣ ጊዜ ፣ በጽኑ ፣ እሥራት ፣ ወይም ፣ በሞት ፣ የሚያስቀጣ ካልሆነ ፣ ሕግ ፣ አስከባሪው ፣ የክስ ፣ ማመልከቻውን ፣ አዘጋጅቶ ፣ ሳይቀርብ፣ጉዳዩ እችሎት ፣ ክፍል ፣ ሳይሆን ፣ ሌላ ፣ ክፍል ፣ አለ ፣ ብዙ ፣ ድግድግ (አለ ፣ ፎርማሊቲ) ፣ እንዲሰማ ፣ ይደነግጋሉ ። አቤቱታው ፣ ለተከሳሹ ፣ ከተነበበለት ፣ በኋላ ፣ ጥፋቱን ፣ ቢያምን ፣ ፍርድ ፣ ወዲያውኑ ፣ ሊሰጥ ፣ ይቻላል ። ጥፋቱን ፣ ቢክድ፣ግን፣ ለወጣቶች ፣ በተሾመው ፣ ዳኛና ፣ በሚከላከልለት ፣ ጠበቃ ፣ ወይም ፣ አሳዳጊ ፣ ምስክሮች ፣ እየተጠየቁ ፣ ጉዳዩ ፣ ይደመጣል ። ዳኛው ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ከተቋቋሙት፣መሠረት፣ ሐሳቦች፣ሳይዛባ፣የአጥፊውን፣ቅጣት፣ ለመወሰን፣ እንዲችል፣ ቅጣቱ ፣ ታግዶ ፣ የፈተና ፣ ጊዜ ፣ ስለሚሰጥ ፣ አኳኋን ፣ ከፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጋር ፣ ተባብረው ፣ ከሚሠሩት ፣ ከሁለቱ ፣ የጠባይ ፣ ማሻሻል ፣ ጥበቃ ፣ ዘበኞች ፣ በአንዱ ፣ ጽሑፍ ፣ መግለጫ ፣ ይዘጋጃል ።[49] ልጃገረዶች ፣ የሚጠበቁበት ፣ ቤት ፣ ገና ፣ ስላልተዘጋጀላቸው ፣ ብዙውን ፣ ጊዜ ፣ ወደ ፣ ወላጆቻቸው ፣ ወይም ፣ ወደ ፣ አሳዳጊዎቻቸው ፣ ይመለሳሉ ፤ ወይም ፣ አንዳንድ ፣ ልዩ ፣ ሁኔታዎች ፣ በተገኙ ፣ ጊዜ ፣ ይታሠራሉ ።[50]

በኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ ወጣቶች ፣ አጥፊዎችን ፣ እንደገና ፣ ለመልካም ፣ ሰውነት ፣ እንዲበቁ ፣ ለማድረግ ፣ የሚረዳ ፣ ድርጅት ፣ በ፲፱፻፶፮ ፣ ዓ. ም. በአዲስ ፣ አበባ ፣ የተቋቋመው ፣ የጠባይ ፣ ማረሚያ ፣ የወጣቶች፣ ማቆያና ፣ ማሠልጠኛ ፣ ትምህርት፣ ቤት፣ ብቻ፣ ነው ።[51] እስከ፣ ግንቦት፣ ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ. ም. ድረስ፣ ትምህርት ፣

49. በ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ. ም. የወጣት ፣ (እካለመጠን ፣ ያላደረሱ) ፣ ወንጀለኞች ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ዳኛ ፣ ከአጥፊዎቹ ፣ በመቶ ፣ ፺፰.፰፫ን ፣ ወደ ፣ ጠባይ ፣ ማረሚያ ፣ የወጣቶች ፣ ማቆያና ፣ ማሠልጠኛ ፣ ትምህርት ፣ ቤት እንዲላኩ ፤ በመቶ ፣ ፲፫ ፣ ቅጣቱ ፣ ሳይፈጸምባቸው ፣ የፈተና ፣ ጊዜ ፣ እንዲሰጣቸው፤ በመቶ ፣ ፴፭ ፣ ደግሞ ፣ ወደቤተሰቦቻቸው ፣ እንዲመለሱ ፣ ፈርዶዋል ። ከላይ ፣ የተጠቀሰው ፣ የራዲሉ ፣ ጽሑፍ ፣ ገጽ ፣ ፩ ።

50. የወጣት (እካለ ፣ መጠንያላደረሱ) አጥፊዎች ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ዳኛ ፣ የሆኑት ፣ አቶ ፣ እንዳርጋቸው ፣ ተሰፋዬ ፣ እ. ኤ. አ. ዲሰምበር ፣ ፲፯ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፷፬ ፣ ባደረግንላቸው ፣ ጥያቄ ፣ መሠረት፤ ለልጅ ፣ አገረዶች ፣ የሚሆን ፣ ድርጅት ፣ ካለመኖሩም ፣ በላይ ፤ ዋናው ፣ ችግር ፣ የአገልግሎት ፣ መሣሪያዎች ፣ አለመኖርና ፤ በጠቅላይ ፣ ግዛቶች ፣ ፖሊስና ፣ በወጣት ፣ አጥፊዎች ፍርድ ፣ ቤት ፣ መካከል ፣ ኅብረት ፣ አለመኖሩ ፣ ነው ፣ ሲሉ ፣ ገልጸዋል ።

51. በየጠቅላይ ፣ ግዛቱ ፣ ያሉ ፣ ወጣት ፣ ወንጀለኞች ፣ በእሥር ፣ ቤቶች ፣ ልዩ ፣ ቦታ ፣ ካለ ፤ የሚታሠሩ ፣ ከሌሎቹ ፣ እሥረኞች ፣ ተለይተው ፣ ነው ።

ቤቱ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሥር፡ ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ጋር ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ነበረው ። ነገር ፡ ግን ፡ እየተስፋፋ ፡ በሚሄደው ፡ የትምህርትና ፡ አጥፊውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ ማብቃት ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፡ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ እድገት ፡ ሚኒስቴር፡ ሥር ፡ ወዳለው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት፡ ክፍል ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ተዛወረ ።

ድርጅቱ ፡ ሲገቡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ በዘጠኝና ፡ በአሥራ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ መካከል ፡ ሁኖ ፡ ለሚታሠሩ ፡ ወይም፡ ለሚታረሙ፡ አንድመቶ፡ ወንዶች፡ ልጆች፡ በቂ ፡ ሥፍራ ፡ አለው ።[52] ትምህርት ፡ ቤቱን፡ የሚያኪያሂዱት ፡ አንድ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሁለት ፡ የጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኞችና ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካይነት ፡ የአንደኛን ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ፤ ከአነስተኛ ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፤ በጠባይ ፡ ማሻሻያ ፡ ጥበቃ ፡ ዘበኞች ፡ ከሚሰጠው ፡ ጥቂት ፡ ሕክምናና ፡ የችግር ፡ ውይይት ፡ በቀር ፡ የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ በመታጣታቸው ፡ ልጆቹ፡ ምንም ፡ መምሪያና ፡ ምክር ፡ አያገኙም ። የትምህርት ቤቱ ፡ በድርጅቱና ፡ በአቅዱ ፡ ልል ፡ የሆነ ፡ በመዛሪያዎችና፡ በቤት ፡ ሁኔታ ፡ ረገድ ደህየት ፡ ያለ፤ በቂ ፡ ሠራተኞች ፡ የሌሉት ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። እስካሁን ፡ ድረስ ከእሥር ፡ ቤት ፡ ሲወጡ ፡ ለወጣቶች ፡ አጥፊዎች ፡ የሚደረግ ፡ ጥንቃቄ ፡ ወይም ፡ መከታተል ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የለም[53] ! ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ኃላፊነት ፡ የተጣለባቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አጥፊውን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ የማብቃትን ፡ መሠረተ፡ ሐሳቦችን ፡ ይደግፋሉ ፤ በዚህም ፡ ረገድ ፡ ደህና ፡ በመራመድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ እንደገና ፡ ለማደርጀትና ፡ ለማስፋፋት ፡ አንድ ፡ የተሟላ ፡ አቅድ ፡ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ፡ እድገት ፡ ሚኒስቴር ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ተዘጋጅቷል ፤ ሥራ ፡ ላይ ፡ ቶሎ ፡ እንደሚውልም ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለ ።[54]

በወጣቶች ፡ የሚደረገውን ፡ ወንጀልና፡ ዘዋሪነት፡ ለመቆጣጠር ፤ እንደዚህ ያሉትንም ፡ ወጣቶች፡ ለማኅበራዊ ኑሮ፡ ጠቃሚ ፡ አባሎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመርዳት የንጉሠ ፡ ነገሥቱ፡ መንግሥት፡ ወጣት ፡ አጥፊዎችን ፡ እንደገና ፡ ለመልካም ፡ ሰውነት ፡ እንዲበቁ ፡ ለማድረግ፡ ጥረት ፡ ያደርጋል ፡ የሚል ፡ መሠረት ፡ ሐሳብ ፡ በሁ

52. በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ፻፴፰ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ከእነዚሁ፡ውስጥ ፻፳፯ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ የገቡ ፡ ሲሆን ፤ ዐሥራ ፡ ሁለቱ፡ለጊዜው፡እንዲቆዩ፡የተላኩ ፡ ነበሩ ። ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የራዴሉ ፡ ጽሑፍ ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ።

53. የተጠቀሰውን፡ የራድሉ ፡ ጽሑፍንና ፡ ሲንግ ፡ "አዲስ ፡ አበባ፡፡ ሆም ፎር፡ ጁቬናይል ፡ ዴ ፡ ሊንኲዌንትስ ፡ (በአዲስ ፡ አበባ ፡ የወጣት ፡ ወንጀለኞች ፡ ቤት)" በሚል ፡ እርእስት ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ (እ. ኤ. አ.) የጻፈውን ፡ ተመልከት ።

54. የተጠቀሰውን ፡ የራዴሉ ፡ ጽሑፍን ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ተመልከት ።

ለተኛው፡ የኢትዮጵያ፡ የአምስት፡ ዓመት፡ የእድገት፡ እቅድ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። [55]
እዚህ ፡ ግብ፡ ለመድረስ፡ አሁን፡ አዲስ፡ ሕግ ፡ እንዲወጣ፡ በጣም ፡ ያስፈልጋል ። [56]
Under the Penal Code, infants who have not attained the age of nine[48] are deemed not to be criminally responsible: offenses committed by such infants are to be dealt with by the family, school or guardian concerned (Art. 52). Children between the ages of nine and fifteen are referred to as "young persons" and are not subject to the ordinary penalties applicable to adults (Art. 53). After a determination of guilt, sentence is assessed taking into account the age, character, degree of mental and moral development of the young person and the educational value of the measures to be applied (Art. 54). The court may use one of the measures from a prescribed list, the most important of which are: admission to a curative institution, supervised education by relatives, guardian, adopting family or charitable institution, reprimand or admission to a corrective institution (Arts. 161-69). In special circumstances the court may require the payment of a fine, corporal punishment or even imprisonment if the offense committed is normally punishable with ten or more years rigorous imprisonment and the offender appears incorrigible (Arts. 170-73). Measures for treatment or supervised education are terminated only when the medical or supervisory authority thinks it is necessary or when the young offender reaches the age of eighteen. In the case of young persons sent to correctional institutions, the commitment is for not less than one year nor more than five years; only in exceptional cases may it extend beyond the age of eighteen years (Art. 167). The Code further provides for conditional release (Art. 167) but lack of an organized probation system has prevented implementation of this provision. The Penal Code also establishes a category of offenders between the ages of fifteen and eighteen, and although ordinary penalties are applicable, the court may, in assessing sentence, take into account special mitigating factors (Art. 56).

Before 1961, young offenders were taken before ordinary adult courts where the offense committed was of more importance than the welfare of the

47. The Penal Code of 1957 expressly repeals "the Penal Code of 1930 and all proclamations amending the same". Although Art. 3 retains "police regulations and special laws of a penal nature," the Vagrancy and Vagabondage Proclamation seems to be closer in nature to legislation amending the Penal Code of 1930 than a special law of a penal nature. The new Penal Code regulates the area of vagrancy (Art. 471, *Dangerous Vagrancy*) and the legislature probably intended, therefore, although it did not expressly so state, to repeal earlier legislation dealing with vagrancy. See Consolidated Laws of Ethiopia, Institute of Public Administration, which lists the Vagrancy and Vagabondage Proclamation as impliedly repealed by the Penal Code of 1957. In 1961, however, the Juvenile Division of the High Court did convict two juveniles under Art. 8 of the Vagrancy and Vagabondage Proclamation, High Court, Juvenile Division, Crim. File No. 522/53 E.C. (1961 G.C.), in Lowenstein, *Materials For the Study of the Penal Law of Ethiopia* 189-90 (1965).

48. The French text of the drafter of the Penal Code states "ten" years: "Les disposition du présent code ne sont applicable aux enfants n'ayant pas atteint l'age de neuf ans revolus." The same translation error has been made for each age mentioned in the section on young offenders.

child. In 1961, a special tribunal of three High Court judges was constituted to hear juvenile cases under the new Criminal Procedure Code; this court functioned until December, 1962 when a special juvenile court was established by order of His Majesty to sit twice a week in Addis Ababa. The Director of Social Defense in the Ministry of National Community Development has been appointed a Woreda Court judge for purposes of hearing cases in the Juvenile Court. In the provinces, young offenders are still heard before adult courts.

The Criminal Procedure Code of 1961 sets out special procedural rules in cases concerning young persons (Arts. 171-80). These rules provide for an informal hearing in chambers without a charge framed by the public prosecutor unless the offense committed is punishable with rigorous imprisonment exceeding ten years or death. A complaint is read to the accused and if admitted, conviction may follow. If not admitted, a hearing is held at which all witnesses are interrogated by the juvenile judge and by the defense, who is either a lawyer or guardian. A probation report is prepared by one of two probation officers presently attached to the court, enabling the judge to sentence the offending youth in accordance with the principles established in the Penal Code.[49] As there is as yet no home for girls, they are usually returned to parents or guardians or, in exceptional cases, committed to prison.[50]

The only institution in Ethiopia concerned with the rehabilitation of juvenile offenders is the Training School and Remand Home established in 1942 in Addis Ababa.[51] Until May, 1964 the school was closely connected with the Prison Administration of the Ministry of Interior but consistent with the growing philosophy of education and rehabilitation, it was in 1964 transferred to the Division of Social Welfare in the Ministry of National Community Development.

The institution provides accommodation for one hundred boys either committed or on remand whose ages upon admission range from nine to eighteen years.[52] The school is staffed by a superintendent, two probation officers and a number of teachers who provide elementary education through the Ministry of Education. Aside from some academic training and a small amount of therapy and case work provided by the probation officers, the boys do not receive any guidance and counseling due to the lack of trained personnel. The

49. In 1956 E.C. (1963-64 G.C.), the Juvenile Court judge committed 58.5% of all cases dealt with to the Training School and Remand Home; 13% were placed on probation and 35% were returned to parents or guardians. Riley, *op. cit.* at 20.

50. Ato Andargatchew Tesfaye, the present Juvenile Court judge, states that aside from the lack of an institution for girls, the main problems are poor equipment and a lack of co-operation between provincial police and the Juvenile Court. Interview, Dec. 16, 1964.

51. Young offenders in the provinces are sent to segregated sections of prisons where such facilities exist.

52. In December, 1964, the School was accommodating 138 boys; 126 formally committed and twelve on remand. Riley *op. cit* at 26.

organization of the school and its planning tend to be loose, equipment and housing relatively poor and staff inadequate.[53] There has been almost no after-care or follow-up of juvenile offenders. Those who are now responsible for the school are in sympathy with the principles of rehabilitation, however, and are beginning to make headway. A comprehensive reorganization and development plan for the school has recently been prepared in the Ministry of National Community Development and there is every hope that it will soon be implemented.[54]

The *Second Five Year Development Plan* 1963-1967 *G.C.* includes a statement in principle that the Empire will undertake "the rehabilitation of youth so that delinquency and vagrancy among teen-agers is controlled and such youths are helped to become useful members of society."[55] New legislation is now badly needed to realize this ideal.[56] The Social Welfare Division of the Ministry of National Community Development is initiating and coordinating efforts in this field and is presently drafting a comprehensive Child Welfare Act. The police force has recently opened a special department dealing with juvenile affairs, and the Municipality of Addis Ababa and such organizations as the Y.M.C.A. and Scouts have begun to form community centers, clubs and other facilities to provide activity and training for youths. Although Ethiopia has been slow in realizing the necessity of preventing juvenile crime and caring for young offenders, it is fortunate to have established a good beginning before the problem has assumed serious proportions.

V. Conclusion

The above is a brief outline of the penal system of Ethiopia. Although a good deal more detail could be added with respect to written law, very little, indeed, is known of the day to day functioning of the system. As has been seen, there is considerable disparity between the principles and ideals set out in the new positive law and their application within the penal system. Both basic research and expanded educational opportunity are very much needed if this gap is to be substantially narrowed. A good start has been made and encouragement can be taken from the growing awareness of the existence of these problems and the desire on the part of many in Ethiopia to see to their eventual solution.

53. See Riley, *idem*, and Singh, "Addis Ababa Home for Juvenile Delinquents" (1959).
54. Riley, *ibid.*, Chap. II.
55. (Addis Ababa, Berhanena Selam Printing Press, 1962) 301.
56. See High Court, Juvenile Division, Crim. File No 522/53 *supra* at note 50 where the Court at the end of its opinion states:

> "The Court considers that a resumé of this judgment should be sent to His Excellency, the Minister of Interior and His Excellency, the Minister of Justice, through the President of the High Court, together with explanations of the difficulties with which the Juvenile Court is faced in dealing with juveniles under the existing legislation."

ሕግና ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ።[1]

ከጆ. ክሪችኖቢች ።

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

መ ግ ቢ ያ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ከቀሩት ፡ ከሰሐራ ፡ በስተደቡብ ፡ ከሚገኙት ፡ አፍሪቃውያን ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ አኳኋን ፡ በጣም ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነትን ፡ ያሳያል ። ኢትዮጵያ ፡ ተለይታ ፡ የራሷ ፡ የሆነ ፡ ጥንታዊ ፡ ሕግ ፡ ነበራት ፤ አሁንም ፡ ከጥንታዊ ፡ ባህሏ ፡ ከልማድ ፡ ሕግ ፡ (ከኮመን ፡ ሎው) ፡ እና ፡ ከአህጉራዊው ፡ ኤውሮጳ ፡ ሕግ ፡ ፅንሰ -ሐሳብ ፡ የተዛመደ ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ ችላለች ። እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የግል - መብት - ነክ ፡ ሕግና ፡ (ፕራይቬት ፡ ሎው) ፡ የጋራ (የሕዝብ) - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ (ፐብሊክ ፡ ሎው) ፡ የሚደረገው ፡ የእድገት ፡ እርምጃ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያልነበረ ፡ አዲስ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ነው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፖለቲካ ፡ አቋሞች ፡ ጥንታዊውን ፡ የአገዛዝ ፡ ፅንሰ - ሐሳብ ፡[2] ሳይለቁ ፡ ቀስ ፡ በቀስና ፡ በጥንቃቄ ፡ ያደረጉትን ፡ መሻሻል ፡ ስንመለከት ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከቀሩት ፡ አፍሪቃውያን ፡ አገሮች ፡ የተለየች ፡ መሆኗን ፡ እንገነዘባለን ፤ በግል - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ ልክ ፡ የዚሁ ፡ ሁኔቴ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ። ዳግም ፡ ከሌሎቹ ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ በመለየት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ በግል - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ መሻሻል ፡ ጠቅላላና ፡ ድንገተኛ ነው ። የኢትዮጵይ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መሻሻል ፡ በዚች ፡ ብጥብጥ በተጸረራት ፡ የአፍሪቃ ፡ አህጉር ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሰላምና ፡ የፖለቲካ ፡ መረጋጋት ፡ ያለባት ፡ አገር ፡ የማድረግን ፡ ውጤት ፡ አስገኝቷል ። የግል - መብት ፡ ነክ ፡ ሕጋችንም ፡ የከመ ፡ ቅጽበት ፡ መሻሻል ፡ ምክንያቶች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ተብራርተዋል ።

በአንድ ፡ በኩል ፡ የመሬት ፡ ይዞታን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግን ፡ እና ፡ ውርስን ፡ የሚመለከት ፡ የጐሣ ፡ ልማድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ እና ፡ በአንድ ፡ አካባቢ ፡ የተወሰነ ፡ መልክ ፡ ስላለው ፤ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ ውልን ፡ የመሰለ ጉዳይን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎች ፡ ጨርሰው ፡ አለመኖር ፡ ንግድን ፡ ገንዘብን ፡ በጥ

1. የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ መጽሔት ፡ ሾልየም ፡ ፩ ፡ ቍ ፩ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም.) ፡ ገጽ ፡ ፶፯ ፡ ላይ ፡ ከጆርጅ ፡ ክሪቼኖቪች ፡ ተጽርሶ ፡ የወጣው ፡ "ሕጊው ፡ ሌጂስሌቲቭ ፡ አፕሮች ፡ ቱ ፡ ካስተመሪ ፡ ሎው" ፡ (የሕጉ ፡ ወደ ፡ ልማድ ፡ አዲስ ፡ አቀራረብ) ፡ የሚለው ፡ ነው ። የዚህ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ጨርሶ ፡ አልቋል ፤ በሱም ፡ ላይ ፡ የወጣው ፡ ድርሰት ፡ በሕግ ፡ መጽሔት ፡ ወይም ፡ ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ታትሞ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ አልወጣም ።

2. ከጆርጅ ፡ ክሪችኖቪች ፡ "ዘሬዥም ፡ ኦቭ ፡ አሰምብሊ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ" (ለኢትዮጵያ ፡ የምክር ፡ ቤቶች ፡ ሸንጎ ፡ አዘረጋጋ) ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ መጽሔት ፡ ሾልየም ፡ ፩ ፡ ቍ ፩ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም.) ገጽ ፡ ፸፱ ፡ ላይ ፡ ከወጣው ፡ ጋር ፡ አነጻጽር ።

ቅም ፡ ላይ ፡ ማዋሐንና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ መሻሻልን ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ [3] እንደ ፡ ጨቆኑት ፡ የታመነ ፡ ነው ። የአፍሪቃን ፡ የግል - መብት - ነክ ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ወደ ፡ ተፈላጊው ፡ ዘመናዊነት ፡ ለማራመድ ፡ ሥራው ፡ ተጀምሯል ፤ ካልተጀመረም ፡ የመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ አልፏል ። ባህል ፡ በተስፋፉባቸውና ፡ ጠንካራ ፡ በሆነባቸው ፡ ከላይ ፡ እንደጠቀስናቸው ፡ ዐይነት ፡ የሕግ ፡ ክፍሎች ፡ ተፈላጊ ፡ ዘመናዊነትን፡ ለማድረግ ፡ በጣም፡ ያዳግታል ። እንደዚህ ፡ ከሆነ ፤ በምን ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ የግል - መብት ፡ ነክ፡ ሕግ ፡ ሊሻሻል ፡ ይችላል ? ላለው ፤ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማሻሻል ፡ (ኢቮሉሽን) ፡ ወይስ ፡ በጠቅላላው ፡ ገለባብጦ ፡ መለወጥ ፡ (ሬቮሊሽን) ፡ ይበጅ ፡ ይሆን ?

የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ረቂቅን ፡ ያወጣው ፡ ሊቅ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አር. ዴቪድ ፡ "በጠቅላላ ፡ ገለባብጦ ፡ መለወጥ ፡ (ሬቮሊሽናሪ) ፡" ይሻላል ፡ የሚለውን ፡ ሐሳብ ፡ ተከትሏል ፡ አስተያየቱንም ፡ እንደሚከተለው ፡ ገልጾአል ፡—

የኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ወደፊት ፡ መራመድና ፡ ዘመናዊ ፡ መሆን ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ የሚሠራበትን ፡ ሕግ ፡ መውሰድ ፡ አስፈላጊ ፡ አደረገው ። ---- ይህም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ተፈላጊውን ፡ ዝቅተኛ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የተረጋገጠ ፡ ሕግ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ---

እኛ ፡ (አውሮጳውያን) ፡ የግል - መብት - ነክ ፡ ሕጋችን ፡ የማይለዋወጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ እንላለን ። ዳግም ፡ በልማድ ፡ ከሚሠሩባቸው ፡ ሌላ ፡ አዳዲስ ፡ ሕጎችን ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መጫን ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ በጣም ፡ ያስቸግረናል ። --- ሆኖም ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ አስተያየት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ፡ አይደለም ። --- ጥቂቶችን፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጡትንና ፡ አሁንም ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ልማዶች ፡ እንደያዘች ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕጎቿን ፡ አቋም ፤ የሕዝቧ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ድረስ ፡ ቢለወጥ ፡ እንኳ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ትሻለች ። ስለዚህም ፡ ኢትዮጵያውያን፡ አዲሱ፡ የፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ የጥንት ፡ ልማዶችን ፡ ለማጠቃለል ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አይገምቱም ። የሕዝቡ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በጠቅላላው ፡ እንዲለወጥ፡ የታሰበ፡ ሥንጠረዥ ፡ እንዲሆን ፡ ስለሚመኙ ፤ በይበልጥ ፡ ሕጉ፡ ወደፊት ፡ እንዲፈጠር ፡ ለታሰበው፡ የማኅበራዊ፡ ኑሮ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ አዲስ ፡ ደንቦች ፡ እንዲያዝ ፡ ይጠይቃሉ ። (የተቀሩትን ፡ ክርክሮች ፡ ከዚህ ፡ አልጠቀስናቸውም ።) [4]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸውን ፡ አስተያየት ፡ የአሁኑ ፡ ደራሲ ፡ ይደግፈዋል ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የባህላዊ ፡ ደንቦች ፡ ለአንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ (ለምሳሌ ፡ ውል) ፡ በፍጹም ፡ አለመኖርና ፡ በሌላም ፡ በከፊል ፡ ደግሞ ፡ (ለምሳሌ ፡ የቤተ ፡

[3] በላለፉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት፡ ለምሳሌ ፡ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ መጽሔትንና ፡ የሬሰይ ፡ ፒናን ፡ ተመልከት ።

[4] ክሬኔ ፡ ዴቪድ ፡ "ኤ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ ፎር ፡ ኢትዮፒያ" ፡ (ፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ) ቱለይን ፡ ሎው ፡ ሬቪው ፡ (የቱሉየን ፡ ሕግ፡ መጽሔት) ቮልዩም፡ ፴፯ ፤ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. (ከገጽ ፡ ፫፻፰—፫፻፱ ፡ እና ፡ ፫፻፫ ።

ዘመድ ፡ ሕግ) ፡ የአብዛኞቹ ፡ የባህል ፡ ደንቦች ፡ አጠራጣሪ ፡ ወይም ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ከጐሣ ፡ ጐሣና፡ ከጊዜ ፡ ጊዜ፡ የተለያዩ፡ መሆን ፤ የባህል፡ ደንቦችን፡ በሙሉ አጠቃሎ ፡ ብቻ ፡ በሕግ፡ ለማውጣት ፡ ይቅርና ፡ ጉዳዩን፡ ለማጥናት፡ እንኳ ፡ የማ ይሞከር ፡ አደረገው ። ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ ሕግ፡ እንዲያው ፡ በቀላሉ፡ "ተገኝቶ" መጽደቅ ፡ አይችልም ፡ ነበር ፡ ከአገር፡ ውስጥና ፡ ከውጭ፡ አገር፡ መነሻ ፡ ነቅሶ ፡ በአእምሮ ፡ሚዛን ፡ አመራረጥ ፡ መደንገግ ፡ ነበረበት ። ለዚህች ፡ አገር ፡ አንድ ዐይነት ፡ መልክ ፡ --- የሆነ ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ የሚቻል ፡ የነበረው ፡ ዐው ቀው ፡ በሚያደርጉት ፡ የማሻሻል ፡ ሙከራ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ በሰጡት ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መሠረት፡ የመጀመሪያው ፡ ነገር ፡ "የንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ግዛታችን ፡ የማኅበራዊ ፡ አኗኗር ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ወደ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥል ጣኔ ፡ ለማራመድ" ፡ ነበር ። ሕግ ፡ የሚገኘው፡ ባልታሰበና፡ ሊታወቅ፡ በሚችል ፡ መንገድ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከባህል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ደጋግመው ፡ የሚያስተምሩ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮንና፡ ታሪክን ፡ በሚመለከት፡ ላይ፡ የተመሠረተ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ሳይንስ ፡ ተከታዮች ፡ እምነት ፡ ዕውነት ፡ የሚመስለው ፡ ----እንደነገሩ ፡ ሁኔታ፡ በማወዳደር ፡ ጽኑ ፡ አካባቢ፡ ባለበት፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸ፡ እምነት ፡ (ትም ህርት) ፡ ጥንታዊ ፡ ባህል ፡ ላላቸው ፡ የውጭው ፡ ዓለም ፡ ያመጣው፡ የሥልጣኔ ፡ ውድድር ፡ በድንገት ፡ የገጠማቸው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላሉ ፡ አገሮች ፡ እምብ ዛም ፡ አይስማም ። እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕጎችን ፡ ያቀረ በው ፡ ዓላማ ፡ የሚሠራበትን ፡ ልማድ ፡ ለማስከበር ፡ ሳይሆን ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡አንድ የሆነ ፡ የሕግ ፡ መነሻ ፡ መደብ ፡ ለመፍጠር ፡ ነው ። (ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ለመረዳት ፡ እንደሚቻለው ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የማሻሻል ፡ ዓላማ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።) [5]

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ልማዶች ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያላ ቸው ፡ ክፍል ፡ አሁን ፡ ተቀንሷል ። ሆኖም ፡ በፍጹም ፡ አልጠፉም ፡ ስለነሱም ፡ ጥናት ፡ ቢደረግ ፡ ጥቅም ፡ ሳይሰጥ ፡ አይቀርም ። በዚህች ፡ ጹሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተንት

5. ከጆርጅ ፡ ክሽቼናቢች ፡ "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሲቢል ፡ ኮድ ፤ ኢትስ ፡ ዩዝፉልነስ ፡ ሪሌሽን ፡ ቱ ፡ ከስተም ፡ ኤንድ ፡ አፕሊክቢሊቲ" ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ጥቅሙ ፡ ከአገር ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ዝምድናና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉ) ፤ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፮ ፡ ቁ. ፫ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም.) ፡ ከገጽ ፡ ፫፻፫ ፫፻፬ ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የዚህ ፡ መሻ ሻል ፡ መሳካት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ትምህርትና ፡ ከፍትሕ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙትን ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ ስሰሙ ፡ ብቻ ፡ የመቀበል፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣው ፡ (ባህላዊ) ፡ አስተያየት ፡ ሳይሆን ፤ አይቀርም ። (ይህም ፡ በቀረው ፡ በአፍሪካ ፡ ክፍል ፡ ሀገር ፡ ከሚገ ኘው ፡ ከቶውን ፡ ከበጎው ፡ ሳይለዩ ፡ የጥንታዊ ፡ አባቶችን ፡ ልማድ ፡ በኩለንተናው ፡ እሜን ፡ ብሎ ፡ ከመቀበል ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ በማነጻጸር ፡ ነው ።) በኢትዮጵያ ፡ ማኅበራዊ ፡ አቋም ፡ ወግ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የምርምር ፡ ፍላጎት ፡ ይኸንን ፡ መልክም ፡ አስተያየት ፡ በ«ልማዳዊ ፡ ሕግ» ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ መትጋት ፡ ሳይለውጠው ፡ የቀረ ፡ ይመስላል ።

ነን ፡ በማጥናት ፤ ልማድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የያዘውን ፡ቦታ ፡ እና ያለን ። እንዲሁም ፤ ልማድን ፡ የሚሽረውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፤ ስለ ሱም ፡ የተሰጡትን ፡ መግለጫዎች ፡ በተጨሪ ፡ ልማድን ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እን ዲውል ፡ የሚያስችሉትን ፡ አምስቱን ፡ መንገዶች ፡ ተራ ፡ በተራ፡ እናብራራለን ። በመጨረሻም ፡ መደምደሚያ ፡ ይሰጣል ።

ልማድን ፡ የሚሽረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ።

የሎንዶን ፡ ስብሰባ ፡ ስለ ፡ "ፊዊቸር፡ ኦቭ፡ ሎው ፡ ኢን ፡ አፍሪካ" ፡ (የሕግ ፡ የወደፊት ፡ ሁናቴ ፡ በአፍሪቃ፡ ውስጥ) ፡ (እ. ኤ. አ. ጥር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. በሚል ፡ አርዕስት ፡ ካደረጋቸው ፡ ክርክሮች ፡ አንደኛው ፡ ሕግ ፡ አውጪዎችና ፡ ዳኞች ፡ ልማድን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ከጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ማስማማት ፡ እንደሚ ችሉ ፡ ነው ። [6] በዚህ ፡ ስብሰባ ፡ በይፋ ፡ የጸደቀው ፡ የቀስ፡ በቀስ ፡ ማለማመድ ፡ ዘዴ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሉንዶኑ ፡ ስብሰባ ፡ በተደረገበት ፡ ዓመት ፡ የወጣው ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ልማድን ፡ አብዛኛውን ፡ ሙሉዊ ፡ አድርጎ ፡ ከሚሽረው ፡ ከኢትዮጵያው ፡ አቀራረብ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ቁ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፤

<u>የተሻሩት ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች ።</u>

<u>ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ፡ ከሌለ ፡ በቀር፡ በዚህ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈውይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ስለተተካ ፡ ተሽረዋል ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ተቃራኒ ፡ ወይም ፡ ያለፉ ፡ ሕጎች ፡ ቢሆኑም ፡ የቀድሞ ፡ ሕግና ፡ ልማዶችን ፡ ሁሉ ፡ ይሽራቸ ዋል ። በፍትሐ ፡ ብሐር፡ ሕግ ፡ ቍ. ፫ሺ፫፻፵፯ ፡ ውስጥ፡ "በዚህ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች" ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ "ከዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙትን" ፡ በሚል ፡ መተካት ፡ የባህልንና ፡ የልማ ድን ፡ መውደም ፡ ያሳንሰው ፡ ነበር ። ይህ ፡ አነጋገር ፡ የመሻሪያው ፡ ሕጉ፡ ሕግን ፡ የሚያሟሉትን ፡ ልማዶች ፡ ሳይነካ ፤ በሚቃወሙት ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይወ ሰነው ፡ ነበር ። [7] በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ይህ፡ ያለፈን፡ ሕግ ፡ ሙሉዊ ፡ አድርጎ ፡ አጥ ፍቶ ፡ መሻር ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደርጎ ፡ የማይታወቅ ፡ ነው ። ይልቁኑ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ሕግ ፤ ቬንቶዝ ፡ ፴ ፤ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፤ የሚመሳሰል ፡ ነው ።

6. ኤ. ኤን. አሎት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያወጣውን ፡ " ዘ ፡ ፊውቸር፡ ኦቭ ፡ ሎው ፡ ኢን ፡ አፍሪካ " ፡ (የሕግ ፡ የወደፊት ፡ ሁናቴ ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ) ፡ ሎንዶን ፤ በተርወርዝ ፡ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፷ ፡)ዓ. ም. የታ ተመውን ፡ ተመልከት ።

7. እርግጥ ፡ ነው ፡ ተፈልጎ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ጠቅላላ ፡ ሽረ ፡ አንቀጽ ፡ ሳያወጣ ፡ ይህንኑ ፡ ዐይነት ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ በተቻለ ፡ ነበር ።
እንደዚሁ ፡ (ዐይነቱ ፡ ዘዴ ፡ «ባልተገለጸ ፡ አኳኋን» ፡ የተሻሩ ፡ ሕጎችን ፡ የመቀበል ፡ ልማድ ፡ ለሌላው ፡ ኅብረ ፡ ሰብ ፡ እምብዛም ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም ።)

ኤም. ፕላኒዮል ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ ትሬታይዝ ፡ (ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያዘጋጀው) ፡ መጽሐፉ ፡ [8] ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ አስተያየቱን ፡ ሰጥቷል ፤ "ያ ፡ ድንጋጌ ፡ (ሕጉ-ግ) ፡ የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግን ፡ ሲያውጅ ፡ ማንኛውንም ፡ የቀድሞ ፡ ሕግ ፡ ሻረ ። — እንደዚህ ፡ ካለው ፡ ታላቅ ፡ አደራረግ ፡ ጋር ፡ የሚነፃጸር ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ አንድም ፡ አልነበረ — ።" ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የፈረንሣይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ እየተሻሻለ ፡ የመጣውን ፡ ሕግ ፡ አሠራር ፡ ለመጨረሻ ፡ ሲያጠናቅቅ ፤ የኢትዮጵያው ፡ ፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ያልተለመደ ፡ አዲስ ፡ የሕግ- ፅንሰ- ሐሳብ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ አስመጣ ። ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ውጤት ፡ "ሕዝቡ ፡ እንዳይሠራም ፡ ቢደነገግ ፡ የተከለከለውን ፡ ተግባር ፡ ስለማይተው ፡ ጥቅመቢስ" ፡ [9] ያደርገዋል ፡ ተብሎ ፡ መጠበቁ ፡ አይቀርም ። በዚህም ፡ ሁናቴ ፡ አንዳንድ ፡ ሕጐችን ፡ ሳይለዩና ፡ ሳይመርጡ ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ ሕግ ፡ ያዘዘው ፡ ሁሉ ፡ እንዲከበር ፡ መጐትጐት ፡ የሕዝቡን ፡ በጸጥታ ፡ መኖር ፡ ያዳክመዋል ። አለመግባባቶችም ፡ ሕግ ፡ ሳይጠቅስና ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይኬድ ፡ መፍትሔ ፡ ሊያገኙ ፡ ይችሉ ፡ ይሆናል ። ከዚህ ፡ ጽሁፍ ፡ ዓላማዎች ፡ አንዱ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሁኔታዎች ፡ የግድ ፡ መሆን ፡ እንደሌለባቸውና ፡ አኳኋናቸውም ፡ በመደዳው ፡ እንዳልሆነ ፡ ለማሳየት ፡ ነው ። በዕውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ በጠቅላላ ፡ ልማድን ፡ በመሻርና ፡ ሁሉንም ፡ ጉዳይ ፡ አቅፎ ፡ በመያዝ ፡ ሁኔታ ፡ የተሠራ ፡ ሕጉ-ግ ፡ በማውጣት ፡ የወሰደችውን ፡ እርምጃ ፡ የሚደግፉና ፡ የሚያስረዱ ፡ (፩ኛ)ባህላዊ ፡ (፪ኛ) ፡ አሁን ፡ የሚሠራባቸውና ፡ (፫) ፡ የቅልጥፍና ፡ (ስሙም ፡ የመሆን) ፡ ምክንያቶች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ ማስረጃዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይብራራሉ ።

ገላጭ ፡ ምክንያቶች ።

ኢትዮጵያ ፡ በባህል ፡ ረገድ ፡ ፍጹም ፡ አፍሪቃዊ ፡ ነች ፡ ተብላ ፡ አትገመትም ። ባህሏም ፡ የመካከለኛው ፡ ባሕር ፡ (ሜዴትራኒያን) ፡ ሥልጣኔ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ (በስሕተት ፡ "የምዕራብ" ፡ ሥልጣኔ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው) ፡ ጠባዮችን ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፤ የአይሁድ ፤ የክርስቲያን ፤ የግሪክና ፡ የሮማን ፡ ሥልጣኔ ፡ ጠባዮችን ፡ ይጨምራል ። ቆንስጣንጡኖስና ፡ የኒቂያው ፡ ጉባኤ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ፤ የአክሱሙም ፡ መንግሥት ፡ ከንጉሥ ፡ ጀስቲኒያን ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ነበረው ። ከማንኛውም ፡ ይልቅ ፡ ይህችን ፡ አገር ፡ በመከራና ፡ በፈተና ፡ ጊዜ ፡ ከመከፋፈል ፡ ያዳናት ፡ አንድ ፡ ማእከላዊ ፡

8. ኤም ፡ ፕላንዮልና ፡ ጂ ሪፒፔርት ፡ ትሬቲዝ ፡ ኦን ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፤ (በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያዘጋጀው ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ (፲፪ኛው ፡ እትም ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፴፱) ፡ በሉዊዝና ፡ ግዛት ፡ ሕግ ፡ ኢንስቲቱት ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. የተተረጐመው ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ቁ. ፪፻፭ ።

9. አሉት ፡ እላይ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ የጠቀስነው ፡ ፯ኛ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፤ ገጽ ፡ ፴፫ ፡ ላይ ።

የሆነ ፡ ሕግና ፡ ሥልጣን ፡ በባህላዊ ፡ ውስጥ ፡ የቆየ ፡ ነገር ፡ ነው ። ሕግን ፣ በሰፊው ፡ ማገግ ፡ በኢትዮጵ ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፣ አይደለም ። ወደ ፡ ፲፮ኛው ፣ መቶ ፣ ዘመን ፡ ገደማ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፣ የሚተዳደሩበት ፡ ጥንታዊ ፣ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሕግና ፣ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ተጠቃላሎ ፣ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፣ (የነገሥታት ፡ ሕግ) ፡ ወጣ ። የዚህም ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፣ የሆኑት ፡ ዋና ፡ ሐሳቦች ፡ የተወሰዱት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እናት ፡ ከነበረችው ፡ ከእስክንድሪያ ፡ የተዋህዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበር ፡ በተጨማሪም፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ክፍሉ ፡ ከምሥራቃዊ ፡ የሮማ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ሐሳቦችን ፡ ወስዶአል ። ስለ ዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በይበልጥ ፡ ለማወቅ ፡ የሚሹ ፡ አንባቢዎች ፡ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ሚላኖ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ አር. አር. ካንቫረ ፡ በተረጐመው ፡ "ፍትሐ ፡ ነገሥት" ፡ በሚለው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ተጨማሪ ፡ መረጃ ፡ ሊያገኙ ፡ ይችላሉ ።[10]

ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ወደ፡ አለው ፡ ሁኔታ ፡ ተመልሰን ፡ ብንመለከት ፣ ምንም ፣ እንኳን ፡ ሕግ ፡ ማገግ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ቢሆንም ፡ ገና ናው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ዘመኑ ፡ ያለፈበት ፡ በመሆኑ ፡ እምብዛም ፡ አይጠቀስም ። እ. ኤ. አ. ከ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገሮች ፡ የሚዳኙት ፡ በልማድና ፡ በርትዕ፡ (ኢኩቲ) ፡ (አግባቢ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርዶችም ፡ ጭምር ፡) መሠረት፡ ሳለ ፡ ልማድም፡ የተለያየና፡ አጠራጣሪ ፡ ነበር ። ከኤርትራ[11] ፣ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በስተቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በጽሑፍ ፡ ተደርድሮ ፡ አያውቅም ። ሆኖም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ልማዶች ፡ በጎብኝዎች ፡ መጽሔትና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ጥናት ፡ (ኤትኒኦሎጂ) ፡ መጽሔት ፡ በሰፊው ፡ ተገልጸው ፡ ይገኛሉ ።[12] የየጎሳውና ፡ የየአገሩ ፡ የልማድ ፡ ሕግ የተለያየ ፡ ዐይነት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መንደላቀቅ ፡ በቀረበት ፣ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጓጓዣ ፡ መሻሻል፡ በጣም ፡ የተፋጠነ ፡ ዘዴ ፡ የሚያሻው ፡ ሲሆን ፡ እነዚህን ፡ ልማዶች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አሻሽሎ ፣ አንድ ፡ ላይ ፡ አጠቃሎ ፣ ማገግ ፡ የብዙ ፡ ትውልድ ፡ ዕድሜ ፡ የሚጠይቅ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ትክክለኛም ፣ ሆኖ ፡ ስህተተኛ ፡ ያለፈውን ፡ ሕግ ፡ ጠራርጎ ፣ የሚሽር ፡ የዛሬውን ፡ የኢትዮጵያ ፣

10. አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ጻድዋ ፣ ወደ ፣ እንግሊዝኛ፣ ከነብራሪያውና፣ ማስረጃው፣ ጭምር ፣ የተረጐሙት ፣ የፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ መጽሐፍ ፡ አሁን ፣ በቅርቡ ፡ በቀዳማዊ ፣ ኃይለ ፣ ሥላሴ ፣ ዩኒቨርሲቲ ፣ የሕግ ፣ ፋኩልቲ ፣ ታትሞ ፣ ይወጣል ።

11. ኤፍ ኤፍ ረሰል ፡ "ኤርትርያን ፡ ካስተማሪ ፡ ሎው" ፣ (የኤርትሪያ ፣ የልማድ ፣ ሕግ) ፣ የአፍሪቃ ፣ የሕግ ፣ መጽሔት ፣ ቮልዩም ፡ ፫ ፣ (እ.ኤ.አ. ፲፱፻፶፱ ፣ ዓ. ም.) ገጽ ፡ ፺፱ ፣ ተመልከት ። በዚህ፣ ጥናት፣ የታወቀው ፣ ጽሑፍ ፡ በኢሉ. እእስቲኒ ፣ የተጻፈው ፣ ትራታቶ ፣ ዲ ዲሪቶ ፣ ኮንስቲቱዲናሪዮ ፣ ዴል ፣ ኤሪቲሪያ ፣ (አሥመራ ፣ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፵፮) ።

12. በተጨማሪም ፡ ለምሳሌ ፣ በኢትዮጵያ ፣ አብዘርቨርና ፣ በላምባራስ ፣ ማኅተመ ፣ ሥላሴ ፣ ወልደ ፣ መስቀል ፣ በጻፏአቸው ፣ የአማርኛ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ጽሑፎች ፣ ውስጥ ፣ ተመልከት ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ በማገግ ፡ አቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ተወስዶል ። ቢሆንም ፡ ይኸ ፡ ያልተለመደ ፡ ዘዴ ፡ ባለፈው ፡ ፤ ባሁኑና ፡ በወደፊቱ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ የተያያዘ ፡ አረማመድ ፡ የተጠበቀ ፡ እንዲሆን ፡ ጥሩ ፡ ብልሃቶችን፡ ጨምሮ ፡ ይዞአል ። ይኸ ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይብራራል ። የአህጉራዊ፡ አውሮጳውያንን ፡ መስመር ፡ በመከተል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ ረቂቅ ፡ ያዘጋጀው ፡ የታወቀው ፡ ሊቅ ፡[13] የራሱን ፡ አስተያየት ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ለመጨመር ፡ ፈቃደኛ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

ለክርክራችን ፡ መነሻ ፡ እንዲሆን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መግቢያ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠውን ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መጥቀስ ፡ ሳይረዳን ፡ አይቀርም ።

> "በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከጥንት ፡ ዘመናት ፡ ከወረስናቸው ፡ በጽኑ ፡ ከተመሠረቱት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ የሕግ ፡ ልምዶች ፡ ጋር ፡ የሚስማሙ ፡ ናቸው ። - - - እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ ተሽለው ፡ የሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ ተጠንተዋል ። ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ የሰዎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ለማግለጽ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላቸው ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ሐሳቦች ፡ ለመግለጽ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ከወጣላቸው፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የሚደርስ፡ ፍላጎታቸውን፤ ልምዳቸውን ፡ ወይም፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም" ።

ይህ ፡ ብልህና ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ አነጋገር ፡ ያለምርማሪ ፡ እንዳለ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሲነበብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደገና ፡ ከተጠቀሰው ፡ ልማድን ፡ ከሚሽረው ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ።

> "ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ፡ በቀር ፡ በዚህ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለተተካ ፡ ተሽረዋል ። "

ነገር ፡ ግን ፡ ጠለቅ ፡ ብለን፡ የተመራመርን፡ እንደሁ ፡ ሲወርዱ ፡ ሲዋረዱ ፡ የመጡት ፡ ባሕላዊ ፡ ደንቦችና፡ ልማዶች፡ የተጠበቁባቸውና ፡ ሊጠበቁ ፡ የሚቻልባቸው ፡ አምስት ፡ ዘዴዎች ፡ መኖራቸውን ፡ እንገነዘባለን ። እነዚሁም ፤ (፩ኛ) ፡

13. ስሙ ፡ ጥሩ ፡ የሆነው ፡ የፓሪስ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲው ፡ ምሁር ፡ በተመዘዘኝ ፡ ጥናት ፡ የታወቀው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬኔ ፡ ዳቪድ ።

ልማድን ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት [14] (፪ኛ) ፡ ልማድን ፡ ማመልከት ፡ (መጥቀስ) ፤ ፫ኛ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ መድፈን ፡ (መሙላት) ፤ (፬ኛ) ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤና ፡ (፭ኛ)፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንገልጻቸዋለን ።

የልማድ ፡ መጠቀሚያዎች ።

(፩ኛ) ፡ ልማድን ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት ።

አብዛኛው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ውስጥ፡ ፡ ተጨምሮ ፡ ከመሸር ፡ ደንግዋል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ቅርጽ ፡ አግኝተው፡ የገቡት፡ ልማዶች ፡ በጠቅላላ ፡ ሕግ ፡ ይሆናሉ ። እንደዚሁ ፡ ያለው ፡ ዘዴ ፡ የራሱ ፡ ፍጥረት ፡ በአገር ፡ ልማድ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይ ሠራበት ፡ ያግደዋል ። ይኸም ፡ ባይሆን ፡ አጋጊው ፡ በጠቅላላ ፡ ልማድ ፡ ላይ ፡ እን ኳን ፡ የነበረው ፡ አቀራረብ ፡ አንዱን ፡ ከአንዱ፡ በመምረጥ ፡ የተመሠረተ ፡ ነበረ ። ይህንንም ፡ ካልን ፡ ዘንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አጋጊ ፡ ለአመራረጡ ፡ የተጠቀመ ባቸውን ፡ ተገቢ ፡ የአመራረጥ ፡ መመጠኛዎች ፤ በዝርዝር ፡ ሳይሆን ፡ በአጭሩ ፤ ከዚህ ፡ ላይ ፡ እናቀርባለን ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ምርጫው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አለው ፤ ምክንያቱም ፡ "የተሻሩት ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች" ፡ በሚለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ሥር ፡ ያልተጨመረ ፡ ሁሉ ፡ እንደተተወና ፡ እንደተሻረ ፡ ስለሚታወቅ ነው ።

ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሲዘጋጅና ፡ ሲታገግ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮንና ፡ ፓርላማ ፡ ያደረጉት ፡ ክርክርና ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ተጽፎ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በግልጽ ፡ አልወጣም ። ቢሆንም ፤ ከአሉባልታ ፡ ሳይሆን ፡ ከመጨረሻው ፡ ከሕጉ ፡ዝግጅት ፡ ውጤት ፡ እንደተረዳነው ፡ "ጠቅላላው" ፡ የአገሪቱ ፡ ልማድ ፡ (የእስዋ ፡ "የልማድ ፡ ሕግ") ፡ በሚከተሉት፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ሲገኝ ፡ ከሞላ ጐደል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደተጨመረ ፡ በቅድ ሚያ ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ እንችላለን ። ሁኔታዎቹም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ (ሀ) ፡ አብዛኞቹ ፡ ደጋ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ የያዙት ፡ ልማድ ፡ የሆነ ፡ እንደሁ ፡ ከላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ ልማዱን ፡ "ጠቅላላ" ፡ (የጥንት) ፡ ሊማስኘት ፡ በቂ ምክንያት ፡ የሆናል ፤ (ለ)ልማዱ ፡ በዚያ ፡ የመጨረሻ ፡ የበላይ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሁለንተና ፡ ውስጥ ፡ ሰርጎ ፡ የሚገኘውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕ የማይጻይፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ (ሐ) ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ የሚደረገው ፡ የወደፊት ፡ እርምጃ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ግዴታ ፡ ልማዱ ፡ የሚቃ

14. " ሕግ ፡ አርጐ ፡ ማዘጋጀት" ፡ ከማለት ፡ ሳይሻል ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም፡ የአገር ፡ ልማዶችን ፡ እንዳሉ ፡ ይዞ ፡ በመጠቀም ፡ ፈንታ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ከተወሰዱት ፡ መፍትሄዎች፡ ጋር ፡ ለማመሳሰል ፡ ተሻሽሉ ፡ ነው ። ወይም "የተጨቃለሉ" ፤ ይህ ፡ ቃል፡ በተጨማሪ ፡ ከጥንት ፡ ልማዶች ፡ ጥቂቶች ፡ አሁንም ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ይገልጻል ፡ ማለቱም ፡ ያስኬዳል ።

ወም ፡ መሆን ፡ የለበትም ፤ (የኋሊት ፡ የሚራመድ ፡ የመሬት ፡ ማስተላለፍ ፡ [15] ሥርዐት ፡ አሁንም ፡ እንዳለ ፡ የተተወው ፡ ለጊዜው ፡ ከመሆንም ፡ በላይ ፡ አንድ ዐይነት ፡ አቅድ ፡ ይዞ ፡ በሌላው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ያለመገኘቱ ንና ፡ እሱም ፡ የሚመለከተው ፡ የአገር ፡ ልማዶችን ፡ መሆኑን ፡ አትዘንጋ ።) (መ) ልማዱ፡ በፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ፡ ቃላት፡ ሊገለጥ፡እንደሚችል ፡ በበቂ ፡ ሁኔታ ፡ ብቃሀና ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ፡ውስጥ ፡ የገቡትም ፡ ልማዶች ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ከተቀበልናቸው ፡ መላዎች ፡ ጋር ፡ አብ ረው ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ዕንስ—ሐሳብ ፣ መደቦችና ፡ አከፋፈሎች ፡ አሠራር ፡ ተቀ ላጥፈው ፡ ነው ፡ የተበጁት ። [16] እንደአጋጣሚ፡ ሆኖ ፤ ከዚህ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ አራት ፡ ሁኔታዎች ፡ መቅድም ፡ ሆኖ ፡ በተሰጠው ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሪ ፡ ቃልም ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። (ሀ)፡ ጥንታዊ፡ "ልምዶችን" ፤ (ለ) ፡ "የተፈ ጥሮ ፡ ፍትሕትን ፤ (ሐ) ፡ የተቀባዮችን ፡ "ፍላጎትንና" ፤ (መ) ፡ የሕግ ፡ ግልጽነ ትን ፡ በመቅድሙ ፡ ውስጥ ፡ ተነግሮል ። [17]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ የአመራረጥ ፡ መመጠኛዎች ፡ ስለግዴታዎች ፡ የሚለውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ አራተኛ ፡ መጽሐፍና ፡ በተለይ ፡ የወጣውን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አፈላለቃቸው ፡ በጣም ፡ ባዕድ ፡ እንዲሆን ፡ አደረገው ። ይህም፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ለነዚሁ ፡ ዘመናዊ፡ ለሆኑት ፡ ሕግ ፡ ክፍሎች፡ ተስማሚ ፡ የሆኑ ፡ የአገሩ ፡ የሆኑ ፡ ደንቦች ፡ ስለታጡ ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፣ ከጥንት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ለመጡት ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ በርስትና ፡ በው ርስ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ብዙ ፡ ተስማሚ ፡ የጥንት ፡ ልማዶች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንዲቆዩ ፡ ተደርገዋል ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ የተደረጉትን ፡ ጠቅላላ ፡ ልማ ዶች ፡ (ከትውስት ፡ ሕጎች ፡ ለይቶ) ፡ መዘርዘር ፡ ከዚህ ፡ ጽሁፍ ፡ ወሰን ፡ ውጭ ፡ ይሆናል ። አብዛኞቹም ፤ ግላዊ ፡ ሕግን ፡ (ስለሰዎች ፡ ሕግ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው) ፡ ዘመድ ፡ ሕግን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። እነዚሁም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በየበ ታው ፡ መለያየታቸው ፡ ቀርቶ ፡ ለሁሉም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ይሆናሉ ። የዚህ ፡

15. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፯፻፹፫—፺፮ ።

16. በነገራችን ፡ ላይ ፡ ከዚህ፡ የተነሣ ፡ በፈረንሣይኛ፡ የተጻፈውን፡ ዋና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ለዚህ ፡ ጥናት፡ ተስማሚ፡ ሳልሆኑት ፤ ግን፡ መደበኛ፡ (ኦፊሰል) ፡ ወይ፡ ሆኑት፡ የአማርኛና (ባለሥል ጣን ፡ ነው)፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋዎች ፡ መተርጒም፡ ከባድ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል ። አማርኛ ፡ የሕግ ቃላት ፡ ያንሱታል ፡ የእንግሊዝኛ ፡ የሕግ ፡ ቃላት፡ ደግሞ፡ ለኢትዮጵያ፡ ፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ አይ ስማሙም ። ከጆርጅ ፡ ክሽቺናቢች ፡ "ኢትዮጵያን፡ ሊጋል ፡ ኢጁኬሽን" ፡ (የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ትምህርት) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ምርመራ፡ መጽሔት፡ ፬ልዩም ፡ ፩ ፡ ቁ. ፩ ፡ (ኡ. ኤ. አ. ፲፱፻፷፫፡ ዓ. ም.) ፡ (የቋንቋ ፡ ችግር ፡ የሚለውን) ፡ ከገጽ ፡ ፷፱—፸ ፡ ተመልከት ።

17. ይኸን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ጥቅስ ፡ "--- በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ፡ የሚገኙ፡ ቃላቶች ፡ ግልጽ እንዲሆኑ ፡ አድርገናል ") ፤ የሚለው ፡ ነው ።

አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሕግ ፡ ማውጣትን ፡ ብዙዎች ፡ የተቃወሙትንና ፡ በአፍሪቃም ፡ ውስጥ ፡ ከሁሉም ፡ የተለየ፡ የራሱ፡ ዐይነት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ ስሜት ፡ የሚቀንሱ ፡ መንገዶች ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እየተደጋገሙ ፡ ይገለጻሉ ። ይህ ፡ ያለፉ ፡ ሕጎችንና ፡ ልማዶችን ፡ የሚሽር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ የእስላሞች ፡ የግል ፡ ጉዳይ ፡ የሚወሰንበትን ፡ የቃዲዎችና ፡ የናኢባዎች ፡ ጉባኤ ቤት ፡ የተቋቋመበትን፡ ሥርዐታዊ፡ አዋጅንም ፡[18] ጭምር፡ ሽሮአልን ? የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ይዞት ፡ አለው ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ስለሆነ ፡ በጉዳዩ ፡ ገብቼ ፡ አሳቤን ፡ ለመስጠት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም ። በእስላሞች ፡ ግላዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ዳኝነትን ፡ የሚሰጠው ፡ የቃዲዎች ፡ ጉባኤ ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የታወቀ ፡ በመሆኑ ፡ ለጊዜው ፡ ለእስላሞች ፡ እንደሚስማማ ፡ ሆኖ ፡ የተተረጎመ ፡ ይመስላል ፤ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ይህንኑ ፡ የሚያብራሩ ፡ ሕጎች ፡ ይወጡ ፡ ይሆናል ።

ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ የጥንት ፡ ባህል ፡ ያስገቡ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ተሰጥተዋል ። ፩፻፶እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ ፩፻፶፪ ፡ ፯፻፷፩ ፡ ፰፻፸፬ ፡ ፰፻፶፪ ፡ (ያለኑዛዜ የተደረገ ፡ ውርስ ፡ ባልየውን ፡ ወይም ፡ ሚስትዮዋን ፡ እንደማይጨምር ፡ ተቁጥሮ ፩) ፲፩፻፸፭ ፡ ከ፲፩፻፸—፸፬ ፡ ፩፲፰፯—ከ፩፲፩፻፲፫—፲፬ ፡ ፩፲፩፻፵፪ ።
(፩ኛ) ፡ ልማድን ፡ ማመልከት ፡ (መጥቀስ) ።

አሁን ፡ በመብራራት ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ልማድን ፡ የሚሽረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ በመላው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛቸውንም ፡ የቀድሞ ፡ ልማድ ፡ ደንቦች ፡ "በግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር" ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከሚያመለክታቸው ፡ (ከሚጠቅሳቸው) ፡ ልማዶች ፡ በስተቀር ፤ ሌሎቹን ፡ ሁሉ፡ ሽሮአቸዋል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ በውስጡ ፡ ያልተመለከተትን ፡ ወይም ፡ ያልገቡትን ፡ ሁሉ ፡ ሽሮአቸዋል ፡ የአጋጊ ፡ ሕጉጎች ፡ ዕንኳንስ ፤ ልማድን ፡ ሊያሟሉና ፡ ራሳቸውም ፡ ቢሆኑ ፡ በልማድ ፡ አልተሟሉም ።[19] የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉም ፡ ፡ ልማድን ፡ የሚያያመለከ

18. የቃዲዎችና ፡ የናኢባዎች ፡ ጉባኤ ፡ ቤት ፡ የ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ. ም. አዋጅ ፡ ፶፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፱ ።

19. ይህ ፡ የአገርን ፡ ባህል ፡ የማያስቀረው ፡ ሕግ ፡ ወደፊት ፡ የሚመጡ ፡ ልማዶችንም ፡ ጭምር ፡ ያስቀር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገና ፡ የሚታይ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሚሽረው ፡ "ከዚህ ፡ --- ፡ በፊት ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩትን" ፡ ብቻ ፡ ነው ። ግን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጡትን ፡ ልማዶች ፡ "እንዲሠራባቸው" ፡ የሚያደርግ ፡ ምን ፡ ይኖር ፡ ይሆን ? ምናልባት ፡ ዳኞች ፡ ሕጎችን ፡ በሚተረጉሙበት ፡ ጊዜ ፡ አዲሶቹ ፡ ልማዶች ፡ የመግባባት ፡ ኃይል ፤ ይኖራቸው ፡ ይሆናል ። (ከዚህ ፡ በታች ፡ "ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ" በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ፡ ከሰጠነው ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ አመዛዝን) ይህ ፡ የፍራንኮ ፤ ኢትዮጵያ ፡ አቀራረብ ፡ ልማድን ፡ በመሰረዝ ፡ ፈንታ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ከሚያውላቸው ፤ ለምሳሌ ፡ ከእስዊዝ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይለያይ ፡ ይሆን ? (የስዊስ ፡ ሕግ ፡ ቁ/፩) ።

ተው ፣ አንዳንድ ፣ ቦታ ፣ ላይ፣ ብቻ፣ ነው ። እንዚሀንም ፣ ቦታዎች ፣ እዚሀ ፣ ባጭሩ ፣ መግለጽ ፣ ትምህርት ፣ ይሰጥ ፣ ይሆናል ። እነሱም ፣ ከዚሀ ፣ በፊት ፣ እንደተገለጸው ፣ ጠቅላላ ፣ ልማዶች ፣ ሳይሆኑ ፣ ከቦታ ፣ ቦታ ፣ የሚለያዩት ፣ የአገር ፣ ልማዶች ፣ ብቻ ፣ ናቸው ። አንድ ፣ ጸንቶ ፣ የቆየ ፣ ልማድ ፣ ጠቃሚ ፣ መስሎ ፣ ከታየ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ ይኸንኑ ፣ ከማመልከት፣ ፈንታ ፣ "በውስጡ ፣ እንደሚያስገባው ፣ " ግልጽ ፣ ነው ።

ከዚሀ ፣ ቀጥሎ ፣ የተዘረዘሩት፣ ማብራሪያዎች፣ በኢትዮጵያ ፣ የፍትሐ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ውስጥ ፣ ስለተመለከቱት ፣ ስለ ፣ አንዳንድ ፣ የአገር ፣ ልማዶች ፣ ናቸው ። የነዚሁም ፣ ጥቂትነት ፣ የሚያስታውሰን ፣ ሕግን ፣ ለማስተባበር ፣ የሚሞከረውን ፣ ጥረት ፣ ነው ። እነዚሀንም ፣ በቤተዘመድ ፣ በውርስ ፣ በንብረት፣ በውልና ፣ ከውል ፣ ውጭ ፣ ስለሚደርሱ ፣ አላፊነት ፣ በሚሉ ፣ አርዕስቶች ፣ እንገልጻቸዋለን ።

<u>ቤተዘመድ ።</u>

ቁ. ፣ ፭፻፷፩ ፣ - <u>የመተጫጨት ፣ ሥርዐት ፣ (ፎርም)</u> ።

የመተጫጨት ፣ ሥርዐት ፣ መተጫጨቱ ፣ በሚደረግበት ፣ ቦታ ፣ ልማድ ፣ መሠረት ፣ ይፈጸማል ።

ቁ. ፭፻፷፫ ፣ - <u>(የመተጫጨት፣ መፈረስ፣ የሚያስከትለው ፣) ፪ ፣ - የሕሊና ጉዳት</u> ።

የዚህን ፣ ካሣ ፣ ልክ ፣ ለመወሰንና ፣ ካሣውን ፣ ለመጠየቅ ፣ የሚችለውን ፣ ባለመብት ፣ ዳኞች ፣ የአገሩን ፣ ልማድ ፣ መሠረት፣ አድርገው ፣ ይከተላሉ ።

ቁ. ፭፻፸፯ ፣ - <u>ልዩ ፣ ልዩ ፣ ዓይነት ፣ ጋብቻ</u> ።

(፩) ጋብቻ ፣ በአንድ ፣ የሕዝብ ፣ የክብር ፣ መዝገብ ፣ ሹም ፣ ፊት ፣ ሊደ ረግ ፣ ይቻላል ። (እነዚሀ ፣ ሹሞች ፣ በገጠር ፣ ያለመኖራቸውን ፣ አትዘንጋ ፤ የክብር ፣ መዝገቦቹ ፣ እስከሚመች ፣ ጊዜ ፣ ድረስ ፣ ሳይሠራባቸው ፣ እንዲ ቆዩ ፣ የሚያደርገውን ፣ ቁ. ፫ሺ፫፻፷፩ ፣ ከዚሀ ፣ ጋር ፣ አነፃጽረው) ።
(፪) እንደዚሁም ፣ ሕጉ ፣ በሁለቱ ፣ ወገኖች ፣ ሃይማኖት ፣ ወይም ፣ ባአገር፣ ልማድ [20] ፣ መሠረት ፣ የሚያደርጉትን ፣ ጋብቻዎች ፣ ያውቃል ፣ (ይቀበ ላል) ።

ቁ. ፭፻፹ ፣ - <u>የልማድ ፣ ጋብቻ</u> ።

(በአንድ ፣ ጎሳ ፣ ልማድ ፣ መሠረት ፣ በአንድ፣ ወንድና ፣ በአንዲት ፣ ሴት መካከል ፣ ነዋሪ ፣ የሆነ ፣ ግንኙነት ፣ የሚያስከትል ፣ የጋብቻ ፣ ሥነ ፣ ሥር ዓት ፣ በተፈጸመ ፣ ጊዜ ፣ የልማድ ፣ ጋብቻ ፣ ተፈጸመ ፣ ይባላል ።)

20. በጣም ፣ የሚያስገርመው ፣ የቤተ ፣ ክህነት ፣ አባል ፣ የሆኑት ፣ የጋብቻ ፣ ሥነ ፣ ሥርዐታቸውን ፣ የሚ ፈጽሙት ፣ በቤተ ፣ ክህነት ፣ ሕግ ፣ ሳይሆን ፣ በአገር ፣ ልማድ ፣ መሠረት ፣ ነው ።

ቁ. ፭፻፸፯ ፡ - <u>የልማድ ፡ ጋብቻ</u> ።

የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈጸም ፡ የሚቻልበት ፡ ሁኔታና ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ዐይነት ፡ በአገሩ ፡ ልማድ ፡ ይወሰናል ።

ቁ. ፭፻፹፩ ፡ - (ለልማድ ፡ ጋብቻ ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑት፡ ሁኔታዎችና ፡ ሥርዐቶች ፡ ሲጓደሉ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ቅጣትና፡ ካሣ፡ ሊወሰንባቸው ፡ ይቻላል ።)

ቁ. ፰፻፸፯ - ፰ ፡ (ወላጆች ፡ ለተወላጆች፡ ወይም፡ ለጋብቻ ፡ ዘመዶች ፡ እንዲሁም ፡ ከአንድ ፡ አባት ፡ ከአንዲት ፡ እናት ፡ ለተወለዱ ፡ እህትና ፡ ወንድም ፡ ከአባት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ከእናት ፡ ብቻ ፡ ለተወለዱ ፡ እህትና ፡ ወንድም ፡ ሕጋዊ ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ሁኔታ ፡ የሚወሰነው ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ልማድ ፡ ነው ።)

<u>ማስታወሻ</u> ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የገቡት ፡ ጠቅላላ፡ ልማዶች ፡ በቤተ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ መገኘታቸው ፡ ተገልጿ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ (ማለት ፡ የቤተዘመድ ፡ ሕግ ፡) የአገር ፡ ልማዶችን ፡ በጥቂቱ ፡ ማመልከቱን ፡ አየን ። ይኸም ፡ ሕጉ ፡ በአንዳንድ ፡ በተወሰኑ ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ የሚያደርሰው ፡ ውጤት ፡ በደህና ፡ እንዲቃለል ፡ መላ ፡ ይሰጠናል ። ሌሎቹም ፡ ተጨማሪ ፡ ማቃለያ ፡ ብልሃቶች ፡ ወደፊት ፡ "በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ፡ " በሚለው ፡ አርዕስት ፡ እናቀርባቸዋለን ።

<u>ውርስ</u> ።

<u>ማስታወሻ</u> ።

የውርስ ፡ ሕግ ፡ ልማድን ፡ ጨርሶ ፡ አይመለከትም ። ስለዚህ ፤ በልማድ ፡ የሚሠራባቸው ፡ የውርስ ፡ ሥርዐቶች ፡ ብቻቸውን ፡ ቆመው ፡ የማይጸኑ ፡ ናቸው ። ሆኖም ፤ በዕርቅና ፡ በኑዛዜ ፡ ላይ ፡ ሊጠቀሱ ፡ ሊጸፉ ፡ ይችላሉ ። ሳይናዘዝ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ ሕግ ፡ "የአባትን ፡ ለአባት ፡ ወገን ፤ የእናት ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ መስጠት ፡ " የሚለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ልማዳዊ ፡ ደንብ ፡ (ቁ. ፰፻፵፪ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡) ሊያስገባ ፡ በየቦታው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት፡ የሆኑትን ፡ የኑዛዜን ፡ ቅደም፡ ተከተል ፡ ሥርዐት ፡ ትቶታል ። የየቦታው ፡ ልማዶችም ፡ በበኩላቸው ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ሥርዐቱ ፡ ጉዳይ ፡ ሕጉን ፡ ሊተውት ፡ ይችሉል ። ይኸውም ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ወደፊት ፡ "በከፊል፡ ሕጋዊ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ፡ " በሚል ፡ አርዕስት ፡ እንደምንገልጸው ፡ ሁሉ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ሽማግሌ ፡ ይዞ ፡ ዕርቅ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ንብረት ።

ቁ. ሺ፪፻፴፪ ፡ - (“የአንድ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍሎች ፡ ”) ፪ ፡ - ትርጓሜ ።

የአንድ ፡ ነገር ፡ ሙሉ ፡ ክፍል ፡ የሚባለው ፡ በልማድ ፡ እንደሚታየው ፡ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠረው ፡ ነው ። (ቁ. ሺ፪፻፴፩ ፡ ይኸንን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከቱን ፡ ጉዳዮች ፡ ይሰጣል ።)

ቁ. ሺ፪፻፳፫ ፡ - መሠረቱ ፡ (የሥሪት ፡ / የይዞታ ።)

(ለ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ሳያቋርጥ ፡ በስሙ ፡ ግብር ፡ ለከፈለ ፡ ባለይዞታ ፡ የንብረቱ ባለቤት ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ።) ስለሆነም ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ መሬት ፡ ሲሆንና ፡ በአገሩ ፡ ሥሪት ፡ መሠረት ፡ የመሬቱ ፡ ርስትነት ፡ የግል ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ ተወላጆች ፡ የሚካፈሉት ፡ በሆነበት ፡ ሥፍራ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የትውልድ ፡ ሐረጉን ፡ መዝዞ ፡ ርስቱ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይህ ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ አያግደውም ።

ቁ. ሺ፫፻፷፩ ፡ - የገጠር ፡ የመተላለፍ ፡ መብትና ፡ የንብረት ፡ አገልግሎት ።

(የመተላለፉ ፡ መብት ፡ መጠን ፡) በቦታው ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ እንዳለው ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ ይሆናል ።

ቁ. ሺ፬፻፹፱ ፡ - መሠረቱ ፡ (የሕብረት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች) ።

ሀብትነታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ (የደሽ ፡) እንደ ፡ የጎጣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ በኅብረት ፡ መሠራታቸው ፡ የሕብረቱን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የተከተሉ ፡ መስሎ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረት ፡ የሚሠሩ ፡ ይሆናሉ ።

ቁ. ሺ፬፻፺ ፡ - (ልማዶችን ፡ በጽሑፍ ፡ ስለማድረግ ።)

ቁ. ሺ፬፻፺፩ - ፺፯ ፡ (በአገር ፡ ልማድ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በልማድ ፡ የሚሠሩ ፡ ሕብረታዊ ፡ የመሬቶች ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፡ መኖራቸው ፡ በተጨማሪ ፡ ተገልጸዋል ።)

ማስታወሻ ።

በቁ. ሺ፬፻፺፰ - ፺፱ ፡ በተሰጠው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የልማድ ፡ “ደንቦች” ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሻሻሉ ፡ እንዲቻል ፡ ሆኖአል ።

ቁ. ፫ሺ፫፻፳፫ -፳፯ ፡ (የርስት ፡ አመዘጋገብ ፡ ሕጎች [21] ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እስኪውሉ ፡ ድረስ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ለማስተላለፍ ፡ ምስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ እንዲሆኑ ፡ (እርጋ ፡ እምነስ ፡) መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ ሥርዐቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልማዳዊያን ፡ ደንቦች ፡ እንዳሉ ፡ እንዲቆዩ ፡ ታዘዋል ።)

21. የኢት ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ።

__ማስታወሻ ።__

በአንዳንድ ፡ በመሻሻል ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ የሚሠራበት ፡ በሕግ ፡ የታወጀ ፡ የምዝገባ ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

__ውሎች ።__

ቁ. ፲፯፻፲፫ ፡ - __ለውለታ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ።__

ውሎች ፡ አስገዳጅነታቸው ፡ በውሉ ፡ በተነገረው ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ልማድ ፡ ቅን ፡ ልቦና ፡ የውለታው ፡ ዐይነት ፡ የሚያስከትሏቸውን ፡ ነገሮች ፡ ጭምር ፡ ነው ።

__ማስታወሻ ።__

ይህ ፡ "ጸንተው ፡ ለሚገኙ ፡ ልማዶች ፡" የተሰጠው ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ የተደረገ ፡ ስለሆነ ፤ ምንም ፡ ሐተታ ፡ አያሻውም ። እነዚህ ፡ ልማድ ፡ የሚሠራባቸውም ፡ ጉዳዮች፡ በተለይ ፡ የመሬትን፡ ኪራይ፡ በሚመለከተው ፡ የስምምነት ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ይገኛሉ ።

ቁ. ፲፯፻፶፫ ፡ (፱) ፡ ፲፯፻፶፪ (፩-፱) ፡ ፲፯፻፶፮ (፪) ፡ ፲፯፻፳ (፪) ፡ ፲፯፻፲፫ (፫) ። __በጥፋት ፡ ላይ ፡ ስለተመሠረተ ፡ አላፊነት ።__

ቁ. ፲፯፻፲፭ ፡ - __ስለ ፡ አገር ፡ ልማድ ።__

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ የካሳውን ፡ (ለሕሊና ፡ ጉዳት) ፡ ልክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሆኑን ፡ በርትዕ ፡ በአስተያየት ፡ ለመወሰንና ፡ እንዲሁም ፡ የቤተዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ለመነጋገር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ዳኞች ፡ የአገር ፡ ልማድን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ይይዛሉ ።

(፪) ዳኞች ፡ እነዚህን ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ ጊዜያቸው ፡ ከሕሊና ፡ ከሰብአዊ ፡ አእምሮ ፡ ተቃራኒያን ፡ መሆናቸውን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባቸውም ።

__ማስታወሻ ።__

ይህ ፡ የቦታን ፡ (የአገሩን ፡) ልማድ ፡ ማመልከት ፡ ስለ ፡ ሕሊና ፡ ጉዳት [22] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የገቡትን ፡ ጠቅላላ ፡ ልማዶች ፡ ያሟላል ። ይህም ፡ በቁ ፡ ፲፯፻፲፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ "የደም ፡ ዋጋ ፡" ተብሎ ፡ ቀድሞ ፡ በቀላል ፡ አነጋገር ፡ ይጠራ ፡ የነበረውን ፡ ይጨምራል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ በአሁን ፡ ዘመን፡ ይገኝበታል ። ይኸውም፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ ቀድሞ ፡ የወንጀል ፡ ክስን ፡ ሲያስቀር ፡ የሕሊና ፡ ጉዳት ፡ ግድን ፡ አያስቀርም ፡ ነበር ።

22. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ ፲፯፻፲፩—፲፩ ።

(፫ኛ) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ መድፈን ፡ (መሙላት) ።

ከላይ ፡ ያብራራነው ፡ የመሸሪያ ፡ ሕጉግ ፡ "በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ " የነበሩት ፡ የበፊት ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ ይሽራል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በልማድ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ላልተመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ያገለግላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ አንዳንድ ፡ ሕጎችን ፡ እንኳን ፡ ለማሟላት ፡ አይጠቅምም ። ለማሟላት ፡ ወይም ፡ ለመተካት ፡ የሚጠቅም ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ አጋጊው ፡ በጠቅላላ ፡ አብረው ፡ የሚሔዱትን ፡ ሕጎች ፡ በሞላ ፡ በመሻር ፡ ፈንታ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑትን ፡ በሻረ ፡ ነበር ።

ከላይ እንደተመለከተው ፤ በዚህ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥ ፡ ላልተጠቀሱ ፡ ጉዳዮች ፡ በልማድ ፡ በሚሠራባቸው ፡ ሕጎች ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ የማይቃወሙ ፡ ሲሆን ፡) መገልገል ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ፫ሺ፫፻፷፯ ፡ ቁጥሮች ፡ ያልሸፈኑዋቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። በበኩሌ ፡ ያገኘሁት ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፤ ይኸውም ፡ በአጋጊው ፡ ከተተውት ፡ ጉዳዮች ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ገንዘብን ፡ በማኅበር ፡ ለማስቀመጥ ፡ ስለሚቋቋሙ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበሮች ፡ ከሚናገረው ፡ በቀር ፡ ስለመረዳጃ ፡ ማኅበሮች ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይጠቅስም ። መረዳጃ ፡ ማኅበሮችን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፬፻፸፭ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ሲያደርጋቸው ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፪፻፲፪ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይወጣሉ ፡ በተባሉት ፡ አሁን ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ ያደርጋቸዋል ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ በመስማማት ፡ ብቻ ፡ በልማድ ፡ የሚቋቋሙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀመጥ ፤ ለመበደር ፡ እንዲሁም ፡ ለሌላም ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያገለግሉ ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበሮች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ እንደ ፡ ዕቁብ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። አብዛኞቹ ፡ ደንቦች ፡ ከጉራጌ ፡ ጎሳ ፡ የመነጩ ፡ ሲሆን ፤ የአሠራራቸውን ፡ ሁኔታ ፡ መግለጽ ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ ውጪ ፡ ነው ።[23] ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፫፻፷፯ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሰው ፡ ባሉ ፡ ልማዶች ፡ የመገልገል ፡ ዕንስ ፡ ሐሳብ ፡ ሌላ ፤ የዕቁብ ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያልተወሰኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሚያሟሉ ፡ እራሳቸውን ፡ እንደቻሉ ፡ በቀጥታ ፡ ሊገለገልባቸው ፡ ይቻላል ።

23. ስለዚህ ፡ እርግጠኛ ፡ በአዲስ ፡ አበባው ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ጥናት ፡ (የኢትኖሎጂ) ፤ ቁ/፭ ፤ (እ. ኤ. አ. ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም) ገጽ ፡ ፩፫ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ "ዕቁብ" ፡ አስፋው ፡ ዳምጤ ፡ የጻፈውን ፡ ተመልከት ።

(፫ኛ) ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ የአህጉራዊ ፡ አውሮፓ ፡ ሕጎች ፡ ዓይነት ፡ ናቸው ። በአህጉራዊ ፡ አውሮጳ ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፤ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ሕግ ፡ መነሻ ፡ ንቅዕ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ ዳኛ ፡ ሠራሽ ፡ ስለአልሆነ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕግ ፡ የተያያዘ ፡ እንጂ ፡ የተለያየ ፡ እንዳይሆን ፡ ማድረግ ፡ ተግባራቸው ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ የነሱ ፡ ፍርድ ፡ የማግባባት ፡ ኃይሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ፕላኒዮል ፡ እንደ ፡ ገለጸው[24] "በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ኢ. ኤ. አ. ፲፰፻፬ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ (በፈረንሳይ ፡ አገር ፡) የተቋቋሙት ፡ ሕጎች ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የአህጉራዊው ፡ አውሮጳ ፡ ሕግ ፡ ማብራሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጣቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ናቸው ። ልማዳዊ ፡ ሕግም ፡ (ከመን ፡ ሎው ፡) ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ይበልጡን ፡ የተመሠረተው ፡ በፍርዳዊ ፡ ሕግ ፡ ነው ። እንደኋለኞቹ ፡ ያሉ ፡ ሕጎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አከራካሪ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ባጋጠማቸው ፡ ጊዜ ፤ ጉዳዩን ፡ ለመወሰን ፡ ሲሉ ፡ ያወጧቸው ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ልማድን ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለማስገባት ፤ ስለማመልከትና ፡ የፍትሐ ፡ ብብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ ሥፍራዎችን ፡ ስለመድፈን ፡ (ስለመምላት ፡) ከአብራራን ፡ በኋላ ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤን ፡ ልማድን ፡ የምንጠብቅበት ፡ አራተኛ ፡ መንገድ ፡ አድርገን ፡ እናቀርባለን ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ የሰጡትን ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ስናስታውስ ፡ ይህ ፡ ፬ኛው ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይይዛል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ ሕግ ፡ መንግሥት[25] ፡ መሠረት ፡ ከበላይ ፡ ሕግ ፡ አውጪዎች ፡ አንዱ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ የተናገሯቸው ፡ ቃላት ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ዋጋ ፡ ይኖረዋል ። መሪ ፡ ቃሉም ፡ እላይ ፡ "ገላጭ ፡ ምክንያቶች ፡" እሚለው ፡ ውስጥ ፡ እንደጠቀስነው ፡ "የተሻሩ ፡ የቀድሞ ፡ ሕጎች ፡" ከሚለው ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ ጋር ፡ በመለየት ፡ ከባህልና ፡ ከልማድ ፡ ለመራቅ ፡ አለመታሰቡን ፡ ያሳያል ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የአጋጊውን ፡ ፍላጐት ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ የለም ። በአህጉራዊው ፡ አውሮጳ ፡ አብነት ፡ መሠረትም ፡ ይህ ፡ የአጋጊው ፡ ፍላጐት ፡ በቅርብ ፡ የታገኑን ፡ ሕጎች ፡ በምንተረጕምበት ፡ ጊዜ ፡ መሪያችን ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

ከባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ለመራቅ ፡ ያልታሰበ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተገቢው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አንጋገር ፡ ልማዳዊ ፡ ትርጕምን ፡ መስጠት ፡ ይኖርባቸዋል ።

24. እላይ ፡ የጠቀስነው ፤ ፕላኒዮልና ፡ ሪፔርት ፡ በቍ. ፲፯ ፡ (ለ) ውስጥ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ፰ ።

25. ለምሳሌ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም.) ቍ. ፹፰ ፡ ጋር ፡ አነጻጻ ፡

ይህን ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ በጥንቃቄ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ።
የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፯፻፴፫ ፡ ውሎች ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ሕጉ
ጎች ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ እንደሆን ፡ እንዲተረጐሙ ፡ አይፈቀደም ። አብዛኞቹ ፡
የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮችም ፡ ግልጽ ፡ ናቸው ። ዳግም ፡ በቀላሉ ፡ ትርጉ
ማቸውን ፡ ከአረፍተ ፡ ነገሩ ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ በፈረንሳይ ፡ ከተጻፈው ፡ የመ
ጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፤ ግልጽ ፡ ባለ
መሆናቸው ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በመናገራቸው ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ትርጉም ፡
የሚሰጡት ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮችን ፡ መለየት ፡ ያስፈልጋል ። ልማዳዊ ፡ ትርጉሞ
ችም ፡ (፩) የበፊት ፡ ልማድን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለሚያስገቡ ፡
ወይም ፡ ለሚያመለክቱ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ (ለምሳሌ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡
ውስጥ ፡) (፪) ከውጭ ፡ አገር ፡ "ለወረስናቸው ፡ (ለተቀበልናቸው ፡)" መሆና
ቸውን ፡ ለሚያመለክቱ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ በማመዛዘንና ፡ በመጠንቀቅ ፡ ሊሰጡ ፡
ይገባል ። ይኸም ፡ ሲሆን ፡ በተቀበልናቸው ፡ አንቀጾች ፡ ላይ ፡ ያለማመዛዘንና ፡
ያልጥንቃቄ ፡ ልማዳዊ ፡ ትርጉሞች ፡ ሊሰጡ ፡ አይገባም ። ይኸም ፡ የተባለበት ፡
እነዚህ ፡ የተወረሱ ፡ አንቀጾች ፡ ፈልቀው ፡ በተገኙበት ፡ አብነት ፡ (ዶክትሪን ፡)
መሠረት ፡ ካልተተረጐሙ ፡ በቀር ፡ ፍች ፡ የማይሰጡ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡
እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተያያዙ ፡ አይሆኑም ። (ስለተወረሱ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡
ምሳሌ ፡ ስለግዴታ ፡ ሕግ ፡ እሚለውን ፡ ተመልከት ።) እነዚህም ፡ የሕግ ፡ ቁጥ
ሮች ፡ "በዓለም ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ ተሽለው ፡ የሚገኙ ፡ ሕጎች ፡" እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡
የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መቅድም ፡) ውስጥ ፡ የተዋስናቸው ፡ ስለሆነ ፤ እዚህ ፡ ሊሰጡ ፡
የተፈለገው ፡ ትርጉም ፡ እዝያ ፡ እንደተሰጡት ፡ ያለውን ፡ ነው ፡

አሁን ፡ ከላይ ፡ ለአቀረብነው ፡ ሐሳብ ፡ ምሳሌ ፡ እንሰጣለን —

(፩) (ሀ) በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ልማድን ፡ ማመልከት ፡ በሚለው ፡ ሥር ፡
የቁ. ፲፯፻፷፰ ፡ የመሬት ፡ ሥሪት ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ ተወላጆች ፡ የሚከፋፍሉትን ፡
ልማዳዊውን ፡ የጋራ ፡ የመሬት ፡ ርስት ፡ የማይጨምርና ፡ ተወላጅ ፡ የሆነም ፡
ሰው ፡ የትውልድ ፡ ሐረጉን ፡ መዝዞ ፡ ርስቱን ፡ ሊጠይቅ ፡ እንደሚችል ፡
ጠቅሰን ፡ ነበር ። "ተወላጅ ፡" የሚለውም ፡ አነጋገር ፡ አለመግለጫ ፡ የተነገረ ፡
እንደሆን ፡ በአውሮጳ ፡ የሚገኘው ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተብሎ ፡ ይተረጐማል ፡
(ማለት ፡ አባት ፡ እናትና ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡) ። በዚሀ ፡ በተጠቀስነው ፡ ቁጥር ፡ ግን ፡
ተወላጅ ፡ ማለቱ ፡ የትውልድ ፡ ሐረጋቸው ፡ የረዘመ ፡ ምንም ፡ ሩቅ ፡ ቢሆን ፡ ርስ
ቱን ፡ ሳይከፋፈሉ ፡ ከወረሰው ፡ ከአንድ ፡ የትውልድ ፡ ግንድ ፡ የተገኙን ፡ ተወላ
ጆች ፡ (ዘመድ ፡ አዝማድን ፡) ነው ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ በጋራ ፡ ከተያዘው ፡ መሬት ፡ ርስቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ድርሻውን ፡
ስጡኝ ፡ ለማለት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ይችላል ። ይኸም ፡ ድርሻን ፡ ለማስጠየቅ ፡
የሚችል ፡ ተወላጅነት ፡ (የትውልድ ፡ ሐረግ ፡ በቁ. ፳፻፹፩ ፡ (፪) የተወሰነ ፡ ይመ

ስላል ። ይህ ፣ ቁጥር ፣ እንደሚያመለክተው ፣ ርስቱን ፣ ሊጠይቅ ፣ የሚችለው ፡ (የመሬት ፣ ሥሪት ፡ የደርጋ ፣ ሕጉን ፣ ሊቃወም ፣ የሚችለው ፤) ተወላጅ ፣ ነኝ ፣ ባይ ፣ ርስቱን ፣ ሳያከፋፍል ፣ ከሞተው ፣ ሰው ፣ ከሰባት ፣ ትውልድ ፣ በላይ ፡ መራቅ ፣ የለበትም ።

(ለ) "ከጋብቻ ፣ ውጭ ፣ በግብረ ፣ ሥጋ ፣ ግንኙነት ፣ ስለ ፣ መኖር ፣" (ቁ. ፯፻፳ ፡) ተብሎ፣ የሚጠራው ፣ እንደጋብቻ ፣ የሚለጥቁትን ፣ ሁለት ፣ ውጤቶች፣ ያስከትላል ። እነዚህም ፣ ከጋብቻ ፣ ውጭ ፣ በሆነ ፣ በግብረ ፣ ሥጋ ፣ ግንኙነት ፣ ጊዜ ፣ ስለተጸነሱ ፡ ወይም ፡ ስለተወለዱ ፣ ልጆች ፣ አባት ፣ ማን ፣ መሆን ፣ መገመትና ፣ (ቁ. ፯፻፲፭ ፣ እና ፣ ፯፻፵፮ ፣) ሴትየዋ ፡ ለምትገባባቸው ፣ ዕዳዎች ፣ የወንድየው ፡ ዋስትና ፣ (ቁ. ፯፻፲፱ ፤ ከዚህም ፣ ጋር ፣ ቁ. ፯፻፳ን ፣ እንገጽር ፣) ናቸው ። በቁ. ፯፻፲፬ ፣(፩) መሠረት ፣ ይህን ፣ ዓይነት ፣ ከጋብቻ ፣ ውጭ ፣ የሆነ ፣ ግንኙነት ፣ የሚመጣው ፣ የሰውዬውና ፡ የሴቲየይቱ፣ ሁኔታ ፣ "እንደተጋቡ ፣ ሰዎች ፣ ዐይነት ፣" የሆነ ፣ እንደሁ ፣ ነው ። የዚህ ፡ ዐይነት ፣ ማመሳሰል ፣ ልክ ፣ እንደሚስት ፣ ሆና ፡ (ከቁ. ፰፻፹ ፣ እስተያይ ፣) በደሞዝ ፣ ለምትቀጠረው ፣ ሴት ፣ ይሠራ ፣ አይሠራ ፣ የሆን ? የሚል ፣ ጥያቄ ፣ ያስከትላል ። ይህ ፣ ማመሳሰል ፣ በደሞዝ ፣ ለምትተዳደረዋ ፣ (እንደ ፣ አሽከር / ገረድ ፣ በደሞዝ ፣ ተቀጥራ ፣ እንደሚስት ፣ በሰማንያ ፣ ለምታገለግለው ፣) ይሠራል ፣ ማለት ፣ በሕጋዊ ፣ መንገድ ፣ ትክክለኛም ፣ ባይሆን ፡ በልማዳዊ ፣ ሕግ ፣ በኩል ፣ አጥጋቢ ፣ መልስ ፣ ነው ። ይኸውም ፣ በደሞዝ ፡ ለሚተዳደሩ ፣ የጭን ፣ ገረዶች ፣ የተወሰነ ፣ መታወቅ ፣ ከመስጠቱ ፡ የተነሳ ፣ የሚወለዱት ፣ ልጆች ፣ የቀጣሪው ፣ ልጆች ፣ መሆናቸው ፣ የተረጋገጠ ፣ ይሆናል ።

(፪) (ሀ) በሳይንስ ፡ ጥበብ ፣ መንገድ ፣ (አርቲፊሴል ፣ ኢንሲሚኔሽን ፣) የሚደረገው ፡ የልጅ ፡ ማስጸነስ ፣ ዘዴ ፡ (ቁ ፯፻፺፩) በኢትዮጵያ ፣ ልማድ ፣ ያልታወቀ ፣ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ጥበባዊ ፡ መንገድ ፣ የተጸነሰን ፣ ልጅ ፣ ስለመካድ ፡ የተደነገገውን ፣ ፍትሐ ፡ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፡ ትርጉም ፣ ዘዴው ፣ ከመነጨበት ፣ አገር ፣ መወሰድ ፡ አለበት ።

(ለ) ከሌላ ፡ አህጉር ፣ የተወረሰው ፡ አብዛኛው ፡ የውል ፣ ሕግ ፣ ሐሳበ ረቂቅ ፣ ከመሆኑ ፣ የተነሳ ፤ ከመነጨበት ፣ አገር ፣ በሮማውያን ፣ አብነት ፣ ትምህርት ፣ ካልተገለጸ ፣ በስተቀር ፡ እምብዛም ፣ ፍችን ፣ አይሰጥም ።

(ሐ) ሆኖም ፤ ውሉ ፡ ግልጽ ፣ በሆነ ፣ ጊዜ ፣ በውጭ ፡ አገሩ ፣ አብነታዊ ፣ ትምህርት፣ መጠቀም፣ አያሻም ። ለምሳሌ ፣ የፍትሐ ፣ ብሐር ፣ ሕግ፡ ቁ. ፲፯፻፹ ፣ ስለውል ፣ አቀራረብና ፡ አቀባበል ፡ በሚናገርበት ፣ ጊዜ ፣ "ፈቃድን - በተለመዱ ፣ ጠቅላላ ፡ ምልክቶች --- ለማስታወቅ ፣ ይቻላል ፤" ሲል ፡ በልማድ ፡ የሚሠራባ

ቸውን ፡ እንደመጨባበጥ ፡ መሸኮት ፡ ፍንጥር ፡ የመሳሰሉትን ፡ ማለቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ የተነጋገርንበትን ፡ ልማድን ፡ ማመልከትን፡ አንዱን ፡ ሁኔታ ፡ ያሳያል ።

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያቀረብናቸውን፡ ሐሳቦች ፡ ቢቀበሉም ፡ ባይቀበሉም ፡ ተፈላጊው ፡ ነገር ፡ ትርጉም ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሁልጊዜ ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ትርጉም ፡ መጽናታቸው ፡ እንዲያገ ፡ ነው ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍርዳዊ ፡ ሕግ ፡ በማበጀት ፡ ፈንታ ፡ ሕግ ፡ የለሽነትን ፡ ያስገኛሉ ። በዚህ መጽሔት ፡ የሚታተሙትም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮችና ፡ ቃላቶች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ፍች ፡ እንዲኖራቸውና ፡ የተያያዙ ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳሉ ። ስለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ፍች ፡ መሠረታዊ፡ ደንቦች፡ በዚሁ ፡ መጽሔት፡ በአንደኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፯) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺፱ ፡ ላይ ፡ ታትሞ ፡ በወጣው ፡ ከጂ. ክሽቾኖቢች ፡ "ዐዋጅ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ትርጉም፡ (ፍች) ፡ በኢትዮጵያ ፡ " በሚለው ፡ አርእስት ፡ ጽፎ ፡ የገለጸውን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

(፰ኛ) በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶች ።

ከላይ ፡ የተነጋገርንባቸው ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ በልማድ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚያገለግሉ ፡ መንገዶች ፡— ልማድን ፡ በሕግ፡ ማስገባት፡ ልማድን ፡ ማመልከት ፡ (መጥቀስ) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባዶ ፡ሥፍራዎችን ፡ መምላትና ፡ ፍርዳዊ ፡ በይቤ ፡ ያሉት ፡ ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ችግር ፡ በሙሉ ፡ አያጠናቅቁም ። ስለዚህ ፡ ቀሪው ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ በመኖሩ ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ ሕጋዊነት ፡ የሌላቸውን ፡ የልማድ ፡ ደንቦች ፡ የሚገለግሉባቸውን ፤ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንገዶችን፡ መመርመር፡ አስፈላጊ፡ ነው ።[26] እነዚህም፡ (፩ኛ) ፡ ስለቤተዘ መድ ፡የተጻፉት ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ለባልና ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ለሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ያልተወሰነ ፡ ሥልጣን ፡ የሚተውት ፡ ሕጎች ፤ (፪ኛ) የግል ፡ ውል ፡ በተዘዋዋሪ ፡ ሁኔታ ፡ ልማዳዊ፡ ፡ ደንቦችን ፡ የሚፈቅድባቸው ፡ ሕጎች ፤ ስለማኅበር ፡ በወጡት ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ መንገዶች ፡ ናቸው ።

(፩ኛ) ስለቤተዘመድ ፡ ሕግ ።

ለሁሉም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆነው ፡ የቤተዘመድ ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ትጽዕኖ ፡ የሀገርን ፡ ወግ ፡ በማመልከት ፡ (በመጥቀስ)፡ ተቃ

26. በልማድ ፡ ሕግ ፡ ለመጠቀም ፡ ዋና ፡ ፍንጭ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አርእስት ፡ ሥር ፡ ለመተንተን ፡ ተስማሚ ፡ ያልሆነው ፡ ምናልባት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጋችን ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጋብቻ ፡ አለመኖሩ ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፭፻፷፭ ፡ የተዘለከለው ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ እንኳ ፡ ሲፈርስ ፡ የሚችለው ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። (ቁ- ፮፻፲፪) ። የመጀመሪያው፡ (በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ- ፮፻፲፭፡ መሠረት ቅጣት ፡ ስለሚደርስበት ፡) ይህንን ፡ ለማድረግ ፡ አይደፍርም ። ሁለተኛው ፡ ማለት ፡ ዐቃቤ፡ሕጉም የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፡ ተግባር ፡ በግዴለሽነት ፡ ያልፈዋል ። ይሆም ፡ ታላቅ ፡ ፍንጭ ፡ የልማድ ፡ ሕግን ፡ በመጠበቅ ፡ ረገድ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ከማብራራት ፡ ይልቅ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ የውጭ ፡ ጥናት ፡ ይጠይቃል ።

ልሷል ፣ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣወን ፡ በጋብቻ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሥልጣንን ፡ የሚያጸድቁ ፡ ሕጉ ፡ ሳይረሰው ፡ ትጽዕና ፡ ትራስ ፡ የሚሆኑለትን ፡ ሁለት ፡ ብልሃቶችን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ እንመረምራለን ።

(ሀ) የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሊሰፋና ፡ ሊጠብ ፡ በሚችል ፡ አዛኘ ፡ በሆነ ፡ መብት ፡ ሰጭ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ ለልማዳዊ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ (የጋብቻ ምስክሮች) ፡ ሰፋ ፡ ያለና ፡ ያልተወሰነ [27] ፡ ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጣቸዋል ። ይህም ፡ ሥልጣን ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚነሱት ፡ ጠቦችና [28] ፡ ስለጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ እንዲሁም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በሰዎችና ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጡ ፡ ያስችላቸዋል ። [29] ውሳኔአቸውም ፡ ከአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ ውጭ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ማጓደላቸውን ፡ ለማስረዳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይግባኝ ፡ አይባልበትም ፡ (ቁ-፯፻፴፪) ። የመተጫጨት ፡ ሥርዐት ፡ ምስክሮችም ፡ በመተጫጨት ፡ ጉዳይ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ሲነሳ ፡ ይዳኛሉ ፡ (ቁ. ፯፻፳፫) ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ሻሪው ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብ/ ር ፡ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ሁኔታ ፡ ባለማመልከቱ ፡ "የተሻሩት ፡ "የአገር ፡ ልማዶች ፡ በመሠረቱም ፡ ባይሆን ፡ በሁናቴው ፡ አኳኋን ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲውሉ ፡ (እንዲገቡ) ፡ በር ፡ ይከፈትላቸዋል ። ስለ ፡ ዚህ ፡ የተሻሩት ፡ የልማድ ፡ ሕጎች ፡ በማይቀረው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ አማካኝነት ፡ እንደገና ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

(ለ) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ-፯፻፳፯ ፡ እና ፡ ፯፻፴፪ - ፴፫ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ልምድ ፡ ሌሎችን ፡ በከፊል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑትን ፡ መንገዶች ፡ ይሰጣሉ ። እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ አግቢው ፡ ወይም ፡ ተጋቢዎቹ ፡ ባንድነት ፡ (ከጋብቻ ፡ በፊት) ፡ ወይም ፡ በቤተዘመድ ፡ ሽማግሌች ፡ በኩል ፡ (በጋብቻ ፡ ጊዜ) በመካከላቸው ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ያለበትን ፡ ግዴቴዎችና ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ የሚያመጣውን ፡ ውጤት ፡ ለመወሰን ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ይፈቅድላቸዋል ። (በዚህ ፡ ረገድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ በስተቀር ፡ ተዋዋዮቹ ፡ እንዳሻቸው ፡ እንዲዋዋሉ ፡ ይፈቅዳል ። ከዚህ ፡ አቀራረብ ፡ ጋር

27. ለምሳሌ ፤ ከቁ ፡ ፯፻፳፮ ፡ (፪) ፡ ጋር ፡ አነፃፅር ።

28. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ/፯፻፴፮ ፡ (፪) ፡ ፯፻፶፰ ፡ (፪) ፡ ፯፻፲፮ ፡ (፪) ፯፻፺ ፡ (፫) ፯፻፰ ፡ (ሐ) እንዲያውም ፡ ዋናውን ፡ ስለ ፡ ነገር ፡ አባት ፡ የሚመለከተውን ፡ (ቁ/፯፻፳፩) ፡ ተመልከት ። ይህም ፡ የነገር ፡ አባት ፡ የጋብቻ ፡ አስታራቂ ፡ ሲሆን ፡ ላለ ፤ ከምስክሮቹ ፡ ውስጥም ፡ "የመጀመሪያው ፡ ምስክር " ፡ እና ፡ ወይም ፡ ለጋብቻ ፡ ሁናቴ ፡ ዋስ ፡ የሚሆነው ፡ እሱ ፡ ነው ።

29. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ቁ.፯፻፳፯—፺፪ ፡ ፯፻፲፮—፲፭ ፡ እንዲያሁም ፡ ዋናውን ፡ ቁ. ፯፻፳፯—፳፰ ፡ ተመልከት ።

ቁ. ፯፻፴፩ን ፣ እንጻጽር ።) በራሳቸው ፡ ብቻቸውን ፣ ሕጋዊ ፣ ያልሆኑ ፡ ልማዶች ፡ በጋብቻ ፣ ስምምነት ፡ ወ ስጥ ፣ ሰግረው ፡ እንደሚገኙ ፣ ግልጽ ፣ ነው ፣ ሆኖም ፡ በትእዛዛዊ ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ የተወሰነውን ፡ የመረዳዳትና ፡ የአብሮ ፡ መኖር [30] ፡ ግዳጅ ፡ ማክበር ፡ አለባቸወ ። የዚህ ፡ ዐይነት ፣ መንገድ ፡ አንዱ ፡ ወ ጤት ፡ ዓለም በሞላ ፡ የግል ፣ መብቶችና፣ ግዴታዎች ፡ የማይለውጡ ፡ የማይሸጡ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ከሚያምንበት ፣ መሠረት ፡ ሐሳብ ፡ በመለየት ፡ ተጋቢዎቹ ፡ በመካከላቸው ፡ ስላ ለው ፣ ግንኙነትና ፣ የግል፡ መብታቸውንና ፣ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ያለውን ፡ ግዳጅ ፣ በራ ሳቸው ፡ ፈቃድ ፣ እንዳሻቸው ፣ መወሰን ፡ እንዲችሉ ፡ አድርጓቸዋል ፣ (ቁ· ፯፻፳፯ (፪) ። የቤተ ፡ ዘመድ ፣ ሽማግሌዎች ፡ እነዚህን ፡ መብትና ፡ ግዳጆች ፡ ሊያሻሽሉ ፡ ይችላሉ ፡ (ቁ. ፯፻፴፪ (፪)) ። የዚህም ፡ ዐይነት ፣ የጋብቻ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ መሻሻል ፣ ትእዛዛዊ ፡ ሳልሆነ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ተቃራኒ ፡ ሆኖ ፡ ለምሳሌ ፣ የቤት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራው ፣ በሚስቲቱ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በባልየው ፡ ነው ፡ (ከቁ. ፯፻፹፯ ጋር ፡ አነፃጽር) (በጣም ፡ የራቀ ፣ ምሳሌ ፣ ቢሆንም) ፤ ወይም ፡ የመኖሪያ ፡ ቦታቸውን ፡ የምትመርጠው ፡ ሚስቲቱ ፡ ነች ፡ (ከቁ-፯፻፹፩ ፡ ጋር ፡ አነ ፃጽር) ፤ ማለት ፣ ይችላል ። ጠልቆ ፣ ሳልተመራመረ ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፣ ስምምነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፹፫ [31] ፡ የተወሰነውን ፡ የመተማመን ፡ ግዴታ ፡ ሕግ ፡ ሊሽረው ፡ ወይም ፡ በአንዳንድ ፡ የአገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ ግዳጅ ፡ በሚ ስቲቱ ፡ ላይ [32] ፡ ብቻ ፡ ሊወስነው ፡ የሚችል ፡ ይመስለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወን ጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ (ቁ. ፯፻፲፭) ዝሙትን ፡ ስለሚከለክል ፤ ይኸን ፡ ለማድረግ ፡ አይ ቻልም ።

ስለዚህ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ጋብቻ ፡ ለተጋቢዎቹ ፡ መብትና ፡ ግዳጃቸውን ፡ በራሳ ቸው ፡ (ምናልባት ፡ የልማድን ፡ ሕግ ፡ በመከተል) ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ የሚ ሰጥ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ አስተያየት ፡ ሊሰጠው ፡ ይቻላል ። ዳግም ፣ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የማያጋጥመው ፡ በጋብቻ ፣ ላይ፣ የሚነሳ፣ ጸብ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያገኘው፣ "በልማድ" ፡ በተመሠረተው፣ የሽምግልና፣ ዳኝነት ፡ ነው ። ይኸም ፡ ሆኖ ፣ ልማድን ፡ ከአንድ፣ ሕጋዊ፣ ነገር ፡ ጋር ፡ ሳያያይዙ ፡ "እንዲያው ፡ ጥሬውን ፡ በቀጥታ ፡ " ማመልከት ፡ (መጥቀስ) የተከለከለ ፡ ነው ። (ቁ- ፯፻፴፭)

(፪ኛ) ግልግል (ስምምነት) ።

የቤተዘመድ ፣ ሽማግሎችን ፡ (የጋብቻ ፣ ምስክሮችን ፡) ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ አብራርተን ፣ ሰጥተናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚሀ ፡ ውጭ ፡ በግዴታ ፡ ወይም በፍ

30. ቁ ፯፻፩ እና ፯፻፵ን እንዲሁም ትእዛዛዊ ቁጥር የሆኑትን ፯፻፸፰—፹፬ ።

31. የተለየ ፣ ስምምነትን ፣ ማድረግን ፣ የሚከለክለውን ፣ ንዑስ ፣ ቁ/(፫) ፤ ፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ ከሚሊዮን መርዛታል ። የኢትዮጵያ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግን ፣ ግረሚያ ፣ ተመልከት ።

32. ይህም ፣ ዝሙትን ፣ ለጋብቻ ፣ መፍረስ ፣ በቁ. ፯፻፹፰—፹፱ ፣ መሠረት ፣ ከባድ ፣ ምክንያት ፣ ከመሆን ፣ አያስቀረውም ።

ትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ በወል ፡ ባልሆነው ፡ በልማድ ፡ በአዛ ወንቶች [33] ፡ የሚደረገው ፡ ዕርቅ ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ሊነካ ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ የመስማማቱ ፡ ግዴታ ፡ ይጫናቸ ወና ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ስለማይፈቅዱ ፡ ጉዳዩ ፡ በዕርቅ ፡ ስለሚያ ልቅ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፣ በውርስ ፡ መሻል ፡ የሚነሳ ፡ አለመግባባት ፡ በፍትሐ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ሻሪ ፡ ቁጥር ፡ በተሻረው ፡ የልማድ ፡ ደንቦች ፡ ውሳኔ ፡ ሊያገኝ ፡ ይች ላል ። የሚያገኘው ፡ ውጤት ፡ በፍትሐ ፡ ብሐ ሩ ፡ ሕግ ፡ ስለግልግል [34] ፡ በሚፈ ቅደው ፡ ውሊ ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ። እንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ ያሉ ፡ ግልግሎች ፡ በፍትሐ ብሐር ፡ ቁ. ፫፻፲፪ ፡ የተደነገገው ፡ "የመብት ፡ ስሕተት ፡ " የማይለውጣቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ ናቸው ። ይኸም ፡ ማለት ፡—

(፩) ግልግል ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ይግባኝ ፡ ሳይንረው ፡ መጨ ረሻ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ተፈረደ ፡ ፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(፪) ግልግል ፡ ያደረጉበትን ፡ መብቶች ፡ በመመልከት ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንዱ ፡ በተደረገው ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ግልግል ፡ ሊነካ ፡ አይቻልም ።

ሀ—ወንጀሎችን ፡ የሚመለከት ፡ ሥልጣን ።

ለ—በታዊ ፡ (ሥፍራዊ—የአጥቢያ) ሥልጣን ።

ሐ—የፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ማጠቃለያ ።

<u>መጀመሪያ ፡ መግቢያ ።</u>

የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወንጀሎችን ፡ በሚመለከት ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሁለት ፡ ጠባዮችን ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። የመጀመሪያው ፡ ጠባይ ፡ የሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ስላሉ ፡ ሰዎች ፡ ነው ።በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ። የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግንም ፡ ጥሰው ፡ ሲገኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ሊፈረድባቸው ፡ ይችላል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ስለአሉ ፡ ስለዚህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ስለሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀለኛ ፡መቅጫ ሕግ ፡ አንደኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ (ከቁ. ፲፩ ፡ እስከ ፡ ፲፪) ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይገኛል ።

ሁለተኛውን ፡ ጠባይ ፡ የሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ሥልጣን ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሰሙ ፡ ያላቸው ሥልጣንና ፡ ክሱም ፡ የት ፡ ቦታ ፡ መሰማት ፡ እንደሚገባው ፡ መገለጽ ፡ አለበት ። ለምሳሌ ፡ ክሱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ባስቻለው ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ወይም ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በጉለሌ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ ይገባው ፡ እንደሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ጉዳዮች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንደኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ምዕራፍ ፡ ፩ እና ፡ አራተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ተደንግገዋል ፡ (ቁ. ፬ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ እና ፡ ከ፺፱—፻፯) ።

<u>ሁለተኛ ፡ አንደኛው ፡ ጠባይ—በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ስለ አሉ ፡ ሰዎች ።</u>

አንድ ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ አለመሆኑን ፡ ለመወሰን ፡ የሚያስችሉት ፡ የሚከተሉት ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ፤ (፩ኛ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ (፪ኛ) የተከሳሹ ፡ ዜግነት ፡ (፫ኛ) የተፈጸመው ፡ ወን

ጇል ፡ ዐይነት ። በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥጣልን ፡ ሥር ፡ ነው ፡ ያሰኛል ። በሌላ ፡ ሁኔታዎች ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ተከሳሹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ባይሆንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተከታይ ፡ (አነስተኛ) ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ነው ፡ ያሰኛል ። አንድ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ ተከታይ ፡ (አነተሰኛ) ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ መሆኑ ፡ በሥልጣኑ ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ልዩነት ፡ ይፈጥራል ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በወንጀል ፡ ተከስሶ ፡ ቢለቀቅ ፡ ወይም ፡ ነፃ ፡ ቢወጣ ፤ ይህ ፡ ነፃ ፡ መውጣቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በዚያው ፡ ወንጀል ፡ ከመከሰስ ፡ አያድነውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰውየው በኢትዮጵያ ፡ ተከታይ ፡ (አነስተኛ) ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ቢደርስ ፡ ነፃ ፡ ይወጣል ።

ሀ—ዋና ፡ ሥልጣን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፩—፲፯) ።

በሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ አላት ። (ሀ)ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰ ፡ (ለ) ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ወንጀሎችን ፡ ፈጽሟል ፡ ተብሎ ፡ በተከሰሰ ፡ (ሐ) በውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀል ፡ ሠርቷል ፡ ተብሎ ፡ በተከሰሰ ፤ ይህም ፡ ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ አገር ፡ ሰውየው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፍረው ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ (መ) በውጭ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ወንጀሎችን ፡ ፈጽሟል ፡ ተብሎ ፡ በተከሰሰ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ ኃይሎች ፡ ባልደረባ ።

(፩) በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ስላሉ ፡ ሰዎች ፤

(ሀ) በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሠሩ ወንጀሎች ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፩—፲፪) ።

ቁ. ፲፩ (፩) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ከተጠቀሱት፡ ማንኛውንም ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደሚቀጣ ፡ ይገልጻል ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ማለትም ፡ የብስ ፤ ባሕርና ፡ አየርም፡ ጭምር ፡ ነው ።

ምሳሌ ፡— አንድ ፡ የኬንያ ፡ ዜጋ ፡ ለጉብኝት፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፹፱ን፡ በመጣስ ፡ በሌላ፡ ኬንያዊት ፡ ላይ ፡ በማስገደድ ፡ የግብረ ፡ ሥጋን ፡ ተግባር፡ ፈጽሞባታል፡ ቢባል ፤ ወንጀሉ፡ የተፈጸመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በመሆኑ፡ ተከሳሹ፡ በኢትዮጵያ፡ ወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ነው ። ስለዚህ፡ ቁ. ፭፻፹፱ን ፡ ጥሰሃል ፡ ተብሎ ፡ በኢት ዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ተከስሶ ፡ ሊፈረድባት ፡ ይቻላል ።

<u>ምሳሌ</u> ፡— አንድ ፡ የሱዳን ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ አኤሮፕላን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ላይ ፡ ሲበርር ፡ አኤሮፕላኑ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ የሱዳን ፡ ዜጋ ፡ ሌላውን ፡ የሱዳን ፡ ዜጋ፡ ቢደበድበው፤ ወንጀሉ፡ የተፈጸመው ፡ ኢት ዮጵያ ፡ አየር ፡ ላይ ፡ በመሆኑና ፡ አየሩም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ስለሆነ ፤ ወንጀሉ ፡ የተሠራው ፡ በኢት ዮጵያ ፡ ን. ነ. መ. ግዛት፡ ውስጥ ፡ ነው ። ይኸም፡ ደብዳቢውን ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ያደርገዋል ። ስለዚ ህም ፡ ቁ. ፭፻፺፬ ን ፡ ጥሰሃል ፡ ተብሎ ፡ በኢትዮዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ተከስሶ ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ።

በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አንዳንድ፡ ሰዎች ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል፡— የዲፕሎማቲክ ፡ መልእክተኞች ፡ የተላኩበት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፍረው ፡ መብት ፡ ስላላቸው ፡ እዚያ ፡ አገር ፡ ወንጀል ፡ ቢሠሩ ፤ በዚያ ፡ አገር ፡ አይከሰሱም። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉም ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፩ (፪) ፡ መሠረት ፡ መብታቸው ፡ የተ ጠበቀ ፡ ስለሆነና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ ስላልሆኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አይደሉም ።

ምሳሌ ፡— ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግ ሥት ፡ አምባሳደር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ በግድየለሽነት ፡ ወይም በቸልተኝነት ፡ መኪና ፡ ያለ፡ አግባብ ፡ ሲነዳ ፡ ሰው ፡ ድጦ ፡ ቢገ ድል ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወንጀሉ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፺፮ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ቢሆን ፡ የአምባሳደሩ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ የተጠበቀ ፡ በመ ሆኑ፤ አምባሳደሩ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ አይከሰስም ።

በቁ. ፲፩ (፫) እንደተደነገገው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አምልጦ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ጥገኝነት ፡ ጠይቆ ፡ ቢቀመጥ ፤ የኢ ትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወንጀለኛውን ፡ በጥገኝነት ፡ ያስቀመጠው፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፤ ኢትዮ ጵያ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ውል ፡ ከብዙ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ስለሌላት ፡ ስምምነት ፡ እስ ኪያደረግ ፡ ድረስ ፡ ሌሎች ፡ አገሮች ፤ ወንጀለኛውን ፤ አሳልፈው ፡ <u>አይሰጡም</u> ። ይህ ፡ ነው ፡ በኢትዮጵያ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አንቀጽ፡ ፶ ፡ እና፡ በወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፳፩ የሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ። ኾኖም ፡ በዚህ፡ ዐይነት ፡ ወንጀለ

ኖችን ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠት ፡ ስምምነት ፡ ከሌላ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ካልተፈጸመ ፤ ቁ/ ፲፩ (፫) ብዙ ፡ ዋጋ ፡ አይኖረውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወንጀለኛውን ፡ በጥገኝነት ፡ ከተቀመጠበት ፡ አገር ፡ በግድ ፡ ለማስመጣት ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፤ ቁ. ፲፪ (፩) ወንጀለኛው ፡ በጥገኝነት ፡ በተቀመጠበት ፡ አገር፡ እንዲከሰስና ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያገኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አስጠጊውን ፡ አገር ፡ ሊጠይቁ ፡ መቻላቸውን ፡ ያሳያል ። በጥገኝነት ፡ ያስቀመጠው ፡ መንግሥት ፡ ጥያቄውን ፡ ተቀብሎት ፤ ወንጀለኛው ፡ ተከሰሶ ፡ ነፃ ፡ ከወጣ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቢያዝ ፤ ወንጀለኛውን፡ እንደገና ፡ በዚያው ፡ ወንጀል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለመከሰስና ፡ ለመቅጣት ፡ <u>አይቻልም ።</u> እንዲሁም ፡ ቁ. ፲፪ (፪) እንደሚያዝዘው ፤ ወንጀለኛው ፡ በጥገኝነት ፡ በተቀመጠበት ፡ አገር ፡ ተፈርዶበት ፣ ምሕረት ፡ ተደርጎለት ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ ቅጣቱ ፡ ተሰርዞለት ፡ እንደሆነ ፤ በዚሁ ፡ ወንጀል ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አይቀጣም ።

<u>ምሳሌ</u> ፡— አንድ ፡ ነፍስ ፡ ገድሏል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠረጠር ፡ የውጭ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሩ ፡ ሔዶ ፡ እዚያ ፡ ይያዛል ። የትውልድ ፡ አገሩ ፡ መንግሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ወንጀለኛውን፡ አሳልፎ ፡ ባይሰጥ ፤ ነገር ፡ ግን ፤ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጠይቆት ፣ በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ በአገሩ ፡ ተከሰሶ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣና ፣ ወደኢትዮጵያ ፡ ቢመለስ ፤ ለዚያው ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አይከሰስም ።

<u>ምሳሌ</u> ፡— ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ምሳሌ ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ ግን ፡ ወንጀለኛውን ፡ በጥገኝነት ፡ ያስቀመጠውን ፡ መንግሥት ፡ ወንጀለኛው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለሠራው ፡ ተከሶ ፡ እንዲፈረድበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሳይጠይቁ ፡ ቀሩ ። የውጭው ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ይዘው፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ፈጽመሃል ፡ ስለተባለው ፡ ወንጀል ፡ ለፍርድ ፡ ቀርቦ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስ ፤ ወንጀለኛው ፡ ለዚሁ ፡ ወንጀል ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተከሶ ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ። ምክንያቱም ፡ ወንጀለኛው ፡ በጥገኝነት ፡ በተቀመጠበት ፡ አገር ፡ የተከሰሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ (እንዲከሰስ) ሳይጠይቅ ፡ በመሆኑ ፡ ቁ. ፲፪ (፪) <u>መከላከያ ፡ ሊሆንለት</u> ፡ ስለማይችልና ፤ ቁ. ፲፯ (፪) በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ሰው ፣ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከሰሶ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣም ፤ በዚያው ፡ ወንጀል ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይከሰሳል ፡ ስለሚል ፡ ነው ። (ቁ. ፲፯ (፪) ወደ ፡ ፊት ፡ በሰፊው ፡ ይብራራል ።)

ቁ. ፲፪ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ወንጀለኛው ፡ በጥገኝነት ፡ በተቀመጠበት ፡ አገር ፡ እንዲከሰስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጠይቆ ፡ ወንጀለኛው ፡ ተፈርዶበት ፡ ቅጣቱን ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስ ፡ በዚሁ ፡ ወንጀል ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አይቀጣም ። ነገር ፡ ግን ፡ ቅጣት ፡ ተወስኖበት ፡ ቅጣቱን ፡ ሳይፈጽም ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ ፈጽሞ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ቢመለስና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢያዝ ፡ የቅጣቱ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ካላለፈ ፡ <u>በስተቀር ፡</u> ቅጣቱን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይፈጽማል ። (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፪ (፪) ።)

<u>ምሳሌ</u> :— አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሩ ፡ ሸሽቶ ፡ እዚያ ፡ ተያዘ ። በሄደበት ፡ አገር ፡ ተከሶ ፡ እንዲቀጣ ፡ ተጠይቆ ፡ ወንጀለኛው ፡ በትውልድ ፡ አገሩ ፡ ተከሶ ፡ ተፈረደበትና ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ የእሥራት ፡ ቅጣት ፡ ተወሰነበት ። ሳይታሰር ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢያዝ ፡ ይህ ፡ እድራጎቱ ፡ ከተረጋገጠና ፡ ቅጣቱ በይርጋ ፡ ሕግ ፡ ካልተሰረዘ ፡ በስተቀር ፡ የአንዱ ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይፈጸምበታል ።

<u>ምሳሌ</u> :— አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሩ ፡ ሸሽቶ ፡ ይሄዳል ። በሄደበት ፡ አገር ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ወንጀለኛው ፡ እንዲከሰስ ፡ ጠይቆ ፡ ተከስሶ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ ቢፈረድበትና ፡ እሥራቱን ፡ ሳይፈጽም ፡ ጠፍቶ ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢያዝ ፡ ወንጀለኛው ፡ እሥራቱን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አይፈጽምም ። ምክንያቱም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፴፬ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ የእስራት ፡ ቅጣት ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በይርጋ ፡ እንደሚሰረዝ ፡ ስለሚያዝ ፡ ነው ።

(ለ) <u>በውጭ ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ወንጀሎች ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፫) ።</u>

ቁ. ፲፫ የሚመለከተው በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚፈጸሙና ፡ ኢትዮጵያን ፡ ስለሚነኩ ወይም ፡ ስለሚጐዱ ፡ ወንጀሎች ፡ ነው ። <u>እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ወንጀሎች ፡ ወንጀለኛውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚያደርጉት ፡ ሁሉም አይደሉም</u> ። በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚያደርጉት ፡ ወንጀሎች ፡ በቁ. ፻፵፫ እስከ ፡ ፻፸፪ (በንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡

ግዛት ፡ ላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ግዛቱን ፡ ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ ለመጉዳት ፡ የተሠሩት) እና ፡ በቁ. ፫፻፳፯ እስከ ፡ ፫፻፴፪ (የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ በሐሰት፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ማሕተሞች ፡ በመጠቀም ፡ የተፈጸሙ) የተከለከሉት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እነዚህን ፡ ወንጀሎች ፡ የፈጸመ ፡ ወንጀለኛ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያዊም ፡ ሆነ ፡ የውጭ ፡ ዜጋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ።

<u>ምሳሌ</u> ፡—አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ካሉ ፡ ኢትዮጵያ ውያን ፡ ጋር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ለመገልበጥ ፡ እውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ ቢያድምና ፡ ይኸንኑ ፡ ዐድማ ፡ ለማከናወን ፡ እንዲረዳው ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገንዘብ ፡ መልክ ፡ ቢያሳትም ፡ ወንጀለኛው ፡ የፈጸማቸው፡ ወንጀሎች ፡ ቁ. ፪፻፵፱ ን ፡ እና ፡ ፪፻፳፯ን ፡ ስለሚጥስ ፡ በቁ. ፲፫ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ በኢ. ትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ። ይኸም ፡ ሰው ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢያዝ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ በመ ጣሱ ፡ ሊፈረድበት ፡ ይቻላል ።

<u>ምሳሌ ፪</u>—አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ ገንዘቡን ፡ ዋጋ ፡ በማሳ ጣት ፡ የሐሰት ፡ ወሬ ፡ እያወራ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የብድር ፡ አክሲ ዮን ፡ እዳይሸጥ ፡ ለማድረግ ፡ ቢሞክር ፡ በቁ. ፫፻፶፱ ፡ መሠረት ፡ ወን ጀል ፡ ይሆንበታል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ወንጀሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚ ጐዳ ፡ ቢሆን ፤ ቁ. ፫፻፶፱ በቁ. ፲፫ ውስጥ ፡ ስላልተጠቀሰ ፡ ወንጀለ ኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አይሆንም ።

(ሐ) <u>በውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እና ፡ ወታደሮች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆነው ፡ የሚሠሩዋቸው ፡ ወንጀሎች፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፩ ፡ ፲፭)</u> ።

በውጭ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ። በውጭ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ ወታደር ችም ፡ እንደዚሁ ፡ ሲሆኑ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በወንጀሉ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ሌሎች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ደግሞ ፤ በቁ. ፲፫ የተጠቀሱትን ፡ ወንጀሎች ፡ ካልፈጸሙ ፡ በስተቀር ፡ በቁ.፲፰ እንደተደነገገው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥል ጣን ፡ ሥር ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቁ. ፲፬ እንደሚለው ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ባሉበት ፡ አገር ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ ስለአላቸው ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ የማይከሰሱ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ መልዕክተኞች ፤ ቆንስሎችና ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆነው ፡ ወንጀል ፡ የሚሠሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ። ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ክስ ፡ እዚህ ፡ ሊቀርብባቸው ፡ ከሚችል ፡ በቁ.፲፫ ከተጠቀሱት ፡ ሌላ) እና ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ከሆነ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊከሰሱ ፡ ይቻላል ። ይኸም ፡ ማለት ፤—ወንጀሉን ፡ የፈጸሙትን ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ለማድረግ ፤ ወንጀሉ ፡ በሁለቱም ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ የሚያስቀጣ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ወንጀሉ ፡ ከሁለቱ ፡ በአንደኛው ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚያስቀጣው ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ሲያመለክት ፡ ብቻ ፡ ከሆነም ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ከሌለ ፡ በስተቀር ፡ በወንጀሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

ምሳሌ ፤—አንድ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ በተላከበት ፡ አገር ፡ በቸልተኝነት ፡ ሰው ፡ ቢገድል ፤ ያለበትን ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ የኢትዮጵያንም ፡ ወንጀለኛ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፳፮ ፡ ይጥሳል ። በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ መሠረት - አምባሳደሮች ፡ በተላኩበት ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ የአለመከሰስ፡ መብት ፡ አላቸው ። የኢትዮጵያውም ፡ አምባሳደር ፡ ይኸ ፡ መብት ፡ ስላለውና ፡ የተላከበትን ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ የኢትዮጵያንም ፡ ሕግ ፡ በመጣሱ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ሙሉ ፡ የሕግ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተከስሶ ፡ በቁ. ፭፻፳፮ ፡ መሠረት ፡ ሊቀጣ ፡ ይቻላል ።

ምሳሌ ፤—አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምባሳደር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሳለ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ አውቆ ፡ ቀላል ፡ የአካል ፡ ወይም ፡ የጤና ፡ ጉዳት ፡ አድርሶ ፤ ይኸም ፡ አድራጎቱ ፡ የተላከበትን ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፭፻፴፱ን ፡ ይጥሳል ። ግን ፡ በቁ. ፭፻፴፱ (፩) መሠረት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወንጀል ፡ የሚያስቀጣው ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ሲያመለክት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ባይኖርም ፡ ወንጀሉ ፡ ያስቀጣል ፡ ቢልም ፡ እንኳ ፤ አምባሳደሩ ፤ ከሳሽ ፡ ካልተነሳበት ፡ በስተቀር ፤ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ አይከሰስም ። እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ወንጀሉ ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ባይኖርም ፡ የሚያስቀጣ ፡ ቢሆንና ፡ በውጭው ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ የግል ፡ ከሳሽ ፡ ከሌለ ፡ ሊያስቀጣ ፡ የማይችል ፡ ቢሆን ፡ ከሳሽ ፡ ካልተነሳባበት ፡ አምባሳደሩ ፡ በአቃቤ ፡ ሕግ ፡ አይከሰስም ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፭ ፡ እንደተገለጸው ፤ በውጭ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ ወንጀል ፡ ቢሠሩ ፤ በሠሩት ፤ በሁሉ ፡

ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አይሆኑም ።
አንድ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወታደር ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ ተራ ፡ (ልዩ ፡ ያልሆነ) ሕግ ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ ቢሠራ ፤ በዚያው ፡ አገር ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ በአገሩ ፡ ተራ ፡ ሕግ ፡ ይቀጣል ፡ እንጂ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አይሆንም ። ሰውየው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አምልጦ ፡ ቢመጣና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ ባይሰጠው ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ስለ ፡ አንስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ በሚያወሳው ፡ አንቀጽ፡ መሠረት፡ ይከሰሳል ።
ይኸንንም ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ወደፊት ፡ እንነጋገርበታለን ።

ወታደሩ ፤ ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በአንቀጽ ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የተጠቀሱትን ፡ (ከቁ. ፪፻፹፩ እስከ ፫፻፴፩) ወንጀሎች ፡ በመሥራት ፡ ማለት ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግን ፡ የጣሰ ፡ ወይም ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ ያለውን ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ እንደሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ በጦር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ይከሰሳል ።

ምሳሌ ፡— አንድ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ኢትጵዮያዊ ፡ የምድር ፡ ጦር ባልደረባ ፡ አንዱን ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በግፍ ፡ አገዳደል ፡ ቢገድለው ፤ የአገሩን ፡ ተራ ፡ ሕግ ፡ በመጣሱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ስለማይሆን ፤ በዚያው ፡ አገር ፡ ፍርድ ቤት ፡ለፍርድ ይቀርባል ። ወታደሩ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አሳልፎ ፡ ባይሰጠው ፤ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ቁ. ፭፻፳፱ን ፡ በመጣስ ፡ በግፍ ፡ መግደል ፡ ወንጀል ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ይከሰሳል ።

ምሳሌ ፡— በውጭ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ባልደረባ ፡ ቁ ፡ ፫፻ ፩ን ፡ በመጣስ ፡ ያለፈቃድ ፡ ቀሬ ፡ ቢሆን ፤ ወንጀሉ ፡ በቁ. ፲፰ ፡ እንደተገለጸው ፡ ወታደራዊ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ስለሆነ ፡ አጥፊው ፡ በኢትዮጵያ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ስለሚሆን ፡ በጦር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይከሰሳል።

ለ ፡— የዋናው ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ ፡ ፲፮) ።

አንድ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ስር ፡ ሲሆን ፤ ተሠርቷል ፡ የተባለው ፡ ወንጀል ፡ በጣም ፡ የሚነካው ፡ ወይም ፡ የሚጐዳው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ንጉ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣንን ፡ የአነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ አይመለከተውም ። የአነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ፍችው ፡ ተሠራ ፡ የተባለው ፡ ወንጀል ፡ ኢትዮጵያን ፡ በጣም ፡ የማይነካ ፡ ወይም ፡ የማይጐዳ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

በኢትዮጵ ፣ ዋና ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ያለ ፣ ሰው ፣ በሠራው ፣ ወንጀል ፡ በውጭ አገር ፣ቢከሰስም ፡ ባይከሰስም ፣ በከሱም ፣ ነፃ ፣ ቢወጣ ፣ ወይም ፣ ቢፈረድበት ፣ ወደ ኢትዮጵያ ፣ ሲመለስ ፣ ወይም ፣ የውጭው ፡ አገር ፡ አሳልፎ፡ሲሰጠው ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ፣ ለፍርድ ፣ ይቀርባል ። በዋናው ፡ ሥልጣን ፣ ላይ ፡ ያለው ፡ ወሰን ፣ ወንጀለኛው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተፈርዶበት ፡ የተቀጣው ፡ ቅጣት ፡ ኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ከሚወሰንበት ፡ ቅጣት ፡ ላይ ፡ የሚቀነስለት ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፣ ነው ።

ሆኖም ፤ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፣ ሰው ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ፍርድ፣ ቤት ፡ ተከሰሶ ፣ የተፈረደበት ፣ በቁ ፣ ፲፪ ፣ እንደተደነገገው ፣ በኢትዮጵያ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ መንግሥት ፣ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ከሆነ ፡ ወንጀለኛው ፣ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ እንደማይሆንና ፤ ኢትዮጵያ ፣ የማይደፈር ፣ መብት ፡ ባላቸው ፣ የዲፕሎማቲክ ፡ መልእክተኞች ፣ ላይ ፡ ያላትን ፣ ሥልጣን ፡ ቁ. ፲፬ ፡ በመጠኑ ፣ እንደሚወሰነው ፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ።

ምሳሌ ፣— አንድ ፡ ኬንያዊ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ የአንዲትን ፡ ኬንያዊት ፣ ሕግ ፡ ያለፈቃዷ ፡ ቢገሥና ፤ ወደ ፡ ኬንያ፡ ተመልሶ ፣ ሔዶ ፣ እዚያ ፡ ተይዞና ፡ ተከስሶ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣ ፣ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተመለሰ ፡ በአገሩ ፡ ነፃ ፡ መውጣቱ ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጠር ፡ ቁ. ፩፻፶፱ ን ፡ ጥሶ ፣ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፣ ይከሰሳል ። ምክንያቱም ፣ ቁ. ፲፯ (፩) ፡ እንደሚያዘው ፡ ወንጀሉን፣ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በመፈጸሙ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ስለሚሆንና ፡ ቁ. ፣ ፲፯ (፪) ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፣ ወንጀል ፡ የሠሩ ፣ ሰዎች ፣ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከሰው ፡ መቀጣታቸው ፡ ወይም ፡ ነፃ ፡ መውጣታቸው ፡ ኢትዮጵያ ፣ ውስጥ፣ በዚያው ፡ ወንጀል ፡ ከመከሰስ ፣ አያድናቸውም ፣ ስለሚል ፣ ነው ።

ምሳሌ ፡ — እንደላይኛው ፣ ምሳሌ ፣ ዐይነት ፣ ሆኖ ፡ ወንጀል ፣ የፈጸመው ፣ ሰው ፣ በኬንያ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ተፈርዶበት ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፣ ከታሠረ ፣ በኋላ ፡ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስና ፡ የዐሥር፣ ዓመት ፣ እሥራት ፡ ቢፈረድበት ፤ ኬንያ ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፣ ወንጀል ፣ ምክንያት ፣ የታሠረው ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፣ እሥራት ፣ ተቆጥሮለት ፣ ኢትዮጵያ ፣ ውስጥ ፣ ከተፈረደበት ፣ ቅጣት ፣ ላይ ፡ ይቀነስለታል ።

ለ — <u>አነስተኛ ፡ ሥልጣን</u> ።

የሚከተሉትን ፡ ወንጀሎች ፡ የፈጸሙ ፡ ተከሳሾች ፣ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፡ ናቸው ፤ (፩) ፣ በውጭ፡ አገር፡ የኢንተርናሲዮናል ፣ ሕግን ፡ የሚጥስ ፣ ወይም ፣ የሕዝብን ፡ ጤንነትና ፡ ሞራል ፣ የሚጐዳ ፣ ወንጀል ፡ ሠርተዋል ፣

በመባል ፣ የተከሰሱ ፤ (፪) ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ አንዳንድ ፣ ወንጀሎችን ፣ በኢትዮጵያ፣ ዜጎች ፣ ላይ ፣ ፈጽመዋል ፣ በመባል ፣ የተከሰሱ ፤ (፫) ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ በማንኛ ውም ፣ ሰው ፣ ላይ ፣ ከባድ ፣ ወንጀል ፣ ፈጽመዋል ፣ በመባል ፣ የተከሰሱ ፤ እንዲ ሁም ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ አንዳንድ ፣ ወንጀሎችን ፣ ፈጽመዋል ፣ በመባል ፣ የተከሰሱ፣ ኢትዮጵያውያንና ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ የአገሩን ፣ ተራ ፣ ሕግ ፣ በመጣስ ፣ ወንጀል ፣ ሠርተው ፣ አምልጠው ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የተመለሱ ፣ ወታደሮች ። (ቀደም ፣ብሎ፤ በሁለተኛ ፣ ሀ—(፩) (ለ) ሥር ፣ ስለ ፣ ቁ. ፲፭ ፣ የተጻፈውን ፣ ሐተታ ፣ ተመልከት ።) አሁን ፣ በመጀመሪያ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ በምን ፣ አኳኋን ፣ በኢትዮጵያ ፣ አነስተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ እንደሚሆን፣ ከተረዳን፣ በኋላ ፣ በአነስተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ላይ ፣ ስላ ለው ፣ ወሰን ፣ እናትታለን ። ይኸም ፣ በዋና ፣ ሥልጣን ፣ ላይና ፣ በአነስተኛ ፣ ሥል ጣን ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ ወሰን ፣ ጉልሕ ፣ ልዩነት ፣ ያሳየናል ።

(፩) <u>በኢትዮጵያ ፣ አነስተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ስላሉ ፣ ሰዎች ፣</u>

(ሀ) በማኅበራዊ ፣ መብት ፣ ላይ ፣ ወይም ፣ በመላው ፣ ዓለም ፣ ጸጥታ ፣ ላይ ፣ በውጭ ፣ አገር ፣ ስለሚሠሩ ፣ ወንጀሎች ፣ (የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቁ. ፲፯) ።

በቁ. ፲፯ ፣ እንደተደነገገው ፤ በውጭ ፣ አገር ፣ የማይደፈር ፣ መብት ፣ ኖሮ አቸው ፣ በቁ. ፲፯ ፣ ውስጥ ፣ የተጠቀሱትን ፣ ወንጀሎች ፣ ከሠሩ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ (እነዚህ ፣ በቁ. ፲፬ ፣ መሠረት ፣ በኢትዮጵያ ፣ ዋና ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ናቸው ።) ከቁ. ፪፻፹፩ ፣ እስከ ፣ ፫፻፴፩ን ፣ በመጣስ ፣ ወንጀል ፣ ከሠሩ ፣ ወታደሮች ፣ (እነዚህ ፣ በቁ. ፲፭ (፪) መሠረት ፣ በኢትዮጵያ ፣ ዋና ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ናቸው) በስተቀር ፤ በዚህ ፣ ቁጥር ፣ የተጠቀሱትን ፣ ወንጀሎች ፣ የፈጸመ ፣ ማንኛውም ፣ ሰው ፣ በኢትዮ ጵያ ፣ አነስተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ነው ። በቁ. ፲፫ ፣ መሠረት ፣ በኢትዮጵያ ፣ ዋና ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ያሉትም ፣ ሰዎች ፣ በአነስተኛ ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ አይደሉም ።

በውጭ ፣ አገር ፣ ኢንተርናሲዮናል ፣ ሕግን ፣ የጣሰ ፣ ወይም ፣ በኢትዮጵያ ፣ ሕግ ፣ ኢንተርናሲዮናል፣ ፣ ወንጀል ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ የተወሰነውን ፣ ወንጀል ፣ የፈ ጸመ ፤ ወይም ፣ ኢትዮጵያ ፣ በተስማማችበት ፣ ኢንተርናሲዮናል ፣ ስምምነት ፣ ወን ጀል ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ የተወሰነውን ፣ የፈጸመ ፣ ማንኛውም ፣ ሰው ፣ በኢትዮጵያ ፣ አነተስኛ ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ ነው ። ኢንተርናሲዮናል ፣ ወንጀሎች ፣ ከቁ. ፪፻፹፩ ፣ እስከ ፣ ፪፻፺፭ ፣ የተዘረዘሩት ፣ ሲሆኑ ፤ ሌሎቹ ፣ ከላይ ፣ የተጠቀሱት ፣ ወንጀሎች ፣ ደግሞ ፣ በኅጋሪት ፣ ጋዜጣና ፣ ኢትዮጵያ ፣ አባል ፣ በሆነችባቸው ፣ ወንጀል ፣ ጠቀ ስ ፣ በሆኑ ፣ ስምምነቶች ፣ ውስጥ ፣ ይገኛሉ ።

ምሳሌ ፦— በአንድ ፣ አገር ፣ ውስጥ ፣ የእርስ ፣ በርስ ፣ ብጥብጥ ፣ ተነስቶ ፣ አን ደኛው ፣ ወገን ፣ የውጭ ፣ አገር ፣ ዜጎች ፣ የሆኑትን ፣ ሁሉ ፣ ይዞ ፣ ቢገ

ድላቸው ፡ ወንጀሉ ፡ በቁ. ፪፻፹፪ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ በሰላማዊ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ የጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ወንጀል ፡ በመሆኑና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወንጀሉ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግን ፡ የሚጥስ ፡ ነው ፡ ስለሚል ፡ ለወንጀሉ ፡ አላፊ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊከሰሱ ፡ ይቻላል ።

በተጨማሪም ፡ (በቁ. ፲፯) ፩ (ሀ) እንደተገለጸው ፡ የሕዝብን ፡ ጤንነት ፡ ወይም ፡ ሞራል ፡ የሚጎዱ ፡ ወንጀሎችን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የፈጸሙ ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ወንጀሎች ፡ በቁ. ፭፻፲ ፡ የተከለ ከለው ፡ (መርዛም ፡ ወይም ፡ የሚያፈዙ ፡ ነገሮችን ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፤ መሥራት ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ማድረግ ፤ በቁ. ፭፻፺፬ ፡ የተከለከለው ፡ (በሰዎች ፡ ለመነገድ) ፤ ከቁ. ፮፻፭ ፡ እስከ ፡ ፮፻፯ ፡ የተከለከለው ፡ (ሴቶችንና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱትን ፡ በማቃጠር ፤ በማከራየት ፡ ስለ ፡ መነገድ) እና ፡ ከቁ. ፮፻፰ ፡ እስከ ፡ ፮፻፲ ፡ የተከለ ከለው ፡ (ኀፍረተ ፡ ነገርን ፡ የሚያሳይ ፤ ወይም ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆ ኑትን ፡ ነገሮች ፡ አሳትሞ ፡ ስለ ፡ ማውጣት) ፡ ናቸው ።

ምሳሌ ፦ ከአንድ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንዲ ን ፡ ወጣት ፡ ሴት ፡ አንድት ሽረሙጥ ፡ ቢያቃጥራት ፡ ቁ. ፮፻፭ን ፡ ስለሚጥስ ፡ ሰውየው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊከሰስ ፡ ይቻላል።

(ለ) በውጭ ፡ አገር ፡ ስለሚሠሩ ፡ ሌሎች ፡ ወንጀሎች ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፫) ።

በቁ. ፲፫ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሚሆነው ፤ ያደረገው ፡ ጥፋት ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ በኢ ትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ማለት ፤ የሚያስቀጣ ፡ ሆኖ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ወንጀለኛውን ፡ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ በቂ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ወን ጀሉ ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ በቂ ፡ ክብደት ፡ እንዳለው ፡ ለማወቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ አሳልፎ ፡ ስለመስጠት ፡ የወጡትን ፡ ሕጎችና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያኗትን ፡ የተዋዋለች ባቸው ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠት ፡ ስምምነቶችን ፡ ተመልክቶ ፡ ይወስናል ። ድርጊቱ ፡ በማናቸውም ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ ወይም ፡ አሳልፎ ፡ መስጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ መሠ ረት ፡ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ በቁ. ፲፫ (፩) (ሀ) መሠረት ፡ አሳ ልፎ ፡ ለመስጠት ፡ ክብደቱ ፡ በቂ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ የድርጊቱ ፡ ፈጻሚ ፡ በኢትዮጵያ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ።

ቁጥር ፡ ፲፬ ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎችን ፡ ይዞ አል ። አንደኛው ፡ ሁኔታ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ በአ ንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ሲሠራ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በውጭ

አገር - ወንጀል ፡ ሲሠራ ፡ ነው ፡፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ወንጀል ፡ ሲፈጸምና ፡ ጥፋቱ ፡ ወንጀለኛውን ፡ አሳልፎ ፡ ለማሰጠት ፡ በቂ ፡ ክብደት ፡ ካለውና ፡ በኢትዮጵያም ፡ በሌላውም ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፤ የተደነገገው ፡ ቅጣት ፡ ልክ ፡ ሳይታይ ፤ ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንተሰኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ፡፡

ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ ሲያጋጥም ፡ ሊጠየቁ ፡ የሚገቡት ፡ ነገሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡፡ (፩ኛ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በአንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉን ፡ የሠራው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መሆኑ ፤ (፪ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግና ፡ በሌላውም ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ወይም ፡ የሚያስቀጣ ፡ መሆኑ ፤ (፫ኛ) ወንጀሉ ፡ በማንኛውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሌላ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ በተዋዋለችባቸው ፡ ስምምነቶች ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ አጥፊውን ፡ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ መሆኑ ፡፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በአሉታ ፡ ከተመለሱ ፡ ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ስለሠራው ፡ ወንጀል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊከሰስ ፡ ይቻላል ፡፡

ምሳሌ ፡- በውጭ ፡ አገር ፤ አንድ ፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ አንዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ እንዲጋባበት ፡ ወይም ፡ እንዲይዘው ፡ ቢያደርግና ፤ ጥፋቱ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ያልተከለከለ ፤ ማለት የማያስቀጣ ፡ ቢሆን ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ.፫፻፫ ፡ የተከለከለ ፡ ቢሆን ፤ በሌላው ፡ አገር ሕግ ፡ ባለመከልከሉ ፤ ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ሥር ፡ አይሆንም ፡፡ እንዲሁም ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመው ፡ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ሰው ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፤ ወንጀሉ ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ባለመከልከሉ ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የአነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አይሆንም

ምሳሌ ፡— «ሀ»እና ፡ «ለ»የተባሉ ፡ ሁለት ፡ አገሮች ፡ አሉ ፡ እንበል ፤«ከለ» ፡ ጋር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በንዝህላልነት ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ የሰው ፡ መግደል ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ አላት ፡ ከ«ሀ» ጋር ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ አሳልፎ ፡ የመስጠት ፡ ስምምነት ፡ የላትም ፡፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የለ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ በ«ሀ» አገር ፡ አንዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በንዝህላልነት ፡ ቢገድለው ፡ ይኸም ፡ በሀ ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ በቁ ፡ ፭፻፩ ፡ መሠረት ፡ ወንጀል ፡ ስለሆነ ፤ ገዳዩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ፡፡ ምክንያቱም ፤ (፩ኛ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ላይ ፡ በመሆኑ ፤ (፪ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያም ፡ "በሀም" አገር ፡ ሕግ መሠረት ፡ የሚያስቀጣ ፡ በመሆኑ ፡ እና ፡ (፫ኛ)ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡

ሕግ፡ መሠረት ፡ አሳልፎ ፡ ለማሰጠት ፡ በቂ ክባድነት ፡ያለው ፡ በመ ሆኑ ፡ነው ።ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን፡ ሥር፡ ባልሆን፡ አንድ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ቢሆንም ፡ ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንተሰኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ።

በቁ. ፲፰ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ ሲፈ ጽም ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ <u>በማንም ፡ ላይ ፡</u> የፈጸመ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፤ የሚከተሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲኖሩ ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ፤ (፩ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያም ፤ ወንጀሉ ፡ በተ ሠራበት ፡ አገርም ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፤ (፪ኛ) በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ወንጀሉ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ ሲሆን ፡ እና ፡ <u>(፫ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ በማያንስ ፡ ከባድ ፡ እሥራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።</u> ሁለተኛው ፡ ሁኔታ ፡ ከአንደኛው ፡ የሚለይባቸው ፡ ሁለት ፡ መንገዶች ፡ አሉ ፤ (፩ኛ) በሁለተኛው ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ላይ ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ፤ (፪ኛ) ደግሞ ፡ በሁለተኛው ፡ ሁኔታ ፡ ወንጀሉ ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ ባላነሰ ፡ ከባድ ፡ እሥራት ፡ ለማስቀጣት ፡ በቂ ፡ ክብደት ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

<u>ምሳሌ</u> ፡=በውጭ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ የዚያው ፡ አገር ፡ ተወላጅ፡ ሌላውን ፡ ተወ ላጅ፡ በግፍ ፡ አገዳደል ፡ ይገድለዋል ። ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፩፻፭፪ ፡ መሠረት ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ በዕድሜ ፡ ልክ ፡ እሥራት ፡ የሚያስቀጣ ፡ እና ፡ በተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግም ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ የግፍ ፡ አገዳደል ፡ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ ወንጀል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ አላት ፤ ገዳዩ ፡ አም ልጦ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ቢገባ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፤ (፩ኛ) ወንጀሉ፡በኢትዮጵያ ፡ በተፈጸ መበት ፡ አገርም ፡ ሕግ ፡ የሚያስቀጣ ፡ በመሆኑ ፡ (፪ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ በመሆኑና ፡ (፫ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ በሞት ፡ ወይም ፡ በዕድሜ ፡ ይፍታህ ፡ የሚያስ ቀጣ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

(ሐ) <u>በውጭ ፡ አገር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ ስለሚሠሩዋቸው ፡ ወንጀሎች ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፰ (፩)</u>።

አንድ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወታደር ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ ተራ ፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ ቢሠራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡

ሥር ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ አይሆንም ። ኢትዮ ጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢያዝም፡ ተከሶ ፡ ሊፈረድበት ፡ ይችላል ። ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ብቻ ፡ የሚሆነው ፤ በዋና ፡ ሥልጣንና ፡ በአነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የሚደረጉት ፡ ወሰኖች ፡ ስለሚለያዩ ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

(፪) <u>የአነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፫ (፫) እና ፡ ፳ ።</u>

በቁ. ፲፫ (፫) እንደተገለጸው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ቢሆን ፡ ወንጀሉ ፡ የተሠራበትን ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ያወቀው ፡ ከሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ለተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ከሚያዘው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ በላይ ፡ ሊቀጣው ፡ አይችልም ።

<u>ምሳሌ</u> ፦ በአንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በታወቀ ፡ አገር ፡ የአገሩ ፡ ተወላጅ ፡ አንድን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በግፍ ፡ ይገድለዋል ፤ ይኸ ፡ ወንጀል ፡ በኢትዮጵያም ፡ በተፈጸመበትም ፡ አገር ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ቁ. ፭፻፳፪ ፡ በሞት ፡ የሚያስቀጣ ፡ ሲሆን ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ግን የሞት ፡ ቅጣት ፡ ስለተሰረዘ ፡ ለዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀል ፡ የተወሰነው፡ ቅጣት ፡ የዕድሜ ፡ ልክ ፡ እሥራት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቁ. ፭፻፳፪ ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ቢያዝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ወንጀለኛ ፡ ላይ ፡ ከዕድሜ ፡ ልክ ፡ እሥራት ፡ በላይ ፡ ሊፈርድበት ፡ አይችልም ።

ቁ. ፳ ፡ የሚገልጸው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሰሰው ፡ ስለተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። አንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከስሶ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣ፡ ይኸ ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከመከሰሱ ፡ <u>አያድነውም</u> ። ነገር ፡ ግን ፡ ወንጀል ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ብቻ ፡ ከሆነ ፡ በውጭ፡ አገር ፡ በወንጀሉ ፡ ተከስሶ ፡ ነፃ ፡ ከወጣ ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንደማይከሰስ ፡ በቁ. ፳ (፩) ተደንግጓል ።

<u>ምሳሌ</u> ፦ በአንድ ፡ አገር ፡ ውጊያ ፡ ተደርጎ ፡ አንድ ፡ የአገሩ ፡ ተወላጅና ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ በውጊያው ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ሀብት ፡ ይዘርፋሉ ። ሁለቱም ፡ በዚያው ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ተይዘው ፡ ተከሰው ፡ ነፃ ፡ ይወጣሉ ። ሰላም ፡ ከተመሠረተ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ወደ ፡

ኢትዮጵያ ፡ ቢመለሱ ፤ የውጭው ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ በቁ. ፲፯ ፡ (፩) መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሲሆን ፤ ኢትዮጵያዊው ፡ ወታደር ፡ ደግሞ ፡ በቁ. ፲፮ (፪) ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ይሆናል ። ኢትዮጵያዊው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ በመሆኑ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በወንጀሉ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከስሶ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣ ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቁ. ፱፻፹፭ን ፡ በመጣሱ ፡ ሊከሰስ ፡ ይቻላል ። የውጭው ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ በወንጀሉ ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አይከሰስም ።

ወንጀለኛው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተፈርዶበት ፡ ቅጣቱ ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ሳይፈጸምበት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቢመለስ ፡ ቅጣቱ ፡ በይርጋ ፡ ካልታገደ ፡ በስተቀር ፡ ቁ. ፰ (፪) ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የቀረው ፡ ቅጣት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይፈጸምበታል ። ቁ. ፰ (፪) ወንጀለኛው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ሸሽቶ ፡ ቢያመልጥ ፡ በሄደበት ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ተከስሶ ፡ እንዲቀጣ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ እንዲጠይቁ ፡ ከሚያዘው ፡ ከቁ. ፲፪ (፫) ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በ፪ (ሀ) (፩) የተሰጡት ፡ ሐተታና ፡ ምሳሌዎች ፡ ለቁ. ፰ (፪) መግለጫና ፡ ምሳሌ ፡ ይሆናሉ ።

<u>(፫) አነስተኛ ፡ ሥልጣንን ፡ ስለሚጠቅሱ ፡ ሌላ ፡ ጉዳዮች ፡ (የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፲፱ (፩) (፪)</u>

ቁ. ፲፱ (፩) ተከሳሹን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ስለሚያደርጉት ፡ አንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ያወሳል ። በዚህ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ወንጀለኛው ፡ ተከሶ ፡ እንዲፈረድበት ፡ የተበዳዩ ፡ አቤቱታ ፡ መቅረብ ፡ ሲኖርበት ፡ አቤቱታው ባይቀርብም ፡ እንደቀረበ ፡ ይቈጠራል ። እንዲሁም ፡ ወንጀለኛው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባይኖርም ፡ እንዳለና ፡ በሠራው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ ወደዚህ ፡ አልፎ ፡ እንዳልተሰጠ ፡ ይቈጠራል ። አልፎ ፡ ተሰጥቶም ፡ እንደሆነ ፡ ይኸ ፡ የሆነበት ፡ በፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ እንደሆነ ፡ ይቈጠራል ። በመጨረሻም ፡ ጥፋተኛው ፡ ወንጀሉን ፡ በሠራበት ፡ አገር ፡ በሕግ ፡ አግባብ ፡ ምሕረት ፡ እንዳላገኘ ፡ ወንጀሉም ፡ በተሠራበት ፡ አገር ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በይርጋ ፡ እንዳልታገደ ፡ ይቈጠራል ። እነዚህንም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ማስረጃ ፡ በማቅረብ ፡ ሊመርታት ፡ ይቻላል ።

ቁ. ፲፱ (፪) ተከሳሹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አነስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ከሆነ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የክስ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያቀርበው ፡ በጉዳዩ ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስ ትር ፡ ጋር ፡ ከተስማማ ፡ በኋላ ፡ እንደሆነ ፡ ያዝዛል ።

ሐ — የፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ማጠቃለያ ።

(፩) ዋና ፡ ሥልጣን ።

(ሀ) የሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ።

(፩) በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ወን ጀል ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ (ቁ. ፲፩) ፡

(፪) በውጭ ፡ አገር ፡ ከቁ. ፪፻፵፰-፸፪ ፡ እና ፡ ከ፫፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ፫፻፺፪ ፡ የተከለከሉትን ፡ ወንጀሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ (ቁ. ፲፫)

(፫) በውጭ ፡ አገር ፡ በአገሩ ፡ ሕግና ፡ በኢትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ወንጀል ፡ የሠሩ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የማይደፈር ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መልእክተኞች ፡ (ቁ. ፲፬) ፡

(፬) ኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግን ፡ በመጣስ ፡ ወይም ፡ በቁ. ፪፻፺፩ ፡ እስከ ፡ ፫፻፵፩ ፡ የተከለከሉትን፡ ወታደራዊ ፡ ሕግ ፡ በመጣስ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀል ፡ የሠሩ ፡ ወታደሮች ፡ (ቁ. ፲፭ ሀ) ።

(ለ) የሚከተሉት ፡ ዋናውን ፡ ሥልጣን ፡ የሚመለከቱ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ናቸው ፤

(፩) አንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከስሶ ፡ ነፃ ፡ መውጣቱ ፡ አተ ሬው ፡ የተከሰሰው ፡ በቁ. ፲፪ ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጥያቄ ፡ አቅርቦ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንደገና ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከመከሰስ ፡ አያድነውም ፡ (ቁ. ፲፯ (፩) (፪) ፡)

(፪) ወንጀሉን ፡ በሠራበት ፡ አገር ፡ ተፈርዶበት ፡ ቅጣቱ ፡ በከፊል ፡ ወይም በሙሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ተከሳሽ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ላይ በውጭ ፡ አገር ፡ የተፈጸመበት ፡ ቅጣት ፡ ይቀንስለታል ፡ (ቁ. ፲፯ (፫)) ።

(፪) አነስተኛው ፡ ሥልጣን ።

(ሀ) የሚከተሉት ፡ ሰዎች በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አነስተኛ ፡ ሥል ጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ።

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ የአገሩን ፡ ተራ ፡ ሕግ ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ ሠር ተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡ ፡ (ጥገኝነትን ፡ የወሰዱ) የኢትዮጵያ ፡ ወታደሮች ፡ (ቁ. ፲፰ (፩)) ፡

(፪) በውጭ ፡ አገር ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግን ፡ በመጣስ ፡ (ቁ. ፪፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፪፻፺፭) ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ወንጀል ፡ የተባሉትን ፡ በመጣስ ፡ ወይም ፡ ቁ. ፭፻፲ ፡ ፭፻፳፯ ፡ ፯፻፲፯ ፡ ፯፻፷ ፡ እና ፡ ፯፻፲ን ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ (ቁ. ፲፯) ።

(፫) በውጭ ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ማንኛውም ፡ ዜጋ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የማይሆን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ (፩ኛ) ጥፋቱ ፡ በኢትዮጵያም ፡ በውጭው ፡ አገር ፡ ሕግም ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ ሲቈጠርና ፡ (፪ኛ) ወንጀሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ወንጀለኛውን ፡ አሳልፎ ፡ የሚያሰጥ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ (ቁ. ፲፰ (፪) ።

(ለ) <u>የሚከተሉት ፡ እነስተኛ ፡ ሥልጣንን ፡ የማመለከቱ ፡ መሠረተ ሐሳቦች ናቸው ።</u>

(፩) በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ የሚፈረደው ፡ ቅጣት ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ለወንጀሉ ፡ ከተወሰነው ፡ ከፍተኛ ቅጣት ፡ አይበልጥም ፡ (ቁ. ፲፱ (፫)) ፡-

(፪) ወንጀለኛው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ተከሰሶ ፡ ነፃ ፡ ከወጣ ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ ከተሰናበተ ፡ እንደገና፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ ፡ አይከሰስም ፡ (ቁ. ፳ (፩)) ፤

(፫) በውጭ ፡ አገር ፡ ተፈርዶበት ፡ ቅጣቱ ፡ በከፊል ፡ የተፈጸመበት ፡ ወንጀለኛ ፡ ቅጣቱ ፡ በይርጋ ፡ ካልታገደ ፡ በስተቀር ፡ ቀሪው፡ ቅጣት ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ፡ እንዲፈጸምበት፡ ሊፈረድበት፡ ይቻላል ፡ (ቁ. ፳ (፪) ።

<u>ሦስተኛ ፡ ሁለተኛ ፡ ጠባይ ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ።</u>

አንድ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ለመስማት ፡ የትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን እንዳለው ፡ ለመወሰን ፡ ሁለት ፡ ነገሮችን ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። እነዚህም ፡ (፩ኛ) ክሱ ፡ በየትኛው ፡ ደረጃ ፡ ማለት ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ እንደሚገባው ፡ ማወቅና ፡ (፪ኛ) ክሱ ፡ በየትኛው ፡ ሥፍራ ፡ ወይም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መሰማት ፡ እንደሚገባው ፡ ማወቅ ፡ ናቸው ። የመጀመሪያው ፡ የወንጀሉን ፡ ሰሚ ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁለተኛው፡ ደግሞ፡ የአጥቢያ፡ ሥልጣንን ፡ የሚመለከቱ ፡ ይባላሉ ።

ሀ- <u>ወንጀሉን ፡ ሰሚ ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁ. ፬ ፡ ፯ ፡ ፪፻፪ ፡ እና ፡ አንደኛ ፡ ሠንጠረዥ) ።</u>

የወንጀለኛ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁ. ፬ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚያዩዋቸውና ፡ የሚፈርዱዋቸው ፡ በዚሁ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡

በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ መሠረት ፡ እንደሚወሰኑ ፡ ያዝዛል ። የመጀመሪያውንም ፡ ሠንጠረዥ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ በማሳተም ፡ ሊለውጠው ፡ ይችላል ፤ እንደ ፡ ወንጀሉ ፡ ዐይነት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ተመድቧል ። ክሱን ፡ ለመስማት ፡ የትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ ለማወቅ ፡ ወንጀለኛው ፡ የተከሰሰበትን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ወይም ፡ ቁጥሮች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ላይ ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ።

ምሳሌ ፩- አንድ ፡ ቁ. ፮፻፵፩ን ፡ በመጣስ ፡ እምነት ፡ ያጐደለ ፡ ተከሳሽ ፡ በየትኛው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደረጃ ፡ መከሰስ ፡ እንዳለበት ፡ ለማወቅ ፡ ቢፈለግ ፡ የወንጀለኛው ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁ. ፮፻፵፩ን ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ይከሰሳል ፡ ስለሚል ፡ በዚሁ ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ።

የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ውስጥ ፡ የሌለ ፡ ቢሆን ፤ ለምሳሌ ፡ ተከሳሹ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ከታተመ ፡ በኋላ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የወጣ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ቢጥስ ፡ የትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ የሚወስነው ፡ ለጥፋቱ ፡ የተመደበውን ፡ ከፍተኛ ፡ የቅጣት ፡ ወሰን ፡ በመመልከት ፡ ነው ። ለጥፋቱ ፡ የተመደበው ፡ ቅጣት ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ቀላል ፡ እሥራት ፡ የማይበልጥ ፡ ከገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ቢሆን ፤ ክሱ ፡ የሚታየው ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ከፍተኛው ፡ ቅጣት ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ የማይበልጥ ፡ ከገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ያለመቀጮ ፡ ቢሆን ፤ በነገሩ ፡ ሥልጣን ፡ የሚኖረው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ከፍተኛው ፡ ቅጣት ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ በላይ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ጉዳዩ የሚሰማው ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ነው ።

ምሳሌ ፪— አንድ ፡ ሰው ፡ አዋጅ ፡ ጥሶ ፡ ቢከሰስና ፡ ለጥፋቱ ፡ የተመደበው ፡ ቅጣት ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ የማይበልጥ ፡ ቢሆን ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ ጥፋቱን ፡ የሚያቃልሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ስላሉ ፡ ወንጀሉ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ አያስቀጣም ፡ ተብሎ ፡ ቢታሰብ ፤ እንዲሁም ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወንጀለኛውን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ እሥራት ፡ ብቻ ፡ እንዲፈርድበት ፡ ለመጠየቅ ፡ ቢያቅድ ፤ ለወንጀሉ ፡ የተመደበው ፡ ቅጣት ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በላይና ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ እሥራት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ክሱ ፡ መሰማት ፡ የሚገባው ፡ በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይግባኝ ፡ ለማየት ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣን ፡ በቁ. ፻፹፮ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ እንደሆነ ፡ ቁ. ፯ ፡ ያገዛል ። ቁ. ፻፹፱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚጀመሩት ፡ ክሶች ፡ በስተቀር ፡ ለሌሎቹ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የይግባኝ ፡ መስማት ፡ አለ ። በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተጀመረ ፡ ክስ ፡ በይግባኝ ፡ ወደ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ፤ በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተጀመረ ፡ ክስ ፡ ደግሞ ፡ በይግባኝ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተጀመረ ፡ ክስ ፡ ግን ፡ በይግባኝ ፡ የሚሰማው ፡ አንዴ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። በቁ. ፻፹፫ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ደርሶ ፡ የይግባኝ ፡ መብቱን ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡ ጉዳዩ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ችሎት ፡ እንዲታይለት ፡ አቤቱታ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

ሉ· <u>የአጥቢያ ፡ ሥልጣን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁ. ፯ ፡ እና ፡ ፺፬-፻፯)</u> ።

የአጥቢያ ፡ ሥልጣን ፡ ክሱ ፡ <u>በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በየትኛው ፡ ሥፍራ ፡ መሰማት</u> ፡ እንደሚገባው ፡ ያመለክታል ። በወንጀሉ ፡ ዐይነት ፡ ክሱ ፡ መሰማት ፡ የሚገባው ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢሆን ፡ በየትኛው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ቤት ፡ መሰማት ፡ እንደሚገባው ፡ በአጥቢያ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ። ቁ. ፯ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በቁ. ፺፬-፻፯ ፡ መሠረት ፡ በተወሰነላቸው ፡ አጥቢያዎች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ ይደነግጋል ፤ ቁ. ፺፬ ፡ ደግሞ ፡ ማንኛውም ፡ ወንጀል ፡ እዚያው ፡ በተፈጸመበት ፡ ሥፍራ ፡ ወንጀሉን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ እንደሚገባው ፡ ይገልጻል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ ቢገባው ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላለ ፤ ክሱ ፡ የሚታየው ፡ ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በጐጃም ፡ ጠቅይ ፡ ግዛት ፡ ቢሆን ፡ ክሱ ፡ የሚታየው ፡ በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሚያስችለው ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንጂ ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አይደለም ።

ወንጀሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያበቁት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ አይፈጠርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወንጀሉ ፡ በሁለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጉዳዩ ፡ በየትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ እንደሚገባው ፡ ለመወሰን ፡

ብዙ ፡ ችግር ፡ ይፈጥራል ፤ ኾኖም ፡ ይኸ ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ በቁ. ፻ ፡ እስከ ፡ ፻፫ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

ቁ. ፻ ፡ እንደሚያዘው ፤ አንድ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተሠርቶ ፡ የወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ ያስከተለው ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ቢደርስ ፡ ወይም ፡ ቢፈጸም ፡ ክሱ ፡ ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ ሥፍራ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ውጤቱ ፡ በደረሰበት ፡ ቦታ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰማ ፡ ይቻላል ። ይኸም ፡ ማለት ፡ ሁለቱም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ የአጥቢያ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

<u>ምሳሌ</u> ፡— አንድ ፡ የበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሰው ፡ በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ለመግደል ፡ አስቦ ፡ የተመረዘ ፡ ፍራፍሬ ፡ ቢልክለትና ፤ ሰውየው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ቢሞት ፡ ጉዳዩ ፡ በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰማ ፡ ይቻላል ።

አንዳንድ ፡ ተግባሮች ፡ ከወንጀል ፡ ሥራዎች ፡ ጋር ፡ ባላቸው ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ ወንጀል ፡ ይሆናሉ ፤ ለምሳሌ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ በሐሰት ፡ እንዲመሰክር ፡ መገፋፋት ፡ የማታለል ፡ ወይም ፡ የማጭበርበር ፡ ወንጀል ፡ እንዲሠራ ፡ ስለሚያደርግ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፡ በቁ. ፬፻፵፬ ፡ የተከለከለና ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ። ቁ. ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ተግባር ፡ ከወንጀል ፡ ጋር ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ ራሱ ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን ፤ ይኸ ፡ ወንጀል ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመበት ፡ ሥፍራ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ መቻሉን ፡ ይደነግጋል ።

<u>ምሳሌ</u> ፡— በሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፤ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሚታይ ፡ ክስ ፡ በሐሰት ፡ እንዲመሰክር ፡ ያነሳሳውና ፡ በሐሰት ፡ እንዲመሰክር ፡ ያደርገዋል ፤ ይህ ፡ ወንጀል ፡ ቁ. ፬፻፵፬ን ፡ በመጣሱ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ በመሆኑና ፤ ሥራው ፡ የተሠራ ፡ በሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሲሆን ፡ ከሥራው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ኖሮት ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ የተሠራው ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በመሆኑ ፡ አጥፊው ፡ በሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊከሰስ ፡ ይቻላል ።

ቁ. ፻፪ (ሀ) ወንጀሉ ፡ የት ፡ እንደተፈጸመ ፡ ለማወቅ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ክሱ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ በሚገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰማ ፡ እንደሚቻል ፡ ይገልጻል ።

ምሳሌ ፡— አንድ ፡ ሰው ፡ ቁ. ፭፻፳፫ን ፡ በመጣስ፡ አንዲቱን ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ቢጠልፍና ፡ ቢወስዳት ፡ ወንጀሉ ፡ መሰማት ፡ የሚገባው ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጅቱ ፡ ከየት ፡ እንደተጠለፈች ፡ ባታስታውስና ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ አውራጃ ፡ ወይም ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ አውራጃ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ መሆኑ ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ቢሆን ፡ ወንጀለኛው ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ወይም ፡ በደብረ ፡ ብርሃን፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊከሰስ ፡ ይቻላል ።

እንዲሁም፡ ወንጀሉ፡ በከፊል ፡ ግማሹ፡ በአንድ፡ ሥፍራ ፡ ግማሹ፡ ደግሞ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ሲፈጸም ፡ (ቁ. ፺፱ ፡ (ለ)) ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በብዙ ፡ ሥፍዎች ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲፈጸም ፡ (ቁ. ፺፱ (ሐ)) ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦታዎች ፡ በተሠሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባሮች ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፡ (ቁ. ፺፱ (መ) ክሱ፡ በአካባቢው ፡ ካሉት ፡ ሥልጣን ፡ ካላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማንኛውም ፡ ሊሰማ፡ ይቻላል ።

ምሳሌ ፡— በሲዳሞና ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፡ በዱላ ፡ መትቶ ፡ ጥሎ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ጐትቶ ፡ ደብድቦ ፡ ቢገድለው ፤ ወንጀሉ ፡ በከፊል ፡ ሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በከፊል፡ ደግሞ ፡ ሸዋ ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት . ውስጥ ፡ ስለተሠራ ፡ በሲዳሞ ፡ ወይም ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰማ ፡ ይቻላል ።

ምሳሌ ፡— ተከሳሹ ፡ ያለአግባብ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ በሰንዳፋ ፡ አውራጃ ፡ ቢይዘውና ፡ ወደ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ በሸኖ ፡ አውራጃ ፡ ቢወስደው ፡ ቁ. ፭፻፺፭ን ፡ በመጣስ ፡ ወንጀል ፡ ስለሚሠራና ፡ የወንጀሉ ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ ሰውየውን ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ በግድ ፡ መያዙ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ስለ ቀጠለ ፡ ክሱ ፡ በሸኖ ፡ ወይም ፡ በሰንዳፋ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊታይ ፡ ይቻላል ።

ምሳሌ ፡— ተከሳሹ ፡ በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት፡ ሆኖ ፡ በሸዋ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ የያዘው ፡ ሐብት ፡ የእርሱ ፡ መሆኑን፡ በማስጽ ፡ የሐሰት ፡ ደብዳቤ ፡ ይጽፍለታል ፤ ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሄዶ ፡ በማጭበርበር ፡ ሀብቱን ፡ ይረከባል ። የሠራውም ፡ ወንጀል ፡ ቁ. ፮፻፺፮ ን ፡ ይጥሳል ። ወንጀሉ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ያሉት ፡ ሲሆን ፤ አንደኛው፡ የሐሰት ፡ ደብዳቤ፡ ሥጻፉ ፡ ሁለተኛው፡ ደግሞ፡ ሀብቱን ፡ በዚሁ ፡ በማጭበርበሪያ ፡ ደብዳቤ ፡ መሠረት ፡ መረከቡ ፡ ናቸው ። ደብዳቤው ፡ የተጻፈው ፡ በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሀብቱን ፡ የተረከበው ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ስለሆነ ፡ ክሱ ፡

በቤጌምድር ፣ ወይም ፡ በሸዋ፡ ጠቅላይ ፣ ግዛት፣ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፣ ቤት ፡ ሊሰማ ፡ ይቻላል ።

በቁ. ፻፫ ፡ መሠረት ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ ተከሳሹ ፣ በጉዞ ፣ ላይ ፣ ሳለ ቢሆን ፤ ወንጀለኛው ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ወንጀሉ ፣ የተፈጸመበት ፣ ነገር ፣ በጉዞው ፣ በሚያልፍበት ፣ ሥፍራ ፡ ውስጥ ፡ ክሱን ፡ ለመስ ማት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፣ ቤት ፡ ክሱ ፣ ይታያል ። ወንጀለኛው ፣ ወንጀለ የተፈጸመበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ (ሌላ ፡ ነገር) ንብረት ፡ በሥፍራው ፣ ካለፈ ፣ ወን ጀሉ ፡ ባይፈጸምም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በነገሩ ፡ ሊፈርድ ፣ ይቻ ላል ።

ምሳሌ ፡ በአንድ ፡ ከጉለሌ ፡ ወረዳ ፡ በአራዳና ፡ በቀበና ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ኡራኤል ፡ በሚሄድ፡ አውቶቡስ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፣ ሰው ፣ በጉለሌ፡ ወረዳ ፡ ተሳፍሮ ፡ ሌላውን ፡ መንገደኛ ፡ ደብድቦ ፣ በዚያው ፣ በጉ ለሌ ፡ ወረዳ ፡ ቢወርድና ፡ ተደብዳቢው ፡ አራዳ፣ ወረዳ ፡ ቢወርድ ፡ ወንጀሉ ፡ የተፈጸመበት ፡ ሰው ፡ በጉዞው ፡ ጊዜ ፣ በአራዳ ፡ ወረዳ ፡ ውስጥ ፡ ስላለ ፣ አጥፊው ፡ ቁጥር፡ ፭፻፶፬ ፡ ጥሶ ፡ በሠራው፡ ወንጀል ፡ በጉለሌ ፡ ወይም ፡ በአራዳ ፣ ወረዳ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ ሊከሰስ ፡ ይቻላል ።

ምሳሌ ፡— በደብረ ፣ ሲና ፡ አውራጃ ፣ በመኪና ፡ የተጫነ ፣ የንግድ ፣ ዕቃ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አቋርጦ ፡ ሸዋ ፡ ሲደርስ ፣ ቢሠረቅ ፣ ዕቃው ፡ በሦ ስቱም ፡ አውራጃዎች ፡ ውስጥ ፡ ስላለፈ ፡ ወንጀለኛው ፣ ከሦስቱ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በማንኛውም ፡ ሊከሰስ ፣ ይቻላል ።

ቁ. ፻፬ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፣ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ አኤሮፕላን ፣ ውስጥ ፣ ቢፈ ጸም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ይቈጠራል ፡ ይላል ። ይሀ ፡ ቁጥር ፡ ክሱ ፡ በየትኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት፡ እንደሚገባው ፣ አይገል ጽም ፡ ሆኖም ፡ ቁ. ፻፯ ፣ ከቁ. ፻ ፡ እስከ ፡ ፻፬ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፣ ክሱ ፡ በየትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ እንዳለበት ፡ ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ሊወስን ፡ እንደ ሚችልና ፡ ክሱ ፡ ሲቀርብ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንደሚኖረው ፡ ይገልጻል ። ይኸም ፣ አንድ ፡ ክስ ፡ በብዙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊታይ ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፡ በየትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ መታየት ፡ እንደሚገባው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ይወስናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምሳሌ ፡—አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ አኤሮፕላን ፣ በሱዳን ፡ ላይ ፡ ሲበርና፡ በአውራጃ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፣ የሚገባው ፡ ወን ጀል ፡ በአኤሮፕላኑ ፡ ውስጥ ፡ ቢፈጸም ፡ ጉዳዩ ፡ ዐቃቤ ፣ ሕግ ፡ በሚ

መርጠው ፡ በማነኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊታይ ፡ ይቻላል ።

ቁ. ፺፮ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ካንድ ፡ ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ካለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ሊዛወር ፡ እንደሚችል ፡ ይገለጻል ። ባለጉዳዩ ፡ ጉዳዩ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይለት ፡ ሲፈልግ ፡ ማመልከቻውን ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፤ ማመልከቻውን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተቀበለው ፡ ጉዳዩ ፡ ክሱን ፡ ለማየት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ወይም ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይዛወራል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጉዳዩ ፡ በአንደኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ መሠረት ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚታይ ፡ ሲሆን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ራሱ ፡ ሊሰማው ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያዛውረው ፡ ይችላል ፤ ግን ፡ ወደ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያስተላልፈው ፡ አይችልም ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻውን ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ላለመቀበል ፡ በሚያደርገው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

በቁ. ፺፮ ፡ መሠረት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ከአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደሌላ ፡ ለማስተላለፍ ፡ የ ቀረበለትን ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቀበልበት ፡ አራት ፡ ሁኔታዎች ፡ አሉ ፤ እነዚህም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤ (፩ኛ) ዝቅተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ አድልዎ ፡ የሌለበት ፡ ትክክለኛ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ እንደማይችል ፡ ግልጽ ፡ ሲሆን ፡ (፪ኛ) ክሱ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪና ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፤ ለውሳኔ ፡ የሚያዳግት ፡ የሕግ ፡ ጉዳይ ፡ ሲኖርበት ፡ (፫ኛ) የክሱ ፡ መዛወር ፡ ለባለጉዳዮችና ፡ ለምስክሮች ፡ በቦታው ፡ ቅርበትም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ምቹ ፡ ወይም ፡ ተፈላጊ ፡ ሲሆንና ፡ (፬ኛ) ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ የሚገኘው ፡ በክሱ ፡ መዛወር ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የክሱ ፡ መዛወር ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የተፈቀደ ፡ ሲሆን ።

<u>ምሳሌ</u> ፦—በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ቤት ፡ ለኑሮዋ ፡ ያጠራቀመችውን ፡ ሐብት ፡ ሠርቀሃል ፡ ተብሎ ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ ሥርቆቱ ፡ በተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ነበርኩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የአካባቢው ፡ ሕዝብ ፡ በቤትየዋ ፡ መዘረፍ ፡ በጣም ፡ ስለተናደደና ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ እንደነበርኩ ፡ የሚያውቁልኝ ፡ ምስክሮች ፡ የማስፈራሪያ ፡ መልእክት ፡ ስለደረሳቸው ፡ እዚህ ፡ ሊመሰክሩልኝ ፡ አይችሉምና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይዛወርልኝ ፡ ሲል ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢያመለክት ፣ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምክንያቱን ፡ ከተቀበለው ፡ ነገሩን ፡ ራሱ ፡ ሊሰማው ፡ ወይም ፡ ወደሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያዛውርለት ፡ ይችላል ።

ምሳሌ ፡—አንድ ፡ ሰው ፡ ቁ. ፯፻፲፫ን ፡ በመጣስ ፡ "የግብረ ፡ ሥጋን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዝንባሌ ፡ ከመጠኑ ፡ በላይ ፡ የሚያነሳሱ" ጽሑፎችን ፡ አሳይቷል ፡ ተብሎ ፡ ቢከሰስ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ተከሳሹ ፡ ለሕዝብ ፡ ያሳየሁት ፡ ጽሑፍ ፡ በቁ. ፯፻፲፫ ፡ አተረጓጐም ፡ "የግብረ ፡ ሥጋን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዝንባሌ ፡ ከመጠኑ ፡ በላይ ፡ አሳነሳሳም" ብሎ ፡ ቢከራከር ፡ "የግብረ ፡ ሥጋን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዝንባሌ ፡ ከመጠኑ ፡ በላይ ፡ ማነሳሳት" የሚለው ፡ ከባድ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ ለመፍጠር ፡ ስለሚችል ፡ ተከሳሹ ፡ ቢያመለክት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ ራሱ ፡ ለማየት ፡ ይወስን ፡ ይሆናል ።

ምሳሌ ፡—አንድ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ የተጫነ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ የያዘ ፡ መኪና ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አውራጃ ፡ አልፎ ፡ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ እንደቆመ ፡ ዕቃው ፡ ተሠርቆ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አውራጃ ፡ እንዲታይ ፡ ቢወስንና ፡ ተከሳሹና ፡ ምስክሮቹ ፡ የሚኖሩት ፡ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ በመሆኑ ፡ ክሱ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ እንዲዛወር ፡ ማመልከቻ ፡ ቢቀርብ ፡ መዛወሩ ፡ ለተከሳሹና ፡ ለምስክሮች ፡ ምቹ ፡ ስለሚሆን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዛወሩን ፡ ሊያዝዝ ፡ ይችላል ።

ቁ. ፲፮ (መ) በሌላ ፡ ምክንያት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ወይም በሌላ ፡ ቁጥር ፡ ክሱ ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ ለማዛወር ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ይገልጻል ። በመጨረሻም ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ እንዲሻር ፡ ሲፈልግ ፡ ስለመሰየም ፡ አቤቱታ ፡ የሚቀርበው ፡ መጀመሪያ ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁ· ፲፭) ።

ሖ· <u>የፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ማጠቃለያ ።</u>

፩. አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ወንጀል ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አንደኛው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ተወስኗል ። ይኸውም ፡ ሰንጠረዥ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ እንደሚገባው ፡ ይወስናል ፡ (ቁ. ፱) ።

፪. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ቦታ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ማለት ፡ ክሱ ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ የሚገባው ፡ ቢሆን ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሰማት ፡ አለበት ፡ (ቁ. ፲፱) ።

፫· የሚከተሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲያጋጥሙ ፡ ከአንድ ፡ የበለጡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች፡ በታዊ ፡ (ሥፍራዊ ፡ የአጥቢያ) ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ። በዚ ህም ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቢ ፡ ሕጉ ፡ በራሱ ፡ ውሳኔ ፡ ወደ ፡ መረጠው ፡ ሥልጣን ፡ ወደአለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ ይመራዋል ፡ (ቁ. ፲፯) ።

(ሀ) የወንጀሉ ፡ ድርጊት ፡ ሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ተፈጽሞ ፡ ውጤቱ ፡ ደግሞ ፡ የተ ለየ ፡ ሥፍራ ፡ የደረሰ ፡ እንደሆነና ፡ እነዚህ ፡ ሥፍራዎች ፡ በአንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ካልሆኑ ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ድርጊቱ፡ በተፈጸመበት ፡ ሥፍራ ፡ በሚገኝ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ውጤቱ ፡ በደረሰበት ፡ ሥፍራ ፡ ባለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይቻላል ፡ (ቁ. ፲) ።

(ለ) አንድ ፡ ድርጊት ፡ ከሌላ ፡ ወንጀል ፡ ጋር ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ምክን ያት ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ ሆኖ ፡ ከተቆጠረ ፤ የዚህ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ ሁለቱ ወንጀሎች ፡ በተፈጸሙበት ፡ ቦታ ፡ ላሉት ፡ ሥልጣን ፡ ላላቸው ፡ ፍርድ ቤቶች ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ዘንድ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፡ (ቁ. ፲፩) ።

(ሐ) ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ በየትኛው ፡ ሥፍራ ፡ ወንጀሉ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፡ ወንጀሉ ፡ በከፊል ፡ አንድ ፡ ሥፍራ ፡ በከፊል ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፡ ወን ጀሉ ፡ ከአንድ ፡ በበለጡ ፡ ሥፍራዎች ፡ መፈጸሙ ፡ ሲቀጥልና ፡ ወን ጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራዎች፡ የተፈጸሙትን ፡ አያሌ ፡ የወንጀል ፡ ተግባሮችን ፡ በመሥራት ፡ ሲሆን ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ሥል ጣን ፡ ባለው ፡ ከነዚህ ፡ ሥፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ዘንድ ፡ ለሚገኘው፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፡ (ቁ. ፲፪) ።

(መ) ወንጀሉ ፡ የተፈጸመው ፡ ወንጀለኛው፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ የሆነ ፡ እን ደሆነ ፤ ወንጀለኛው ፡ ወይም ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመበት ፡ ነገር ፡ በጉዞው ፡ በሚያልፍበት ፡ ሥፍራ ፡ ለሚገኘው ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፡ (ቁ. ፲፫) ።

(ሠ) በኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ አኤሮፕላን ፡ ላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ የተፈጸመ ፡ ወንጀል ፡ በማንኛውም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰማ ፡ ይችላል ። ይኸም ፡ ገቢ ፡ ነው ፡ (ቁ. ፲፬) ።

(ረ) ክሱንም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሥፍራ ፡ የማዛወር ፡ ትእዛዝ ፡ በሕግ ፡ ቁ. ፺፲ መሠረት ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

CRIMINAL JURISDICTION IN ETHIOPIA: A COMMENTARY *

by Robert Allen Sedler, Faculty of Law, Haile Sellassie I University

(Title I, Chapter II, Section 2 of the Penal Code and Book I, Chapter 1 and Book IV, Chapter 2 of the Criminal Procedure Code)

I. Introduction

II. The First Element: Persons Subject to the Penal Code

A. Principal Jurisdiction

1. Persons subject to Ethiopia's principal jurisdiction

a. Offences committed in Ethiopia

b. Offences committed in a foreign country against Ethiopia

c. Offences committed in a foreign country by Ethiopian officials enjoying immunity and by members of the Ethiopian Armed Forces

2. Limitations upon the exercise of principal jurisdiction

B. Subsidiary Jurisdiction

1. Persons subject to Ethiopia's subsidiary jurisdiction

a. Offences committed in a foreign country against international law or universal order

b. Other offences commited in a foreign country

c. Offences committed in a foreign country by members of the Armed Forces

2. Limitations upon the exercise of subsidiary jurisdiction

C. Summary

1. Principal jurisdiction

2. Subsidiary jurisdiction

III. The Second Element: Jurisdiction of Courts

A. Jurisdiction over Offences

B. Local Jurisdiction

C. Summary

I. Introduction

There are two elements involved in the exercise of criminal jurisdiction by the Ethiopian courts. The first element deals with persons subject to the Penal Code of Ethiopia. All persons subject to the Penal Code of Ethiopia are subject to the jurisdiction of the Ethiopian courts, and they may be tried here for violations of the Penal Code. Title I, Chapter II, Section 2 (Arts.

* The purpose of this commentary is to provide explanatory treatment of this area of law. It is not intended to be a detailed analysis of all the legal problems that may arise and it does not contain a discussion of cases and secondary material.

11-22) of the Penal Code covers the question of what persons are subject to the Penal Code, and hence to the jurisdiction of the Ethiopian courts.

The second element deals with the jurisdiction of courts. It must be determined which court in Ethiopia has jurisdiction to hear the case and in which area of Ethiopia the case must be tried, *e.g.*, should the case be tried before the High Court sitting in Addis Ababa or the Awradja Court of Debre Berhan Awradja or the Woreda Court of Guellele Woreda. These questions are covered by Book I, Chapter 1 and Book IV, Chapter 2 of the Criminal Procedure Code. (Arts. 4, 6, 7 and 99-107).

II. The First Element: Persons Subject to the Penal Code

Whether or not a person is subject to the Penal Code depends on (1) the place where the offence was committed, (2) the nationality of the accused and (3) the kind of offence that has been committed. In certain circumstances an accused is said to be subject to Ethiopia's *principal jurisdiction*; in other circumstances, although he is not subject to Ethiopia's principal jurisdiction, he is said to be subject to Ethiopia's *subsidiary jurisdiction*. The conditions for the exercise of jurisdiction differ depending on whether the accused is subject to Ethiopia's principal or subsidiary jurisdiction. Most significantly, where a person is subject to Ethiopia's principal jurisdiction, discharge or acquittal in a foreign country does not prevent a prosecution for the same offence in Ethiopia; it does so if he is only subject to Ethiopia's subsidiary jurisdiction.

A. *Principal Jurisdiction* (Penal Code, Arts. 11-16)

Principal jurisdiction exists as to an accused who is (1) charged with the commission of an offence in Ethiopia, (2) charged with the commission of certain offences against Ethiopia in a foreign country, (3) charged with the commission of an offence in a foreign country where he possesses immunity from prosecution by virtue of his status as an Ethiopian official, (4) charged with the commission of certain offences in a foreign country while a member of the Ethiopian Armed Forces. First we will consider when an accused is subject to Ethiopia's principal jurisdiction; then we will consider the conditions for the exercise of principal jurisdiction.

1. *Persons subject to Ethiopia's principal jurisdiction*

a. *Offences committed in Ethiopia* (Penal Code, Arts. 11, 12)

Article 11 (1) provides that the Code is applicable to *any person* who commits *any offence* specified in the Code on Ethiopian territory. Territory consists of land, sea and air.

EXAMPLE: A national of Kenya, while visiting Ethiopia, allegedly rapes another Kenyan in violation of Article 589. Since the alleged offence was committed on the territory of Ethiopia, the accused is subject to the Code and may be tried in the Ethiopian courts for a violation of Article 589.

EXAMPLE: While a Sudan Airways flight is passing over Ethiopia, a Sudanese national aboard the flight allegedly assaults a fellow passenger, who is also Sudanese. Since Ethiopian air space is Ethiopian territory, the alleged offence was committed on Ethiopian territory, which subjects the accused to the Penal Code, and he may be tried in the Ethiopian courts for a violation of Article 544.

Certain persons such as diplomatic officials are immune from criminal prosecution in the country to which they are accredited under principles of public international law. Such immunity is recognized under Article 11 (2), and a person enjoying this immunity is *not* subject to the Penal Code, and thus, not subject to the jurisdiction of the Ethiopian courts.

EXAMPLE: The ambassador of a country with whom Ethiopia has diplomatic relations recklessly drives his automobile in Addis Ababa, killing an Ethiopian. Such conduct would constitute homicide by negligence under Article 526. Since under principles of public international law, ambassadors are not subject to the penal law of the country to which they are accredited, the ambassador may not be tried in the Ethiopian courts for a violation of Article 526.

A person who has committed an offence in Ethiopia may have successfully escaped and taken refuge in a foreign country. In such a case the Ethiopian authorities are directed under Article 11 (3) to request his extradition so that he may be tried under Ethiopian law. Extradition is the process by which a person who has committed an offence in one country and has taken refuge in another is returned to the country where the offence was committed in order that he may stand trial there. Unfortunately, Ethiopia does not have extradition treaties with very many countries, and most countries will not permit anyone to be extradited unless there is a treaty with the country requesting extradition. That is the law in Ethiopia; no one may be extradited from Ethiopia except in accordance with international agreement. Rev. Const., Art. 50. See also Penal Code, Art. 21. In light of the absence of extradition treaties, Article 11 (3) is not likely to be very effective.

እነዚህም ፣ ምርጥ ፣ ቃላት ፣ በበኩሉ ፣ የሕግ ፣ ቅንጅትን ፣ ለመገንባት ፣ የሚ ያስችል ፣ የዕውቀት ፣ ሀብት ፣ መገኛ ፣ የሆነን ፣ ሙያን ፣ ለማደርጀት ፣ የሥራው ፣ ረዳቶች ፣ (ደጋፊዎች) ለመሆን ፣ ያለንን ፣ ዓላማ ፣ በግልጽ ፣ ያሳያሉ ። ከአርስቶ ትል ፣ ጊዜ ፣ ጀምሮ ፣ እስከአለንበት ፣ ዘመን ፣ ድረስ ፣ መልካም ፣ ገዥዎችና ፣ ፈላ ስፎች ፣ ሊደረስበት ፣ የሚቻል ፣ ምኞትን ፣ ለማስገኘት ፣ ለሰዎች ፣ እምነትን ፣ ለመ ስጠትና ፣ ነፃነታቸውንም ፣ ለመጠበቅ ፣ ተብሎ ፣ በተዘጋጀ፣ ሕግ ፣ ሥር፣ የሚተዳ ደሩ ፣ ካልሆኑ፣ በቀር ፤ ሰዎች፣ በነፃነትና፣ በደስታ፣ ሊኖሩ፣ ያለመቻላቸውን፣ ደጋግ መው ፣ (አጉልተው) ገልጸዋል ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ የሕግን ፣ ተግባርና ፣ አገባብ ፣ እን ደዚሁም ፣ የአፈጻጸሙን ፣ ዘዴና ፣ የተወሳሰበ ፣ መሆኑን ፣ በሚያውቁ ፣ ሰዎች ፣ የተ ዘጋጀና ፣ የሚካሄድ ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ በየትኛውም ፣ ዘመናዊ ፣ አገር ፣ ቢሆን ፣ ሕግ ፣ የተባሉትን ፣ ዓላማዎች ፣ ሊያገለግል ፣ አይችልም ። ለሕዝብ ፣ አገልግሎትና ፣ ለኢ ኮኖሚ ፣ ልማት ፣ ለማሕበራዊና ፣ የፖለቲካ ፣ ለውጥ ፣ ለሚያመጣ ፣ ፕሮግራም ፣ ለመፈጸም ፣ የሚያስችልና ፣ ዘወትርም ፣ ወደፊት ፣ ለሚራመድ ፣ የሕግ ፣ እድገት ፣ የተሰዋ ፣ ከፍተኛ ፣ ሙያ ፣ ከሌለ ፣ በቀር ፣ በየትኛውም ፣ አገር ፣ ሕግ ፣ መከበርን ፣ ሊዋጅ ፣ (ሊግርክ) አይችልም ።

ስለዚህ ፣ በቀዳማዊ ፣ ኃይለ ፣ ሥላሴ ፣ ዩኒቨርስቲ ፣ የሚሰጠው ፣ የሕግ ፣ ትም ህርት ፣ ትክክለኛ ፣ ዓላማው ፣ አገሪቱን ፣ የገጠሙዋትን ፣ ችግሮችና ፣ እነዚህንም ፣ ችግሮች ፣ ለማስወገድ ፣ የተወሰዱትን ፣ እርምጃዎችና ፣ የሕግ ፣ ሙያም ፣ በዚህ ፣ ተግባር ፣ ረገድ ፣ ያለውን ፣ አገባብ ፣ ማስጠናት ፣ ነው ። እነዚህም ፣ የመጀመሪያ ዎቹ ፣ ዓመታት ፣ በተለየ ፣ ሁኔታ ፣ በዚህ ፣ ዩኒቨርስቲ ፣ ውስጥ ፣ ለመሥራት ፣ ለታ ደልነው ፣ ሁሉ ፣ የአእምሮ ፣ አድናቆትን ፣ ሊያተርፍልን ፣ መቻሉን ፣ ከዚህ ፣ ላይ ፣ መግለጽ ፣ ያለበታው ፣ እንደተሰነዘረ ፣ እንደማይቆጠርብኝ ፣ ባለተስፋ ፣ ነኝ ።

በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ እድገት ።

(፩) የኅሚስ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ መስፋፋት ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ ተጀመረ ። በዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈለገው ፡ ችሎታ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ መገኘት ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መምህራን ፡ በቃል ፡ ለሚጠይቁት ፡ ጥያቄ ፡ ተገቢ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ መቻልና ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ችሎታን ፡ የሚመሰክር ፡ መጠነኛ ፡ ፈተናን ፡ ማለፍና ፡ በተጨማሪም ፡ በሕግ ፣ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ መሰል ፡ በሆኑ ፡ የሥራ ፡ ስምሪቶች ፡ የሙያ ፡ ልምምድ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ያላት ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ነው ። ትምህርቱም ፡ ለመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለጠበቆች ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪዎች ፡ ለዳኞችና ፡ ለፓርላማ ፡ አባሎች ፡ ተብሎ ፡ የታቀደ ፡ ነው ።

በመስከረም ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. በዲፕሎማ ፡ ክፍል ፡ ዘጠና ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ተቀበልን ፤ በሰኔ ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. አምሳ ፡ አምስት ፡ ያህል ፡ ለዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ፈተና ፡ ተቀመጡ ፤ ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ወደፊት ፡ ቁጥራቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ይሄዳ ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ የዲፕሎማ ፡ ትምህርት ፡ ለሚጠይቀው ፡ እድካሚ ፡ ሥራ ፡ ችሎታና ፡ መንፈስ ፡ ጠንካራነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚገበዩት ፡ ትምህርት ፡ ለኑሮሩና ፡ ለኢትዮጵያም ፡ የሚጠቅም ፡ እንደሚሆን ፡ እናምናለን ።

ከነዚህም ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ በመሥራታቸው ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ እንደ ተሰማቸው ፡ መምህራኑ ፡ ገልጸዋል ። ወደፊትም ፡ በዚህ ፡ ፕሮግራም ፡ የበለጠ ፡ የሥራ ፡ ትጋት ፡ እንደሚታይ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ከተማሪዎቹም ፡ የሚበዙት ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ከመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ ብዙዎቹ ፡ በቀጥታ ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተመደቡ ፡ ናቸው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመስከረም ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ለምስክር ፡ ወረቀት ፡ ፕሮግራም ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎች ፡ ተቀብለናል ። በዚህም ፡ ፕሮግራም ፡ በሳምንት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕጎችና ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ የመሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል ።

በዚህ ፡ ክፍልም ፡ ከሚገኙት ፡ የሚበዙት ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎች ፤ የመንግሥት ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ዳኞችና ፡ ጠበቆች ፡ ናቸው ። እንደዚሁም ፡ በኅዳር ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ከተመረቁት ፡ ቁጥራቸው ፡ ከመቶ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በተጨማሪም ፡ በሰኔ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ሰባ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተቀብለዋል ። በአሥመራ ፡ በሚገኙ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ለማስተማር ፡ ልዩ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ በዚያ ፡ ጀምረናል ። እነዚህን ፡ ትምህርቶች ፡ የሚያስተምሩት ፡ ከሠራተኞቻችን ፡ አንዱ ፡ የሆኑት ፡ ሚስተር ፡ ኖርማን ፡ ሚትዝ

ገር ፡ ናቸው ። የተማሪዎቹም ፡ ብዛት ፡ ከስድሳ ፡ ሲደርስ ፤ ጻዎች ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ምችና ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትም ፡ ይገኙበታል ። ረዳት ፡ ዲኑና፡እኔም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አሥመራ ፡ እየሄድን ፡ ጎብኝተናል ። በኛ ፡ አስተያየት ፡ እቅዱ ፡ የተቃና ፡ ሆኖአል ። በጠቅላላውም ፡ ፈተናው ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ አሳይቶናል ። ተማሪዎቹም ፡ በትጋት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ይከታተላሉ ።

ኦልቁንም ፡ ተማሪዎቹ ፡ ለሌላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሕዝብ ፡ መብትን ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ (ሪፑብሊክ ፡ ሎው) ትምህርት ፡ ተሰጥቶአቸው ፡ በሕግ ፡ የዩኒቨርስቲውን ፡ የሕግ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲቀበሉ ፡ ይደረግላቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠይቀዋል ።

በተጨማሪም ፡ አምሳ ፡ ያህል ፡ ሌሎች ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ አዲስ ፡ ክፍል ፡ እንዲከፈትላቸው ፡ ጠይቀዋል ። ይህንንም ፡ ጥያቄ ፡ ለሟሟላት ፡ በአሥመራ፡ ያለንን ፡ የቅጥያ ፡ ፕሮግራም ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለመቀጠል ፡ ወስነናል ። አቶ ፡ ዐማኑኤል ፡ ዐምደ ፡ ሚካኤልና ፡ አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፍትሕ ፡ ዐወቀ ፡ ምስጋናችን ፡ ይድረሳቸውና ፡ ባሳዩት ፡ በጐ ፡ ፈቃድ ፡ በአሁኑ ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ተጨማሪ ፡ መምህራን ፡ ለማግኘት ፡ በመቻሉ ፡ ያሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ትምህርታቸውን ፡ ከመቀጠላቸውም ፡ በላይ ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎችን ፡ በተጨማሪ ፡ ለመቀበል ፡ ተችሎአል ። በአሥመራ፡ ከተማ ፡ በሚቋቋመው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የሚሆን ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ በመጠኑ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ መሰብሰብ ፡ ጀምረናል ። የገንዘብ ፡ ዐቅማችንም ፡ ሲፈቅድልን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መጻሕፍት ፡ በሟማላት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ወደ ፊት ፡ ለማደርጀት ፡ እንደምንችል ፡ ባለተስፋ ፡ ነን ።

በዚሁ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በአማርኛ ፡ ለዲፕሎማ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ የሚቻልበትን ፡ ሁኔታ ፡ አጥንተናል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተመድበው ፡ ለሚገኙ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዩኒቨርስቲ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ለማስተማር ፡ ከተፈለገ ፡ ይህ ፡ እርምጃ ፡ በአስቸኳይ ፡ ሊወሰድ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

የገጠመን ፡ ችግር ፡ በአማርኛ ፡ ማስተማሪያ ፡ መጻሕፍትና ፡ ሌላም ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ አለማግኘት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጥያቄው ፡ ለከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ በቂ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ለማስተርጐም ፡ እንችላለን ፡ ወይ ፡ የማለት ፡ ነው ። ልንሞክር ፡ ወስነናል ።

ዓላማውም ፡ በእርግጥ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ስለዚህ፡ አሁኑኑ፡ መጀመር ፡ ይኖርብናል ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ከመስከረም ፡ ፲፱፻፷፫፡ ዓ. ም. ጀምሮ፡ ለሦስት፡ ዓመታት ፡ ማታ ፡ ማታ ፤ በእንግሊዝ ፡ የዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ ማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በመተርጐምና ፡ በዚሁ ፡ ውጤት ፡ በመጠቀም ፡ በዲፕሎማ ፡

ደረጃ ፡ በአማርኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ ይጀምራል ። በእንግሊዝኛና ፡ በአማርኛ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ በሚያስተምሩት ፡ መምህራን ፡ መካከል ፡ የቅርብ ፡ መተባበር ፡ ይደረጋል ። አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ ሥርዐት ፡ ትምህርት ፡ በሁለቱም ፡ ቋንቋ ፡ ለማስፈጸምና ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ ፈተና ፡ ለመስጠትና ፡ የፈተናውም ፡ ውጤት ፡ አመዳደብ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦበታል ። ይኸም ፡ ሁሉ ፡ ሙከራ ፡ ነው ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሊደከሙበት ፡ የሚገባ ፡ ሙከራ ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ የግሚስ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራሞች ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የሰውን ፡ ሥራ ፡ ጉልበት ፡ ለማስገኘት ፡ በማለት ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ። በኢትዮጵያ ፡ የሚገኙት ፡ የተማሩ ፡ ጠበቆች ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ፤ የተማሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ቁጥር ፡ በማነሱ ፡ ያሉትን ፡ የሠራተኞች ፡ የሙያ ፡ ትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ በማድረግ ፡ ለመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፤ ለባንኮችና ፡ ለልማት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የተማሩ ፡ ሹማምንትን ፡ ለማስገኘት ፡ መጣጣር ፡ ተገቢ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

የግሚስ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ቢያንስ ፡ በሕግ ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚያስገኝና ፤ እንደዚሁም ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ኖሮአቸው ፡ ከሥራ ፡ ልምምዳቸው ፡ ጋር ፡ በማጣመር ፡ የሙያ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ለማበርከት ፡ እንደሚበቃ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

የዩኒቨርስቲው ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ፕሮግራም ።

ለአገሪቱ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎችን ፡ የሥራ ፡ ጉልበት ፡ ለማበርከት ፡ በሚሰጠው ፡ በትምህርት ፡ ምኩራብ ፡ (ፒራሚድ) ሦስተኛ ፡ ዓመቱን ፡ የጀመረው ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ እቁንጮው ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በመስከረም ፡ ፲፱፻፰፩ ፡ ለዚህ ፡ ፕሮግራም ፡ ከተቀበልናቸው ፡ ሠላሳ ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎች ፡ እኩሌታው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ሲሆኑ ፤ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ የዩኒበርስቲ ፡ ትምህርት ፡ ሲከታተሉ ፡ የቆዩ ፡ ናቸው ።

በየፈተናው ፡ ምክንያት ፡ የተማሪዎቹ ፡ ቁጥር ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ሀያ ፡ አምስቱ ፡ ወርዶአል ። ወደፊትም ፡ ጥቂት ፡ ሳይቀንስ ፡ አይቀርም ። ሆኖም ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ መሻሻልና ፡ እንደዚሁም ፡ የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ተማሪዎች ፡ በሁለተኛ ፡ ዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የማታ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ባሳዩት ፡ ጉልሕ ፡ የሆነ ፡ መሻሻል ፡ መምህራኑ ፡ ተደስተዋል ። ለእነዚህም ፡ ተማሪዎች ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ባገኙት ፡ መልካም ፡ ውጤትና ፡ ለሙያ ፡ ስላላቸው ፡ አርኢያነት ፡ መልካም ፡ ምኞቱን ፡ እገልጽላቸዋለሁ ። በኤል. ኤል. ቢ. ፕሮግራም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በጣም ፡ ሰፊና ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡

ለመስጠት ፡ እንጣጣራለን ። የምንሠራውን ፡ በየጊዜው ፡ የመገምገምና ፡ የራስንም ፡ ሥራ ፡ በገዛ ፡ ራስ፡የመቆጣጠሩ ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሊያቋርጥ ፡ አይገባውም ። በዚሁ፡ምክንያት ፡ ፋኩልቲው፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አራት ፡ ጥረቶችን ፡ አድርጉአል ።

ሀ) ከካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ በመጡት ፡ በፕሮፌሰር ፡ ኤም. ኤል. ሸዋርትዝ ፡ የሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጉብኝት ፡ ምክራቸውንና ፡ ስለ ፡ ሥራችንም ፡ ያሳቸውን፡ የሥራ ፡ ግምት ፡ በማግኘት ፡ ለመጠቀም ፡ ችለናል ። ፕሮፌሰር ፡ ሸዋርትዝ ፡ ብዙ ፡ የአፍሪካ ፡ ዩኒበርስቲዎችን ፡ የመጐብኘት ፡ ዕድል ፡ ያጋጠማቸው ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ ያላቸው ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ ናቸው ።

እርሳቸውም ፡ ስለ ፡ ሥራችን ፡ የሰጡት ፡ የሥራ ፡ ግምት ፡ መግለጫ ፡ አደፋፍሮናል ። ከኤሮፓ ፤ ከእንግሊዝና ፡ ከአሜሪካ ፡ አገር ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ የሚመጡ መምህራንና ፡ የሥራችንን ፡ ሁኔታ ፡ አመዛዝነው ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለመስጠት ፡ የሚመጡ ፡ እንግዶች ፡ ጉብኝት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በሚመጣውም ፡ ዓመት ፡ ቢያንስ ፡ ሁለት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጉብኝት ፡ እንደምናገኝ ፡ ባለተስፋ ፡ ነኝ ።

ለ) የትምህርትን ፡ ደረጃ ፡ የሚቆጣጠር ፡ በፋኩልቲው ፡ ልዩ ፡ ኮሚቴ ፡ ተቋቋማል ። ኮሚቴውም ፡ በተለይ ፡ አተኩሮ ፡ የተመለከተው ፤ ሐሳብን ፡ በጽሕፈት ፡ የማስፈርን ፡ ለማሻሻል ፡ ፕሮግራማችንን ፡ እንደምን ፡ አድርገን ፡ እናጠንክር ፡ ስለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። አዲስ ፡ (ጥሬ) የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ የበለጠ ፡ የሚማሩት ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ነው ። የሕግ ፡ አዋቂዎችም ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያከናውኑት ፡ በጽሕፈት ፡ ነው ። ብዙ ፡ የሕግ፡ ጥበቦች ፡ በመጀመሪያ ፡ ሊገኙ ፡ የሚችሉት ፡ አዘውትሮ ፡ በመመራመርና ፡ ሥርዐት ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ የመጻፍን ፡ ችሎታ ፡ በማሻሻል ፡ ነው ። ከብዙ ፡ ስብሰባዎች ፡ በኋላ ፡ ኰሚቴው ፡ የፋኩልቲውን ፡ አባሎች ፡ ሐሳብ ፡ አጠቃሎ ፡ የሚያሳይ ፡ መግለጫ ፡ አቀረበ ።

በፋኩልቲው ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ የሚገባውን ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ እየጻፈ ፡ የመማርን ፡ ሥራ ፡ በመዘርዘር ፡ የተዋሃደ ፡ ፕሮግራም ፡ አቀረበ ። በፕሮግራሙም ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ቀለል ፡ ያሉ ፕሮብሌሞችን ፡ በመተንተንና ፡ ማስታወሻ ፡ በማዘጋጀት ፡ ጀምረው ፡ ጠለቅ ፡ ወዳለ ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ፡ ምርምር ፡ የሚያሻው ፤ ሕግ፡ የማርቀቅ ፤ በፍርድ፡ቤት፡ምስያ ፡ (ሙት ፡ ኮርት) በመካፈል ፡ እየተከራከሩ ፡ እንዲራመዱና፡ በመጨረሻው ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ ገና ፡ መፍትሔ ፡ ያላገኙ ፡ ወይም ፡ በሚስፋፋ ፡ የሕግ ፡ ክፍሎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ አርዕስቶች ፡ ላይ ፡ በመመረቂያ ፡ ጽሑፍ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛ ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ተመልክቷል ። እነዚህም ፡ ሐሳቦች ፡ በሥርዐተ ፡ ትምህርቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ተደርጉአል ። በዚህ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያጠኑት ፡ ተማሪዎች ፡ "በኢትዮጵያ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ የመለቀቅ" እና ፡ "የብሔራዊ ፡ ቡና ፡ ቦርድ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም" በሚሉ፡ አርእስቶች ፡ የአንድ ፡ ትምህርት ፡ ወራት ፡ጊዜ ፡

ጽሑፍ ፡ ጽፈው ፡ አቅርበዋል ። ብዙ ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ መመራመርንና ፡ በየሥፍራው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ መጠያየቅን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ጽሑፎች ፡ በተማሪ ፡ ዎቹ ፡ ተጽፈዋል ።

ከነዚሁም ፡ የተሻሉት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ በጣም ፡ እንደሚያበለጽጉት ፡ እየተማመንን ፡ ከነዚሁም ፡ ጥቂቶቹን ፡ ፋኩልቲው ፡ አሳትሞ ፡ የሚያወጣበትን ፡ ቀን ፡ በናፍቆት ፡ እጠባበቃለሁ ።

ሐ) የፋኩልቲው ፡ የትምህርትን ፡ ደረጃ ፡ የሚቆጣጠር ፡ ኮሚቴ ፡ ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ ጠቅላላውን ፡ ፕሮግራም ፡ አጥንቶአል ። ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በሕግ ፡ መምህራን ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርቱ ፡ ዝርዝር ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መስማማት ፡ አይኖር ፡ ይሆናል ፤ በኔ ፡ አስተያየት ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ የማይለወጥ ፡ ሁኖ ፡ መታየት ፡ የለበትም ። ሆኖም ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታዊ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተወስነዋል ። ፋኩልቲው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ በመመረቂያ ፡ ጽሑፍ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛ ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ ማዘጋጃ ፡ ፕሮግራምና ፡ ለዚህም ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ይሁን ፡ ለተባለው ፡ ሐሳብ ፡ ተስማምቶአል ።

እንደዚሁም ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ ተመራቂዎቻችን ፡ የሚበዙት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ አማካይነት ፡ በአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ እንደሚቀጠሩና ፡ የከፍተኛ ፡ ሕጎችን ፡ ረቂቅ ፡ ወይም ፡ የአፈጻጸም ፡ ደንቦችን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ እንደሚጠየቁ ፡ በመገመት ፤ በሕግና ፡ በልማት ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ (ፖሊሲ) አወሳሰን ፡ መካከል ፡ ስለሚኖረው ፡ ግንኙነት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ እንዲኖራቸው ፡ በማሰብ ፡ ከሥርዐተ ፡ ትምህርታችን ፡ መካከል ፡ የሕዝብ ፡ መብትን ፡ ነክ ፡ ሕግ ፡ (ፐብሊክሎው) ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቶታል ። ምክንያቱም ፤ ሕግን ፡ ማዘጋጀትና ፡ ሕግን ፡ ማስፈጸም ፡ የልማት ፡ ፕሮግራሞች ፡ የሚፈጸሙባቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። ተራ ፡ ሰዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሕግን ፡ ማርቀቅና ፡ ማስፈጸም ፡ የመንግሥትን ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ረገድ ፡ የሚወስድ ፡ የቅልጥፍና ፡ ስምሙ ፡ የሆነ ፡ ዘዴ ፡ አድርገው ፡ ይገምቱታል ። እርግጡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ።

ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ስለሆነው ፡ አዳዲስ ፡ ብሔራዊ ፡ ሕጎች ፡ ዓላማና ፡ ችግር ፡ በሰፊው ፡ እንዲያውቁ ፡ ካልተደረገ ፡ እና ፡ የሕግ ፡ አዘጋጅነት ፤ አማካሪነት ፡ ወይም ፡ አስፈጻሚነት ፡ ተግባርን ፡ ሥርዐት ፡ ባለውና ፡ በተሟላ ፡ ሁኔታ ፡ ሊፈጸሙ ፡ እንዲችሉ ፡ ካልተደረገ ፤ ሞያቸውም ፡ በሚገባው ፡ መንገድ ፡ ካልተመራ ፡ በቀር ፤ የሚታቀደው ፡ ታላቅና ፡ ጠቃሚ ፡ መሻሻል ፡ ወይም ፡ ለውጥ ፡ ሁሉ ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የሰፈረ ፡ በገቢር ፡ የማይገለጽ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሰው ፡ የሥራ ፡ ጉልበት ፡ ፍላጎት ፡ ፅንስ - ሐሳብ ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተገቢው ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ አይመስለኝም ። በአገር ፡ እድገት ፡ ጉዳይ ፡ “ እንደመሐንዲሶች ” ሕግ ፡ ዐዋቂዎችም ፡

ርሻ ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚገባ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ ማስተ
ማር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ የሕግ ፡ አወጣጥና ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ
ሥርዐትን ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በሕግ ፡ በአስተዳደር ፡ አመራርና ፡
በኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በተመሰጠ ፡ አኳኋን ፡ የሚ
ያስረዱ ፡ የተመረጡ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ማጥናትም ፡ ያሻል ።

በዚህም ፡ መሠረት ፡ "ሕግና ፡ የመንግሥት ፡ የኢኮኖሚ ፡ ሥራ ፡ መሪ - ሐ
ሳብ" ተብሎ ፡ የተሰየመ ፡ ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ የሚሰጥ ፡ የከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትም
ህርት ፡ ለማስተማር ፡ አስበናል ። ይኸውም ፡ ትምህርት ፡ በተቀዳሚ ፡ የልማት ፡
እቅድ ፤ የእቅዱ ፡ ዝግጅትና ፡ ሕጋዊ ፡ አግባቡን ፡ ይመለከታል ። በተጨማሪም ፡
የቀረጥ አወሳሰንና ፡ አሰባሰብን ፡ ችግሮች ፤ ማለት ፡ ገቢ ፡ የማግኛ ፡ ዘዴዎች ፡ የሚ ፡
ደረጁበትን ፤ የቀረጥ ፡ ሕጎችን ፡ የማዘጋጀትና ፡ ፍች ፡ መስጠትን ፤ እንዲሁም ፡
የቀረጥን ፡ አስተዳደር ፡ የሚነኩ ፡ ችግሮችን ፡ ይመረመራል ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፤
ገንዘብን ፡ (ሀብትን) አጠቃቀም ፡ ላይ ፡ ስለሚዋል ፡ በወጡ ፡ የመንግሥት ፡ የንግድ
ማኅበሮችን ፡ የሚያቋቁሙ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ሕጎችና ፡ እን
ዲሁም ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከ
ተው ፡ ሁሉ ፡ የንግድን ፡ ልማት ፡ ለማሻሻል ፡ የሚረዱ ፡ የመንግሥት ፡ የሥራ ፡
መሪ ፡ ሐሳብና ፡ እርምጃ ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ ያጠናል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ብዙና ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። እነዚህም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አስ
ፈላጊና ፡ ለአእምሮም ፡ አንቂነት ፡ የተለዩ ፡ ጉዳዩ ፡ ይሆናሉ ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ ካደ
ረግናቸው ፡ ውስጥ ፡ ለምሳሌ ፡ ብቻ ፡ የተጠቀሱ ፡ ናቸው ።

መ) ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ በፊት ፡ የሚሰጥ ፤ ከዩኒቨርስቲው ፡ የፋኩልቲ ፡ ጉ
ባኤ ፡ በተሰጠን ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ በአርትስ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ ከሕግ ፡ ትም
ህርት ፡ በፊት ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ ማስተማር ፡ ጀምረናል ። በዚሁም ፡ መሠ
ረት ፡ ቁጥራቸው ፡ የተወሰነ ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ተማሪዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡
የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ይኸን ፡ ትምህርት ፡ የመምረጥ ፡
ዕድል ፡ ይኖራቸዋል ።

ሥርዓተ ፡ ትምህርቱ ፡ ከአርት ፡ ፋኩልቲ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ የሚዘጋጁ
እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ እነዚሀ ፡ ተማሪዎች ፡ ለሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የዩኒቨርስቲ ፡
ትምህርታቸው ፡ በአርት ፡ ፋኩልቲ ፡ ከሚሰጡት ፡ የትምህርት ፡ ዐይነቶች ፡ መካ
ከል ፡ ምርጫ ፡ ይፈቀድላቸዋል ። በተጨማሪም ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሚመለከቱ ፡ የተ
መረጡ ፡ ችግሮችን ፡ በመመርመር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግን ፡ መማሪያ ፡ ዘዴዎችን ፡
እንዲያውቁ ፡ የመለማመጃ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ይኖራቸዋል ። በዓመቱም ፡
መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የፈተናቸው ፡ ማዕከላዊ ፡ ውጤት ፡ የሚያስደስት ፡ ሁኖ ፡ ከተገኘ ፤
ወደ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተዛውረው ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ የሞያ ፡ ጥናት ፡ እን
ዲከታተሉ ፡ ይደረጋል ።

“ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ በፊት ፡ የሚሰጥን ፡ ትምህርት” ፕሮግራም ፡ በመደገፍም ፡ ሆነ ፡ በመቃወም ፡ ብዙ ፡ መናገር ፡ ይቻላል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ያለንበት ፡ ሁኔታ ፡ በጥብቅ ፡ እናስብበት ፡ ዘንድ ፡ የሚያስገድድ ፡ ነው ። ከሁሉ ፡ በፊት ፡ በጊዜው ፡ ሁኔታ ፤ በተለይም ፣ ከፍተኛ ፡ ወጭ ፡ በሚያስፈልገው ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርት ፡ ምክንያት ፤ ለሕግ ፡ የሞያ ፡ ትምህርት ፡ የመግቢያ ፡ ደረጃ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርት ፡ መጨረሻ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ተገድደናል ። ይኸም ፡ ማለት ፤ ከፍተኛና ፡ ሰፊ ፡ ለሆነው ፣ የሞያ ፡ ትምህርት ፡ ተማሪዎችን ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለብን ፡ ማለት ፡ ነው ። የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ነክ ፡ የሳይንስ ፡ ትምህርቶች ፡ ለማሳወቅና ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴዎች ፡ (በቋንቋ ፡ ችሎታ) በማሻሻል ፡ ረገድ ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ መስጠት ፡ ያሻል ።

የወደፊት ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ስለሚገጥማቸው ፤ ሰፊና ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ የትምህርት ፡ መሠረት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ስለማምን ፤ በኔ ፡ አስተያየት ፤ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መግቢያ ፡ ደረጃን ፡ ወደፊት ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ማሰብ ፡ ይኖርብናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ የበለጠ ፡ ጥናት ፡ በማድረግ ፡ የሚወሰን ፡ ነው ፤ ለጊዜው ፡ ግን ፡ ተገቢው ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ተማሪዎች ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለመምረጥ ፡ በመቻላችንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ቢያንስ ፡ ሀያ ፡ ተማሪዎች ፡ ከዩኒቨርስቲው ፡ በየዓመቱ ፡ ለማግኘት ፡ እንደምንችል በማወቃችን ፡ ተደስተናል ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ዝግጅትና ፡ መታተም ።

የማስተማሪያ ፡ መጻሕፍት ፤ የሕግ ፡ አስተያየት ፡ መግለጫ ፡ አለመኖርና ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ታትሞ ፡ አለመውጣት ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ ችግር ፡ አይደለም ። እንደነዚሁ ፡ ያሉት ፡ ጽሑፎች ፡ በብዛት ፡ የሌሉት ፡ ማናቸውም ፡ የሕግ ፡ ሙያተኛ — አሳቢ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂ — እምሀበ ፡ አልቦ ፡ እንደሚሠራ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። እነዚሁ ፡ መማሪያዎች ፡ ለማንኛውም ፡ ዘመናዊና ፡ የተስተካከለ ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ በእርግጥ ፡ የደም ፡ ሥሮች ፡ ናቸው ።

በትጋት ፡ በሚሠራው ፡ በፋኩልቲው ፡ ኮሚቴ ፡ አማካይነት ፡ የታቀደው ፡ ፕሮግራማችን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ፍላጎቶች ፡ የሚያሟሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ አዘጋጅቶ ፡ የማውጣት ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ነው ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ፋኩልቲው ፡ ከተቋቋመበት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የሚከተሉትን ፡ የመጀመሪያ ፡ ተግባሮች ፡ ፈጽሞአል ።

(፩) የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ። ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ይህን ፡ መጽሔት ፡ ማሳተም ፡ ጀምረናል ። በዚሁም ፡

አማካይነት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎችንና ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አስተያየት ፡ መግለጫዎች ፡ መታተም ፡ ጀምረዋል ። መጽሔቱም ፡ በየመንፈቁ ፡ ታትሞ ፡ የሚወጣ ፡ ሲሆን ፤ የአዘጋጅ ፡ ኮሚቴ ፡ አባሎች ፡ ሽያጩን ፡ ለማብዛት ፡ ባአደረጉት ፡ ብርቱ ፡ ጥረትና ፡ የሕዝብ ፡ ማስታወቂያ ፡ በውስጡ ፡ በማሳተም ፡ ይልቁንም ፡ የመጽሔቱ ፡ ደጋፊዎች ፡ በመሆን ፡ የሚረዱ ፡ ሰዎች ፡ ለማግኘት ፡ በአደረግነው ፡ ሙከራ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤት ፡ በማግኘቱ ፡መጽሔቱ ፡ ወጭውን ፡ እራሱ ፡ የሚችል ፡ ለመሆን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ <u>የመጽሔቱ ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች</u> ፡ በመሆን ፡ ሀያ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ የከፈሉት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ በመጽሔቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል ። የነዚህም ፡ ሰዎች፡ ዕርዳታ፡ መጽሔቱን፡ ለማሳተም፡ እንዲቻል፡ በማለት፡ ለጠበቆች፡ ወይም ፡ ለሕግ ፡ አዋቂዎችና ፡ ለዳኞች ፡ ለቀረበው ፡ ሕዝባዊ ፡ ልመና፡አስደሳች ፡ መልስ ፡ ነው ። የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬደን ፤ ሚስተር ፡ ሉውንሽቴን ፡ ሚስተር ፡ ኪንድረድ ፤ ሚስተር ፡ ሲንገርና ፡ሚስተር ፡ ፊሸር፡ በመጽሔቱ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ የሚያሳልፉ ፡ መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ሳልገልጸው ፡ ሳልና፡ አልፈቅድም ። እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ከተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ አራት ፡ አባሎች ፡ በአዘጋጁ ፡ ኮሚቴ ፡ ውስጥ ፡ መግባታቸውና ፡ ስማቸውም ፡ በመጽሔቱ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑን ፡ ልገልጽ ፡ እወዳለሁ ። የሥራትም ፡ ሥራ ፡ የሚመሰገን ፡ ነው ። ይኸ ፡ የመጀመሪያው ፡ ሲሆን ፡ መጽሔቱን ፡ በማዘጋጀት ፡ ሥራ ፡ ተማሪዎችም ፡ ተካፋይ ፡ የመሆናቸው ፡ ልማድ ፡ ለወደፊትም ፡ የሚቀጥል ፡ ሆኖ ፡ የመጽሔቱን ፡ ሳያቋርጥ ፡ መውጣት ፡ የሚያረጋግጥ ፡ እንደሚሆን ፡ ባለተስፋ ፡ ነን ።

(፪) <u>የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ያሳተማቸው፡ መጻሕፍት ።</u> በሐምሌ ፡ ወር ፡ <u>፲፱፻፷፩</u>፡ ዓ. ም. የመጀመሪያዎቹን ፡ ሦስት፡ መጻሕፍትን፡ አሳትመናል። እነዚሁም፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤ <u>የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ (ከቁ. ፩ ፡ እስከ ፡ ፹፬)</u> በሚል ፡ አርእስት ፡ በዶክተር ፡ ፊሊፕ ፡ ግራቬን ፡ የተዘጋጀው ፡ መጽሐፍ ፤ የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የጠቅላላው ፡ ክፍል ፡ የመጀመሪያው ፡ አስተያየት ፡ መግለጫ ፤ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮንን ፡ ማስታወሻና ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ የስዊስንም ፡ ነቅዕ - መነሻ ፡ የሚጠቅስ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ <u>በኢትዮጵያና ፡ በስዊዘርላንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ አነፃፃሪ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ጽሑፎች</u> ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በስቲቮን ፡ ለውንሽቴን ፡ የተዘጋጀው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። በዚሁም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከኢትዮጵያ ፤ ከስዊስና ፡ ከሌሎችም ፡ ነቅዕ - መነሻዎች ፡ የተገኙ ፡ ጽሑፎችና ፡ ከሕግ ፡ ቃሎች ፡ ሌሎችም ፡ ማስታወሻዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ለማስተማሪያ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ የተዘጋጁ ፡ ጥያቄዎችና ፡ ምርምሮች ፡ ተጠቃለው ፡ ይገኙበታል ።

ሦስተኛው ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕጎች ፡ መጋጨት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ በሮበርት ፡ አለን ፡ ሲድለር ፡ የተዘጋጀው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ የሕጎች ፡ መጋጨትን ፡ ታሪካዊ ፡ ሁኔታና ፡ በጠባያቸውም ፡ የሚነገሩትን ፡ እምነቶች ፡ የሚያትትና ፡ በኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ወደፊት ፡ የሚደርሰውን ፡ እድገት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

በተጨማሪም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬደን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ ሞዴል ፡ (ፎርም) መጽሐፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። በዚሁም ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ ሞዴሎች ፡ ከነመቅሚቸው ፡ እንደዚሁም ፡ የንግድ ፡ ሞዴል ፡ የኪራይ ፡ ስምምነቶች ፡ የውል ፡ (የኮንትራት) ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ዶኪማዎችና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉትም ፡ ለዓይነት ፡ ያህል ፡ ይገኙበታል ። ይኸውም ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚጠቅም ፡ መጽሐፍ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለሕግ ፡ ሙያም ፡ የሚበጅ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

(፫) ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ የተዘጋጁ ፡ መጻሕፍት ፡ መታተም ፤ የመሬት ፡ ሕግና ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ለማሻሻል ፤ እንደዚሁም ፡ የንብረት ፡ ሕግ ፡ በሚገባ ፡ ለማስተማር ፡ አስቀድሞ ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ሥሪት ፡ በይበልጥ ፡ ሊታወቅ ፡ ይገባል ። የኢትዮጵያ ፡ ምርምርና ፡ ጥናት ፡ ኢንስቲትዩት ፡ ከሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለማሳተም ፡ ወስኖአል ። የመጀመሪያዎቹም ፡ ሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ታትመዋል ። እነዚህም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

የመጀመሪያው ፡ የሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ሥሪት (ቻርተርስ) በሚል ፡ አርእስት ፡ በለንደን ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የምሥራቃዊና ፡ የአፍሪካ ፡ ጥናት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፕሮፌሰር ፡ በሆኑት ፡ በዶክተር ፡ ጂ. ደብሊው. ቢ. ሀንቲንግ ፡ ፎርድ ፡ የተዘጋጀው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በቀየው ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ነገሥታቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለመኳንንት ፡ መሬት ፡ የሰጡባቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ምርምር ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በሸዋ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ በቆሬ ፡ የተደረገ ፡ የሙከራ ፡ ጥናት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የምግብና ፡ የእርሻ ፡ ድርጅት ፡ የገጠር ፡ አጥኚዎች ፡ ሹም ፡ በሆኑት ፡ በዶክተር ፡ ኤች. ኤስ. ማን ፡ የተዘጋጀው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጽሑፍ ፡ በደቡባዊ ፡ ሸዋ ፡ ለዐይነት ፡ በተመረጠ ፡ በአንድ ፡ አነስተኛ ፡ ሥፍራ ፡ የተደረገውን ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጥናት ፡ የሚያስረዳ ፡ ሲሆን ፤ የይዞታውን ፡ መበላለጥና ፡ ከመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጋር ፡ የተያያዘውን ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታም ፡ ይገልጻል ። በተለይም ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ በባለመሬትና ፡ በጭሰኛ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ አስፋፍቶ ፡ ያስረዳል ።

(፬) የማስተማሪያ ፡ መሣሪያዎች ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንጮች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በጣም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ።

ሀ) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ምንጩ ፡ የስዊስ ፡ ሕግ ፡ (ኮድ) ሲሆን ፡ ከዩጎዝላቪያ ፡ ከግሪክና ፡ ከብራዚል ፤

ለ) የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ ከፈረንሣይና ፡ ከጀርመን ፤

ሐ) የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፤ በሕንድ ፡ አማካይነት ፡ ከኮመን ፡ ሎው ፡ የተገኙ ፡ ሐሳቦች ፡ የሚገኙባቸው ፡ ሲሆን ፤ እንደዚሁም ፤

መ) ሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ ብዙ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ ደግሞ ፡ መሠረታቸው ፡ በከፊል ፡ ከእንግሊዝ ፡ አሜሪካን ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ በውጭ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍትና ፡ ጥናቶች ፡ ለማስተማር ፡ አይቻልም ። የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ለማስተማር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዐትና ፡ የአገሪቱን ፡ አቋሞችና ፡ ተለዋዋጭ ፡ ፍላጎቶች ፡ በተለይ ፡ የሚመለከቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ያስፈልጋሉ ። ስለዚህ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የትምህርት ፡ ዐይነት ፡ የተለየ ፡ የማ ፡ ስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ማሰናዳት ፡ የያንዳንዱ ፡ የፋኩልቲው ፡ አባል ፡ (መምህር) ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ ተዘጋጅተው ፡ በማባዣ ፡ መኪና ፡ እየተባዙ ፡ ይሠራባቸዋል ። እነዚህም ፡ ጽሑፎች ፡ የሚያገለግሉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፎችን ፤ ሕጎችና ፡ ጉዳዮችን ፡ ከዛሬይቱ ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ጋር ፡ ለማዛመድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሊገኙ ፡ የቻሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጽሑ ፎችም ፡ በማስተባበር ፡ ተማሪዎች ፡ ጠቃሚውን ፡ የሕግ ፡ ጥበብ ፡ እንዲገበዩና ፡ የገዛ ፡ ራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ነፃ ፡ አስተሳሰብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ለማበረታታት ፡ የታ ቀዱ ፡ ጥያቄዎችና ፡ መግለጫዎችን ፡ ለማቅረብ ፡ ጭምር ፡ ነው ። በነዚህም ፡ መጻሕፍት ፡ ተማሪዎቹ ፡ እንደመማሪያ ፡ ይጠቀሙባቸዋል ። እነዚህም ፡ የተባዙ ፡ የማስተማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደተጣሩና ፡ እንደተሟሉ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይበልጥ ፡ ነዋሪ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ታትመው ፡ እንዲገኙና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ባለሞያ ዎችና ፡ የተማሪዎችም ፡ መጠቀሚያ ፡ ለመሆን ፡ እንደሚበቁ ፡ የፋኩልቲው ፡ ተስፋ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ሲሆን ፡ የፋኩልቲውን ፡ የወደፊት ፡ አባሎች ፡ ጊዜያቸውን ፡ ሌላ ፡ ከፍተኛ ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ እንዲያውሉ ፡ ያስችላቸዋል ።

(፩) <u>ሌሎች ፡ በፋኩልቲ ፡ አባሎች ፡ የተዘጋጁ ፡ ጽሑፎች</u> ፤ የፋኩልቲ ፡ አባ ሎች ፡ ሁሉ ፡ አድካሚ ፡ በሆነው ፡ የምርምር ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋይ ፡ ሁነዋል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ያልተጠቀሱት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ሀ) ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቢች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ብዙ ፡ ጽሑ ፎች ፡ ከማበርከታቸውም ፡ በላይ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ግዴታዎች ፡ ቁጥሮች ፡ በፈረንሣይኛው ፡ መሠረት ፡ የተ ሻሻለ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ትርጉም ፡ አዘጋጅተዋል ። ይኸውም ፡ ትርጉም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ እላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ክፍል ፡ ለመረዳት ፡

በጣም ፡ የሚረዳ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ ተረቅቆ ፡ የሚገኘው ፡ የዚሁ ፡ ክፍል ፡ አስተያየት ፡ መግለጫ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆናል ።

(ለ) ሚስተር ፡ ፊሸር ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ከሕንድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ጋር ፡ በማስተናበር ፡ የሚገናኙበትን ፡ ምንጭ ፡ የሚያብራራ ፡ ጽሑፍ ፡ አሳትመዋል ። ይኸውም ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ምንጭ ፡ መጽሐፍ</u> ፡ ለተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ነው ።

ሐ) ዶክተር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ “ ላ ፡ ኖሲዮን ፡ ደ ፡ ኮድ ፡ አን ፡ ኤሮፓ ፡ አክሲዴንታል ፡ ዱዝ ፡ ዊትዬም ፡ ሲክል ፡ ኤሰ ፡ ደ ፡ ደፊናንሲዮን ” ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ የሚያዘጋጁትን ፡ መጸሕፍትና ፡ “አስፔክት ፡ ዲ ፡ ላ ፡ ጁስቲስ ፡ ኢንዲጄን ፡ ኤን ፡ ፔይ ፡ ዘንድ ፡ ኤን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ኤ ፡ ፲፱፻፶፰” ብለው ፡ የሰየሙትን ፡ ጽሑፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ በቅርቡ ፡ ጨርሰዋል ። ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔትም ፡ “ ዘ ፡ ሬሌቫንስ ፡ ኦቭ ፡ ዘ ፡ ስተዲ ፡ ኦቭ ፡ ሊጋል ፡ ሂስትሪ ፡ ፎር ፡ ቤቱር ፡ አንደርስታንዲንግ ፡ ኦቭ ፡ ሞደርን ፡ ኢትዮፕያን ፡ ሎው” (ዘመናዊውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ በይበልጥ ፡ ለመረዳት ፡ የሕግን ፡ ታሪክ ፡ ማጥናት ፡ ተገቢ ፡ ስለመሆኑ) በሚል ፡ አርዕስት ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅተዋል ። እንደዚሁም ፡ “ኩተሜ ፡ ዱ ፡ ማኑኤል ፡ ኤ ፡ ጁሪስፕሩዳንስ ፡ ዱ ፡ ድሩዋ ፡ ዛንድ ” ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ዝግጅት ፡ በማጠናቀቅ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚገለጸውን ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ እቅድ</u> ፡ ጀምረዋል ።

(፭) <u>ያልታተሙ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎች ፤ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ እቅድ</u> ፤

የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መምህራን ፡ የተመደበላቸውን ፡ የትምህርት ፡ ዐይነት ፡ ለማስተማር ፡ የሚረዱዋቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጽሑፎች ፡ በየበኩላቸው ፡ መሰብሰብ ፡ ነበረባቸው ። ብዙው ፡ የተሰበሰበው ፡ በአንቀጽ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመጽሐፍ ፡ መልክ ፡ ታትሞ ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ፤ ሆኖም ፡ ለክፍል ፡ መነጋገሪያ ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የተሰበሰቡት ፡ መረጃዎች ፡ ማለት ፡ የባንክ ፡ ሥርዐት ፡ የታክስ ፡ ሁኔታ ፤ ሐብትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ ድንጋጌ ፤ የባጀት ፡ ዝግጅት ፡ የፓርላሜንት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ወዘተርፈ ፡ ምርምር ፡ ለሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ በሚያመች ፡ አኳኋን ፡ ማውጫ ፡ ተበጅቶላቸው ፡ አዲስ ፡ በተቋቋመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ በሚገባ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ተደርጎአል ። በዶክተር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ የሚመራው ፡ ይኸ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ባህልን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጽሑፎች ፡ አሰቀማጭም ፡ ነው ። ይኸም ፡ የጽሑፎች ፡ መሰብሰብና ፡ ማስተርጐም ፡ እንደዚሁም ፡ ለወደፊት ፡ የሕግ ፡ ምሁራን ፡ በሚገባ ፡ ጠብቆ ፡ ማቆየት ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

(፯) <u>የተማሪዎች፡የክረምት፡ወራት፡ምርምር</u}፤ በረጅሙ፡የክረምት፡ወራት፡የረፍት፡ጊዜ፡ውስጥ፡የሕግ፡ፋኩልቲ፡ተማሪዎቹን፡በምርምር፡ሥራ፡ላይ፡አሰማርቶ፡ነበር። በ፲፱፻፶፮፡ዓ.ም. የክረምት፡ወራት፡በፋኩልቲው፡መምህራን፡መሪነት፡ተማሪዎቹ፡በአዲስ፡አበባ፡በስተደቡብ፡መቶ፡ኪሎ፡ሜትር፡ያህል፡ርቆ፡በሚገኘው፡በጉራጌ፡ክፍለ፡አገር፡ውስጥ፡በሚገኝ፡ሥፍራ፡የሙከራ፡የመሬት፡ይዞታ፡ጥናት፡አድርገው፤ ለንብረት፡ትምህርት፡ማስተማሪያ፡የሚጠቅም፡መረጃ፡ለማግኘት፡ተችሎአል። ሌሎች፡ተማሪዎች፡ደግሞ፡በኢትዮጵያ፡ሕጎች፡(ኮዶች) ውስጥ፡በአማርኛውና፡በእንግሊዝኛው፡ጽሑፍ፡መካከል፡የሚገኙትን፡ልዩነቶች፡እንዲለቅሙና፡በውጭ፡አገር፡መምህራን፡ዘንድ፡በቋንቋ፡ምክንያት፡የሚገጥመውን፡ችግር፡ለማቃለል፡በማሰብ፡ከአማርኛም፡ብዙ፡የሕግ፡ጽሑፎችን፡ወደ፡እንግሊዝኛ፡እንዲተረጉሙ፡ተደርጐ፡ነበር። በ፲፱፻፶፯፡ዓ.ም. የክረምት፡ወራት፡ደግሞ፡በአዲስ፡አበባና፡በሌላም፡ሥፍራ፡በጠቅላይ፡የንጉሠ፡ነገሥትና፡በከፍተኛው፡ፍርድ፡ቤት፡ባለፉት፡ዓመታት፡ውስጥ፡ከተወሰኑ፡ፍርዶች፡መካከል፡ጠቃሚ፡የሆኑትን፡ፍርዶችን፡ለመምረጥ፡ይቻል፡ዘንድ፡የፍርድ፡ቤት፡ውሳኔዎችን፡የማቅረብ፡ፕሮግራም፡ተጀመረ። ይኸንንም፡ሥራ፡የሥራ፡ጓደኛዬ፡ሚስተር፡ኪንድሬድ፡ይከታተሉት፡ነበር። የተሰበሰቡትም፡ፍርዶች፡ሁሉ፡ተራ፡ቁጥርና፡መግለጫ፡ተሰጥቶአቸው፡በሕግ፡ቤት፡መጻሕፍት፡ውስጥ፡እንዲገኙ፡ተደርጎአል። ከነዚህም፡በጣም፡ጠቃሚ፡ሆነው፡የሚገኙት፡በዚህ፡የሕግ፡መጽሔት፡ውስጥ፡ታትመው፡እንዲወጡ፡ይደረጋል።

ከዚህም፡ጥረት፡የተነሳ፡ብዙ፡የፍርድ፡ውሳኔዎች፡የሚገኙ፡የሆነ፡እንደሆነ፡ምናልባት፡ለፍርድ፡ቤት፡ውሳኔዎች፡መግለጫ፡ሌላ፡የተለየ፡እትም፡ማውጣት፡ያስፈልግ፡ይሆናል። የሕግ፡ቤተ፡መጻሕፍትን፡በከፍተኛ፡የፍርድ፡ቤት፡ውሳኔዎች፡ማበልጸግ፡እንዲቻል፡ጽሑፎችን፡በሚገባ፡ለመቅዳት፡የሚያስችል፡የማባዣ፡መኪና፡ተገዝቶአል። ተማሪዎችም፡በልዩ፡ልዩ፡የምርምር፡አቅድ፡ለፋኩልቲው፡አባሎች፡የግል፡ዕርዳታ፡በማድረግ፡ላይ፡ናቸው። ይኸንንም፡የክረምት፡ወራት፡ከፍተኛ፡ተግባር፡ለሚፈጽሙት፡ተማሪዎች፡በመጠኑ፡ገንዘብ፡ይከፈላቸዋል።

በፋኩልቲው፡መምህራን፡የቅርብ፡ተቆጣጣሪነት፡ቁጥራቸው፡ከሀያ፡አምስት፡የበለጠ፡ተማሪዎች፡በዚሁ፡ተግባር፡ተካፋይ፡ሁነዋል። በዚሁም፡ሙከራ፡ለመረዳት፡እንደተቻለው፡ሥራው፡ለተማሪዎቹ፡ተጨማሪ፡የሕግ፡ትምህርት፡የሰጣቸው፡ከመሆኑም፡በላይ፡አስፈላጊያቸው፡የሆነ፡ውን፡የገንዘብ፡ዕርዳታ፡ሊያስገኝላቸው፡ችሎአል። ለወደፊትም፡በቂ፡ገንዘብ፡ካገኘን፡የክረምት፡ወራት፡ሥራን፡ከሕግ፡ትምህርት፡ቤት፡ፕሮግራም፡እንዳንዱ፡ለማድረግ፡እንደምንችል፡ተስፋ፡አደርጋለሁ።

በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸሙ ፡ ሌሎች ፡ ተግባሮች ።

(፭) የክብር ፡ ትንጅት ፤ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረጉት ፡ እድገቶች ፡ አንዱ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ የክብር ፡ ትንጅት ፡ መቋም ፡ ነው ። የተለዩ ፡ ሙያቸው ፡ እንደሚጠይቀው ፡ ሁሉ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ሲፈጸም ፡ የሚገባውን ፡ የሙያ ፡ ዐመል ፡ (ጠባይ) የሚቆጣጠር ፡ ሕግ ፡ አውጥተው ፡ ከአንድ ፡ የፋኩልቲው ፡ መምህር ፡ ጋር ፡ በመረዳዳት ፡ አሥራ ፡ ላይ ፡ አውለውታል ። እኔም ፡ አሁንም ፡ ወደ ፊትም ፡ የምመኘውና ፡ የማምነው ፡ ይኸ ፡ አድራጐት ፡ በቅርቡ ፡ በሕግ ፡ ሙያተኞነት ፡ ተርታ ፡ ለሚሰለፉት ፡ ወጣቶች ፡ ዋጋ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ነው ።

(፮) ስለ ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚ ፡ በፋኩልቲው ፡ የተደረጉ ፡ የጥናት ፡ ጉባኤዎች ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከንግድ ፡ ሥራ ፡ ኮሌጅ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ውስጥ ፡ አሥር ፡ ተከታታይ ፡ የሕግና ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ጥናት ፡ ጉባኤዎች ፡ አድርጐአል ። የጥናቱም ፡ ጉባኤ ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ የሁለቱ ፡ ፋኩልቲ ፡ አባሎችን ፡ ለዚህ ፡ ዐይነተኛ ፡ ተግባር ፡ ለማነቃቃትና ፡ በይበልጥም ፡ እንዲብራሩላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። የውጭ ፡ ተናጋሪዎች ፡ የሚበዙትም ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ዐዋቂዎች ፡ (ኤክስፐርቶች) የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በየስብሰባው ፡ አንዳንድ ፡ መግለጫ ፡ እንዲሰጡ ፡ ተጠርተው ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለጉባኤው ፡ ገልጸዋል ።

ከነዚህም ፡ ተናጋሪዎች ፡ ብዙ ፡ የንግድ ፡ አቋሞችን ፤ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የፕላኒንግ ፡ ቦርድ ፡ አባሎችና ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ መምህራንም ፡ ጭምር ፡ ነበሩ ።

ንግግሩንም ፡ ለመምራት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ተገኝተዋል ። በብዙዎችም ፡ ስብሰባዎች ፡ ግልጽና ፡ ጠቃሚ ፡ ውይይት ፡ ተደርጐአል ። በነዚሁም ፡ ስብሰባዎች ፡ በሚከተሉት ፡ አርዕስቶች ፡ ጉዳዮች ፡ ንግግር ፡ ተደርጐ አል ፡፡

ሀ- ስለ ፡ ልማት ፡ ሕግና ፡ የኢኮኖሚ ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፤

ለ- ሁለተኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፤

ሐ- የኢትዮጵያ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ልማት ፤

መ- የኢትዮጵያ ፡ የሰው ፡ የሥራ ፡ ጉልበት ፡ ፍላጎት ፤

ሠ- ሀብትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ ሕግና ፡ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኝባቸው ፡ ምንጮች ፤

ረ- በኢትዮጵያ ፡ የሚገኙ ፡ የአበዳሪ ፡ ድርጅቶች ፤

ሰ- በኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስለማቋቋም ፡ ሕጋዊና ፡ የአፈጻጸም ፡ ችግሮች ፤

ሸ- የኢትዮጵያ ፡ የቀረጥ ፡ አሰባሰብ ፡ ዘዴ ፤
ቀ- በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በአማዳዊ ፡ ሕግም ፡ ጥምር ፡ የሚፈጠሩ ፡ የመሬት ፡ ሕግ ፡ ችግሮች ፡ እና ፡
በ- የሙያተኞች ፡ ሕግ ፡ ችግሮች ።

(፫) <u>በተማሪዎች ፡ የተደራጀ ፡ የሕግ ፡ ሸንጐ</u> ፤ ሚያዝያ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ የሕግ ፡ ሸንጐ ፡ ኰሚቴ ፡ እንዲቋቋም ፡ ፈቀደ ፤ ኮሚቴው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ቤተሰቦች ፡ የሚጠቅሙ ፡ ተከታታይ ፡ የንግግሮች ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ማኅበሩ ፡ አዘዘ ። ይኸን ፡ ዐይነቱም ፡ የትምህርት ፡ ሸንጐ ፡ በዩኒበርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ በተማሪዎች ፡ ሲዘጋጅ ፡ ይኸ ፡ የመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

የማኅበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የሆኑት ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ካሣ ፤ እንዲሁም ፡ አባሎቹ ፡ አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ደነቀው ፤ አቶ ፡ ግርማ ፡ ታደሰና ፡ አቶ ፡ ፍሥሐ ፡ ባይህ ፡ ፕሮግራሙን በቶሎ ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ተመረጡ ። በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥም ፡ ሦስት ፡ በጣም ፡ የውመሩና ፡ የሕግ ፡ ቀን ፡ ተብሎ ፡ በተሰየመው ፡ በግንቦት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ከፍተኛ ፡ አድናቆትን ፡ በማግኘት ፡ የተፈጸሙ ፡ የንግግር ፡ ፕሮግራሞችን ፡ አዘጋጁ ። ግንቦት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የካሊፎርኒያ ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ (ስቴት) የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ስታንሊ ፡ ሞሰክ ፡ ንግግር ፡ ያደረጉበት ፡ ሸንጐ ፡ ተደረገ ። ጀስቲስ ፡ ሞሰክ ፡ በሔግ ፡ የሚገኘውን ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ፍትሕ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቅርቡ ፡ የጐበኙና ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚታየው ፡ በደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ላይ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በላይቤሪያ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ሲሰማ ፡ ጉዳዩን ፡ የተከታተሉ ፡ ናቸው ።

እርሳቸውም ፡ በንግግራቸው ፡ ውስጥ ፡ የዚህን ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛና ፡ አከራካሪ ፡ የሆነውን ፡ ክስ ፡ ሁኔታ ፡ ከመግለጻቸው ፡ በፊት ፡ የዚህን ፡ የዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ታሪክና ፡ ሥራ ፡ በቅድሚያ ፡ ገለጹ ። በንግግራቸውም ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ የዓለም ፡ ሰላምና ፡ ፍትሕ ፡ በሕግ ፡ አማካይነት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይኸ ፡ የዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊፈጽመው ፡ ስለሚገባው ፡ ተግባርና ፡ ስለ ፡ ወደፊት ፡ ዕድሉም ፡ ለቀረቡላቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ ሰጥተዋል ።

ከሁለት ፡ ሳምንታት ፡ በኋላም ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ውስጥ ፡ "በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ የፓርላማ ፡ ተግባር" በሚል ፡ አርዕስት ፡ የሸንጐ ፡ ኰሚቴ ፡ አንድ ፡ የውይይት ፡ ፕሮግራም ፡ አበረከተ ።

በዚሁም ፡ ሸንጐ ፡ ላይ ፡ አፈ ፡ ጉባዔ ፡ የመሆንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ፓርላማም ፡ ሕጋዊ ፡ አቋቋም ፡ የመግለጹ ፡ ዕድል ፡ ለኔ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ። የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተከበሩ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ግርማ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እርሳቸው ፡ የሚገኙበትን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስለሚመለከተው ፡ የፓርላማ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፤ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ (የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ተማሪ)

የሆኑት ፡ ሻሸራሻ ፡ ዘውዱ ፡ ኦቶር ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ በዝርዝር ፡ አስረድተዋል ። እንደዚሁም ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪ ፡ የሆኑትና ፡ በአለፈው ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መማክርት ፡ ምርጫ ፡ በእጩነት ፡ የቀረቡት ፡ ወይዘሮ ፡ ያይኔ ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምርጫ ፡ ውድድርና ፡ አፈጻጸም ፡ ተናግረዋል ። የብዙ ፡ ጥያቄዎችም ፡ መሰንዘር ፡ ጥያቄና ፡ መልስ ፡ የመስጠቱ ፡ መሟሟቅ ፡ ፕሮግራሙን ፡ ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ ለበለጠ ፡ ጊዜ ፡ እንዲራዘም ፡ አድርጎት ፡ ነበር ።

ግንቦት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. የሸንጎ ፡ ኮሚቴ ፡ የ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም. ትምህርት ፡ ወቅት ፡ የመጨረሻ ፡ የሆነውን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ የተገኙበትን ፡ የመጨረሻ ፡ ፕሮግራሙን ፡ በራስ ፡ መኰንን ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ አቀረበ ። የፕሮግራሙም ፡ አርዕስት ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፤ በፓርላማ ፡ የሚገኘው ፡ የጭሰኝነት ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ የሚል ፡ ነበር ። የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የፋኩልቲው ፡ ተማሪዎች ፡ የጭሰኛን ፡ ችግር ፡ በንብረት ፡ ትምህርታቸው ፡ ተከታትለው ፡ ስለነበረ ፤ የሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ የነበረው ፡ አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ የፕሮግራሙ ፡ አፈጉባዔ ፡ እንዲሆንና ፡ የጭሰኛ ፡ ሁኔታ ፡ መሻሻል ፡ የሚመለከቱትን ፡ ጊዜያዊ ፡ ችግሮች ፡ ውይይት ፡ እንዲደረግባቸው ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ተጠየቀ ። በዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የጂኦግራፊ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊ ፡ የሆኑት ፡ አቶ ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሲወራረሱ ፡ ስለመጡት ፡ ልማዶችና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ መስፋፋት ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትሉት ፡ ችግሮች ፡ ተናገሩ ። ከእርሳቸውም ፡ ቀጥሎ ፤ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የንብረት ፡ ሕግ ፡ አስተማሪ ፡ የሆኑት ፡ ሚስተር ፡ ኦዌን ፡ ሲልኪ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙት ፡ የመሬት ፡ ጭሰኝነት ፡ ሥርዐቶች ፡ ሁኔታ ፡ በአጭሩ ፡ ገለጹ ። በመጨረሻም ፡ የተከበሩ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ግርማ ፡ ወልደ ጊዮርጊስ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በፓርላማ ፡ ስለሚመከርበት ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ሁኔታና ፡ ለወደፊትም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ሊወጣ ፡ ስለሚቻልበት ፡ አኳኋን ፡ ተናገሩ ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ የሸንጎ ፡ ኮሚቴ ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እድገትና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ አቋም ፡ በሚደረግ ፡ ውይይት ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ አስተያየቶችን ፡ ሊያካፍሉ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባዘጋጃቸው ፡ ሦስት ፡ ስብሰባዎች ፡ በሥራ ፡ ሊያሳይ ፡ ችሎአል ። ስለዚህ ፡ ላለፈው ፡ ድካማቸው ፡ ተማሪዎቹ ፡ ሊመሰገኑ ፡ ይገባል ። ይኸም ፡ የመልካም ፡ ሙያውዋን ፡ ዘላቂ ፡ እንዲሆን ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

(፬) ሌሎች ፡ እንግዶች ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ፋኩልቲው ፡ በብዙ ፡ የታወቁ ፡ ሰዎች ፡ የመጐብኘት ፡ ዕድል ፡ ገጥሞታል ። ከዓለም ፡ የሙያተኞች ፡ ድርጅት ፡ የመጡት ፡ ዶክተር ፡ ሲ. ደብሊው. ጀንክስ ፡ በኛ ፡ ፋኩልቲ ፡ አማካይነት ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ድርጅቶች ፡ የሕግ ፡ ተግቢ ፡ አፈጻጸም ፡ (ዲውፕሮሲስ ፡ ኦቭሎው) በሚል አርዕስት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

እንደዚሁም ፡ የካርቱም ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ዲን ፡ ዛኪ ፡ ሙስጠፋ ፡ በሱዳን ፡ የሕግ ፡ እድገትና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ለተማሪዎቻችን ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ። የኢንተርናሽናል ፡ የሕግ ፡ ሊቆች ፡ ኮሚሽነር ፡ ዶክተር ፡ ሲን ፡ ማክብሪጅ ፡ በቅርቡ ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ በባንኮክ ፡ ስለአደረገው ፡ ስብሰባና ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ድርሻ ፡ ተግባር ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ።

ለጉብኝት ፡ የመጡ ፡ እንግዶች ፡ የሚቺጋኑ ፡ ዳኛ ፡ ቻርለስ ፡ ፋርመርና ፡ የሬዲንግ ፡ ዩኒቨርስቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤም. ጂ. ሊሕማን ፡ በተገኙበት ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከተማሪዎች ፡ ግማሾቹ ፡ በተገኙበት ፡ የመወያየት ፡ ስብሰባዎች ፡ ተደርገዋል ። ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ድርጅቶችና ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ በሚያደርጉት ፡ ምርምር ፡ ምክንያት ፡ የመጡት ፡ የሚቺጋን ፡ ዩኒቨርስቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ደብሊው. ቢ. ሐርቤይ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ጎብኝተዋል ። የካሊፎርኒያ ፡ ዩኒበርስቲው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኤም. ኤል. ሸዋርትዝ ፡ ለሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ጐብኝተውናል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተገለጸውም ፡ ስለ ፡ ሥራችን ፡ አካሄድ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ያሰፈሩበት ፡ መግለጫ ፡ ለዩኒቨርስቲው I ለፎርድ ፡ ፋውንዴሽንና ፡ ለሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቀርቦአል ።

(፭) ስለ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ። የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በዝግታ ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ የሚገኙት ፡ መጻሕፍት ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ፳ሺህ ፡ እንደደረሰ ፡ ተገምቶአል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ መጻሕፍት ፡ ኃላፊ ፡ ሠራተኛ ፡ አለን ። በቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ የሕግ ፡ ሙያተኞች ፡ የመንግሥትና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሠራተኞች ፡ ይገለገሉበታል ። ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ የሕግ ፡ ምርምር ፡ ምንጭ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚገመት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ ነው ። ሳምንቱን ፡ በሙሉና ፡ በረጅሙ ፡ የእረፍት ፡ ጊዜም ፡ አዘውትሮ ፡ የሚሠራ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ነው ። በሰኔ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አማካሪያችን ፡ በፕሮፌሰር ፡ አልበርት ፡ ብሉሽቴን ፡ ጉብኝት ፡ ለመጠቀም ፡ ችለናል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ወደፊት ፡ ልናደርገው ፡ የሚገባንን ፡ እድገት ፡ የሚያመለክት ፡ ሰሌዳ ፡ በማዘጋጀት ፡ ረድተውናል ። ፕሮፌሰር ፡ ብሉሽቴን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍታችንን ፡ በማቋቋም ፡ ረገድ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ በጣም ፡ ጠቃሚና ፡ አስፈላጊም ፡ የሆነ ፡ አገልግሎት ፡ ፈጽመዋል ። ቤተ ፡ መጻሕፍታችንን ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ደረጃ ፡ ለማስገኘት ፡ በምናደርግበት ፡ ጊዜ ፡ እኚህ ፡ የታወቁ ፡ ሰው ፡ አገልግሎታቸውን ፡ እንዲቀጥሉልን ፡ የፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ስለሚረዳን ፡ በጣም ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ የአፍሪካ ፡ አንድነት ፡ ድርጅትና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የአፍሪካ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ መንበር ፡ ናት ። አዲስ ፡ አበባ ፡ የኢንተርናሽናል ፡

ከተማ ፡ ናት ። ስለዚህ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ የአፍሪካን ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ በብዛት ፡ መሰብሰብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አመራር ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምንጭ ፡ የተውጣጣና ፡ በዓለም ፡ ከሚገኙ ፡ የሕግ ፡ ሐሳቦች ፡ ብዙዎችን ፡ የሚያጣምር ፡ በመሆኑ ፡ ከሲቢልና ፡ ከኮመንሎው ፡ ከሁቱም ፡ የሕግ ፡ ዐይነቶች ፡ መጻሕፍት ፡ በመሰብሰብ ፡ የተሟላ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ማቋቋም ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በአጭሩ ፡ በአፍሪቃ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ፡ ሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ያስፈልገናል ፡ የገንዘብ ፡ ዕርዳታ ፡ በማግኘት ፡ ረገድ ፡ በመታደላችን ፡ የምንመኘው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደሚኖረን ፡ እተማመናለሁ ።

(፮) የውጭ ፡ አገር ፡ ጉብኝት ። በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ከሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ ከፕሮፌሰር ፡ ጂ. ክሽችናቢችና ፡ ከአቶ ፡ ነጋ ፡ ተሰማ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢባዳን ፡ ናይጄሪያ፡ ሄደን ፡ ነበር ።

በአፍሪቃ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ስለሚስፋፋበት ፡ ሁኔታ ፡ ለመነጋገር ፡ በተሰበሰቡበት ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ መምህራን ፡ ስብሰባ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነናል ። ጉባኤውም ፡ በተባበረ ፡ ድምጽ ፡ ከአጸደቃቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ አንዱ ፡ በአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ መምህራን ፡ ማኅበር ፡ ተቋቁሞ ፡ ለወደፊቱ ፡ ስብሰባዎችን ፡ እንዲያዘጋጅና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ በጣም፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ እንዲኖር ፡ እንዲያደርግ ፡ የቀረበው፡ ሐሳብ ፡ ነው ።

በግንቦት ፡ ወር ፡ ደግሞ፡ ከአርት፡ ፋኩልቲው ፡ ዲን፡ ከዶክተር ፡ አብርሃም ፡ ደሞዝ ፡ ጋር ፡ በሴኔጋል ፡ ወደሚገኘው ፡ የዳካር ፡ ዩኒበርስቲ ፡ ሄደን ፡ በአፍሪቃ፡ በሚገኙ ፡ የእንግሊዘኛና ፡ የፈረንሣይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተናጋሪ ፡ ዩኒበርሲቲዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚኖረው ፡ መተባበር ፡ በተደረገው ፡ ንግግር ፡ ተካፋይ ፡ ሆነናል። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ በዳካር ፡ ከሚገኘው ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ተገናኝተን፡ የቤተ መጻሕፍት ፡ ዕቅድ ፡ ከማዘጋጀታችንም ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ መጻሕፍትና ፡ ተስፋም ፡ እንደሚደርገው ፡ መምህራንን ፡ ስለመለዋወጥ፡ ለመነጋገር ፡ ዕድል ፡ አግኝቼ ፡ ነበር ።

በረጅም ፡ የእረፍት ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለና ፡ አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡ የተባሉት ፡ ሁለት ፡ ተማሪዎቻችን ፡ የጐረቤት ፡ አገሮችን ፡ የዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ጐብኝተዋል ። አቶ ፡ ፋሲል ፡ በካርቱም ፡ ዩኒቨርስቲ ፤ አቶ ፡ ሰላሙ ፡ ደግሞ ፡ በዳሬሰላም ፡ በምሥራቅ ፡ አፍሪቃ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ፡ ገብተው ፡ ትምህርቱን ፡ ተከታትለዋል ። ለወደፊትም ፡ ይኸን ፡ ዐይነቱ ፡ መለዋወጥ ፡ እንደሚቀጥል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

ማጠቃለያ ።

በመጨረሻም ፡ ለፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፤ ለኒው ፡ ዎርልድ ፡ ፋውንዴሽንና ፡ ለሌሎችም ፡ የግል ፡ በጎ ፡ አድራጊዎች ፤ ለሕግ ፡ መጽሔት ፡ ጠባቂዎችና ፡ ደጋፊዎች ፤ ለታላቋ ፡ ብሪታንያ ፤ ለቤልጂክ ፤ ለፈረንሳይ ፤ ለሕንድና ፡ ለዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ መንግሥታት ፡ ለሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ስለሰጡት ፡ ዕርዳታ ፡ ምስጋናችንን ፡ ልገልጽ ፡ እወዳለሁ ።

በዩኒቨርስቲው ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ውስጥ ፡ በየጊዜው ፡ የትንንሹ ፡ አቤቱታ ፡ መሰንዘሪያ ፡ ኢላማ ፡ የሆነውን ፡ የዩኒቨርስቲውን ፡ አስተዳደር ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ማለፍ ፡ ተገቢ ፡ አይሆንም ። በነዚህ ፡ በመቋቋሚያው ፡ የመጀመሪያ ፡ ዓመታት ፡ የዚህን ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ መሪዎች ፡ የሚገጥማቸውን ፡ ብርቱ ፡ ተግባር ፡ ወደመርሳት ፡ የምናዘነብል ፡ ይመስለኛል ። በዚህ ፡ ፋኩልቲ ፡ ላይ ፡ እስካሁን ፡ ስለተጣለው ፡ አደራና ፡ እምነት ፡ በእርግጥ ፡ አደንቃለሁ ። የሥራ ፡ ጓደኞቼም ፡ በበኩላቸው ፡ ፕሮግራማችንን ፡ ለማቃናትና ፡ በትጋት ፡ ለመምራት ፡ ተባብረው ፡ ይሠራሉ ። ስለዚህ ፡ የዲኑ ፡ ተግባር ፡ የቀለለ ፡ ሆኖአል ። በመጨረሻም ፡ ተማሪዎቹ ፡ በብዙ ፡ አስፈላጊ ፡ ምክንያቶች ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ እራሱ ፡ ናቸው ። የሥራ ፡ ባልደረቦችና ፡ እኔም ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ እንደምንሠራ ፡ እናምናለን ። በዚህም ፡ መንፈስ ፡ ለነዚህ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ ሰላምታችንን ፡ እናቀርብላቸዋለን ።

በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪዎች ፡ የ፲፱፻፶፯—፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ።

በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

ሚስ ፡ አሌክሳንድራ ፡ ሐማዊ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ማሞ ፡ መዘምር ፡
አቶ ፡ ሥሑል ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ በላሙ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ሽመልስ ፡ ሑሴን ፡
የሻምበል ፡ ቀነዓ ፡ ጉማ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ከበደ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ባንቲዋሉ ፡
የሻምበል ፡ አበበ ፡ ጓንጉል ፡

አቶ ፡ አባቢያ ፡ አባጀቢር ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኢያሱ ፡ አያል ፡
አቶ ፡ ዘርዓ ፡ ብሩክ ፡ አበራ ፡
አቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ጎሩይ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዳንኤል ፡ ዘለቀ ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ አረጋይ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ጌታሁን ፡ ዳምጤ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ታደሰ ፡

በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ የሙሉ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎች ።

የመቶ ፡ አለቃ ፡ መስፍን፡ ገብረ ቃል ፡
አቶ ፡ ሠመረ ፡ አብ ፡ ሚካኤል ፡
የመቶ ፡ አለቃ፡ ሽመልስ፡ መታፈሪያ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ወልዴ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ብርሃኑ ፡ ባይህ ፡
አቶ ፡ ተክሉ ፡ መኮንን ፡
አቶ ፡ ታየ ፡ ንጋቱ ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጉርሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ኃይሉ ፡ መኮንን ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ወርቄ ፡
አቶ ፡ ከበተ ፡ ኃይሌ ፡

አቶ ፡ ከበደ ፡ ካሳ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ወንዳየን ፡ ምሕረቱ ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ደነቀው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዓለማየሁ ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ ዘመነ ፡ ካሰኝ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዘርአይ፡ ሀብተ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዘገየ ፡ አስፋው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ይልማ ፡ ግዛው ፡
አቶ ፡ ጠዓመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ጥኡመልሳን ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡
አቶ ፡ ፍሥሐ ፡ ባይህ ፡

በሕግ ፡ የኤል. ኤል. ቢ. ዲግሪ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው የሚመረቁ ፡ የተማሽ ፡ ቀን ፡ (የማታ ፡ ተማሪዎች) ።

አቶ ፡ መብራሀቱ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ መንገሻ ፡ ወርቅነህ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ እውነቱ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ፈለቀ ፡
ሚስተር ፡ አር. ኤች. አር. ራጂያ ፡

አቶ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ቡልቻ ፡ ደመቅሣ ፡
አቶ ፡ ነቢየ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ጸጋዬ ፡

አቶ ፡ አበራ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ እያሌው ፡ ዘለቀ ፡
አቶ ፡ እጅጉ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ፡ አየለ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ ዓቢዮ ፡ ገሊታ ፡

በሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።

አቶ ፡ መስፍን ፡ እምባቸው ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ፋንታ ፡
አቶ ፡ መንክር ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ መንግሥቱ ፡ እምሩ ፡
አቶ ፡ መንግሥቱ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡
አቶ ፡ ሙሉቱ ፡ ልካሳ ፡
አቶ ፡ ምናሴ ፡ ደጉ ፡
አቶ ፡ ሠይፉ ፡ ፈይሣ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ አናጌ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ የተሻ ፡ ወርቅ ፡
አቶ ፡ ሳሙኤል ፡ ወርቅነህ ፡
ሚስተር ፡ ሳካጂያን ፡ አራኪል ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ተስፋዬ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ሣህለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ክፈተው ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ሣህሌ ፡
አቶ ፡ ተስፋየ ፡ ዓለሙ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ተሾመ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገ. ሥላሴ ፡
የሻምበል ፡ ታምሩ ፡ ኃይለ ፡ ገብርኤል ፡
አቶ ፡ ታረቀኝ ፡ ኃይለ ፡ ልዑል ፡
የሻምበል ፡ ታዬ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አቶ ፡ ታዬ ፡ ወንድማገኘሁ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ተክለ ፡ ማር
ያም ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ በቀለ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አበራ ፡ ጐበና ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ጺጋዬ ፡
ሚስስ ፡ ማሪካ ፡ አርቫኒቶፖ ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ አጥላባቸው ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ አድነው ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ እርጻው ፡ ዳርጌ ፡
የሻምበል ፡ ካሣዬ ፡ ማንደፍሮ ፡
አቶ ፡ ካሣዬ ፡ አደም ፡
አቶ ፡ ከፈለኝ ፡ ማንያዘዋል ፡
የሻምበል ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ገብረ ፡
ማርያም ፡
ሻሽራሻ ፡ ዘውዴ ፡ ኦቶሮ ፡
የሻለቃ ፡ ይልማ ፡ ወልደሰማያት ፡
አቶ ፡ ደምሴ ፡ በቀለ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዳምጠው ፡ ምንልኬ ፡
አቶ ፡ ጀማነህ ፡ መኰሻ ፡
ሚስተር ፡ ጆዋኪም ፡ ማቶቹ ፡
አቶ ፡ ጆሴፍ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ገብረየሱስ ፡ ኃይለማርያም ፡
አቶ ፡ ጉደታ ፡ ቦሩ ፡
የሻምበል ፡ ጌታሁን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ ደሳለኝ ፡
አቶ ፡ ግርማይ ፡ ዘወልደ ፡
አቶ ፡ ጸደቀ ፡ ተክሌ ፡

በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. ያገኙ ፡ መረቁ ፡ ተማሪዎች ።

አቶ ፡ ለማ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ ለማ ፡ ወልደሰማዕት ፡
አቶ ፡ ለገሠ ፡ አበበ ፡
መዘምር ፡ መልከጼዴቅ ፡ ወልደሥላሴ ፡
አቶ ፡ መብራቱ ፡ ጉባ
አቶ ፡ መኰንን ፡ አገኘናፍር ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ ወልደማርያም ፡
አቶ ፡ መጨጊያ ፡ ቢራቱ ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ሀብተገብርኤል ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ መኰንን ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ በሪሁን ፡
የሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ እንዳይላሉ ፡
ሌተና ፡ ኰሎኔል ፡ ምሕረት ፡ ገብረ ፡ ሰላም ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ አስረስ ፡
አቶ ፡ ሱልጣን ፡ ሰይድ ፡
አቶ ፡ ሸዋንግዛው ፡ ወልደዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ሸዋየ ፡ ለማ ፡
አቶ ፡ ሽመልስ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ አብቤ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ገድሌ ፡
አቶ ፡ ብርሃነመስቀል ፡ ጺጋየ ፡
የሻምበል ፡ ብርሃኔ ፡ ንጋቱ ፡
አቶ ፡ ብዙአየን ፡ ሀዱግ ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገሠሠ ፡
የሻምበል ፡ ተሰፋዬ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ ደነቀ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ እንግዳ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደመስቀል ፡
አቶ ፡ ኃይለማርያም ፡ ተስፋት ፡
አቶ ፡ ኃይለማርያም ፡ ገመዳ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ በየነ ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ቢሰጥ ፡
አቶ ፡ ነጋሽ ፡ ተክለማርያም ፡
አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ነውጤ ፡
አቶ ፡ ንጉሤ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
አቶ ፡ አሥራት ፡ ለገሠ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሰፋ ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ቦርሺ ፡
ያምባ ፡ አለቃ ፡ አበበ ፡ ወልደ ጊዮርጊስ
አቶ ፡ አባተ ፡ ስመኝ ፡
ፊታውራሪ ፡ አባይነህ ፡ ፊና ፡
አቶ ፡ አክሊሉ ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ አየነው ፡ ወልደማርያም ፡
አቶ ፡ አድማሱ ፡ እውነቱ ፡
አቶ ፡ እሸቱ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ እንዳለ ፡ ወልደሚካኤል ፡
አቶ ፡ እሳና ፡ በቲ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ቸኰል ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ከተማ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ከፋለ ፡ ወልደማርያም ፡
ግራዝማች ፡ ካሣ ፡ አበራ ፡
አቶ ፡ ክፍሌ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ወልደሙሴ ፡ ይህደጎ ፡
አቶ ፡ ወልደሚካኤል ፡ ገብረአብ ፡
የእሥር ፡ አለቃ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ደበላ ፡
አቶ ፡ ወልዴ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ዋለልኝ ፡ መራ ፡
አቶ ፡ ዓለሙ ፡ መለሠ ፡
የሻለቃ ፡ ባሻ ፡ ዘውዴ ፡ ኃይሌ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ይልማ ፡ መንግሥቱ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ ታደሰ ፡

አቶ ፡ ደርብ ፡ ቡታ ፡
አቶ ፡ ገብረመስቀል ፡ ካህሣይ ፡
አቶ ፡ ገብረማርያም ፡ መርጊያ ፡
አቶ ፡ ገብረማርያም ፡ አምባየ ፡
አቶ ፡ ገዛኸኝ ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ወልደሰንበት ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ምንልክአለው ፡
አቶ ፡ ጌታቸው ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ግርማ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ግዛው ፡ ብዛኔ ፡
አቶ ፡ ጐሣዬ ፡ ዘመድኩን ፡
አቶ ፡ ጐይቶም ፡ በይን ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ፈቃዱ ፡ ዋኬኔ ፡

በሕግ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. አግኝተው ፡
የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።
(አዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍል «ሀ») ።

አቶ ፡ ሰማ ፡ ደገፉ ፡
ሌ/ኰ መርድ ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ መቆያ ፡ እሸቴ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ ይመኑ ፡
አቶ ፡ ምስጋና ፡ ታረቀኝ ፡
መምሬ ፡ ሣህለድንግል ፡ ገብረክርስቶስ
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ዳኛቸው ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሰብስቤ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ሰዋሰው ፡ እንየው ፡
አቶ ፡ ስለሺ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ በላይ ፡ ጌታሁን ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ወልደዮሐንስ ፡
ሌ/ኰ/ በየነ ፡ ዘአማኑኤል ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ በዛብህ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ገላግል ፡
አቶ ፡ ተካ ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡
አቶ ፡ ተፈራ ፡ በየነ ፡
የሻለቃ ፡ ታምራት ፡ ጉበዜ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አብተው ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደኪዳን ፡
አቶ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አረፈ ፡ ዓይኔ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሐጐስ ፡
አቶ ፡ ኃይለሥላሴ ፡ በዛብህ ፡
የሻምበል ፡ ኃይሉ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሐና ፡
አቶ ፡ ንጋቱ ፡ ሀብተማርያም ፡
የሻምበል ፡ አግረ ፡ አደራ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ተገኝ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ አካለ ፡ ሕይወት ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ አየለ ፡
አቶ ፡ አስፋው ፡ ይትባረክ ፡
አቶ ፡ አስቤ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ አሻግሬ ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አወጣቸው ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ተክሉ ፡
አቶ ፡ አብርሃም ፡ ድሬሳ ፡
አቶ ፡ አንዱ ፡ ዓለም ፡ በላይ ፡
አቶ ፡ አየለ ፡ ወልደሐዋርያት ፡
አቶ ፡ እያሌው ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ እሸቴ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ እንዳለው ፡ መንገሻ ፡
አቶ ፡ እንግዳ ፡ ጌጥ ፡ ወርቁ ፡
የሻምበል ፡ ከበደ ፡ ሰንበቶ ፡
አቶ ፡ ካሣሁን ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡ ወልደ ፡ አረጋይ ፡
የሻለቃ ፡ ወንድሙ ፡ ገብረ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ውቤ ፡ ወልደየስ ፡

የሻለቃ ፡ ዘሪሁን ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ መዝገቡ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ ተድላ ፡
አቶ ፡ የማነብርሃን ፡ ወንድምአየሁ ፡
የሻለቃ ፡ የኔነህ ፡ ዓለሙ ፡
አቶ ፡ ደሳለኝ ፡ ዓለሙ ፡
ሌ/ኰ/ ደባልቄ ፡ ገዳ ፡
አቶ ፡ ጥላሁን ፡ ኃይሌ ፡
አቶ ፡ ጥላሁን ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ ጸጊ ፡ ደርሰህ ፡
አቶ ፡ ፈለቀ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ፍሬ ፡ ሕይወት ፡ በይበይን ፡

በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. አግኝተው ፡ የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።

(አዲስ ፡ አበባ ፡ ክፍል ፡ ፩ኛ) ።

አቶ ፡ ለማ ፡ ተረፈ ፡
ሌ/ኰ ሉልሰገድ ፡ ኃይሌ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሉልሰገድ ፡ ንጉሤ ፡
የሻምበል ፡ መለሰ ፡ መቼሳ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መለሰ ፡ ዓለሙ ፡
ሐጂ ፡ መሐመድ ፡ ሲራጅ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ማሞ ፡
አቶ ፡ መስፍን ፡ ተፈራ ፡
አቶ ፡ መርጋ ፡ ሰኝ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መንገሻ ፡ ዘውዴ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ መንግሥቱ ፡ ቢጋሻው ፡
አቶ ፡ ሙሉጌታ ፡ እንዳለ ፡
አቶ ፡ ማሙዬ ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ ማሞ ፡ ወልደማርያም ፡
የአሥር ፡ አለቃ ፡ ምንይል ፡ ሸዋ ፡ ሀብቴ ፡
አቶ ፡ ሞቢሳ ፡ ጋሪ ፡
አቶ ፡ ሰይፉ ፡ ቦጂያ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ኃይለሚካኤል ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ግሀሴ ፡ ምሕረቴ ፡
አቶ ፡ ሽፈራው ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ በቀለ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ አባይ ፡
አቶ ፡ ብርቁ ፡ አባሠራን ፡
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዱባለ ፡
አቶ ፡ ተረፈ ፡ ገብረመስቀል ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ቢረሳው ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ ተሾመ ፡ ደምሴ ፡
አቶ ፡ ተከስተ ፡ ብርሃን ፡ ድባቡ ፡
ኰሎኔል ፡ ተክለማርያም ፡ አባይሬ ፡
አቶ ፡ ተክሌ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡
አቶ ፡ ተገኝ ፡ ሀብቱ ፡
አቶ ፡ ተገኝ ፡ ወንዳፍራሽ ፡
የመቶ ፡ አለቃ ፡ ታየ ፡ ቁምላቸው ፡
የሻምበል ፡ ታደሰ ፡ ተበኩ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ አበበ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ወልደጻድቅ ፡
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጭጭ ፡ አይበሉ ፡
ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ታደሰ ፡ ፈይሳ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ልዑል ፡ ሀብተዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ሥላሴ ፡ አሰፋው ፡
አቶ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ሙላት ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ አጐናፍር ፡
ሌ/ኰ አህመድ ፡ አሚኑ ፡
አቶ ፡ አለኑ ፡ ወንዴ ፡

የሻምበል ፡ አማረ ፡ ንጋቱ ፡
አቶ ፡ አማረ ፡ ደግፌ ፡
አቶ ፡ አራጋው ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ዘአማኑኤል ፡
አቶ ፡ አሰፋ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ አሰፋው ፡ መሸሻ ፡
አቶ ፡ አሰፋው ፡ ገብረኢየሱስ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ ተሰማ ፡
አቶ ፡ አበበ ፡ አስገልጥ ፡
አቶ ፡ አድማሱ ፡ አስረስ ፡
የሻለቃ ፡ አድማሱ ፡ ጀምበሬ ፡
አቶ ፡ አድማሴ ፡ ገሠሠ ፡
ወይዘሮ ፡ ዓይኔ ፡ አበባ ፡ ሸዋንግኸው ፡
አቶ ፡ አጋ ፡ ነጋሽ ።
አቶ ፡ እሼቴ ፡ ከበደ ፡
አቶ ፡ ከበደ ፡ ተረፈ ፡
መቶ ፡ አለቃ ፡ ከፋለ ፡ አድገሀ ፡
አቶ ፡ ካሳሁን ፡ ወርቅነህ ፡

አቶ ፡ ወልደትንሣኤ ፡ ገብረሚካኤል ፡
አቶ ፡ ወልደጻድቅ ፡ ወልደሰማዕት ፡
አቶ ፡ ወንድሙ ፡ ገብረመድኅን ፡
አቶ ፡ ወንድወሰን ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ አጋ ፡
አቶ ፡ ዓለማየሁ ፡ ወንድሙ ፡
አቶ ፡ ዓለምሰገድ ፡ አርአያ ፡
አቶ ፡ ዕጹብ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ የማነ ፡ ብርሃን ፡ መላኩ ፡
አቶ ፡ ይልማ ፡ በቀለ ፡
አቶ ፡ ይትባረክ ፡ ተሾመ ፡
አቶ ዲሚጥሮስ ፡ ገብረሐና ፡
አቶ ፡ ዳባ ፡ ሱንጣ ፡
አቶ ፡ ገላሁን ፡ አባተ ፡
አቶ ፡ ገመቹ ፡ ጉታ ፡
አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ፈንታሁን ፡ ብርሃኔ ፡
አቶ ፡ ፍታወቅ ፡ ደመኢየሱስ ፡

በሕግ ፡ ሠርቲፊኬት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. አግኝተው ፡

የሚመረቁ ፡ ተማሪዎች ።

(አሥመራ) ።

አቶ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ደባስ ፡
አቶ ሐሚድ ፡ ዑስማን ፡ አድሪስ ፡
አቶ ፡ ሑሰን ፡ ፋራሕ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ሐንኪል ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኑር ፡ ቁስማላ ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ አሊ ፡ ሐሰን ፡
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢብራሂም ፡ ሐንጋላይ
አቶ ፡ መሐመድ ፡ ኢድሪስ ፡ ዑመር ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ አስረሱ ፡
አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ መዋእል ፡ መብራህቱ ፡
አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ ኪሕሳይ ፡

አቶ ፡ ሰይድ ፡ ሐሊፋ ፡
አቶ ፡ ሰይድ ፡ ከሊፋ ፡
አቶ ፡ ሳልሕ ፡ ሺፋ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ይሕደጐ ፡
አቶ ፡ ሥዩም ፡ ፍስሐ ፡ ጸጋይ ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ በየነ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ ብርሃኔ ፡ ክፍለማርያም ፡
አቶ ፡ ተስፋት ፡ ዘሚካኤል ፡
አቶ ተስፋ ፡ ጸጋይ ፡ ኢያሱ ፡
አቶ ፡ ተክኤ ፡ ገብረክርስቶስ ፡
አቶ ፡ ተኽለ ፡ ካሕሳይ ፡

አቶ ፡ አርአያ ፡ ገብረሥላሴ ፡
አቶ ፡ አስፍሐ ፡ አብተው ፡
አቶ ፡ አፈወርቅ ፡ ጆርጆ ፡
አቶ ኢሳይያስ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡
ግራዝማች ፡ እዮብ፡ ተኸሉ ፡
አቶ ፡ ከሊፋ ፡ መሐመድ ፡ ዓሊ ፡
ፍስአቶ ከሰተ፡ ፍስሐየ ፡
አቶ ፡ ኪሕሳይ ፡ አስፍሐ ፡
አቶ ፡ ካሣሁን ፡ ደረሰ ፡
የሻምበል ፡ ከብረ ፡ አብ ፡ በርሄ ፡
አቶ ፡ ክብሮም ፡ ዘይሉ ፡
አቶ ፡ ወልዱ ፡ በርሄ ፡

ያምሳ ፡ አለቃ፡ወረታ፡ ተክለሃይማኖት
አቶ ፡ እቁባዝጊ ፡ ኢድከመ ፡
ያምሳ ፡ አለቃ ፡ ዮሐንስ ፡ተክለየስ ፡
አቶ ፡ ገብረሚካኤል ፡ ብሥራት ፡
አቶ ፡ ገብረሥላሴ ፡ ገረንሰኤ ፡
አቶ ፡ ገብረእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ሚካኤል ፡
አቶ ፡ ገብረትንሣኤ ፡ ወልደሥላሴ ፡
የሻለቃ ፡ ግርማይ ፡ ካሣሁን ፡
አቶ ፡ ጸሐየ ፡ ዮሐንስ ፡
አቶ ፡ ጸጋይ ፡ ባይሩ ፡
የአሥር ፡ አለቃ ፡ ፋሲል ፡ ደምሳስ ፡

SECOND ANNUAL REPORT FROM THE DEAN
1964-65 (1957 E.C.)

by
James C.N. Paul, Professor of Law and Dean
Faculty of Law, Haile Sellassie I University

I

INTRODUCTION

Once again I am happy, at the request of the Editors, to report on the progress of our Faculty of Law during its second year in operation.

My report covers only the academic year 1964-65 (1957 E.C.), and I will use Gregorian Calendar dates for the benefit of foreign readers of it.

On November 25, 1964, there occurred the first graduation of students under the auspices of this Faculty — the award of Certificates in Law to the first class to complete that program. For all of us who attended, this was a moving event. The significance of the occasion may be reflected in these remarks of His Imperial Majesty who, as Chancellor of the University, presided:

> "... The law of the Empire is now modern, complex and scientific in the sense that it has been prepared by experts after careful study. The administration of the law of the Empire increasingly demands highly trained persons.
>
> In a real sense the development of the nation depends upon the development of our legal institutions....
>
> ... So the need for persons trained in law is obvious.
>
> ... We are pleased to learn that others are following hard upon the footsteps of this class. We are pleased to know that soon the number of Ethiopian lawyers holding a university degree in law will be virtually doubled.
>
> We are especially pleased to see that so many judges and other civil servants and advocates are taking time to continue their education even as they continue to perform their regular daily duties.
>
> ... Ethiopia needs a modern legal profession just as she needs the modern legal system she is building. The one cannot exist with the other.
>
> You — all of you who are taking University training in law — are helping in the task of building a profession ...."

These words identify our mission here — to help in the building of a *profession* which in turn will be a resource for building the legal system. From

the time of Aristotle to our own day statesmen and philosophers have stressed the theme that men cannot live in freedom and happiness unless they live under law — under laws framed to secure attainable ideals, inspire men's confidence and guard their freedom. But in no modern nation can law serve those ends unless it is framed and administered by men who understand its function as well as its letter and its method as well as its intricacy. In no nation can law win respect unless there is a profession dedicated to public service and to progressive, on-going development of the law as an instrument to execute programs of economic development and social and political change. Thus the study of law at Haile Sellassie I University is, in a very real sense, the study of problems confronting the Empire and measures taken to meet and solve those problems and the role of the profession in this task. I hope it is not amiss to add my belief that these initial years, in a unique way, have been intellectually exciting for all of us who have been privileged to work here.

II

The Development of Educational Programs During Our Second Year

(1) *The Development of Programs of Part-Time Legal Education.* The past year marked the initiation of the Law Diploma program — a three-year evening course. The entry requirement for this program is liberal: completion of secondary school, an interview and passing an English comprehension test, plus professional experience in law, public administration or some closely related field. The course is designed for government officials, advocates, prosecutors, judges and members of Parliament.

We enrolled, in September, 1964, about ninty persons in the Diploma course. Approximately fifty-five sat for final examinations in June, 1965. There may well be some further attrition. But for those who have both the capacity and the perserverance for the hard work which the Diploma course requires, we believe the experience will be beneficial to them and to Ethiopia. The teachers have expressed a deep sense of satisfaction in working with the students, and we hope there will continue to be considerable enthusiasm in this program. Most of the students are employed by government, and many directly in legal capacities.

We also enrolled in September, 1964, a new class of two hundred in the Certificate program, which provides instruction for three afternoons a week in the basic principles of the Ethiopian codes and Constitution. The majority in these classes are prosecutors, government lawyers, judges and advocates. Seventy-nine persons were awarded Certificates in June, 1965 and over one hundred in the class which graduated in November, 1964.

At the request of officials from the Ministry of Justice in Asmara, we initiated special extension courses in penal law and penal procedure there.

These courses were taught by Mr. Norman Metzger of our staff. The student body of sixty persons was made up of judges, prosecutors and government officials. The Assistant Dean and I visited Asmara several times. In our opinion the project has been successful; the examinations show, generally, a good performance; student interest has been keen. In fact the students have asked for a further year of instruction in the Civil Code and public law — and the award of the University's Certificate in Law. Further, some fifty additional persons have requested the starting of a new course of instruction next year. We have decided to continue and expand our extension program in Asmara by meeting these requests. Thanks to the willingness of Ato Amanuel Amdemichael and Justice Negussie Fitawake, additional instruction is being furnished in the fall. 1965, a new class enrolled and the present class continued. A small law collection will be established as a new part of the Asmara city library; when resources permit we hope we can build up that basic collectiton of books necessary for elementary legal reference.

